# ይቅርታና እርቅ

(በዓይነቱ ልዩ የሆነ መጽሐፍ)

«በቅንነት ብንነጋገርና ብንሠራ የሁላችንም ሐሳብ

ለኢትዮጵያ ይጠቅማል እንጂ አይጐዳም»

ከይልማ ኃይሉ

ሐምሌ/2000 ዓ.ም.

አሳታሚ እና አከፋፋይ
ይልማ ኃይሉ
091 112 32 31
ተዋሕዶ መዝሙር ቤት

የሽፋን ስዕል ብርሃነ ሕይወት

# ማውጫ

ገጽ


| | |
|---|---|
| መቅድም ........ | 1 |
| መግቢያ ........ | 2 |
| የእርቅ ሐሳብ ........ | 4 |
| ይቅርታ ከየት ይጀምር ........ | 25 |
| ከራስ ጋር መታረቅ ........ | 29 |
| ከቤተሰብ ጋር መታረቅ ........ | 41 |
| ከሴቶች ጋር መታረቅ ........ | 59 |
| ከሕፃናት ጋር መታረቅ ........ | 82 |
| ከሕግ ጋር መታረቅ ........ | 101 |
| ከሥነ ጥበብ ጋር መታረቅ ........ | 129 |
| ከችግረኞች ጋር መታረቅ ........ | 145 |
| ከሥራ ጋር መታረቅ ........ | 149 |
| ከታማኝነት ጋር መታረቅ ........ | 169 |
| ከሥነ ምግባር ጋር መታረቅ ........ | 186 |
| ነጋዴው ከንግድ ጋር ይታረቅ ........ | 193 |
| ከተፈጥሮ ጋር መታረቅ ........ | 196 |
| ከውሃ ጋር መታረቅ ........ | 203 |
| ከኃይል ጋር መታረቅ ........ | 221 |
| ከዓላማ ጋር መታረቅ ........ | 251 |
| ከትምህርት ጋር መታረቅ ........ | 255 |
| ከአስተዳደር ጋር መታረቅ ........ | 274 |

© ይልማ ኃይሉ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

ALL RIGHTS RESERVED

2000 ዓ.ም.

**መታሰቢያነቱ**

**ለእናቴ ለወይዘሮ ሽዋማማሽ ሕይወት**

**እና**

**ለአባቴ ለ፻ አለቃ ኃይሉ ወ/መድኅን ይሁንልኝ::**



## መ ቅ ድ ም

የእዚህ መጽሐፍ ዓላማ እርቅ ነው:: ከዚህ በፊት ባልታየ አቀራረብ ሰው ከሰው ጋር ይታረቅ ዘንድ ከራሱ ጀምሮ ከሰፀዋቱ፣ ከአፀዋፉ፣ ከወንዙ፣ ከሸንተረሩ፣ ከሕፃናት ከሴቶች ጋር ሁሉ ይታረቅ ዘንድ ጻፍኩኝ::

ታላቁ ቁም ነገር በዚህ ዘመን ይቅርታ ነው:: እኛ መካከል የነበረ ዛሬ ግን ያጣነው የፍቅር እና የትብብር መንፈስ የሚዳብረው ከይቅርታ በኋላ ነው::

ሰውና ሰው ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮና ሰው እንኳን በሀገራችን የተጣሉ ይመስላሉ:: ለዚህ ነው ምድር በረከቷን ሰማይ ጠሉን የነፈገን:: ይህ የእግዚአብሔር ጠብ ነው ይታረቀን ዘንድ መጸለይ ይኖርብናል::

ከእዚህ በተረፈ ግን ፀቡን በእርቅ፣ ተፈጥሮን በብልሃት መደለል ይቻላል:: እነዚህ ሁለት ቦታዎች ካልተጠገኑ የምንሠራው ሁሉ መና እየሆነ እንዳይቀር ያሰፈራል::

የትኛውም ሕዝብ ግለሰብ እና መንግሥት ከይቅርታ ውጪ መፍትሔ የለውም:: በአንዲት አዳራሽ ተሰብስበን በሀገራችን ባሕል መታረቅ አለብን::

በእዚህ ዘመን እንኳን ፀብን አራግበውት በፍቅር የተገነባውን ቤት ሁሉ እየከፋፈተ የሚገባበት ዘመን ነው:: ሰው ተጣልቶ የማይታረቅበት ክፉ ዘመን ነው:: ስለዚህ ቀድሞም አለመጣላት፣ ከተጣሉም ፀሐይ ሳትጠልቅ መታረቅ ብልጥነት ነው:: ከፀብ ማንም አያተርፍም::

እርግጥ ነው በመከባበርና በመደጋገፍ የመኖር ግዴታን መወጣት የሁሉ ድርሻ ሊሆን ይገባዋል:: ሁሉም እርምጃውን ጠብቆ አካባቢውን በአንደበት እና በተግባር ሳይጉዳ መኖር አለበት:: ይህ ድንበር ቢጣስም እንኳን ግን ወደመጠፋፋት የሚያደርሰውን መንገድ ለመዝጋት ይቅርታ ወሳኝ ነው::

ይቅርታ የዘመናችን ቁስል መድኃኒት ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ላይ በሰፊው ለማብራራት ተሞክሯል፣ በተረፈ በእዚህ ጽሑፍ ሁሉ ሊካተት ስለማይችል በአስተዋይነቱ እና በትዕግሥቱ የሚታወቀው ሕዝባችን በእርጋታ ለሁሉ መፍትሔ እንደሚሰጥ በመተማመን የይቅርታ አምላክ ይቅርታ በሀገራችን ይሰፍን ዘንድ እንዲረዳን መጸለይ ይገባል::

## መግቢያ

ከሁሉ አስቀድሜ ለወገኔ ድንገት ቢጠቅመው በማለት የሕሊናዬን የዘወትር ሕመም በጽሑፍ ለማስፈር ዕድሜ ለሰጠኝ እግዚአብሔር መጋቢነቱና አስተዳዳሪነቱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ለማይጓደለው የፍጥረታት ፈጣሪ የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ።

ከወገኔ ተለይቼ በምኖርበት የምዕራቡ ዓለም ለዕድገታቸው መሠረት የሆኑትን ቁልፍ ጽንሰ ሐሳቦች በማየት፣ በመስማት፣ በማንበብና በመቅሰም ይህ በሀገሬ ቢደረግ ሕዝባችን እነሱ የደረሱበት ደረጃ ላይ ይደርሳል በማለት ዘወትር አሰላስለው የነበረውን ለምን አልጽፈውም ብዬ ተነሳሳሁ። ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጌ የዛሬ 3 ዓመት የጀመርኩት ይህ መጽሐፍ በኅዳር ወር 1998 ዓ.ም ተጠናቀቀ።

በእዚህ ሥራ ውስጥ ከሁሉ በላይ ባለቤቴ ወ/ሮ ሒሩት ገዛኸኝን ላመሰግን እፈልጋለሁ። የልጆቼን ሸክም ሰባ አምስት በመቶ በመሸከም ጽሑፌን በትእግሥት እንድፈጽም ስለረዳችኝ፤ ልጆቼን መንከባከብ በሚገባኝ ሰዓት በጽሑፍና በንባብ በመጠመድ የአባትነት ተግባሬን ባስተጓጐልኩባቸው ወቅቶች ሁሉ በሕፃንነት ሕሊናቸው እንኳን ለሥራዬ አክብሮት ስለነበራቸው እጅግ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

በተለይ እግዚእኃረያ በጽሑፌ መሐል ተስፋ በመቁረጥ ላቋርጠው ስወስን «አባቴ ስትጽፍ፣ ስትስል ደስ ይለኛል፤ አታቋርጥ» ብላ በእምባ ወደ ሥራዬ የመለሰችኝ ፈጽሞ አይረሳኝም። ኢያቄምና ይኩኖ አምላክም እንደዚሁ።

ይህንን መጽሐፍ በማረም፣ በመተየብና በማሳተም የረዳችሁኝን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

ባለችኝ ውስን ዕውቀት ግለሰቦችን ሳይሆን ሥራን ብቻ በምተችበት ጊዜ የግለሰቦች መንፈስ እንዳይረበሽብኝ፣ ወደ ጥላቻ እንዳይሄድብኝ አደራ እያልኩ ይህ መጽሐፍ ከሥራ እንጂ ከቡድንም ሆነ



ከግለሰብ ጋር ዝምድናም ሆነ ጸብ የለውም ስል በትሕትና እስታውቃለሁ። ግን እንደአንድ ኢትዮጵያዊ በሕይወት ዘመኔ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ ለማስጠንቀቅ፤ ያልተከናወኑትን ለመጠቆም የተሠሩትንም በቀና መንፈስ ለማመስገን ይህንን ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ።

በጽሑፉ ውስጥ የታሪክ እና የመልካም ሥራ ምሳሌዎች ተጠቅሰዋል። ይህም የሆነው ዛሬም የእዚህ መልካም መንገድ ቀጣዮች እንድንሆን በማሰብ ነው። የዛሬ ታሪክ ገና ስላልተፈፀመ በጉውንም ሆነ ክፉውን ለመጻፍ የሚቻል አይመስለኝም።

በእኔ ሕሊና ይህ ሐሳብ፤ በወገኔ ሕሊና ቢመላለስ እና ወደ ተግባርም ቢለወጥ ይጠቅማል እላለሁ። ይህንንም ስል ጽሑፌ እና ሐሳቤ ፍጹም ነው ለማለት አይደለም። ግን ለሀገር እና ለወገን መልካም የሚያስቡ ወርቃማ ሕሊና ያላቸው ቀና ምሁራን በየሞያቸው ለመጻፍ ይነሳሳሉ ብዬ ስለማምን ነው። የእዚህ መጽሐፍም ዓላማ ይህ ነው፤ የጻፍነውን እግዚአብሔር ያስፈጽመን።

**ለጸብ ከተማ ወዮላት !**

**ይቅርታ ለማታውቀው ለጸብ ዓይንዋን ሳጉረጠረጠች ከተማ ወዮላት! ሐሰትና ቅሚያ ሞልቶባታል ንጥቂያ ከእርስዋ አያልቅም። የአለንጋ ድምፅ የመንኩራኩርም ድምፅ፣ የፈረስም ኮቴ የፈጣን ሠረገላም ጩኸት ተሰምቷል። ፈረሰኛውም ይጋልባል፤ ሰይፍም ይንቦገቦጋል፤ ጦርም ይብለጨለጫል፤ ይቅርታን የማያውቅ ሕዝብ ለመጠፋፋት ይፋጠናል፤ ወዮው ለማይታረቅ ቤተሰብ፣ ጐረቤት፣ መንደር፣ አገር።**

# ምዕራፍ አንድ

## የእርቅ ሐሳብ

ስለ ይቅርታ የተለያዩ ሕዝቦች የተለያየ ትርጉምና እሳቤ አላቸው:: ይህም በሦስት የተከፈለ ነው:: አንደኛው አካል በፍጹም ይቅርታ የሚያምን:: አንድ ጊዜ ይቅር ከተባለ ፈጽሞ ከልብ መርሳት ያስፈልጋል ብሎ የሚያምን እና ለማድረግም የሚጣጣር አካል ሲሆን፤ ሁለተኛው ይቅር ማለት ይቻላል ግን በደልን መርሳት አይቻልም መ ረሳትም የለበትም ብሎ የሚያምነው ክፍል ነው:: ለእዚህም ምሳሌ የምትሆነን Maja Abramovitch የተባለች እስራኤላዊት ፀሐፊ To forgive ... But not forget በተባለው መጽሐፍዋ ለይቅርታ ሌላ ትርጉም ሰጥታው እናያለን::

ሦስተኛው በደልን የማይረሳ ይቅር የማይል የበቀል ዓለም ነው:: እስቲ በዝርዝር ለማየት በጥቂቱ ሦስቱንም ክፍሎች እንያቸው::

### ሀ. ፍጹም የሆነ ይቅርታ

የመጀመሪያው ይቅርታ ያስፈልጋል ከልብ መርሳትም ይቻላል የሚሉ የይቅርታ ወገኖች ናቸው:: እነዚህ ወገኖች በፍጹም ፍቅር እና በንጹሕ ልብ የትናንት ስህተትን ዛሬ በማረም እና አብሮ በመሥራትና በመፋቀር መርህ የሚያምኑ ናቸው:: የደረሰባቸውን በደል በይቅርታ የሚደመስሱ ናቸው:: ውስጣቸው ቅንነት፣ መልካም ነገር፣ አስተዋይነት የተሞላበት ነው::

በደልን አለመቁጠር የመጨረሻው የፍጹምነት ደረጃ ነው:: ፈጽመው በደልን የረሱ ወይም ቂም መያዝ የማይችሉ ሁሉን በበጐ የሚተረጉሙ ልበ ንጹሐን በዚህ ምድር ታይተው አልፈዋል አሁንም ቢሆን ተደብቀው አሉ::



ቀድማ የነበረችውን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረችውን ወይም የተገለጠችውን ትዕዛዝ የይቅርታ ሕግ «ዓይን ስለዓይን፤ ጥርስም ስለጥርስ እንደተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉውን አትቃወሙ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጐናጸፊያህን ደግሞ ተውለት:: ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ:: ለሚለምንህ ስጥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል:: ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላታችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁንም መርቁ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ:: እርሱ በክፉ ዎችና በበጐዎች ላይ ፀሐይ ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና:: የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሱ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ» ይለናል::*

የቀደመችይቱ ሕግ ዓይን ላጠፋ ቅጣቱ ዓይን ማጥፋት ነበር:: ሁለተኛይቱ ግን ቀድማ የነበረችይቱ ሕግ በይቅርታ ሕግ አደሰችው:: የቀድሞ ደጋግ አባቶች በእዚህች ደገኛ ሕግ ተመሩ ኑሯቸውን፣ ዓላማቸውን ሰላማዊ አደረጓት:: ብፁአን የሆኑ ይቅር ባይ አባቶች እግዚአብሔርን አዩት:: ይህንን ለማረጋገጥ እሩቅ መኳዝ አያስፈልግም:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እስጢፋኖስ በፈሪሳውያን ድንጋይ ሲወገር «እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ» በማለት ተናግሯል:: ለመሆኑ እስጢፋኖስን ለዚህ ማዕረግ ያደረሰው ምን ነበር::

* ማቴ. 5፥38–48

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል» ካለ በኋላ «ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው» ብሎ በታላቅ ድምፅ በመጮሁ እውነትም የይቅርታ ልብ ያላቸው እንደ እስጢፋኖስ እግዚአብሔርን ማየት ተሰጥቷቸዋል እንላለን::*

የሚያስታርቁስ እነዚህንም ብፁዓን ብሏቸዋል መጽሐፍ ቅዱስ እንደውም የእግዚአብሔር ልጆች ብሎ እጅግ ያከብራቸዋል::* ግሩም ነው በዝምታ ውስጥ በፍቅር ውስጥ ሆነው ሰውን በይቅርታ ዓይን ብቻ የሚያዩ የይቅርታ ሰዎች አልፎ አልፎ መታየታቸው፤ እውነትም እግዚአብሔር ይህን ዓለም በይቅርታው ዘወትር እንደሚጐበኘው የሚያሳይ ምልክት ነው::

### ለ. መቻቻል

«በደልን መርሳት አይቻልም ወይም ፈጽሞም ይቅርታን ማውረድ ይከብዳል፤ ግን ለበለጠው የዓለም ጥቅም ሲባል ነገሮችን ማቻቻል ይቻላል» **Maja Abramovich** (fixing the world) ብላለች::

ይህ ዓይነቱ መቻቻል እውነትም በእዚህች ምድር የተዘወተረ እና እንደ ትክክለኛ መንገድም የተቆጠረ ይመስላል:: የሆድን በሆድ ይዞ ነገሮችን በይደር አቆይቶ በይስሙላ ፈገግታ ታራቂ መምሰል ይህንን ዓለም የመሸንገያ ብልሃት ተደርጐ ተወስዷል ::

የሚገርመው አገሮች ከአገሮች ጋር ከሚያደርጉት የለበጣ የዲፕሎማሲ መኩነስነስ ጀርባ ያደባ ፀብ የተሸመቀ እና የተጐነጐነ ደባ ቢኖርም ለጊዜያዊ ጥቅም ሲባል መርዘኛውን ቂም ቀብሮ የባሕል፣ የሳይንስ እና የንግድ ስምምነቶችን መፈራረም የተለመደ ነው::

---

* የሐ.ሥራ 7፥54-60
* ማቴ. 5፥9



በግለሰቦችም መካከል ይህ ጠባይ በሰፊው ይታያል:: የማይወዱትን የጠሉትን ሰው በጥርስ ብቻ መሸንገል ቀዝቃዛ ጦርነት ቀዝቃዛ በቀል የብልህነት፣ የጀግንነት እና የአዋቂነት ምልክቶች ከሆኑ ቆይተዋል::

ከልብ ይቅር ማለት የተሳናቸው ግለሰቦችም ሆኑ አገራት ለምን ፈጽሞ በደልን መርሳት ተሳናችሁ ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት ምክንያት እንዴት መርሳት ይቻላል? ለምሳሌ የናዚ የጦር ወንጀለኞች 6 ሚሊዮን አይሁዶችን አሰቅቀው በጭካኔ መጨፍጨፋቸውን እንዴት መርሳት ይቻላል ይላሉ:: ነገር ግን ነገሮችን ማቻቻል ይቻላል:: ይኸውም ልክ ዛሬ ጀርመን እና እስራኤል የሚያደርጉትን የንግድ፣ የሳይንስና የባሕል ግንኙነት የመሳሰሉትን ትብብር ማየቱ ብቻ በቂ ነው::

ይህ ዓለም አሁን የደረሰበት ደረጃ በምጣኔ ሀብት በኩል ያለውን መቀራረብ ለማስተናገድ ይቻለው ዘንድ ወራሪዎችን ብሎም በግፍ ሥራ የታወቁትን ሁሉ በቸልታ እያለፈ የሆዱን በሆድ ይዞ አብሮ መኖርን እየለመደው መጥቷል::

በቂም በቀል የነደደን ልብ ይዞ እና ሸሽጐ በገጽታ ፍቅር ታራቂ እና ይቅር ባይ መስሎ መታየት እውነተኛ ይቅርታን አያመጣም:: ከራስ ጀምሮ ለጐረቤት ለቀየው ለአገር ለዓለም ይቅርታ ማድረግ ይገባል::

ስለዚህ ታራቂ የሚመስሉ ግን የቂም ልብ ያላቸው ወገኖች አሉ ወደሚለው ማጠቃለያ እንደርሳለን::

ከዚህ በላይ ነገሮችን ማቻቻል እንጂ ፈጽሞ መርሳት አይቻልም በሚለው ርዕስ ተነጋግረናል፤ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በሦስተኛው ርዕስ ላይ እንነጋገራለን::

### ሐ. በቀልን የማይረሳው ይቅርታን የማያውቀው ዓለም

ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የሚመነጨው ለማንኛውም ጭካኔ የነፍስ ግድያ ቅጣት ወይም አፀፋ ካልተመለሰ እኩይ ባሕርይ ያላቸው ነፍሰ ገዳዮች ይሰለጥኑብናል:: ስለዚህ ነፍሰ ገዳዮች መገደል፣ መቀጣት አለባቸው ከሚል እጅግ አሻሚ ጽንሰ ሐሳብ በመነሳት ነው::

ለምሳሌ ቪክቶር ፍራንክሊንን የመሳሰሉ ፈላስፎች «በእኛ ላይ በሚደርስብን በደል አይደረግብን፣ አትግደሉን ልንል መብት ከሌለን የሚደርስብንን በአጸፋው ለመከላከል እኛም መብት አለን» ብሏል።

ይህ አካል ይቅርታ ፈጽሞ የማያውቀው የበቀል ዓለም ነው። በቀል ይህችን ዓለም ከታች እሳት ከላይ እሳት ሆኖ እያጋያት ይገኛል። ከአዳም የበኩር ልጅ ቃየን ጀምሮ ወንድሙን ለመበቀል የማይጐመጅ ፈጽሞ አይገኝም። እንዴት? እስቲ በዝርዝር እንመልከተው።

አዳም ሁለት ወንዶችንና ሁለት ሴቶች ልጆች ወለደ።* አንደኛዋ የቃየን መንትያ ስትሆን ሁለተኛዋ ደግሞ የአቤል መንትያ ነበረች። የአቤል መንትያ መልኳ ውብ ቢሆንም እንደ የቃየን መንትያ አልነበረችም። ስለዚህ ታላቅየው ቃየን ከእራሱ ጋር የተወለደችውን ማግባት ይፈልግ ነበር።

አባታቸው አዳም ግን ዘር ለማራቅ ሲል ከአቤል ጋር የተ ወለደችውን ለቃየን፤ ከቃየን ጋር የተወለደችውን ደግሞ ለአቤል አለዋውጦ አጋባቸው። በእዚህም ቃየን እጅግ ተናደደ፤ ቂም በወንድሙ ላይ ያዘ። በእዚህ ሳይበቃ እግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርቡ ዘንድ ሁለቱንም አዘዛቸው። ከሁሉ በፊት ወንድሙን የጠላው ቃየን መሥዋ ዕት ከማቅረቡ በፊት ከወንድሙ ጋር መታረቅ ሲገባው ከነቂሙ ከስንዴው ምርት አሰሱን ገሰሱን እንክርዳዱን ሳይለይ «እግዚአብሔር አይበላው» በሚል የቸልተኝነትና የንቀት ፈሊጥ መስዋዕት አቀረበ።

አቤል ግን ከበጐቹ መካከል በእርጋታ ለአምላኩ የሚሆን ነጭ ቀንዱ ያልከረከረ፣ ጸጉሩ ያልዘረዘረ፣ ጥፍሩ ያላረረ ንጹሕ በግ ከንጹሕ ሕሊና ጋር ለአምላኩ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደመሥዋ ዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም ይለናል መጽሐፍ ቅዱስ።

* ኦሪት ዘፍ. 4



ለመሆኑ የአቤልን ምኑን ነው የተመለከተው? የሰውን የውስጠኛ ውን ክፍል የሚመረምረው እግዚአብሔር የአቤልን ልብ ነበር የተመለከተ ው። አቤል ከቂም በቀል የነጻ ትሑት ደግ የዋሕ ልብ ነበረው። አቤል ቃየንን ወንድሙን ከልቡ የሚወድ ንጹሕ ጠባይ ነበረው። አቤል የአምላኩን ዓይኖች በትሕትናው ሳባቸው፤ ከዚህ በኋላ ነው እግዚአብሔር ወደ አቤል መሥዋዕት የተመለከተው።

በአቤል ልብ ውስጥ እግዚአብሔር ምን የሚያስደስት ነገር አየ? የአቤል ልብ የይቅርታ ልብ ነበር። ይህ ነው እግዚአብሔርን የሳበው። መሥዋዕቱንም እንዲያሸት ያደረገው፣ ከሰማይ የወረደች እሳት የተ ዋሃደችው ይህንን የይቅርታ መሥዋዕት ነው።

ታዲያ አቤል እና ይቅርታው በድንጋይ ከተገደሉ በኋላ ጌታ እስከተወለደ ጊዜ ድረስ ይህች የይቅርታ መሥዋዕት ተስተጓጉላ ነበር። ከባድ ናት፤ ይቅርታ ከልብ ውስጥ በደልን አጥቦ በንጹሕ ሕሊና መሆን፣ በደልን ዞር ብሎ አለማሰብ እና መርሳት በጣም ከባድ ነገር ነው። ለዚህም ይመስላል ዓለም በተለባበሰ ይቅርታ እያዘገመ ያለው።

ቃየን የይቅርታ ሰው አልነበረም። እግዚአብሔር ቃየንን «ለምን ተናደድህ ለምን ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚያበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅህ ታደባለች ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው» ብሎ ነው እግዚአብሔር የመከረው። ቃየን ግን በበቀል መንፈሱ ሐሳቡ ጸና። ወንድሙ አቤልንም በድንጋይ ጨፍጭፎ ገደለው። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ቃየንን «ወንድምህ አቤል ወዴት ነው?» አለው።

ልብ በሉ ቃየን ፊቱ ሲጠቁር ሲናደድ ከእራሱ ጋር ተጣልቷል። ወንድሙን በመግደሉ ከወንድሙ ጋር ተጣልቷል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ስለወንድሙ ስለአቤል ሲጠይቀው በድፍረት «አላውቅም የወንድሜ ጠባቂ እኔ ነኝ ወይ?» ብሎ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣላ።

«ምን አደረገህ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ ሰማይ ይጮኻል። አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ። ምድርንም ባረስህ ጊዜ እንግዲህ ምድር ኃይልዋን አትሰጥህም በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ» ብሎ እግዚአብሔር ረገመው።

ከሁሉ የሚያሳዝነው ቃየን ስለእራሱ የተናገረው ነው። «ኃጢያቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት። እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ ከፊትህም እሰወራለሁ በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል።»*

ቃየን ፈጽሞ ይቅርታ የሌላቸው ሰዎች አባት ነው ዘወትር ለበቀል ዓይኑ የፈጠጠ፤ ለጥላቻ ጥርሱ የገጠጠ ሰው ነው። በግልጽ የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማ እንኳን ወደኋላ ሊመለስ ተሳነው።

በእዚህ ዓይነት የተገደሉ አቤሎች የደም ድምፅ ከምድር ወደ ሰማይ እየጮኸ ይገኛል። የበቀል ሰዎች ግን እራሳቸውን ሲጠቅሙ ፈጽሞ ታይተው ተሰምተውም አይታወቁም። ኰብላይ ተቅበዝባዥ መሆን ነው ትርፋቸው።

ለእነዚህ ሰዎች ምድር እንኳን አትታዘዛቸውም ኃይልዋን አትሰጣቸውም። በቀልን የሚወዱ ይቅርታን የሚጠሉ ሰዎች መጨረሻቸው ውድቀት መሆኑን የእዚህችን ዓለም ታሪክ መመልከት ብቻ ይበቃል።

የይቅርታ ሐሳብን የሚያከብሩ በየዋህነት የሚጓዙ ቅን ሰዎች ስለጠፉ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት «ደግ ሰው አለቀ» ብሎ በምሬት ተናግሯል።

* ዘፍ. 4÷1–፩፯



የበቀል ሰዎች ስለበዙ ደግሞ «ሰነፍ በልቡ (እግዚአብሔር) አምላክ የለም» ይላል ካለ በኋላ «በሥራቸው ረከሱ ጐሰቆሉም በጐ ነገርን የሚሠራ የለም የሚያስተውል እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ ሁሉ አመጹ በአንድነትም ረከሱ። በጐ ነገርን የሚሠራ አንድስ እንኳ የለም። ጉሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው። በምላሳቸውም ሸነገሉ። ከከንፈራቸው በታች የእባብ መርዝ አለ። አፋቸው መርገምንና መራራ ተሞልቷል። ደምን ለማፍሰስ እግራቸው ፈጣን ነው። ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳቸው አለ። የሰላምን መንገድ አላወቋትምና። እግዚአብሔርን መፍራት በፊታቸው የለም። ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉ» እያለ የሰላምን መንገድ ስለማያውቁ ስለበቀል ሰዎች ጥፋት አምርሮ ይናገራል።*

ከዚህ ዓለም ፈላስፎች መካከልም የጸብን እና የበቀልን መንገድ የሚደግፉ አሉ። ለምሳሌ ያህል Nietzsche የተባለው ፈላስፋ የክርስትናን፣ የፍቅርን፣ የእርቅን፣ የይቅርታን መንገድ እንደ ወኔ ቢስነት ይቆጥራል። የሞራል ሕግን ሳይቀር ይነቅፋል፤ ትህትና፣ ይቅርታና መቻቻል ወደ ስቃይና እንግልት የሚወስድ ደካማነት ነው ብሎ ያስተምራል።

ይህ አቀራረብ ታላላቆቹን የይቅርታ ሰዎችን ሳይቀር ሳይፈትን አልቀረም። የሕዝቦችን ስቃይ ለመታደግ አመጽ ጥሩ አማራጭ ይሆን ብለው እንዲጠራጠሩ ገፋፍቷቸዋል።

እስከዚህ ድረስ ስለጨካኙ የበቀል ዓለም ካወሳን ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስለይቅርታ በጥቂቱ እንዳስሳለን ።

* መዝ. 10÷1–፩፯

**የዘመናችን ይቅርታ**

በእዚህ ዘመን ይቅርታ በጥላቻ እና በበቀል ተጠቅታ ትገኛለች:: ብዙዎቻችን ለይቅርታ ጀሮ መስጠት ተስኖናል ዓለም በበቀል ተራ ቅቃለች:: ከጥላቻዋም የተነሣ በአንድ ጊዜ የሰውን ልጅ የሚያዳፍን አዳፍኔ ፈልስፋለች::

ሂሮሽማና ናጋሳኪ የተባሉ የጃፓን ግዛቶች ላይ አውቶሚክ በምብ ጥላ ፍጹም ጥላቻዋን ገልጣለች:: ኃይልን በኃይል ማሸነፍን እንደ ትክክለኛ መንገድ ቆጥራዋለች::

**ጥላቻ እና በቀል በኢራቅ ከተሞች አጥፍቶ ማጥፋትን አውጃለች:: አውሮፕላን ተሸክማ በኒውዮርክ ሕንፃዎች ላይ እንደሚሳኤል ፈንድታለች:: በአፍጋኒስታን ሰማይ ምደሩን በፈንጂ አተራምሳዋለች:: በቀል በእዚህ ዘመን እጅግ ሰልጥና ትገኛለች:: የእስራኤል እና የፍል ስጤም ጦርነት ይኸው ዓለምን አስጨንቆ ይገኛል::**

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት 6 ሚሊዮን አይሁዳውያንን የጨ ረሰችው ቂም በቀል ነች:: ክፋና ደጉን የማይለይ ሕፃንን በግፍ ያስገደለችው ጨካኟዋ በቀል ነች:: ለእዚህም ነው የዓለማችን ትልልቅ ሰዎች የበቀልን ሐሳብ ሲዋጉ እራሳቸውን አሳልፈው ለሞት የሰጡት:: በነገራችን ላይ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ያለቀው ሕዝብ ብዛት 36 ሚሊዮን ይባል እንጂ ከዚያ በኋላ በጦርነቱ ምክንያት የጠፋው ሕይወት ቤት ይቁጠረው::

ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የተባሉት የሰብአዊ መብት ተሟጋች «እንደወንድም እና እህት አብረን መኖር ካልተማርን እንደቂል አብረን እናልቃለን» ብለው እንደተናገሩት ብልሆች ከሆንን ከይቅርታ ጉራ መሰለፍ ይኖርብናል:: አለበለዚያማ ባለፈው ቂም ላይ ቂመን ካለይቅርታ ከኖርን እኛም ሆነን አካባቢያችን እንዴት ሰላም ሊያገኝ ይችላል?

ኢትዮጵያ ሀገራችን የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የመጀመሪያዋ ተጠቂ ነበረች:: በዚህም ሰበብ በጊዜው የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃ/ሥላሴ በቢቢሲ ሬዲዮ ጣቢያ ለመላው ዓለም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ ንግግር አድርገው ነበር:: ጊዜውም ታኅሣሥ 1930 ዓ.ም. እ.ኤ.አ ነበር::



«ደግነት፣ ትህትና መሥዋዕትነት የሞላበትን የዓለም መድኃኒት ሕይወት ልብ አድርገን ስናስብ የሰጠንንም ሕግጋት ስንመለከት የክርስቲያን ሕዝብ እየተ ባለን እርሱን ባለመከተላችን እንዴት የሚያሳፍረን ነው:: በእዚህ ስም የተገባን ብንሆን ሰላም በምድር ሁሉ ላይ ይነገሥ ነበር:: ሰው በዘለዓለማዊ አምላክ ፊት ስብሐት እያሉ ሳያቋርጡ ከሚዘምሩት ሕያዋን መላእክት ይስተካከል ነበር» ብለው ተናገረዋል::

እኚህ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በሥራቸው የዓለም አክብሮት እንደማኅተማ ጋንዲ እና ማርቲን ሉተር ኪንግ የተጐናጸፉ ቢሆንም የገዛ ሕዝባቸውና ወገናቸው ግን በምቀኝነትና በበቀል መንፈስ ተነሳስቶ ታላቅነታቸውን ሊሸፍን ሲጣጣር በማየታችን ልባችን እጅግ ያዝናል::

ጆን ፖል የተባሉት የሮም ሊቀ ጳጳስ በቅርቡ የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ሲፈጸም ከመላው ዓለም የአክብሮት የፍቅር ገፀ በረከት ተለ ግሷቸው ነበር:: ታዲያ እኚህ ሰው ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የበለጠ እንዴት አክብሮት ሊቀዳጁ ቻሉ ብለን ስንጠይቅ? ጆን ፖል የሚያከብር ሕዝብ ነበራቸው:: የእኛው ኃ/ሥላሴ ግን ገድለው አርቀው በሚቀብሩ ታሪ ክን በሚሸፍኑ፣ በበቀልና በክፋት አውራዎች ተከበው ነበር ከማለት በስተ ቀር ሌላ ልንለው የምንችለው ነገር የለንም::

ወደቀደመ ነገራችን እንመለስና ንጉሡ የይቅርታ ሐሳብን እንዴት እንደገለጹት ማስተዋል ይገባል::

ክርስቲያኖች የክርስቶስን ይቅርታ የወረሱ፣ በሰላም ፋና ቀሪውን ዓለም የሚያበሩ የይቅርታ መቅረዞች ናቸው:: ይህም በአንደኛው ክፍለ ዘመን በሚገባ ታይቷል:: ከእዚያ ወዲህም በእግዚአብሔር ምርጥ ቅዱሳን ሲገለጥ ይገኛል:: ግን እኛ የአዳም ልጆች ለይቅርታ ሐሳብ ሕይወታችን የተገዛ ቢሆን ይህንን የጨለማ ዓለም መለወጥ በቻልን ነበር::

አሁንም ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃ/ሥላሴ ከተናገሩት መካከል እንዲህ የሚል ቃል ይገኛል:: «ማንኛውም ጥቅም ወይም ማንኛውም ምክንያት ጦርነትን ማጽደቅ የለበትም» ይሉና በታላቅ ጸጸት «መቼስ ምን ይደረግ? ምንም እንኳ የጠቢባንን ድካም ዋጋ የማያስከብርም ቢሆን የክፉ መንፈስ ጥላ በዓለም ላይ እንደተንሰራፋ መኖሩም እውነት ነው:: ትዕቢተኞች በፈተናው እየወደቁ ሕዝባቸውን ወደ ወንጀልና ወደ ጥፋት ሲመሩ ይገኛሉ» ብለዋል::

ቂምንና ጥላቻን በአጭሩ መቅጨት ይቻላል:: እንደ እሳት ከተ ቀጣጠለ ሥር ከሰደደ በኋላ ግን የሚጠይቀው ዋጋ ከ... እስከ አይባልም:: ለትልቁም፣ ለትንሹም ጥቅም ሲባል የሚፈሰው የሰው ደም ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ይቅርታ በየትኛውም ዋጋ ሊተመን አይችልም::

### የይቅርታ ሐሳብ ከየት ተገኘ?

የይቅርታ ሐሳብ ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ ነው:: እግዚአብሔር ወልድን ከመንበሩ የሳበው ይቅርታ ነው:: በሰዎችና በሰዎች መካከል፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል፤ በገዛ በሰው ውስጥ በሕዋሳቱ መካከል ያለውን ጠብ ለማስወገድ ነው ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣው:: እስከመስቀል የታዘዘው የሞተው፣ የተቀበረው፣ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ለእዚህ ለታላቅ ቁም ነገር ይቅርታ ሲል ነው::

ቅዱስ ኤፍሬም የተባለ ሊቅ «ዘኢይትአወቅ ተከሥተ ወዘኢይት ረአይ ተርአየ ያልታወቀ ታወቀ የማይታየው ታየ»* ሲል ጠፍቶ የነበረው እንደ አዲስ የተከሠተው አምላካዊ ይቅርታ ታየ፣ ተገለጠ ማለቱ ነው:: ነገር ግን እኛ ክርስቲያኖች ይህንን ክርስቲያናዊ ይቅርታ በተግባር ለመተ ርጐም ተስኖናል::

በኢሳይያስ መጽሐፍ ላይ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ጥያቄ ይጠይቁታል:: አንተን ካላወቅንህ እንዴት እንጾማለን? እንጠወልጋለን፣ እንክሳለን፣ እንሰግዳለን ከቤተ መቅደስህ እንጸልያለን አንተ ግን በምሕረት

* የረቡዕ ውዳሴ ማርያም ም.6



አልጐበኘኸንም ለምን ተውከን? ብለው ሲማረሩ ሰምቶ ኢሳይያስን ጮክ ብለህ ንገራቸው ይለዋል በኃይል ጩህ! ለሕዝቤም መተላለፋቸውን ንገራቸው::

«እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ ሠራተ ኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ:: እነሆ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ» ይላቸውና:: እኔ የመረጥኩት ጾም ይህ ነውን? ብሎ ይጠይቃቸዋል:: አመድ ነስንሰን ብንጾም ብንዘልና ብንጐሰቁል ዋናው የጾም መሠረታዊ ቁም ነገር ካልተፈጸመ ጾሙ ከንቱ ነው ይለናል::

እግዚአብሔር እንዴት እንድንሆን ነው የሚፈልገው? በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ የጾም ቀን ምን ዓይነቱ ነው:: ከመጾማችን እና ከመጸለያችን በፊት «የበደልን እሥራት ትፈቱ ዘንድ፣ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ፣ ቀንበሩን ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? እንጀራችሁንስ ለተራበ ትቆርስ ዘንድ፣ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታስገባ ዘንድ» ብሎ በአምልኮ ውስጥ ያሉ ሁሉ ከበደል ከግፍ ከበቀል የነጹ ሆነው ንጹሕ ነፍስ ይዘው ይቀርቡ ዘንድ በአጽንዖት ያሳስባል:: እንዲህ ብናደርግ የይቅርታ ሰዎች ብንሆን ምን እናገኛለን?

«የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል፤ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል፤ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል፤ የእዚህን ጊዜ ትጠራለህ፣ እግዚአብሔርም ይሰማሃል፤ ትጮሃለህ፣ እርሱም እነሆኝ ይልሃል» እግዚአብሔር እንዲህ እያለ የይቅርታ ሰዎች እንሆን ዘንድ ይመክረናል::

«ከመካከልህ ቀንበርን ብታርቅ፣ ጣትህንም መጥቀስ ብትተ ው፣ (በሰው ላይ ባትጠቁም ባትከስ) ባታንጐራጉርም፣ ነፍስህንም ለተራበ ብታፈስ፣ የተጨነቀውንም ነፍስ ብታጠግብ ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል:: ጨለማውም እንደ ቀትር ይሆናል:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያበራልሃል:: ነፍስህንም በመልካም ነገር ያጠግባታል አጥንትህንም ይጠግናል:: አንተም እንደሚጠጣ ገነት፣ ውሃውም እንደማያቋርጥ ምንጭ ትሆናለህ:: ከድሮ

ዘመን ጀምሮ የፈረሱት ሥፍራዎች ይሠራሉ፤ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል:: አንተም ሰባራውን ጠጋኝ፣ የመኖሪያ መንገድንም አዳሽ ትባላለህ» ይለናል::*

ለእዚህ ሁሉ ክብር ለመብቃት ግን ከሁሉ በፊት የእርቅ የሰላም ሰው መሆን ያስፈልጋል:: የይቅርታ ሰው ቢጸልይ ጸሎቱ ከጸባዖት ጆሮ ይደርሳል፤ ይሰማል:: የይቅርታ ሰው ቢጾም ጾሙ ዋጋ አላት:: ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ሥርቆት ትርጉም የለውም:: ነፍሰ ገዳይ አንድ መቶ ሃምሳውን መዝሙረ ዳዊት በቃሉ ቢያነበንብ፣ ቢጾም፣ ቢጸልይ ከነፍሰ ገዳይነቱ ካልተመለሰ፣ ካልተጸጸተ ሊድንና ስዕለቱ ሊሰማ አይችልም:: አንድ ሰው በሽፍትነት ይኖር ነበር ይባላል:: ግን በልማድ ክርስቲያን ነው፤ ለእዚህም በልምድ ጠዋት መዝሙረ ዳዊት ሳይደግም መዋል አይችልም ነበር:: ይህ የሽፍቶች አለቃ አንድ ጊዜ ጭፍሮቹን ለቅሚያ አሠማርቶ እርሱ ጸሎት ይዟል::

ጭፍሮቹ የሚዘረፉ ሰዎች ያገኙና ገንዘብ አምጡ ይላሉ ተዘራፊዎቹ እንቢ በመንግሥት አገር እያሉ ሲጨቃጨቁ የሽፍቶቹ አለቃ ይሰማል:: ዳዊቱን እየደገመ እረዷቸው በሚል የምልክት ቋንቋ አንገቱን ያሳያቸው ጀመረ:: እጁን አሰይፎ እረዷቸው እረዷቸው እያለ ተመልሶ ግን ዳዊቱን ያነባል:: ታዲያ የዚህ ሽፍታ ጸሎት እውን ከጸባዖት ጆሮ ትደርሳለች? ይልቅ የሚያሳርዳቸው የሚያስገድላቸው መንገደኞች ደም ወደ ጸባዖት መጮሁ ነው እውነቱ:: ስለዚህ የበቀልና የግፍ ሰዎች ፈጽሞ የእግዚአብሔር ወዳጆች ሊሆኑ አይችሉም::

## በጸብ መንገድ የተሞከሩ አንድነቶች ውጤት

የግብጽ ነገሥታት ፈርዖኖች፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር፣ ታላላቆቹ ነገሥታት እነ አርጤክስስ እና ብልጣሶር፣ የሮማ ነገሥታት ቄሳሮች በዘመናቸው አውሮፓን፣ እስያን፣ ከፊል አፍሪካን በግዛታቸው ጠቅልለው በኃይል አንድ ለማድረግ ሞክረዋል:: በመካከለኛው ዘመንም የኦቶማን ቱርክ፣ ከዚያም ቀጥሎ አዳዲሶቹ የቅኝ ገዥዎች እነ ናፖሊዮን፣

* ኢሳ. 58፥1–ፍጻ



የራሽያ ዛሮች፣ የቻይና ጥንታውያን ነገሥታት፣ የዐረቡ ዓለም ሡልጣኖች በተቻላቸው ግዛታቸውን በኃይል ለማስፋፋት ተጣጥረዋል:: የቅርቧ እንግሊዝ «በግዛቴ ፀሐይ አይጠልቅም» ብላ ትፎክር የነበረበት ዘመን እሩቅ አይደለም:: የጃፓን ወታደራዊ ጥንካሬ የሩቅ ምሥራቅ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን አዲሲት/ዋን ዓለም አሜሪካንም በሁለተኛው ዓለም ጦርነት አስደንግጦ ነበር:: ግን ይህ ሁሉ በኃይል የተነሣ ጦረኛ በየተራ በሌላው ኃይለኛ እየተሸነፈ፣ እየተኮማሸሸ፣ እየተሰበሰበ እርቦ የምታክል ምድር ውስጥ ሲታሠር እናየዋለን::

ናፖሊዮን አውሮፓን አንድ ለማድረግ ቢጥርም ኃያልነቱ በሌላ ኃይል ተገትቷል:: ዘንድሮም ይኸው የኃይል ግፊያ ትንንሽ አገራትን እስኪጨፈልቅ ድረስ ዓለም ሲተረማመስ እናየዋለን:: ግን በዚህ ሁሉ የኃይል፣ የሁከት፣ የማደናገር አካሄድ ዓለማችን ወደ አንድነት ልትመጣ ፈጽሞ አልቻለችም:: የቅርቦቹ የቅኝ ገዥዎች በግፍ ያስጨነቋቸው ሕዝቦች በታላቅ መሥዋዕትነት ሠንሠለቶቻቸውን ከእጃቸው ላይ አውልቀውታል::

ታላቁ ሰላማዊ ሰው ማኅተመ ጋንዲ ህንድ በእንግሊዞች ቅኝ በተያዘች ጊዜ የተወለደ በባርነት እና በጥቃት ውስጥ ያደገ ሰው ነው:: የሚገርመው የበቀል ሰው መሆን ሲገባው ካለ አመጽ ሕዝቡን የሚታደግ ነጻ የሚያወጣ ሰው ለመሆን ታድሏል::

አንድ ጊዜ ይህ ሰው «ባንቤ» የተባለው የባሕር ዳር አካባቢ ምስኪኖች ህንዳውያን የጨው ምርት የሚያመርቱበትንና ለዕለት ምግባቸው የሚሆን ገቢ የሚያገኙበትን አካባቢ እንግሊዞቹ ወስደው ጦማቸውን ሲያሳድሯቸው ማኅተመ ጋንዲ ከስምንት ሰዎች ጋር ሆኖ የ228 ማይል ጉዞውን ጀመረ:: ይህ ቁጥር ግን ቀስ በቀስ እየጨመረ በሚሊዮን የሚቆጠር ሆነ:: ጋንዲ ወደ ወንዙ ዳርቻ ሄዶ በግሉ ጥቂት ጨው ቀረጥ ሳይከፍል ወሰደ:: ይህም እንግሊዞች የሚፈጽሙትን ሕገወጥ ጭካኔ ለመቃወም ነበር:: በዚህ ጊዜ የእንግሊዝ ወታደሮች በድብደባ እና በጥይት ሕዝቡን ለማገድ እንቅስቃሴ ጀመሩ:: ማኅተመ ጋንዲ ለሕዝቡ የሰጠው መመሪያ ቀጭን ነበር::

«ቢመቷችሁ መልሳችሁ አትምቷቸው፤ ሌላው ቀርቶ ቢጮሁባችሁ መልሳችሁ አትጩሁባቸው:: ነገር ግን ጉዟችሁን አታቁሙ ምናልባት ከግባችን ከመድረሳችን በፊት ከመካከላችን የሚሞቱ ሊኖሩ ይችላሉ:: ምናልባት ከእኛ መካከል ጥቂቶች ወደ እሥር ቤት ልንወረወር እንችል ይሆናል ካሰብንበት ከመድረሳችን በፊት:: ነገር ግን ወደፊት መጓዛችንን ማቆም የለብንም» ብሏል:: ስለዚህም ቡድሂስቱ ማኅተመ ጋንዲ በሰላም መንፈስ ክርስቲያኑን ማርቲን ሉተር ኪንግን ማርኮት ነው፤ «ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ገና በዚህች ዓለም የሚፈልጉት ግብ ላይ አልደ ረሱም» ያለው፤ በየትኛውም የአስተሳሰብና የሃይማኖት ጥላ ውስጥ ያሉ ሰላማውያን ሁሉ አንድ ቋንቋ እንዳላቸው ያሳያል:: ስለዚህ ነው እነናፖሊዮን ያልቻሉትን፣ እነሒትለር የተሳናቸውን ዓለምን የመጨበጥ ሕልም የሰላም ሰዎች በአንድ መዳፍ ተቀዳጅተውት የምናየው::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአምላክነቱ በኃይሉ ይህችን ዓለም እንደ ብረት አቅልጦ ሊያስተዳድራት ሲችል በሰላምና በእርቅ መንገድ ብቻ በመጓዙ በበቀል የነደደችው ዓለም ሳትራራ ሰቀለችው::

ከዚያ ወዲህ የተነሱ ሐዋርያትም ለእርቅ ሐሳብ በሮም አደባባይ ቁልቁል ተሰቀሉ:: ቆዳቸው እንደ ሌጦ ከሰውነታቸው ተገፎ ጨው እየተነዛበት የገዛ ቆዳቸው አሸዋ የተሞላ ስልቻ ሆኖ መከራን ተቀበሉ:: በዚህ ሁሉ ግፍ ውስጥ ግን የሰደቧቸውን መልሰው አልተሳደቡም:: የገ ረፏቸውን መልሰው አልገረፉም:: ይልቁንም ለሚገሏቸው ሲጸልዩ ታዩ እንጂ ስለማንም በክፉ ፈንታ ክፉ አልመለሱም::

ማኅተመ ጋንዲ በእዚህ የፍቅር መርህ ተመርቶ ይመስላል ካለ አመጽ ሕዝቦቹን ከባርነት ያወጣው:: ለብዙ ሕዝብም ምሳሌ የሚሆን ሥራ የሠራው:: ማርቲን ሉተር ኪንግ ለእዚህ ይመስላል ከሰብአዊ ፍጡር በታች ይቆጠሩ የነበሩ ጥቁር አሜሪካውያንን ካለ ጥይት ባለመብት ያደ ረጋቸው::



የሚያስደንቀው ግን ሁሉም የሰላምና የእርቅ ሰዎች በግፍ ተገ ድለዋል:: ማርቲን ሉተር ኪንግ ከማኅተመ ጋንዲ በቀዳው መርህ መሠ ረት አንድ ጊዜ ወደ ነፃነት መጓዝ ከጀመርን መጓዝ ብቻ ነው:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦችም በአንድነት ይቆማሉ:: ይህ ታላቅ ሰው በሚሊዮን የሚቆጠርን ሕዝብ በአንድ ዓላማ በማሰባሰብ በዓለማችን ታሪክ ተወዳዳሪ የለውም:: ፍቅርን እና መልካም ነገሮችን ብቻ በማድረግ:: ከሁሉ የበለጠ ከክፉ አስተሳሰብ እና ክፉ አድራጊዎች ጋር ባለመተባበር የእርቅ የሰላም ሐሳብን ብቻ በመከተል በዓለማችን የተደነቀ ሰው ሆኗል::

እነዚህ ሰዎች ናቸው በእያንዳንዱ ሕዝብ ሕሊና ተቀብረው ሁሉን አንድ ያደረጉና ያስማሙ:: እነሒትለር ያለያዩአትን ዓለም የሰላም ሰዎች አንድ አደረጓት:: በዚህ ባለንበት ዘመንም እግዚአብሔር ዓለምን ካለእርቅ አልተዋትም:: በዘመናችን ትልቅ አክብሮት የተሰጠው ኔልሰን ማንዴላ 27 ዓመት በእሥር ቤት በከፍተኛ ሥቃይ ካሳለፈ በኋላ ከእሥር ቤት ሲለቀቅ ሁሉ የገመተው ይህ ሰው በምን ዓይነት ጥላቻ ተውጦ ይሆን? የሚል ግምት ነበር::

ይህ ግሩም ሰው ግን የእርቅና የሰላም እጁን ለገረፉት ላሰቃዩት ቀድሞ በመዘርጋት ፀበኛውን፣ ክፉውን፣ የበቀልና የጥላቻ ጉራ አስደነገጠ::

«ኔልሰን ማንዴላ ከእሥር ቤት ሲወጣ የጥላቻንና የበቀልን ቃላት ከአንደበቱ አላወጣም:: በይቅርታ እና በእርቅ በተሞላው ክቡር ታላቅ ሰውነቱ አስደነቀን እንጂ» ብለው ዴዝሞን ቱቱ ተናግረዋል::

ከብዙ ዓመታት እንግልት በኋላ ስለፍቅር እና ስለእርቅ ይናገራል ብሎ የጠበቀም የለም:: ከመታሠሩ በፊት ለብዙ ጊዜ በስድብ፣ በአሽሙር፣ በድብደባ ተንገላቷል:: ቢናገር ኖሮ ማንም ሰው ይህንን አልክ ብሎ ሊከሰው የሚችል አልነበረም:: ቤተሰቡን በአግባቡ መምራት አልቻለም ነበር:: እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር የካቲት 4 ቀን 1990 ዓ.ም. ከእሥር ቤት ሲለቀቅ ማንም ስለሥቃይ ይህ ሰው አያውቅም አልተሰቃየም ማለት አይችልም፤ እጅግ ታዋቂ የሆነው ፎቶግራፍ እንደሚያሳየው

ሚስተር ሱሱሉ ከተባለው ጓደኛው ጋር ታስሮ ሳለ ከብዙ እስረኞች መሀል ቋጥኙን ወደ ትንንሽ ፍርክስካሽ ድንጋዮች ሲለውጣቸው ሲሰባብራቸው የሚያሳየውን በመመልከት ብቻ የዚህን ሰው የግፍና የሥቃይ ዘመን መመልከት ይቻላል:: በእስር ቤት ውስጥ የሚደረገው ግፍ ሁሉ የእዚህን ክቡር ሰው መንፈስ ለመስበር፣ በጥላቻም እንዲሞላ ለማድረግ ነበር:: ከዚህ ሁሉ የሥቃይ፣ የጥላቻ፣ የግርፋት ግፊት በኋላ ግን ኔልሰን ማንዴላ በይቅርታና በቅንነት የተሞላ ሆኖ በመገኘቱ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ብለዋል ዴዝሞን ቱቱ::

በአዲሲቱ ደቡብ አፍሪካ አዳዲሶቹ የፍቅር የሰላም አውራዎች ምን ዓይነት አመራር ፈጠሩ:: እንደሚታወቀው በደቡብ አፍሪካ አብዛኛው ጥቁር በጥቂቶቹ ነጮች በከፍተኛ ሥቃይ ብዙ ዘመናትን አሳልፏል:: የበቀል መንፈስ፣ የፍራቻ እና የንዴት መንፈስ በሕዝቡ ውስጥ ታምቆ ቆይቷል:: የአንግሎ ጦርነት ተብሎ በሚታወቀው ወቅት ሁለት መቶ ሺህ ሕዝቦች በአሰቃቂ የማጐሪያ ካምፕ ውስጥ አልቀዋል:: ልክ በአይሁድ ማኅበረሰብ ላይ ሒትለር እንዳደረገው የግፍ ጭፍጭፋ ዓይነት:: ለመቶ ዓመታት እነዚህ ሕዝቦች ከሰው በታች ተቆጥረው ሲማቅቁ ዓለማችን በፓስፖርቷ ላይ ደቡብ አፍሪካ መግባት አይቻልም ከሚለው ማኅተም በስተቀር እነዚህን ተጠቂዎች ነጻ ለማውጣት እምብዛም አልተጨነቀችም:: ኢትዮጵያን ከመሳሰሉት ጥቂት አገሮች በስተቀር ብዙም ከጐኗ የቆመ አገር አልነበረም::

መጋቢት 14 ቀን 1953 ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፍ ባደረጉ ሕዝቦች ላይ ፖሊሶች መተኮስ ጀምረው አብዛኞቹ ሲሸሹ ከኋላቸው በጥይት ተ ደብድበው ያለቁበት ሁኔታ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: በነገራችን ላይ እነዚህ ሰዎች የተቃወሙት በትምህርት ላይ አዲስ የመጣ የግፍ ሕግን ነበር:: በዚህ ጭፍጨፋ 62 ሰዎች ሕይወታቸውን በቅጽበት አጥተዋል::

የሰዌቶው እንቅስቃሴ በተባለው ግንቦት 8 ቀን 1969 ዓ.ም. የትምህርት ቤት ሕፃናት የተገደሉበትም ዘግናኝ ነበር::



«ደቡብ አፍሪካ በፖሊስ ጣቢያ ማጐሪያ ሚስጢራዊ በሆነ ሁኔታ ያለቁትን ሕዝቦች ዘወትር ታስታውሳለች::»

የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ (ስቲቭ) የተባለው ደቡብ አፍሪካዊ 1500 ኪሎ ሜትር እርቃኑን በፖሊስ መኪና መጐተቱን እስከዚህ ዘመን አይ ረሳውም:: ይህንን ሁሉ ጥቃት የያዘ ሕዝብ ነጻነቱን ሲቀዳጅ ምን ማድረግ ነበረበት:: እንደዓለማችን ትርጉም የዚህ ሁሉ መልስ በቀል መሆን ነበ ረበት::

በሁለቱም የዘር ወገኖች ሕይወታቸውንና የፖለቲካ የሥራ መስካቸውን አደጋ ላይ ለመጣል ዝግጁ ሆነው ሰላምን፣ ይቅርታን፣ ዕርቅን ለማምጣት የወሰኑ መሪዎች በማግኘታችን ዕድለኞች ነን:: የደቡብ አፍሪካ ሕዝቦች ለዚሁ ሁሉ የሰላም መንፈስ በር የከፈተው ግን ከእሥር ቤት ውስጥ የተገኘው ኔልሰን ማንዴላ ነበር::

የእውነት አፈላላጊና አጣሪ አካል የተባለ ዴዝሞን ቱቱ በተባሉ የሃይማኖት ሰው ወይም ጳጳስ የሚመራ ቡድን ተቋቋመ:: በዚህ ኮሚሽን ውስጥ የተመደቡት የበሰሉና በሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚታወቁ ንጹሓን ሰዎች ነበሩ::

ከቂም በቀል ከቅጣትና ከፍርድ ይልቅ ሌላ ዓይነት የሕግ የፍትህ መንገድ እንዳለ ተረዳን:: ይኸውም ባሕላዊው የደቡብ አፍሪካውያን የእርቅ ባሕል ነው:: ዋናው ሐሳብ በቀል ወይም ቅጣት ሳይሆን Unbuntu በተ ባለው ቃል መንፈስ ቁስልን ማዳንና መጠገን ነው:: ስህተቶችን ማረም፣ ሚዛኑንም ማስተካከል፣ የተሰበረውን ግንኙነት መጠገን ታላቁ ፍላጐታችን ሲሆን፤ ተጐጂውንም ሆነ ጐጂውን ማቋቋም፣ በሠራው ሥራ ተጸጽቶ የተጐዳው ወደ ኅብረተሰቡ በሰላም እንዲመለስ ማድረግ ነበር::

ይህ ዓይነቱ የእርቅ መንገድ በብዙ ሕዝብና መንግሥታዊ ተቋ ማት ያልተሞከረና ውጤታማነቱም መሰናክል የበዛበት መሆኑ አያጠያይቅም:: የብዙዎቻችን እምነት ማግኘትውም ወንጀለኛ ቅጣት መቀበል አለበት የሚል ነው:: ሐሳቡ እውነትም አሻሚም ሊሆን ይችላል::

ለመቶ ዓመት የጥቁሩን ዓለም ያስቀቀውን አፓርታይድን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተገላገሉት የደቡብ አፍሪካ ሰዎች በነጻነታቸው ማግሥት የተለያዩ ችግሮች ከፊታቸው ተደቅነው ነበር።

አንደኛ የነጩ ማኅበረሰብ ብዛት በሚሊዮን የሚቆጠር በመሆኑ እና የደቡብ አፍሪካ ዜግነት ያላቸው በምርጫ ውስጥም መሳተፍ የነበረባቸው ሲሆን ከመካከላቸው የአፓርታይድ የፀጥታ ክፍል ሠራተኞች፣ በማወቅም ባለማወቅም ወንጀል የሠራው ክፍል ቀላል ቁጥር አልነበረውም። እነዚህ ሰዎች የጦር መሣሪያ በእጃቸው አለ። አስተዳደሩ ገና ከእጃቸው አልወጣም፤ የንግድ ቁልፍ የሆኑ ተቋማትን ከመምራት ጀምሮ ብዙዎቹ ባለሀብቶች ነጮቹ ነበሩ።

ስለዚህ ደቡብ አፍሪካ ነፃ ብትወጣ አደገኛው ነገር በሕዝብ መካከል የሚነሳው የእርስ በእርስ ጦርነት ነው። በእዚህ ረገድ ደግሞ አሸናፊውና ተሸናፊው ሊለይ አይችልም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ደቡብ አፍሪካውያን ከድጡ ወደማጡ ሂደት ሊጓዙ ነው።

ስለዚህ ነው እነኔልሰን ማንዴላ፣ እነዴዝሞን ቱቱ እና የመሳሰሉት በሳል አመራር ያስፈለገው። በዚህ ጊዜ ነው ሁለቱም ወገን የቀለም እና የስግብግብነትን ባሕርይ ሳያሳዩ ሆደ ሰፊ ሆነው ቁጭ ብለው መምከር የጀመሩት። የሚገርመው ኔልሰን ማንዴላ ለአሠሯቸው እና ላሰቃዩአቸው ባለሥልጣናት ያሳዩት የነበረው ርህራሄና ገርነት በመካከላቸው መተማመንና መደማመጥን ፈጠረ።

የመገናኛ ብዙኃን ሬዲዮው ቴሌቪዥኑ እና ጋዜጣው በሰፊው የሰላም የእርቅ መልእክት እንዲያስተላልፉ ሆነው ተቀረጹ። የአገር ሽማግሌዎችና ምሁራን የሃይማኖት መሪዎች ስለእርቅና ስምምነት ማስተማሩን ተያያዙት።

«ሁለት አማራጭ መስመሮች በፊታችን ተደቅነው ነበር» ይላሉ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን አባላት «በእውነት ባለፈው ስለተሠራው ወንጀል እያጋለጥን እያሠርን እየቀጣን እንሂድ ወይስ ያለፈውን በትምህርትነቱ በታሪክነቱ ወደኋላ ትተን ወደፊት ለሚሆነው እንጨነቅ?»



ለምሳሌ ወንጀለኞቹን አጣርቶ በፍርድ ሂደት ማጋለጥ ተመጣጣኝ ቅጣት መስጠት የሚለውን እንኳን ብንደግፍ። የሰብአዊ መብት ወንጀል ፈጻሚዎች አብረውን እጐናችን የሚኖሩ የእኛው ዜጐች ናቸው። እናም ኃይል ያላቸው አደገኛም ሊሆኑ ይችላሉ። የጦር ሠራዊቱም ሆነ የፖሊስ ኃይሉ የወንጀል ወይም የሥቃይ መሣሪያ ሆኖ ከቆየ በአንድ ጀንበር ወደ በጐ ሥራ ምሳሌነት ወይም ወደ ሰብአዊ መብት አክባሪነት ሊለወጥ አይችልም። የቁጥራቸው መብዛትና የገዳይ መሣሪያ አጠቃቀማቸው ዕውቀታቸውም ከፍተኛ ግንዛቤ ሊሰጠው የሚገባ እውነት ነው።

አዲሲቷን ደቡብ አፍሪካ ለመገንባት ያለፈውን ትቶ በአዲስ መንፈስ ማደግ አማራጭ የሌለው ተግባር ነበር። ሌላው በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቢታይ መልካም ነው የሚለውን አስተሳሰብም ውድቅ በማድረግ ችግራችንን በአፍሪካ ባሕላዊ የችግሮች መፍቻ መንገድ ለመፍታት በሐሳባችን ጸናን።

በሕሊና እሥር ቤት ውስጥ ከእኛ ይልቅ ያላችሁት እናንተ ናችሁና በእርቅ መንፈስ ሁላችንም የባርነት ሠንሠለታችንን እንስበረው። በተከበረው ባሕላዊ እርቅ ሁሉን እንፍታ ብለን ቆርጠን ተነሳን።

Ubuntu

Ubuntu is very difficult to render into western language. It speaks of the very essence of being human. When we want to give high praise to someone we say “Yu u nobuntu;” “Hey, so-and-so has Ubuntu” Then you are generous, you are hospitable, you are friendly and caring and compassionate. You share what you have. It is to say, “my humanity is caught up, is inextricably bound up, in yours.” We belong in a bundle of life.

አቦንቱ የሚባለውን የደቡብ አፍሪካውያን ቃል ለመተርጐም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ቃሉ ሰፊ ሐሳብን የሚያካትት በመሆኑ። ለከፍተኛ ሰብአዊ ስሜት የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ለምሳሌ ለአንድ ሰው ትልቅ አክብሮት መስጠት ሲያስፈልግ ይህንን ቃል እንጠቀማለን። ትርጉሙም «አንተ እጅግ በጣም የምትመች ቀና ሰው ነህ። ከሁሉ ተግባቢ ነህ ስለሰው ትጨነቃለህ ይቅርታ አድራጊ ነህ ወይም በይቅርታ ታምናለህ፤ ያለህን ታካፍላለህ፤ ነፍሴ ከነፍስህ ጋር ተጣምራለች። የውስጠኛው ሕሊናዬ ከሕሊናህ ጋር ተጣምሯል እንለዋለን» ይህንን ሁሉ ሐሳብ የሚተካው ግን Ubuntu አቦንቱ የተባለው ቃል ነው።

ታዲያ ብልጦቹ የደቡብ አፍሪካ ሰዎች ብሔራዊ ችግራቸውን ለመፍታት ይህን ቃል መሪ አደረጉ። ችግሮችንም ቀስ በቀስ መንቀስ ጀመሩ። ዛሬ የእነዚህን ሕዝቦች ምሳሌ ለምን ሩዋንዳውያን ወይም እስራኤላውያን እና ፍልስጤሞች አይጠቀሙበትም የሚል የዓለም አስተያየት በሰፊው ይደመጣል።

ለምን ሩዋንዳውያን ይህንን የአቦንቱ የእርቅ መንገድ አልተጠቀሙበትም በእዚያ ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እርስ በእርስ ከሚጨራረሱ ለምን ይህን አልመረጡም ለምን እጅግ ውብ አገራቸውን አጠፉት?

ለምን ኢትዮጵያውያን ለ30 ዓመታት የብዙዎችን ሕይወት ያጠፋውን ጦርነት በአቦንቱ የእርቅ መንገድ አልፈቱትም። ለምን አሁንስ በመካከላቸው ያለውን ቀላል ችግር በብሔራዊ እርቅ አያስወግዱትም? ለመሆኑ ኢትዮጵያውያን በዚህ ሁሉ የታሪክ ዘመናቸው ችግሮችን የሚያስታርቁበት ቃል የላቸውም ይሆን? ከሌላቸው ለምን ከደቡብ አፍሪካውያን አይዋሱም? ብዙ የአመጽ ቃላት ወርሰን አልነበረ ከእነዚህ ሁሉ የፀብ ቃላቶች ጋጋታ ይልቅ አቦንቱ የተባለውን የእርቀ ሰላም ሐሳብ ብንወርስ ምንኛ በጠቀመን። ግን እኛ ኢትዮጵያዊያን መታረቅንና ማስታረቅን በሚገባ እናውቃለን «ይቅር ለእግዚአብሔር» የተባለ የመታረቂያ ቋንቋም አለን፤ ታዲያ ለምን አንጠቀምበትም ለምንስ ብሔራዊ እርቅ አናደርግም?!



በዚህ የእርቅ ሐሳብ ውስጥ በሰዎች መካከል እርቅን ስናሰፍን መረሳት የሌለባቸው ደግሞ ዕፀዋቱ፣ እንስሳቱ የተፈጥሮው ኃይል እና ውኃው ሁሉ እርቅ ይፈልጋል ።

ምን ይህ ብቻ ከፍትህ፣ ከሥነ ጥበብ፣ ከሥራ፣ ከዓላማ፣ ከትምህርት፣ ከአስተዳደር ጋር ሁሉ መታረቅ አለብን፡

በሁሉም መስክ የታረቀና የተስማማ አካሔድ ካለን ልማቱም ሆነ ዕድገቱ ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን ከላይ የጠቀስናቸው ጉድለቶች ካሉና ካልታረቁ ዘወትር በሽንፈት ውስጥ ይጥሉናል። እርቅ በሁሉም መስክ።

## ምዕራፍ ሁለት

## ይቅርታ ከየት ይጀመር?

ከውስጠኛው ሕሊና ስለይቅርታ ካላሰቡ በስተቀር ወይም በእውነት ካልተለወጡ ይቅር ባይ መሆን አይቻልም። በቀራጥነት ሰውን ሁሉ በምሕረት ዓይን መመልከት የይቅርታ ሰው ያደርጋል። በእውነ ከፍቅር ሰው የበለጠ የታደለ በእዚህ ምድር ማን ይኖራል። የይቅርታ ሰው መሆን ሕፃናትን መሆን ማለት ነው። ሰውነቱ ቆሽሾ ሰላም የሚሰማው ማን ነው? የሕሊና ቆሻሻ ቂመኝነት ነው።

«በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሿሿ ጸናጽል ሆኛለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉ ባውቅ፣ እውቀት ሁሉ ቢኖረኝ፣ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድሆችንም ብመግብ፣ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፣ ሥጋዬንም ለእሳት አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። «ፍቅር ያስታግሳል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አያስመካም ፍቅር አያስታብይም ብቻዬን ይድላኝ አያስብልም አያበሳጭም ክፉ ነገርን አያሳስብም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመጻ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፤ ሁሉን ያምናል፤ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፤ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር

አይወድቅም ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ:: ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል::»* ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ውስጣዊውን የሰው ልጆች የእውነት ምሥጢር የሚያጐለብት ነው:: የፍቅር ስጦታ ያለው ሰው በመላእክት ልሳን ከሚናገረው አንሳለሁ ወይም ተራራዎች በሃይማኖት ከሚያፈልሰው ያነሰ ስጦታ ተሰጠኝ ብሎ እራሱን በትህትና ዝቅ ያድርግ እንጂ ከሁሉ የበለጠው እንደተሰጠው የታወቀ ነገር ነው:

ለምትበልጠዋ ጸጋ ሰው መትጋት ይኖርበታል ያችም ፍቅር ነች፤ ርህራሄ ነች:: ይቅር ባይነት የምትመነጨው ከፍቅር ሕሊና ነው:: አባ ሲድራስ የተባለ ጻድቅ አባት «ወንድሙን የማይወድ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ የለም» እያለ አዘውትሮ ይናገር ነበር::

ፍቅርም በሁለት ትከፈላለች:: ሰውን ማፍቀርና እግዚአብሔርን ማፍቀር:: እግዚአብሔርን ማፍቀር የምትገኘው ሰውን ከማፍቀር ነው ወይም እግዚአብሔርን ማፍቀር የምትገለጠው ወንድምን በመውደድ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ «ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው:: ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙንም ደግሞ እንዲወድ ይህች ትዕዛዝ በእርሱ አለች::»* ይለናል::

ኃጢአትም በሁለት ይመደባል እግዚአብሔርን በመጠራጠር እና ወንድምን በመበደል:: ምክንያቱም ስለእግዚአብሔር ስንል ለወንድሞቻችን ይቅርታ ብናደርግ በጽድቅ ሕይወት እንኖራለን::

ንጹሕ ልቡና ውድ እንቁ ነች:: ይህችም ወንድምን ከመውደድ የምትገኝ ነች:: ወንድሙን የሚወድ ልቡናው ከቅናት፣ ከስስት፣ ከምቀኝነት፣ ከቂጣ፣ ከአድመኝነት ይነጻለታል:: ስለዚህም የበቀል ሰው ለሰው ሁሉ ፍቅር ሊኖረው ፈጽሞ አይችልም:: ከእዚህ ዓይነቱ ሕሊና ሽሽ ይላል የእርቅ፣ የሰላም፣ የፍቅር ዓለም::

* 1ኛ ቆሮ. 13÷1–ፍጻሜ
* 1ኛ ዮሐ. 4÷20–21



ሲያል ወዴት አለ? ጥርጥር የለውም ከበቀለኛ ሰው ሕሊና ውስጥ ብቻ ነው:: የዲያቢሎስ ሌላኛው ስሙ ሰይጣን ይባላል:: ትርጉሙም ባለጋራ፣ ጠላት፣ ወደረኛ አሳጭ፣ ይቅርታ የማይወድ በቀለኛ ማለት ነው::

የበቀል አገሯ ወዴት ነው? ባሕረ ጽልመት፤ የበቀል መኖሪያዋ ጽልመት ጥልቅ ነው ይኸውም የክፉ ሰው ልቡና:: ፍቅር አልባ ልቡና እንዴት አስፈሪ ነው? የበቀል ሰው ከሁሉ በፊት የገዛ እራሱ ጠላት ነው ሁሉን ይጠራጠራል፤ ሁሉም ጠላቱ ነው:: በዚህ ምድር ብቸኛ የነገር የክፋት ዶሴ የታጨቀበት ልብ መልካም ነገሮችን ሊያስገባ ፈጽሞ አይችልም::

ከበቀል ሕሊናን ቶሎ ቶሎ ማጠብ ያስፈልጋል:: አንድ ቤት ጠዋትና ማታ እንደሚታጠብ እንደሚጸዳ ሁሉ:: የሰላም ሰው ልቡናውን ከክፉ ሐሳብ ዘወትር ማጠብ ይኖርበታል:: ዘወትር ነጻ ያልወጣ፣ እርንት ያልዳሰሰው ልቡና በቂም ሠንሠለት ታስሮ በበቀል ጽልመት ጉድጓድ ውስጥ ይወድቃል:: ይህንን የተጐዳ ለቂም ባርያ የሆነ ሰው ሁሉም በእውነት ሊያዝንለት ይገባል፤ ሊታደገውም ይገባል::

ለቂመኛ ሰው እዘኑለት:: ከሁሉ በፊት የተጐዳው እርሱ ነውና:: በሕሊና የተቀበረችን የበቀል እሳት በአንድ ትንፋሽ ማጥፋት ይቻላል:: ያም ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ነው::

ብዙዎቻችን እስከዚህ ዘመን ሌሎችን ይቅር ማለት ተስኖናል:: ሌላው ቀርቶ ለገዛ ራሳችን እንኳን ይቅርታ የለንም:: ወንድሞቻችንን ጠልተናል፤ አካባቢያችንን ጠልተናል፤ ማኅበረሰቡን ጠልተናል፤ ከዚህ በኋላ ራሳችንን ጠልተናል:: ወዴት እየሄድን ነው? የበቀል ድንበሯ አጥሯ ታላቅ ጥፋት ነው::

ከመጻሕፍት ሁሉ የላቀው መጽሐፍ ቅዱስ «ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ እርስ በእርሳችን እንዋደድ ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና»* ይለናል:: ዓመጽን ሁሉ

* 1ኛ ዮሐ. 4÷7

የምትሰባብረው የእርቅ ዓለም ነች። ስለዚህ ወንድምን በመውደድ ከሁሉ በፊት ይቅርታ ይጀምራል።

የይቅርታ ሰው ሰላማዊ ነው፤ ስግብግብ አይደለም ለእኔ ይድላኝ ብሎ ለገዛ እራሱ ብቻ አይኖርም። የእርቅ ሰው ቀና ነው። አብረውት ቢኖሩ ቢሠሩ አይቆረቁረውም። በሰው ሁሉ ዘንድ የተወደደ የተደነቀ ነው።

የይቅርታ ሐሳብም መጀመር ያለበት ከእዚህ ነው የእዚህ ግዙፍ ሐሳብ ዓላማ ምንድነው። ዓላማችንን ማስታረቅ፤ ሰውን ከገዛ እራሱ፣ ሰውን ከቤተሰቡ፣ ከሕፃናቱ፣ ከሚስቱ፣ ከቀዬው፣ ከአገሩ ጋር ሁሉ ማስታ ረቅ ነው። ታዲያ ለእዚህ ታላቅ ሐሳብ እራሳችንን የሰጠን፣ በሐሳቡ ተስ ማምተን የሰላምና የእርቅ ማኅበር አባል ለመሆን የወሰንን ስንቶቻችን ነን።

ብዙዎቻችን በእዚህ በክፉ የበቀል ዓለም ተመርረን ይሆናል። ማን ያውቃል? በበቀል ጥይት አባቶቻችንን ወንድሞቻችንን የምንወዳቸውን ሁሉ አጥተን ይሆናል። ምን እናድርግ «ለጥርስ ጥርስ፤ ለዓይን ዓይን» እንደተባለው ይህችን ዓለም እኛም በበቀል እናቃጥላት?

አይደለም! ማኅተማ ጋንዲን ተከታዮቹ የሕንድን ሕዝብ የሚገድሉትን መግደል አለብን «ዓይን ስለዓይን» ተብሏል ብለው ቢጠይቁት። «ዓይንህን ሲያጠፋህ ዓይኑን ካጠፋኸውማ ዓለማችን በሙሉ ዓይነ ስውራን ትሆናለች» ብሎ መልሶ ነበር።

ይልቅ የጌታችን የመድኃኒታችን አምላካዊ ቃል ነው የሚያዋጣው «ግራህን ሲመቱህ ቀኝህን ስጥ» የሚለው።

ይልቅ ከእነሱ ተከትለው ባርነትን የተዋጉ የነፃነት ልጆች መንገድ ነው የሚያዋጣን፤ ሰላም የሚሰጠን፤ የሚያስማማን የእርቅ መንገድ ብቻ ነው።



# ምዕራፍ ሦስት

## ከራስ ጋር መታረቅ

«ብዙ ሰዎች እራሳቸውንም ሌሎችንም ሰዎች ይቅር ለማለት ፈጽሞ ተስኗቸዋል። በእዚህ ፈንታ እራሳቸውን በማታለል በመሸንገል መኖርን መርጠዋል።» እራሳችንን ጥያቄ ብንጠይቀው እንዲህ የሚል «ለስንት ጊዜ ከእራስህ ጋር ተጣልተህ ታውቃለህ?» ውስጠኛው አካላችን የሚመልስልን እኔ ከእኔ ጋር መቼ ተስማምቼ አውቃለሁ? የሚል ነው። እንዲህ ከሆነ እርቅ መጀመር ያለበት ከገዛ እኛነታችን ነው ማለት ነው።

በመሠረቱ በአንድ ሰው ውስጥ ሁለት ከተሞች አሉ። መንፈሳዊ ከተማ እና ሥጋዊ ከተማ። የመንፈሳዊ ከተማ ጠባይ የታወቀ ነው። ለነፍስ ያደላ ከምድራዊ ሐሳብ ይልቅ ወደ ዕውቀትና ጥበብ ልግስና እና ሰላም ያዘነበለ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሥጋና መንፈስ ይጣላሉ እንዳለው። አንዱ የአንዱ የበላይ ለመሆን የመሽቀዳደማቸውን ነገር ስናስብ በውስጣችን ፉክክር እንዳለ እንረዳለን።

የታወቀ የሥጋ ጠባይ ሥራ ተገልጿል። ይህንን ሐሳብ ለማብራራት ያህል «ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር» እነዚህ ላይ ማተኮር ነው። ከእራሱ ጋር የተጣላ ሰው ከላይ የዘረዘርናቸው ጠባያት በውስጡ ይሞላሉ።

በተጻራሪው እራሱን ከራሱ ጋር ያስታረቀ ደግሞ የመንፈስ ፍሬ በውስጡ ይሞላል። ይኸውም «ፍቅር፣ ደስታ፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጐነት፣ እምነት፣ የዋሃትና ራስን መግዛት ናቸው»* እነዚህ ናቸው የውስጥን ሰላም የሚያረጋግጡት። ከእራሱ ጋር የተጣላ ግን መንፈሱ የተ ረበሸ የተሰበረ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በአንደኛው መልዕክቱ «ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው ምላሱን ከክፉ

* ገላ. 5፥16–26

ከንፈሩንም ተንኮል ከመናገር ይከልክል፤ ከክፉ ፈቀቅ ይበል፤ መልካምንም ያድርግ፤ ሰላምንም ይሻ ይከተላትም። የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸውና ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው ተከፍተዋል፤ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው»* ይል የለ።

የውስጠኛው ሰውነታችን ማዕበል ነፋስና ንውጽውጽታ ከሌለው ሁሉን በእርጋታ ማከናወን እንችላለን። የብዙዎቻችን ሕይወት ሲፈተሽ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ እልህና ተንኮል ተሞልቶ ይገኛል። ይህ ጠባይ ደግሞ ለቤተሰባችን ለማኅበረሰቡ ለአገርም ታላቅ ሕመም ሆኗል። ረጋ ብለን ወደ ውስጠኛው አካላችን ስንመለከት ብሩህ ሕሊናችን የማይረቡ ቆሻሻ ባሕርያት አውድማ ሆኗል። እንክርዳድ የሚወቃበት ከምርቱ ይልቅ ገርዱ የሚታፈስበት ሕሊና በዝቷል።

ዞሮ ዞሮ ክፉ ጠባይ የሚጎዳው እኛን እራሳችንን በመሆኑ የምንጎዳው ሰው ሁለተኛ ተጠቂ ሊሆን ይችላል። ከእራሳችን ጋር መታረቅ ከሁሉ በፊት አስፈላጊ ነው።

የእዚህ እራስን የመጥላት መንስኤ የተለያየ ነው። ከሁሉ በላይ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው ግን ከልጅነት ጀምሮ የሚቀበሉት ፈተናና ሥቃይ ጥርቅም ነው። ሕሊናን የሚያሳውር ለሰው ከክፉ በስተቀር ደግ የማያሳስብ የበቀል መንፈስ በከፊል የሚመጣው ተደጋጋሚ በሆነ ጥቃት ሥቃይ እና ጭካኔ በተጠቁ ሰዎች ነው። ከሕሊና ሊወጣ የማይችል ትውስታ ስለሚረብሻቸው በእነዚህ ሰዎች ዘንድ ይቅርታ የማይታሰብ ነገር የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። የዚህ በሽታ ምልክቶችና ውጤቶች ከዚህ በታች በዝርዝር የተመለከቱት ይሆናሉ።

ከፍተኛ ራስ ወዳድነት ፣
ኃላፊነት አለመስማት ፣
በወረት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ያለው ፣

* 1ኛ ጴጥ. 3፥10–12



እራስን ከሚገባው በላይ ትልቅ አድርጎ ማየት ፣
ውስጡ በውሸት የተሞላ መሆን ፣
ፍሁም የመሀሀት ወይንም የማዘን ስሜት ማጣት ፣
ጨካኝነት ፣
ባሕርይን መቆጣጠር መሳን ፣
በድንገት ያልተጠበቀ ክፉ ድርጊት መፈጸም ፣
በጥፋቱ ተጠያቂነትን አለመቀበል ፣
እስካልተያዘ ድረስ ወንጀል ከመፈፀም አለመቆጠብ ... ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

ይህ በሽታ የሚመጣው ከላይ እንደተጠቀሰው ሌላው ሰው የማያውቀውም ሆነ የሚያውቀው ጥቃት በለጋ ዕድሜያቸው ይደርስባቸውና ሲያድጉ በውስጣቸው እየተመላለሰ ለሰው ሁሉ ቀና እንዳያስቡ፣ እንዲቆጡ፣ ከፍ ሲልም እስከ ነፍስ ማጥፋት አሰቃቂ ወንጀል እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል። የጉዳቸውን ዓለም ስለማያምኑ ዘወትር በጥርጥር እና አፀፋዊ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ በመዘጋጀት ይኖራሉ።

እንዲህ ዓይነት ሰዎች ለእራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ፈጽሞ ይቅርታ የላቸውም። ምክንያቱም ያጠቋቸው ሰዎች ይቅርታ የማያውቁ ነበሩና። በእዚህ ዓይነት የበቀል ሕይወት የሚታወቁት በአጋጣሚ በትረ መንግሥትና ገንዘብ ከልክ በላይ በሆነ መንገድ በእጃቸው የገባ ጨካኝ መሪዎች ይህንን ዓለም አስቅቀውት አልፈዋል።

ነገሩ ለፍርድ ይቸግራል። ከሰው ጋር መኖር ልክ በጫካ ከክፉ አውሬ ጋር እንደመኖር ሆኖ የሚታየውን ሰው በምን ቋንቋ ስለፍቅርና ርህራሄ ሊያስረዱት ይቻላል?

ሌሎቻችን ግን የበደልን መንገድ በመምረጥ እንደ ቃየል የገዛ ወንድሙን እንደገደለው የሠራነው ክፉ ሥራ እራሳችንን የሚገርፈን የበቀል ሰዎች ነን። የሚያዋጣ መስሎን የበደልን መንገድ መርጠን ብዙ ግፍ ከሠራን በኋላ የባነንን ምሕረት ከእግዚአብሔር ለመለመን እና

ሕሊናችንን ከበቀል ከተንኮል ለመጠበቅ የተሳነን ሰዎች ነን እራሳችንን ለመጥላት የደረስነው።

እኛ በእግዚአብሔር ስንፈጠር ንጹሕ ባሕርይ ተቀዳጅተን እንጂ ያደፈ የቆሸሸ ማንነት አልተፈጠረብንም። ቢሆንም ቅሉ የሥጋችን ባሕርይ ልክ ጢስና አቧራ እንደሚያሳድፈው እንደ ነጭ ልብስ በመሆኑ ኃጢአት በእጅጉ ይስማማዋል።

«ርትዕና ጽንት ለሰው ቢወድ የሚሠራቸው ቢጠላ የሚተዋቸው ለባሕርይው ተስማሚ ግብሮች ናቸው» ጽንት የተባለው በደል በዚህ ዓለም እያየለ በመምጣቱ ሰውም ለእዚህ ተጋልጦ ይገኛል። ከበደል ዓይነቶች ዋነኛው ደግሞ ይቅር አለማለት ነው። ይህ ይቅርታ የተባለ የሕሊና ሀብት ከውስጣችን መጥፋቱ በምን ያስታውቃል? «ንዴትና ጥላቻ በውስጣችን እያደገ ሲመጣ ሌሎቹ መልካም ጠባዮች ተገፍተው ከሕሊናችን ይወጣሉ። ከሁሉ በላይ ግን ይቅርታ ሙልጭ ብሎ ከሕሊናችን ይታጠባል። ጥላቻና ፍቅር፤ በቀልና እርቅ በአንድ ሰው ሕሊና አብረው ሊቀመጡ አይችሉም።»

ሰዎችን ይቅር ማለት ሲያቅተን ወደገዛ ሕሊናችን ዘወር ብለን የበደሉ የቂሙ እና የችግሩ ምንጭ እኔ እሆንን? ብለን ልንጠይቅ ይገባል። ፈጥነን ሕሊናዬን ለማን አሳልፌ እሰጣለሁ? ብለን ልንደነግጥ ወደ ይቅርታም ልንመለስ ይገባል። ምክንያቱም ሕሊናችንንና አካላችንን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ* ተብለን ታዘናልና። ያለ ይቅርታ ደግሞ እግዚአብሔርን ማስደሰት ሰውነታችንንም ቤተ መቅደስ ማድረግ አይቻልም። በሕሊናችን ጓዳ ማነው ያለው? ወደ በቀል የሚስበው እርኩስ መንፈስ ነው ወይስ ለይቅርታ የሚጣራ መንፈስ ቅዱስ?

አንዲት ሴት ልጅ ለመውለድ ትመኝ ነበር ይባላል። ታዲያ ዘወትር እግዚአብሔርን በጸሎት ስትጠይቅ ቆየች። ጸሎትዋ

* ሮሜ 12÷1–3



በበደሏ ተሸፍኖ በቂም በጥላቻ ታጅሎ እየቀረበ ከእግዚአብሔር ጆሮ ሊደርስ አልቻለም። ብዙ ሞከረች በንጽሕና በይቅርታ እንደምንም በቀረበች ጊዜ ተሰማላት ግን በፈለገችው ፍጥነት ልጅ አልተሰጣትም።እግዚአብሔር ግን የለመኑትን አይነሳም የነገሩትን አይረሳም እና እርሱ ባቀደው ሰዓት ይሰጣት ዘንድ ፈቀደ። ሴቲቱ አልታገሰችም አይ እግዚአብሔር ካልሰማኝ ወደ ሰይጣን ልሂድ ስዕለትም ልሳል አለች አደረገችውም። ዛሬም ብዙ ሰዎች ወደ በዕድ አምልኮ እንደሚሔዱት ማለት ነው። ስዕለትዋም ልጅ ከሰጠኸኝ ሰይጣን ሆይ ጋቢ ፈትዬ አለብስሃለሁ የሚል ነበር።

የእግዚአብሔር ጊዜ ደርሶ ኖሮ በአምላካዊው ዕቅድ መሠረት ልጅ ተሰጣት። እርሷ ግን ምንም የሌለው ደሃውና ንፋቱ ክፉውና ጨካኙ ስዕለት የተሳለችለት ሰይጣን ልጅ የሰጣት መሰላት። ልጁ ተወለደ ሴቲቱም በስዕለቷ መሠረት ነጩን ጋቢ ይዛ ሰይጣንን ጋቢ ልታለብስ ፍለጋ ጀመረች። ብዙዎችን ሰይጣንን አሳዩኝ ስትላቸው ይደነግጣሉ። ልጇን ያዘለች እናት ጋቢውን ተሸክማ ሰይጣንን ስትፈልግ ሁለት ሰዎች ተጣልተው ቁሉና ሽማግሌዎች መሀል ተቀምጠው የሚሸመግሉበት ቦታ ትደርሳለች። ጠጋ ብላ መምሩን ሰይጣንን አይተውት ያውቃሉ ትላቸዋለች፤ እክህደከ ሰይጣን ብለው ያማትቡና እንኳን ሳየው እንዲቀርበኝም አልፈልግ ይሏትና ግን ለምን ፈለግሽው ቢሏት «ልጅ የሰጠኸኝ እንደሆነ ጋቢ አለብስሃለሁ ብዬ ተሣልኩ ስዕለቴን ሞላልኝ ይኸው ጋቢውን ላለብሰው እየፈለኩት ነው» ትላቸዋለች።

የተሰበሰበው ሕዝብ በመደነቅ ያያታል፤ መምሩ ግን ፈገግ ብለው «ሰይጣን ሙልጭ ያለ ድሃ ነው እንኳን ልጅን የሚያክል ስጦታ ሊሰጥ አባታችን አዳምን እስከ ልጅ ልጆቹ በእግረ አጋንንት ሲያስቀጠቅጥ በመንፀፈ ደይን ሲጥል ሌላው ቀርቶ አሁን እንኳን ስንሞት ነፍሳችንን ሊቀማ ሊያደባ ነው ኑሮው። ግን ሰይጣንን ጋቢ ለማልበስ ከፈለግሽ እዚህ ጥጉ ጋ ተቀመጪ እና አሳይሻለሁ» ይሏትና ወደ ማስታረቃቸው ይመለሳሉ። ታዲያ ሁለቱን ተገላጋዮች ለማስታረቅ እና ሰላም ለማውረድ ሽማግሌዎች እና ቄሱ ሲሞክሩ አንደኛው ወደረኛ ወይም ጸበኛ አልታረቅም ብሎ ይሟገት ጀመረ። «ፈጽሞ! ሰይፍ በአንገቱ ቢሆር እንኳን

ባለጋራዬን ይቅር አልልም» እያለ ኩታውን ጠብ እርግፍ እያደረገ ሲምል ሲገዘት ቆይቶ ሽማግሌዎቹን ከቁሱ ጋር ትቶ ሲወጣ ካህኑ ያችን ሴት በፍጥነት ይጠሩና «በይ ተከተይና ጋቢውን አልብሽው ሰይጣን ማለት እርቅ የማይወድ እልኸኛ ልብ ያለው ከራሱም ከሰውም ጋር የተጣላ ቸኮ ነው» ይሏታል። ሴቲቱም ሮጣ ጋቢውን ትከሻው ላይ ትጥልበታለች። ሰውየው ምንድነው ይኼ ጋቢ ይላታል? ሴቲቱ ስትመልስ «ሰይጣን ማለት አንተ ነህ። እርቅን እንቢ የምትል በቀለኛ ወደረኛ» ተብዬ ነው ጋቢውን ስዕለቴን የምሰጥህ ትለዋለች። በዚህ ጊዜ ይህ ሰው ተጸጸተ ወደ አስታራቂዎቹ ተመልሶ በፍጹም ንስሓ ታረቀ።

ይህን ስናነብ እኛነታችንን ከእዚህ ምሳሌ ውጪ አድርገን ማየት የለብንም። ይቅርታ የማይወድ ልብ ካለን የዲያቢሎስ ልጅ ለመሆን መርጠናል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ክፉ የክፉ ክፉ ነው።

በተለይ ክርስቲያኖች ከሆንን የሃይማኖታችን መሠረት ይቅርታ ነው። ይኸውም እስከ መስቀል ድረስ የእግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን ለሞት ያውም ለመስቀል ሞት ይታዘዝ ዘንድ ያደረገው ይቅርታን ሊያስተ ምረን ነው።

መሠረታዊው ጽንሰ ሐሳብ ይህ ሆኖ ሳለ ክርስቲያን ነኝ ግን የበቀል ሰውም ነኝ ማለት ፈጽሞ አይቻልም ከሁለት አንዱን መምረጥ የግድ ነው። ቀደም ብለን እንደገለጽነው ከልጅነት ጀምሮ በተጠራቀመ የመጠቃት፣ የመገለል፣ የመሰቃየት ቁስል በቀል አርግዘው ለሚኖሩ ሰዎች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥልቅ ሐዘናቸው ውስጥ ከእንባቸው ውስጥ የርህራሄውን ዘይት ሊያንቆረቁር አብሯቸው መኖሩን ሊረዱት ይገባል።

ቀስ እያለ የሚፈስ ውኃ የሚንበለበለውን እሳት እንደሚያጠፋው ሁሉ፣ ያዘኑ ሰዎች እንባም በውስጣቸው ያለውን የበቀል እሳት ያወድመው ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት በእንባ መነጋገር ይገባቸዋል።

ቀላል አይደለም በዚህች ጨካኝ ዓለም ሕፃናት ሰው ሳያውቅላቸው



በጨካኞች ሲገረፉ ቆይተዋል፤ አሁንም የሚገረፉ አሉ። ከአቅማቸው በላይ ሌሊትና ቀን የጉልበት ሥራ እየሠሩ የሚያድጉ፣ የተናቁና የተራቡ በተ ለይ በተለይ በዋልጌዎች የተደፈሩ ሕፃናት የክፉ የልጅነት ቀን አሻራ በአእምሯቸው ታትሞ በመኖሩ የበቀል ሰዎች ቢሆኑ እምብዛም ሊያስደንቅ አይችልም።

ግን እንዴት ከእዚህ ክፉ ሐሳብ ይፈወሱ ያለፈን መርሳት እንጂ ማስታወስ እራስን የሚያስጠቃ ስለሆነ የሕሊናን ወቀሳ ፀጥ ለማድረግ የበቀልን የጭካኔን የቂምን አባት ሰይጣንን ደጋግሞ መካድ መንቀፍ እና መገሰጽ ያለፈን በደል ወደ መርሳት ያደርሳል። በእዚህም ከእራስ ጋር መታረቅ ይቻላል።

በቸልተኝነት ወይም ፈልጉ ኃጢያትን በመሥራት ሰውን በመበደል ከእራስ ጋር መጣላትም አለ። ይህ ጠባይ ነው ሊተኮርበት ሊታ ረም የሚገባው። ሳይቸግር ጤፍ ብድር እንደሚባለው ቀና ሕሊናን በመጥፎ ጠባይ ለማበላሸት ክፋትን መምረጥ ሲበዛም ውስጥ እያመ ረረ ንግግርን እያጉመዘዘ ከሁሉ ጋር እሳትና ጭድ ስለሚያደርግ በእዚህ ሳቢያም የሚመጣው መገለል መሰደብ የሚያመጣብንን ጥላቻ ለመቋቋም የምናደርገው ማጥቃት ከሰው እያራራረቀን እያቀያየመን ይመጣና መልካም የነበረው ጠባያችን ተለውጦ ቂመኛ፣ በቀለኛ፣ ቁጡና እልኸኛ ያደርገናል። ከእዚህ ሕሊና ነው መጠበቅ የሚኖርብን።

ከኅብረተሰብ መገለል መናቅ ወደ ጥፋት ይወስደናል፤ ሥጋውያን ያደርገናል። ሁሉን በሥጋ አቅም ልንቋቋም ልንመክት ስንጣጣር በውስጣችን ጥል ይበቅላል። ተከራካሪነት ባሕሪያችን ይሆናል። ቅንአት ይከተላል። ቁጣ ባሕሪያችን ይሆናል። በአድማ ችግራችን የሚፈታ ይመስለናል፤ መለያየትን የሚሰብኩ መራር ሰዎች ተንኮለኞች ናቸው። እነዚህ ሁሉ ባሕሪያት ወደ ምቀኝነት ይዘውን ይሄዳሉ። እናም በውስጣችን ያለው እልኸኝነት ሲያይል ለመግደል እንኳን አንመለስም።

ይህንን ሁሉ ዲያቢሎስ በውስጣችን ካስቀመጠ በኋላ ፈጽሞ ተስፋ እንድንቆርጥ ያደርገናል። እራሳችንን እንድንጠላ በእዚህች ምድር

የምንኖርባት ዘመን እንድታጥር እንመኛለን:: ምክንያቱም ማኅበራዊ ሕይወታችን ተቃውሷል፤ ደግነታችን ተለውጦ የክፋት ምንጭ ሆኗል::

ብዙ ተስፋ የቆረጡ ሰዎች እራሳቸውን መርሳት ይፈልጋሉ፤ ስለእውነት የሚወቅሳቸውን የውስጥ ሕሊናቸውን ለማደንዘዝ መጠጥን እንደ መልካም አማራጭ አድርገው ይወስዱታል:: ከዚህ በኋላ ሰካራሙ የሚል ቅጽል ስም ይወጣላቸዋል::

በእዚህ ዙሪያ ኣንድ ምሳሌ ሊሆነን የሚችል አባወራ አለ:: ስሙ አይታወቅም ግን በቅጽል ስም «አቶ ምን ዋጋ አለው» ተብሎ ነው የሚጠራው:: ይህ ሰው በሥራ ቦታው ትጉህ፣ በጊዜ የሚደርስ ፈጣን እና ብቁ ችሎታ ያለው ሲሆን ግን በኅብረተሰቡ ዘንድ በቅጽል ስም ነው የሚጠራው:: ጠዋት የሥራ ልብሱን ለብሶ ጺሙን ተላጭቶ ፈጠን ፈጠን እያለ እቢሮው ሲገባ ላየው ይህ ሰው ምን ይጐለዋል እና ነው «አቶ ምን ዋጋ አለው» ተብሎ የሚጠራው ያሰኛል::

ችግሩ በግልጽ የሚታየው ግን አመሻሹ ላይ ነው:: ልክ ከሥራ እንደወጣ የሚሄደው ወደ መጠጥ ቤት ነው:: «አቶ ምን ዋጋ አለው» አንድ መለኪያ አፉ ላይ ከደረሰች በኋላ ዝምተኛነቱ ወደ ተሳዳቢነት፣ ጨዋነቱ ወደ ዋልጌነት ይለወጣል፤ ከሁሉም የሚጣላ፣ የሚያስቸግር ይሆናል፤ ራሱም ይቸገራል::

ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል እንደሚባለው ለቅሶውና ቁጭቱ ያን ጊዜ ነው የሚወጡት:: በየመሀሉ ታዲያ «ምን ዋጋ አለው» የምትለዋ ቋንቋ ተደጋግማ ትሰማለች ከሚኾጐደጐደው ስድብ መካከል «ምን ዋጋ አለው» የተስፋ መቁረጥ ዘዬ ስትሰማ ይህች ቃል ሥር አላት ብሎ አድማጭ ሊጠራጠር ይገባው ነበር::

«ምን ዋጋ አለው» ከመጠጥ ቤት እግሩ ተጠላልፎ እንደበቱ ተበላሽቶ ከየግድግዳው ከየስልክ እንጨቱ እየተላጋ ወደ ቤቱ ሲመጣ እራሱን ለራሱ «ምን ዋጋ አለው» ይላል::



በየመንደሩ ድምፁ ሲሰማ ሁሉም በሩን እየከፈተ እብደቱን ያጅበዋል «አቶ ምን ዋጋ አለው» እያሉ:: ሴቶች ሳይቀሩ በመስኮት አንገታቸውን ብቅ አድርገው «አቶ ምን ዋጋ አለው» ይሉታል:: የስድብ መዓት ያስታቅፋቸውና «ምን ዋጋ አለው» ይላል ለገዛ እራሱ::

እቤቱ ሲገባ የተጐሳቆለውን የተሸማቀቀውን ቤተሰብ ተመልክቶ በስካር መንፈስም ቢሆን የባሰ ልቡ ያለቅሳል:: ለዚህ ምክንያቱ እኔ ነኝ ይላል:: እራሱን ደግሞ ደጋግሞ ይከሳል:: ሚስት እንደፈረደባት ያሰካራም ባሏን ሱሪ፤ ጫማ ማውለቅ ይኖርባታል:: በእዚህ መሀል ግን እንባዋ እላዩ ላይ ጠብ ሲል ይሰማዋል:: ሚስት ገንዘብ ለማግኘት እኪሱ ትገባለች ከድቃቂ ፍራንክ በስተቀር የምታገኘው የለም:: አቶ ምንዋጋ አለው ገንዘቡን ረጭቶታል ወይንም በክፉ ሰዎች ተበርብሯል:: ወሩ እንዴት ሊገፋ ነው በብድር? ይህ ሁሉ ተጠራቅሞ በነጋታው አቶ ምንዋጋ አለውን የሚያሳብድ ችግር ይሆናል::

በላይ በላዩ የተወለዱት አምስት ሕፃናት በሆድ ወስጥ ያለው ስድስተኛ ልጅ የወደፊት ሕይወት ምን ይመስላል ይህ ሁሉ «ለአቶ ምን ዋጋ አለው» የራስ ምታት ነው:: ሕፃናቱን ማነው ማታ የቤት ሥራ የሚያሠራቸው? ማን ልብሳቸውን ያጥባል? ማን ቁርሳቸውንና ምሣቸውን ያዘጋጃል? ምኑስ ይዘጋጃል? የተራቡትን ሕፃናት ለቅሷቸውን መስማት እራሱ ያሳብዳል:: ሆዳቸው በበሽታ የተቆዘረ ልብስ አልባ ሕፃናት አላፊ አግዳሚው የሚያለቅስላቸው የአቶ ምን ዋጋ አለው ልጆች ታላቅ አደጋ ላይ መሆናቸው ጥርጥር የለውም::

ይህ ሰው የተጣላው ከሚስቱ፣ ከልጆቹ፣ ከኅብረተሰቡ ጋር ብቻ አይደለም:: ከቤቱ ዕቃ፣ ከአጥር ግቢው ሁሉ ነው:: የተሁባበሩት ወንበሮች ሰው በተቀመጠባቸው ቁጥር « ሲጢጢጢ » እያሉ ያለቅሳሉ፤ ኮሞዲኖው በሮቹን አጥቶ ጥርስ አልባ ከመሠለ ቆይቷል፤ ጠረጴዛው ሁለቱን እግሮቹን አጥቶ በግድግዳው ድጋፍ ነው የቆመው::

የግቢው አጥር ለማገዶ አንድ አንድ እየተመዘዘ አልቋል:: የቀረውም ቢሆን ተጋድሟል እንጂ አልቆመም፤ ግቢው ሙጃ እና አረም

ምልቶታል፡፡ ስለዚህ «አቶ ምን ዋጋ አለው» የተጣላው ከቁሳቁሱ ጋር ሁሉ ነው፡፡ እንደውም አንደበት አውጥተው ሙጃውና አረሙ የወደቀው አጥርና የተሰባበሩት ወንበሮች «አቶ ምን ዋጋ አለው» እያሉ የሚያላግጡበት ይመስለዋል፡፡

ይህ እንግዲህ ሀገር ተስፋ የጣለችበት አባወራ የነገዋን ኢትዮጵያ በአምሳሉ የሚቀርጽ፡፡ ይህ ነው አገሪቱን ያቀናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ቤተሰቡን እንኳን በአግባቡ መምራት ያልቻለ፡፡ ሚስቱን በሻማ ጨርቅ ከዓመት እስከ ዓመት የሚያሰቃይ ልጆቹን የማያስጠና ተስፋ የቆረጠ የመጠጥ ሱሰኛ ሲጋራውን በላይ በላይ የሚያጤሰው ጤንነቱ የተቃወሰ ሞራሉ የደቀቀ በመጪው ብሩህ ዘመን ለዕድገት፣ ለሥልጣኔ ስንቅ የሌለው እና ኃላፊነቱን መወጣት የማይችል የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነው፡፡

የከተማውን አልን እንጂ ገጠሬው የዓመት ምርቱን ሸጠ ልጆቹን ጥብቆ ሳያለብስ በየአረቄ ቤቱ ገንዘቡን የሚያጠፋ አባወራ መኖሩን መዘንጋት አይኖርብንም፡፡ በአገር ላይ የበቀለውን ይህንን ተስፋ መቁረጥ፣ ወደ መጠጥ ማዘንበል፣ ግዴለሽነት፣ ቁልቁል ማደግ ልብ ብለን ስንመለከት ሥረ መሠረቱ ከእራስ ጋር መጣላት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህ ከእራስ ጋር መታረቅ የጊዜው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡

«ትዕግሥት የንጹት ጠላት ነው» ይላል አባ ዮሐንስ የተባለ መንፈሳዊ አባት ሕይወት በቀስታ የሚንጠባጠብ ውኃን ትመስላለች፤ እርካታ የሚገኘው በብዙ ትዕግሥት ያጠራቀምናትን ጠብታ በመጉንጨት ነው፡፡ ስለዚህ ነው ንጹትን ለማስቀረት በእርጋታ መራመድ የሚያስፈልገው፡፡

ወደ ቤተሰባችን መመለስ ከጥቃቅኗ ነገር ጀምሮ ሁሉን ማስተካከል፣ ማሰናዳት፣ የጨዋታን፣ የዕረፍትንና የመዝናናትን ጊዜ ከቤተ ሰብ ጋር ማድረግ ከሕሊና ሕመም ያድናል፡፡ ለልጆቻችን ጊዜአችንን መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ በሕይወታችን ስንፍና እንዳይገባ ጥቃት እንዳይሰማን ሁሉን በጊዜውና በአግባቡ ለማከናወን ውድ የሆነውን ጊዜ ማባከን አግባብ አይደለም፡፡



ከገዛ እራሳችን ጋር እንታረቅ ስንል፤ አለአግባብ ለመጠጥ አሳልፈን ከሰጠነው ሰውነታችን ጋር እንስማማ ማለታችን ነው፡፡ የተቀደስከው የተከበርከው አካሌ ሆይ ይቅርታ አድርግልኝ ካለዕውቀት ለመጠጥ እና ለዝሙት አሳልፌ ሰጥቼህ ነበር ልንለው ይገባል፡፡

ይልቁንም በስፖርት እና በሥራ አካላችንን ብናጉለብተው እረጅም ዕድሜ ጤንነት እንጎናጸፋለን፡፡ ሕሊናዬ ሆይ ክቡር ስትሆን መጠጥ ቤት ይዤህ ሄጄ ያዋረድኩህ ያሰደብኩህ ይቅርታ አድርግልኝ ልንለው ይገባል፡፡ ሕሊና በማንበብ በመመራመር ሊዳብር ሊዋብ ይገባዋልና፡፡

ፈላስፋው «ብልህ ለሆነ ሰው አዋቂ ይሆን ዘንድ ከልባሞችና ከአዋቂዎች ጋር መኖር መወዳጀትና ጥበባቸውን መከታተል እንዲሁም ምክራቸውን መስማት ይገባዋል» ይላል፡፡ ጥበብ ደግሞ ከመጻሕፍት የሚገበይ እንጂ መጠጥ ቤት በአምባጓሮ መካከል የሚሸመት አይደለም፡፡ ሊሆንም አይችልም፡፡

እርግጥ ነው ታላላቅ የዕውቀት ሰዎች ሳይቀሩ ሰው ከሚያውካካበት የመጠጥ ቤት ብዕርና ወረቀት ይዘው የሐሳብ ብልጭታ እንደሚቃርሙ ይታወቃል፡፡ ግን ሕይወትን ወደ አጉል ልምድ የሚከትን ልማድ ላለመውረስ ከእዚህ ክፉ ቦታ ሕሊናንና ሰውነትን ማራቅ ግን በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡

የሥነ ጥበብ ሰዎች አንድን ኪነ ጥበብ ሲፈጥሩ ከሁሉ በፊት በዛ ፈጠራ ውስጥ እራሳቸውን ፈልገው ነው የሚያገኙት፡፡

ለምሳሌ ሰዓሊው በደስታ መንፈስ ውስጥ ከሆነ ቀለሞቹ በደስታ የሰከሩ፤ የሚፈነጥዙ ሆነው ሊታዩ ይችላሉ ወይም በሐዘን ውስጥ ያለ የፈጠራ ሰው ከውስጠኛው ስሜቱ ውጭ ቀለማቱን ሊያስቃቸው፣ ሊያስበርቃቸው ፈጽሞ ይሳነዋል፡፡ ይህ የውስጥ ስሜት ነው ዘመናትን አልፎ ድንቅ የአስተሳሰብ ለውጥ ያመጣው፡፡

ልክ እንደዚሁ የነፍስ የውስጠኛው መዝሙር እርጋታ እና ደስታ፣ የፍቅር እና የጸጥታ ኃይል ከተሞላ ለአካባቢውም ይህንኑ የነፍስ መዝሙር ነው የሚያቀነቅነው፡፡

ከእራስ ጋር የታረቀ ሕሊና ለአካባቢው ሰላም፣ ደስታ እና ፍቅር ምንጭ ይሆናል:: ከእራሱ የተረፈው ፍሥሐ ቤተሰቡን ያጠግባል::

የምናስበው መልካም ከሆነ የምንሠራውም መልካም ይሆናል፤ በውስጣችን የሌለውን በተግባር ልንፈጽመው ከቶ አንችልም::

የጥበብ ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት እራሱን ፈልጉ ያገኘ በመሆኑ ኪነ ጥበቡ ብዙዎችን ያስተምራል:: አንዳንዴም ደራሲው ወይም ሰዓሊው የተዘበራረቀ ሕይወት ሲመራ በሥራው ላይ ይህ ሁሉ የውስጥ ስሜት ይንጸባረቃል::

ከእራስ ጋር መታረቅ የሥራ ሁሉ መጀመሪያ ሊሆን ይገባዋል:: የሰከነ ሕሊና ያለው ኅብረተሰብ ለመፍጠር ከእራሱ ጋር የታረቀ ግለሰብ በቅድሚያ ማፍራትን ይጠይቃል:: አካባቢውን የሚረዳ፣ የሚለውጥ ግለሰብ ተጠራቅሞ ነው ትልቅና እራሱን በአግባቡ የሚመራ ኅብረተሰብ መፍጠር የሚቻለው::

ልበ ብርሃኖች፣ እራሳቸውን ፈልገው ያገኙ መሪዎች፣ ተመራማሪ ዎች፣ የፈጠራ፣ የሳይንስና የተለያዩ ሙያ ባለቤት የሆነ ኅብረተሰብ ለመፍጠር ከሁሉ በፊት ሁሉም እራሱን መፈለግ ከእራሱ ጋር መታረቅ ይኖርበታል::

ታላቁ ይቅርታ ከእራስ ነው የሚጀምረው፤ እኛ ከእኛነታችን ጋር ከተስማማን ሁሉም በደረጃው ይታረቃል:: ከእኛነታችን ጋር መታረቅ ያስፈልገናል «ጠላትን ከማሸነፍ ይልቅ የራስን ክፉ ፈቃድ ማሸነፍ ይከብዳል» ብሎ ፈላስፋው እስክንድር እንደተናገረው ድካማችንን ወደ ጽናት እድፋችንን ወደ ንጽሕና በመመለስ ሰይጣናዊ ሕሊናን ከእኛ አርቀን የሞት ጨለማ እንዳይውጠን ቀኑ ብርሃኑን እንዲያበራልን ከእራሳችን ጋር በእውነት ልንታረቅ ይገባናል:: በእዚህች ምድር እራሳቸውን አሸንፈው ለሌ ሎች የተረፉት ከእራሳቸው ጋር የታረቁ ብቻ ናቸው:: ከራስ ጋር መታረቅ ወደ ቀጣዩ መንገድ ይዞን ይሄዳል ከቤተሰብ ጋር መታረቅ::



# ምዕራፍ አራት

## ከቤተሰብ ጋር መታረቅ

ቤተሰብ ማለት ከጋብቻ በፊት እናት አባት እህት ወንድም አሳዳጊን ሁሉ የሚያካትት ቃል ሲሆን፤ ከጋብቻ በኋላ ደግሞ የትዳር ጓደኛ ን፣ ልጆችን፣ የማደጉ ልጆችን የሚያካትት የሚረዳና የሚረዳ አካላችን ማለት ነው::

ከባሕርዩ ባሕርይን አካፍሎ የሚያሳድግ የእኛንም ባሕርይ የሚወርስ የዕድገታችን መሠረት ነው:: የደስታችን፣ የሐዘናችን፣ የጥንካሬያችን እና የድካማችን ተጠያቂ በአብዛኛው ቤተሰብ ነው::

«አንተ ከማንም የበለጥክ ታላቅ ነህ» ትለኝ ነበር ይላል ማርቲን ሉተር ኪንግ የተባለው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ስለአባቱ ሲናገር:: «የመጀመሪያዎቹ ሃያ አምስት ዓመታት እስኪያልፉ በወጣትነት ዘመኔ ሁሉ ነገር ተመቻችቶልኝ እኖር ነበር:: ችግር ሲኖርብኝ ወደ አባቴ እደውላለሁ:: ሁሉ ነገር ይመቻችልኛል፤ ሕይወት እንደ ስጦታ በእጄ ተመቻችቶ የተሰጠኝ ሰው ነበርኩ:: ይህን ስል ግን በቤተ መንግሥት የተወለድኩ የተቀማጠልኩ ነበርኩ ማለቴ አይደለም፤ ግን ሁሉን አባቴ ያሟላልኝ ነበር» ብሏል::

ይህ የሚያሳየን ማንኛውም ሰው ከቤተሰቡ የሚወርሰው ጥንካሬ ለወደፊት ሕይወቱ ጠቃሚ መሆኑን ሲሆን፤ ይኸው ሰው ስለሚስቱ የሚናገረውን በማስከተል ቤተሰብ ምን ማለት እንደሆነ ለማሳየት እንሞክራለን::

«ባለቤቴ በአስቸጋሪ ጊዜ ሁሉ ካለማቋረጥ ምክር በጥልቀት የምትለግሰኝ በከፍተኛ የትግል ጉዞዬ ወቅት ሳትረበሽ ወይም ሳትደነቅ የምታበረታታኝ ጥንካሬዬ ነበረች» ብሏል::

ልጆችም ብዙ ጊዜ የወላጆቻቸው ጥንካሬ ሲሆኑ ይታያሉ፤ ጆን ፓርከንስ የተባለ ፀሐፊ ሚስጥራዊ መጽሐፉን በሚጽፍበት ጊዜ ከፍተኛ

አደጋ የሚያስከትል መሆኑን የተረዳችው ልጁ «አባቴ ሆይ አትጨነቅ ይህንን መጽሐፍ ስትጽፍ ክፉ ሰዎች ቢገሉህ እንኳን እኔ ከቆምክበት እቀጥለዋለሁ:: ይህ ሥራህ ግን ለልጅ ልጅ የሚጠቅም ስለሆነ መቆም የለበትም» ብላ አበረታትታዋለች:: ስለዚህ ቤተሰብ የጥንካሬ ምንጭ የፍቅር ምንጭ ሆኖ እናገኘዋለን::

ከቅዱሳት መጻሕፍት ቤተሰብን በሚመለከት ብዙ ቁም ነገር ይገኛል:: አብርሃም የሚወደውን አንድ ልጁን ይስሐቅን ይሰዋ ዘንድ ሲታዘዝ በሞሪያም ምድር ልጁን ይስሐቅን አሥሮ በመሰዊያው ላይ ሲያርደው ሲያኖረው:: ይስሐቅ የታዘዘ ልጅ መሆኑ ከአባቱ የወረሰው ታዛዥነት መሆኑን እንረዳለን::

አብርሃም እግዚአብሔር አባቱን ካለማንገራገር የሚታዘዝ በመሆኑ ከዚህ የተማረው ይስሐቅ እስከሞት ድረስ ሲታዘዝ እናየዋለን::*

ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ያወጣ የሕዝብ እረኛ፣ በግብጻዊትዋ ልዕልት እጅ በቤተመንግሥት ሲያድግ እናቱ ሞግዚት ሆና ታሳድገው ስለነበር የዕብራዊያንን ታሪክ እንግልትና ግፍ አስተምራው ስላሳደገችው ለእስራኤል አብነት ሲሆን እናየዋለን::*

ቤተሰብ የመጀመሪያ ትምህርት ቤታችን ነው:: የእናቶች የወተት ት/ቤት ብዙ የማይረሱ ትዝታዎችን ያስታውሰናል:: በኢትዮጵያውያን ልማድ እንጉቻ እና ወተቱ ዳቦውና እርጎውን መመገብ የተለማመድነው በእናቶቻችን እጅ ነው::

የሥራ ዓይነቶችን የምንለምደው የምንማረው ደግሞ ወንዶች ልጆች ከአባቶቻችን ሲሆን፣ ሴቶች ልጆች ደግሞ ፈትሉን ስፌቱንና የምግቡን አሠራር ከእናቶቻቸው ተምረው ያድጋሉ:: ትጉህ ቤተሰብ ያለው ልጆቹ ሥራ የሚችሉ ዕውቀት የገበዩ ሆነው ስለሚያድጉ ለወደፊት ሕይወታቸው ሳንካ አይገጥማቸውም:: ይህ ከላይ የተመለከትነው አጠቃላይ የቤተሰቡን ክፍል ሲሆን፣ ከርዕሳችን እንደተመለከትነው

* ዘፍ. 22÷1–19



ከቤተሰብ መታረቅ በሚለው ዐብይ ርዕስ ሥር ከዚህ ግዙፍ የሕይወታችን ምዕራፍ ጋር እንዴት እንታረቅ? ወደሚለው ርዕስ እናመራለን::

«እግዚአብሔር መሥዋዕታችሁን የማይቀበለው የቃል ኪዳን ጓደኞቻችሁ ለሆኑት ለወጣትነት ሚስቶቻችሁ ታማኝነታችሁን ስላፈረሳችሁ ነው:: በእናንተም መካከል እግዚአብሔር ምሥክር ነበር:: ታዲያ እግዚአብሔር እናንተንና ሚስቶቻችሁን አንድ አካልና አንድ መንፈስ እንዲኖራችሁ አድርጐ አልነበረምን? በዚህስ የእርሱ ዓላማ ምን ነበረ? ዋና ዓላማው የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሆኑ ልጆችን እንድትወልዱ በመፈለግ ነበር:: ስለዚህ ከእናንተ እያንዳንዱ ለሚስቱ የገባውን ቃል ኪዳን ቢያፈርስ እኔ የባልና የሚስትን መፋታት እጠላለሁ» ይላል እግዚአብሔር::*

አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ የሕይወት መሠረት ተጣለ ማለት ነው:: ይህ ግዙፍ ዓለም የሁለት ባልና ሚስት ውጤት ነው:: አዳም አጥንትሽ ከአጥንቴ ነው ሥጋሽም ከሥጋዬ ነው ሲል ሔዋን ምን ያህል አካሉ መሆንዋን ማሳየቱ ነው::*

ከላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መሠረት እግዚአብሔር በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ያለውን ቀጥተኛ ፍላጐት ገልጿል:: መልካም ሕፃናት ይወለዱ ዘንድ መልካም ቤተሰብ አስፈላጊ ነው::

በእኛ ኅብረተሰብ ውስጥ የቤተሰብ ትርጉም ሰፊ ሲሆን፣ ከአጐትና ከአክስት ከአያትና ከአዝማድ አጥንት እየቆጠረ የሚሳሳብ ኅብረተሰብ ውስጥ ነን ያለነው::

እንደአብዛኛው ዓለም በጋብቻ መኖር እውነተኛ መንገድ የሆነበት በተለይ በ1953 ዓ.ም. ሁለት ተጋቢዎች በሕግ ፊት ያላቸውን መብትና ግዴታ ጥምረቱም በአገሪቱ ምን ዓይነት ዕውቅና እንደሚኖረው ከወንድ እና ሴት ጋብቻ ውጪ ወይም ከአንድ ለአንድ ጥምረት ውጪ ሌላ ዓይነት ኃጢያት በሕግ የተከለከለ ስለመሆኑ በሕግ ተደንግጓል::

* ዘጸ. 2÷1–10
* ዘፍ. 2÷23

ቤተሰብም ቅርጽ ይዞ በኃላፊነት የሚመራበት ሁኔታ ከሞላ ጐደል ቢታይም እያደር የዚህ ግዙፍ የኅብረተሰብ መሠረት መናጋት ለአገር ሥልጣኔም ሆነ ለኑሮአችን ትልቅ ጉዳት ማስከተል ጀምሯል::

በባሕላዊው የትዳር አኗኗር ዘይቤ አባወራ ሚስቱን ከሚገባው በላይ የሚጫን ሲሆን፤ ዘመናዊው ደግሞ በአንድ ሚስት የማይረጋ ሆኖ ተገኝቷል:: ሁለቱንም አካሄድ አስወግዶ ጤነኛ ቤተሰብ ለመቅረጽ የሚቻለው ግን ከቤተሰብ ጋር እርቅ በማድረግ ብቻ ነው::

ታማኝ አባወራና ታማኝ ሚስት የመጥፋቱ ውጤት በከፊል ምክንያት የሚሆነው የፍቺው ቁጥር እያሻቀበ በመምጣቱ ሲሆን ይህም የሚያሳየው በቤተሰብ ሕይወታችን ላይ ያለውን ችግር ነው::

ከሁሉ አስቀድመን የቀደሙት የሕግጋት መጻሕፍት ስለቤተሰብ ሕይወት ምን ይላሉ? ብለን እንነሳለን::

ጋብቻ ያስፈለገበት ምክንያት መጀመሪያ ነገር ልጅን ለመውለድ፣ ፍትወትን ለማራቅ፣ ለመረዳዳት እና አንድ ለመሆን ነው ይሉናል የሕግጋቱ መጻሕፍት::

ይህ ቢከበር ኖሮ ባለትዳር ሰው ልጆቹን እቤት አስቀምጦ ከሌላ ሴት ሌሎች ልጆች ከጋብቻ ውጭ አይወልድም ነበር:: ሴቲቱም በትዳር ላይ የሚመጣን አለመታመን አጥብቃ በተከላከለች እና ታማኝ በሆነች ነበር:: ሁለተኛ ፍትወትን ለማራቅ ነው ይሉናል:: ምነው ይህማ በባለትዳሮች ብሶ ከሚስት ውጭ ከባል ውጭ የሚማግጥ በበዛበት ዓለም ነውና የምንኖረው:: ለመረዳዳትና አንድ ለመሆን ይላል ታዲያ እህቶቻችን ከባሎቻቸው የሚያገኙት እርዳታ ሳይሆን ጥቃትና ጭቅጭቅ ስድብ ምነው ሆነ? ወንዶችም እንደዚሁ በሚስቶቻቸው ጭቅጭቅ ቤት መግባት ለምን አስጠላቸው?

ጋብቻ በእግዚአብሔር የተፈቀደ የተወደደ ስለመሆኑ ግን ሚስቱን ትቶ የሚያመነዝርን እግዚአብሔር እንደሚፀየፈው በሚገባ ተጽፏል::



ወደ ዋናው ሐሳብ ከቤተሰብ ጋር መታረቅ ስናመራ በማኅበረሰባችን መካከል የትዳር መላላት፣ የቤተሰብ መፈታትን እያስከተለ ትዳር ለስድስት ወር የሚል ፊሊጥ ውስጥ ገብተናል::

ከዚህም የሚብስ አለ:: በሠለጠኑት ዓለማት ከዚህ ጊዜ እስከዚህ ጊዜ ብቻ አብሬህ አብሬሽ እኖራለሁ እየተባባሉ የጋብቻ ኮንትራት ሲፈራረሙ መታየታቸው አዲስ አይደለም:: ይህ ዞሮ ዞሮ ውል አይፈረምበት እንጂ በስድስት ወር የሚፋቱ ባልና ሚስቶችን ስናይ እኛስ ምን እንሻላለን? እንድንል ይገፋፋናል::

አብረው እስከ እርጅና የደረሱ በመጨረሻው ዕድሜያቸው ወጣት ለማግባት ሲፋቱ ማየት ኢ-ሃይማኖታዊ ብሎም ኢ-ሞራላዊም ነው::

ዘመናችን ግብረ ሰዶም የተንሠራፋበት ጊዜ ነው:: በቅጣት የጠፉት የሰብአ ትካት፣ የሰዶምና ገሞራ ልምድ ዓለምን ከተቆጣጠራት ሰንብቷል::

ወንዶች ከግብራቸው ውጪ ከሚመስላቸው ፆታ ጋር ጋብቻ ካልፈፀምን እያሉ ሲከራከሩ ይስተዋላሉ:: ሴቶች ከሴቶች ጋር መጋባታችን በሕግ ይጽደቅልን ሲሉ ይሰማሉ:: የሚደንቀው ደግሞ እነዚህ ልቆች በጉዲፈቻ (በማደጐ) ሕፃናት ሲያሳድጉ መታየታቸው ነው:: የማደጐቹ ልጆችም የሚወሰዱት ኢትዮጵያን ከመሳሰሉ ድኃ አገራት ነው:: ይህ አስጸያፊ ተግባር የሕግ ድጋፍ ያገኘባቸው የአውሮፓ እና የአሜሪካ ግዛቶች ቀላል አይደሉም:: በዚህ ዘመን መፈጠራችን ያሳዝነናል::

የሥነ ተፈጥሮን ሕግ በሰው ሠራሽ ሕግ ሊለውጡ የሚጥሩትን ክፉዎች እግዚአብሔር ከስህተታቸው ይመልሳቸው ዘንድ ዓለማችንንም በቁጣ እንዳያጠፋት ቅዱሳን ሁሉ ሊጸልዩ ይገባል:: ይህ መጥፎ ሐሳብ ወደ አገራችን እንዳይገባ ጥንቃቄ ሊደረግም ይገባል በድህነትና በጉስቁልና ላይ ይህ እብደት ከተጨመረ አስፈሪ ሁኔታ ከፊታችን ይጠብቀናል::

ታዲያ የጥፋቱ ዋዜማ እኛም ጋ አልደረሰም ማለት አይቻልም የተከበረው ትዳር ከትዳር ውጪ በሚደረግ ውስልትና መኝታው ሲጉድፍ እኛ ከሌሎች እንሻላለን ብለን ልንመጻደቅ አይገባንም::

ለትዳሩ ታማኝ ያልሆነ ኅብረተሰብ ስናፈራ ሌሎችንም በዚህ ደረጃ ያደጉ ኃጢአቶች ናቸው ብለን ሳይቃጠል በቅጠል ማጥፋት ይኖርብናል።

ይህ በዚህ እንዳለ አንድ ኢትዮጵያዊ አባወራ ከመሠረተው ቤተ ሰብ ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ብለን ስንጠይቅ ከልጆቻችን፣ ከትዳር ጓደኞችን ጋር የምናሳልፈው ጊዜ የምናደርገው እንክብካቤ ምን ይመስላል? ብለን ብንጠይቅ የኢትዮጵያዊው አባወራ ስዕል ከዚህ እንደሚከተለው ይመስላል።

በአብዛኛው አባወራ ለልጆቹ ምግብ መጠለያና እንደነገሩ ልብስ ለማደራጀት ይጥራል።

ለወደፊት ዕድገቱ ለፈጠራው ለዕድሜው ሊረዳው የሚችለውን የተመጣጠነ ምግብ አግኝቶ የሚያድግ ሕፃን ግን ጥቂት ነው። ይህ ከማጣት ብቻ የመነጨ ሳይሆን ከማስተዋል እጥረትም ነው።

አገራችን ውስጥ ያሉ ጥራጥሬዎች በአግባቡ ከተዘጋጁ፣ የሥጋውና ጥሉላት ምግቦቹ ሥርዓት ከያዙ፣ ከተፈጥሮ ምግብነታቸው ጋር (የኬሚካል ምግብ በሠለጠነው ዓለም አለ) ወተቱና ማሩ ዕቅድ ከወጣለት፣ ገበያውን ሞልቶ የተረፈው አትክልት ከታሰበበት፣ ወጣቶቻችንን የሚገነባ በአእምሮም በአካልም ብቃት እንዲኖራቸው የሚያደርግና ንቃት የሚሰጥ ምግብ አለን። ስለዚህ ቤተሰብን በጥሩ አመጋገብ መገንባቱ ለወደፊት የአገሪቱ የሰው ኃይል ብቃት ለዜ ጐቻችን ረጅም ዕድሜ ታላቅ አስተዋፅዖ አለው። ይህም እርቅ ይፈልጋል። ግን ይህንን ስንል ምግብን ሥርዓት ለማስያዝ የምግብ አስተዳደር ብቃት ይኖረን ዘንድ ከመሐይምነት መላቀቅ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ምግብን በዕቅድ ለማዘጋጀት ሰፊ ትምህርት በየመንደሩ በየቀየው ሊሰጥ ይገባል። ይህም በመገናኛ ብዙኃን በሰፊው በመታገዝ ሊፈፀም የሚችል ነው።

በነገራችን ላይ በአማካይ ሲሠላ የሕዝባችን ዕድሜ ከ45 ዓመት አይበልጥም። ይህ ከፍተኛ የጤንነት ችግር እንዳለና የአመጋገብ ጉስቁልና ያጠቃን ሕዝቦች መሆናችንን ያሳያል።



በቤተሰብ ደረጃ የንጽሕና አጠባበቃችን ካለማወላወል ደካማ እንደሆነ በግልጽ ልንነጋገርበት ይገባል። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለው ንጽሕና ምን ይመስላል በድህነት ምክንያት ሳንችል ከሚቀረው ውጭ በዚህ ረገድ የሥራ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚደረገውን ጨምሮ ንጽሕናችን ከግምት በታች ስለሆነ በጥንካሬ ልናስተካክለው ይገባል።

የተስቦ፣ የዓይን ማዝ እና ሌሎች በሽታዎች ሁሉ የሚፈለፈሉት ከቤተሰብ ንጽሕና ጉድለት ነው። ታዲያ የቤተሰቡ ጠባቂ አባወራ ቆሻሻውን ሁሉ ዝንቡን ሁሉ በማጥፋት የቤተሰቡን ጤንነት የመንከባከብ ኃላፊነት ይኖርበታል። ዝንቦችንና ቆሻሻዎችን ሁሉ ለማስወገድ መንግሥት ከተ ጠበቀ የማያዋጣ መንገድ ነው። ሁሉም ቤተሰቡን በንጽሕናና በጥንቃቄ ሊያስተዳድር ኃላፊነት አለበትና ይህም እርቅ ይፈልጋል።

የልጆቻችን ትምህርት ሁኔታ እንዴት ነው? ለዚህም ቤተሰብ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሊያበረክት ይችላል ኮስተር ብሎ የልጆችን የጨዋታ እና የጥናት ጊዜ ወስኖ ተቆጣጥሮ እምብዛም ነፃነት ሳይነፍጉ፣ ሥርዓትም እንዲያጡ ሳያደርጉ፣ ከመምህራኑ ጋር የጠበቀ ግንኙነት የሚያደርግ ወላጅ በቁጥር ጥቂት ነው። በሠለጠነው ዓለም ወላጆችና መምህራን በእያንዳንዱ ተማሪ ሁኔታ ላይ ውይይት ያደርጋሉ። የሕፃናቱን ችግር በጋራ ለመፍታት ይጣጣራሉ። ልጆች ክፍል ይግቡ አይግቡ ደብተር ይኑራቸው አይኑራቸው ሌላው ቀርቶ ምን ዓይነት ጓደኛ እንደአላቸው እንኳን የማያውቅ ወላጅ ተፈልጐ አይገኝም። በእኛ ልምድ ፈጽሞ ይህ አይታሰብም።

ልጆች የተጣመመ አመል ከመልመዳቸው በፊት ሥነ ልቡናቸውን ፈትሾ በማየት በቁጣ፣ በድብድብ ሳይሆን በፍቅር ጠንከር ባለ ግሳጼም መምራት ያስፈልጋል።

በዚህ ዘመን ሕፃናት እና ወጣቶች የመንፈሳዊው ጦርነት ሰለባዎች ሆነዋል። እንዴት ልንከላከል እንችላለን? ይህንን በተመለከተ በሕፃናት ክፍላችን በሰፊው እንነጋገርበታለን። በጥቅሉ የቤተሰብ ሕይወት በሕፃናቱ በወጣቱ በሚቀጥለው ትውልድ ላይ ሁሉ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ ሊተኮርበት ይገባል።

ቤተሰብ እራሱ መምህር ነው። «ተናካሽ ውሻህንና ባለጌ ልጅህን ተቆጣጠር» የሚለው ጥንታዊ ሕግ የሚገስጸው ያሳደገን ቤተሰብ እንጂ ባለጌውን ሕፃን አይደለም።

እንደውም የሕፃኑ ምስል ቤተሰቡን የሚያሳይ መስታወት ነው። የሥነ ልቡናችን ማኅተም ቁልፉ፣ ድፍረትና ፍርሐት፣ በእራስ መተማመንና ደካማነት፣ ድንጉጥነትና ቆራጥነት የሚወረሰው ከቤተሰብ ነው።

መልካም አባት ከጥንካሬው ጥንካሬን፣ ከዕውቀቱ ዕውቀትን፣ ከተፈጥሮ ባሕሪው ጥሩውን ሁሉ አጋርቶ ልጁን ካሳደገ አባት የማንነት መሠረት መሆኑ አያጠራጥርም።

አባት ቤተሰቡን በፍቅር ሲያኖር ግዴታ አለበት ሚስቱንም ከእራሱ በላይ ሊወድ አምላካዊ ትዕዛዝ ግድ ይለዋል።

እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ውብ ኑሮ እንዲገጥመን በፈቃዳችን በሕሊናችን ቅርጽ የተመጠነች ሚስት ይሰጠናል። ሴቶችም ለተፈጥሮ ባሕሪያቸው የሚስማማ ባል ይሰጣቸዋል።

ታዲያ ሰው በገዛ ፈቃዱ ስጦታውን ሲያከብረው ወይም ሊያዋርደው ይችላል። ቢያከብረው ይከበራል፤ ቢያዋርደው ግን ከሁሉ በፊት አምላካዊ ጥያቄ አለበት። ከዚህ በኋላ ግን ምድራዊውንም የሰዎች ሥርዓት ስለሚያፋልስ በሁለት ወገን ተጠያቂ ይሆናል።

ሰው እንዴት ዓይነት ትዳር ይመሥርት? በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ይገኛል።

«እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ በመንገዱም የሚሄዱ ምሥጉኖች ናቸው።

የድካምህን ፍሬ ትመገባለህ፤

ምሥጉን ነህ መልካምም ይሆንልሃል፤

ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት፤



ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው፤

እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ እንዲህ ይባረካል፤

እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ፤

በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፤

የኢየሩሳሌምን መልካምነትዋን ታያለህ፤

የልጆችህንም ልጆች ታያለህ፤

በእስራኤል ላይ ሰላም ይሁን።»*

ምን ይህ ብቻ ያዕቆብ የአባቱን የይስሐቅን ምክር «ከከነዓን ሴቶች ልጆች ሚስትን አታግባ» ብሎ እንዳለው ያዕቆብ የአባቱንና የእናቱን ምክር ሰምቶ ወደ እናቱ አገር ወደ አጐቱ ወደላባ በሁለቱ ወንዞች መካከል ወዳለችው አገር እንደሄደ የከነዓንም ሴቶች በአባቱ በይስሐቅ ፊት እንደተጠሉ ስላወቀ ሚስት ፍለጋ ሩቅ አገር እንደተጓዘ ተመልክተናል።

ከሁሉ የሚያስደንቀው የላባን ልጅ ራሔልን ባያት ጊዜ የወደፊት የሕይወት ጓደኛው በመሆንዋ ራሔልን ሳማት ቃሉንም ከፍ አድርጐ አለቀሰ።

ምን አስለቀሰው ወደፊት የሚመሠርተው ቤተሰብ እናት ራሔል መሆንዋን ሲያይ ሕሊናው ተነካ ስለዚህም እንባ አውጥቶ አለቀሰ።

የሕይወት ነገር ጥልቅ ነው። አንድ ጊዜ በቃል ኪዳን ታገባት ዘንድ ወይም ታገቢው ዘንድ የተሰጠህ (የተሰጠሽ) አካልሽ (አካልህን) መፈለግ ሕሊናን እስኪያናወጥ ድረስ የሚያስጨንቅ ወይም በተገኘ ጊዜም የሚያስደስት ነገር ነው።

ብዙ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል። የአብርሃምና የሣራ፣ የይስሐቅና የርብቃ፣ የሳሙኤል እናት ሐና እና የሕልቃና እነዚህ ሁሉ የመልካም ቤተሰብ ምሳሌ ናቸው። በዚህ ዘመን ያለው የቤተሰብ አስተዳደር እንዴት ይታረቅ?።

* መዝ. 127(128)፥1–6

ከሁሉ በፊት መሠረታዊ ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል:: ንግግር፣ ውይይት የኅብረተሰብ ችግር መፍቻ ነውና በግልጽ የመነጋገር ልምድን ማዳበር ይኖርብናል:: በቤተሰባችን መካከል ታላቅም ሆነ ታናሽ ችግር ሲኖር በግልጽነት መነጋገር:: ያለንትርክ ወደ መፍትሔ ሐሳብ ማምራት:: ለበለጠ የማኅበራዊ ዕድገት የታላላቅ ሕዝቦችን ምሳሌ መከተል ያስፈልጋል:: የእኛ ሕዝብ በምጣኔ ሀብት ኋላቀር ከሆኑት ሕዝቦች አንዱ ነው:: የነፍስ ወከፍ ገቢው በዓመት እጅግ ጥቂት ነው::

የቤተሰባችን ገቢ ሲሠላ ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች ነው:: ስለዚህ ለዚህ የማኅበረሰብ ውድቀት የዳረገንን የችግር ቁልፍ መፍታት ይኖርብናል::

የቤተሰብ አስተዳደራችን በአግባቡ ስላልተመራ ነው ለማኅበራዊ ቀውስ የተዳረግነው:: የወር ገቢያችንና የልጆቻችን ብዛት ማመጣጠን፣ የተ ወለዱትንም በአግባቡ መምራት ካልተቻለ ከድጡ ወደ ማጡ እያዘቀጥን መሄዳችንን መገንዘብ ይገባል::

የአባቴ ደመወዝ ከማንኛውም የተራ ሰው ደመወዝ በልጦ አያውቅም:: ግን ምሥጢሩ አባቴ ቁጠባውንና በአግባቡ በሚገባው ቦታ ላይ የማዋልን ጥበብ ማወቁ ላይ ነበር ብሏል አንዱ ታላቅ ጸሐፊ::

ሕይወታችን የተጣበበ እንዳይሆን የአኗኗራችን ጥበብ ከዕለት ዕለት ማደግ ይኖርበታል:: ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት የፈጠራ ውጤቶቻችንን ለማዳበር ልጆቻችንን የተማሩ ለማድረግ ብልሆች ልንሆን ይገባል::

በስደት ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሕይወት እንደሚመሰክረው ኅብረተ ሰባችን ለመሥራት ፈቃደኛ፤ ለማደግ ዝግጁ ነው:: ሌላው ቀርቶ ኑሮውን ለማሸነፍ በየቦታው የሚከፍታቸው ሱቆች የሞት ሽረት ትግሉን ያሳያሉ:: በቡድን፣ በኅብረት፣ በቤተሰብ መሥራት መበረታታት ይኖርበታል፤ የሥራው ገጽታ ሊስተካከል ሊነደፍ ሊተኮርበትም ይገባዋል::



ታላላቅ መሪዎች ነገን ዛሬ ላይ ሆነው ይመለከቱታል:: "Great leaders see the future first." Caralyn corbin ትልቁ አመራር ደግሞ ከቤተሰብ ነው የሚጀምረው::

ለዚህ ሁሉ ችግር ምላሽ የሚሰጠን የቤተሰብ ምጣኔ ነው:: በሥነ ሕዝብ ጉዳይ ላይ ጥናት ያጠኑ ምሁራን እሱን የእነዚህ ሙያዊ አስተዋፅዖ ሥር ሰዶ በመላው ሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ሊንቀረቀር ይገባል::

በ80 ሚሊዮን የሚቆጠር ትልቅ ቤተሰብ ያላት አገር በጥንቃቄ ቤተሰቧን ካልመራች፣ ከምትቆጣጠረው በላይ ጣሪያ እየነካ ያለው የሕዝብ ብዛት በአግባቡ ካልተመራ በራሱ አደጋ ነው::

ይህንን ለማስላት ብዙ መራቀቅ አያስፈልግም፤ ብዙ ቤተሰብ ያለው እና ቤተሰቡን የመጠነውን አባወራ ሕይወት ብቻ ማመሳከር ይቻ ላል:: እንዲህ ሲባል ቤተሰብን ለመመጠን ሳይንሳዊና ክፉ መንገዶችን እንጠቀም ማለት አይደለም፤ በዚህ ረገድ ሃይማኖታዊውንም ሆነ ባሕላዊውን ሥርዓት ሳያፋልሱ ቤተሰብን መመጠን ይቻላል::

የሕዝባችን ብዛት ከቁጥጥር ውጭ ሆኗል:: ይህንን የሕዝብ ብዛት ይዘን እንዴት ልንበለጽግ እንችላለን? ብዙ ሕዝቦች ያሏቸው መንግሥታት የሕዝብ ብዛትን እንደ ሀብት ይቆጥሩታል:: ለዚህም ሁለት አገራትን በምሳሌነት ልንጠቅስ እንችላለን:: እነዚህም አገራት ቻይና እና ሕንድ ናቸው::

የቻይና የሕዝብ ብዛት ከዓለም አንደኛ ነው:: 1.3 ቢሊዮን ሲሆን፤ ሕንድም እንደዚሁ በሕዝብ ብዛት ቻይናን ትከተላታለች:: ካለጥርጥር ይህንን ሁሉ ሕዝብ ለመመገብ፣ ሥራ ለመስጠት በመንግሥት አቅም አይታሰብም::

ስለዚህ በጥበብ ይህንን ፈተና መወጣት ይኖርባቸዋል፤ ይኸውም የሥነ ሕዝብ ንድፍ ጥናት በመቀየስ ነው:: ቻይና እንደሚታወቀው ርዕ ዮተ ዓለሟ ኮሚኒዝም ነው የቻይና መሪዎችና ኢኮኖሚስቶች ድርቅ ብለው (Communism theroy) የኮሚኒስቶችን ንድፍ ብቻ አልተከተሉም::

ርዕዮተ ዓለሙ በአንድ ጐራ ሆኖ በምጣኔ ሀብቱ በኩል ከምዕራባውያኑ ጋር እንዴት እንደሚሠሩ ያሳዩት ነፃ የንግድ ልውውጥ ቻይናን በምጣኔ ሀብት በከፍተኛ ደረጃ እንድታድግ አድርጓታል፡፡ በነገራችን ላይ ቻይናን ምሳሌ ያደረግናት ከእርሷ የሚበልጡ የሉም ለማለት ሳይሆን የሕዝብ ብዛት ችግርን በዘዴ መፍትሔ ሰጥታ ለማደግ በመቻልዋ ለእኛ ምሳሌ ትሆናለች በማለት ነው፡፡

ይኸውም የሕዝቧን ብዛት እንደመዋዕለ ንዋይ መገበያያ በማድረግ ነው፡፡ የምዕራቡ ዓለም ሀብታሞች በገዛ አገሮቻቸው የሰው ጉልበት ተጠቅመው እጥፍ ድርብ ማትረፍ ስለተሳናቸው ማለትም የሰው ጉልበት በሰዓት ውድ ስለሆነ ቻይና ግን የበለፀገችው እርካሽ ጉልበት በማቅረቧ እና ፋብሪካዎችን በመትከል ነው፡፡ ሀብታሞችን እየጋበዘች በአንድ ጊዜ መላ ሕዝቧን ወደ ብልፅግና የሳበችው፡፡ ይኸውም ቻይና (Massive public-works projects) ግዙፍ ሕዝብን ለሥራ የማሠማራት መርሐ ግብር በመዘርጋት በተጨማሪም (Strong manufacturing sector) ጠንካራ የማምረቻ ግዙፍ ፋብሪካዎችን በመገንባት ወይም በማስገንባት ዓለማችን ሞክራው የማታውቀውን መጠነ ሰፊ የመዋዕለ ነዋይ ግስጋሴ አድርጋለች፡፡ ይህንን ስንል የቻይናን አጠቃላይ ርዕዮተ ዓለም፣ የእስረኞችን ጉልበት በግፍ መጠቀምን፣ በተለይ ሐልዎተ እግዚአብሔርን መካድንና ሌሎችንም የግፍ ሥራዎችን ወደ አገራችን እናምጣ ማለት አይደለም፤ የዴሞክራሲ መንገድንም ቻይናዎች አይከተሉም፡፡ ይህ ሁሉ መጥፎ አርአያ ነው፤ ግን በልማት በኩል አርአያ ልናደርጋቸው እንችላለን፡፡

ይህ ታዲያ በቤተሰብ አስተዳደር የመበልፀግ ውጤት ነው፡፡ ሥራዎችን ሁሉ በታለመላቸው አካሄድ መሠረት በመፈጸም በዕቅድ በመመራት የተገኘ ውጤት ነው፡፡

በዚህም መሠረት አብዛኛው የቻይና ሕዝብ ቴሌቪዥን፣ በየቤቱ ልብስ ማጠቢያ ማሽኖችና የውጭው አየር በሚሞቅበት ጊዜ ሊያቀዘቅዝ የሚችል በአጠቃላይ ከተራው ኑሮ ከፍ ያለ የቅንጦት ኑሮ ጀምረዋል፡፡



እንደውም ቻይናን ከ20 ዓመት በኋላ የሚያስፈራት የመኪናዎች ካለቅጥ መብዛት ነው ይባላል፡፡ እንዲህም ሆኖ በቻይናም እንኳን ከድህነት በታች የሚኖሩም አልፎ ናቸው፡፡

ከሁሉ ከሁሉ የሚያስገርመው ግን ቻይና የተማረ ሙያተኛ የሞላባት አገር ነች፡፡ በ2006 እኤአ በወጣው መረጃ መሠረት ቻይና 210,000 ኢንጂነሮች (መሐንዲሶች)፤ 150,000 የሕክምና ጠበብት፤ 250,000 በተለያዩ የሙያ ዓይነቶች የተካኑ ባለሞያዎች አሏት፡፡ ይህ ሁሉ የተማረ ኃይል ግን በተአምር የተገኘ አይደለም፤ የቻይና መንግሥት ከልብ የመሥራት ውጤት ሕዝቡም ስለቤተሰብ አስተዳደር ልጆቹን በምን ዓይነት ጥንካሬ ማስተማር እንዳለበት ስለተረዳ ነው፡፡

ይህ እያስገረመን ሕንድ ቻይናን አስናቀቻት የሚል ዜና ስንሰማ የአገሮች እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እሩጫ ትርጉም ሊሰጠን ይገባል፡፡ ለዚህ ውጤት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉት የሥራ ነፃነት የተሰጣቸው ምሁራን ጥናታቸው ዋጋ ኖሮት፣ ትምህርቱ የወደፊቱን የወጣቶች ሕይወት ይደግፍ ዘንድ ቀድመው ያሰቡ ኢኮኖሚስቶች የመሳሰሉ የኖቤል ተሸላሚ፣ በየሥልጣኑ ተዋረድ በጥናት ላይ የተመረኮዘ የቤተሰብ አስተዳደር ወደ አጠቃላይ የአገር ዕድገት ብቃት እንዲሸጋገሩ አግዟቸዋል፡፡

የሕንድ ጠበብት አንድ ነገር ተረዱ፤ የማምረቻ ፋብሪካዎች በቴክኖሎጂው መራቀቅ በዘመኑ የኮምፒዩተር ጥበብ ምክንያት ዘላቂ ቋሚ እንዳልሆኑ በመገንዘባቸው በሌላ መንገድ ሕዝባቸውን ማሠልጠን ጀመሩ፡፡ ምክንያቱም ባለፉት ዓመታት ብቻ ከቻይና ፋብሪካዎች 15 ሚሊዮን አምራቾች ከሥራ ውጭ ሆነዋል፡፡ (ተራ ያልተማሩትንም ይጨምራል) ስለዚህ ወጣቶቻቸውን በዓለም የንግድ መድረክ የበለጠ ተፈላጊ ለማድረግ የትምህርት ጥራቱንና የተማሪውን ብዛት ከፍ አደረጉት፡፡ የሕንድ መዋዕለ ነዋይ ግማሹ (Service-sector) ለተባለው ለአገልግሎት ሰጪ የሙያ ዓይነት መፍሰስ ጀመረ፡፡ እነዚህም የሕክምና፣ የቴክኖሎጂ እና የመዋዕለ ነዋይ ዘርፉን ባለሙያ በማሳደግ ነው፡፡

ስለዚህ ሕንድ 200,000 (መሐንዲሶች) 180,000 (የሕክምና ጠበብት) ወደ 410,000 (የመዋዕለ ነዋይ ጠበብት) ወደ 1,000,000 የተለያዩ ሞያ ያላቸው ጠቢባን እንደአሸን አፈላች:: (India is not only producing more young professional; it is also producing better qualified ones, too) እንደዘገባው ሕንድ ብዙ ወጣት ሞያተኞች ማፍራትዋ ብቻ አይደለም የሚያስደንቀው ጥራት ያላቸው መሆናቸውም ጭምር እንጂ::

በ2008 ሕንድ ከቻይና እጥፍ ሙያተኞችን ታስመርቃለች:: ስለዚህ ዓለም ያረጀውን የማምረቻ መሣሪያ ለውጦ በኮምፒዩተርና በተራቀቁ ቀላል መሣሪያዎች በትንሽ ሰው ማምረት ስለጀመረ ያ ሁሉ የቻይና ሙያተኛ በጥቂት ምሁራን ሊተካ ነው ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ሕንድ የተማረውን ወጣት ለዓለም ሰጥታ አንደኛ ሥራ አጥነትን ታጠፋለች፤ ሁለተኛ የሕንድን መዋዕለ ነዋይ ታሳድጋለች ማለት ነው:: በዚህ ምዕራፍ በዚህ ርዕስ በጥቂቱ ተወያየን እንጂ በሕፃናት ዓምድ ደግመን በሰፊው ስለምናነሳው በአጭሩ እዚህ ላይ ይብቃን::

እኛ ከዚህ ምን እንማራለን? ለመሆኑ በቸልታ ሁሉን የምንመለከትበት ጊዜ ይሆን? እነ ሕንድ ከ40 እና 50 ዓመት በፊት ከእኛ በከፋ ሁኔታ የደኸዩ ሕዝቦች ነበሩ:: አሁን ግን በጥቂት ዓመታት እንደ ሮኬት ተስፈንጥረዋል ያንን ሁሉ ሕዝብ ተሸክሞ ተኝቶ የሚያድር መንግሥትም ሕዝብም እርባና የለውም::

ዋናው የሕንድ ሕዝብ ዕድገት የተገኘው ሕዝቡ በንቃት በአገሩ ዕድገት ላይ ስለሚመክር ስለሚወስንም ነው:: ይህ የቤተሰብ የማኅበረሰብ አጠቃላይ እንቅስቃሴ እንጂ የጥቂት ግለሰቦች ብቻ ውጤት አይደለም::

የዓለም ኅብረተሰብ ዕድገት መሠረት ቤተሰብ መሆኑን ደጋግመን ለማብራራት ሞክረናል::

የሕንድ ወጣቶች በመንግሥታቸው አርቆ ማሰብ በተለያዩ ሙያ የሠለጠኑ ምሁራን ከመንግሥታቸው ተመካክረው እጅና ጓንት ሆነው



ምሁራዊ ራዕያቸውን ወደ ተግባር ስለለወጡት ነው:: ይህም በቤተሰብ ላይ የተመሠረተ እርምጃ ስለሆነ መላውን ሕዝብ የሚያሳትፍ እና ከልብ የሚያሠራ ሆኖ በመገኘቱ ዕድገት ተገኝቷል::

የሕንድ መሪዎች ለሙያ ሰዎች ሙሉ መብት በመስጠት በየመስኩ የሚደረጉ ጥናቶችን በተቻለ መጠን ካለመዝረክረክ ሥራ ላይ በማዋል ሌት ከቀን በመድከም በመሥራት፤ በዚህ ዘመን ሕንድ የሳይንስ ውጤቶች ተጠቃሚ ብቻ ሳትሆን የፈጠራ ባለቤት ልትሆን በቅታለች::

የሚያስደንቀው ነገር ከብዙ አገሮች ተሞክሮ እንደምንማረው ለማንኛውም የሳይንስ ጥበብ ኅብረተሰቡ በዘመናት ውስጥ ያዳበረው ችግሮችን የመፍቻ የማቃለያ ዘዴ መሠረት ሆኖ ሲያገለግል እናገኝየለን::

ይህ የሚጠቁመን አንድ ዓቢይ ነገር አለ:: በየቤተሰቡ የሚከወኑ የኑሮ ማሸነፊያ ዘይቤዎች ተጠራቅመው ነው ወደ ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች የሚለወጡት::

በእጅ የሚሸመነው በማሽን ተለወጠ:: ሌላ ትርጉም የለውም፤ ግን ይህንን ለመለወጥ የሸማኔው ቤተሰብ፤ ከባለእጁ (ከብረት ሠራተኛው) ቤተ ሰብ ጋር በኅብረት መሥራት ይኖርባቸዋል::

አንዱ ለሌላው ቤተሰብ መድኅን መሆን የሚኖርበት ለገዛ እራሱም ሲል ነው:: አገሪቱን ከድህነት ማውጣት ማለት የእራስን ነፃነት ማወጅ ነው:: በግል መበልፀግ ከማኅበረሰቡ በገዛ ገንዘብ መለየት ማለት ነው:: ስለዚህ በቤተሰብ በኅብረት መበልጸግ ይገባናል::

ስለዚህ ነው ማርቲን ሉተር ኪንግ «ድኅነት በዓለም ላይ እስካለ ድረስ ሀብታም መሆን አልችልም ሌላው ቀርቶ ሚሊዮን ብር ቢኖረኝ እንኳን በሽታ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በዓለማችን ላይ እየገደለ ጤነኛ ነኝ ማለት እንዴት ይቻላል? የዓለማችን ማዕከላዊ ዕድሜ (አንድ፡ ሰው በሕይወት የሚኖርበት ዘመን) 28 እና 30 በሆነበት ሁኔታ እኔ ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ነኝ ማለት እንዴት ይቻለኛል? በውድ ሆስፒታሎች በየጊዜው ጤንነቴ ቢጠበቅም እንኳን እኔ የምፈልገውን ደስታ ማግኘት

አልችልም፤ የሌላው ፍላጐት ካልተሟላ። ይህ ነው ዓለማችን የተሠራችበት ሁኔታ። ማንኛውም ሰው ወይም ፍጡር ለብቻዬ መኖር ሁሉን ማድረግ እችላለሁ ብሎ ሊታበይ አይችልም። እኛ በሌላው ላይ ጥገኞች ነን ብሏል።» የቤተሰብ ሕይወታችን ማደግ ያለበት ከቀዬ፣ ወደ መንደር፣ ወደ ወረዳ፣ ወደ አውራጃ፣ ወደ አገር፣ ወደ ዓለም ይህም በኅብረት በመወያየት በመሥራት የሚገለጽ ነው።

አንድ መምህር የሰጡት አስተያየት ዘወትር ሲታወሰኝ ይኖራል ይላል የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ።

ቦስተን ማራቶን ላይ የተሳተፉ ሴት ሯጮቻችን አሸንፈው የአሜሪካ ቴሌቪዥኖች እና ጋዜጦች ሬዲዮው ጭምር «ፋጡማ ሮባ» በሚለው ውድ አትሌታችን ስም አሽብርቆ ልባችን ከመጠን በላይ ተደስቶ ከርሞ ነበር። ታዲያ በዕለተ ሰንበት ቤተ ክርስቲያን መሄድ ስለነበረብን ሄድን። ቀኑ የቅዱስ ሚካኤል ክብረ በዓል ስለነበረ መምህሩ መጥተው ነበር። ታዲያ እኚህ መምህር «ለመሆኑ በሩጫ በማሸነፋችን ተደስታችሁ ወይ?» ብለው ጠየቁን። ምንም ጥርጥር የለውም ልባችን እስከሚነድ ድረስ ስንጮህ ነው የዋልነው። ኢትዮጵያዊቷ ሯጭ ቻይናዊቷን አስከንድታ ገብታ እንዴት አንደሰት አልን? መምህሩ ግን እኔ ብደሰትም እንኳን በውስጤም ሐዘን አለ አሉ። ደነገጥን። እንዴት ኢትዮጵያዊቷ ስታሸንፍ አይደሰቱም ብለን። «እኔ ሩጫ ቢያስደስትም እንኳን እግር ኳስ የበለጠ ያስደስተኛል አሉን። ምክንያቱም እግር ኳስ አሥራ አንድ ሰዎች አንዲትን ኳስ ተጋርተው በሌሎቹ አሥራ አንድ ተጫዋቾች ላይ ግብ ለማግባት በኅብረት የሚያጠቁበት ጨዋታ ስለሆነ እግር ኳስን እወደዋለሁ አሉና። ለመሆኑ የእግር ኳስ አጨዋወት እንዴት በኅብረት እንደሚያምር ልብ ብላችሁ አይታችሁ ታውቃላችሁ። አንዱ ለአንዱ ሲያቀብል ሌላው ቦታውን ይዞ ሲጠብቅ በደቂቃዋ በሰከንዷ ኳሷ የታለመላት ቦታ ደርሳ ግብ ለማግባት የተመደበው ካለችግር ከመረብ ሲያሳርፋት ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ። ሌላው ቀርቶ ጐል ከደረሰ በኋላ ካልተመቸው ለጓደኛው ያቀብላል እንጂ ተስገብግቦ አያበላሻትም። ስለዚህ በኅብረት በመጫወት የተካኑ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ብራዚል፣ ከአፍሪካ ካሜሮን፣ ግብጽና



ናይጀሪያ ድል በድል ሆነው ከሜዳ በደስታ ሲዘሉ ኢትዮጵያዊው ብቻውን ሊያገባ ሲጣጣር ከጐል እስከ ጐል አሥራ አንድ ተጫዋቾች ካላለፍኩ ብሎ ሲርበተበት በጉበዞቹ ይቀማና በገዛ ጅራፉ ሲገረፍ ይታያል። ግን የተናጠል ጥንካሬአችን ከሌላው ዓለም ከማንም አለማነሳችን የሚለካው በሩጫ ነው። ይህ ጥንካሬ የተናጠል ጥረት ተናቦ ተባብሮ ተያይቶ ስግብግብ ሳይሆኑ በእግር ኳሱም ላይ ቢታይኖሮ በየኳስ ሜዳው አራት እና ስድስት ግብ እየቃምን መሣቂያ ባልሆን ነበር።» ብለዋል። ከዚህ ጋር ግን የአካል ብቃታችንም ችሎታ ማነሱም ከግምት ሊገባ ይገባዋል። በነገራችን ላይ ሩጫውም ዘንድሮ በኅብረት መሮጥን ጠይቋል አትሌቶቻችን ተናበው በቡድን ስለሚሮጡ ተከታትለው ሲገቡ ስናይ ይሄ በቡድን የመሥራት ውጤት መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። ታዲያ እነኃይሌ እና ቀነኒሳ ሴቶቹ እነ ደራርቱ እነ ፋጡማ በኅብረት እየሮጡ የድልን መንገድ ሲያሳዩን በሌላውም መስክ ይህ የማይደገምበት ምክንያት ምን ይሆን? ደግመን ደጋግመን በኅብረታቸው ምሳሌ የሆኑንን ሯጮች ከልብ ልንከተል ልናደንቅ ይገባል።

እውነትም እግር ኳስ የኅብረት ሥራን የሚጠይቅ ነው። ይህ ደግሞ ከቤተሰብ ጀምሮ ተጠናክሮ የሚወጣ ነው። የእሳት አደጋ ሠራተኞች ተፋቅረው በኅብረት ለመኖር ካልተስማሙ በየተራ እሳቱ ይበላቸዋል። ከዚህ አደጋ ለመትረፍ በኅብረት ማሰብ፣ በፍቅር፣ በትብብር መኖርና መሥራት ወሳኝ ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ከእሳት አደጋ ጊዜ ያልተናነሰ የፈተና ጉድጓድ ውስጥ ያለችበት ጊዜ ላይ ነች። ቤተሰብ ለቤተሰብ እየተሳሰበ አብሮ እየሠራ ካልተጓዘ በየተራ ሁሉም መጥፋቱ አይቀርም።

ወደ ቤተሰብ እርቅ ስንመለስ አባቶችም እናቶችም ልጆቻቸውን በተቻለ አቅም በሳል አድርገው ለማሳደግ መሞከር ይኖርባቸዋል። በአካባቢያቸው ካሉ ትምህርት ቤቶች ጋር በመሰባሰብ የትምህርት ጥራቱን ለማሳደግ ወጣቶች የሚውሉበትን የመዝናኛ ቦታ በማዘጋጀት በኅብረት መንቀሳቀስ አለባቸው።

ክፉና ደጉን በእርጋታ ለማሳየት ቀዳሚውን ቦታ የሚይዙት ወላጆች ናቸው:: ይህንን ለማድረግ ግን የዕለት ተዕለት ክትትል እና ትዕግሥት ያስፈልጋል::

ወጣቶች የፈጠራ ኃይላቸውን እንዲያወጡት አቅማችን የፈቀደውን ያህል በቁሳቁስ ልናግዛቸው ይገባል:: ሲቆፍሩ፣ ብረት ሲቀጠቅጡ፣ ሲስሉ፣ ሲያነቡ፣ ክራር እና ማሲንቆ ሲጫወቱ፣ ግጥም ሲጽፉ፣ ሲያነቡ፣ ብስክሌት ሲነዱ፣ ሲሮጡ፣ ኳስ ሜዳ ሲሄዱ፣ ብይ ሲጫወቱ፣ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ የዝንባሌያቸውን ሀሁ የሚያደናቅፍ የቃላት ጉሽምታ ተስፋ ማስቆረጥና የሚሠሩት ሥራ ዋጋ ቢስ እንደሆነ መናገር ሀገራችንን እጅግ ጉድቷታል::

እርግጥ ነው ሲደባደቡ፣ ሲሠርቁ፣ ሲዋሹ በእርጋታ መመለስ ሲበዛም መገሰጽ ያስፈልጋል:: ግን ዝንባሌያቸውን እየተቹ በአጭር ማስቀረት ሊቀር የሚገባው ጠባይ ነው::

ባልና ሚስት የሚፋቀሩ እና የሚተሳሰቡ ከሆነ ልጆችም ያንኑ ቅርጽ ይዘው ነው የሚያድጉ:: ስለዚህ ምን ቢናደዱ በልጆች ፊት ክፉ ደግ መነጋገር አግባብ አይደለም::

ይህ ሁሉ በሚቀጥለው ትውልድ ላይ ክፉ ወይም ደግ ጠባሳ ጥሎ ያልፋል:: ሰንካላ ትውልድ ላለማፍራት ወላጆች በከፍተኛ ጥንካሬ ልጆችን ማሳደግ አለባቸው:: ይህ ነው የቤተሰብ እርቅ::

እዚህ ላይ የአንድ ሕፃን ቤተሰቦች እነማን ናቸው? ከቅርብ ወላጆቹ ቀጥሎ ጎረቤቱ ሁሉ ቤተሰብ ነው:: ስለዚህም ዘመድ አዝማዱ ጎረቤቱ ሳይቀር የቤተሰብ ሕይወትን በኅብረት ሊመሩ ይገባቸዋል:: ሕፃናትንም ካለልዩነት ልናሳድግ ግዴታ አለብን:: ነገ ቀበሌአችን ብሩህ ሕሊና ባላቸው ወጣቶች እንዲሞላ አንዱ የሌላውን ልጅ በፍቅር ሊያሳድግ ይገባል:: እናም ከቤተሰባችን ጋር እንታረቅ::



# ምዕራፍ አምስት

## ከሴቶች ጋር እንታረቅ

ታላቁ ፈላስፋ ፕላቶ በእሰጥ አገባ መልክ ባዘጋጀው (Plato's Republic) በተባለው መጽሐፉ፡ «የወንዶች ፆታ ከሴቶች ፆታ ያነሰ ነው? ብሎ ይጠይቅና ብዙ ሴቶች በብዙ ነገር ከወንዶች ሊያስንቁ ይችላሉ:: ግን በአጠቃላይ ስናይ ወንዶች ከሴቶች ያንሳሉ» ይላል:: አንደኛው ተከራካሪ «ሴቶች እራሳቸው በሁለት የተከፈሉ ናቸው ጠንካራና ደካማ» ሲል ይከራከራል:: እንደሱማ ከሆነ ወንዶችም በጠንካራ እና ደካማ ይከፈላሉ:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ በሴቶችና በወንዶች መካከል ምን ልዩነት አለ? ይላል ሌላው ተሟጋች:: ይኸውም በፕላቶ መምህር በሶቅራጥስ የተመሰለው ገፀ ባሕርይ መሆኑ ነው:: ማብራሪያውን በመቀጠልም እርግጥ ነው ሴቶች በተፈጥሮ ከወንዶች ያንሳሉ:: ስለዚህ ወንዶች ይበልጣሉ እንበላ ይላል ተከራካሪው::

በሶቅራጥስ የተመሠለው ገፀ ባሕርይ ሲመልስ «አንዷ ሴት ሐኪም ልትሆን ትችላለች፤ ሌላዋ ግን አይደለችም:: አንዷ ደግሞ ስፖርተኛ ወይም ጦርነት ወዳድ ልትሆን ትችላለች:: ነገር ግን ሌላዋ ጦርነት የማትወድ ለስፖርትም ፍቅር የሌላት ትሆን ይሆናል::»

አንዷ ከፍተኛ የሞቀ የጥበብ መንፈስ ሊኖራት ይችላል:: ሌላዋ ደግሞ መንፈሷ የሞተ ልትሆን ትችላለች::

ከሴቶች መካከል የመሪነት ተፈጥሮ ያላቸው ሊመረጡ ይችላሉ ከወንዶች መካከል እንደምንመርጠው ሁሉ:: ስለዚህ ለሚስቶቻችን የመሪነትን ወይም የአማካሪነትን ወይም የወታደርነትን ሙያ መስጠት ከተፈጥሮ ጋር መጣላት አይደለም የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረስ ይቻላል::

የእነዚህን ፈላስፎች በፆታ የበላይነትና የበታችነት ጉዳይ ላይ መፈላሰፍን ስናይ ይህ ርዕስ ጥልቅ እሳቤን እንደሚጠይቅ ጥንታዊ

ጥያቄም እንደሆነ እንረዳለን:: እነዚህ ፈላስፎች የነበሩበት ዘመን ጌታ ከመወለዱ ከ469 ዓመተ ዓለም በፊት ሲሆን ዘመኑም ግሪክ በፐርሺያ ነገሥታት በተወረረችበት ወቅት ነበር::

የወንዶች የበላይነት ባየለበት በዚያ ዘመን እነዚህ የጥበብ ሰዎች ስለሴቶች ድርሻ ሲመራመሩ ተገኝተዋል:: የምንመሠርተው ሕገ መንግሥት በተቻለ መጠን የተሻለ እንዲሆን «ሴቶች ከተማዋን ለመጠበቅ በጦርነት፣ ከአማካሪነት ጀምሮ እስከተለያዩ ሥራዎች ድርሻ ይኑራቸው» እስኪሉ ድረስ ጥንታዊ ሥልጣኔያቸውን አርቆ አሳቢነታቸውን የጥንቶቹ የግሪክ ፈላስፎች አሳይተዋል::

ሌላው ቀርቶ በቀደሙት ዘመናት በግብጽ ነገሥታት መካከል ንግሥቶቹ በግርግዳ ሪሊፍ ስዕሎች ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይዘው መገኘታቸው በተለያዩ ሥራዎች ላይ ሁሉ ሲሳተፉ የሚያሳየን ከጥንት ጀምሮ ሴቶች በእኩልነት ከወንዶች ጋር መታየታቸውን ነው::

ርዕሳችን ከሴቶች ጋር መታረቅ ነውና ከጥንታዊያኑ ፈላስፎች ቅንጣት ሐሳብ ተነሥተን ወደ ዋናው ርዕስ ጉዳያችን እንደርሳለን::

ሁላችንም ከሴቶች ማኅፀን የወጣን፣ የምንወዳቸው እህቶች ያሉን የምናፈቅራቸው ሴት ልጆች የተሰጠንና የትዳር ጓደኛ ያገኘን ቢሆንም አየል ብሎ የሚሰማውን የፍቺ ቁጥር፣ የሴቶች እሮሮ፣ ከረጅሙ የትዳር ሕይወት ተሰናክለው በክፉ ሕይወት ውስጥ ያሉትን ሴቶች እህቶቻችንን ስናይ ለመሆኑ ይህ ሁሉ ጥቃት የሚደርስባቸው ለምንድነው? ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፋናል:: የሴቶች አቅም አነስተኛ መሆኑ በአብዛኛው በወንዶች ጥቃት ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል:: ከጥንት የተጻፉ መጻሕፍትን፣ ወይም በትውፊት፣ በተረት የተላለፉ ታሪኮችን ስንመለከት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች የሕሊና እና የአካል ጥቃት ሲደርስባቸው ቆይቷል::

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ቅዱሳት አንስት (ሴቶች) በሁለት የተከፈሉ ናቸው:: አንደኛ በመልካም ትዳር በቅድስና ሕይወት የኖሩ ሲሆኑ፤ ሁለተኞቹ ደግሞ ጥቃት የደረሰባቸው ናቸው:: ከሁሉ በፊት ግን ስለሰው ሥነ ፍጥረታዊ ሕግ በአጭሩ መመልከት ይገባል::



ስለዚህም «ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከባድ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገ:: እንቀላፍቶም ሳለ ከጐኑ አጥንቶች አንዱን ወሰደና ባዶውን ቦታ በሥጋ ሞላው:: እግዚአብሔር አምላክ ከአዳም ጐን የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጐ ሠራት:: አዳምም ከአጥንቶቼ የተገኘች አጥንት ናት፤ ከሥጋዬም የተገኘች ሥጋ ናት» ብሎ «ሴት ትባል አለ»*

በድሮ ዘመን ሴቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ ክብር ነበራቸው ወይስ ይዋረዱ ነበር የሚለውን ጥያቄ ደግሞ ቀጥሎ እንፈትሽ::

እናታችን ሔዋን በአዳም ትከበር ነበር:: በአብርሃም ሣራ፤ በይስሐቅ ዘመን ርብቃ፤ በያዕቆብ ራሔልና ልያ የከበሩ ታላላቅ እናቶች ነበሩ:: እነአስቴርን የመሳሰሉ ሕዝባቸውን ሲታደጉ ተገኝተዋል:: የሩት፣ የሐና፣ የሙሴ እህት ማርያም ታሪክ የሚያስረዳን መጽሐፍ ቅዱስ ለሴቶች ምን ያህል ቦታ እንደሰጠ ነው:: በተለይ ነቢይት ዲቦራ አገር አስተዳድራም ነበር፤ ባርቅን በቆራጥነት ለነፃነት አስነስታዋለች::

ይህ ታሪካቸው ተመዝግቦ ከወንዶቹ እኩል ባለታሪክ ሆነው የተገኙትን የሚጠቁም ሲሆን፤ በአዲስ ኪዳን ዘመን ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሰው ልጅ ታሪክ በሚደነቅ መልኩ የሚለወጥበት ምዕራፍ በመሆኗ ከጌታ ቀጥሎ ተጠቃሽ እናደርጋታለን:: የዘካርያስ ሚስት ኤልሣቤጥ፣ ነቢይት ሐና የተባለች በዕድሜ ያረጀች፣ እነ አርሴማ እና እነ ማርያም መግደላዊት፣ ማርታና የዮሐንስ እናት ማርያም፣ ሣምራዊቷ ሴትና የምጽዋት ምሣሌ የሆነችው አንዲት መሐለቅ በስጦታ ያወጣችው ድኃ ሴት እነዚህ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመሠገኑ እና በእጅጉ የተከበሩ አንስት ናቸው::

እንደውም ጌታ የመሠረተው አንድ መቶ ሃያው ቤተሰብ ለሦስት የተከፈለ ሲሆን፤ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፣ ሰባ ሁለቱ አርድዕት ይልና ሰላሣ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ብሎ ሴቶችን ከመጀመሪያ የወንጌል ገበሬዎች ውስጥ ይቆጥራቸዋል::*

---

* ዘፍ. 2÷20–23

* ማር. 12÷41–44

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ከመጣባቸው ርዕሶች ሁለተኛ ደረጃ የሰዎችን ማኅበራዊ ሕይወት ለማደላደል ሲሆን፤ ይህንን ማኅበራዊ ቀውስ ለማቃናት ደግሞ በእጅጉ የተጐዳውን የሴቶችን ሕይወት ማስተካከል ከታላላቅ ሥራዎቹ አንዱ ነበር።

ስለዚህም በትምክህተኛ ወንዶች በድንጋይ እየተወገረች እና እየተሰደበች የነበረችውን ዘማዊት ሴት ጌታ ይፈርድባት ዘንድ ይዘዋት ሲመጡ እርሷ የሠራችውን ኃጢአት ያልሠራ ሰው ይውገራት ብሎ ትክክለኛ ፍርድ ፈርዶ ነጻ አውጥቷታል።*

ለብዙ ዘመናት ጀርባዋ ጉብጦ የነበረችውን የድካም መንፈስ የተጫወተባትን ሴት ጀርባዋን እንደ እንጨት አንቋቁቶ የተልፈሰፈሱትን አጥንቶች ሲያበረታ፤* አሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት ጨርቁን ነክታ ስትፈወስ፤* ይህ ሁሉ የሚያሳየን ከጌታችን ዐበይት ሥራዎች መካከል ጥቂቶቹን ነው።

«የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ልባቸው የተሠበረውን እጠግን ዘንድ ለተማረኩትም ነፃነትን፤ ለታሠሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል»* በማለት ስለጌታ በትንቢተ ኢሳይያስ እንደተጻፈው ሁሉ ከሴቶች መካከል የተመረጠችውን እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አክብሮ በእርሷ ማደሩ። ሌላም ምሳሌ ቢያስፈልግ በሰው ሁሉ ዘንድ የተናቀችውን ሴተኛ አዳሪ በርህራሄና በፍቅር ከመቀበሉም በላይ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ለብዙዎች የተሠወረውን ትንሣኤውን ታውጅ ዘንድ ማርያም መግደላዊትን መምረጡ በእውነት እናቶቻችን፣ እህቶቻችን፣ ሚስቶቻችን ምን ዓይነት የተባረኩ የተቀደሱ ፍጥረታት ናቸው ብለን እንድናስብ ያደርገናል።

* የሐዋ.ሥራ 1÷15
* ዮሐ. 8÷1–11
* ማቴ. 9÷20–23
* ሉቃ. 4÷17–19



ስለዚህ ነው ከእነዚህ በእመቤታችን ምክንያት ከከበሩ ሴቶች ጋር እንታረቅ የሚለው ርዕስ ጐላ ብሎ የሚነገረው። ሴቶች በእናትነታቸው ተፈጥሮ የመውለድ ጸጋን ያደለቻቸው ከመሆኑም ባሻገር በአዲሱ የክርስትና ዘመን ልብ ብሎ ላስተዋለ ስለነፃነታቸው፣ በዘመናት ውስጥ ስለተፈራረቀባቸው የመገለል፣ እንደ እርኩስ የመታየት ከባድ ሸክም፣ የበታች ሆኖ የመገመት፣ የባርነት እና የድቀት ኑሮ ተላቀው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ መስቀል በደረሰ ሞት ነፃነት የታወጀላቸው ባለድሎች ሆነዋል።

ከዚህ በኋላ አምኖንን የመሳሰሉ ልባቸው የታወረ ወንዶች ያስነውሯቸው ዘንድ አይቻልም። ሴቶች የሚደርስባቸውን ክፉ ጥቃትን ለማሳየት የያዕቆብን ልጅ ከልያ የተወለደችውን ዲናን ማስታወስ ብቻ ይበቃል። ሴኬም የተባለው ወጣት ከሕግ ውጭ አስነውሯት ነበርና።*

ከእነዚህ ከሁለቱ ታሪኮች ግን አምኖን በገዛ እህቱ በትእማር ላይ ያደረገው ግፍ የቀደሙት እና የጊዜአችንን ግፎች ስለሚወክል በጥቂቱ ልንተነትነው ይገባል። ትእማር እና አቤሴሎም ከአንድ እናት እና አባት የተወለዱ ወንድምና እህት ናቸው። አባታቸው ንጉሡ ዳዊት ነው፤ በድሮ ዘመን ብዙ ሴቶች ማግባት እንደነውር አይቆጠርም ነበርና ዳዊት ከሌላ ሴት የወለዳቸው ሌሎች ልጆችም ነበሩት። ከእነሱ መካከል አምኖን የተባለ ልጅም ነበረው።

ይህ ወጣት የአባቱን ልጅ እህቱ ትእማርን ያፈቅራታል። በዚህም ምክንያት ይጨነቃል፤ ይቆዝማል፤ ይከሳል፤ ይጠቁራል በዚህ ጊዜ የአጐቱ ልጅ ኢዮናዳብ የተባለው የቅርብ ጓደኛው መጥፎ ምክር ይመክረዋል። «ለምን አስገድደህ አትደፍራትም» አለው። በዚህ ምክር አምኖን ይስማማና በሐሰት ታምሜአለሁ ብሎ ይተኛል፤ ታስታምመው ዘንድ እህቱ ትእማር ትላክለት ዘንድ ይጠይቃል፤ ዳዊት ምንም ሳይጠራጠር ይልካታል። ከዚህ በኋላ በሥርዓቱ አባቴን ጠይቀህ ልታገባኝ ስትችል ለምን ይህንን ነውር ትፈጽማለህ ብላ ብትከላከለውም እንኳን ሊሰማት አልቻለም።

* ዘፍ. 34÷1–8

እዚህ ላይ ትእማር አምኖንን እንዲህ ስትል ነግራው ነበር። «ወንድሜ ሆይ አይሆንም እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል ዘንድ አይገባምና አታሳፍረኝ ይህንንም ነውረኛ ሥራ አታድርግ፤ እኔም ነውሬን ወዴት ልሸከም? አንተም በእስራኤል ዘንድ ከምናምንቴዎች እንደ አንዱ ትሆናለህ እንግዲህስ ለንጉሡ ንገረው እኔንም አይነሳህም» አለችው እርሱ ግን ቃልዋን አልሰማትም። ከእርስዋ ምክር ይልቅ የራስ ወዳድነት ፍላጐቱ ብርቱ ነበረና በግድ አስነወራት ከእርሷም ጋር ተኛ።

ከዚህም በኋላ አምኖን ፈጽሞ ጠላት አስቀድሞም ከወደዳት ይልቅ በኋላ የጠላት ጥል በለጠ። አምኖንም ተነስተሽ ሂጂ አላት። እርሷም አይሆንም ቀድሞ ከሠራኸው ክፋት ይልቅ እኔን በማስወጣትህ የበለጠ ክፋት ትሠራለህ አለችው። እርሱ ግን አልሰማትም። የሚያገለግለውንም ብላቴና ጠርቶ ይህችን ሴት ከፊቴ አስወጥተህ በሩን ዝጋባት አለው። ብዙ ኅብር ያለውንም ልብስ ለብሳ ነበር። እንዲህ ያለውን ልብስ የንጉሡ ልጆች ደናግል ይለብሱ ነበረና አገልጋዩም አስወጥቶ በሩን ዘጋባት። ትእማርም በራስዋ ላይ አመድ ነስንሳ፣ ብዙ ኅብር ያለውን ልብሷን ተርትራ እጅዋን በእራስዋ ላይ ጭና እየጮኸች ሄደች። በመጨረሻም ወንድሟ አቤሴሎም ይህንን ነውረኛ ልጅ አምኖንን ተበቀለው (ገደለው)።*

ይህ በጥቂቱ መጽሐፍ ቅዱስ በሴቶች ላይ የደረሰውን ግፍ የሚያስረዳ ሲሆን፤ ጌታችን ግን ይህንን ፈጽሞ ለውጦታል፤ እዚህ ላይ በፈሪሳውያንና በጌታ መካከል የተደረገውን ክርክር በማየት ብቻ ጌታ ምን ያህል የባልና ሚስትን ሁኔታ ወይም የሴቶችን ስብራት ሲጠግን እንደነበረ መረዳት እንችላለን።

ጌታ በይሁዳ አውራጃ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ በመጣ ጊዜ ፈሪሳውያን ወደ እርሱ ቀርበው ጥያቄ ይጠይቁታል። ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት። እርሱ መልሶ እንዲህ አለ «ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፤ ስለዚህ ሰው አባትና

* ሳሙ. ካል. 13፥1–19



እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።» እንኪያስ ሙሴ የፍቺዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቷት ስለምን አዘዘ አሉት። እርሱም መልሶ ሙሴ ስለልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም። እኔ ግን እላችኋለሁ ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።

ደቀ መዛሙርቱም የባልና ሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም አሉ።* በዚህ ጥያቄና መልስ ውስጥ በድሮ ዘመን ወንዶች እንደፈለጋቸው ሴቶችን እየፈቱ ሌሎች ሴቶችን ማግባት ባሕላቸው አድርገውት እንደነበር እና ሙሴ ይህንን ችግር በጥቂቱ መፍትሔ ለመስጠት ቢያንስ ቢያንስ የተፈቱ ሴቶች ሌላ ሰው በነውር ምክንያት የተፈቱ ሆኖ እንዳይሰማው ታሥረውም እንዳይኖሩ የፍች ደብዳቤ ከባሎቻቸው እንዲሰጣቸው ፈቅዶ ነበር።

ጌታችን ግን የትዳር ሕይወትን ሠርግ ቤት ሄዶ ከቀደሰ በኋላ የቀደመውን አዳማዊ ሥርዓት ተከትለው ይሄዱ ዘንድ የሴቶችን ሕይወት ለማስተካከል አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚለውን እውነተኛና ብቸኛ ሥርዓት ደነገገ።

ለዚህም ከሁሉ በፊት ባሎቻቸው ትተዋቸው እየሄዱ ሕፃናቱን ብቻቸውን የሚያሳድጉ እናቶች ዕረፍት አገኙ አባቶቻቸውን የማያውቁ ወይም የአባት የቅርብ ክትትል የሌላቸው ሕፃናትም የረጋ የፍቅር ቤተሰብ ውስጥ ማደግ ጀመሩ። ይህም በዚህ ዘመን ያለውን የማኅበረሰብ ኑሮ ግንባታ መሠረት በመሆን በእጅጉ ረዳ።

ከዚህ በላይ ያለው የቅዱሳት መጻሕፍት ሐሳብ ከሴቶች ጋር እንዴት መታረቅ እንዳለብን፣ በአምላካችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ

*ማቴ. 19፥3–11

ክርስቶስ በተሰጠው ጥንታዊ ሥርዓት መሠረት ለቤተሰባችን ምን ዓይነት አክብሮት ማድረግ እንደሚገባን የሚያስረዳ ሲሆን፤ ከዚህ በኋላ በዚህ ዘመን ስለአለው የሴቶች በደል በመተንተን እንዴት መታረቅ እንዳለብን ለማየት እንሞክራለን።

አገራችን ኢትዮጵያ በሕሊና ሥልጣኔ ከሚታወቁት ከነግሪክና ከሮም ከሌሎችም ሥልጡን ሕዝቦች አንዷ ናት። ይህ የሕሊና ሥልጣኔ ደግሞ ለሁሉም ዕድገት የመግቢያ በር ነው። ይህ ታላቅነት ከሚለካባቸው ዐበይት ርዕሶች አንዱ የቤተሰብ ሕይወት ሲሆን፤ አንድ ሰው ለልጆቹ፣ ለሚስቱ የሚያስተምረው ሥርዓትና ነፃነት የግለሰቡን ማንነት በአብዛኛው ያሳያል።

ስለዚህም በአብዛኛው የማኅበራዊ ሕይወታችን ሥርዓት ያጣ ሳይሆን አንድ አባወራ የአንዲት ሴት ባል ሆኖ ልጆች ኖረውት የረጋ የትዳር ሕይወት ሲመራ የሚታይባት አገር ኢትዮጵያ ነች። እንዲህ ሲባል ጉድለታችንን እና አንዳንድ የጎጂ ልምዶቻችንን ለመሸፋፈን ሳይሆን ከብዙ አገራት ጋር በማነጻጸር ሲታይ ያለውን ሚዛን ለማሳየት ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ በቀደመው ዘመን በሽማግሌና በቤተ ክርስቲያን በሚፈፀም ሥርዓተ ተክሊል፣ በአዋጅ፣ በሠርግ ወጣቶችን የምታጋባ ሲሆን፤ ፍችም በማኅበረሰቡ ዘንድ ነውር ሆኖ ቆይቷል። ይህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይከተለው ነበር ባይባልም ሁሉም ኅብረተሰብ በጋብቻ የሚያምን በአብዛኛው አንድ ለአንድ ጋብቻ የተወሰነ ነበር። ግን በጥቂቱ ከዚህ ውጪ መኖሩም አይካድም።

ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ (Family code) የቤተሰብ ሕግ ተቀርጾለት አንድ ቤተሰብ ሲመሠረት የመንግሥት ሕጋዊ ዕውቅና ይኖረው ዘንድ ተደርጓል። ይህም ቀደም ብሎ በነበረው ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ በተደነገገው መሠረት የጋብቻን ሕግ የበለጠ ለማጽናት ነው።



የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በአጽንዖት ከሚፈቅዳቸው የጋብቻ ዓይነቶች (monogamous) አንድ ሴት ለአንድ ወንድ የሚለውን ብቻ ሲሆን፤ (polygamous unions) አንድ ወንድ ለብዙ ሴት ተቀባይነት የለውም። ነውር ሆኖም ይቆጠራል፤ የኢትዮጵያ የጋብቻ ሕግ ሦስት ዓይነት ስምምነቶችን ይቀበላል። በማዘጋጃ የሚካሄደውን (civil marriage) ሃይማኖታዊ እንዲሁም ባሕላዊ ጋብቻን እንደትክክለኛ ጥምረት ይቀበላል።

ሕጋችን የጋብቻ ዕድሜ ሳይቀር ያስታርቃል። ለወንዱ 18 ዓመት ለሴቲቱ 15 ዓመት። እስከዚህ ዘመን ድረስ የጊዜ ገደብ ተሰጥቶ ጋብቻ በኮንትራት አይፈጸምም የማኅፀን ውስት፣ የብልቃጥ ሕፃናት ሁሉ ከእርግማን ይቆጠራሉ። እርግጥ ነው ሌላ ሚስት ማግባት በአንዳንድ ቦታ ዎች ይዘወተራል። ከሕግ እና ከሥልጣኔ ከሰብአዊነት ጋር ግን ይጻ ረራል።

የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ ግብረ ሰዶም ከሕግም አልፎ የሕዝባችንን ቁጣ የሚያነሳሳ እጅግ አፀያፊ ተግባር በመሆኑ መንግሥትም ሆነ የሃይማኖት ሰዎች ይህ ርዕስ እንዲነሳ እንኳን ፍቃድ አይሰጡም። ድንገት ይህንን በምዕራቡ ዓለም እየተስፋፋ ያለ ነውረኛ የተረገመ ባሕል እናስፋፋ የሚሉ የፋሽን ሰዎች ቢኖሩም እንኳን ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያጋጥማቸው የከፋ ቅጣት ነው።

ስለዚህ ሕጋችን አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚለውን ሕግ በሃይማኖት፣ በባሕል ከዚያ አልፎ ተርፎም በሕግ መወሰኑ ሕዝቡም ሕጉን ተቀብሎ በተግባር ማዋሉን ስናይ ኢትዮጵያ ውስጣዊ የሕሊና ሥልጣኔ ባለቤት መሆንዋን እንረዳለን። ይህ በአጠቃላይ ሲታይ ነው።

ይህም በጋብቻ በኩል መልካም መሠረት እንደአለን ለማሳየት የተተነተነ ሲሆን፤ ከዚህ በኋላ ግን ሴቶች በሕዝባችን መሀል የሚደርስባቸውን በደል በመተንተን ወደተቀደሰው ሥልጡን ሥነ ምግባር እንዴት ልንጓዝ እንደምንችል ከሴቶቻችን ጋር እንታረቅ በማለት ዘመናችንን እንዋጃለን።

ዘመናዊዋ ኢትዮጵያ ሴቶችን በተመለከተ ምን ትመስላለች? የሴቶች መብት የሚከበርባት አገር ናትን? የሕዝባችንስ ሥልጡንነት በዚህ ዘርፍ ምን ይመስላል?

ሴቶች ከቤታቸው ወጥተው እስኪመለሱ ምን ያጋጥማቸዋል? ከዚህ እንጀምራለን:: በዋልጌ ወንዶች መሰደባቸውና መጐንተላቸው ሊሸሸግ አይገባውም:: ክፉ አጋጣሚ ተጠቅሞ ለሚደፍራቸው ጨካኝም የተጻፈው ሕግ በቂ ዋስትና አይሰጥም:: ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በጕረቤት ከመንደር በሚያደባ ሸለምጥማጥ ወንድ፤ ሕፃናት በትምህርት ቤት ካደጉም በኋላ በየሕይወታቸው ምዕራፍ ሊተናኰላቸው የሚሯሯጠውን ነውረኛ እና አውሬ መከላከሉን ሕዝባችን ከቁብ ሲቆጥረው አይታይም:: ከዚህ ነው እርቅ መጀመር ያለበት::

በትክክል ሴቶችን በተመለከተ ብዙ አገራት የተለየ ሕግ ይቀርጻሉ:: ሕጉ በሴቶችና በሕፃናት ላይ ፍፁም የሚሆንበት ምክንያት እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች በቀላሉ ሊቀጠፉ የሚችሉ አበቦች በመሆናቸው ነው::

የሴቶች ነፃነት ከመደላደሉ የተነሳ ከምዕራቡ ዓለም ወደተቀዱ ወደ ጥፋት የሚወስዱ መንገዶች ውስጥ እንዳንገባ ጥንቃቄ እየተደረገ የመሥራት፣ የመማር፣ በፖለቲካውም ሆነ በዕደ ጥበብና ሥነ ጥበብ ሙያ ዎች ካለገደብ ይሳተፉ ዘንድ ሊፈቀድላቸው ይገባል::

ሣራ ግርሚካ ስለሴቶች መብት የምትታገል ሴት ትምህርት ለእኔ ስቃይ ነበር:: እኔ በኅብረተሰቤ ውስጥ ጥቅም የምሰጥ አባል መሆን ለምን አልችልም? ሌላው ቀርቶ ንብረቴን ለመቆጣጠር ሕይወቴን ለመምራት እንኳን አልቻልኩም ስትል በምሬት የተናገረችበት የትግል ውጤት ተቀጣ ጥሎ በዚህ ዘመን በምዕራቡ ዓለም ሴቶች ነፃነት አላቸው:: ስለዚህም «እኮ ማነው? ሴቶችን በታላቅ የምርምር ሥራዎች እንዳይሳተፉ የሚያግዳቸው እንደ ወንዶች ነፍስ የላቸውም ይሆን? እኮ ለምንድነው ሴቶች የጥበብ ብርሃን ተጠቃሚዎች የማይሆኑት? ምን ዓይነቱ ሃይማኖት፣ የትኛው የክርስትና ሕግ ነው? በየትኛው አሳማኝ ሕግ ነው እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ



ሕግ ለሴቶች የተሰጠው? እኔ ጥበብን የማጥናት ዝንባሌ ሕግንና ሳይንስን የማወቅ ዝንባሌ አለኝ ማንም ሰይጣናዊ ነው ቢለኝም እንኳን አደርገዋለሁ:: ማንም በዚህ ሕግ ውስጥ አልፍ ዘንድ አያስገድደኝም:: ለዚህ ዓላማ ተወልጃለሁ፤ ለዚህ ዓላማም ልሞት ዝግጁ ነኝ» እያለች ሣራ ግራሚካ በጥንካሬ ተናግራለች ይህ ከፍተኛ እልህ አስጨራሽ ትግል ተካሂዶ በዚህ ዘመን ሴቶች ከወንዶቹ ጋር በአንድ ክፍል ይማራሉ በአንድ የሥራ ገበታም ተቀምጠዋል:: ግን እስከአሁን ድረስ ሠለጠነች በምትባለዋ አሜሪካ እንኳን ሴቶችን ለአገር መሪነት መምረጥ አስቸጋሪ ሆነዋል::

ለምሳሌ በቅርቡ ለፕሬዝዳንትነት ዕጩ ሆነው የቀረቡት ወይዘሮ ሒላሪ ክሊንተንን ለመምረጥ በሴትነታቸው ሥልጡኑ ዓለም ሲቸገር እናየዋለን:: «አሜሪካ ሴት ፕሬዝዳንት ለመምረጥ ገና ነች የሕሊና ዝግጅት አላደረገችም ሲባል» እንዳይደንቀን ገና ዓለም ሴቶችን የበታች አድርጐ እያሰበ ነው::

ይህ ሁኔታ በእኛ ሕዝብ ውስጥ ምን ዓይነት አንድምታ አለው? ብለን ስንጠይቅ በዚህ በሃያኛው ክፍለ ዘመን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴት ወጣቶች ት/ቤት አይሄዱም:: (ከማጀት አይወጡም) ከ9 እስከ 15 ዓመታቸው ስለሚዳሩ ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጠዋል:: ውሃ ለመቅዳት ረጅም ቦታ እንስራ ተሸክመው መጓዝ አለባቸው:: 90 በመቶው የሴቶች ሕይወት በወንዶች ቁጥጥር ሥር ነው:: እንዲህ ሲባል አንዳንድ ሴቶች ካለወንድ እርዳታ ብቻችንን መኖር አለብን ብለው ከተፈጥሮ ሕግ እና ከማኅበራዊው ክብር ውጪ እንደሚያስቡት እናስብ ሳይሆን መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶችን ድንጋጌ እና አግባብ የሆነውን ጥቅም በተመለከተ ብቻ ለማመልከት ነው:: እንደ ጀሲስ በርናርድ ዓይነቶቹ ሴቶች ብቻቸውን መኖር አለባቸው ብላ እንደምታምነዋ አምርረው የትዳርን ሕይወት መጥላት እና እንደሽንፈት መቁጠር ወደ ሌላ ኃጢአትም ማምራት ክፉ መንገድ መሆኑን እየጠቆምን:: ግን እጅግ የተጐሳቆለችውን የኢትዮጵያ ሴት ደግሞ የተሻለ ሕይወት እንድትኖር መቀስቀስና ማነቃቃት ይገባናል::

ከሴቶች ጋር እንታረቅ ስንል ምን ማለት ነው? እስከዚህ ዘመን ድረስ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሴቶችን የሕሊና ብቃት በብዛት ተጠቅማ አታውቅም:: እንዲያውም በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ሴት ምን ታውቂያለሽ? ነው የምትባለው:: ሴቶች ተምረው የኃላፊነት ቦታ ለመያዝ ከሁሉ በፊት የመማር ፍቃድ አለማግኘት ከዚያም በኋላ የወንዶች ማነቆ ሕሊናቸውን ያቆስለዋል::

ስለዚህ በቤተሰብ ውስጥ እኩል ድርሻ ይኖራቸው ዘንድ በሥራ ቦታም እንደወንዶቹ አለቆች ቃላቸው ሊሰማ ሊከበሩ ይገባል ይህም እርቅ ይፈልጋል::

የማጀቱ ሥራ ለሴቶች ብቻ በመተውና ከዚህ በተጨማሪም ሕፃናትን መጉዳቱ እህል ማስፈጨቱ፣ ወይም መፍጨቱ፣ ውኃ መቅዳቱ እና የቤት ንጽሕናው ሁሉ ለሴት እህቶቻችን ብቻ ነው የተተወው::

የሠለጠነ ሕዝብ ግን ይህንን አያደርግም:: ክርስትናን የሚያውቅ የሰውን ክቡርነት የተረዳ ግን ሚስቱን በተቻለው ሁሉ ሲያግዝ ነው የሚታየው:: ወንዶች ለምሳሌ ማጀት ቢገቡ ምን ጥፋት አለው? ሕፃናትን ቢያጥቡ፣ የሽንት ጨርቅ ቢቀይሩ፣ ጡጦ ቢያጠቡ እና አባብለው ቢያስተኙ ክብራችው ይነካ ይሆን? በእውነቱ ይህ እርቅ የሚፈልግ ጉዳይ ነው::

በምድራችን አንቱ የተባሉ የምግብ አዘጋጆች ወንዶች መሆናቸውን አልተረዳን ይሆን? በምዕራቡ ዓለም ልጆች እናቶቻቸውን እንደሚቀርቡ ሁሉ አባቶቻቸውን የሚወዱት በምንም ሳይሆን ከሕፃንነት ጀምሮ የፍቅር እንክብካቤያቸውን ስለተረዱ ነው:: ከዚህ አልፎ ተርፎም የሕፃናት መጻሕፍት ጸሐፊዎች፣ የካርቱን ፊልም ደራሲዎችና ተዋናዮች፣ ስለሕፃናት አስተዳደግ በሳል ዕውቀት ያላቸው ወንዶች በብዛት ይታያሉ:: እንዲህ ብናደርግ በእህቶቻችን ላይ የተጫነውን የኑሮ ክብደት ማቅለል እንችላለን::

ብዙ ትዳሮች የሚጨናገፉት ካለመረዳዳት ነው:: ኑሮው ሁሉ እጅ እጅ የሚለው ሴቶች ሳያቋርጡ በማጀት ጭስ ሲጨናበሱ፣ ሲወጡ ሲወርዱ አንድ ቀን የማይታረፍበት ሕይወት ነው ትዳራችንን የፈታው::



ከዓመት እስከ ዓመት የማይለወጠው የተርመጠመጠ ኑሮ ሊያበቃ ይገባዋል:: ወንዶች በአንድ እጅ እስከመቼ ያጨበጭባሉ:: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሴቶችን ተሳትፎ በማበልጸግ የቤተሰብ ሕይወታችን ማደግ ይኖርበታል:: ነገር ግን ከዕለት ወደ ዕለት አመለካከታችን እየጫጨ አባቶቻችን እንኳ ንቀው ያለፉትን ሕይወት መድገም የለብንም:: ልብ ብለን ታሪክን ስናስተውል የኢትዮጵያ ታሪክ ቀደም ብሎ የሴቶችን ልዕልና ከፍ ያደረገ እንደነበር እንረዳለን እያደር ግን እያሽቆለቆለ መጥቷል::

(Every Napaleon has his waterloo) እያንዳንዱ ወንድ በአንዲት ሴት ይሸነፋል ድል ይሆናል:: የእኛም ቴዎድሮስ በተዋበች የጀግና ሽንፈት ተሸንፎ ማንኛውንም የፖለቲካ አመራሩን ለመወሰን በሚስቱ ይመክር እንደነበር ይነገራል:: ለዚህም ይመስላል ተዋበች ከሞተች በኋላ የሕሊና ውድቀት የተሰማው እና ብስጩ የሆነው::

«በሐሳብ የማልገናኛትን ሐሳቧ የማያስደስተኝን ሚስት ማግባት አልፈልግም:: ግን ሚስቴ እኔ ለዓላማዬ ከተመሰጥኩት የበለጠ ጠንካራ ስሜት ነበራት» ብሎ ማርቲን ሉተር ኪንግ ኮሬቲን ኮሪ ስለተባለችው ሚስቱ ሲመሰክር የመከራውን ጊዜ ሁሉ አብረን ተጓዝን ሲል ተሰማ እንጂ ሚስቴን ትቼ እንዲህ አደረግሁ ብሎ አያውቅም::

የዛሬ 150 ዓመት እና ከዚያ በፊት የነበረው ቴዎድሮስ ለሚስቱ አክብሮት ነበረው ስንል ንግሥት ተዋበች ለባልዋ ቀራጥ አመራር እንደ ሕሊና ታገለግል እንደነበረ መረዳት ይቻላል::

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበረችው ሴት ደግሞ ከዚህችኛዋ ከፍ ብላ ተገኝታለች:: በዓለማቀፋዊው ጦርነት ከዳግ ምኒልክ ጐን ሆና የጦርነት አመራር ከመስጠት ጀምሮ ረቂቅ የጦር ብልሃት በመንደፍ የጣሊያን ምሽጐችን ስታስለቅቅ የተገኘችው ጣይቱ በዚህ ዘመን ብትኖር ኖሮ ምን ታውቂያለሽ? ምድብ ሥራሽ ጓዳ ነው ሳትባል አትቀርም ነበር ያሰኛል:: ምክንያቱም በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤት ጓዳ ገባ ያልታወቁ ብዙ ጣይቱዎች አሉና::

በዚህ ዓፄ ቴዎድሮስም ሆኑ ዓፄ ምኒልክ ይህንን ዘመን ሳይቀር ተራምደው አልፈዋል ለማለት ያስደፍራል:: ብዙ ባለድል ወንዶች ከኋላቸው ብልህ ሴቶች ስለአሏቸው ነው የተሳካላቸው የሚል አባባል አለ:: ይህንንም በሚስቱ ብርታት በእጅጉ የታገዘው እና የጥሩ ባለትዳር ምሳሌ የሚሆነው ጥቁር አፍሪካዊ የነፃነት ታጋይ ማርቲን ሉተር ኪንግ የሚከተለውን ተናግሯል::

«በዚህ ትግል ውስጥ ምናልባት የሠራሁት እና ያከናወንኩት ማንኛውም ነገር ቢኖር ከኋላዬና ከጐኔ ሆና በትጋት የምትረዳኝ በተመስጦ የምትከታተለኝ ትዕግሥተኛ ጓደኛዬ በሆነችው በባለቤቴ ምክንያት ብቻ ነው» ብሎ በጨዋነት የሠራውን ክቡር ሥራ ከአካሉ ከሚስቱ ጋር እንዲህ ተጋርቶ ስናይ እኛ እንዴት ነን ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፋናል::

ታላላቅ ሰዎቻችን ንግግር ሲያደርጉ ሲሸለሙ እና ሲከበሩ ሚስቶቻቸው በአዳራሹ ውስጥ አለመኖራቸውን ስናይ ምናልባት ማዕድ ቤት ውስጥ ወጥ እየሠሩ ይሆናል ብለን ብንገምት መዳፈር አይሆንብንም:: የትኛውም መሪ ሚስቱን ሲያሞግስ ታይቶ አይታወቅም ይሄ በነምኒሊክ ጊዜ ቀረ:: የሠለጠነው ዓለም ግን ሥራውን ከማስመረቁ በፊት ከሕይወትዋ ከፍላ ለባልዋ ስኬት ጊዜ የሰጠችውን ሚስቱን ሲያቆላምጥ ይታያል::

ይህም ይቅር ገጠር ያለው አባወራ ሚስቱ እንሥራ ተሸክማ የአንድ ሰዓት መንገድ ከምትጓዝ ከደጁ ተባብሮ የውኃ ጉድጓድ እንዲቆፍር ሌላው ቢቀር በሲሚንቶ የተለሰኑ ጉድጓዶች አሰናድቶ በክረምት የሚንዠቀዠቀውን ዝናብ አጠራቅሞ በጋውን ለመጠቀም ቢጥር፤ እግረ መንገዱን በውኃው ከብቶቹን ቢያረካ የጓሮ ተክሎችን ቢያፀድቅበት ቃሪያውን፣ ጐመኑን፣ ሽንኩርቱን፣ ቆስጣውን፣ ካሮቱን፣ ድንቹን፣ ቀይሥሩንና ቲማቲሙን ለማምረት እኮ ብዙም ብልሃት ላያስፈልግ ይችላል:: በአራት እና አምስት ሜትር እስኩዌር ተቆፍሮ የተጠራቀመ ውሃ በጋውን ሊያወጣው ይችላልና:: ይህን የሚያደርግ ገበሬ አጅሬ ሚስቱ እንሥራ ይዛ እንዳትንከለከል ውኃ አቋረላት ተብሎ ይመሰግናል እንጂ



ይወነጀል ይሆን? በእርግጥ ይህም ትምህርት እውቀት ከሚጠይቁ ነገሮች አንዱ ነው::

በየገጠሩ የተከፈቱት የአረቄ ቤቶች የገበሬውን ገንዘብ እና ጊዜ ጤንነትና አልፎ አልፎ ዕድሜ እየቆማመጡ መሆናቸውን ያስተዋለ ይኖር ይሆን? ባላገሩን ካቲካላው ፈጀው ሲባል ያልሰማ አለ? ታዲያ ሚስት በአረቄ ተነክሮ የሚመጣውን አባወራ በሐዘን እስከ እኩለ ሌሊት ስትጠብቅ ምን ገጠመው? ብላ በር በሩን ስታይ ማንጋት ይኖርባታል? ወዴት እያመራን ነው? ከሴቶቻችን ጋር እንታረቅ::

ምን የገጠሩ ብቻ ከተሜውም ከሥራ በኋላ ድራፍት ቤት አይደል የሚያመሸው ልጆቹ ማታ የቤት ሥራ ይኑራቸው አይኑራቸው ለእሱ አያስጨንቀውም:: ሚስቱ ምግብ እየሠራች ሕፃኑ ሲያለቅስ እያባበለች እያፀዳች ስትባክን አባወራው ከጓደኞቹ ጋር የዓለምን ፖለቲካ ሲፈታ ሲቋጥር ማምሸቱ ሊስተዋል ይገባዋል:: መቼ ነው ከልጆቻችን ጋር የምንጫወተው? ልክ እንደ እንግዳ ካመሸንበት መጥተን ልጆቻችንን ሳንስም፣ ሳናቅፍ፣ ሳናጫውት፣ ሳናስቦርቅ እስከመቼ:: ከነተረቱ የኢትዮጵያ ሕፃን ለአባቱ ግድ የለውም ለእናቱ እንጂ ይባላል:: አባቱን አያውቅም ቢባል አይሻልም?

ለሚስቶቻችን ጊዜ መስጠት ይገባናል፤ የውይይት ጊዜ፣ የጨዋታ ጊዜ፣ የሳቅና የፈንጠዚያ ጊዜ ለቤተሰባችን የደስታ ምንጭ ሊሆን ይገባል::

ከልጅነት ጀምሮ የለመድነው አባቶቻችን ሲመጡ ሮጠን ቤት መግባት፣ ጥግ ያለ ወንበር ላይ ተሸማቆ መቀመጥ፣ በምን እንገረፍ ይሆን? ብለን ማሰብ፣ መሥጋት ነበር:: አሁን የልጆቻችን ሁኔታ መለወጥ አለበት:: ኳስ አብረናቸው ልንጫወት፣ አብረን መጽሐፍ ልናነብ፣ ጣፋጭ ታሪኮችን እየተጫወትን ልንስቅ ልንዝናና ያስፈልጋል:: የተሸማቀቀው የቤተሰብ ሕይወት መለወጥ አለበት:: ከሚስቱ ጋር ነፋስ ለመቀበል የእግር ጉዞ የሚያደርግ አባወራ እምብዛም በአገራችን አይታይም:: ባልና ሚስት ለረጅም ሰዓት ሲያወሩ፣ ሲስቁ፣ ሲቀላለዱ ማየት ብርቅ ነው፤ ይህ ሁሉ ሊታረቅ ይገባዋል::

ኣርግጥ ነው የኑሮው ውጣ ውረድ ጊዜ ሰጥቶን የሕሊና ዕረፍት ያገኘንበት ጊዜ እጅግም ላይሆን ይችላል፤ ግን በምሬት ላይ ምሬት እንዳይሆን በተቻለ መጠን የኑሮን ውጣ ውረድ በዋዛ ልናጣፍጠው ይገባል።

የሴቶች ሕይወት በአፍሪካ ውስጥ ምን ይመስላል? ኢትዮጵያ ሥልጡን በነበረችበት ጊዜ በፖለቲካው ሕይወት ውስጥ እንደነጣይቱ ብጡል፣ ንግሥት ዘውዲቱን የመሳሰሉ ሴቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረው ነበር። ከዚያ ወዲህ ግን ብዙም የሚታዩ ሴቶች የሉንም። በሥነ ጥበቡም፣ በፖለቲካውም፣ በሰብዓዊውም መስክ ሁሉ ስመጥር ሴቶች ለማፍራት ኖረውም እንኳን አጉልተን ልናሳያቸው አልቻልንም። ለምን? በዚህ ሁሉ ከሴቶች ጋር መታረቅ አለብን። በእሩጫው የሴቶች ጥንካሬ ምን ያህል እንደሆነ እየተረዳን ይሆናል።

ባቅድመ ታሪክ በኢትዮጵያ ውስጥ ከታወቁት ታላላቅ የታሪክ ትውስታ ሴት ነገሥታት ብቅ ጥልቅ እያሉ መታየታቸው፣ እነ ንግሥት ማክዳና ንግሥት ሕንደኬ ሌሎቹም ጥበብን ፍለጋ አገር አቋርጠው የሚሄዱ፣ ሕዝባቸውንም የሚያስተምሩ፣ አስተዋይ ሴቶች በነበሩባት አገር ዘንድሮ የተማሩ ሴት ባለሥልጣናት እምብዛም አለመታየታቸው፣ በየሥራ መስኩ የኃላፊነት ቦታ ሲመሩ አለመገኘታቸው እርቅ ከሚፈልጉ ዐበይት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው።

ሴቶቻችን ዕድሉን ካገኙ ካለጥርጥር ሥራ መሥራት ይችላሉ። እኛ ግን በአንድ እጃችን እያጨበጨብን የሴቶችን ተሳትፎ ገድበን በድህነት እየማቀቅን እንገኛለን።

ለምሳሌ የሥራ ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ወደ ውጭ አገር የሄዱ እህቶቻችን በሥራው መስክ ሁለት ሥራ እየሠሩ በቀን 16:00 ሰዓት ቤተ ሰቦቻቸውን አገራቸውንና እራሳቸውን ሲረዱ ስናይ ይህ ዕድል ምነው አገር ቤት በተገኘ ማለታችን አይቀርም።

ይህችው አገር ቤት ምን ታውቂያለሽ? አርፈሽ ተቀመጪ የተ ባለች ሴት ት/ቤት ገብታ በሕሊና ብቃትዋ አንቱ ስትባል ሲታይ፤



ጊዜዋንና የኑሮዋን መጠን ከፈጣኑ ዓለም ጋር በፍጥነት ስታጣጥም ላያት የኛዋ ሴት እንዲህ ነበረች እንዴ? ብለን እንድንገረም ይገፋፋናል። እስቲ ከሴቶቻችን ጋር እንታረቅ፤ ሥልጣኔም እኮ ሩቅ አልነበረም። ከቤታችን ውስጥ ያሉ በተለያዩ ጥበባት እራሳቸውን ከትውልድ ትውልድ ያሠለጡኑ እናቶችን መስማት ቤተ ሙከራ ማዕድ ቤታቸውንም ማክበር ብቻ ይበቃል።

ከዚያ ማዕድ ቤት ፈረንጆች (ferment) የሚሉት ባክቴሪያው (በረቂቅ ተሕዋስያኑ) እርሾ የሚቦካ ኮምጠጥ ያለው እርሾ ይወጣል ይህም ዳቦውን አፋፍቶ ኮምጠጥ ያለ ጣዕም ይሰጠዋል። ሲያፈሉት ደግሞ አረቄ ይሆናል። ይህ ነው ሳይንሱ ዛሬ ዓለም ወደ etanol (E85) የለወጠው መኪና የሚነዳበት ጥበብ የእነ biogas መሠረት የእናቶች ማዕድ ቤት ነች። የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካው መሠረት እኛ ሁልጊዜ የምንዘላት የምንንቃት የእናቶች ባልትና ነች።

የመድኃኒት ቅመማው፣ ማዋለዱ እና ወጌሻነቱ በተፈጥሮ ዶክተር ከሆኑት እናቶች ልምድ ተመዞ ነው ሳይንስ የሆነው። የዕለት ተዕለት ኑሮ የሚያስተምራቸውን ተመርኩዘው ሴቶች የብዙ ፈጠራ ውጤቶች ባለቤት ሳይንቲስት ሆነዋል።

ሔለን ኬለር የተባለችው ማየት፣ መናገር የማትችል እና መስማት የተሳናት ታላቅ ሴት «እኔን የሚገርሙኝ መስማት እየቻሉ የማይሰሙ ማየት እየቻሉ የማያዩ ሰዎች ናቸው» ስትል የማትናገረውን ሴት የሠለጠነው ዓለም ሰማት። እኛ ግን እየተናገሩ አንሰማቸውም የሠሩትንም አናደንቅም ይህም እርቅ ይፈልጋል።

ሔለን ኬለር እንዳለችው ዓይናችንን ልንገልጥ ያስፈልጋል። (The rising of Egypt) የግብፅ መነሳሳት የተሰኘውን ሐውልት የቀረፀው ቀራጺ በኪነ ጥበቡ ውስጥ ያካተተው አስገራሚ ሐሳብ አለ። ይኸውም አንዲት ወጣት ዓይነ ርግቧን በእጆችዋ ገለጥ አድርጋ የምትታይበት እና በአንበሣ ምስል የተሳለው ከጥንታዊው የፒራሚድ ምስል የተቀዳው ከመዳፉ ቀና

ብሎ የሚታየው ሐውልት በወጣትዋ የተመሰለችው ግብጽ ዓይነ ርግቧን መግለጧ ተሸፍኖ የነበረው ተከድኖ የነበረው ሥልጣኔ እንደገና ትንሣኤ ያገኘ የሚል ምኞት የያዘ ሲሆን፤ ከሁሉ በላይ ግን የሥልጣኔ ሁሉ ምንጭ ሴቶች በመሆናቸው ዓይነ ርግባቸው ይገለጥ የሚል አንድምታ የያዘ ነው::

ይህም የግብጽ ሥልጣኔ መሠረት ክሊዮፓትራን የመሠለ ብልህ ሴት መሪዎችን ማስታወሱም ሊሆን ይችላል:: «የክሊዮፓትራ አፍንጫ ጥቂት ብታጥር ኖሮ የዓለም የፖለቲካ አቅጣጫ ሌላ ገጽታ ይኖረው ነበር::» የተባለላት ግብጻዊት ሴት የጥንቱን ሥልጣኔ መልሶ ለማምጣት ወሳኝ ነች የሚል አንድምታ ያለው ይመስላል::

በሴቶች ሕይወት ላይ ያለን ራዕይ ምን ይመስላል? ምንስ ሊሆን ይገባዋል? ይህ ቢሆን አይሻልም?

ከሕፃንነት እስከ ዕውቀት ሙሉ የመተማመን መንፈስ ያላቸው ከወንድ አቻዎቻቸው እኩል ትምህርት ቤት የሚሄዱ፤ የቤት ውስጥ ሥራ ከወንድሞቻቸው ጋር አብረው የሚጋሩ፤ የጥናት ሰዓታቸው የተመጠነ፣ ምግብ ማብሰልና ሌላውም የዕለት ተዕለት ሥራቸው የማንበቢያ ጊዜ ያቸውን እንዳይሻማ ሁሉ የሚያስብላቸው ስለነገ ሕይወታቸው በቤተሰብ ውስጥ የሚታሰብ ሆነው ቢያድጉ አይሻልም?

ማንም ጉረምሳ ባለጌ የማይሰድባቸው፣ የማያንጓጥጣቸው፣ የማይደፍራቸው፣ የማይቀማቸው፣ በሁሉም ኅብረተሰብ ዘንድ በዓይነ ምሕረት የሚታዩ ቢሆኑ ቀና ብለው የሚሄዱ በማንኛውም በጐ ተግባር ሁሉ የሚሳተፉ ሴቶችን ለመፍጠር ምን ያህል ተዘጋጅተናል? ካደጉም በኋላ በትጋት የምናስተምራቸው፤ በሥራው መስክ ተወዳድረው የሚፈልጉት ደረጃ መድረስ የሚችሉ ቢሆኑ አይሻልም? ይህ ሁሉ እርቅ ያስፈልገዋል::

እንዴት ያስፀይፋል፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ሴቶቻችንን የሴተኛ አዳሪነት ሥራ ብቻ ነው ክፍት ቦታ ብለን በየቡና ቤቱ በየዳንስ ቤቱ እህቶቻችንን ዕቃ ማድረጋችን:: ሕሊናቸው የደኸየ፣ የዝሙት ፈረስ በሆኑ ነውረኞች የራባቸው እህቶቻችን የጣርና የባርነት ሕይወት ሲገፉ ዝም



ብለን እኛ ብቻ ይድላን ብለን ማየታችን ንስሐም ይቅርታም የሚጠይቅ ጉዳይ ነው:: ምን አልባት ሁላችንም አውሬነቱን አልተጋራን ይሆናል፤ ግን ውይይቶች ሰላማዊ ሰልፎች ጥያቄዎች ይኸጉደጉዳሉ:: በኢትዮጵያ ምድር ይህ ሲፈፀም አለመጮህም ከተጠያቂነት አያድነንም በብዙ ዓለማት ይህ ዓይነት ጥቃት ሲፈፀም ከመንግሥት ጀምሮ መንደሩ ሁሉ ሳይቀር ለመፍትሔ በትጋት ይሠራል::

ሳይንቲስቷ ነች የዝሙት ሰለባ የኤድስ መፈንጫ የሆነችው:: አገር የምታስተዳድረዋ ጣይቱን የምትመስለው፣ እንደተዋበች ብልሃት የተሞላችው ኢትዮጵያዊት ነች ግራ ገብቷት ቡና ቤት የገባችው:: ምን ዓይነት ንግድ ነው? ዳንስ ቤትና ቡና ቤት ከፍቶ የዜጐችን አካል እፍረት እየቸረቸሩ መክበር ሌላ ሥራ ጠፋ? ገንዘብ የተሸከመው ሁሉ የሴተኛ አዳሪ ቤት የሚከፍተው? እነአሪ በከንቱ፣ ካዛንችስና አቧሬ እነ ደሴና ነቀምት፣ ባሕርዳር፣ ሀዋሳ፣ ዝዋይና ናዝሬት ሌሎቹ ጥቃቅን ከተሞች በሴተኛ አዳሪ ቤት የተጥለቀለቁባት አገራችን ኢትዮጵያ መሆንዋ ሊያስለቅሰን ይገባል::

ከዚህ አልፎ ተርፎ የአሥራ አምስት ዓመት ሕፃናት ሳይቀሩ በየጥጉ ቆመው በእርኩሰት የሰከረ አውሬ ሲጠብቁ የአካልና የሕሊና ቁስለኞች ሲሆኑ ማየት አገሬ ኢትዮጵያን ኤሎሄ አሰኝቶ ሱባኤ ሊያስገባ ሊያወያይ ሊያከራክር የመፍትሔ ሐሳብም ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው:: በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ነው ሴቶች የተጠቁት እርቅ እርቅ እርቅ ያስፈልጋል::

ይህ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን የወረራት ነቀርሳ ነው:: ስለዚህም የአፍሪካ ሴቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እያሰሙ ይገኛሉ:: ስለዚህም ከእኛ ኋላ የተነሡ የእኛው አባቶች አርአያ ሆነዋቸው ወይም ሄደው ተዋግተውላቸው ከኮሎኒያሊዝም ነጻ የወጡ አገራት የሴቶችን መብት አክብረው ወንዶች የሚሳተፉበትን የሥራ መስክ እንዲጋሩ አድርገዋቸዋል::

መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም. የወጣው ኒውስዊክ የተሰኘው መጽሔት (Africa Healing Powers) የአፍሪካ የፈውስ ኃይሎች ብሎ ባወጣው ጽሑፉ ሴቶች የአፍሪካ ተስፋዎች ይሆኑ ይሆን? ብሎ ይጠይቅና (Ellen Johnson-Sirleaf) (ኢለን ጆህንሰን ሰርሊፍ) የተባሉትን የ60 ዓመትዋ አያት በቅርቡ የላይቤሪያ ርዕሰ ብሔርነትን 60 በመቶ ድምፅ ተቀዳጅተው ሥልጣን መያዛቸውን ያበስራል።

የአፍሪካ ሴቶች አዲሱን ሕግ በማዘጋጀት ኃላፊነት ወስደዋል። ሌሎችም አመራራቸውን እየተከተሉት ነው። ያለፈውን ያረጀውን ገጽታ ለመለወጥ የተሰበረውንም የአህጉሩን ሁኔታ ለመጠገን ማነው ከጐናቸው የሚቆመው? የሚል ጥያቄ አቅርቧል።

የቀድሞዋን የደም ውቅያኖስ ላይቤሪያን ለማስተዳደር በትረ ሥልጣኑን የተረከቡት የ67 ዓመትዋ አያት ከታወቀው ቦስተን ከተማ በሚገኘው የሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ በመዋዕለ ነዋይ ጥናት የማስተርስ ዲግሪያቸውን ይዘው በዓለም ባንክ ያገለገሉት ኢለን ጆህንሰን ሰርሊፍ ናቸው።

ስድሣ በመቶውን ድምፅ አግኝተው በእውነተኛ ውድድር በትረ መንግሥቱን የጨበጡት። ይህም ከርዕሱ እንደተረዳነው ቁስልን የሚጠግኑ ኃይላት ወይም የፈውስ የመድኃኒት ኃይላት አሰኝቷቸዋል።

በመድፍ፣ በታንክና በመትረየስ የተበሳሱ ሕንፃዎችን የተዘበራረቀውን የላይቤሪያን ሕይወት ያክሙታል የተባለላቸው ተሿሚዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ ድምፅ አግኝተው የተሾሙ የተመረጡ ሴቶች መሆናቸው እውነትም አፍሪካ ከተዘፈቀችበት የድህነት አዘቅት ለመውጣት መቁረጥዋን አመላክቷል።

ባለፉት የእርስ በእርስ ጦርነቶች ምክንያት ላይቤሪያ 150,000 ወጣቶችዋን አጥታለች። ሦስት ሚሊዮን ዜጐችዋ በስደት ዓለምን አጥለቅልቀዋል። ሞኖሮቪያ የተባለችዋ ዋና ከተማ ከ1991 እስከአሁን የኤሌክትሪክ መብራት የላትም፤ በእኛ አቆጣጠር 1984 ዓ.ም. መሆኑ ነው



የሥራ አጡ ቁጥር 80 በመቶ ከሆነ ቆይቷል። ከአንድ ሺህ አዲስ የሚወለዱ ሕፃናት በድህነት ምክንያት ደግሞ 129 ይሞታሉ። ከሁሉ በላይ አስገድዶ መድፈር ልማድ ሆኖ ነበር፤ በዚህ መካከል ነበር እኝህ አዛውንት የላይቤሪያ መድህን እኔ ነኝ በማለት ወደ አስተዳደር መድረክ የወጡት።

በዓለም ባንክ ሲሠሩ አርቆ አሳቢነታቸው የተፈተነው የሕሊና ብቃታቸውን የተረዳው ዓለም በታላቅ አክብሮት ነበር የተቀበላቸው። የላይቤሪያ ሕዝብ ገጽ ላይም የእፎይታ ምንባብ ታይቷል። አንዲት ቀን ጠብመንጃ ጨብጠው የማያውቁት ወይዘሮ በሕሊና እና በሰብአዊ ብቃት ብቻ አገራቸውን ሊያስተዳድሩ ተዘጋጅተዋል።

«እኛ» ይላሉ አዲስዋ ተሿሚ «እኛ በሕዝባችን ፍላጐት ነው የተሾምነው። በላይቤሪያ የሰቆቃ ጊዜ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ላይ የተሳተፉ ነፍሰ ገዳዮችን ይቅርታ ወይም ፍርድ የሚወስነው ሕዝቡ ነው።» ብለዋል።

ዞሮ ዞሮ ጊዜ ይፍጅ እንጂ ሕፃናትን ለጦርነት የዳረገ፣ አዛውንቱን ያሳረደው ትምክህተኛውና ጨካኙ ጆዋል ሀዋርድ ቴለርን ጨምሮ በየዘርፉ ያሉ ደም አፍሳሾች ዛሬ በዓለም ዳኝነት ሸንጐ ፊት ቆመዋል የጦር ወንጀለኞች ስማቸው እየተመነጠረ በሥራቸው እየተዳኙ ነው።

እነዚህ ሰዎች የዓለምን ምሕረት ይቅርታ ያግኙ ወይም አያግኙ የሚለው ጥያቄ እራሱ አጠያያቂ ነው። የዚህ መጽሐፍ ሐሳብ ይቅርታ በመሆኑ አንዲት አገርን ያመሱ ጃዊሳዎች በሕግ የበላይነት ጥላ ሥር በእውነት ካለአድልዎ ካለማጭበርበር ከበደል በነጹ ዳኛ ቢዳኙ የእርቅ እሳቤን ያጠፋው ይሆን? ወይስ ለማንኛውም ወንጀል ማንም ዋጋ ሳይከፍልበት ማለፍ የለበትም ብለን እንለፈው። ግራ ያጋባል።

በአንድ በኩል ዓለምን ያመሱ ጨካኞች መቀጣታቸው የሚገባ ነው ስንል የይቅርታ ሐሳብ ደግሞ ጥልቅ በመሆኑ ደፍሮ እንዲህ ይሁንባቸው ለማለት ያስቸግራል። ስለዚህ ሕግና ርህራሄ ከሩቅ ሲተያዩ ይኖራሉ ከማለት በስተቀር ሌላ የምንለው የለም።

ወደ ቀደመ ርዕሳችን ስንመለስ አዲሶቹ ሴት መሪዎች «የሴቶች በፖለቲካው መስክ መሰለፍ በወንዶች የበላይነት ተደፍቆ ኖሯል:: ለምሳሌ ሴት መሪዎች እንኳን በአፍሪካ በዓለምም ላይ የነበሩበት ዘመን በጣም ጥቂት ነው:: ሌላው ቀርቶ ብዙ የአመራር ቦታዎች በወንዶች ነው የተያዙት:: ስለዚህ ሚዛኑ ወደ ወንዶች ሐሳብ አድልቷል:: በቤተሰብ አስተዳደር ከወንዶች የበለጠ በቂ ልምድ ያላት እናት እና ሚስት ማስተዳደርዋ ጦርነት ላሰቀቀው፣ በመዋዕለ ነዋይ ለደቀቀው አፍሪካ መድኃኒት ነው» ይላሉ:: እንደውም የአፍሪካ ሙስና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተገለባበጠ የመጣው የእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት በወንዶች ብቻ ተጠፍሮ ተቆልፎ የተያዘው ኢ-ዴሞክራቲክ አስተዳደር ውጤት ነው» ይላሉ::

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የአፍሪካ እናቶች ለዓለም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እያሰሙ ያሉት:: «ከምዕራባውያን የሚለገሰውም ሆነ አገር ያፈራውን ሀብት እኛ ሴቶች ብናገኘው ኖሮ የጦር መሣሪያ በጭራሽ አንገዛበትም ነበር:: ጓዳችንን ለማሸነፍ አብቃቅተን እንጠቀምበት ነበር እንጂ» እያሉ ነው:: ሴቶች ቢመሩ ጦርነት ይጠፋ ይሆናል የሚለው ግምት ግን ከብዙ የታሪክ መረጃዎች አንጻር አሻሚም ነው::

በሩዋንዳ የቱሪዝም ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ሮጋምባ የአገራቸውን የቱሪዝም መስክ ለማስፋፋት አዲስ ዕቅድ አውጥተዋል:: ይኸውም ከሚሸጠው አንድ ኪሎ ቡና አንድ ብሩን በሩዋንዳ ጫካ ውስጥ ለሚጉማለለው ጉሬላ ዝንጀሮ ጥበቃ እናውለዋለን ያሉት:: (ይህ ትልቅ ዝንጀሮ በዓለማችን የብዙ ቱሪስቶችን ዓይን የሳበ ፍጡር ነው) ይህ ሐሳብ በዓለም የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ምን አንድምታ እንዳለው በሙያው የተሠማራ ብቻ ነው የሚያውቀው:: ታዲያ ከዚህም የበለጡ አገር የሚገነቡ ኃይላት የሚመነጩት ልዩ የፈጠራ ኃይል ከተሰጣቸው ሴቶች ነው::

በገጠርም በከተማም ያለን ኢትዮጵያውያን ዘወር ብለን በአብዛኛው የአካል ብቃት የሌላትን ሴት ግን የሕሊና ብሩህነትዋ እንደማዕድን ተቆፍሮ ያልተደረሰበትን ሴት እናይ ዘንድ ያስፈልጋል:: ከማጀት በጭስ



እየተሰቃየች ያለችውን ሴት ከአመድ ውስጥ ልናነሳት ይገባል:: ብናዋያት አንገቷን ከደፋችበት ቀና ሳትል ብዙ ቁም ነገር ታጫውተናለች::

ብልህ አባወራ የሚስቱን ሕሊና ያከብራል፤ ይጠቀምበታል:: ሠርግ ቤት ሲሄድም ሆነ ሲንሸራሸር ከሚስቱ አይለይም:: የክት ልብሷን አልብሶ እሱም ሽክ ብሎ በሚስቱ ይከበራል::

ብልህ አባወራ ሚስቱን ያከብራል፤ ጮክ ብሎም አይቆጣት ቤቱም ፀጥታ የተሞላ ነው:: ልጆቹም ሥርዓት አላቸው:: ብልህ አባወራ ሚስቱ ስትደክም ያውቃል፤ ስትታመም ያመዋል፤ ስታዝን ያበረታታታል፤ በቀልድና በፈገግታ ሐዘኗን ያስረሳታል:: በዚህ ሁሉ ከሴቶቻችን ልንታረቅ ያስፈልጋል::

እናቶቻችን ውቦች ናቸው፤ልጆቻችንን ተንከባክበን ከያዝናቸው ጣፋጭና ብሩህ ሕሊና የታደሉ ናቸው:: ካከበርናቸው ያስከብሩናል::

ግን እንዴት እህቶቻችን ልጆቻችን እየተሸጡ በየዐረቡ ዓለም ይንከራተቱ ከፎቅ በውበታቸው ምክንያት ይወርወሩ? የፈላ ውኃ ይከለስባቸው? ይህንን እያዳመጥን ጥቃት እንዴት አይሰማንም?

ለመሆኑ በየከተማው በምሽት የሚኮለኮሉት ሕፃናት የዝሙት ሰለባ ሴቶቻችን የወደፊት ሕይወት ምን ይሆን ይሆን? ለምን ያህል ጊዜ በዚህ ሁኔታ ይቀጥላሉ:: እመኑኝ ለኤድስ ጭዳ ሊሆኑ የተመለመሉ ናቸው:: ታዲያ እንዴት ወደ ጤነኛ ሕይወት እንመልሳቸው::

እባካችሁ ከሴቶች ጋር እንታረቅ:: ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ እንዴት በሴተኛ አዳሪነት ትጥለቀለቅ? እንዴት በኤድስ አንደኛ እንውጣ? ጥቃቱ ይሰማን::

የግል ውሣኔ እንወስን መንገድ ላይ የቆመችይቱን ሕፃን ሕይወት ለመለወጥ:: ሌላው ቢቀር እራሳችንን ተቆጣጥረን አልፈናት ለመሄድ ሲርባት ብናጉርሳት ሥራ ብንፈጥርላት:: በእውነት ከሴቶቻችን ጋር እንታረቅ::

# ምዕራፍ ስድስት

## ከሕፃናት ጋር መታረቅ

ከሕፃናት ጋር እንታረቅ ስንል በማኅፀን ካሉት ጀምረን መሆን አለበት። ስለሁሉ ጥያቄ መልስ የሚሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ ነውና በመጽሐፈ ኢዮብ በማኅፀን ስለአሉ ሕፃናት ምን እንደተነገረ እናይና ወደሰፊው ርዕሳችን እናመራለን።

**«እጆችህ ፈጠሩኝ ሠሩኝም ....**
... በእውኑ እንደወተት አላፈሰስኸኝምን?
እንደእርጐ አላረጋኸኝምን?
ቁርበትና ሥጋ አለበስከኝ
በአጥንትና በጅማት አጠነከርከኝ
ሕይወትና ቸርነት አደረክልኝ።»

በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በማኅፀን ያለው ሰው ምን ዓይነት ደረጃዎችን አልፎ እንደሚወለድ የሚያስረዳን ሲሆን፤ ኢዮብ እኔን እንዲህ አድርገህ አበጃጀኸኝ እያለ ሲናገር ሰውን ሁሉ ወክሎ ነው። እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ሰማይና ምድርን ብርሃናትን ሁሉ ሲፈጥር መልካም ነበር እያለ በመጨረሻው ሰውን ሲፈጥር ግን እጅግ መልካም ብሎ የሰውን አፈጣጠር አድንቋል።

ሰለሞንን አባቱ ዳዊት ሲመክረው «ልጄ ሆይ ሰው ሁን» ነበር ያለው። በዚህ ሁሉ ሰው ምን ያህል ዕፁብ ድንቅ ፍጥረት መሆኑን እንረዳለን።

ታዲያ ከዕለት ጽንስ ጀምሮ ሰው ሰው መሆኑን ከዚህ ቃል መ ረዳት እንችላለን። ሰው እጅግ በተወሳሰበ ረቂቅ መንገድ የሚፀነስ የሚወለድም ባለአእምሮ ፍጥረት ነው። ብዙ የጥበብ ሰዎች የሰው የአእምሮው መጠንና ውስብስብነት ከዝንጀሮ እና ከሌሎችም እንስሳት ይበልጣል ሲሉ በተዘዋዋሪ ሰውን በጥበብ እግዚአብሔር ሠራው የሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሱናል።



በማኅፀን ያለው ሰው ይሰማል፤ ይደሰታል፤ ያዝናል፤ ይጨነቃል በማኅፀን ያለው ሰው እንክብካቤ ፍቅርና ርህራሄውን ይፈልጋል። ይህን ዓለም በደግነቱና በርህራሄው በጭካኔውና በኃጢያቱ ይታዘበዋል።

ስለዚህም ነው በዚህ ዘመን በማኅፀን ላሉ ሕፃናት መጽሐፍ ሲነበብላቸው አባትና እናት እየተፈራረቁ ጆሯቸውን ደቅነው ሲያዳምጡ የሚውሉት። ለስላሳ እና ጣፋጭ ዜማዎችን እስኪወለድ ድረስ የሚያስሙት ስሜት አለው ብለው ነው።

እውነትም አንድ ጽንስ ከእናቱ በቀጫጭን ሥሮች የሚሰጠውን ምግብ የሚመገብና የሚያጣጥም ከሆነ በጣፋጭ ምግቦች ሲቦርቅ፣ ሲደሰት ቆይቶ ምግብ ሲያጣ ደግሞ ድምፁን የሚያጠፋ ከሆነ በአጠቃላይ ከአምስቱ ሕዋሳት መቅመስን ከለየ መስማትን የማይለይበት ምክንያት ምንድነው? ይህ ሁሉ ስሜት ያለው ሕፃን ደግሞ ሰው የማይባልበት ምክንያት ምንድነው?

ኤልሣቤጥ የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ጽንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ* ሲል ጣፋጭ ድምጾችን አስደሳች ንግግሮችን የለየው ሰው የተባለው ጽንስ የእመቤታችንን የሰላምታ ድምጽ ሲሰማ እንደ እንቦሳ ጥጃ ያዘለለው ከመስማትም አልፎ መንፈስ ቅዱስን በመሞላቱ አይደል? ንጹሕ አእምሮው ከእውነት መንፈስ ጋር ቢስማማ እንጂ የስድስት ወር ጽንስ በሰው ልማድ ምን ሊለይ ሊያውቅ ይችላል?

እግዚአብሔር በማኅፀን የነበሩትን ያዕቆብንና ኤሳውን ገና ሳይወለዱ ከሰውም አልፎ ሕዝብና ሕዝብ ሲላቸው እናያለን። ሲጣሉ ገና ከማኅፀን መንታዎቹ ሲከፋፈሉ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሲበረታ እናያለን። ይህ ሁሉ ትዕይንት የሚታየው በማኅፀን ውስጥ ባለው ዓለም ነው።

እንደውሃ የፈሰሰውን አጥንትና ጅማት ሰጥቶ ቁርበት አልብሶ ንፁሕ ጠባይ ያለው ባለአእምሮ ሰው የሚፈጥረው እግዚአብሔር ሼክስፒር

* ሉቃ. 1፥41

እንዳለው «እፍኝ አፈር ዘግኖ በሥነ ፍጥረት ርቀት መደሰት ያሰኘው እግዚአብሔር እፍ ብሎ ሰው ነህ ሲለው ከመመርመር በላይ ከማሰብ በላይ የሆነውን የአንድ ቀን ጽንስ እኛም እንድናከብረው እንድንጨነቅለት እንገደዳለን።

ስለዚህ በኑሮ ድቀት ምክንያት በጊዜ ማግባት የሚገባቸው ወጣቶች ሳያገቡ ብዙ ዘመን ይቆዩና ሰዎች በመሆናቸው በትዳር ሥርዓት መያዝ የሚገባው የሥጋ ባሕርይ ተጋልጦ ከትዳር ውጭ በሚፈጠር እርግዝና ሲጨነቁ ወደ ውርጃ ያመራሉ። ሊፈረድባቸው አይገባም። ሰው ናቸውና መታገስ አይችሉም የኢኮኖሚ አቅማቸው አናሳ ነውና ልጆቻ ቸውን ማሳደግ ይሳናቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በኅብረተሰባችን ውርደት ሆኖ የሚቆጠረው ይህ ከትዳር ውጭ የመውለድ ጉዳይ የባሰ የበደል በደል እያስፈፀመን ተገ ኝቷል። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ጽንስን ከማስወረድ መውለዱ ሊያስመሰግን ሲገባው ከትዳር ውጪ በስህተት ያረገዙ ሴቶች ሲሰደቡ ሲሳቀባቸው የሚያዩ ሌሎች ወጣቶች በእነሱም ላይ ይህ ስህተት ሲከሰት ወደ ውርጃ በማምራታቸው፤ አንደኛ ጽንስን በማስወረድ ለኃጢያት ይበቃሉ፤ ሁለተኛ እስከነ አካቴው የእራሳቸውንም ሕይወት ያጣሉ።

መቼም ሳናውቅ በስህተት አውቀንም በድፍረት ስለሠራነው በደል እግዚአብሔር የምሕረቱን ዝናብ ያጉርፍልን። ካወቅን ዘንዳ ላለመድገም ከመቁ ረጥ ባለፈውም ከመጸጸት በቀር ሰው ነንና የጠፋውን ሕይወት መመለስ ፈጽሞ አይቻለንም። ስለዚህ ውርጃን በመቃወም በማኅፀን ካለው ሕፃን ጋር ልንታረቅ ይገባናል።

እናቶች በእርግዝና ወቅት መጉሳቆላቸውና ምግብ ማጣታቸው በማኅፀን ያለውን ሕፃን ስለሚጐዳው እንደባሕል አንድ ነገር መልመድ ይገባናል። በኢትዮጵያ ምድር ነፍሰጡር ሴት ዕቃ ተሸክማ ስናይ ልናግዛት ቃል መግባት ይገባናል። 50 ኪሎ ጤፍ በጀርባዋ፣ በማኅፀንዋ ደግሞ ሕፃን፣ በእቅፏ ሌላ ልጅ ተሸክማ የምትሄደውን እናት ማገዝ ከሁሉ በላይ ጽድቅ ነው። የዜግነት ግዴታን ከመወጣትም በላይ ከሕፃናትና ከእናቶች ጋር እውነተኛ እርቅ ማድረግ ነው።



ለነፍሰጡር እናቶች ማንኛውም ሰው ሙዝና ብርቱካን ገዝቶ መስጠትን ልምድ ብናደርግ። በሠለጠነው ዓለም ቫይታሚን ያላቸው እንክብሎች የሚታደላቸውን እናቶች የሚያስንቁ በእርግዝናቸው የደረቁ ሳይሆኑ አበባ የሚመስሉ እናቶችን ማየት እንችላለን። በአጠቃላይ አላፊ አግዳሚው ለእርጉዞች የእራሱን ግዴታ ሊወጣ ይገባዋል። ይህ ሕዝባችንን ወደ ቤተሰብነት የሚቀይር የእርቅ መንገድ ነው።

አስተውሉ በማንኛውም የበለፀጉ ዓለማት እናቶች በእርግዝና ወቅት ምግባቸው ሕክምናቸው ይሟላላቸዋል። በመንግሥት ደረጃ ይህንን ለማድረግ አንችልም ግን ይህን ሸክም በግላችን ልንጋራው እንችላለን። ይህም በጥንታዊው «ነፍሰጡር ያምራታል» በሚለው ጥሩ ባሕል ከምንመገበው በመመገብ ነው።

በማኅፀን ያለውን ሕፃን እንዲህ ከተንከባከብነው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ምን ማድረግ ይገባናል ወደሚለው እናመራለን።

ኢትዮጵያዊው ሕፃን ምን ይመስላል። በዚህ የእርቅ ጽሑፍ ላይ መሞጋገስ እምብዛም ላይኖር ይችላል ስህተትን ማረም እንጂ።

በአገራችን ያሉ ሕፃናት አስተዳደግ በሁለት ይከፈላል። በከተማ እና በገጠር ከሁሉ በፊት በከተማ ስለሚያድጉ ሕፃናት እንመለከታለን። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በከተማም ሆነ በገጠር ያለውን ዕድገት በመጠኑ በመኖርና በማየት የእራሱን ምሥክርነት ለመስጠት ይሞክራል። ስለዚህ ከዚህ በኋላ የእኛ ሕይወት እንዴት ነበር? በሚል እኔ በሚል ይትበሃል ይጽፋል። እኛ በከተማ ውስጥ ያደግን ሕፃናት እንዴት ያለ ሕይወት አሳለፍን?

በበኩሌ ይላል የጽሑፉ አቅራቢ በበኩሌ የእናቴንና የአባቴን ፍቅር አግኝቼ ያደግሁ ሕፃን ነበርኩ። ግን የማልሸሽገው አባትና እናቴ ተለያ ይተው ስለነበር እስከዚህ ዕድሜዬ ድረስ ቅር የሚሉኝ ጉዳዮች አሉ።

በተለይም አባቴ በጦርነት ምክንያት አብሮኝ ብዙ ጊዜ ስላልኖ ረ ጥንካሬውን፣ ብልሃቱንና አስተዋይነቱን ለመውረስ በአጭሩ

የግንኙነታችን ጊዜ ተጣዳፊ ነበር:: ብዙዎች በእኔ ዕድሜ የነበሩ ሕፃናት በቤተሰብ ፍች ይሰቃዩ ነበር:: አንድ ሕፃን እናቱንና አባቱን በአንድ ላይ እያየ ማደጉ እጅግ ያስደስተዋል:: እኔም በለጋ አስተሳሰቤ ወላጆቼን ለማስታረቅ እደክም እንደነበር ትዝ ይለኛል::

አባቴ እጅግ አስተዋይ ደግና ቆፍጣና ሰው ነው:: ጨዋታ የሚያውቅ፤ አስታራቂና ታማኝ ነበር:: ታዲያ ይህ ታላቅ ሰብዕና ተልከ ስከሶ እንዲቀር የሆነበት ዐበይት ምክንያት የትዳሩ አለመሳካት መሆኑን የምረዳው በዚህ ዕድሜዬ ነው::

ትዝ ይለኛል እናቴ ማገር ማግራ ቆርቆሮ ላይ ወጥታ ሚስማር እየመታች ቤት ስትሠራ፣ ግድግዳውን ምሣ በር ስታበጅለት፣ ጭቃ አቡክታ ምርጊት ስትመርግ በዚህ በአሁኑ ሕሊናዬ ይህች ሴት እኮ ብትማር የወጣላት መሐንዲስ ልትሆን ትችል ነበር ያሰኘኛል::

ታዲያ ሁለቱም ወላጆቼ የየራሳቸው ጥንካሬና ልበ ሙሉነት ስለነበራቸው ይመስለኛል አንዱ ለአንዱ ማሸነፍ ተስኗቸው የተፋቱት:: በዚህ ውስጥ ግን የእኛ የሕፃናቱ ሕይወት ከጥያቄ ውስጥ የገባ አይመስልም:: ስለዚህ በሕፃንነት ዘመናችን የምንወያይበት ርዕስ ስለቤተ ሰብ ስለነበር በብዥታ የሚታዩኝ ስዕሎች ዛሬ ጐልተው ይታዩኝ ጀምረዋል:: የእኔ ቤተሰቦች ካለዕውቀት ቢለያዩም ማግኘት የሚገባኝን እንክብካቤ አገኝ ዘንድ ሲጣጣሩ አስተውል ነበር:: ግን ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ዘወትር አባቴን ሳየው ባለመታደሌ በውስጤ ሰቀቀን መሰቃየቴን መደበቅ ይሳነኛል:: በነበረችን አጭር የግንኙነት ጊዜ ከጥንካሬው ጥንካሬ፤ ከብልሃቱ ብልሃት የንግግር ዘዬውን ሁሉ ለመቅሰም ተጣጥሬአለሁ፤

አባት በአንድ ሕፃን ሕይወት ውስጥ የሚያሳድረው የሥነ ልቡና ጥንካሬ ነገሮችን በቀላሉ ለመሥራት አቋራጭ መንገዶችን፣ ትዕግሥትንና ከሰው ጋር የመኖርን ብልሃት ሁሉ በመሆኑ አባትና እናት መለያየታቸው አንድን ሕፃን በጐዶሎ ሕይወት ማስቀረት ነው:: ከዚህ በላይ ወላጆች በልጆቻ ቸው ፊት መጨቃጨቃቸው አልፎ ተርፎ ድብድቡ አስደንጋጭ ነው::



አባቶቻቸው ትተዋቸው፣ ረስተዋቸው የሚያድጉ ሕፃናት በኢትዮጵያ ሞልተዋል:: በጥቂቱም ካለእናት የተተው ይታያሉ:: ይህ የቤተሰብ ሚዛን መዛባት የፈጠረውና የሚፈጥረው ውጥረት ክብደቱ በዚህ ትውልድ ላይ ተጭኗል:: ስለዚህ ስለሕፃናት ስንል ጉዳቱን ሁሉ ውጠን ታግሰን ልንኖር ይገባል:: ከሕፃናት ጋር እንታረቅ:: ከዚህ ሁሉ በላይ በኤ ድስ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ሁኔታ አስደንጋጭ ነው::

ትዝ ይለኛል ከእኔ ጋር የሚማሩ ሰፈር አብረውኝ የሚጫወቱ ሕፃናት በጉማሬ ተገርፈው፣ በጥፊ ዓይናቸው በልዞ በቁንጥጫ ሰውነታቸው በልዞ፣ በርበሬ ታጥነው፣ ከአልጋ ጋር ታስረው ይገረፉ የነበሩ ናቸው:: ከሁሉ ከሁሉ የማይረሳኝ በሰካራም አባቱ በጋለ ካውያ ከዓይኑ በታች ጉንጩ ላይ የተተኮሰውና ለብዙ ጊዜ ትንሿ ፊቱ ስትመግል የነበረውን ጓደኛዬን ልረሳው አልችልም::

ባዶ ቤት ካለጠባቂ የሚተው ሕፃናት እሳት አቃጥሏቸው ምናምን ውጠው አለቁ ሲባል፤ ጥበቃ የሌላቸው ሕፃናት ወንዝ ገብተው ሲሞቱ፤ በርሃብ፣ ሕክምና በማጣት የሚያልቁ ሕፃናት ለቅሶ የጆሮ ቀለብ ሆኖ እንደነበር በእኔ ዘመን የነበሩ ሁሉ ሲሰሙት የነበረና የአደባባይ ምሥጢር ነው::

በሕፃንነታቸው የቤት ሥራ የሚያሠራ ወላጅ በመጥፋቱ ጠዋት በአስተማሪ የሚቀጠቀጡ ብዙዎች ነበሩ:: ይህ የሦስተኛው ዓለም አጠቃላይ ችግር ነው፤ ግን እኛ ከሰው በፊት ሰለጠንን ካልን በሕፃናት አስተዳደግ ላይም ሥልጣኔው መታየት ይገባዋል:: እኛ ያደግንበት ዘመን ታላላቆቻችን በፖለቲካ ቡድን ይተራመሱ የነበረበት፤ ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር የተፋፋመበት ዘመን ስለነበር ሬዲዮውም ሆነ ቴሌቪዥኑ በጭካኔ ንግግር የተሞላ ነበር:: የሚበተኑት ምንባቦችም ሆኖ የሚሰቀሉ መፈክሮች ይወድማል፤ ይደመሰሳል የሚሉ እርግማን የተሞሉ ነበሩ:: ሁሉም ይካሰሱ ነበር ግን ሁሉም ጥፋተኞች ነበሩ:: ሳይቸግራቸው የሰው አገር ሽብር ስበው የወደፊት ሕይወታችንና አገራችንን የደም ውቅያኖስ አደረጓት:: አዛውንቱን አስቀድመው ስለጨረሷቸው አስታራቂ የለም:: የሽብር አይዶሎጂ ስበው ሀገሪቱን የአጋንንት መፈንጫ አድርገዋት ነበር::

በከፍተኛ የተደለደለው በቀበሌ የተሸነሸነው አገር በዛው መጠን ወጣቶችን በሚያጉሩ እሥር ቤቶች ተሸንሽኖ ነበር። ይህ በሥነ ልቦናችን ላይ ፍርሀትን ስለአሳደረ መንፈሳችንም ባሪያ ሆኖ ነው ያደገው። ከትምህርት ቤት ስመጣ እስፋልቱ በነጠብጣብ ደም ተሞልቶ ወላጆቻችን በሹክሹክታ «ጨረሳቸው» እያሉ ሲያለቅሱ።

ታዲያ ትምህርት ቤታችን መንደሩ እና አካባቢው በሽብር የተሞላ አስፈሪ ከመሆኑ የተነሣ ሕፃናት ወደ ትምህርት ቤት ሂዱ ሲባሉ እናታቸው ቀሚስ ውስጥ ተደብቀው ሲያለቅሱ ተመንጭቀው ከመወሰዳቸው በስተቀር ምን አጋጠማቸው ምን ለዚህ አደረሳቸው የሚል አልነበረም። እውነቱን ለመናገር ትምህርት ቤቱም አስፈሪ ነበር። ገና ከመግቢያው በር ላይ ጉማሬ የያዘው ፊደል ያልቆጠረ፣ ስለሕፃናት አስተ ዳደግ ዕውቀቱም ጭንቀቱም የሌለው ዘበኛ እግር እግራችንን እየለበለበ ያስገባናል።

በኑሮው ውጣ ውረድ የከፋው ማታ መጠጥ ቤት ተሸልሞ የሚያመሸው መምህር የተለመደውን አለንጋ በእጁ ጨብጦ ሊያስተምረን ይሞክራል። እኛ ግን የምትለበልበዋ አለንጋ ላይ ነው ልባችን ያለው።

የሦስተኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ እንግሊዝኛ ማንበብ ስለተሳነኝ በመጥረጊያ እንጨት ይደበድበኝ የነበረው መምህር፣ በደበደበኝ ቁጥር ደግሞ የማውቀው እየጠፋኝ ስሰቃይ በዓይነ ሕሊናዬ አሁን ድረስ ይታሰበኛል።

በሕፃናት ላይ የሚፈራረቀው የሥቃይ ዓይነት አይረሳኝም፣ በመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ የሂሣብ መምህሩ ጣትና ጣት መካከል እስክሪብቶ አስገብቶ በጠንካራ መዳፉ ትንሿን ጣታችንን ሲያልመዘምዛት ሊሠባብራት ልባችንን አልፎ ውስጠኛው ነፍሳችን ውስጥ የሚገባው ሕመም። በሁለተኛ ው ክፍለ ጊዜ የአማርኛ መምህር በማስመሪያ ጠርዝ ያችኑ ጣታችንን ሲሰባብሯት። በሦስተኛው ክፍለ ጊዜ የሳይንስ መምህር ወንበር ላይ አስተ ኝተው በአለንጋ ሲጠዘጥዙን በአራተኛው ክፍለ ጊዜ ተንበርክኩ ስንባል፣ ከእኛ መካከል ዱላ የያዘ ከፍ ያለ ልጅ አለቃ ሲሾምብን።



ይህንን ሁሉ መከራ አልፈን እቤት ስንገባ ፍቅር አልባ ቤተሰብ፣ መንደሩና ከተማው በተኩስ ሲሸበር ካለጥርጥር አካባቢያችን ሕፃናት ሊያድጉበት የሚገባ አልነበረም ለማለት ያስደፍራል። ጐረቤቱ ሁሉ ሳይቀር ጆሮ ቆራጭ ጭራቅና ምናምን የሚል ቅጽል የማስፈራሪያ ስም ነበረው። ይህ ነበር ከተማችን። ግን በዚህ ውስጥ መልካም ወላጆች አልነበሩም ማለት አይቻልም። በፍቅርና በርህራሄ የሚያጫውት ከወላጅ የበለጠ የምናስታውሰው ጐረቤት የለንም ማለታችን አይደለም።

ሌላውን ክፍል ትተን የእነሱን ክፍል መርጠን ስናዳምጣቸው ብንውል የማይሰለቹ በእጃቸው ከመጽሐፍና ከጠመኔ በስተቀር አለንጋ የማይታይ መስህብ ያላቸው መምህራንም ነበሩን። እነዚህን ብልህ ባለተ ሰጥዖ የጥበብ አባቶቻችንን በልባችን ውስጥ የማይረሳ ሐውልት አቁመንላቸዋል።

በመሠረቱ በፍቅር ካስረዱት የማይገባው ሕፃን የለም። ደደብ ሕፃናት፣ ደንቆሮ ለትምህርት ያልተፈጠረ ፍጥረት በዚህ ምድር የለም። የሕሊና ብቃቱ የሰው ልጅ የማሰብ ኃይሉ የአእምሮ መጠኑ በትምህርት የሚበለጽግ የሚያድግ ነው። እርግጥ ነው በተፈጥሮ ከፍተኛ ጸጋ የተ ሰጣቸው አሉ። አንድን ሕፃን በዘዴ በብልሃት ካስጠኑት ሁሉን መቀበል መያዝ ይችላል። የአእምሮ መጠኑም ይበለጽጋል።

ከዚህ ይልቅ ግን መማር የሚገባው ሕሊና ገና በለጋነቱ የቤተሰብ ረብሻ፣ የመምህር ዱላና ስድብ ከታጨቀበት እንዴት ለዕውቀት የተዘጋጀ ሕሊና ይኖረዋል? ስለዚህ ወላጆች መምህራን ማኅበረሰቡ ሳይቀር ከሕፃናቱ ጋር ሊታረቅ ይገባዋል።

በአመጽ ውስጥ ያደገ ትውልድ ከውይይት ይልቅ አመጽ ነው የሚቀናው። በውይይት ማመን ሊፈጠር የሚችለው አሳዳጊው ኅብረተሰብ ቀድሞ በውይይት በሰላም አሳድጐት ቢሆን ነበር። የዘራነውን ነው የምናጭደውና በጥይት፣ በአርጩሜ፣ በቁንጥጫ እና አንበርክከን ያሰቃየነው ትውልድ የሰላምን የእርቅን መንገድ ስለማያውቃት ኅብረተሰቡ ያስተማረውን ትምህርት ተግባራዊ እያደረገው ይገኛል።

አሁንም ያለፈውን ያሳደገንን ትውልድ ፈጽሞ እንዳንክንን የጥበብ መምህራን ዓይናችን ላይ ድቅን ይላሉ። በግጥም የሚያስተምሩን ደራሲ ከበደ ሚካኤል፣ በተረት የሚያስተምሩን አባባ ተስፋዬ፣ በጥልቅ ድርሰት የገነቡን ሐዲስ ዓለማየሁ፣ በተውኔት ያበለፀገን ፀጋዬ ገ/መድኅን፣ የኢትዮጵያን ራዕይ በስዕል ያሳዩን እነ አፈወርቅ ተክሌ፣ ወርቁ ማሞ፣ ወርቁ ጉሹ፣ ዘሪሁን የትምጌታ፣ ገብረክርስቶስ ደስታ፣ እስክንድር በጉሲያን፣ ቲያትረኛው ወጋየሁ ንጋቱ፣ ደበበ እሸቱ ስብዕናችንን ከፍ አድርገው ባለራዕይ እንድንሆን ማርከውናል።

ትዝ ይሉናል በትጋት የሚያስተምሩን በፍቅር እራሳችንን የሚያሻሹን የማስተማር ተሰጥኦ የነበራቸው የዓመትዋን ትምህርት በክፍለ ትምህርቱ መድበው በፊሊጥ እያዋዙ ጥበብን ያስተማሩን አሁንም በሕይወታችን የሥራቸው ማኅተም ታትሞ ይገኛል።

በዚያ የትርምስ ጊዜ ግን ስንት የዓለማችን ጥበብ አመለጠን፤ እኛ በኮሚኒዝም ሽብር ስንታመስ ብዙ አገሮች ሕፃናትን በትጋት አስተምረው ለታላቅ ሥልጣኔ አብቅተዋል። ብዙ የጥበብ መንገዶች እንደትንሽ ነገር ይታዩ ነበር። ሕፃናት የጥበብ ዝንባሌ የስፖርት ዝንባሌ፣ የፈጠራ ዝንባሌ ሲያሳዩ ከመደነቅ ይልቅ እርግፍ አድርገው እንዲተውት ይደበደባሉ።

እግር ኳስ የሚጫወቱ ሕፃናት ስማቸው ዱርዬ ነው። ከርቀት አስተካክሎ ብይን በብይ የሚቀውር ዓላሚ ሕፃን ጨዋታው ከብልግና ይፈረጅበታል። በወረቀት እና ግድግዳው ላይ የሚሞነጭር ሰዓሊ ሕፃን ትምህርትህን አታጠናም ተብሎ ይገሰጻል። በዛ ስዕል ውስጥ ግን የኪነ ጥበብ፣ ኪነ ሕንፃ፣ ምህንድስናው ጂኦሜትሪ እና ፊዚክሱ ሕልቆ መሣፍርት የሌለው የጥበብ ሀሁ ዳዴ እንደነበረ የሚረዳ እጅግም ነው።

ክራርና ዋሽንት የሚከረክርና የሚነፋ ሕፃን በውስጡ ከነቅዱስ ያሬድ እና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የመዝሙር መንፈስ የተቀዳ የጥበብ ጠብታ መኖሩን ማንም የተረዳ አልነበረም። እስከዚህ ዘመን ድረስ ስዕልና ሕፃናት አይተዋወቁም ትምህርት ቤት ውስጥ የስዕል ትምህርት መስጠቱ እንደጊዜ ማጥፋት ነው የሚቆጠረው። ግን ንድፍ የጥበብ ወይም የሥራ ሁሉ መጀመሪያ ነው።



ይህ ሁሉ ጥበብ ተጠራቅሞ ነው ዛሬ ዓለምን ዓለም ያደረጋት። እነ ፒካሶን የመሳሰለ ሰዓሊ አድናቂ ባይኖረው ኖሮ ስዕሉ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ባላወጣ ነበር። የሕፃናትን ሰብዕና የሚያሳድገውም ሆነ የሚቀብረው የተደራሲው እና የአድማጩ የተመልካቹ አስተያየት ነው። እንደዚህ ባይሆን በዕድሜአችን የነበሩ የት ይደርሳሉ ያልናቸው ወጣቶች እንደጉም በነው ባልጠፉ ነበር።

ከአንደኛ ክፍል እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል አንደኛ እየወጡ ያስደነቁን ሁለት ጭንቅላት አላቸው ብለን የቆጠርናቸው ዕንቁዎቻችን የት ገቡ? ሥነ ጥበብ ት/ቤት ስንማር በነበርንበት ጊዜ እንጨቱን በረቂቅ ዲዛይን ይጠቀጥቁ የነበሩ በቴክስታይል በሐረጉ እና በረቂቅ ጌጣጌጥ ለዓይን የሚያሳሳ ተአምር ይሠሩ የነበሩ፤ በቀለም ቅብ ሸራውን በሦስት አውታረ መጠን ስዕል አርቀው ሰማይና ምድሩን ያስዳሰሱን። በግርግዳ ስዕ ል ሞዛይክ ግድግዳውን የሚከፍቱ በሐውልቱ ሥራ የረቀቁ የጥበብ ሕፃናት ለኢትዮጵያ ተፈጥረው እንደሚጨት ለምን ተበተኑ?

ከያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት የተመረቁትስ? በየዓመቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምህንድስና ኮሌጅ፣ ታላቁ አለማያ፣ ጉንደርና ጅማ የሕክምና ተቋማት ያፈሯቸው የጥበብ ሕፃናት ለምን አገሪቷን መለወጥ ተሳናቸው? ለምን ተሰደዱ? የጥበብ ሰዎች የዕውቀት ሰዎች በቀቢፀ ተስፋ መንከሰው ያሉባት አገር ኢትዮጵያ ነች።

እነዚህ ሕፃናት ቢደነቁ ቦታ ቢሰጣቸው ምን ሊለውጡ ይችላሉ? ሥነ ጥበብ ሀብት ነው። በቱሪዝም መስክ የተሠማሩ የጥበብ ሰዎች እጅግ ጥቂት በመሆናቸው በየገዳማቱ የሚጐበኙ ቱሪስቶች ሊያፈሱት ይዘውት የመጡትን ገንዘብ የተለያዩ ዕደ ጥበባትም ሆነ ኪነ ጥበባት ሊገዙበት መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት በዓመት 20 ወጣቶችን ብቻ እየተቀበለ እነርሱንም ካለ ሥራ ከሚበትናቸው በሙያቸው ቢመደቡ አንደኛ የአገራቸውን ባህል ያስተዋውቁ ነበር። ሁለተኛ በሙያቸውም ገንዘብ ማግኘት ይችላሉ። ታዲያ ጥንታዊውን ቅርሳችን አይተው ከመሄድ በስተቀር በእጃቸው ይዘውት የሚሄዱት ዕደ ጥበብ ስለሌለ ስለእነአክሱም ላሊበላ እና ጉንደር ፋሲለደስ ስለዓባይና ስለሌሎቹም ቅርሶቻችን ዓለም የሚያውቀው በጣም ጥቂት ነው።

ግብጾች በእርግጥ ከእኛ የበለጠ ታላላቅ ቅርሶች አሏቸው፤ ግን ፒራሚዶቹ እና ምስሎቹ ከቁልፍ መያዣ ጀምሮ በትናንሽ ብረቶች በሸራ ምችና በቆዳዎች ላይ ተስለው ዓለም ሲዝቃቸው ግብጽ በሥነ ጥበብ ሰዎችዋ የምታስገባው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ መገመት ይቻላል::

የተናቁት ተቋሞቻችን የጥበብ ሕፃናት የሚፈልቁባቸው ናቸው:: እዚህ አሜሪካ ውስጥ wounder of the Nile የተሰኘ ፊልም ተዘጋጅቶ በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ እየተሻማ ሲመለከት ወይ ዓባይ ወይ አገሬ ምን ዓይነት ሀብት ላይ እንደተኛሽ ብታውቂው እያልኩ ስቆጭ ነበር::

የእኛውን ዓባይ በፊልም የቀረፀው ድርጅት ሚሊየነር ሆነ ሲባል የባሕል ሚኒስትር መሥሪያ ቤታችን ወጣቶችን በፊልም ጥበብ ቢያሰለጥን ገበያው የእኛ ነበር::

ይህንን ሁሉ ገበያ ለመቋቋም በሥነ ጥበብ በዕደ ጥበብ የሠለጠኑ ወጣቶች ማፍራት ይኖርብናል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሥራ ገና አልተነካም ትኩስ ስሜት ያለው የሥራ ፍቅር የተሞላ ወጣት ይፈልጋል:: ግን ከሁሉ በፊት በጥቃቅኗ ሙያ ሳይቀር መሠልጠን ከዚህም በላይ በዕቅድ ተግባር ላይ የሚውል የሰው ጉልበትና የአእምሮ ውጤት ሁሉን ወደ ገበያ ለመለወጥ የተጉ ሙያተኞች ርብርብ ያስፈልገናል::

ርዕሳችን ከሕፃናት ጋር እንታረቅ ነውና:: በአገራችን ያሉ ችግሮች ዘርፈ ሰፊ ሆነው ይታዩ እንጂ በጥቂት መፍትሔዎች ግን ሊጠቃለሉ ሊቃለሉም ይችላሉ::

ከሁሉ በላይ የሥራ አጡ ወጣት ቁጥር አስደንጋጭ ከሆነ ሰንብቷል:: ይህ ወጣት ደግሞ በቂ የሙያ ብቃት የለውም:: ስለዚህ በአደንዛዥ ዕጽ በጫትና ሲጋራ ሱስ ተበክሎ ከጠዋት እስከ ማታ (ዕጣን ወይም ሰንደል) የደመነበት ቤት ውስጥ ዙርባ ጫት እየቀነጠሰ የወሬውን ተራራ ሲገፋ የሚውለው የኢትዮጵያ ወጣት በአግባቡ ቢማር ኖሮ የብሩህ ጭንቅላት ባለቤት መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም::



እጅግ የሚደንቀው በአደንዛዥ ዕፅነቱ የሚታወቀው ጫት ካለምንም ከልካይ ወጣቱን ሲያደነዝዝ በተለይ በካርቶን እየታሸገ እንደጥሩ ምርት በየክፍለ አገሩ ሲጓጓዝ በማየታችን ግራ ተጋብተናል:: ለመሆኑ ጫት እንዴ ሀሺሽ መሆኑ ግልጽ ሳይሆን ቀርቶ ነው ወይ የወጣቱን ጭንቅላት ሲያበላሽ እያየን እንዳላየ ዝም የምንለው::

ሚኒያፖሊስ ውስጥ የሚታተመው እስታር ትሪዩቡን ተብሎ የሚጠራው ጋዜጣ ላይ መጠኑ ተጠቅሶ አደገኛ ከሆኑ ሀሺሽ ውስጥ ጫትም ተመድቦ በአሜሪካ ውስጥ ይዞ የሚገኝ ይቀጣል:: ታዲያ ኢትዮጵያ ለምን ለወጣቶቿ እስባ ከአደገኛ ዕፅ መታደግ አቃታት ወይስ የኢኮኖሚያችን የጀርባ አጥንት ነው ብለን እንለፈው:: ለውን ያክል ክቡር ፍጡር አጥፍቶ አሳብዶ ኢኮኖሚው ቢገነባ ምን ዋጋ አለው?

ይህንን ማንነታችንን ከዚህ ከአሁኑ ዓለም ሥልጣኔ ጋር እያነጻጸርን እስቲ እንየው:: ለምሳሌ ያህል እንደእኛው በሕዝብ ብዛት የተጥለቀለቁትን ሕንድንና ቻይናን እንመልከት:: መማር ያለብን ከጉበዞቹ ነው፤ ምሳሌ ማድረግ ያለብን በጥንካሬ የሚሠሩትን ነው:: ደጋግመን እንደጠቀስነው ሕንድ በሕዝብ ብዛት ከዓለም ሁለተኛውን ቦታ ይዛለች:: ቻይና ግን የዓለም ቁንጮ ስለሆነች ወደ 1.3 ቢሊዮን የሚጠጋው ሕዝቧ የቻይናን ከተሞች መተላለፊያ አሳጥቷል::

ሕንድ በተፈጥሮ ሀብት ከእኛ ትበልጣለች፤ በቱሪዝምም ከዓለም የበላይነቱን የሚነጥቃት የለም:: አንጻራዊ ሰላም ያላት ሀገር ናት፤ በድህነት ያጠ የነጠ ወይም በሀብት የናጠጠ በኅብረት የሚኖሩባት በባዕድ አምልኮ የታወቀች አገር ናት:: ባሕሉ እጅግ የተዥጐረጐረ ብዙ ጉሳ ይኖሩባታል፤ በአብዛኛው ሒንዱ የተባለ ሃይማኖት የሚያምኑ በቀላሉ የማይገመቱ እስላሞች በጣም ጥቂት ክርስቲያኖች ያሉባት አገር ነች::

ሕንድ ነፃነትዋን ካገኘች በኋላ የመጀመሪያ ሥራ ያደረገችው የመዋዕለ ነዋይ ጠበብትዋን የተሻለ የዕድገት ደረጃ ላይ ወደነበረችው ሶቪየት ኅብረት ወደ ሞስኮ መላክ ነበር:: በዚህም ምክንያት በኮሚኒስታዊው አስተዳደር የተመሰጡት የሕንድ ወጣቶች መሪያቸው

(Nehru) ኔሩን ይህንን ርዕዮተ ዓለም እንዲከተል ያማከሩትና የሶቪየትን መርሆ ሲከተሉ ይቆያሉ። ምንም በድህነት ቢማቅቁም እንኳን እምብዛም ርዕዮተ ዓለሙን ሳያጋንኑ የመዋዕለ ነዋዩን መስክ ማጠናከር ይጀምራሉ። ግን ኑሮ ከቦታው ፈቀቅ ማለት ስለአልቻለ በ1991 እ.ኤ.አ. ሕንድ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ባጠቃት ወቅት ማሀሙሀን ሲን የተባለው የኖቤል ተሸላሚ የገንዘብ ሚኒስትር (በዚህ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነዋል) ሕንድ በነጻ ገበያ መመራት እንዳለባት ጥናት አቅርበዋል። ይህ ማለት የነብርን ፀጉር እንደመላጨት አደገኛ ነበር ይላሉ፤ ታዛቢዎች በኮሚኒዝሙ ሥርዓተ ማኅበር ዕድገቷ ሦስት ነጥብ ብቻ የነበረው ሕንድ በነጻ ገበያ መሠረት መሥራት ከጀመረች ከሦስት ዓመት በኋላ 7 በመቶ በማደግ መፈንጠር ጀመረች።

በዚህ ዕድገት ውስጥ ወሳኝ ሚና የተጫወቱት የሕንድ ወጣት ምሁራን ናቸው። በተዘጋው ኮሚኒስታዊ የምጣኔ ሀብት የሕንድ የውጭ ምንዛሪ ገቢ አንድ ቢሊዮን ነበር። ከነጻ ገበያው በኋላ 118 ቢሊዮን ደርሶ የተገኘው እንደማዕበል በኃይል ለሥራ በተነሳው የሕንድ ወጣት ምክንያት ነው።

እንዲህ ዓይነት ብቁ ምሁር ወጣት የተገኘው እንዴት ነው? «በሕንድ ሕዝብ ውስጥ ትምህርትን ማበረታታት የተለመደ ነው። አንድ ወጣት በ20ዎቹ ዓመታት ውስጥ በቂ የዕውቀት ደረጃ ላይ ይደርስ ዘንድ ቤተሰብ መንግሥትና ቀጣሪ ድርጅቶች ያበረታታሉ፤ ጫና ያደርጋሉ»

ስለዚህ ሕንዳውያን በዚህ ዘመን ቻይናን አስንቀው ተገኝተዋል የካቲት 1999 ዓ.ም. በወጣው FP (Foreign Plociy) በተባለው መጽሔት (India outsmarts China) በሚል ርዕስ የሕንድ ግሥጋሴ በሰፊው ተተንትኖ ይገኛል።

እንደሚታወቀው ቻይና ምንም የሕዝቧ ብዛት ከሀብቷ ብዛት ጋር ሲነጻጸር ከሀብታሞቹ አገራት አትወዳደር እንጂ የመዋዕለ ንዋይ ግሥጋሴ እያደረገች ያለችውን ቻይናን ሕንድ እንዴት ልታስንቅ ቻለች? ቢባል መልሱ ወጣቶችን ተግቶ በማስተማር ነው።



በቻይና እና በሕንድ መካከል ያለው የመዋዕለ ነዋይ እመርታ የዓለምን የንግድ ጠባይ ይለውጠው ይሆናል። በ2050 እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር እንደሚገመተው የዓለምን የአገር ውስጥ ፍጆታ ግማሽ ሁለቱ አገሮች ብቻ ይሸፍናሉ። በዚህ ጊዜ እንኳን ስድስት በመቶውን ተቆጣጥረውታል ማለት ነው። ግን የየትኛው አገር ዘዴ ነው የተሻለ ውጤት የሚያስገኘው የቻይና ፋብሪካዎች ወይስ የሕንድ የመዋዕለ ነዋይ ጠበብት ባለሙያዎች ገበያ። ከቻይና ፈጣን ግሥጋሴ በቀላሉ ለመድረስ የሕንድ የአእምሮ ኃይል ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ ተገኝቷል።

ይህ የአእምሮ ኃይል ደግሞ በአዲሱ የሕንድ ወጣቶች ላይ ተስፋ ያደረገ ነው። ስለዚህ ሕንዳውያን ልጆቻቸውን ካለመታከት በማስጠናት ፍፁም የሆነ ሥራ በመሥራታቸው ዛሬ የዓለምን ሥራ እያግበሰበሱ እየወሰዱ ይገኛሉ እንዴት?

በዚህ ዘመን በምዕራቡ ዓለም የሰው ጉልበት ዋጋ እጅግ ውድ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካ ለአንድ ሰው በሰዓት በአማካይ 5 ዶላር ሊከፈለው ይገባል። ይህ ለተራው ሁሉ ሠራተኛ ነው። ለመሐንዲሶችና ለሌሎችም ሞያተኞች ግን በዓመት ከ40-50 ሺህ ዶላር በታች አይከፈልም። ዶክተሮች በአማካኝ እስከ 150 ሺህ ብር ይከፈላቸዋል። ታዲያ አንድ አሜሪካዊ ባለሀብት ይህንን ሁሉ ከፍሎ በውድ ከሚያሠራ ሥራውን ወደ ሕንድ ወስዶ 300 ዶላር በወር እየከፈለ አንድን መሐንዲስ ሊያሠራው ስለሚችል እኩል የዕውቀት የብቃት ደረጃ ያለውን ሕንዳዊ ፍለጋ ባለሀብት ሁሉ ወደ እስያ መጉረፍ ጀምሯል። ስለዚህ አሜሪካ ውስጥ ያሉ የታክስ ክፍያን ጨምሮ የአበዳሪ ድርጅቶች፣ የስልክ ሥራ፣ የምህንድስና ንድፎች እና የመሳሰሉት ሥራዎች ሁሉ ወደ ሕንድ ሄደዋል። በዘመናዊው ኮምፒውተር እየተረዱ ዓለም አቀፍ ምሁራንን የሚፈልጉ ሥራዎችን ሕንዳውያን እያቀላጠፉት ይገኛሉ። ስለዚህ ደሞዛቸውም ከ300 ዶላር ወደ 500 ዶላር አድጓል። ይህ የአእምሮ ንግድ ነው ወደ 118 ቢሊዮን ዶላር ሕንድን ያሳፈሳት። በዚህ ዘመን የሕንድ ወጣቶች እንደጨው ተፈላጊ የሆኑበት ምክንያት ዕቅድ ባለው አስተዳደግ ከሕፃንነት ጀምሮ በተገነባ ልምምድ ስለተቀረፁ ነው።

የሚባክን ጊዜ ፈጽሞ የለም። ሕፃናት ከምን ተነሥተው ምን ላይ መድረስ እንዳለባቸው በሚገባ ዕቅድ ወጥቷል። በሂሣብ የበለፀገ ሕሊና ይኖራቸው ዘንድ በከፍተኛ ክትትል ሕፃናቱን ይስሏቸዋል። ስለዚህ ሳይደናገሩ በየደረጃው ለትልቁ ደረጃ መድረስ ይችላሉ።

ወጣቱ ኅብረተሰብ እንደ ወራጅ ውኃ ቦይ ብቻ ነው የሚፈልገው በመልካም ትልሞች ካፈሰስነው አገር ያሳምራል። በተጣመመ ቦይ ከሰደድነው አገር ያጠፋል። ከሕፃንነቱ ጀምሮ በዕቅድ የተመራ ሕይወት በወጣትነት በዕውቀት ከተገነባ በጉልምስና ፍሬው ጣፋጭ ሆኖ ይገኛል። በአረጋዊነት ሳይቀር ለሀገር ጠቃሚ ሆኖ ይገኛል።

ወደ እኛ ኅብረተሰብ ዘወር ስንል ከትውልዱ ብዛት፣ ከትምህርት ጥራቱ ማሽቆልቆል፣ ከፀጥታው መታወክ ጀምሮ የተረጋጋ ኅብረተሰብ ሊሆን የሚችል ወጣት መቅረጽ እንዲሳነን አድርጐናል። የትምህርት ተቋማት የሚያስመርቋቸው ወጣቶች ከነሞቀ የሥራ መንፈሳቸው በአሽጥርና በዘመድ የሚናቆር ሽባ የሆነ ቢሮ ውስጥ ስለሚመደቡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከነፈጠራ ውጤታቸው በዛገው የአስተዳደር መንኩራኩር ውስጥ ይፈጫሉ።

ከሌላው ዓለም መማር የሚኖርብን ዐበይት ነገር የትውልዱ ብዛት በአግባቡ ከተመራ ልማቱን ያፋጥናል እንጂ የሚያመጣው ጥፋት የለም። እርግጥ ነው የሕዝባችን ብዛት ከጣሪያ በላይ መውጣቱ ከፍተኛ አደጋ አለው። ግን የሆነው ሆኗልና እንዴት እናስተናግደው ወደሚለው የመፍትሔ ሐሳብ እንጂ ለምን ሆነ? ብለን መቆጨት አይጠቅመንም።

ወላጆች ልጆቻችሁን ካላስተማራችሁ በዚህ ክፉ ዓለም ውስጥ የሚደናበሩ አሳዛኞች ስለምታደርጓቸው ለጨዋታው ለወሬው ጊዜ ሳትሰጡ ልጆቻችሁን ጠንክራችሁ በማስተማር ከሕፃናት ጋር ታረቁ።

መንግሥት ካለው መጠነ ሰፊ ችግር ዋነኛው እና ሌሎቹን ችግሮች ልናስወግድበት መንገድ የሚሰጠን ወጣቶችን ማስተማር ነውና የማይማር ሕፃን አይኑር የሚል መርህ በማዘጋጀት ከፍተኛውን በጀት ለትምህርት ይመድብልን ዘንድ ጥሪ እያደረግን ከሕፃናት ጋር



መንግሥታችን ይታረቅ እንላለን። እርግጥ ነው ለትምህርት ዕድገት መንግሥት ከሚመድበው በጀት በተጓዳኝ ሌሎች የበለጠ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መኖራቸው እሙን ነው። ለምሳሌ ጤናና የምግብ ዋስትናን የመሳሰሉ ማለት ነው። ለዘለቄታዊው መፍትሔ ግን የተማረ ኃይል ማፍራቱ ወሳኝ ስለሆነ ሕፃናትን በማሠልጠንና በማስተማር መስክ ሁሉም ሊረባረብ ይገባል። መንግሥትም የኅብረተሰቡ ድጋፍ ያስፈልገዋል።

እንዲህ ሲባል የተሠሩትን ሁሉ ጨፍልቀን እንዳልተሠሩ ቆጥረን ሳይሆን ስለተሠራው እያመሰገንን፤ ግን ከዓለማችን ጋር በሚደረገው እሽቅድምድም እጅግ ወደኋላ መቅረታችንን እያስተዋልን ጥፋቱ የጋራችን በመሆኑ ሁላችንም ተጋግዘን የነገውን ትውልድ ሕይወት ብሩህ በማድረግ ከሕፃናት ጋር እንታረቅ።

ምሁራን በጠባብዋ ዕድል ተጠቅማችሁ ሀገራችሁን በትምህርት ለማበልፀግ በመፍገምገማችሁ ዘወትር ከኢትዮጵያውያን ሕሊና አትረሱም ምንም በየአደባባዩ ላይ ሐውልት ባይሠራላችሁም በትውልዱ ልብ ውስጥ የሥራችሁ ታላቅ ምስል ተስሎ ይገኛል። አንድን አገር ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማምጣት የብዙዎች ሕይወት ሻማ መሆን ይኖርበታል። አዲሱን ኅብረተሰብ ወደተሻለ ዕድገት ለማሸጋገር የምሁራን የጥናት መጽሐፍ ወሳኝ ነው።

ዛሬ ኢትዮጵያ ብዙ መሐንዲስ ጸሐፊዎችን ትፈልጋለች ለምን? ምህንድስና በቋንቋ መጋረጃ ተሸፍኖ የማይገለጥ ዕውቀት የመሠለውን ሕዝባችንን ገበሬው እንኳን በራሱ ቋንቋ ቢጻፍለት ጥሩ መሐንዲስ መሆን እንደሚችል ይረዳ ዘንድ። በየገጠሩ በሕይወት ገጠመኝ የሚቀምማቸው፣ የሚገጥምና የሚፈታቸው፣ የሚያፈስና የሚያቀዘቅዛቸው ነገሮች ሁሉ የሳይንስ ቀመር እንዳላቸው ይረዳ ዘንድ ሳይንቲስቶቹ መጻሕፍት ሊጽፉ ወይም ከሌላው ቋንቋ ሊተረጉሙ ይገባል።

የአየሩ ጠባይ በዚህ ዘመን በሚገባ ይተነበያል። ዝናብ ይመጣል ወይስ አይመጣም? ነፋስ አለ ወይስ አይነፍስም? የፀሐይ ዋእይ መጠን ምን ያህል ነው? ይህ ሁሉ ዘንድሮ በሳይንስ ተሰፍሯል ገበሬው በጥቂቱ

የዚህ ዕውቀት መሠረት ቢሰጠው ከልምድ ካዳበረው ጋር ተጨምሮ እንዴት በጠቀመው:: እዚህ ላይ ስለሜትሮሎጂ አንድ የሚነገር ቀልድ ለበስ ቁም ነገር ጠቅሰን እንለፍ::

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የአየር ኃይሉን እና አየር መንገዱን ይረዳ ዘንድ የሜትሮሎጂ (የአየር ጠባይ ተመራማሪ) መምሪያ ያቋቁሙና ተመርቆ ይከፈታል:: በዚህ ኩራት የተሰማቸው ንጉሡ ዘወትር ከመምሪያው እየደወሉ የነገው አየር እንዴት ነው? ማለት ልምድ አድርገው ነበር ይባላል:: በቅጡ ያልዳበረው መምሪያ የተቻለውን መረጃ መስጠት ይጀምራል::

ከዕለታት አንድ ቀን እንደተለመደው ይደውሉና «ወደ ደብረ ዘይት መሄድ እፈልጋለሁ እና አየሩ እንዴት ነው?» ብለው ጠየቁ:: የአየር ጠባይ ተመራማሪው እርግጠኛ ባልሆንም ባለን ውስን መሣሪያ መሠረት ነገ ፀሐይ ሳይሆን አይቀርም ይላቸዋል ስለዚህ በጠዋት ተነስተው ጉዞ በመኪና ይጀምራሉ::

ነገር ግን ጉዞው ከተጀመረ በኋላ ደመናው ይከብዳል፤ አህዮችም የመንገዱን ጠርዝ ተከትለው ጆሯቸውን አቁመው ይሮጣሉ:: ከንጉሡ ጋር አብረው እየተጓዙ ያሉ አረጋዊ ሰው «አይ ግርማዊ ሆይ ዝናቡ ሳያውክን አይቀርም» ይሏቸዋል:: ንጉሡም በቀልድ ዘዬ ፈገግ ብለው «በምን አወቅህ?» ይሏቸዋል:: አዛውንቱም «ያዩዋቸዋል አህዮቹ ጆሮቸውን አቁመው ሲሮጡ ይህ የዝናብ መምጣት ምልክት ነው» ይላሉ:: ንጉሡ ይስቁና «አይጨነቁ እኛ የአየር ጠባይ ተመራማሪውን ደውለን ጠይቀናል ደመናው ይገፋል ፀሐይም ይሆናል» ይላሉ:: ነገር ግን ጥቂት እንደተጓዙ ድብልቅልቅ ያለ ዝናብ ይዘንብና መኪኖቹ ጥግ ቆመው ዝናቡን ለማሳለፍ ይገደዳሉ:: ንጉሡም በሐዘን «አዬ ከእኛ ሜትሮሎጂስ ይልቅ የገበሬዎቹ አህዮች የአየሩን ጠባይ ይበልጥ ይተነብያሉ» አሉ ይባላል:: ይህ ማለት ግን የመሥሪያ ቤቱን ትንበያ ስህተት ነው ማለት ሳይሆን ገበሬው በተፈጥሮ ታግዞ አየሩን እና የሰብሉን አበቃቀል የመረዳት የዳበረ ልምድ ያለው ጠቢብ መሆኑን ተረድተን ምሁራን በዚህ ዕውቀት ላይ ዘመናዊውን ጥበብ ቢያክሉበት ለማለት ያህል ነው::



ርዕሳችን ከሕፃናት ጋር መታረቅ ነው:: ምሁራኑ የሚጠበቅባቸው መጻሕፍትን መተርጎም ሲሆን፤ ባለሀብቶች ደግሞ ማሳተም መሆን አለበት:: ስለዚህ ምሁራን ዕውቀታቸውን በመናገር በመጽሐፍ ለትውልዱ ሊያስተላልፉ ይገባል፤ በዚህም ከወጣቱ ጋር መታረቅ ይቻላል::

የዚህ ዘመን የኢንተርኔት አገልግሎት ተጨማሪ ግልጋሎት ስለሚሰጥ በዚህም መጠቀም ያስፈልጋል:: ዛሬ ዕውቀት እንደድሮው ብርቅና ድንቅ አይደለም፤ ድሮ በአንድ በሬ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ይለወጥ ነበር:: በብራና ለመጻፍም ብዙ ፍየሎች ያልቁ ነበር፤ ዛሬ ግን በወረቀትም መጻፍ አያስፈልግ ለእያንዳንዱ ዕውቀት ጥልቅ ትንተና የሚሰጡ ድረ ገጾች ሞልተዋል:: የተቀረጹ ፕሮግራሞች ስለረቂቅ ንድፍ ሌላውንም የተግባር ትምህርት በቀላሉ ያስተምራሉ::

ሕፃናትን የቤት ሥራ ለማሠራት ለማስጠናት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ማስጠኛ በየድህረ ገጹ አለ:: ይህ ድንገት ለገጠሪቱ ኢትዮጵያም ሆነ በአብዛኛው ለከተሞች ሩቅ ሊመስል ይችላል:: ግን በየአካባቢው ያሉ ትምህርት ቤቶች በዚህ ቅርጽ ቢደራጁ በቀላሉ ዕውቀትን ለማሠራጨት ይቻላል:: እውነቱን ለመናገር በ20ኛው ክፍለ ዘመንም ኢትዮጵያ በሯን ለጥበብ ዘግታለች:: ልጆችዋ ገና በላንባ መብራት ነው የሚያጠኑት:: በቀላሉ ሊጠኑ የሚችሉ ነገሮች ለእኛ ተማሪዎች ታላቅ ፈተና ናቸው::

ለምን? በቃል የሚነገሩ ነገሮች ሁሉ በተግባር ስለማይታዩ ለተማሪው እንቆቅልሽ ስለሆኑ ነው:: ለምሳሌ ኬሚስትሪ ስንማር ንጥረ ነገሮች ተደባልቀው ሌላ ንጥረ ነገር ይፈጥራሉ ከሚለው ቃንቋ ውጭ እንዴት እንደሚሆን ስለማናይ ትምህርቱ አይገባንም፤ አልገባንም:: ግን መምህራኖቻችን ቢያስቡበት ኖሮ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን አስፈቅደው ቤተ ሙከራውን ሊያስጎበኙን ሊያሳዩን ይገባ ነበር:: ሌላውንም እንደዚህ ነው::

ለሳይንስ ምርምር የባዮሎጂ መምህር ተፈጥሮውን እንድንመ ረምር ወደ ጫካ ወደ ወንዝ አይወስደንም። ስለዚህ የባዮሎጂ ትምህርትና እንቁራሪቶች ያላቸውን ዝምድና አናውቅም። ትምህርት ሁሉ ለፈተና የምንማር ይመስለናል። እንሸመድድና እናልፋለን በቃ ደብተሩ ከዛ በኋላ ጠላታችን ነው። ብዙ ተማሪዎችን በፈተና ያሰቃየ ወይም የጣለ መምህር ጀግና። ብዙ ተማሪዎችን ያሳለፈ ደግሞ ሰነፍ ይባል ነበር።

የሃይማኖት ተቋማትስ? ሕፃናትን በማሳደግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ልትመሰገን ይገባታል ፊደል ቀርጻ፣ ቀለም ፈልስፋ፣ በብራና እና በድንጋይ ላይ ሳይቀር እየጻፈች ጥበብ ለትውልድ ያስተላለፈች በመሆንዋ በውስጧ ተወልደው የጥበብ መቅረዝ ለሆኑት ልጆችዋ ለነቅዱስ ያሬድ፣ ለእነ አባ ጊዮርጊስ እና ለእነ አቡነ ተ ክለሃይማኖት ምሥጋና ይግባቸውና በሕሊና ዕውቀት ድሆች እንዳንሆን አድርገውናል።

እጅግ የሚገርመው እነዚህ ሊቃውንት መጻሕፍት ጽፈው ነው ያለፉት ቅዱስ ያሬድ ድጓውን፣ ጾመ ድጓውን፣ መዋስዕቱን ተንትኖ ለትውልድ ይተርፍ ዘንድ የዜማ ባህል አስቀርቶልናል። አባ ጊዮርጊስ ኖኅተ ብርሃን (ኖኅተ ፀሐይ)፣ አርጋኖን፣ ዕንዚራ ስብሐትን፣ ሕይወተ ማርያምን፣ ተአምኖተ ቅዱሳንን፣ መስተብቁዕ ዘማርያምን፣ መስተብቁዕ መስቀልን፣ መጽሐፈ ምሥጢርን ... ወዘተ አሥራ አንድ መጻሕፍትን መዝገበ ቃላት፤ እነ ሊቀ መዘምራን ላዕከ ማርያም ወ/ኢየሱስ ግብረ ሕማማቱን በአማርኛ ሲተረጉሙ በሚቀጥለው ትውልድ ቤተ ክርስቲያንና ሊቃውንቷ ታርቀው ማለፋቸውን ልንረዳ ይገባል።

በዚህ ዘመን ደግሞ በመንፈሳዊው ዓለም ጐን ለጐን ሰው ሊኖርበት የተገባውን የሥጋ ጥበብ በመመራመር በመጽሐፍ በማስቀመጥ ወጣቱን ኅብረተሰብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ይመራመር ዘንድ ማነቃቃት ያስፈልጋል። ትውልዱን ከዓለም ጋር በእኩል ለማስለፍ ለምርምር የሚጋብዝና ወደ ተግባር ለመለወጥ የተዘጋጀ ሁኔታ ያስፈልጋል።

ትምህርት ትውልድን ያንጻል፤ ለሥራ ያነሳሳል፤ ሰው ያደርጋል፤ ስለዚህ ከሕፃናት እና ከወጣቶች ጋር እንታረቅ።



# ምዕራፍ ሰባት

## ከሕግ ጋር መታረቅ

ምሥጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፤
በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ፤
በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፤
ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል፤
እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች፤
ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፤
ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤
የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።*

ይህ የመዝሙረ ዳዊት ጥቅስ ስለሕግ ሰፊ ትንታኔ ስለሚሰጥ ከሕግ ጋር መታረቅ የሚለውን ርዕስ በዚህ ጀመርነው።

ክፉዎችን በፍርድ የምትዳኛቸው ሕግ ስለሆነች ሰላምን የምታ ረጋግጠው ሕግ ስለሆነች ዓለም ከእውነት ሕግ ጋር እንዲታረቅ መዝሙ ረኛው ዳዊት በቅኔው ሌሊትና ቀን የሕግ ነገር እንደሚያሳስበው ገለፀ።

እርሱ ብፁዕ ነው የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያሰላስል። ከዚህ አትለፍ ከዚህ አትትረፍ የምትለዋን ዓለምን በጽድቅ የምትመራዋን ሕግ የሚያስብ ብፁዕ ነው ሲል ይህ ዓይነቱ ሰው ከሕግ ጋር በመታረቁ ነው ምሥጉን ክቡር ያሰኘው።

ሕግ በሰዎች መካከል የምትለይ የጽድቅ መስመር ነች። መዝመ ረኛው ዳዊት እንደውም ሕግን ተላልፈው ግፍን ኃጢያትን የሚሠሩትን «ከማኅፀን ጀምረው የተለዩ» ይላቸዋል። እጆቻቸው ግፍን ስለተሞሉ ከሆድም ጀምረው ሳቱ፤ ቁጣቸው እንደ እባብ መርዝ ነው፤ ጆሯቸው እንደ አውሬ የተደፈነ ነው ይላቸዋል። ይህ ሁሉ እርግማን ከሕግ ጋር ለተጣሉ ሰዎች ነው።

* መዝ. 1፥1–3

ለሳይንስ ምርምር የባዮሎጂ መምህር ተፈጥሮውን እንድንመረምር ወደ ጫካ ወደ ወንዝ አይወስደንም። ስለዚህ የባዮሎጂ ትምህርትና እንቁራሪቶች ያላቸውን ዝምድና አናውቅም። ትምህርት ሁሉ ለፈተና የምንማር ይመስለናል። እንሽመድድና እናልፋለን በቃ ደብተሩ ከዛ በኋላ ጠላታችን ነው። ብዙ ተማሪዎችን በፈተና ያስቃየ ወይም የጣለ መምህር ጀግና። ብዙ ተማሪዎችን ያሳለፈ ደግሞ ለነፍ ይባል ነበር።

የሃይማኖት ተቋማትስ? ሕፃናትን በማሳደግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ልትመሰገን ይገባታል ፊደል ቀርጻ፣ ቀለም ፈልስፋ፣ በብራና እና በድንጋይ ላይ ሳይቀር እየጻፈች ጥበብ ለትውልድ ያስተላለፈች በመሆንዋ በውስጧ ተወልደው የጥበብ መቅረዝ ለሆኑት ልጆችዋ ለነቅዱስ ያሬድ፣ ለእነ አባ ጊዮርጊስ እና ለእነ አቡነ ተ ክለሃይማኖት ምሥጋና ይግባቸውና በሕሊና ዕውቀት ድሆች እንዳንሆን አድርገውናል።

እጅግ የሚገርመው እነዚህ ሊቃውንት መጻሕፍት ጽፈው ነው ያለፉት ቅዱስ ያሬድ ድጓውን፣ ጾመ ድጓውን፣ መዋስዕቱን ተንትኖ ለትውልድ ይተርፍ ዘንድ የዜማ ባህል አስቀርቶልናል። አባ ጊዮርጊስ ኖኅተ ብርሃን (ኖኅተ ፀሐይ)፣ አርጋኖን፣ ዕንዚራ ስብሐትን፣ ሕይወተ ማርያምን፣ ተአምኖተ ቅዱሳንን፣ መስተብቁዕ ዘማርያምን፣ መስተብቁዕ መስቀልን፣ መጽሐፈ ምሥጢርን ... ወዘተ አሥራ አንድ መጻሕፍትን መዝገበ ቃላት፤ እነ ሊቀ መዘምራን ላዕከ ማርያም ወ/ኢየሱስ ግብረ ሕማማቱን በአማርኛ ሲተረጉሙ በሚቀጥለው ትውልድ ቤተ ክርስቲያንና ሊቃውንቷ ታርቀው ማለፋቸውን ልንረዳ ይገባል።

በዚህ ዘመን ደግሞ በመንፈሳዊው ዓለም ጐን ለጐን ሰው ሊኖርበት የተገባውን የሥጋ ጥበብ በመመራመር በመጽሐፍ በማስቀመጥ ወጣቱን ኅብረተሰብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ይመራመር ዘንድ ማነቃቃት ያስፈልጋል። ትውልዱን ከዓለም ጋር በእኩል ለማስለፍ ለምርምር የሚጋብዝና ወደ ተግባር ለመለወጥ የተዘጋጀ ሁኔታ ያስፈልጋል።

ትምህርት ትውልድን ያንጻል፤ ለሥራ ያነሳሳል፤ ሰው ያደርጋል፤ ስለዚህ ከሕፃናት እና ከወጣቶች ጋር እንታረቅ።



# ምዕራፍ ሰባት

## ከሕግ ጋር መታረቅ

ምሥጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፤
በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ፤
በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፤
ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል፤
እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች፤
ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፤
ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤
የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።*

ይህ የመዝሙረ ዳዊት ጥቅስ ስለሕግ ሰፊ ትንታኔ ስለሚሰጥ ከሕግ ጋር መታረቅ የሚለውን ርዕስ በዚህ ጀመርነው።

ክፉዎችን በፍርድ የምትዳኛቸው ሕግ ስለሆነች ሰላምን የምታረጋግጠው ሕግ ስለሆነች ዓለም ከእውነት ሕግ ጋር እንዲታረቅ መዝሙረኛው ዳዊት በቅኔው ሌሊትና ቀን የሕግ ነገር እንደሚያሳስበው ገለፀ።

እርሱ ብፁዕ ነው የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያሰላስል። ከዚህ አትለፍ ከዚህ አትትረፍ የምትለዋን ዓለምን በጽድቅ የምትመራዋን ሕግ የሚያስብ ብፁዕ ነው ሲል ይህ ዓይነቱ ሰው ከሕግ ጋር በመታረቁ ነው ምሥጉን ክቡር ያሰኘው።

ሕግ በሰዎች መካከል የምትለይ የጽድቅ መስመር ነች። መዝመረኛው ዳዊት እንደውም ሕግን ተላልፈው ግፍን ኃጢያትን የሚሠሩትን «ከማኅፀን ጀምረው የተለዩ» ይላቸዋል። እጆቻቸው ግፍን ስለተሞሉ ከሆድም ጀምረው ሳቱ፤ ቁጣቸው እንደ እባብ መርዝ ነው፤ ጆሯቸው እንደ አውሬ የተደፈነ ነው ይላቸዋል። ይህ ሁሉ እርግማን ከሕግ ጋር ለተጣሉ ሰዎች ነው።

---

መዝ. 1፥1–3

ስለዚህ ሕግ ከጥንት ጀምሮ ሰዎችን ያስጨነቀ፣ ያፈላሰፈ፣ ሕይወታቸውን ያቃና ሲሆን፤ ሕግ ከሌለ ደግሞ ልቅነት፣ አውሬነት ዓለምን ሲያስቸግራት በየታሪኩ ምዕራፍ እናያለን:: ከሕግ ጋር የታረቀ ግለሰብ፣ ማኅበረ ሰብና እና መንግሥት ሰላማቸውና ብልጽግናቸው የተረጋገጠ ነው::

## ኢትዮጵያና ሕግ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአስተዳደር ጸጋ ከታደሉት አገሮች አንደኛዋ ነበረች:: ክፉም ይሁን ደግ መሪ የሚሾምባት ሕዝቡም «አሳምረህ ግዛኝ ብቻ» ብሎ በጩኸኙ ሲያለቅስ፣ ደጉን እምዬ ሲል ለሚወጣውም ሕግ ለመገዛት ሲያዘነብል የኖረ ሕዝብ ነው::

መቼም ይህ አጠቃላይ የዓለማችን ጉዞ በመሆኑ እኛም ከተጨባጩ እውነታ ውጭ መሆን አንችልምና እርቆ አሳቢ ወይም የቅርቡን የሚያስብ ራዕይ ያለው ወይም ዕውር ድንብሩን የሚመራ መሪ ሲፈራረቅብን ኖሯል:: ሁለቱም በሰው ልጅ ታሪክ የሚፈራረቁ በመሆናቸው::

ከቤተሰብ አስተዳደር ጀምሮ የቀበሌው የወረዳው የአውራጃውና የክፍለ ሀገሩ አስተዳደር በበሰሉ ወይ ባልበሰሉ በእውነተኞች ወይም በስግብግቦች ሲተዳደር ቆይቷል::

የሕዝብ ሥልጣንና የመንግሥት ሥልጣን ተመጣጥኖ መንግሥትም ግፍ ሳያበዛ ሕዝቡም ሁካታ ሳያበዛ በሚዛን ሲኖር የሚችለው ግን ሕግ ሲኖር ነው:: ሕግ ከአንድ ግለሰብ ይጀምራል፤ በሀገር ደረጃ ይሰፋል፤ በአህጉር ደረጃ ከዚያም ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች አገራትን በሥርዓት እንዲኖሩ ያደርጓቸዋል::

ስለዚህ ኢትዮጵያም ትደኸይም በመሐይምነት ጨለማም ትውደቅ በሕግ የምትተዳደር አገር ነበረች፤ አሁንም ነች:: በታሪክም እንደምንረዳው ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና ትኖር እንደነበረ ይልቁንም የኖህ የልጅ ልጅ (ሣባ) እና አቢስ (ሰብታ) እግዚአብሔርን ያመልኩ ስለነበረ በሕገ እግዚአብሔር የምትመራ አገር እንደነበረች እንረዳለን::



ለዚህም ይመስላል የጥንት ግብጻዊያን ኢትዮጵያን ቶ-ኔቴር ብለው በመዝሙራቸው ቃል ሀገረ እግዚአብሔር ወይም በሕገ እግዚአብሔር የምትመራ ምድር ያሏት:: (አባ ጋስፓሪኒ ጉ-ማ የኢትዮጵያ ታሪክ ብለው በጻፉት እንዳሠፈሩት ገጽ 5)

ኢትዮጵያዊው አርበኛ በዐረብኛ ነሐስ የተባለው በአማርኛ አንበሣ ማለት ነው:: ሕግ ባይኖረው ኖሮ በዘመኑ ግብጾች ታላቅ ባላሉት ነበር:: በወርቃማው የዴሞክራሲ ሕግ የሚተዳደሩት ግሪኮች በታላቁ የሥነ ጽሑፍ ሰው በሆሜር አማካኝነት «በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሕዝቦች ኃያላን ውብና ክቡራን» ናቸው ሲሉ፤ በፍልስፍናቸው ሁሉን የሚንቁ ለቢባኖቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ዓይነት ወርቃማ ሕግ አይተው ይሆን ብለን እንድንጠራጠር ያደርገናል:: ሆሜር ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ490 ዓመተ ዓለም ቀደም ብሎ የነበረው ሄሮዶቶስ ይህንኑ ሐሳብ ደግፎ ጽፏል::

የታሪክ ሰዎች አሁንም እንደዘገቡት ከግብጽ ሥልጣኔ ጋር መገዳደር የቻሉ ፒአንኪን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ነገሥታት ግብጽን በጦርነት ሲያስጨንቁ ሕግ አልባ ነበሩ ለማለት ያዳግታል:: በግብጽ ታሪክ ላይ ተመዝግቦ የሚገኘው ንጉሥ ሻባካ 25ኛውን የግብፅ ንጉሥ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ስናይ ከዚያም ወዲህ የሻባካ የልጅ ልጆች 712 ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነግሰዋል ሲባል የግብጽን ሥልጣኔ የተጋሩ ወይም ሕግን ያስተማሩ ነበሩ ለማለት ያስደፍራል:: ስመጥሩ ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ቲርሃካ ግብጽን መርቷል ሲባል የሚደነግጡ ካሉ የግብጾችን ታሪክ ማገላበጥ ይጠበቅባቸዋል::

በጥቂቱ ከላይ የጠቀስነው ሀገራችን ኢትዮጵያ በጥንት ዘመን ሕግን ለመከተል የሞከረች አገር መሆንዋን ነው:: እንዲህ ሲባል እንደዘመናዊው ሕግ የበላይ ባለሥልጣናትን ሥልጣን የሚገድብ ሕግ ሳይሆን በሕዝቦች መካከል ግፍ እንዳይኖር የሚከለክል፣ ሚዛኑም እንደየጊዜው የሚስተካከል ወይም የሚጣመም መሆኑ አይካድም::

ሕግ በሕግ አውጪው በጉ ፈቃድ ወይም ብቃት የሚሰፈር ነበር:: አንዳንዱ መንግሥት ኃይል ስለአለው ድሆችን፣ ወይም ግለሰቦችን ሲወርስ፣ ሲያስር፣ ሲገድል ትክክል ተሠራ ተብሎ በሕዝቡ መታመኑ የጥንቱ ዕውቀት የፈጠረው በመሆኑ የሚደረጉት ግፎች ጥያቄ ውስጥ ሳይገቡ ነው::

አንዳንዱ መንግሥት ጥጋብ ሲሰማው ቋንጃ መቁረጡ፣ እጅ እና ምላስ መጉመዱ፣ ሕዝብን አሰቅቆ ተቆጥቶ ማኖር የኑሮ ብልሃት ተደርጐ እስከአሁንም ስለሚገመት ይህ ሁሉ ችግር ሥልጣኔ ሥር እየሰደደ ሲመጣ የሚስተካከል መሆኑን መዘንጋት አይኖርብንም::

ርዕሳችን ከሕግ ጋር መታረቅ ነውና ኢትዮጵያና ሕግ ይተዋወቁ ነበርን? የሚለውን ከላይ በታሪክ ባመሳከርነው መሠረት ወደ ዋናው ሐሳብ ከመግባታችን በፊት ስለሕግ አጭር ትንታኔ ሰጥተን ለማለፍ እንገደዳለን::

ሕግ በቁሙ ስምምነት ማለት ነው:: ይህም በቃል የሚወረስ ወይም በጽሑፍ የሚቀረጽ ሆኖ እንደ ድንበር ከዚህ አትለፍ ወይም ከዚህ አትትረፍ ብሎ የሚያገለግል እና የሚዳኝ ውል ነው::

ከዚህ ቀጥሎ የሕግ ቅርጽ በኅብረተሰባችን ውስጥ ምን ይመስላል ወደሚለው ጥልቅ እሳቤ እናመራለን::

ሕግ በኢትዮጵያ ነበረ:: በጽሑፍ የተጻፉ፣ በቃል የተተነተኑ ወይም የተወረሱ ሕግጋት በስፋት የታዩ ናቸው:: ችሎት ያለው ዳኝነት፣ ክርክር የሚደረግበት አደባባይ አለን:: ይህም ዕድሜአቸው በገፉ አዛውንት ተጀምሮ በንጉሡ ችሎት የመጨረሻ ብያኔ ይግባኝ የሌለው ፍርድ የሚሰጥበት ነው::

ከሕግ መጻሕፍት የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፤ አሥርቱ ትዕዛዛት እና ስድስቱ ቃላተ ወንጌል የሕግጋት ሁሉ ቁንጮ ሆነው በሌሎች ሕግጋት ሲተነተኑ እናያለን:: እንደዚሁም ጥንታዊ የሕግ መጻሕፍት ነበሩን፤ ምንም እንደዘመናዊው ሕግ በእያንዳንዱ ነገር ላይ



የሕግ ትንታኔ ለመስጠት ባይችሉም አጠቃላይ የሆኑ መንደርደሪያ ሐሳቦችን የሚሰጡ ናቸው:: ከእነዚህ መካከል ዲዲስቅልያ፣ ቀሌምንጦስ፣ ቀኖና አበሊዲስ፣ ፊውስ መንፈሳዊ እና ፍትሐ ነገሥት የመሳሰሉ ታላላቅ የሕግ መጻሕፍት ናቸው::

መጽሐፈ መነኮሳት የተባለው የገዳማዊውን ሕይወት በጥልቅ የሚተነትን እጅግ ትሁት የሚያደርገውን መጽሐፍ ስናነብ የትዕግሥትን፣ የፍቅርን፣ የይቅርታንና የሰላምን ሕግጋት ሲያስተምር እናገኘዋለን::

ምንም ከላይ የተጠቀሱት መጻሕፍት ከሃይማኖት ጋር ቢያያዙም እጅግ ፍትህ የተሞሉ ድንጋጌዎች በመሆናቸው ሰው ምንም ቢሰለጥን ሕግን ከመንፈሳዊ አስተሳሰብ ሲያወጣው ፈጽሞ እንደማይችል ያረጋግጡልናል:: ስለዚህም ይመስላል እነዚህን ይሉኝታ፣ ፈሪሐ እግዚአብሔር እና ጥልቅ ሰብአዊነት የሚያስተምሩ መጽሐፍ ያነበቡ ነገሥታት በሕሊና ሕግ ታስረው ግፍ ሳያበዙ ያለፉት::

የፍትሕ አባት እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህም ፍትሕ ፍለጋ ከጸባዖት የደረሱ እንባዎችን ሲያብስ፣ የተበዳዮችንም ጩኸት ሲያዳምጥ እናገኘዋለን:: ለምሳሌ ራሔል ወደሰማይ የረጨችው እምባ ፍትሕ የሚፈልግ ነበር:: የአቤል ደም፣ የኦርዮ ደም ከጸባዖት ደርሰው ፍትሕ ይዘው ተመልሰዋል:: ለምሳሌ ያህል ምንም ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ቢሆንም የኤልያብ ልጅ የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህን ሚስት አድርጐ ባልዋን ኦርዮንን በማስገደሉ ነቢዩ ናታን ወደ ዳዊት ከእግዚአብሔር ተልኮ ሄዷል፤ ነቢዩ ናታን ዳዊትን ምን አለው?

የሕግ ጥያቄ ነበር የጠየቀው፤ በአንድ ከተማ አንዱ ባለጠጋ አንዱም ድኃ የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ:: ባለጸጋውም እጅግ ብዙ በግ ነበ ረው:: ለድኃው ግን ከገዛት አንዲት ታናሽ በግ በቀር አንዳች አልነበረውም አሳደጋትም ከልጆቹም ጋር በእርሱ ዘንድ አደገች:: እንጀራውንም ትበላ ከዋንጫውም ትጠጣ ከብብቱም ትተኛ ነበር፤ እንደልጁም ነበረች:: ወደ ባለጠጋውም እንግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ወስዶ ለዚያ ወደ እርሱ ለመጣው እንግዳ ያዘጋጅለት ዘንድ ሳሳ:: የዚያንም የድኃውን ሰው በግ

ወስዶ ለዚያ ለመጣው ሰው አዘጋጀ።» ብሎ ናታን ንግግሩን ሲጨርስ ዳዊት በዛ ሰው ላይ እጅግ ተቆጥቶ ናታንን ፡ ሕያው እግዚአብሔር ይህንን ያደረገ ሰው የሞት ልጅ ነው። ይህን አድርጓልና አላዘነምና ስለአንዲቱ አራት ይመልስ አለው።

ናታንም ዳዊትን አለው። ያ ሰው አንተ ነህ፤* የእግዚአብሔር እውነተኛ ፍትሕ በዘመናት ውስጥ ከቃየል ጀምሮ ሲታይ የኖረ ቢሆንም በሚወደው ዳዊት ላይ እንኳን ስለእውነት መፍረዱ ፍትህ ከሁሉ በላይ መሆኑን እንረዳ ዘንድ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ለዳዊት ልጅ ለሰሎሞን እግዚአብሔር የሰጠው ስጦታ ታላቅነት እና የሕግን ፍጹምነት የሚያስረዳ ነው።

እግዚአብሔር ሰለሞንን እጅግ ይወደውና ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ? ብሎ ይጠይቀዋል። ብልሁ ሰሎሞን «በዚህ ታላቅ ሕዝብ ላይ አስተዳድር ዘንድ ከመረጥከኝ ዘንዳ እኔ መግቢያና መውጫውን የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ስለሆንኩ በሕዝብህ ላይ በቅንና በእውነት እፈርድ ዘንድ አስተዋይ ልቡናና ጥበብን ስጠኝ አለበለዚያማ በዚህ ሕዝብ ላይ ማን ሊፈርድ ይችላል?» ብሎ የጠየቀው ጥያቄ ሕግና ጥበብ ያላቸውን ታላቅ ዝምድና የሚያስረዳ ነው።

በሰሎሞን ጥያቄ እጅግ የተደሰተው እግዚአብሔር «ፍርድን ትለይ ዘንድ ለራስህ ማስተዋልን ለመንህ እንጂ ለራስህ ብዙ ዘመናትን ባለጠግነትንም የጠላቶችህንም ነፍስ ሳትለምን ይህን ነገር ለምነሃልና እነሆ እኔ እንደ ቃልህ አድርጌልሃለሁ። እነሆ ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ከአንተም በኋላ እንዳይነሳ አድርጌ ጥበበኛና አስተዋይ ልቡና ሰጥቼሃለሁ። ባለጠግነትንና ክብርን ጨምሬልሃለሁ።»* እያለ እግዚአብሔር ጸጋ በዲበ ጸጋ ያደለው ደገኛይቱን ሕግ በመለመኑ ብቻ ነው። ታዲያ ኢትዮጵያም በእውነትና በጥበብ የተሞሉ የሕግ መጻሕፍትን በማስፋፋት ነገሥታትዋ በተቻለ መጠን በእውነት ይፈርዱ ዘንድ ስትጥር ቆይታለች።

* ሳሙ. ፤ል. 12፥1–23
* ነገ. ቀዳ. 3፥4–13



በእርግጥ በዘመናት ውስጥ ጥበብ እና እውነተኛ ፍትሕ የጐደላቸው ሥራዎች ቢፈጸሙም በአንጻራዊ መልኩ የአሕዛብነት የአረመኔነት እና የጭካኔ ሥራዎች በሕግ የተገደቡ ነበሩ። እኛ ኢትዮጵያውያን ፍትሕንና ሕግን በማክበር የታወቅን ጨዋ ሕዝቦች ነን። ሰይጣናዊ የሆነ ጭካኔም አልተጠናወተንም፤ የዛሬን አያድርገውና።

ከእዚህ በላይ ስለመንፈሳዊው ሕግ እና የጥበብ የእውነት ገጽታችን በጥቂቱ ያየነው በቂ ሆኖ ከዚህ በኋላ ደግሞ በሕዝባችን ውስጥ ስለነበሩት ከእግዚአብሔር የተሰጡ በሕገ ልቡና ተጠብቀው የኖሩ ሕጐች በጥቂቱ እናያለን።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ሕዝብ አካባቢውን የሚያስተዳድርበት ሕግጋት አለው። የእነዚህ ሕግጋት ተንታኞች ፈጻሚዎችና ሕግ አውጪ ዎች በሚገባ አሉ። ለምሳሌ ያህል የሰባት ቤት ጉራጌ ቂጫ በሚል ሕግ የበላይነት ነው የሚተዳደረው። ለዚህም የጀካ የተባለ የጥድ ዛፍ በቸሃ ውስጥ እንደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚያገለግል አለ። ይህ ሕግ ከግለሰብ ሥርዓት እስከ ቤተሰብ መንደርና ማኅበረሰብ ሕግ በማካተት የያዘ ነው። እንደዘመናዊው ሕግ አንድን ሰው መዝለፍ፣ መምታት፣ ማቁሰልና መግደል ወንጀል ሆኖ ያስቀጣል። ሌላው ቀርቶ አንዱ ሰው ሌላውን ሰው በዱላ ቢመታ ዱላው የጽድ ነው፤ ከዱላው ጫፍ ላይ ብረት አለው ወይ? ብሎ የሚጠይቅና በየደረጃው የሚዳኝ ሕግ ነው። ግለሰቦች ድንበር ለድንበር እንዳይገፋፉ አልፈው መንገዶችና የማኅበራዊ ጉዳዮች ማከናወኛ ቦታዎችን የሚዘርፉ ግለሰቦችን ሳይቀር ሕጉ ይከላከላል።

ይህንን ሕግ የሚያስፈጽሙ ዳኞች ሽማግሌዎች ብቻ ሲሆኑ፤ ከሕጉ ውጪ የሚሆነውን ግለሰብ ያለማወላወል ከማኅበረሰቡ ውጪ በማድረግ ሁሉ ሊቀጡ የሚችሉ ናቸው። ታዲያ በጉራጌ ኅብረተሰብ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቃል ይወረስ እንጂ ከቀበሌ እስከ ቂጫ (የመጨ ረሻው ችሎት) ድረስ እንደሠንሠለት የተያያዘ ነው።

ነፍስ ያጠፋ ሰው በአስቸኳይ ተሰውሮ ሄዶ ዳኝነት ከጠየቀ ከዚያን ጊዜ በኋላ ጉዳዩ በቂጫ ወይም በሕግ ጥላ ሥር ስለሆነ የሟች ቤተሰቦች

ሊያጠቁት ፈጽሞ አይችሉም፡፡ ጉዳዩ ግን ቄጫው የሚወስነውን የገንዘብ መጠን ከኅብረተሰቡ ሰብስቦ እስኪከፍል ድረስ ድንጋይ ተሸክሞ «ነፍስ በእጄ ጠፍቷል» ብሎ በመለመን ካሣ ይከፍላል፡፡ ይህንን የሚያደርገው ለካሣው ተብሎ ሳይሆን ወንጀለኛው ጥፋቱን አምኖ በየሰው ደጅ እየተንከራተተ ድንጋይ በጫንቃው ተሸክሞ በሚለምንበት ጊዜ በሠራው ስህተት ጥልቅ ሐዘን ይሰማዋል፡፡ የሚያየውም ይቀጣል የሚል እምነት ስለአላቸው ነው፡፡

ይህ ዓይነቱ ዘዴ በኦሮሞውም ጉሳ ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ አንድ ነፍስ ገዳይ ጉማ ካለ በሕግ የበላይነት ስላመነ የሟች ቤተሰብ ሊገድሉት አይፈቀድላቸውም፡፡ እጅግ ረጋ ብሎ ሳጠናው የኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ሕግ (ሴራ) አስገራሚ ቅን ሕግ ነው፡፡ በገዳ ሥርዓት መሠረት በየስምንት ዓመት የሚለዋወጥ አስተዳዳሪ የሚሾምበት የሕግ አባት የጦር አባት በተሰኙ የማዕረግ ደረጃዎች የፍትሕ ባለሥልጣን የሚሰየምበት ታላቅ ሕግ ያለው ጉሳ ኦሮሞ ነው፡፡

አንጋፋ የተባሉ የኦሮሞ ሽማግሌዎች ለሰው ሳያዳሉ ለእውነት ሲፈርዱ ለተመለከተ ሕዝባችን በሕገ ልቡና የአምላኩን ሕግ የቀረፀ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ኦሮሞዎችም ዛፍን የፍትህ አዳራሽ አድርገው ይዳኛሉ፡፡ ይህ ከባዕድ አምልኮ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ተፈጥሮን የማክበር ዝንባሌ ነው፡፡ ለተፈጥሮ ሳይቀር ዳኝነት ስለአላቸው በዘመናዊው አጠራር የ(Greer party) የአረንጓዴው ቡድን አባላት ይመስላሉ፡ ዛፍ መቆረጥ የለበትም መሬቱም መደህየት ወይም መራቆት የለበትም የሚሉ የኦሮሞ ሽማግሌዎች በብዛት ስለአሉ፡፡ እነዚህ ከእግዚአብሔር የተማሩ የሕግ ሰዎች ሊደመጡ ሊሰሙ ይገባቸዋል፡፡ በዚህም ከሕሊና ከተፈጥሮ ሕግ ጋር መታረቅ አለብን፡፡

በእነዚህ በሁለቱ ማኅበረሰብ ሕግ ኢትዮጵያዊያን በሕገ ልቡና የሚመሩ ስለመሆናቸው ከዘመናት በፊት የሕግ የበላይነትን ጠንቅቀው የተረዱ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡



ከዚህ በላይ ከሕግ ጋር መታረቅ በሚለው አጠቃላይ ሐሳብ ውስጥ ሕገ እግዚአብሔርን በሁለት ከፍለን ሕገ ልቡና እና የተጻፈውን ሕግ ለያይተን በየማኅበረሰቡ ውስጥ የደረጀውን ሕግ ቃኝተናል፡፡

አሁን ዘመናዊው ሕግ በሀገራችን ኢትዮጵያ እንዴት መቼ መሠረት ያዘ? ከሚለው ሐሳብ ከመድረሳችን በፊት ዓለም አቀፋዊው ሕግ ምን ይመስላል? ወደሚለው እናመራለን፡፡

ዓለማችን አንዴ በሕግ የበላይነት ስታምን ሌላ ጊዜ ሕግን ስትጥስ ሰንብታ ለዚህ ደርሳለች፡፡ ሕግ የተራቀቀበት፣ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት፣ የሥልጣኔ ምዕራፍ ከቅድመ ታሪክ በፊትና በኋላ ብዙ ቢሆንም፤ በሙሴ አማካኝነት ለሕዝበ እስራኤል የተሰጠው ሰማያዊው የተጻፈ ሕግ፣ ወርቃማ በተባለው ዘመን የተጻፈው የግሪክ ሕግ፣ ረጅም ዕድሜ የኖሩ እና የተተነተኑ ጥልቀት እና አጠቃላይነት ያላቸው ሕግጋት፣ የሩቅ ምሥራቅ ሃይማኖታዊ ሕግ፣ በዚህ ዓለም የሰው ልጅ ለሕግ የተገዛባቸውንና የተጨነቀባቸውን ጊዜ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ከዚያ ወዲህ የሮማን ነገሥታት፣ የፋርስና የባቢሎን አስተዳደርን ስናየው ጭካኔ የበዛበት እና በጦርነት የታጀበም ቢሆን እንኳን ሰፋፊ የግዛትና የሥልጣኔ ሕግጋት የታየባቸው ነበሩ፡፡ በተለይ ሮማውያን ይሁዳን ለመግዛት በእራሳቸው የአስተዳደር ሠንሠለት ያሠለጠኑትን ይሁዳዊ በመሾም ለብዙ ዘመናት ሰፋፊ ግዛቶችን ሊያስገብሩ መኖራቸው ክፉም ይሁን ደግ የሥነ መንግሥት አወቃቀራቸው ጠንካራና የተቀናጀ ስለመሆኑ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡

እንዲህ እየተንገዳገደች ከሕግ ውጭ በአሕዛብና በሕገወጦች ስትታመስ የከረመችው ዓለም የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በተወለደው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከፍትህ ጋር ታረቀች፡፡ ያ... ሕግ የርህራሄ የሰላም ሕግ ነበር፡፡ በቀልን የሚያጠፋ የሚያስተሳስብ የሚያፋቅር እውነት ነበር፡፡ ለድኃዋ የፈረደላት፣ ወንበዴውን በርህራሄ ነጻ ያወጣ፣ የባርነትን ሠንሠለት የሰበረ ፈውስ ነበረ፡፡

ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ሕግን እያመሳጠረ እያራቀቀ እንዲህ ገለፀው:: እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢያትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ አትመኝ ባላለ ምኞት ባላወቅሁም ነበርና፤* እያለ ሕግ ክፉና ደጉን የመለያ አጥር እና ጥልቅ እውቀት መሆኑን ያስረዳል::

«ሕግ መልካም እንደሆነ አውቃለሁ:: ሕግ መንፈሳዊ ነው:: እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ:: የማደርገውን አላውቅምና የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርግም:: እንዲህ ከሆነ እኔን ኃጢአት እንዳልሠራ የሚከለክለኝ ሕግ መልካም እንደሆነ እመሰክራለሁ::»* እያለ ስለሕግ ሲተነትን ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋ በመጠቀም በመልዕክቱ አስቀምጦታል:: «በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ::» ይህ ገማልያል በተባለው የሕግ ሰው እግር ሥር ሕግን የተማረ ነገር ግን በክርስቶስ አዲስ ሕግ የተጠራና የተመራው ጳውሎስ የሚሰጠው የሕግ ሐሳብ ብዙ ሊቃውንትን ሲያወያይ የከረመ ነው::

ስለዚህ ከጌታችን የሰላም ሕግ አዋጅ በኋላ ከእውነተኛው ሕግ ጋር የታረቁ እነ ጳውሎስን የመሳሰሉ ተገኝተዋል:: ከዚህ ከጌታ የመስቀል ሞት በኋላ የፍትሕ ብርሃን ወጋገን እየሰፋ መጥቷል:: በተጻራሪም የሐሰት ዓለምም ሥራውን አላቆመም::

እነ ቅዱስ ዳዊት ጌታ ከመወለዱ በፊት ደስ የተሰኙበት ሕግ ቀንና ሌሊት ያሳሰባቸው «ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፤ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል» ያ ሲሰማ ብቻ የነበረው እውነት ሆኖ የታየው የጽድቅ ሕግ ፍጹም ሕግ ተገለጠ:: ስለዚህ መዝሙረኛው ዳዊት «ምሕረትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተሳሳሙ» አለ::

* ሮሜ 7 7
* ሮሜ 7 14 16



ለመሆኑ እውነት ከምድር በቀለች ያለው መቼ እውነት ከምድር ተገኝታ ታውቃለች? ነገር ግን ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ ሲጠራት ፍትህ ይቅርታና ሰላም ሆና መጣች በሕግም ፀደቀች:: የፍትሕ ወይም የሕግ መንፈሳዊነት እውነት ነው:: አካል ገዝቶ የማይታይ በሕሊና ሆኖ የሚወቅስ እና የሚከስ የሚፈርድ ሕግ መንፈሳዊ ብቻ ነው::

ከላይ ሰው ለሕግ የችሎት ቦታ ሲሰጠው ከዛፍ ሥር፣ ከአዳራሽ ሲጠራው እናያለን:: በጉባኤ፣ በሸንጎ፣ በእሰጥ አገባ ሲሞግተው፤ ሕግ ግን በሕሊና ችሎት ዙፋኑን ዘርግቶ በዳይን ሲቀጣ ተበዳይን ሲክስ በዚህ መንፈሳዊነቱን እናያለን:: ታዲያ ሕሊና በራሱ ሊዳኝ እንዴት ይችላል? በሕሊና በኩል ዓለምን ሲዳኝ የምናየው እግዚአብሔር ነው:: የገዛ ሕሊናችንን እንኳን በማየት በመፍራት ከሕግ ጋር ስንታረቅ እንገኛለን::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ በዲያቢሎስ ሲፈተን በደል ወይም መተላለፍ ወይም ኃጢያት በሦስት ተከፍለው ነበር የቀረቡለት:: የዚህ ዓለም ኃጠአት በሦስት ይከፈላል:: እርሱም ሥልጣንን ክብርን ከመውደድ የሚመጣ ሕግን መተላለፍ ትዕቢት፣ ማንአለብኝነት እና አፍቅሮተ ነዋይ (ገንዘብን ማፍቀር) ናቸው:: ሕግም ገደብ የሚሰጠው ሥልጣንን፣ ትዕቢትንና ስስትን ነው:: ሰውም ከሕግ ጋር ሲታረቅ ሥልጣንን በአግባቡ በመያዝ ከትዕቢት ይልቅ ትህትናን በመምረጥ ስግብግብነትን በመቃወም ነው:: ሥልጣኔ ሲባልም ከሁሉ በላይ ከሕግ ጋር መታረቅ ነው:: ያም ከአምላካዊው ሕግ ጋር ነው:: ከዚህ በላይ የተተነተነውን የሕግ እሳቤ በሥራ ላይ ለማዋል ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቅድመ ታሪክ ጀምሮ ስትጥር ቆይታለች፤ ከብሉይ ኪዳን ሕግ ጋር ታርቃለች:: በሐዲስ ኪዳን ሕግ ጸንታለች::

ማኅበረሰብዋም አካባቢውን የሚያስተዳድርበት የተጻፈም ሆነ በቃል የተወረሰ የሕሊና ሕግ ነበረው ብለናል:: ስለዚህ ከሕግ ጋር ለመታረቅ ሞክራለች:: ሕግ ነፃነት ነው፤ ሰላም ነው፤ መንገድ ነው:: የነፃነት ዋጋ የሚያውቅ ሕዝብ የሕግ ሚዛን አለው:: ሥልጡን ሕዝብ ለአንደበቱ ልጓም:: በእጁም የሕግ ካቴና ስላለ የፈቀደውን ሊያደርግ አይችልም::

ሕግን መለማመድ ማለት ነፃነትን መለማመድ ማለት ነው:: ቅዱ ጳውሎስ ከገማልያል እግር ሥር ቁጭ ብሎ የተማረው የሕግ ነፃነ ነው:: ያ ብርሃን በውስጡ ስለነበር ጌታ በሌላ የመብረቅ ፍንካች ሕ ሲጠራው ዓይኑ ላይ የነበረው ቅርፊት ተገፈፈ:: ስለዚህ ሕግ መልክ ነው አለ::

ይኸው ነው ሥልጣኔ:: ብዙዎቻችን መሠልጠን ብረትን በለ ብረት ሰፍቶ መኪና መሥራት ብቻ ሊመስለን ይችላል ይህ በአንድ መ መመረቅ ነው:: ሥልጣኔ ግን የሰዎችን ሰውነት ተረድቶ የሕሊ አጥራቸውን አለመዝለል ነው:: ከዚህ አልፎ ተርፎ ተደጋግፎ መኖ ነው፤ ከእንስሳ ለይቶ ሰው ያደረገን:: በተለይ ኢትዮጵያውያን የመቻቻ ሕግ አለን፤ የዕድር፣ የዕቁብ፣ የሰንበቴ፣ የቤተሰብ ሸንጎ ማኅበራዊ መረዳጃዎች አሉን::

ዘመናዊው ሕግን በኢትዮጵያ ስንመለከት በ1945 ዓ.ም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዓለም አቀፋዊውን ሕግ እና የሀገሪቱን የተጻፉ የየጎሳው የባላባቱን የተወረሰ ሕግ በማገናዘብ ሕዝብ የሚመርጣቸው የፓርላማ አባላት የሚወከሉበት ምክር ቤት ለመመሥረት ችለው ነበር:: ይህም ሕግን ለተለማመደችው ኢትዮጵያ ቀላል ነበር::

ይህም በሌላው ዓለም እያቆጠቆጠ የመጣውን የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት ለማስያዝ ንጉሡ ቀስ በቀስ ከፍጹማዊው የዘውድ አስተዳደር ለመውጣት ዳዴ የጀመሩበት ጊዜ ነበር:: ምን ማለት ነው? ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ከሦስቱ የኃጢአት ሥሮች መካከል ሥልጣን በአግባቡ ካልተያዘ በሕግ ካልታረቀ ወደ መጠፋፋት ስለሚወስድ ይህንን አጋንንታዊ ፈቃድ ቅዱስ ለማድረግ ዓለም የተጠቀመችበትን ፈሊጥ መመልከት ያስፈልጋል::

የዘመናዊው ሕግ ቅርጽ መያዝ የጀመረው በእነ ዓፄ ቴዎድሮስ፣ ዓፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ሲሆን፤ ለሀገር ውስጥና በተለይም የቤተ መንግሥቱን ማዕረግ ለማደላደል በሥርዓትም ለማስተዳደር የተሞከረበት ጊዜ ነበር:: በተለይ በዓፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት በ1900 ዓ.ም. ሚኒስትሮች ሲሾሙ ሕግም በመጠኑ የተሰጣቸው ይመስላል::



«አሁንም በዚህ ባስያዝኋችሁ ሥራ ሳትጣሉ ሳትመቀኛኙ እንቅልፍ ሳትወዱ፣ መጠጥ ሳታበዙ፣ ገንዘብ ጠልታችሁ በእውነት መንግሥታችንን የምትረዱ ሁኑ» ብለው ዓፄ ምኒሊክ የጽሑፍ መልዕክት ስለአዳኝ ስለተለያዩ ጉዳዮችም ሕግ አውጥተው ነበር:: ከሕግ አልፎ ሕገ መንግሥት በተሳካ ሁኔታ የተቀረፀው ግን በአዋጅ በንጉሠ ነገሥቱ የፀደቀው ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም. ነበር:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ በዚህ ዕለት ስለሕግ ታላቅ ነገር ተናግረዋል::

«ሕግ ለሰው ሁሉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን ማንም አይስተውም፤ መከበርም መጠቀምም የሚገኙት በሕግ መስተካከል የተነሣ ነው:: መዋረድም፣ መጐዳትም የሚመጡት ከሕግ መጓደል የተነሣ ነው:: ግፍና በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ ነው» ብለው ነበር:: ይህ ሕገ መንግሥት ሲመሠረት ቀደም ብሎ ከመሣፍንት ወገን ሥልጣን በዘር ይተላለፍላቸው የነበሩትን እና በዘመናዊ አስተዳደር የተካኑትን አንድ ላይ በማዋቀር የተከናወነ ሥራ ነው::

ከንጉሡ ማስታወሻ እንዳገኘነው «በኢትዮጵያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ሦስት ሺ ዘመን ያህል የተለመደው አገዛዝ ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ በሥልጣኑ እያዘዘ እንጂ ምክር ቤት አቁሞ በሕገ መንግሥት የሚያስተዳድር ንጉሥ አልነበረም፤ የተለያዩ ወዳጆቻችን የሆኑ አንዳንድ ሰዎች ነገሩ ስላልገባቸው እንዴት በገዛ እጅዎ የመንግሥትዎን ሥልጣን ለሕዝብ ይሰጣሉ» ብለው ያማክሩኝ ነበር ብለው እንደጻፉት ንጉሡ ያሰኘውን በሚፈጽምበት የፍጹማዊ አስተዳደር ዘመን ለአገር ዕድገት ሲሉ ምክር ቤት ማቋቋማቸው የሚያስመሰግናቸው ሲሆን፤ ከሁሉ በፊት ሕገ መንግሥቱን ለማርቀቅ ከመኳንንቱ እና ከሚኒስትሮቹ ስለተውጣጣው የሕግ አርቃቂ ቡድን ከንጉሡ ማስታወሻ ያገኘነው ሐሳብ እንዲህ ይላል:: «ሕገ መንግሥት ለማቋቋም ቆረጥን:: ስለዚህ የልዩ ልዩ አገሮችን ሕገ መንግሥት መርምረን የውጭ አገር ልምድና ትምህርት ያላቸውን ከሀገሩም ውስጥ የአውራጃውን ልማድና የቀድሞውን ታሪክ የሚያውቁ ሰዎች መርጠን ከዚሁ ከውጭ አገሮች ሕገ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚስማማው ተመርጦ እየተዋጣ እንዲቀርብልን አዘዝን» ይሉና ለዚህ

ሥራም ከመሣፍንቱ ወገን ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት፣ ራስ ሥዩም መንገሻ፣ ራስ ጉግሣ አርአያ እና ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ፤ ከሚኒስትሮች (ከዘመናዊዎቹ) የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል፣ የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ጐሹ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ የጽሕፈት ሚኒስትሩ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ መስቀል ታሪኩ:: ከመኳንንቱ ወገን ደጃዝማች ይገዙ በሀብቴ እና በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በአንድነት ሆነው እንዲመክሩ ተሰየሙ::

ይህ ቡድን በሁለት የተከፈለ ነው:: ይኸውም ሥልጣን ከልጅ ልጅ ሲተላለፍለት የነበረ ችሎታ ኖረውም አልኖረውም ሕዝብን ያስተዳድር ዘንድ ሁልጊዜ መብት ያለው አካል ነበረ:: ልብ እንድንል የሚገባው ይህ ክፍል ከየብሔረሰቡ ተወክለው ከየአካባቢው ልምድ ሕግ የሚቀርፁ እና የውጪ አገሩን ዕውቀት ገብይተው ሕገ መንግሥትን አንብበውና ተረድተው ለሀገሪቱ የሚጠቅመውን ያዘጋጁ አካላትን የተጨመቀ የተጣራ ሕግ የሚያጣራና ለንጉሡ የመጨረሻ ፊርማ የሚያቀርብ ነበር::

ይህ ከመሣፍንቱ እና ከሚኒስትሮቹ የተውጣጣው አካል ግን አንድ ችግር አጋጠመው:: ይኸውም የመኳንንቱ ወገን ሥልጣን በችሎታ ሳይሆን በዘር መተላለፍ አለበት የሚል ሲሆን ዘመናዊው ክፍል ግን የለም ሥልጣን እና ማንኛውም ጥቅም በዘር የሚተላለፍ ከሆነ ተራው ሕዝብ እንዴት አገር አለኝ ማለት ይችላል:: ሁሉ በችሎታው ሕዝብን ማገልገል ስለሚኖርበት ሥልጣን በዘር ሳይሆን በችሎታ መሆን አለበት በማለት ሁለት ወገን ተከፈሉ::

በዚህ ጊዜ ከመሣፍንቱ ወገን በብልህነታቸው በችሎታቸው ዘወትር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሕሊና የማይረሱት ራስ እምሩ ኃ/ሥላሴ ወደ ዘመናዊው አስተሳሰብ በማድላታቸው ከዚህ ሁሉ በላይ ንጉሡ እራሳቸውም የሚኒስትሮቹን ሐሳብ በመደገፋቸው ከዘር ወደ ዘር ሲንከባለል የመጣው ሥልጣን በሕገ መንግሥት ለሕዝብ ተሰጠ::



በዚህ ሕገ መንግሥት ላይ ሥልጣን ለሕዝብ የመስጠት ሀሁ የተጀመረ መሆኑን ማየት ይቻላል:: ለምሳሌ ቁጥር 1 ላይ «ንጉሠ ነገሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን ነው:: ገገርነቱ ግን በሕግ አወሳሰን ነው» ይላል:: ይህ ማለት ንጉሡ ምንም ገዥ ቢሆን ሥልጣኑ ግን በሕግ የተወሰነ ነው የሚል ሲሆን፤ የሕግ መወሰኛው እና የሕግ መምሪያው አባላት ከሕዝብ መካከል ይመረጣሉ ይላል:: ሁለተኛው ክፍል እና አራተኛው ክፍል ላይ ደግሞ ለየዝርዝር ጉዳዮች ምክር ቤቱ እየመረመረ በድምጽ ብልጫ ይወስናል ይላል::

ይህን ሁሉ የዴሞክራሲ ሀሁ ኢትዮጵያ 1923 ዓ.ም. ጀምራ ነበር:: ሀገሪቱ በነጻ ገበያ ደንብ የምትተዳደር ሆና ለአገር ውስጥ ነጋዴዎችና ለውጭ ባለሀብቶች በርዋን የከፈተችበት የኢኮኖሚውም ዕድገት አዝጋሚም እንኳ ቢሆን የተጀመረበት ጊዜ ነበር:: ይህንን ሁሉ ማኅበራዊ እና የመዋዕለ ነዋይ ዘርፍ ለማስተናገድ በየዘርፉ ሕግ የሚያስፈልጋት ኢትዮጵያ በ1923 ዓ.ም. ቀድማ እንደነቃችው ቀጥላ ቢሆን ዛሬ የአፍሪካ ምሳሌ እናትና ብርሃን ሆና በታየች ነበር::

የመጀመሪያው የአፍሪካ መሪዎች ከቅኝ ግዛት በኋላ እነ ንኩሩሁማ፣ ናስር፣ ሴንጐር፣ ሁፋቴ ቢጊበይ ሴኩቱር፣ ኬኒያታ፣ ኔሬሬ፣ ባንዳ በአብነት ከፍ አድርገው የሚያይዋት ኢትዮጵያ የእራስዋ ባሕላዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ሕግም ቢኖራት ዓለም አቀፍ ሕግንም ሳትንቅ የሚጠቅመውን በመውሰድዋ ፓርላማ ያላት በመልካም ዕድገት ውስጥ የነበረች አገር ነበረች::

በ1923 ዓ.ም. የተረቀቀው ሕገ መንግሥት ፍጹም ነው ማለት ፈጽሞ አይቻልም:: ግን የትኛውም ሕገ መንግሥት ከጊዜ ብዛት በእርጋታ እየተስተካከለ ነው የሚሄደው:: ስለዚህ ነው የአሜሪካ ሕገ መንግሥት 27 አንቀጽ በ200 ዓመት ውስጥ የተስተካከለው መሠረቱ ግን በዚህ ሁሉ ዘመን ያው ነው::

ከ1967 ዓ.ም. ወዲህ ግን የኢትዮጵያ የሕግ ሁኔታ እጅግ ሕገወጥ ሆኖ ተገኝቷል:: እጅግ ስሜታዊ በሆኑ አዋጆች ሕዝብ ሳይመክርበት

ምሁራን ሳይተቹበት በጥቂት ግለሰቦች የአገራችን ሕግ ከመሠረቱ ተነቃቅሎ መውደቅ ጀመረ::

ለሦስት ሺህ ዓመት የዳበረው ባሕላዊ ሃይማኖታዊ ሕግ እንደማሾፊያ እንደኋላ ቀርነት ተቆጠረ:: ግን ታላላቆቹ የአፍሪካ መሪዎች ሁሉን ያዩት እነ ንክሩሁማ «የእኔ ፍልስፍና አዲሲቷን አፍሪካን መገንባት ነው:: እራስዋን የቻለች ፈጽሞ ነጻ የሆነች የተከበረች አፍሪካ ለመገንባት ዘመናዊውን ጥበብ እና ሳይንስ ከአፍሪካ ባሕላዊ ሕግ ጋር በማዛመድ ደረጃ በደረጃ በራስዋ ማንነት የምትተማመን አንድ አፍሪካ መመሥረት ነው» ብለው ተናግረው ነበር::

እርግጥ ነው ፍጹማዊው የነገሥታት ዘመን ከሕዝብ በተመረጡ እና ጊዜአቸውን ጠብቀው በሚወርዱ መሪዎች መለወጥ ነበረባቸው:: ግን ዶክተር መኩንን ቢሻው በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ያስገነዘቡት እነደነበረው አብዮት በተባለው የተረገመ እልቂት ሳይሆን ጥገናዊ ለውጥ በማካሄድ ነበር:: ከሕግ ውጪ ስድሣ የኢትዮጵያ ምሁራን ሹማምንቶችን በአንዲት ሌሊት በመጨፍጨፍ መሆን አልነበረበትም:: ከሕግ ውጪ የድኃዋን ሴት ትርፍ ቤት ሳይቀር በመውረስ አልነበረም:

ከፍተኛ የመዋዕለ ነዋይ ግሥጋሴ ለማሳየት ያቆበቆበችው ኢትዮጵያ ባለሀብቶችን ከወረሰች በኋላ ከሁሉ በላይ የሕዝቡ የመሥራት መንፈስ፣ ሀብት የማግኘት፣ የመበልጸግ መንፈስ በኮሚኒስታዊው ሥርዓተ ማኅበር ተሽመደመደ::

«Communism was a great system for making people equally poor. Infact, there was no better system in the world for that than communism.)» «ኮሚኒዝም ሁሉን በአንድነት ድኃ የሚያደርግ ታላቅ ሥርዓተ ማኅበር ነው» እንዳለ ቶማስ ኤል ፍሪድማን የተባለ ፀሐፊ ከሌሎች በቀዳው ሐሳቡ በአግባቡ ሊስተካከል የሚገባውን የመሬት ይዞታ ተመርኩዞ ሀብታም በዓይናችን አንይ የሚል ሥርዓተ ማኅበር በመፈጠሩ ሀገራችን ያልታሰበ አዘቅት ውስጥ ተወረወረች::»



የኢትዮጵያ ለውጥ ግብታዊ ከመሆኑ የተነሣ አሸባሪ በአንድ ሀገር ከሚያጠፋው የበለጠ የሰው ሕይወት የንብረት ውድመት ስደትና ሰቆቃ አስከትሎብን አልፏል:: ከዚህ ይልቅ ሁሉ በጥናት እና በእርጋታ ቢከናወን በአንድ ጀንበር የውጪ ግንኙነታችን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሁኔታ ባይጨላልም ለዛሬ ባልበቃን ነበር::

ይህ ሁሉ ሥርዓተ አልበኝነት ያመጣው ውድቀት ነው:: ኢትዮጵያ ለማደግ በሕግ መተዳደር አለባት:: ይህ ሕግ ደግሞ የመላውን ሕዝብ ድጋፍ ማግኘት አለበት:: በእያንዳንዷ ጉዳይ ላይ ሕዝቡ በተወካዮቹ አማካይነት ድምፁን መስጠት አለበት::

ከ1967 ዓ.ም. በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስደተኞች ሁለት ብቻ መሆናቸውን ማስረጃዎች ይጠቁማሉ:: ይህም ምሁራን በአገራቸው የሥራ ነፃነት እንደነበራቸው የሚጠቁም ሲሆን፤ ሕዝቦችም አገራቸውን ለቀው የሚሰደዱበት ጦርነትን የመሳሰሉ ችግሮች በኢትዮጵያ የለም ባይባል ለስደት የሚዳርግ አልነበረም::

በተለይ ምሁራን በአገራቸው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደልባቸው ምሁራዊ ወይም ሞያዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ዕቀባ መሠናክል ሲያጋጥማቸው ሊሠሩበት ወደሚችሉበት አገር መሰደድ ይጀምራሉ:: ባለፉት 30 ዓመታት በአገራችን ያጋጠመው ችግር እጅግ በውድ ዋጋ የሠለጠኑ ምሁራን አገር ጥለው ነፍሳቸውን ለማትረፍ በመሰደዳቸው ነው::

በየቦታው የጥይት እራት የሆኑ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መምህራን በየዘርፉ ያሉ ምሁራን ሥቃይ በማይመጥናቸው አለቃ መመሪት እና የመሳሰሉት የኢትዮጵያን የተማረ ኃይል ሽባ አድርጐ የእውቀትና የሥልጣኔ በሩ ተከርችሞ ይገኛል::

ሰፊው ሐሳብ የሥልጣኔ አቅጣጫ በምሁራኑ አቅጣጫ ካልያዘ አደጋዎች በምሁራኑ ካልተተቸባቸው አደጋ ሆነው መቅረታቸው አያጠራጥርም:: ታዲያ ይህንን ሁሉ መዘበራረቅ ያተረፍነው ሕግን እና መሠረቱን ነቃቅለን በማጥፋታችን ነው:: ዘመናችን እጅግ በከፍተኛ

ፍጥነት እየሠለጠነ ስለሆነ እኛም ከዓለም ሕዝብ ጋር በመልካሙ ሕግ መስማማት ይኖርብናል:: ከሕግ ጋር እንታረቅ::

ሥልጣኔ የሚረጋገጠው በግለሰቦች መብት ነው:: የአንድ ሰው መብት በሕግ ከተከበረ የማኅበረሰቡ ሁሉ ነፃነት እውነት ይሆናል:: ይህ የግለሰብ ነፃነት ሕግ ደግሞ በሁለት ይከፈላል:: አንደኛ እርስ በእርስ የምናደርገው መብትን የማክበር መንገድ ነው:: የአንድ ሰው ቤቱ ቤተ መንግሥቱ ነው:: አጥሩን መነቅነቅ፣ አልፎ ተርፎ ካለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ግለሰቡ ቤት መግባት በሕግ ያስቀጣል፤ ግለሰቡ ካልተስማማ ወይም በወዳጅነት በዝምድና ካልሆነ በቀር::

ሌላውን ሰው መሳደብ እና አልፎ ተርፎ መምታት የሰብዓዊ መብትን ስለሚጻረር ወንጀል ነው:: ከዚህ እንነሳና አንድን ግለሰብ በተክለ ቁመናው፣ በቀለሙ፣ በአካል ጉዳተኝነቱ፣ በፆታው፣ በጸጉሩ፣ በአፍንጫውና በትውልዱ ምክንያት መሳደብ ወንጀል ስለሆነ ከሕግ ጋር እንታረቅ ሲባል ከዚህ ሁሉ ጋር ነው:: በብዙ ቀልደኞች (ኮሜዲያን) የሚዘወተርው አፍን አኮላትፎ መቀለድ የሕግ ድንበርን ማለፍ ነው:: ከፍ ሲልም ለዳኝነት ወይም ለመሳሰሉት ጉዳዮች ምልጃ መቀበል፣ ፍትህን ማዛባት፣ ሕዝብን መካድ ስለሆነ ይህም እርቅ የሚፈልግ ጉዳይ ነው::

ዓባይ ዳኛ የአንዱን ፍርድ ለአንዱ በጉቦ በማለዋወጥ መቀለድ ፈጽሞ መቅረት ያለበት ጉዳይ ነው:: አንድ ጉበኛ ዳኛ በዳኝነት የሚመሩት ችሎት ከመጀመሩ በፊት በጠዋት ባለጉዳይ መጥቶ ጉቦ ብር ይሰጣቸዋል ለእኔ ይፍረዱልኝ ብሎ:: ወደ እረፋዱ ላይ ደግሞ ባለጋራው ይመጣ እና በቅሎ ይሰጣል:: ፍርዱ ሲታይ ዳኛው በቅሎ ለሰጣቸው ይፈርዳሉ:: ታዲያ በጠዋት የመጣው «ምነው በጠዋት ብር ብዬ መጥቼ» ብሎ በቅኔ ብር ምነው ጉቦ ሰጥቼዎት ቢላቸው እሳቸውም ምነው እርሱ (ባለጋራሀ) መጭ ብሎ ቀድሞህ በማለት አሳበው፣ ባለጋራህ በቅሎ ሰጥቶ ቀደመህ አሉት ይባላል:: ታዲያ ሕዝባችን ከድሮ ጀምሮ በዓባይ ዳኛ ሲገፈፍ በመኖሩ ከሕግ ጋር መታረቅ ፈጽሞ ይኖርብናል:: ጉቦ ተቀባዩ ብቻ ሳይሆን ጉቦ ሰጭውም ለዚህ ተወቃሽ ነው::



አንድ ጊዜ አንዲት ባለሙያ በአዲስ አበባ አካባቢ ለሚተከሉ ፋብሪካዎች አስፈላጊ የቅድመ ጥንቃቄ እና ደረጃቸውን በመገምገም የመወሰን ሥራ ትሠራ ነበርና ፋብሪካ የሚተክሉ ባለሀብቶችን ድርጅት ስትገመግም በተዘዋዋሪ መንገድ ጉቦ እንስጥሽ እያሉ እንዳባበልዋት እና ድርጅቱ ግን የሚገባውን ሁሉ አሟልቶ በማግኘትዋ መሥፈርቱን አሟልቷል ብላ ስታስተላልፈው ዓይተውና ጉቦ ሳይሰጧት በመፍቀዷ ተደንቀው እንደነበር አጫውታኛለች::

አንድ ሠራተኛ ዳኛ እውነተኛ ሥራ መሥራት ግዴታው፣ የተቀጠረበት ኃላፊነቱ ሆኖ ሳለ ካለአግባብ የመማለጃ ቀሳቀስና ገንዘብ መስጠት መዘዙ ለልጅ ልጅ የሚተርፍ አደገኛ መሆኑን መረዳት ኣለብን:: ይህ ጉቦ ከገንዘብም አልፎ ሥራ ፈላጊ ሴት ወጣቶችንም አስቸግሮ ይገኛል:: ሥራ ለመቀጠር ከባለሥልጣኖች ጋር ይወሰልቱ ዘንድ ስለሚጠየቁ ብዙዎች ሲያለቅሱ በዕድሜአችን ሰምተናል::

እግዚአብሔር አባይ ሚዛንን እጅግ ይፀየፋል:: ከትንሺ ንግድ ጀምሮ ቡና እና ጥራጥሬ የሚሰፈርባቸው ጣሳዎች ሳይቀሩ ከኋላቸው ወደ ውስጥ ተቀጥቅጠው ሚዛን እንዲሠርቁ መደረጉ በሕግ ላይ ማመጽ ስለሆነ ሊስተካከል ሊታረም ይገባዋል:: አስመስሎ የመሥራት (Copy right) ሕግ አለመክበር ፈጠራን ያጠፋ፣ ሥራን ያዳከመ፣ ዕድገታችንን ያቀጨጨ ሕገወጥነት ነው:: የሰውን የአእምሮ ውጤት መዝረፍ ከባድ ወንጀል ስለሆነ ሊታረቅ ይገባዋል:: የዘመናችን ታላቁ ንግድ ሕሊና ነው:: የኪነ ጥበብ፣ የሳይንስ ፈጠራዎች ሁሉ ቢከበሩ ባይዘረፉ ሁላችንም እንጠቀማለን:: ሥርዓት የሌላቸው ንግዶች የድህነት መሠረቶች ናቸውና::

ከላይ የጠቀስናቸው የመንግሥት ሕግ አስከባሪነትን የሚጠይቁ ቢሆኑም በአብዛኛው ኅብረተሰቡ እርስ በእርስ ሥርዓት በማክበር በታማኝነት የሚያከብራቸውና የሚያስከብራቸው ደንቦች ናቸው:: እኛ ጥቃቅን የምንላቸው ሥነ ምግባሮች የሕሊና ሕግን የሚጠይቁ፣ አንድን ሕዝብ ሥልጡን የሚያሰኙ ዋናና መሠረታዊ ቁም ነገሮች መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም:: ለምሳሌ ቀድመን ከፍተን የገባነውን በር ከኋላችን

እየተከተለ ላለው ሰው ሳይዘጉ ከፍቶ መጠበቅ፣ በር የተከፈተለትም ሰው አመሰግናለሁ ብሎ አክብሮቱን መግለጽ ሌላው ቀርቶ ሰው ላይ አለማነጠስ፣ በየቦታው አለመትፋት፣ እጣቢ በራችን ላይ አለመድፋት፣ የሰውን ግቢ አጥር አለመነቅነቅ፣ አለማመጽ፣ ድንበር አለመግፋት፣ የሕዝብ መተላለፊያ መንገዶችን አጥር እያሰፉ አለመዝጋት፣ የዕድር፣ የዕቁብ፣ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አለመስረቅ፣ ይህ ሁሉ በሕሊና ሕግ በጨዋነት የሚከናወን በሳልነትና ሥልጡንነት ነው።

ስለዚህ ነው ከሕግ ጋር እንታረቅ ሲባል ዘወትር መንግሥት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዳችንም ከፍትሕ ጋር በእውነት መታረቅ የሚኖርብን።

በሚያስደንቅ ሁኔታ ከላይ የተዘረዘሩ ባሕርያት ከንግድ ጋር ይያያዛሉ። ማንኛውም ቱሪስት በሠለጠነ ሕዝብ መካከል ሲጓዝ ሙሉ ነፃነት ይሰማዋል። ግን በሩን ከፍቶ በላዩ ላይ የሚዘጋበትን ታክሲ ነጂው ሳይቀር በር ከፍቶ አክብሮ እንደምን አደርክ እና እንኳን ደህና መጣህ ካላለው፣ በየመንገዱ የሚተፋ፣ የሚፀዳዳ ኅብረተሰብ ውስጥ ማንኛውም ጐብኚ ነፃነት ሊሰማውና ገንዘቡንም ሊመነዝር ፈጽሞ አይችልም።

ማንኛውም ባለሀብት በዚህ ዘመን የሠለጠነ ተራማጅ ኅብረተሰብ ቀልጣፋ እና ሥርዓት ያለው ሕዝብ ይፈልጋል። ለነፍሱ ዋስትና ለንብረቱ እና ለንግዱ ፀጥታ ካላገኘ ማን ሞኝ አለ ለአሞራ ገንዘቡን የሚረጭ።

የሆቴል አስተናጋጆች ሳይቀሩ ለአዲሱ የንግድ ዓለም የተስማማ መስተንግዶ ይዘው ካልተገኙ ለንግድ ሕግ ካልተገዙ በተኮሳተረ ፊት ማመናጨቅና ወይ ከልክ በላይ መቅለስለስ እንዳይኖር በየመስኩ ሥልጠና ያስፈልጋል። እንዲህ ሲሆን ለዕድገት ለሥልጣኔ የተዘጋጀ ሕዝብ ዘወትር የውጭ ባለሀብትም ሆነ የአገር ውስጥ ቱጃርን ይማርካል፣ ይጠራል፣ ቀስ በቀስም ሳናስበው መዋዕለ ነዋያችን እየዳበረ ይሄዳል።

በተለያየ ሙያ ያለን ሁሉ ከሥራ ገበታችን ሰዓትም ሆነ ገንዘብ ካለመስረቅ ጉቦ ካለመብላት ሕግ ጋር መታረቅ ይኖርብናል።



ማንኛውም ዜጋ በአካባቢው ወንጀል ሲሠራ ምን ቸገረኝ ብሎ ማለፍ የለበትም። ሰዎች ሲደባደቡ ዝም ማለት አይገባም፣ ሲዘረፉ በእኔ ካልደረሰ ምን አገባኝ አይባልም። አካባቢያችን የሕገወጦች መናኸሪያ፣ የጋንግ ስታሮች መፍለቂያ ሲሆን፣ የእኔ ልጅ ካልተደፈረች ምን አገባኝ፣ የእኔ ቤት ካልተሰበረ ምን ቸገረኝ ብሎ ሕግን አለማስከበር ወንጀል ነው።

በኢትዮጵያ ደካማ አይጠቃም፣ ሴት አትደፈርም፣ ሕፃን አይጉሳቆልም የውጭ አገር እንግዶቻችን አይዘረፉም ብሎ በጠንካራ የሕሊና ሕግ ሥነ ሥርዓት መታነጽ ያስፈልጋል። ከዚህ በላይ ከሞላ ጎደል ያሰፈርነው ግለሰቦች አክብረው የሚያስከብሩት የሕሊና ሕግ ሲሆን፣ ይህ ሥርዓት ከያዘ ወደ ቀጣዩ የዴሞክራሲ ሕግ እናመራለን።

በዓለማችን ላይ የተለያዩ የኅብረተሰብ አስተዳደር ፍልስፍናዎች ቢኖሩም ጉላ ብለው የሚታዩት ግን የኮሚኒዝም ሥርዓተ ማኅበር እና የካፒታሊዝሙ ሥርዓተ ማኅበር ናቸው።

ማርክስ የተባለው ፈላስፋ (Communism ethical relativism) በተሰኘው ፍልስፍናው በሥርዓተ ሃይማኖት የተዋቀረ ወይም የሃይማኖት ሥርዓት ያለው ሥነ መንግሥት ስህተት ነው በሚለው አቀራረቡ፣ የሥነ ምግባር ሕግ ሳይሆን የማይለወጥ የተፈጥሮ ሕግን በማበልፀግ የኃይልን፣ የነውጠኝነትን፣ ግድያንና ውሸትን በሕጋዊ አካሄድ መፍታት ነው፣ ሐቁ በማለት ሕግን እና የተፈጥሮ ዝግመታዊ ለውጥን አዛምዶ እናያለን። ይህ በቁሳዊ ታሪካዊ ትንታኔ መሠረት የሰው ልጅ የመዋዕለ ነዋይ ግሥጋሴ ኃይል (Economic forces) በ(dialectical process) በዝግመታዊ ለውጥ ኅብረተሰቡ ወደፊት እየገፋ ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም ከዚያም ወደኮሚኒዝም ያድጋል፣ ይህም የመጨረሻው ሥርዓተ አልባ ሥርዓተ ማኅበር ነው በሚለው ንድፈ ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ (Traditional Capitalism) ካፒታሊዝም የተባለው ሥርዓተ ማኅበር ደግሞ ሀብትን ብልጽግናን ካለገደብ የሚያበረታታ በኅብረትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ እስከተፈለገበት ደረጃ ድረስ በሀብት፣ መጐልበትን የሚፈቅድ ሥርዓተ ማኅበር ሲሆን፣ እነዚህ ሁለቱም ሥርዓተ ማኅበራት የራሳቸው ጠንካራና ደካማ የሕግ አካሄድ አላቸው።

ማርክሲዝም ቁሳዊ የታሪክ ትንታኔው የፈላስፎች ቀመር ሆኖ ምንም በአንዳንድ ታሪካዊ ለውጦች ላይ እውነት የሚመስሉ ሁኔታዎች ቢታዩም ህልዎተ እግዚአብሔርን የሞራልና የሥነ ሥርዓትን ክብር እና እውነት ያቃለለ በመሆኑ ሰባ ዓመት ሳይሞላው ወደፊት ይደረስበታል ከተባለው ሥርዓተ ማኅበር ኮሚኒዝም ሳይደርስ ተልከስክሶ ቀርቷል:: ይህም የማርክስን ቀመር ከግል ምኞትና ፍልስፍና እንዳይዘል አድርጐታል::

እንዲህ ሲባል የመደብ ልዩነትን ለማጥፋት የሚጥረው ማርክሲዝም ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው ማለት ሳይሆን በ(Collective enterprise) በጋርዮሽ ሥልጣኔ (ሥራ) ላይ መልካም ትንታኔን የሰጠ መሆኑ አይካድም (individual enterprise) የግል ጥቅምን ብልጽግናን በመካዱ ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ ሆኖ ግን እናገኘዋለን::

ካፒታሊዝም በአንጻሩ የጋርዮሽ ጥቅምን ሥልጣኔን ክዶ ግለሰቦችን ብቻ ስለሚያበለጽግ ሁለቱም ሥርዓተ ማኅበራት የየራሳቸው ደካማ ጐን አላቸው:: ስለዚህ የምዕራቡ ዓለም ለካፒታሊዝም ጥቂት ልጓም ይሆን ዘንድ በዴሞክራሲ ወርቃማ ሕግ አልሚነቱን ሲያጣፍጥ እናገኘዋለን::

በዚህ የፍልስፍና ውጣ ውረድ ውስጥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ምንን እና ማንን ትከተል ነበር::

> "The legendary ruler who had inspired Mandela as a boy of seventeen when he first heard how he stood firm against Mussolini's invading forces. Selassie was neither a socialist nor a capitalist, but he ruled over the one African nation that had always been independent, and was shrewdly encouraging and advising the leaders of the other new nations."



ማንዴላ ገና የአሥራ ሰባት ዓመት ወጣት ሳለ የሰማው ከሞሶሎኒ ወራሪ ኃይል ጋር በጥንካሬ ቆሞ የተፋለመው ዝነኛው መሪ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማንዴላን ቀስቅሶት ብርታት ሰጥቶት ነበር:: ኃይለ ሥላሴ ሶሻሊስት አልነበረም:: ካፒታሊዝም አልነበረም ግን ምን ጊዜም ተደፍራ የማታውቅ ነጻ አገር እና ሕዝብ ይመራ ነበር:: ሌሎቹንም የአፍሪካ የነፃነት መሪዎች ነጻ አገር ይፈጥሩ ዘንድ ለነፃነታቸው ይታገሉ ዘንድ ያበረታታ ነበር ብለዋል::

ኢትዮጵያ ማርክሲስት ካልሆነች ካፒታሊዝምንም ካልተከተለች በምን ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ነበረች? ብዙ ሰዎች ኢትዮጵያ ኋላቀር በሆነ የፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ነበረች ይላሉ::

እውነት ነው ወራሪዎችን ለመቋቋም ኢትዮጵያ በርዋን ዘግታ በነበረበት ዘመን ከኅብረት ሥልጣኔ ወደኋላ ቀርታ ነበር:: ከዓለም ተነጥላ ከብዙ ሥልጣኔዎች ተስተጓጉላ ነበር:: ግን ከማንኛውም ዓለም የበለጠ በእራስ መተማመንና በክፉ ባሕል ሳትከለስ ኖራለች:: በሕሊና ሥልጣኔም ረቂቅ የሆነ የዕድገት ደረጃ ላይ ነበረች::

ማርቲን ሉተር ኪንግ እንደተናገረው ሶሻሊዝም የኅብረት የጋርዮሽ ሥርዓትን ያበለጽግና የሰውን መሠረታዊ የተናጠል መብት ይክዳል ብሏል:: ካፒታሊዝም ደግሞ የተናጠል ሀብትን ብልጽግናን ያከብርና የጋርዮሽ ሕይወትን ያቀጭጫል::

የእግዚአብሔር መንግሥት የግለሰቦችንም ሆነ የጋርዮሽንም ጥቅም ማዕከል ያደረገ ሁለቱንም ያዋሀደ እውነቱን በማስታረቅ የሚመራ ሥርዓት ነው::

የኢትዮጵያም መንግሥት ከጥንት እንዲህ ያለ ነበር:: ከሞላ ጐደል ንጉሡም በዚህ የነፃነት ሕግ ይመሩ ስለነበር ዓለም በኢትዮጵያ እጅግ ይገረም፣ በነፃነትዋም ይኮራ፣ ይደሰት ነበር:: ብልጦቹ አባቶቻችን የዓለምን ግብስብስ ፍልስፍና ሳያጣሩ ወደ አገራቸው አያስገቡም ነበር:: አንድ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ከውጪ ያስገባናቸው ፍልስፍናዎች ሌላው ቀርቶ ሃይማኖቱ እንኳን ኢትዮጵያዊ ሆኗል:: ከኢትዮጵያዊነት ጋር ተዋሕዷል ብለው ነበር::

ይህንን ታላቅ አፍሪካዊ መንገድ በመከተላቸው እነ ንክሩሀማ የአፍሪካ መሲሕ ተብለው ነበር። ፕሬዝዳንት ሊዮፖልድ ሴንጐር በቅኔው ስለባሕላዊው የአፍሪካ አመራር ጽፈዋል። ጁሊየስ ኔሬሬ በሰላም ታንዛኒያን የመራበት መመሪያ የምዕራቡን እና የምሥራቁን ከራሱ ባሕል ጋር አዛምዶ ነበር። ይህ ሁሉ የነፃነት ደወል የተስተጋባው በዚህ ዘመን በሚናቁ በሚንቋሸሹት ከራሳቸው ነፃነት አልፈው ለመላው አፍሪካ በተረፉት በእኛ ሽማግሌዎች ነው።

ስለዚህ የገዛ አገራችንን ሕግ ልንቆፍር ይገባናል። ረጋ ብለን የዓለምን ደገኛ ሕግም በእኛ ሕግ ላይ መደመሩ አይከፋም፤ ግን ሀብታሞቹ አገሮች ሁሉ ፍትህም ለፍኖባቸዋል ብሎ ማሰብ ስህተት ነው። ከሌሎችንም መልካሙን መውሰድ አለብን። ለምን የምዕራቡ ዓለም የፖለቲካ ፀጥታ ተረጋጋ መመርመር ያለበት ጉዳይ ነው። ሌላ ምሥጢር የለውም የዛሬ 200 ዓመት የተፈታው ችግር ተደጋግሞ እንዳይከሰት በሕግ ስለታሠረ ነው።

እስቲ በዚህ ዘመን ያለችውን ልዕለ ኃያል አገር አሜሪካንን የሥነ መንግሥት አወቃቀር እንመልከት፤ እንዴት በሕግ ሁሉን አስታረቁት?

ሕብ በሉ የእኛ ኅብረተሰብ የተፈጥሮ ሕግጋት እንዳሉ ሆነው የውጪው ዓለም እኛ ልንፈታው ያልቻልነውን ችግር እንዴት ሊፈታ ቻለ? የእኛ ችግር ሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋም ነው፤ የእኛ ችግር ሕግን ማስፈን ነው፤ የእኛ ችግር መዋዕለ ነዋያችንን ማሳደግ ነው፤ እነዚህ ታላላቅ ክንውኖች ሊስተካከሉ የሚችሉት አጠቃላይ ሕግ (Constitution) ሲኖረን ብቻ ነው። ለዚህም ከእኛ ቀድመው የነቁ ለገዛ አገራቸው ምን ዓይነት ብልሃት ነድፈዋል?

ከሁሉ በፊት ግሪኮቹ ከክርስቶስ ልደት በፊት የተራቀቁበት የዴሞክራሲ መርህ ከግለሰብ ጀምሮ የሥነ መንግሥት አወቃቀርን ሁሉ በሚገባ የሚተነትን በመሆኑ ከሞላ ጐደል ምዕራቡ ዓለም የሥልጣኔዉ ምንጭ ነው የሚለው ይህንኑ ሥርዓተ ማኅበር ነው። ከምዕራቡም ዓለም አሜሪካ በአገሯ ውስጥ የዴሞክራሲ ዕቅድ ከሞላ ጐደል ለማሟላት ስትጥር ትታያለች።



ይህ ዕቅድ የተጀመረው እንዴት ነው? አሜሪካ በኮሎምቦስ እንደ አዲስ ምድር በተገኘች ጊዜ ቀይ ሕንድ የሚባሉ ሕዝቦች በስፋት የሚኖሩባት ያልሠለጠነች ሰፊ ምድር ነበረች። ከተመሠረተችም ከተገኘ ችም 300 ዓመትዋ ነው። እስከ 1776 እኤአ ድረስ ይህች አገር በእንግሊዛውያን ቅኝ ሥር ትተዳደር ነበር። በዚህ በቅኝ አገዛዝ ዘመን እንግሊዞች በወታደራዊ ኃይል ነጮቹን ሳይቀር ረግጠው ይገዟቸው ስለነበር በአንድ ታላቅ መንግሥት ጥላ ሥር በአንድነት መኖርን ጠልተ ውት ነበር።

የመጀመሪያው የነፃነት አዋጅ ስምምነት ከተፈረመ በኋላ 13ቱ ግዛቶች (confederation) የተባለ ላላ ያለ ኅብረት መሠረቱ፤ ከላይ እንደተ ጠቀሰው የውጭ ወራሪ ሲመጣ ሠራዊት ከሞላ ጐደል እያዋጡ የንግድና የአስተዳደር ሥርዓቱ የተለያየ ሆኖ የይስሙላ ኅብረት መሥርተው የነበሩበት ምክንያት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

እውነተኛ ጥምረት ብንመሠርትና ማዕከላዊ መንግሥት ብናቋቁም፤ ማዕከላዊው መንግሥት ከመጠን በላይ ኃይል ይሰማውና ከእንግሊዝ መንግሥት ያዳንነውን ነፃነታችንን ይቀማናል። ስለዚህ ግዛታችንን እያስተዳደርን ላላ ያለ ግንኙነት ብንመሠርት ይበጃል ብለው ተስማሙ።

በ1787 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ፊላዴልፍያ በተባለው ከተ ማ (Confederation) የተባለውን ውል ለማዳበር እና ለመቀየር ስብሰባ ተደረገ። የኮንፌዴሬሽኑን ዐረፍተ ነገሮች ከመለወጥ ይልቅ አዲስ ዕቅድ ለማዘጋጀት ታላላቅ የአሜሪካን መሪዎች ጀምስ ማድሰን፣ ሞሪስ፣ ቤንጃሚን ፍራንክሊን፣ አሌክሳንደር ሂመልተን እና ጆርጅ ዋሽንግተን ተስ ማሙ።

አዲሱ ዕቅድ ፌዴራል አስተዳደሩ ሦስት ቅርንጫፎች ያሉት ሆኖ ተቀረፀ። ይኸውም የሕግ መምሪያ፣ የሕግ መወሰኛና የሕግ አስፈጻሚ ክፍል ነው። ሌላው ታላቅ ፈተና ታላላቅ ግዛቶች (States)

በሕዝባቸው መጠን ልክ በምክር ቤቱ ውክልና እንዲኖራቸው መፈለጋቸውና አነስተኛ ሕዝብ ያላቸውም እኩል ድምጽ እንዲኖራቸው መፈለጋቸው ነበር፡፡ ይህም ችግር ምክር ቤቱን ለሁለት በመክፈል ተፈታ የተወካዮች ምክር ቤቱ በየግዛቱ ባሉ ሕዝቦች ብዛት ልክ የሚወከልበት ሲሆን፤ (Senete) ሴኔት የተባለው ደግሞ ግዛቶቹ እኩል ውክልና እንዲኖረው ተደረገ፡፡

በባርነት ውስጥ ያሉ አፍሪካ አሜሪካዊያን በምክር ቤተ እንዲወከሉ በምዕራቡ ግዛት የተነሳው ጥያቄ በሰሜኑ ተወካዮች ተቀባይነት ስላላገኘ በማከያው አንድ ጥቁር እንደ ሦስት አምስተኛ ሰው የአውሮፓ አሜሪካውያን ተቆጥሮ ይመርጣል በሚል ተስማሙ፡፡ ይህ ሊያስቆጨንና ሊያንገበግበን የሚገባ ጥቃት ነው፡፡ ግን ዘወር ብለን የገዛ አህጉራችንን ሁኔታ ስናይ ዛሬ መላው አፍሪካ ድምጹን አሰምቶ እንኳን የገዛ መሪውን የመምረጥ መብት አለው ወይ? ስንል ከአውሮፓ የመጡ አሜሪካውያን 3/5ኛውን አፍሪካ አሜሪካዊ መብት ማክበራቸው ከአፍሪካ መሪዎች የተሻሉ አስብሏቸዋል፡፡

ዕድሜ ለአብርሃም ሊንከን እና ለእነማርቲን ሉተር ኪንግ ትግል በዚህ ዘመን ማንኛውም አፍሪካ አሜሪካዊ በሙሉ ድምጹ መምረጥ ችሏል ይመረጣልም፡፡ ከዚህ ሁሉ ውሣኔ በኋላ እልባት ያላገኘው ልዩነትና አንድነትን በሚቀበሉ እና በማይቀበሉ መካከል የተፈጠረው አለመግባባትን ማስታረቅ ነበር፤ ዋነኛ ሁኔታ ሆኖ የቀረበው፡፡ ልዩነትንና አንድነትን የሚቀበሉ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት መመሥረትን የሚያክል መልካም መንገድ እንደሌለ የዛሬዋን አሜሪካንን በመመልከት ብቻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ጠንካራ የራስ ገዝ አስተዳደርን የመረጡት በምን ችግር ምክንያት ነው ብለን ብንጠይቅ፡፡ እባብን ያየ በልጥ በረየ እንደሚባለው በጠንካራ ማዕከል ይገዟቸው የነበሩት እንግሊዞች ባደረሱባቸው ፍርሃት ምክንያት ነበር፡፡

ስለዚህ ይህ ጥያቄ በመላው የአሜሪካ ሕዝብ ይወሰን ዘንድ ሁለት ተጻራሪ መስመር የተሰለፉ ተከራካሪዎች ለሕዝቡ ሐሳባቸውን



እንዲያሰሙ ሆኖ በሕዝብ ውሳኔ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የሚለው ሐሳብ ቢጸድቅም የራስ ገዝ አስተዳደሩም ሐሳብ ተሸቀንጥሮ አልተጣለም፡፡

እያንዳንዱ ግዛት በመዋዕለ ነዋይ ግሥጋሴው በውስጣዊ ጥቃቅን ሕግጋት ሁሉ ነጻ ሆኖ እንዲተዳደር ፖሊስን በመቅጠር ለማዕከላዊው መንግሥት ሠራዊት በማዋጣት የየግዛቱን ነፃነት እንዲጠብቅ ሲደረግ የጋራ ፕሬዝዳንት ከመምረጥ ጀምሮ ዜጉች ከቦታ ቦታ ይዘዋወሩ ዘንድ በግዛቶች መካከል ቀረጥ ሳይኖር በኅብረት መሥራትን እያሳደጉት መጡ፡፡ ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ ግን በጐሣ፣ በሃይማኖት ተከፋፍሎ መቆምን ፈጽመው አልሞከሯትም፡፡ የጐሣ ፖለቲካ ማራመድ እንደ ሱማሌ አስተዳደር መዝቀጥ ነው፡፡ በጐሣ ፖለቲካ መሠልጠን የሩዋንዳን እልቂት መጋበዝ ነው፡፡

ታላላቆቹ የዓለማችን ፖለቲከኞች ፈጽመው የጐሣንና የሃይማኖትን እሳት አራግበው አያውቁም፡፡ ከዚህ አደጋ ሕዝባቸውንም ሒሊናቸውንም ሲያርቁ ነው የታየው፡፡ ይልቅ የኤርያን ዘር ነኝ፤ የደች ሕዝብ ትልቅ ነው ያለው፤ የሴም ዘሮች ማለቅ አለባቸው ብሎ ያወጀ 16 ሚሊዮን ሕዝብ የጨፈጨፈ ዘረኛው ሒትለር ነው፡፡ የዘርን ፖለቲካ የሚያራምድ የሰው ዘርን ለማጥፋት የተዘጋጀ ሒትለራዊ ነው፡፡ አሜሪካውያን ሕግ ሲያወጡ የዘርን ነገር ነክተውት አያውቁም፡፡ የጐሳዎች ነፃነት የሚረጋገጠው የግለሰቦች መብት በሚገባ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የአንድ ሰው ምርጫ ዋጋ ሲኖራት ብቻ ነው፡፡ ዴሞክራሲ ከዘር ፖለቲካ ጋር ፈጽሞ አይነካካም ሁለቱም በተጻራሪ አቅጣጫ ነው የሚሄዱት፡፡

የጐሣ ፖለቲካ በቱትሲ እና በሁቱ ጐሣ መካከል የነበረውን እልቂት የሚያስከትል አጋንንታዊ መንገድ ነው፡፡ የዘረኝነት ወታደሮች ፋሽስቶች፣ ናዚዎች ናቸው፡፡ የጐሣ አርበኞች ኢንተርሀምዌ ናቸው፡፡ የጐሣ ፖለቲካ (The circle of hatred) የጥላቻን ቀለበት የሚፈጥር አንዱ ሲያጠቃ አንዱ ሲበቀል መኖሩ ለዘመናት የማይለቅ ክፉ የሞት መንፈስ ነው፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደዚህ ዓለም ሁሉ ከሩቅ ወደሚሸሸው ጽልመት ድቅድቅ ጨለማ እንዳይገባ በእግዚአብሔር ስም እንማጸናለን፡፡ በጐሣ ፖለቲካ አሸናፊ ስለሌለ የዋሆች መሆን አይኖርብንም፡፡

ከዚህ በተረፈ ግን አካባቢያችንን ለማሳደግ መጣራችን እንደውም ማዕከላዊውን መንግሥት ያጠናክረዋል እንጂ ጉዳት የለውም። አካባቢን ከአካባቢ የሚያቆራኝ፣ የሚያዛምድ አዲሱ መንገድ የመዋዕለ ነዋይ ትስስር በመሆኑ ይልቅ በዚህ መስክ መበልጸግ ይጠበቅብናል።

ሕዝባችን በቆየ ታሪኩ በአስተዋይነቱ ሁሉን መርምሮ ከክፉ የሚሸሽ በመሆኑ ጠላቶቹ ያለሙለት ቀለበት ውስጥ እንደማይወድቅ ተስፋ አለን። አዳዲሶቹ የአፍሪካ መሪዎች ከቅኝ ገዢዎች ሲላቀቁ አልመውት የነበረው የተባበረች አንድ የሆነችውን አፍሪካን ነበር። በዚህ ዘመን ግን የተቆራረጡትን ትንንሽ አገሮች እንኳን የባሰ የሚበጣጥሱ ደካሞች የተፈጠሩበት ዘመን ነው።

ድሮ አንድ አፍሪካ ብለው የተነሱ ታላላቅ ሰዎች ነበሩን። ዘንድሮ ግን ፓን ሁቱ ወይም ፓን ቱትሲ ብለው ለጉጣቸው የቆሙ ልፍስፍሶች ተፈጥረዋል። ግን ሕዝቦች እንደ ሕዝብ ማንንም በዘርም ሳንለይ ሳንጣላ በአንድነት መቆማችን የሕልውናችን መሠረት መሆኑን መረዳት ይገባናል።

ከሕገ መንግሥት ጋር ስንታረቅ ብቻ የሰከነ አስተዳደር ይኖረናል። ሽር ሳይኖር በእርግጠኝነት ቢበዛ ለሁለት ፈረቃ ብቻ የሚመረጥ መሪ ከመ ረጥን በዚህኛው መሪ ብንከፋ በሚቀጥለው ልንደሰት እንችላለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ከዚህ ሁሉ ጋር መታረቅ አለብን።

ከግለሰብ ጀምሮ ማኅበረሰቡ ከዚያ በላይም መንግሥት በሕግ የተ ወሰነ መብት ይኖራቸው ዘንድ ሕግ የበላያቸው እንዲሆን ያስፈልጋል። የፖለቲካው መስመር ሥርዓት እንዲይዝ ሕዝብ የመከረበት ሕገ ደንብ ያስፈልጋል። አብርሃም ሊንከን እንዳለው እኛም «government of the people, by the people, for the people» ልንል ያስፈልጋል። «የሕዝብ አስተዳደር፣ በሕዝብ የተመረጠ አስተዳደር፣ ስለሕዝብ የተመረጠ አስተዳደር» በዚህ ሁሉ ግን የየግላችን ሥርዓት ወሳኝ ነው። ያም ከሕግ ጋር በጽኑ መታረቃችን ነው።



# ምዕራፍ ስምንት

## ከሥነ ጥበብ ጋር መታረቅ

የደቡብ አፍሪካው የአሁኑ ፕሬዝደንት እምቤኪ ቶኪዮ ውስጥ በ1998 ዓ.ም. ስለአፍሪካ ንግድ ሁኔታ ሲናገሩ በመሀሉ ስለታላቁ የቱሪዝም ሞተር ስለሥነ ጥበብ ሳይናገሩ አላለፉም። «ከአፍሪካ አዲስ ነገር ጠብቁ» ብለው ስለ ጥንታዊ ቅርስዋም ዝና አንስተው ነበር። ዓለማችን ከሚደነቅባቸው ታላላቅ የሥነ ጥበብ ውጤቶች የግብጹ ፒራሚድ ካሉ በኋላ በናይጄሪያ ያለው ቤኒን ውስጥ የተሠራው እንዲሁም በኢትዮጵያ ያለው ታላቁ የአክሱም ሐውልት ማሊ የሚገኘው የቲምቡክቱ መጽሐፍ ቤት እያሉ የአፍሪካን ቅርስ ተንትነው በአህጉራቸው ያላቸውን የጥበብ ኩራት ተናግረዋል።

ሥነ ጥበብ እና ኢትዮጵያ ጥንታዊ ዝምድና አላቸው። ሕልቆ መሳፍርት የሌለው የሰው ልጅ የአእምሮ ውጤት የሚታፈስባት ኢትዮጵያ መሆንዋን ይኸው እነ እምቤኪ ሳይቀሩ ጃፓን ድረስ እየሄዱ እያወጁ ናቸው። ስለዚህ ለኢኮኖሚያችን ታላቅ አስተዋፅዖ ሊሰጥ ከሚችለው ሥነ ጥበብ ጋር መታረቅ ይኖርብናል።

እርቁ በሁለት ይከፈላል። አንደኛው አባቶቻችን የሠሩትን በየጉሳው ውስጥ ያሉ ጠቢባን የቀረጹትን፣ የሸመኑትንና የሳሉትን በወጉ በሥርዓቱ መያዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው የትውልዱን የሥነ ጥበብ ዝንባሌ በሰ ቅድ የሥነ ጥበባት ማዕከላትን ት/ቤቶችን በማስፋፋት ከሥነ ጥበብ ጋር መታረቅ ነው። በመጀመሪያው እርቅ እንጀምር ቅርሶቻችንን የተረሱትን እንዴት እንንከባከብ እንጠብቅ እንጠቀምባቸው? የሚለው ይሆናል። በእጅ ያለ ወርቅ እንደመዳብ ይቆጠራል እንደሚባለው የእኛን ጥንታዊ ቅርስ የታሪክ ዝና የባሕል ሀብት እንደተራ ነገር ካልቆጠርነው ያሉንን ቅርሶች እያስጎበኘን ብቻ ከፍተኛ ገቢ በዓለም አቀፍ ደረጃም ዝናን መጎናፀፍ እንችላለን።

ከአክሱም ጀምሮ ጐንደር፣ ወሎ፣ ጐጃምና ሸዋ የሰፍዑመር ዋሻ በጥልቀት ቢሠራባቸው ለብዙ ሕዝቦች የዕለት ጉርስ ለትውልድም መመኪያ ይሆኑ ነበር። ለምሳሌ የአክሱም ሐውልት ከአካባቢው ጽዳትና ውበት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሐውልቱን የሚያጐሉ ተጨማሪ የመዝናኛ ሁኔታዎች አልተፈጠሩበትም። በዙሪያው ያሉ መንደሮች ታላላቅ የታሪክ ክልሎችም ቢሆኑ እንኳን ለምርምርና ለመጐብኘት ነጻ ይሆኑ ዘንድ ቢደረግ ያልተገመቱ የተደበቁ ሌሎች ቅርሶች መገኘታቸው አያጠራጥርም። የወደቁት ድንጋዮች የአካባቢው ግርማና ድባብ ይህ ቦታ ካለምርምር ዝም ተብሎ የሚታይ እንዳልሆነ ይጠቁማሉ፤ አክሱም ከርሰ ምድር ወስጥ የተደበቀው ምን ይሆን? ከመሬቱ በላይ ያንን የሚያክል ሐውልት ካየን ዘንዳ በጦርነት ወይም በጊዜ ብዛት የተዳፈነ የተቀበረው ምን ያህል ነው? ብለን ልንጠይቅ ይገባል።

ያለውንስ እንዴት እንጠቀምበት? ከላይ እንደጠቀስነው ለቱሪስቶች ይስብ ዘንድ በሙያተኞች ሊዘጋጅ ይገባዋል። የቦታውን ታላቅነት ወይም ምንነት የሚያስረዱ መጣጥፎች በተለያየ ቋንቋ ሊዘጋጅ ይገባል። መጻሕፍት እና መጽሔቶች የመሳሰሉት ተዘጋጅተው ቢቀመጡ ከሚጐርፈው የቱሪስት ብዛት አንጻር ምንኛ ሀገራችንን ባስተዋወቃት ገንዘቡም ለሀገር በጠቀመ ነበር። አክሱምን የሚያክል የታሪክ ቦታ እጅግ ትንሽ ቤተመዘክር ነው ያለው። ታላላቅ ሙዚየም ሊዘጋጅለት ይገባል። ሕፃናቱ እና አዛውንቱ ከእንጨት እየፈለፈሉ የሚያዘጋጁዋቸው የአክሱም ምስሎች አይከንስ እና ስዕሎች እንደዋዛ መታየታቸው አግባብ አይደለም። በተደራጀ እና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ቢቀናጅ ከታላላቆቹ የቱሪስት ከተሞች ያላነሰ እንቅስቃሴ በፈጠርን ነበር። ከቅርሶቻችን ጋር እንታረቅ።

እነዚህ ቦታዎች በጥንቃቄ እንዲጠበቁ ደረጃውን የጠበቀ ሆቴልና ሌላም የመዝናኛ ሁኔታዎችን ማቀናጀት ይቻላል። እንዲህ ሲባል ቦታዎቹ ቅዱሳት መካናት ናቸውና፤ ቡና ቤቶችን እና የመሳሰሉትን የኃጢአት ንግዶችን ማከናወን አይገባም። ይህም አንዱ መስሕብ ነው። በዓለማችን ብዙ ለነፍሳቸው ፀጥታን የሚመኙ ከሁከት ከቁማር ይልቅ መልካም ቦታዎችን በማየት የሚረኩ እጅግ ብዙ ናቸው።



የቱሪዝም ጠባይ እራሱን የቻለ ጥናት የሚፈልግ ነው ለግንዛቤ ያህል በአብዛኛው ቱሪስቶች በዕድሜ የገፉ ናቸው። ከ65 ዓመት በላይ እነዚህ አዛውንቶች ዕድሜአቸውን ሙሉ በሥራ ያሳለፉ ለጡረታቸው ከፍተኛ ገንዘብ ያከማቹ ከ60 በመቶ በላይ የሆነውን የጐብኚ ቁጥር የሚሸፍኑ ናቸው። ስለዚህም ለመጐብኘት በሚመጡበት ጊዜ አስተማማኝ መጓጓዣ ንጹሕ የመኝታ ቤት አስደሳች የአካባቢ መዓዛ እና ጥሩ ጸጥታ ይፈልጋሉ። ለብቻቸው ሆነው የሚመረምሩት፣ መጽሐፍ የሚያነቡበትና የግል ፈቃዳቸውን የሚያከናውኑበት ጊዜ ይፈልጋሉ። አካባቢውን ከጐበኙ በኋላ ለአያያዝ የሚመቹ የአካባቢውን ታሪክ እና ቅርስ የሚያሳዩ ትንንሽ ምስሎችን ይፈልጋሉ። መጻሕፍትንና በራሪ ወረቀቶችን፣ ፖስት ካርዶችን በብርጭቆ በስኒ እና በሣህን ላይ የታተመ በካኒቴራ፣ በሹራብ፣ በቁታና በተለያዩ ሁኔታዎች የተዘጋጁ ምስሎችን ይዘው ለመሄድ ይጓጓሉ።

እኛ ግን ይዘን የምንጠብቃቸው የሚለምኑ ሕፃናት፣ ቅንጅት የሌለው የተዝረከረከ ቤተመዘክር ነው። አስጐብኝዎቹ ሳይቀሩ ከሥራ ገበታቸው ሳይሆን ከመንደር ተፈልገው ነው የሚገኙት። በቂ የመኝታ ክፍል፣ ፀጥታ እና መረጃ ፈጽሞ የለም ቢኖርም አያረካም። ኢትዮጵያን ከውጪ በዝና ሰምቶ የመጣ ጐብኚ በዝንብ እና በቢምቢ የተወረሩ ሆቴሎች ውስጥ ሲበሳጭ አድሮ ጠዋት ከኋላው እንደግሪሳ ወፍ የሚያጅቡትን ሕፃናት፣ የችግረኛው ልመና እና ወከባ፣ በእውነቱ በእርጋታ ሊጐበኝ ለመጣው እንግዳ ጐብኚ እረፍት የሚያሳጣ ነው።

ችግረኞች መረዳት አለባቸው። ግን እንዴት? በአንድ ገዳም አካባቢ ያሉ ተረጅዎችን ስም ዝርዝር መዝግቦ የድሆች መርጃ ሣጥኖችን አዘጋጅቶ ጐብኝው እግረ መንገዱን እንዲመለከታቸው በማድረግ ሳይረበሽ የተቻለውን ለግሶ መሄድ ይችላል። ነገር ግን እየተርገበገቡ የሚለምኑ ሕፃናትን እጅ ዐይቶ ሕሊናው አዝኖ ከሚሄድ በስተቀር ለታላቁ የቱሪዝም ኢንዱስትሪያችን የሚያበረክተው አስተዋፅዖ እጅግ ደካማ ነው የሚያደርገው። ሌላው ቀርቶ በልመና የሚተዳደረውን የኅብረተሰብ ክፍል በየአቅሙ የእጅ ሥራ እየሠራ ለጐብኝ እንዲያቀርብ ማድረግ ቢቻል ካለጥርጥር ከፍተኛ ጥቅም በተገኘ ነበር።

በአጠቃላይ በገዳማቱ እና አድባራቱ በወንዞቻችንና በሐይቆቻችን ተስቦ የሚመጣውን ቱሪስት ነጻ አድርገን አስደስተን መጠቀም ስንችል፤ አንደኛ በተዝረከረከ አሠራር፤ ሁለተኛ ለሙያው ባዕድ በሆኑ አስጎብኝዎች፤ ሦስተኛ ለጉዳዩ እምብዛም ባልተጨነቀ ሁኔታ መረጃ ዎች እና የሥነ ጥበብ ውጤቶችን ማቅረብ ባለመቻላችን ብዙ ሲሳይ እያመለጠን ይገኛል:: ይህ መስክ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ክፍት ሆኖ ኅብረተ ሰቡ ሥርዓት በተከተለ ሁኔታ ከገዳማቱ፣ ከአድባራቱ ራቅ ባሉ ከተሞች ቢንቀሳቀስ ከፍተኛ ጥቅም ሊሰጥ ይችላል::

ይህም ገዳማቱ እና አድባራቱ በንግድ እንዳይጥለቀለቁ ያደርጋቸዋል:: ምንም ቢሆን እነዚህ ቅዱሳት መካናት በፀጥታ ለጎብኝዎች ክፍት ከመሆን በስተቀር ሊነገድባቸው አይገባም:: ግን በአቅራቢያቸው ባሉ ከተሞች ስለጥንታዊ ቅርሶቻቸው የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን በመሸጥ ኅብ ረተሰቡም መንግሥትም ሊጠቀሙ ይገባቸዋል:: ይህም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር በቅንጅት በመሥራት ነው::

ለዚህ ሁሉ ሥራ መንግሥት በሙያው የሠለጠኑ እና ለለውጥ የተዘጋጁ የሞቀ መንፈስ ያላቸው ባለሙያዎች ሊመድብ ይገባል:: ቤተ ክህነቱም በዚህ ጉዳይ የሠለጠኑ፣ ለቅርሶቻችን የሚቆረቆሩ፣ ሥርዓት የሚያሲዙ፣ በማስተርጎምና በመጻፍ የተካኑ ሙያተኞችን መጠቀም ይኖርበታል:: በየገዳማቱ ተዘዋውሮ ለተመለከተ በአቅማቸው በጥሩ ብቃት መግለጫ የሚሰጡ መነኮሳትን በማየታችን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: በተለይ አብርሃ ወአጽብሃ ገዳም ውስጥ ጥሩ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው አስጎብኝ እንደነበሩ የሚታወስ ነው:: ይህ ብቻ ሳይሆን በታሪክ ዕውቀታቸው በአገላለጽ ስልታቸውና ትህትናቸው ጎብኝዎች ሲረኩ አስተውለናል:: እንዲሁም በጣና ገዳማት ውስጥም ይህንኑ አይተናል:: ደብረ ሊባኖስም ጥሩ ባለሙያ አይተናል::

ታዲያ እነዚህ ሕይወታቸውን ለዚህ ግልጋሎት የገበሩ ሌሎቹም አበው ጥቂት የሞያ ዕገዛ ቢደረግላቸው ቋንቋውን እንዲማሩ ቢታገዙ በገዳማት በኩል ያለው ችግራችን በተቃለለ ነበር:: የሚያስገርመው እነዚህ



አባቶች ለአንዲት ደቂቃ ከቦታው የማይለዩ በተጠየቁበት ጊዜና ቦታ የሚገኙ እጅግ ትሁታን በመሆናቸው ጎብኝዎች ከአክብሮት የበለጠ በቅድስናቸው ሲገረሙ ለማየት ችለናል:: እርቅ የሚያስፈልገው ከእነዚህ የሕይወት መስዋዕትነት ከከፈሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ሁሉ ነው::

ሌላው በየገጠሩ ያሉ ሕፃናት እና ወጣቶች ቱሪስቱን ከመላመዳቸው የተነሣ ጥራት ያለው እንግሊዝኛ፣ ፈረንሣይኛ ሌላውንም ቋንቋ ሲያቀላጥፉት መታየታቸው ነው:: እነዚህ ሕፃናት አሁንም ጥሩ ክትትል ከተደረገላቸው የዚህን ሙያ ሊካኑት ይችላሉ::

በነገራችን ላይ የአስጎብኝው ችግር የሆቴሎቻችንን ጥራትና አጠቃላይ ዝግጅታችን ደካማ መሆኑን ለማየት በ1999 ዓ.ም. እንደ ፈ ረንጆቹ አቆጣጠር ሔነሪ ሊዮስ ጌትስ የተባለ የሀርቫርድ ፕሮፌሰር በ'ቢቢሲ በመረዳት መላው አፍሪካን ዞሮ በፊልም በመቅረጽ ለዓለም አስተ ዋውቆ ነበር:: የፊልሙ ርዕስ Wonders of the African world የሚል ነው:: በዚህ ፊልም ላይ በየአፍሪካ ከተሞችና ገጠሮች ተዘዋውሮ ስለጥንታዊ የታሪክ ቅርሶቹ ጥናታዊ ፊልም አዘጋጅቶ ነበር:: ማንም ሰው እንደሚታዘበው የወንድሞቻችን የሌሎች አፍሪካ አገራት አስጎብኝዎች ጥራትና ስሜት ከእኛዎቹ ጋር ሲነጻጸር እጅግ የተራራቀ ነው:: ይህ አፍሪካዊ አሜሪካዊ ፕሮፌሰር ስለአፍሪካ ተቆርቁሮ በተዘዋዋሪም በወገኖቹ ትምክህት ተሰምቶት ነው የመጣው:: ግን እንሰጠው የነበረ መረጃ ውስን ነበር እራሳችንንም ለመግለጽ ፈጽሞ አልቻልንም ነበር::

በተለይ አንዷ አስጎብኝ መነኩሲት ለምን ቤተ ክርስቲያኒቱን እንደተጠጉ መንፈሳዊ ዓላማቸውን እንኳን ማብራራት ተስኗቸው ስናይ ሐፍረት ነው የተሰማን:: ካሕናቱ በብሩህ ሕሊና ለማብራራት መስቀል ይዘው ሲመጡ ስለታቦቱ ጽዮን በካሕናቱ ሕሊና የጥርጣሬ መንፈስ ወይም የማቃለል ዘዬ ያለው «ታቦቱን ማየት እችላለሁ» የሚለውን ዐረፍተ ነገር አስተርጉሞ የካህኑን ስሜት መለወጥ በዚህም ሁኔታ ካህኑ «ታቦቱ የሚታየውማ ኃይሉን ሲገልጽ ነው» ብለው እንዲቆጡ የሚያደርግ አቀራረብን አስጎብኝዎች ማዋዛት ሲችሉ በግርድፉ ማቅረባቸው ቱሪስትና ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዳይቀራረቡ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ተመልክተናል::

ሀብት በሩን እንኳኩቶ እየመጣ ልንጠቀምበት አልቻልንም:: ይህ ፕሮፌሰር ከብዙዎች አጥኚዎች የሚለየው አፍሪካዊ በመሆኑ ነው:: በታላቅ ዓላማ የአፍሪካን ቱሪዝም ሊያስተዋውቅ የመጣ በአሜሪካ መንግሥት የመገናኛ ብዙኃን የታገዘ ግለሰብ ነው:: ይህ ፊልም በተ ከታታይ ሣምንቶች በመላው አሜሪካ ለሕዝብ የቀረበ ትዕይንት ነው:: ታዲያ ሌሎቹ የአፍሪካ አገራት በዕድሉ በእጅጉ ሲጠቀሙ እኛ ግን ዝርክርክነታችንን ለዓለም አሳይተናል:: ያም ቢሆን ከሒልተን ሆቴል መዋኛ ጀምሮ የእነ ዓባይ የስሜን ተራሮች በሌሎቹም ቅርሶቻችን ዓለምን አስደምመናል::

ተፈጥሮ ያደለችንን በተራራ የተከበበ መልክዐ ምድር የፏፏቴውና የሰፍዑመር ዋሻ የእነ ሻላ፣ ላንጋኖ፣ ወንዶ ገነት፣ አዋሣ እና ሌሎቹም ውብ ሀብቶቻችን በእውነት ቢሠራባቸው የእኛን ችግር ማቃለል አያቅታቸውም::

ቅዱሳን አባቶቻችን ድንጋይ አለዝበው እና ጠርበው ቋጥኙን አለስልሰው ገርተው ፈልፍለው ያቆዩልን ቅርሶች፣ እንዲሁም በ1181 ዓ.ም. አካባቢ ነግሦ የነበረው ቅዱስ ላሊበላ አሥራ አንድ አብያተ ክርስቲያናትን የሠራበት የሥነ ጥበብ መንገድ በአንድ በሙያው በሠለጠነ አርክቴክት ወይም መሐንዲስ ቢመረመር እና መጽሐፍ ቢጻፍ ስንት መጽሐፍ ይወጣዋል ብለን እንገምት:: ይህ በብዙ ቋንቋዎች ቢጻፍስ?

ቤተ ደናግል፣ ቤተ ማርያም፣ ቤተ መድኃኔዓለም፣ ቤተ መስቀል፣ ቤተ ጐልጐታ፣ ቤተ ሚካኤል፣ ቤተ ገብርኤል፣ ቤተ አባ ሊባኖስ፣ ቤተ መርቆሬዎስ፣ ቤተ አማኑኤል እና ቤተ ጊዮርጊስ:: እያንዳንዳቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሚመረቁ አርክቴክቶች ምን ያህል ጥናት አድርገውባቸዋል? ለተማራማሪዎች እንቆቅልሽ የሆኑ በዘመናዊው ካስቲንግ ወይም በተለየ ጥበብ ተሠሩ የማይባሉት የድንጋይ ላይ ጌጣጌጦች እንኳን ብዙ ጥራዝ አይወጣቸውም ወይ? ከሥነ ጥበብ ጋር እንታረቅ::



እኛ እኮ ብርቱ ብንሆን ኖሮ ስምንተኛው አስደናቂ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአክሱም ሐውልት ወይም የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ:: እራስን መግለጥ ማሳየት ማክበር ብቻ ነው በዓለም ላይ የሚያስከብ ረው አንገቱን ያቀረቀረ ሲደፈቅ ነው የሚኖረው:: ሰዎች በሌላቸው ነገር ሲኮሩ እኛ አባቶቻችን የሠሩትን እንኳን ቀብረነው እንኖራለን:: ከሥነ ጥበብ ጋር እንታረቅ::

በየገዳማቱ ያሉ ቅርሶች ጥበቃ በዚህ ዘመን አስጊ እየሆነ ተገኗ ል:: በውጭ አገር ያለን ኢትዮጵያውያን ቅርሶቻችንን መልሰን በውድ ዋጋ ለመግዛት የተገደድንበት አጋጣሚም አለ:: በተለይ በአንድ ወቅት በቦስተን ከተማ አንድ ነጭ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አማኝ ጥንታዊ የመጾር መስቀል ሲሸጥ አግኝተን አዋጥተን ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲመለስ ያደረግንበት አጋጣሚ ትዝ ይለኛል:: ይህ መስቀል የ150 ዓመት ታሪክ ያለው ነው::

የብራና መጻሕፍቱ የሮማ አብያተ ክርስቲያናትን ሙዚየሞች አጣበዋል:: ጀርመንና እንግሊዝ ቅርሶቻችንን ሀብታቸው አድርገውታል:: በየቤተ መዘክሩ፣ በየመጋዘኑ፣ በየግለሰቡ ቤት የቤት ማድመቂያ ሆኖ የተ ቀመጠው ቅርስ ብዛት ቁጥር አይባልም:: ግለሰቦች ሳይቀሩ በግል ቤተ መዘክራቸው ዋጋ ያላቸው ጥንታዊ መጻሕፍቶቻችንን መስቀሎቻችን ወስደዋል፤ ታቦታቱ ሳይቀሩ እየተዘረፉ ነው:: እርቅ ይፈልጋል::

በቃጠሎ ያጣናቸው ደብረ ዳሞ እና አዲስ ዓለም ማርያም የነበሩ ቅርሶቻችን እንደዋዛ ተረስተዋል:: ዛሬም በአብዛኛው በጧፍ ብርሃን የሚገለገሉት ገዳማትና አድባራት ከሥራ ብዛት በእንቅልፍ ወይም በመርሳት እሳቱን ሳያጠፉት ቃጠሎ የሚነሳበት ዘመን ልፋት መና እየቀረ ነው:: በወሎ ክፍለ ሀገር ያለው የፍልፍል ቤተ ክርስቲያን በውሃ በመሸርሸር እየተናደ ከጥቅም ውጪ ሲሆን ይታያል::

አንዳንድ ጊዜም በዘመናዊነት ካለጥናት የምናድሳቸው በቆርቆሮ ልባስ የምንተካቸው የሣር ክዳኖችና የመሳሰሉት ልማት የመሰሉ ጥፋቶች በባሕል ሚኒስቴር በቤተ ክህነት ባለሙያዎች ለዕደሣም ሆነ ለመሳሰሉት ሁኔታዎች ጥንቃቄ ወይም ሙያዊ እገዛ ሊደረግ ይገባል::

በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን የተደረገው ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያኑ በአጸድ የተከበበ አስፋልት የሌለው በመሆኑ የግቢው ሣር እራሱ ውበት እንደነበረ በልጅነታችን የማንረሳው ትዝታ ነው። ግን የግቢው አፀድ እየተቆረጠ በአስፋልት መተካት ጀመረ።

በቅኔ ማኅሌቱ በመቅደሱ እና ቅድስቱ ወለል ላይ የተነጠፈው የበኻ ድንጋይ በአህያ እየተጫነ ከሩቅ ቦታ እንደመጣ አባቶቻችን ሲናገሩ እንሰማ ነበር። ይህ ድንጋይ ቅዝቃዜ የሌለው ውበት የነበረው ትልልቅ ነበረ። በጊዜው የነበረ ባለሙያ በጥናት ያስቀመጠው ድንጋይ አንድ ሰበካ ጉባኤ በማዘዝ ከመሬት እየተፈለፈለ እንዲነሳ በሲሚንቶ ንጣፍም እንዲተካ አዘዘ። ይህ ሁሉ ሲደረግ ቤተ ክህነቱ አያውቅም ባሕል ሚኒስቴርም አያውቅ አይሆንምም ቢል የሚሰማው የለም። የብዙ ሕዝብ ቅርስ የሆነ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን በግለሰቦች ፈቃድ መልኩን እና ድባቡን ሲያጣ መመልከት አሳዛኝ ነው። ከሥነ ጥበብ ጋር እንታረቅ።

ከአንዱ ደብር ውስጥ ደግሞ ለ40 ዓመታት በግብዝና ያገለገሉ ቄስ ገበዝ ከጥንቃቄያቸው፣ ከታማኝነታቸው ብዛት ጥንታዊዎቹ አልባሳት በሣጥን ተቆልፈው እንዳይበሉ፣ በቁልፍ ተቆልፎባቸው ከመቆየታቸው የተነሣ በ40ኛው ዓመት ለርክክብ ሲወጡ ሁሉም በብል ተበልተው ወደ ዱቄትነት የተለወጡበት አጋጣሚ ይታወሳል። የሚያስገርመው ግን እኚህ ታማኝ ቄስ ገበዝ ለሚቀጥለው ተረካቢ ሲያስረክቡ የወርቅ ጽሕልና ጽናጽል ብሩሩ ሳንቃው በጥንቃቄ ሳይሠረቅ መገኘቱ በእውነቱ በካህናቶቻችን እንድንኮራ በመቃብር ያሉትን ነፍሳቸውን በእነ አብርሃም እቅፍ በሕይወት ያሉትንም በእምነ እንድናስታውሳቸው ያደርገናል። በቃላቸው የጠኑት የሥነ ጽሑፍ ሀብት በገዳማቱ ያኖሩልን ቅርስ ካላስመሰገናቸው ምን ያስመሰግናቸዋል? ከሥነ ጥበብ ጋር እንታረቅ ሲባልም ከእነዚህ ሁሉ ጋር ነው።

ግን ከላይ እንደጠቀስነው በአዲስ አበባ ደብረ ጽጌ በሌሎቹም አድባራት ያሉት ዓይነት የማስገብኛ የመስታወት ቁም ሣጥኖች ለደረጋቸው አላባሳቱን ከብል ከመሠረቅ ለገብኝም አመቺ የእይታ ሁኔታን በጥቂቱ ይፈጥራል።



ከዚህ ጋር የሚታሰብበት ዋነኛ ነገር የሥርቆቱ ጉዳይ ነው የዋሆች ካልሆንን በስተቀር አንድ ገዳም የያዛቸው መጻሕፍት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገንዘቦች ናቸው። በወርቅ የተሠሩ ዕቃዎች ጽላቱ እና የተለያዩ ቅርሶች ሃይማኖት ለሌላቸው ግለሰቦች ከገንዘብነት ውጪ ትርጉም የላቸውም። ኢትዮጵያን አገሬ ለማይል ሁሉ ለባዕድ ምንም ስሜት ሊሰጠው አይችልም።

ዛሬ እንደድሮ አይደለም፤ እግዚአብሔርን የማይፈሩ ለአገርና ለቅርስ ደንታ የሌላቸው ስግብግቦች እንደ አሸን ፈልተዋል። ስለዚህ መንግሥትም ሆነ ቤተክህነት ሁነኛ የጥበቃ ኃይል ሊያሠማሩላቸው ያስፈልጋል። በተቻለ የቅርስ ቆጠራ እና በዘመናዊ የቪዲዮ የአላርም ሲስተም ቤተመዘክሩ እና አድባራቱ መጠበቅ ይገባቸዋል። ይህ ቅርስ የሀገር ሀብት ነው የትውልድ ሀብት ነው። የታላላቅ አድባራት የወርቅ መስቀሎች መሠረቅ፣ የጽላቱ በሌቦች መታደን ሊያሳስበን ያስፈልጋል። ከሥነ ጥበብ ጋር እንታረቅ።

ከላይ የዘረዘርነው ስለገዳማቱ እና አድባራት ቅርስ ሲሆን፤ ዘወትር ልብ አድርገን የማንመለከተው ሌላ አስገራሚ ቅርስም አለን። በሕዝባችን ውስጥ የሚሠሩት የዕደ ጥበብ እና የሥነ ጥበብ ውጤቶች ሌሎቹ ትዕንግርቶች ናቸው። በአርሲ ክፍለ ሀገር ገንፎ የሚበላባቸው ረጃጅም ቅሎች እግር ተሠርቶላቸው በጥንቃቄ ዲዛይን ወጥቶላቸው በጨሌና በዶቃ መርገፍ ተጊጠው ላያቸው ስሪዎቻቸው የገጠር እናቶች የሐሳብ ብስለት ምን ዓይነት እንደሆነ መገመት አያዳግትም። በጨሌ ያጌጠው የቆዳ ልብስ፣ የጸጉር ጌጥ፣ ማበጠሪያ፣ የአንገት እና የእጅ የእግር ሽዋሊያ የየራሱ ዲዛይን አለው።

ይህ የዕደ ጥበብ ውጤት ክቡር መሆኑን ዋጋ እንዳለው ለመረዳት እዚህ አሜሪካ በታላላቅ አየር መንገድ ሱቆች ውስጥ የቀይ ሕንዶች ሱቅ አለ። ግርም የሚለው የሕዝቦች የባሕል ዝምድና በብዙ ማይል ርቀት አንድ መሆኑ ያስገርማል። የእኛ የባሌ እናቶች ቅሎቹ ላይ የሚሠሩት ጌጣጌጥ ዓይነት ማዕረግ አግኝቶ ዋጋ ተለጥፎበት ለገበያ ቀርቦ ስናይ

መለስ ብለን የናቅናቸውን ጮጮዎች እንድናደንቅ እንገደዳለን:: ሠሪዎቹንም እናከብራቸዋለን::

ቆዳዎቹ እንዳሉ በቅባት እርሰው ለሽያጭ ተንጠልጥለዋል:: የቀዮቹ ሕንዶች የሥነ ጥበብ ውጤት ባሕላቸው በመሆኑ ዋጋ ተሰጥቶት ብዙዎችን ማርኳል:: በኦሮሞ ጐሳ ውስጥ የሚሠሩት የዕደ ጥበብ ውጤቶች ምን ዓይነት ዋጋ እንዳላቸው መረዳት አያዳግተንም:: በዚህ ሁሉ ጉዳይ ነው ከሥነ ጥበብ ጋር መታረቅ የሚኖርብን::

ከሥነ ጥበብ ወጣ ብለን የፈረስ ጉግስ ጨዋታ የሚያውቀው ይህ ኅብረተሰብ ጥሩ ቱሪስቶችን የሚያዝናናበት ገጠመኝን ፈጥሮ በገቢው መምነሽነሽ ይችላል:: የፈረስ ጉግስ በውጭው ዓለም በጣም ተወዳጅ ጨዋታ ነው:: ታዲያ በየቦታው የፈረስ ጉግስ ሜዳዎች በዕቅድ ቢዘጋጁ ጐብኝውም ሆነ የአገሬው ሰው ጊዜውን በደስታ ቢያሳልፍ የሚፈጥረውን ደስታ ገቢ እና ዕድገት መገመት ይቻላል:: አንዳንድ ሰዎች ይህ ሁሉ ቅንጦት ነው ብለው ሊያምኑ ይችላሉ:: ግን መሬቱን በማረስ የሰማዩን ዝናብ በመጠባበቅ ብቻ አይደለም ገንዘብ የሚገኘው ከእርሻ ውጭ ሌሎች የገቢ ምንጮችን በመፍጠር እንጂ::

አንድ ቱሪስት ከአውሮፓ ወይም ከአሜሪካ በሺህ የሚቆጠር ገንዘብ ይዞ ይመጣል በኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚዘጋጀው የሰላምታ መጽሔት ስለቅርሶቻችን ጥሩ ስዕል ዋና የጽሑፍ መረጃ በመስጠት ቱሪስቱን ያጓጓዋል:: ልክ ከአይሮፕላን እንደወረደ ጥራት ያላቸው ታክሲዎች ፈገግታን ከተሞሉ ሾፌሮች ጋር ሆነው ይጠብቁታል:: በር ከፍተው ሻንጣጭነው:: የታክሲዎቹ ሾፌሮች በከተማይቱ ውስጥ ያሉትን የመዝናኛ ቦታዎች ታሪካዊ እና ቄልፍ የሆኑ ለቱሪስት የሚያገለግሉ ማዕከላትን ያውቃሉ:: ለቱሪስቱ በጥሩ እንግሊዝኛ ያብራሩለታል:: የተዘጋጁ በራሪ ወረቀቶችን መጽሔቶችን የሆቴል ማስታወቂያዎችን ይሰጡታል:: ቱሪስቱ በዚህ አቀራረብ በደስታ ይፍነከነካል:: ኢትዮጵያ የጸጥታ ችግር እንደሌለባት የታወቀ ስለሆነ ይህም ታላቁ ሀብታችን ነው:: ቱሪስቱ ሆቴል እንደደረሰ የሆቴሉ የበር ላይ አስተናጋጅ እንኳን ደህና መጣህ ብሎ ሻንጣውን



ይዞ ወደ ውስጥ ያስገባዋል:: የሆቴሉ እንግዳ ተቀባይ በተለመደ ፈገግታ የክፍሉን ቁልፍ ታስረክበዋለች:: የፀዳ መኝታ መስኮቶቹ የከተማውን ውበት የሚያሳዩ ፀጥታው አስተማማኝ የሆነ ሆቴል:: በዚህ ልቡ የተነካው ቱሪስት በየቦታው ከመደበኛው ክፍያ የበለጠ መክፈሉ አያጠራጥርም::

ወደ ሶፍዑመር ዋሻ ሊጐበኝ የሄደ ቱሪስት ከአስጐብኝ ድርጅት የተላከው ሾፌር በታላቅ ትህትና ዕቃውን ከጫነ በኋላ ቱሪስቱን እንዲዝናና በብሩህ ሕሲና ለጉዞው በተስማማ አለባበስ እና ንጽሕና ወደ ባሌ ጉዞውን ያቀናል::

በየመንገዱ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ማለት ከዝንብ የፀዱ፤ በፈጣን አስተናጋጆች በመታገዝ ምግብ ያቀርባሉ፤ ቡና፣ ሻይና አምቦውኃ:: በዚህ እጅግ የተደሰተው ቱሪስት የባሕላዊ ዕቃ መሸጫ መደብሮችን ይፈልጋል:: በጥንቃቄ የተዘጋጁ የአካባቢው ዕደ ጥበባት ይቀርቡላታል::

እስቲ በዚህ ደስታው መሀል ፈረንጅ ፈረንጅ እያሉ የሚያጅቡ ሕፃናት ቢሯሯጡ ይህ ቱሪስት ምን ስሜት ይሰማዋል:: በየእናቶቻቸው እቅፍ መዋል የነበረባቸው ሕፃናት ት/ቤት መሆን ያለባቸው ሕፃናት መንገዱን ሞልተው መኒ መኒ ሲሉ ማን የማይታወክ ሰብአዊ ፍጡር አለ?

ለማንኛውም በእንደዚህ ሁኔታ ከሶፍዑመር ዋሻ የደረሰው ቱሪስት አካባቢውን ጐብኝቶ ብቻ ከሚመለስ ዋሻውን የመሰሉ ትንንሽ ምስሎችን ቢያገኝ መጻሕፍት እና ሌሎችንም መረጃዎች ቢገበይ እርሱ ተደስቶ አገሩ ሲሄድ ለሌሎችም ባሳየ ነበር::

የታወቁት ዓለም አቀፍ መጻሕፍት መሸጫ ድርጅቶች በአሜሪካ የባርንስ እና የኖብልስ የመጽሐፍት መሸጫ የግብጽ፣ የራሽያ፣ የግሪክ አይከንስ መጻሕፍትን እንደልብ አግኝተው ሲያሳትሙ፣ ሲሸጡ የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራትን የሚያሳዩ መጽሐፍ መረጃዎች ግን ቢፈለጉ አይገኙም::

በቅርቡ በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች እየታየ ያለው ዓባይ (ናይል) የተሰኘው ፊልም ሲታይ በሳይንስ ሙዚየም መደብር ውስጥ ተዘዋውረን ስንመለከት የግብጽ ቅርሳ ቅርሶች ብቻ ሲሸጡ ተመልክተናል:: ለመሆኑ የኢትዮጵያን ለምን አትሸጡም ብለን ስንጠይቃቸው የሚያቀርቡልን መልስ አጣን ነበር ያሉን:: ከሀገራችን አልፎ ዓለም እራስዋ ገበያችን ነች::

ሁለት ነጭ ጓደኞሞች በየጸሉት መጻሕፍቱ ላይ ያሉትን ስዕሎችና ሐረጐች ፎቶ አንስተው ብቻ መጻሕፍት በማሳተም እንደከበሩ ብንነግራችሁ የቅርሶቻችን ዋጋ ምን መሆኑን መገመት ይቻል ይሆን? ካለፉት የሥነ ጥበብ የኪነ ሕንፃ ሀብቶቻችን ጋር ያለማወላወል መታረቅ ይገባናል:: ጥንቃቄ በተሞላ በባለሙያ በታገዘ በታማኝነት፤ ቅርሶቻችንን ልንጠቀማቸው እንችላለን::

## የፈጠራ ሰዎች ሕሊና እና የሥራ ብክነት

ሌላው በቅርቡ እየባከነ ያለው የፈጠራ ሕሊና የሥነ ጥበብ ሞያ እርቅ የሚፈልግ ጉዳይ ነው:: የእኛ የሥነ ጥበብ ሰዎችም ሆኑ ኪነ ጥበባቸው እንደዋዛ ታይቷል፤ የአዲስ አበባ ሥነ ጥበብ ት/ቤት የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት የአዲስ አበባ የቲያትር ጥናት ጥቂት ሰዎች ያስመርቃሉ:: ለእነዚህ ባለሙያዎችም እንኳን ሥራ የለም:: ሰዓሊያኑ እና ሥራዎቻቸው ማዕከል ስለሌላቸው በየእስቱዲዮቻቸው ሰዓሊው በረሃብ ስዕሉ በምስጥ እየተበሉ ነው::

አቶ ወርቁ ማሞ የተባሉት የቀለም ቅብ ጠቢብ ከአስደናቂ ንድፎቻቸውና የቀለም ቅብ ሥራዎቻቸው ጋራ ብቻቸውን ሙዚየም ሊሠራላቸው ሲገባ ወንዝ ዳር በነበረች ደሳሳ ቤታቸው ውስጥ ያሉ የጥበብ ሥራዎች በጐርፍ እስኪወሰዱ መረሳታቸው ሐዘን ነው:: እነታደሠ ወርቁ፣ ታደሠ ማመጫ፣ ዘሪሁን የትምጌታ እና ታደሠ መስፍንን የመሳሰለ ወጥ የጥበብ ሰዎች ኢትዮጵያ አላት ሲባል ግን በእነዚህ ታላላቅ ሰዎች መጠቀም አለመቻልዋ አሳዛኝ ነው::



የግራፊክስ ፈላስፋው ዘሪሁን ብቻውን የሚጐበኝ ነው:: በንድፍ ኃይሉ የታወቀው ታደሠ በእኛ እጅ ባይሆን ንድፎቹ ብቻ ሙዚየም ይፈልጋሉ:: አቶ ወርቁ ጐሹ የፈጠሩት ኢትዮጵያዊ የስዕል ዘየ በዓይኖች ብቻ የሚሠሩት ተአምር:: ዋ ... ወገኔ በእጅህ ያለውን የሥነ ጥበብ ሀብት ብታየው ያስብላል::

ይህ የጥበብ መንጋ መቼ አባራ ዛሬም ትልሙን ተከትሎ እየተመመ አይደለም ወይ፤ በችግር አረንቋ የተተበተበው ሕዝብ የጥበብ ብቃቱን የአእምሮውን ርቀት ባገኛት ቀዳዳ እያሳየ ይገኛል:: እርቅ ስናደርግ ለእነዚህ ሁሉ ዋጋ ሰጥተን ነው::

የእነዚህን ጠቢባን ሥራ ሰብስቦ ሙዚየም ማዘጋጀት፣ በፖስት ካርድ በመጽሐፍ አባዝቶ ማዘጋጀት እና መሸጥ ይቻላል፤ ይህ ሁሉ ገንዘብ ነው::

በአዲስ አበባ ያለችው ሙዚየም የድሮ ሰዓሊያንን ስዕል ይዛ ጥቂት የድንጋይ ቅርሶችን እያሳየች ጭልጭል ማለትዋ የጐብኝዎችን እርካታ አያሟላም:: ሊሰማን ይገባል ሰዓሊያኑ ኦሪጅናል ሥራዎቻቸውን በእርካሽ ያውም ከተገኘ ሲሸጡት:: ከዚህ አልፎ ተርፎ በአዲስ አበባ ሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ውስጥ ተሠርተው እዛው የተገተሩ የምረቃ ሥራዎች በየአደባባዩ ለምን እንደማይቀመጡ ግራ ያጋባል:: የምረቃ ሥራዎቹ፣ ሞዛይኩ እና ሌላውም ምናለ አዳዲስ ሕንፃ ላይ ድርጅቶች ሳይቀሩ ከትምህርት ቤቱ ጋር በመቀናጀት የወጣቶቹን ሥራዎች በየቦታው በመስቀል ቢያስተዋውቁ:: ይህ በበለፀጉት አገራት ስለሚደረግ ነው::

የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት የሲንፎኒ ዝግጅት በኢትዮጵያ ሬዲዮ በሣምንት አንድ ቀን እንኳን ቢሰጠው እንደ ምዕራቡ ዓለም እከሌ የተባለው የሙዚቃ ቀማሪ በዚህ ዓመተ ምሕረት የቀመረው ተብሎ ቢተዋወቅ:: የመሰንቆው፣ የበገናው፣ የዋሽንቱና የክራሩ ጥበብ ትንሣኤ ቢያገኝ ባሕላዊ ቀመር ቢጠና መንፈስን በእጅጉ ይመስጥ ነበር::

ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት እንዳየነው የባሕሉ ክፍል ብዙም ትኩረት ሲሰጠው አላየንም:: የነሞዛርት፣ ቤትሆቨን ጥበብ ሲጠና የነቅዱስ

ያሬድ፣ የነአባ ጊዮርጊስ የተዘነጋው ለምንድነው? የእኛ ወርቆች ስለሆኑ ይሆን?

ያሬድ በተወለደበት አክሱም አንድ ሐውልት የለውም፤ ቤተ መዘክር ሙዚየም የለውም፤ በፊልም የተሠራ መረጃ የሚሆን ጥናት የለውም፤ ይህ ሁሉ ያንገበግባል:: አባ ጊዮርጊስ የጻፋቸው ከ8 በላይ መጻሕፍት ትዝታቸውም መኖራቸውም በኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ አይታወቅም::

በቅዱስ ያሬድ ስም የተሰየመው ሙዚቃ ትምህርት ቤት ደግሞ የባሰ የያሬድን የዜማ ትምህርት አያስተምርም:: የያሬድ ዜማ እኮ ከሃይማኖታዊነቱም ባሻገር ጥበብም ነው:: 1400 ዘመን ተሻግሮ የመጣ መሠረቱ ሰማያዊ የሆነ ጥበብ:: የያሬድ ዜማ እኮ ፊደል ያለው ሕግና ሥርዓት ያለው ቀመር ነው:: ያ .. ሁሉ ልፋት ያ ሁሉ ሕብር ያለው ዜማ ያላት ኢትዮጵያን ማየት የሚፈልግ ጉብኝ አገሩ የሰለቸውን ራፕ ብልግና ብናሳየው የሚያደንቀን ይመስላችኋል?

እንዴት እኛ የደናቁርቱን ራፕና ምናምን እንቀላውጥ ደርዝ ያለው ማኅሌት፣ የሚስረቀረቅ መሰንቆ፣ የሚተም ከበሮ ያለን እኛ እንዴት ምንም በሌላቸው እንቅና? አፍሪካውያን ወንድሞቻችንና አረቦቹ የሙዚቃቸው ባሕል እንዳለ ነው:: እንቅስቃሴያቸው የራሳቸው ነው፤ እኛ ግን ከከበሩት ባሕላዊ መሣሪያዎቻችን ጀምሮ እንቅስቃሴያችን ሁሉ እየተ ለወጠ ነው::

እነዚህ የጥበብ ማዕከላት የሚያስመርቋቸው ምሁራን እና ሥራዎ ቻቸው ባክነው በመቅረታቸው በሥነ ጥበብ ሥራዎች መጥለቅለቅ የነበ ረባት ሀገራችን አንድ ሙዚየም ብቻ ነው ያላት:: አንድ የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ነው ያላት:: ምክንያቱ ምንድነው? ሁሉ ነገር በጀት ይፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ እራሱ የስዕሉ ውጤት ወይ ዋናው ስዕል ወይ ተባዝቶ መሸጥ መገኘት አለበት::

ስዕሉ ይሠራል እንጂ ከገበያው ጋር ዝምድና የለውም ወይም ሰዓሊ ማለት ጠቢብ ማለት በድህነት መኖር ያለበት፤ ሌላ ሕይወት የሌ



ለው ሆኖ ይቆጠራል:: ስለዚህ እንዴት ለአገር ዕድገት የሚሆን ኪነ ጥበብ ማዘጋጀት ወደ ገንዘብ መለወጥ ይቻላል? ብሎም ማጥናት ያስፈልጋል:: ይህም ሲባል የሥነ ጥበብ ዓላማ ገንዘብ ማሳደድ አይደለም:: ግን ሙሉ ጊዜውን ለጥበብ የሚሰጥ የጥበብ ሰው ለማግኘት በውጤቱም የሚጠቀም የኅብረተሰብ ክፍል ለማፍራት ስዕልን ዋናውን ሳይሆን አባዝቶ መሸጥ ያስፈልጋል::

ከዚህ በላይ ያለው በሥነ ስዕል በዜማ በኩል ያለውን ሲሆን፣ ሌላው እጅግ የተዘነጋ ነገር ቢኖር እኛ ጥንታዊያን ሕዝቦች እንደመሆናችን መጠን እንደሌሎቹ ሕዝቦች እውነተኛ ታሪኮች እና ተረቶች አሉን:: እነዚህ ሁሉ በዘመናዊው ፊልም ካርቱንና የመሳሰሉት ጥበባት ሊቀናበሩ የሚችሉ ናቸው:: ይህም በቅርቡ ኬንያ ውስጥ የተሠራውን አንበሣ የተባለውን የካርቱን ፊልም ብቻ በማየት የእኛ ምን ያህል ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ የሚያስደንቅ ሌላው ቀርቶ ሕፃናቶቻችንን የሚያስተምር እንደሆነ መገመት ይቻላል:: ይህም እርቅ ይጠይቃል::

ብቅ ብቅ ብለው የነበሩ የተረት መጻሕፍት ልብወለድ ጥናታዊ ጽሑፎች እየከሰሙ መጥፋት ጀምረዋል:: ብዙዎች ጸሐፍቶቻችን የእራሳቸው የአጻጻፍ ዘይቤ ብስለት እና የቋንቋ አጠቃቀም ብቃት የነበራቸው ሲሆን፤ ዛሬ የሐዲስ ዓለማየሁን፣ የበዓሉ ግርማን ፖለቲካዊ ልብወለድ፣ የብርሃኑ ዘሪሁንን ፈለግ፣ የሀጋዬን ቅኔ፣ የከበደ ሚካኤልን ተረትና ምሳሌያዊ ግጥም፣ የነዮፍታሔ፣ የነአገኘሁ እንግዳን ስነሉነትና ገጣሚነት፣ የእነ ገ/ክርስቶስ ደስታን ሰዓሊነትና ገጣሚነት ጥልቅ ሐሳብ እንደገና ለማምጣት ወይም በአዲስ ድንቅ ጥበብ ለመተካት እያስቸገረ መጥቷል:: እነዚህ መጻሕፍት ከአእምሮ ማሳደግ ብቃታቸው በተጨማሪ ታላቅ የገቢ ምንጭም ነበሩ:: እነዚህም እርቅ ይፈልጋሉ::

ቀደም ብለን እንደገለጽነው ዓለም ወደ አንድ ገጽታ እየተለወጠች ነው መረጃ ባመጣው መቀራረብ አንድ አውሮፓዊ ጸሐፊ የሚጽፈው መጽሐፍ ለብዙ ዓለማት ይሠራጫል፤ በተለያዩ ቋንቋዎች ይተረጎማል::

በአሜሪካ የሚዘጋጀው የሥነ ጥበብ ሽልማት ተሸላሚዎች በዚህ ዘመን አሜሪካውያን ብቻ አይደሉም። በቅርቡ ደቡብ አፍሪካውያንም ተቀዳጅተውታል። ለምን ሥራቸውን በዓለም አቀፍ ገበያ ስላስተዋወቁት።

አንዱ ደራሲ ጽንሰ ሐሳብ ያፈልቃል፣ ተርጓሚዎች በእንግሊዝኛ በፈረንሣይኛ ይተረጉሙታል። ሌላው አሳታሚ ድርጅት ይፈልጋል፣ ሌላው ገበያውን ያስማማል፣ ቲምወርክ (የኅብረት ሥራ) ማለት ይህ ነው። ሁሉም በየሙያው ይሠማራል። በነጋታው ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ እንግሊዝ አገር ገበያ ያገኛል። ይህንን ብዙ የአፍሪካ ወንድሞቻችን እየሠሩት ይገኛል።

በውጭው ዓለም ያሉ የመጻሕፍት መሸጫዎች የተጣበቡት በአገሪቱ ጸሐፍት ብቻ አይደለም። በውጪ ጸሐፍትም እንጂ የአገሬ ወጣት ደራሲያን የሙያ ጥራታቸውን ካበለፀጉ ዓለም አቀፍ ጸሐፊ የመሆኛው ጊዜ አሁን ነው። ለምሳሌ ከአፍሪካ በቅርቡ አዳዲስ ግሩም ጸሐፍት ወጥተዋል፣ ታዋቂው ዴዝሞን ቱቱ እንደ ብርቅ ጸሐፊ ይቆጠራሉ። የራስዋን የሕይወት ታሪክ የጻፈችው ኢማኩሊ ሊባጊዛ እና የመሳሰሉት ጸሐፍት ዓለም አቀፍ ዝናን አትርፈዋል።

ይህ ሁሉ ተጠራቅሞ ነው አንድን ሕዝብ የሚያሳድገው ኢኮኖሚውን ከፍ የሚያደርገው። ወደ ዓለም አቀፍ ጠቢብነት የተጠጉት ኢትዮጵያዊያን ሰዓሊዎች ሜትረን አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ መተካት አለባቸው። እነ ገ/ክርስቶስ ደስታ (Non-Figurative) ጥበብ ውስጥ እራሳቸውን ሲገልፁ ዓለም አድንቋቸው እንደነበረ እስክንድር ቦጎሲያን እና የመሳሰሉ ሁሉ ትውልዱ ፈለጋቸውን መከተል አቅቶታል፣ ይህ ሁሉ እርቅ የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

በየጉሣው ያሉ ታሪኮች፣ ተረቶች የሕይወት ገጠመኝ ሁሉ የሚጻፍ ነው፣ የሚሳል ነው፣ የሚቀረጽ ነው። በቀላሉ በእጅ እና በእግር የሚሽከረከሩ የሸክላ ማቡኪያ መቅረጫ እና ማቃጠያ የሚሠሩ የሸክላ ጥበባት በዚህ ዘመን ታላቅ ዋጋ አላቸው። እንሥራው ድስቱና መግላሊቱ ጭምር በዲዛይን በቀለም ከተሽቆጠቆጠ በሴራሚክስ እና በተለያዩ ጥበባት



ልንጠቀም ስለምንችል በጥራትም በብዛትም ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ወደዚህ ሙያ ያዘነበሉ ዘንድ መሳብና ማበረታታት ይገባል።

አባቶቻችን ያስተላለፉልንን ቅርስ በመጠበቅ፣ በመንከባከብ ከሥነ ጥበብ ጋር እንታረቅ። አዳዲስ ወጣት ጠቢባን የሚፈልቁባቸው ማዕከላት ይስፋፉ፣ ያሉት ጠቢባን ይከበሩ፣ በዚህ ሁሉ ከሥነ ጥበብ ጋር እንታረቅ።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ከችግረኞች ጋር መታረቅ

የሀገራችን ሰዎች እጃቸውን እንዴት ለልመና ዘረጉ? የሚለው ጥያቄ ያሳስበናል። ኩሩ አይደሉ ልመናን የሚፀየፉ አይደል እንዴ? ታዲያ ምንው በልመና የሚተዳደረው በዛ?

ችግሩ የከፋ በመሆኑ ከጉረቤቱ እህል መበደር የሚጸየፈውን ገበሬ እጁን ለልመና እንዲዘረጋ ገፋፋው። ረሃብ፣ ጥምና እርዛት ተረባርበው ወገኔን ከጐጆው አስወጡት። ወደ ከተሞች ጉረፈ፣ ለማኝ ሆነ፣ እርቅ ይፈልጋል። ደጁ ያለውን ወርቅ ማፈስ አቅቶት በልመና የምትንጠባጠበዋን ፍራንክ ፍለጋ ከቀዬው ተሰደደ። ማነው የሚያሳየው ዝናብ ባይኖር እንዴት ማረስ እንደሚቻል?

ሴቶቹ ልጃገረዶች እንጀራ ፍለጋ የተወለዱበትን አካባቢ ጥለው ግራ ወደገባው ከተሜ ፈለሱ። ከተሜውም እግዚአብሔር ይስጠው ያለውን እያካፈለ አስቀምጧቸዋል። ግን ሁሉም በየእጃቸው ዲቃላ ታቅፈዋል ወይም በበሽታ ተለክፈዋል ያስደነግጣል።

ከተሜውም እራሱ ሕፃናቱን ማሳደግ አቅቶት ለቋቸዋል በየመንገዱ እየተሹለከለኩ ይለምናሉ፣ ማታ ቤንዚን ምገው ይተኛሉ፣ ያጨሳሉ፣ ምኑ ቅጡ። ወላጅ አልባዎቹም ሕፃናት የመከራ ሕይወት እየገፉ ይገኛሉ፣ መታረቅ ያለብን ከእነዚህ ሁሉ ጋር ነው። በአፍሪካ ውስጥ የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናትን ማየት የዘወትር ትዕይንት ነው። ሕይወታቸው ግን በምን ይስተካከላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የለም።

ከሁሉ አስቀድመን እንስ ማውታ ሕፃናት ወደ ጉዳና ተዳዳሪነት ሲሄዱ ምን ችግር እንደሚከተል በጥሞና እንመልከት:: ጉዳና ተዳዳሪዎች እንደማንኛውም ሰው ሕሊና የአካል ብቃትና ሰብአዊ ስሜት አላቸው ብለው የማያምኑ ብዙ አሉ:: ነገ ሰው የሚሆኑ የነርን ጫና በተአምር ፈነቃቅለው ወጥተው ከአስተዳደር ቁንጮ ሁሉ የሚደርሱ አሉ:: ታዲያ እነዚህ ፍጡራን በዚህ የመከራ ዘመናቸው የረዳቸውን ኅብረተሰብ የሚረዱ ሲሆኑ፤ የጨከነባቸውን ደግሞ እነሱም ሲያድጉ ይጨክኑበታል:: ስለዚህ ከዚህ ግዙፍ የኅብረተሰብ አካል ጋር ይቅርታ ማድረግ፣ እርቅ ማድረግ ይገባል የሚባለው በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ ጥቅም ሲባል ነው::

ሕይወት ፊትዋን አዙራባቸው በመከራ ምድጃ የሚለበለቡ ሁሉ ቸርነትን ይለምናሉ፤ ፍቅርን እንክብካቤን ይፈልጋሉ:: በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት የተጠሉ፣ የተዋረዱና የተረገጡ መስለው ስለሚሰማቸው ብዙ ጊዜ ተስፋ ሲቆርጡ ሲያለቅሱ ይሰነብታሉ:: እንባቸው አልቆ ደም ካለቀሱ በኋላ መገፋታቸው ታይቶ ከፀባዖት መልስ ይሰጣቸዋል:: እናም ሀብትን ሥልጣንና ዝናን ይጐናፀፋሉ:: ከዚህ በኋላ የዋሆች ከሆኑ የደረሰባቸውን ይረሳሉ፤ ብዙዎች ግን የበቀል መንፈስን ሲሞሉ ይስተዋላሉ::

ሥራ እጥ ሆነው ማንቱም ሳይወረውርላቸው ያለፈው የሳቀባቸውንና የገላመጣቸውን ያስተውላሉ:: ሲርባቸው ዳቦ እየገመጠ በፊታቸው ሲያልፍ ያላስታወሳቸውን፣ እጃቸውን አርገብግበው ሲለምኑት ፊቱን አዙሮ የሄደውን ሁሉ ያስታውሳሉ::

እነዚህ በዘኔዎች የተባሉትን ሁሉ አይረሱም፤ የጠጡትን የግፍ ጽዋ መልሰው መጋት ይጀምራሉ፤ መራሩን ጉምዛዛውን ስለዚህ ነው በአስቸኳይ ከእንለማውታ ሕፃናት ጋር መታረቅ የሚገባው::

ግን ለሥራ እጡ፣ ለጉዳና ተዳዳሪው የሚያዝን ሕሊና ካለን ጤናማ ኅብረተሰብ እንፈጥራለን:: የእንለማውታ ሕፃናቱን (የጉዳና ተዳዳሪ ዎቹን) ለቅሶ አብረን ማልቀስ ከቻልን ለቀጣዩ ሕይወታቸውም በርህራሄ ካሰብን ከተጨነቅን የነገይቱን አገር የፍቅር አውድማ ልናደርጋት



እንችላለን:: ስለዚህም የጉዳና ተዳዳሪዎችን እንባችሁ እንባችን ነው ብለን እስቲ በቅኔና በሥነ ጽሑፍ እንባ አብረናቸው እናልቅስ::

### አብረናችሁ እናልቅስ

ዓለም በእንባ ተራጭቷል፣
እንባ አልቆበት ደም ያዠው ዓይናችሁ፣
በየምናምኑ ሥር በየጥጋቱ የተኛችሁ፣
ከሰብዓዊ ፍጡር በታች ተቆጥራችሁ፣
ኑሮና የሰው ዓይን የወጋችሁ::
ቤንዚን ናፍጣ የመኪና ጢስ፣
ዋእይ ቃጠሎው ብርዱ የሚጠዘጥዝ፣
እንደ አውሬ እንደ እንስሳ፣
ካለጥጋት ካለ ገሳ::
የሰማይ ጠል ያረሰረሳችሁ፣
ቁርና ዋእይውን ታግሳችሁ::
በሕፃንነት በለጋነት፣
መራራ ጉምዛዛ ሕይወት::
የቀመሳችሁ ሁሉ እናንተ ጉሳቋሎች፣
በገዛ አገራችሁ ስደተኞች ባይተዋሮች ለማኞች::
ግራ የገባችሁ የአምላክ ያለህ ያላችሁ፣
የሐዘናችን ቃል የነፍሳችን የውስጥ እንባ ያውላችሁ::
እኛም ስደተኞች ነን መፃተኛ ምስኪን፣
ከእናንተ እንባ የሳግ ለቅሶ የተጋራን::
ብክን ያልን የባከንን ባገር አሳብ፣
የወገን ሥቃይ ያጠሚረረን የፍቅር ረሃብ::
ዓለም ሁሉ እንደናንተ አልቅሷል፣
በድህነት ከእናንተ ጋር ተንገላቷል::
የችግሩም ቋት ሞልቶ ቢተርፍ፣
የእልሃቸው ስሜት ቢደርስ ከአፋፍ::

ይቅር በሉን ይቅር በሏት ኢትዮጵያን ፤
በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይጥለቅ ቀን ይሁን።
ነገ እስከሚነጋ ብርሃን ለሁሉ እስኪፈነጥቅ፤
ዛሬን ግዴለም እንለማውታ ሆይ እንታረቅ፤
ሌሊቱ እስኪነጋ የንጋቱ ጉኅ እስኪሠርቅ።

በእንባ የምናስታውሳችሁ የእኛው ድሆች ሆይ አትፍረዱብን እኛም ግራ ቢገባን ነው መፍትሔ ያልሰጠናችሁ ብለን ደግመን ደጋግመን ይቅርታ መጠየቅ አለብን።

በሕፃናት ዓምድ እንዳየነው የሕዝባችን ብዛት አስፈሪ ሆኗል። ስለዚህም ሕፃናቱ ከቤት ውስጥ እየተከለበሱ ወደጉዳና ወጥተው እያየናቸው ነው። በእውነቱ በዚህ ዘመን ይህንን ሕልቆ መሣፍርት የሌለው የጉዳና ተዳዳሪ ለማስተናገድ አንድ ብልሃት እንጂ የገንዘብ ወይም ሌላውም ሁኔታ ሊመክተው አይችልም።

የአሥራ ሁለት ዓመት ሕፃናት ለሴተኛ አዳሪነት እየተመለመሉ ይገኛሉ። ወዴት ነው መድረሻችን? ለዚህ ታላላቅ ሕዝባዊ ሸንጐዎች የመገናኛ ብዙኃን ዘመቻ አስፈላጊ ነው። በውጭ ያለነውም አንድ ወይም ሁለት ሕፃናት ብንካፈል እና ብናስተምር ችግሩን በጥቂቱም ለማቃለል ሞከርን ሊባልልን ይቻላል። ግን ይህ ለችግሩ ፈጽሞ መፍትሔ አይሆንም።

በአንደበት ብቻ አስተያየት መስጠት ሳይሆን የተግባር መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ሥራ ነው። አገር መክሮ ተረባርቦ መፍትሔ ማምጣት አለበት። ያም አጠቃላይ የኅብረተሰቡ ችግር ነው። እስቲ ይህንን ጉዳና ላይ የወጣ የሕፃናት የወጣቶች ብዛት ወደ ምርታማነት ለመለወጥ እንሞክር፤ የመጨረሻው መፍትሔ የሕዝቡ ኑሮ እንዲያሻሽል ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። ስለዚህ ከችግረኞች ጋር እንታረቅ።



# ምዕራፍ አሥር

## ከሥራ ጋር መታረቅ

አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፤
መንገድዋ ተመልክተህ ጠቢብ ሁን፤
አለቃና አዛዥ ገገርም ሳይኖራት፤
መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች፤
መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች፤
አንተ ታካች እስከ መቼ ትተኛለህ?
ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሳለህ?
ጥቂት ትተኛለህ ጥቂት ታንቀላፋለህ፤
ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ፤
እንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፤
ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል።*

መጽሐፈ ምሳሌ እንዲህ ስለሥራ አብራርቶ አስፋፍቶ በጥበብ ይናገራል። ሥራ ጽድቅ ነው፤ የሚሠራ ገበሬ እንደበቱ ከሐሜት እጁ ከስርቆት፤ ዓይኑ ከስስት ይታቀብለታል። ምክንያቱም መላ መንፈሱ ከሰብሉ ዛላ ላይ ስለሚያርፍ ነው።

ከላይ በረቂቅ የሥነ ፍጥረት ሕግ ገብረ ጉንዳን እንዳስተማረን ሁሉ። ከፍጥረታት በሥራ የታወቁ ንብን የመሳሰሉ ትጉህ ሠራተኞች የሰው ልጅ የኑሮውን ዕቅድ ይፈትንባቸው ዘንድ ለትምህርት ለተዘክሮ በምድር ሲርመሰመሱ ይታያሉ።

* ምሳ. 6÷6–11

በተለይ ገብረ ጉንዳን እጅግ ከፍጥረታት የሚለይበት ጠባዩ ከገዛ ክብደቱ ወይም ቁመቱ ጋር የማይመጣጠነውን ከፍ ያለ ነገር እንኳን ተሸክሞ ቀጥ ባለው ግድግዳ ሽቅብ ቁልቁል ሲል መታየቱ ነው፡፡ ሌላው መስመሩን ተከትሎ ምግቡን እያመላለሰ ማከማቸቱ፤ መሬቱን ታላቅ መሐንዲስ ያሳመረው ግንብ አስመስሎ መፈልፈል በታላቅ ትጋት ይህን ሁሉ ሲያከናውን ግን እንደሌሎቹ ትልልቆች ወይም ትንንሽ እንስሳት ጠብ የማያውቁ ከሥራ በቀር ከመጓዝ በቀር መቆም የማይሳካላቸው በመሆናቸው፡፡ ገብረ ጉንዳን ከሁሉ የተለየ ፍጥረት እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በምድራችን ዓይነታቸው እጅግ የበዛ የጉንዳን ዓይነቶች አሉ፡፡ ግማሾቹ እንጨት የሚመገቡ፤ አንድ የቆመን ግንድ ውስጥ ውስጡን በልተውት በእጅ ሲነኩት እንዲፈረካከስ የሚያደርጉ መጋዝ ጥርስ ያላቸው ጉንዳኖች አሉ፡፡ ሌሎቹ አንድ የጭቃ ቤት ውስጥ ውስጡን ሰርስረው አንድ ቀን ሲጥሉት መቼም ያችን የምታክል ፍጥረት እንዴት እንዲህ ጠነከረች ያሰኛል፡፡ ርዕሳችን ከሥራ ጋር እንታረቅ በመሆኑ ከመነሻው እኛ ከሥራ ጋር ለመሆኑ ተጣልተናል ወይ? ብሎ ለሚጠይቅ፡፡ አዎ በሚገባ ተጣልተናል ብለን እንመልስና፡፡ እንዴት? በምን? ለሚለው ጥያቄ ከብዙ ምሳሌዎች ጋር በሰፊው ርዕስ ላይ እየተወያየን እንቆያለን፡፡

ከአንድ ሰው ጋር ስንታረቅ የተሠራ በደል እንዳይደገም ቁርጡን መነጋገር የተለመደ እንደሆነ ሁሉ፡፡ ከሥራ ጋር ተጣልተናል ሲባልም ያስቀየምነውን የበደልነውን በሰፊው መናዘዝ የግድ ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ3 ሺህ ዓመት በላይ የደረጀ ታሪክ አላት፡፡ እውነት ነው አይካድም፡፡ እንዲህ ከሆነ በታሪካችን ውስጥ ያዳበርነው ታላቅ ነገርም አለ፡፡ እውነት ነው በታሪክ ተመዝግቦ እንደተገኘው ታላላቅ ሠራተኞች ግዙፍ ሥራቸውን አስቀምጠውልን አልፈዋል፡፡ ታዲያ በትጋት የተፈለፈሉት የላሊበላ ቤተ መቅደሶች አክሱም የቆመውን ሐውልት የሥራ ትዕግሥትና ብቃት፤ የሥራ ፍቅር፡፡ ድንና ጾመ ድንውን ለዚህ ዘመን ያደረሰ ጥንካሬ በዚህ ዘመን ያፍዝ አደንግዝ ይዞት ዓለም በሥልጣኔ



ሲወረወር እኛን የገተረን ከሥራ ጋር መጣላት አይደለም ወይ? ቀደም ባሉት ጊዜያት ዓለምን አስከትላ ትሮጥ የነበረች ኢትዮጵያ ዛሬ ከኋላዋ እየተፈተለኩ ሲቀድሟት አለመራመድዋ ከሥራ ጋር መጣላት እንጂ ሌላ ምን ይሉታል?

እኛ ስለእራሳችን ምን እንላለን ሳይሆን፤ ዓለም የተራቀቀበት የሥራ ሚዛን የት ቦታ ያስቀምጠናል ብሎ መጠየቁ ይጠቅመናል፡፡ ከሁሉ በፊት መሞጋገስን እኛ እንበልጣለን የሚለውን ከንቱ ሐሳብ ወደኋላ አሽቀንጥረን እንጣል፡፡ ከዚህ ተነሥተን እጅግ መልካም የተባሉ የዚህችን ምድር ክንውኖች እንመርምር፡፡ ፍርጥ አድርገን እኛ የቱ ጋ ነን? ብለን ደግመን ደጋግመን እራሳችንን እንፈትሽ፡፡ ሠራተኞች ነን ወይ? ከሆንን የታለ የሥራ ፍሬአችን? ብዙ ጊዜ በሌሉ ተስፋዎች ላይ ከመንጠልጠል ያለውን የሚያዩትን ብቻ ማመን ያስፈልጋል፡፡

ጃፓኖች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ብዙ ጊዜ በጥበብ ከሁሉ እንበልጣለን የሚል ትምክህት ነበራቸው ይባላል፡፡ ግን ሒሮሽማ እና ናጋሳኪ ላይ የተጣለውን የአቶም ቦምብ ካዩ በኋላ ለካ እንበላለጣለን ወደምትለዋ የዕድገት ቁልፍ ሐሳብ መጡ ይባላል፡፡ ስለዚህ ሕፃናቱን በትጋት በማስተማር በልማት ዛሬ እውነትም ከብዙዎች በለጡ፡፡

እራስን እንደ እንግጫ ካወረዱ በኋላ የምትገኝ ጥበብ ሲናገሯት እጅግ ታምራለች፡፡ እንዲህ መንፈሳችንና ውስጣችንን ዝቅ አድርገን ከሁሉ ትምህርት ለመገብየት የተዘጋጀን ከሆንን ምን ዓይነት ትምህርት እንቅሰም? የቱ ነው ለሥራ የሚያመቸው? ብለን መምረጥ ያስፈልገናል፡፡

ከሁሉ በፊት ግን ደረጃ በደረጃ ወደ ሥራ መንፈስ የሚወስዱ እርቆችን በዝርዝር እንይ፡፡

ሀ. ከባሕል ጀምሮ የፀረ ሥራ ፍልስፍናዎችን መንቀል ፤

ለ. ከሌላው ዓለም ፈልሰው የሚመጡ ፀረ ሥራ ፈሊጦችን መግረዝ ናቸው፡፡ ሁለቱን በበይት የሥራ ጠላቶችን ዘርዝር አድርገን እናያቸዋለን፡፡

## ሀ. ለሥራ የማያመቹ ባሕሎችን ማረም

በእያንዳንዱ ሕዝብ ውስጥ እንደ ባሕል ሥራን የሚቃወሙ ልምዶች ዳብረው ሥር ሰደው ይገኛሉ። እነዚህን መጥፎ አረሞች በትምህርት በማረም ዜጐችን ለሥራ ማነሳሳት ያስፈልጋል።

ለሥራ ብቻ ሳይሆን ለጤና፣ ለትምህርት፣ አብሮ ለመኖር ሳንካ የሆኑብንን ጠባዮች ሁሉ በሥልጣኔ ሰይፍ መቁረጥ አግባብ በመሆኑ በዚህ መልክ የእርቅ ሐሳባችንን እናቀርባለን።

ነገር ግን በዚህ መሀል ጠቃሚው ባሕልም እንዳይጐዳ በከፍተኛ ጥናት የተደገፈ ረጋ ያለ ከግብታዊነት የጸዳ እርምት በትምህርት በእርጋታ መካሔድ ይኖርበታል።

ሕዝብ በረጅም የሕይወት ጉዞው ያዳበረው የአብሮ መኖር ጠባይ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሥራ፣ የትብብር፣ የፍቅር መንገድ እንዲዳብር፤ በአንጻሩም ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ጐን ለጐን ሲያስቸግረን የኖረውን ለጤና፣ ለትምህርት፣ አብሮ በመኖር፣ ለሥራ እንቅፋት የሆነ የደረጀ ጐጂ ባሕልም እንደአረም ሊነቀል ይገባዋል። ችግሩ አረሙ ሲነቀል መልካሙም ተክል አብሮ እንዳይነቀል ምን ያህል ጥንቃቄ ይደረግበታል የሚለው ሐሳብ አስጨናቂ እየሆነ መምጣቱ ነው።

ለምሳሌ አንዳንድ ተቋማት ካለስማቸው ካለግብራቸው ስም ተሰጥቷቸው ለሀገራችን ያበረከቱት የሥራ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የሥነ ጥበብ እንቁ በጥቂት ሰነፍ ሠራተኞች ክፉ ትምህርት ተሸፍኖ በመገኘቱ በዚህ ዘመን ላለው ትውልድ ሐቁ እውነቱ ተሸፍኖ ስለሚገኝ ገላልጦ ማስተማር ያስፈልጋል ይላል የእርቅ ሐሳብ።

እቅጩን ነው የምንነጋገረው ከተባለ ባሕላችን ሥራን እንዲያግዘ ሆኖ መቀረጽ አለበት እንላለን። ለሥራ የማያመቹ ልምዶች በፍፁም መወገድ አለባቸው።



## ለ. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና የሥራ ባሕል

ከሁሉ በፊት አንዳንድ ያልገባቸው ሰዎች እንደሚገምቱት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሥራ ጋር ትጣላለች ወይ? ይህንን ጥያቄ የምንጠይቀው ቤተ ክርስቲያኒቱ ያላለችው ያልደነገገችው ብዙ ዝባዝንኬ ስለሚናፈስ ነው። ብዙ አባቶችን ጠይቀን መጻሕፍትን አገላብጠን እንዳረጋገጥነው ቤተ ክርስቲያኒቱ በሥራ ተወልዳ በሥራ ያደገች ለልማት ግንባር ቀደም የሆነች መሆንዋን ነው።

ለዚህም ሃይማኖተ አበው የተባለው መጽሐፍ ለመነኮሳት ከሚሰጠው የኑሮ መመሪያ ውስጥ «መነኮሳት ተግባረ ዕድ ማዘውተር እንዳለባቸው ነው» እንደውም ለአባ እንጦንስ መልአኩ የሠሌን ሥራን እየሠራ በጸሎትና በሥራ ጊዜውን ያሳልፍ ዘንድ ምሳሌ ሆኖታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቀን በወንጌል ሥራ ተጠምዶ ሌሊት ደግሞ ለዕለት ጉርሱ የምትሆነውን ተግባረ ዕድ ያከናውን እንደነበረ።* ሉቃስ በሕክምና፣ በስዕል ሥራ፤ እነ ጴጥሮስ ዓሣ በማስገር ሥራ መተዳደራቸውን ስናይ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ጀምራ ከሥራ ጋር የታረቀች መሆንዋን ማረጋገጥ እንችላለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች አልከበድኩባችሁም እያለ ሲጽፍ እራሴን የማስተዳድርበት ሥራ አለኝ ያለኝን መንፈሳዊ ሀብት ላካፍላችሁ የመጣሁ ሠራተኛ ነኝ እንጂ ካለሥራ የተቀመጥኩ ወይም ከሥራ ጋር የተጣላሁ ሰነፍ አይደለሁም ማለቱ ነው።*

ከድሮ ጀምሮ ገዳማት በእርሻ የታወቁ ናቸው። በመጻሕፍት ድጐሳ በብራና መፋቅ በጽሑፍ ምኑ ቅጡ። ከጸሎቱ ጋር ገዳማውያን ዕረፍት ፈጽሞ የላቸውም። በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ ታሪኬ የምትላቸው አድባራት እራሳቸው የሥራ ውጤቶች ናቸው። በውስጡ የተሳሉት የተፈለፈሉትና በሐረግ የተሸቆጠቆጠው ግድግዳ ሁሉ በትጋት የተሠራ ተአምር ነው።

* የሐዋ.ሥራ 18፥3
* የሐዋ.ሥራ 20፥33–35

ስለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን የሥራ መምህር ናት የምንለው:: ግን በዚህ ዘመን በግላቸው የስንፍና መንፈስ ተነሳስተው ያልተሰበከ የስንፍና ድርሰት የሚያነቡ በእውነት ጥንታዊትዋን፣ ታሪካዊትዋን፣ የሥራና የጥበብ እናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አይወክሉም::

በፍትሐ ነገሥቱ አንቀጽ 19 በቁጥር 713 ላይ ሌላው ቀርቶ ቀዳሚት ሰንበትን እንኳን «ክርስቲያኖች እንደ አይሁድ በዕለተ ቀዳሚት ተግባርን ማጉደል አይገባቸውም በዚህች ዕለት እንደ ክርስቲያን ይሥሩ እንጂ ከሕዝቡ ወገን የአይሁድን ሥራ ሲሠሩ ቢገኙ እነርሱ ከክርስቶስ ፊት የተለዩ ይሆናሉ» ይለናል::

ምን ማለት ነው? አይሁድ እግራቸውን ካጠፉ የማይዘረጉበት:: ከዘረጉ የማያጥፉበት፤ ቅጠል እንኳን የማይቀነጥሱበት እጅግ ጠንካራ ሕግ ነበራቸው:: በሐዲስ ኪዳን ዘመን ግን ሰው የሚድንበት የጽድቅ ሥራ ሁሉ በሰንበት ተፈቅዷል:: ይህም ጌታ እራሱ በሰንበት ድውይ እየፈወሰ ምሳሌ የሆነበት ነው:: ይልቅ በዚሁ በፍትሐ ነገሥት ም. 19 ቁ. 719 ላይ «ጥቅም የሌለበትን ነገር ትናገሩ ዘንድ ወይም መልካም ያይደለውን ሥራ ትሠሩ ዘንድ አይገባም» ሲል እናገኘዋለን:: ይህ ሲባል በዕለተ ሰንበት ሰውነታችንን የምናሳርፍበት፣ በሽተኛ የምንጠይቅበት፣ የታረዙትን፣ የተራቡትን የምንመግብበት፣ የቅድስናና የትሩፋት ቀን በመሆኗ ከሌላ ዓለማዊ ሥራ እንታቀብም ዘንድ ተጽፏል::

የዓመቱን የበዓላት ቀናትን በተመለከተ ግን ፍትሐ ነገሥቱን በማንበብ መረዳት ይቻላል:: በሀገራችን ቄሱም ገበሬ ነው:: ጠዋት የጠመደ የከሰዓት ቅዳሴ ከሆነ ጸሎቱን ከእርሻው ጋር እያስኬደ በአፉ እያጉተመተመ ከዘወትር ጸሎት ጀምሮ ውዳሴዋን ዳዊቱን ሁሉ በቃሉ ይወጣዋል:: የቅዳሴ ሰዓት ሲደርስ ደግሞ ገብቶ ይቀድሳል ወይም ያስቀድሳል፤ እንዲህ ነው ሥራውንና ሃይማኖቱን በአንድ አቀናጅቶ የኖረው:: በዚህች ምድር ሥራን የሚከለክል ሃይማኖት ተፈጥሮ ስለማያውቅ የአንዳንድ ሰነፎችን ልብ ወለድ ድርሰት እየሰማን ከሥራ ጋር እንዳንጣላ ያስፈልጋል::



አባቶቻችንን አነጋግረን የቤተ ክርስቲያኒቱ አቋም ሥራን በተመለከተ ምንድነው የሚለውን እንዳገኘነው እራስዋ እየሠራች ሌሎችንም ለሥራ የምታነሳሳ ከመሆንዋ በላይ ከተደነገጉት ዐበይት በዓላት በስተቀር አትሥሩ ብላ እንደማታውቅ አረጋግጠናል:: ይህንንም በተግባር ስትመሰክር በቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር ውስጥ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ዘርፍ የተቋቋመ መሆኑን አገልግሎቱም በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም የልማት ሥራን ማከናወን መሆኑን ተረድተናል:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ውክልና በሌላቸው ሰዎች የሚሰበከው ፀረ ሥራ ስብከት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ድምጽ አይደለም፤ እርሷ ይልቅ ከሥራ ጋር የታረቀች ነችና::

ይህንንም በተግባር ለማየት በገዳማት ብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ የተባሉ የሥራ እና የልማት መምህር ሰፊ የትምህርት ቤቱን ቦታ በብርቱካንና በሌሎችም ዕፅዋት የሞሉ መሆናቸውን እራሳቸው እየሠሩ ሌሎችንም ያሠሩ እንደነበር ሥራቸው ዛሬም ይመሠክራል:: በሰበታ የሴቶችን ገዳም፤ በዋልድባ እና በሌሎችም ገዳማት በእውነተኞቹ ባሕታውያን የክብት እርባታው፣ የልብስ ስፌቱ፣ እርሻው እየተቀላጠፈ እንደሆነ አይቶ መረዳት ይቻላል::

ከዚህ በላይ ያለው ለባሕላዊው የሥራ ማነቆ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መልስ እንደምትሰጥበት በአጭሩ የሚያብራራ ክፍል ነው:: ለማጠቃለል ያህልም ቤተ ክርስቲያን ከሥራ ጋር የታረቀች እና የሥራም መሪ መሆንዋን ተረድተን መቼም ቢሆን የትም ምዕራፍ ላይ ሥራ ኃጢያት ነው ተብሎ እንዳልተጻፈ መገንዘብ ይገባናል:: ከሥራ ጋር እንታረቅ::

ቀጥሎ ደግሞ ይህ በውስጣችን ያለውን በእምነት አሳቦ የሥራን መንፈስ የማጥፋት መጥፎ አዝማሚያ እየተቃወምን ለሥራ የማያመቹ ከሌላው ጎለም የሚወረሱ ጠባዮችን ደግሞ በዝርዝር እናያለን::

## ሐ. ከውጪው ዓለም የመጡ ባሕሎች

የውጪው ዓለም በሁለት የተከፈለ ትምህርት አለው:: አንደኛው የሚያለማ ጠቃሚ ሲሆን፤ ሌላው ግን እጅግ ጉጅ ጥፋትን የሚያስከትል ነው::

በዚህ ዘመን ዓለማችን በፈጠረችው ዘመናዊነት የተነሳ በትክክል ምድራችን የአንድ መንደርን ያህል ጠባለች:: ዛሬ አንድ ከአሜሪካ እንግሊዝ የሚጓዝ መንገደኛ በድሮው ጊዜ ከካዛንቺስ አቃቂ የሚሄድበትን ያህል ሰዓት እንኳን ሳይወስድ ይደርሳል::

ስለዚህ ኢራቅ ውስጥ የተተኮሰች አንዲት ቀለህ ኒውዮርክ ካለው የተባበሩት መንግሥታት አዳራሽ ድረስ ድምጽዋ ያስተጋባል እንደሚባለው:: በቴሌኮሙኒኬሽን፣ በኮምፒውተርና በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ምክንያት ዓለም ጥሩውንም መጥፎውን በትንሽ ደቂቃ ውስጥ ትጋራለች:: በድሮው ዘመን አባቶቻችን አገራችንን ከባዕዳን ወረራ ለመታደግ የተለየችና በሯን የዘጋች አገር ሆና እንድትኖር አድርገዋታል::

ሌሎችን የአፍሪካና የኤዥያ ዓለማት የሚወሩትን ወራሪዎች ለመከላከል አማራጭ አድርጐ የወሰደው በርን መዝጋት ብቻ ነበር:: በዚህ ምክንያትና በሌሎችም በጥቂቱ ከሥልጣኔ የተቆራረጥን ይመስላል:: ግን ዛሬ ወደድንም ጠላንም የዚህ ዘመን የመረጃ ልውውጥ ጠባይ ከእኛም የበለጡ ጠንካራ አገራትን በር እያስከፈተ ይገኛል::

ይህ ደግሞ የሚደረግብንን የባሕል ወረራ እንዳናጣራ ዕድል አሳጥቶናል:: በፊልም አዘጋጇ አሜሪካ ፊልም ቤቶች ገና ያልቀረበ ፊልም በአዲስ አበባ መንደሮች ውስጥ ሲቸበቸብ ማየት የተለመደ ነው:: በዚህ መሀል ከሥነ ጥበብ ሰውነት ይልቅ ወደ ወሮበላነት የሚስቡ የብልግና ዘፈኖች እየሰማ የሚውልና የሚያድር ብሎም ከሥራ ጋር የተጣላ ትውልድ እናፈራ ዘንድ እነዚህ ከንቱ ሽቀጦች የወጣቱን ሕሊና እንዳይሞሉት ያስፈራል::



አንድ ሮኬት ወደ ሰማይ የሚወነጨፍበት ሰዓት በደቂቃ ሳይሆን በሰከንድ፤ በሰከንድ ሳይሆን በሰከንድ ክፍልፋይ በሚለካበት ዘመን ቀኑን ሙሉ መዚቃ ማዳመጫ ጆሮው ላይ ሰክቶ ሱሪውን ከዳሌው በታች አድርጎ የሚፈረጋገጥ ወጣት ማፍራት የለብንም፤ ይህ ትውልዱን ከሥራ ጋር ማጣላት ነው::

ቢታመንም ባይታመንም እጅግ ዘመናዊ የሆኑ ጥሩ የአውሮፓም ሆነ የአሜሪካ አሳዳጊዎች (ወላጆች) ሣሎናቸው ውስጥ ቴሌቪዥን እንኳን የለም:: ጌምና ምናምን ሳይሆን ታላላቅ መጻሕፍት፣ የስፖርት መሣሪያ ዎችና የሳይንስ መሞከሪያ የተለያየ ጥበብ መቅሰሚያ መኝታ ቤት ውስጥ ነው ልጆቻቸውን የሚያሳድጉት:: ይህም ትውልዱን ከሥራ ጋር ለማስታ ረቅ የሚደረግ ጅምር ነው::

አንድ ወጣት በሥራ ይኮተኮት ዘንድ በስፖርት እንዲዳብር ዋና፣ ብስክሌት የመሳሰሉት ዝንባሌዎችን ያዳብር ዘንድ ሌሎቹን ዝባዝንኬዎች ማስወገድ ወጣቶችን ከሥራ ጋር ማስታረቅ ተገቢ ነው::

አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት ግቢውን እንዲቆፍር፣ ተክሎችን እንዲተክል፣ እንዲንከባከብ ማድረግ ከትምህርት ማስተጓጐል አይደለም:: ጨሊስን ብሎ ከውጪ የሚገቡ እርካሽ ሲኒማዎችን ማገድ ወጣቱ ብዙ ጊዜ ውን ጥናትና ሥራ ላይ እንዲያውል መርዳት ታላቅ ጥቅም አለው:: ይህም በውይይት እንጂ በማስገደድ አይሁን:: ብዙው ወጣት ከሥራ ጋር እንዳይጣላ ወላጆች ልጆቻቸውን ሥራ ማስለመድ አለባቸው:: የውጭው ዓለም ጥሩ ነገሩ እንጅ መጥፎው እንዳይወረን በእጅጉ ጥንቃቄ ይገባል:: ይልቅ ወጣቱ ሊቀስመው የሚገባ ዕውቀት ልክ እንደ ሕንዶቹ ወጣቶች ዓለም አቀፍ ገበያን የሚስብ ኢንጂነርነትን፣ ሐኪምነትን፣ ሳይንቲስትነትን መሆን ይገባዋል::

በ1492 እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር አሜሪካን ያገኛት አውሮፓዊ ኮሎምበስ በአሮጌው ዓለም አውሮፓ እና በአዲሱ ዓለም አሜሪካ መካከል የንግድ ልውውጥ እንዲደረግ ፋኑ ከከፈተ፣ መንገድ ከጠረገ ወዲህ የዚህች የምንኖርባት ምድር ሰድነት እጅግ እየተራቀቀ ሄዷል:: በእነዚህ ዘመናት

አውሮፓውያን ከሌላው ዓለም እየቀሙም እየወረሩም በንግድና በሥራ እየተቀራረቡ ሲሄዱ፣ በዚህ ዓለም የሀብትና የሥራ ውድድር እኛ ኢትዮጵያውያን ተዘለን በመቅረታችን የዓለማችንን የሥራ ዕድገት እንቅስቃሴ ሳንረዳ መዘግየታችን ጉድቶናል።

(የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ) በተባለው ከእንግሊዝ በተነሳው፣ መላው አውሮፓን ባጥለቀለቀውና ወደ አሜሪካ በዘለቀው የሥልጣኔ ዘመን እኛ በመሳፍንት አገዛዝ ስንታመስ የነበርንበት የኋላቀርነታችን ዘመን ነበር። በዚህ ዘመን ዓለማችን በተለያዩ መጠነ ሰፊ ልማቶች እጅግ ተፈ ትልካለች። ዓለም ከመካከለኛ መጠን ወደ ትንሽነት የተሰበሰበችው ከአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ነው። ይህ የሥልጣኔ ጉዞ በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተደናቀፈ. ቢመስልም እንደ አዶልፍ ሒትለርና ሌሎቹም ተቀናቃኞች እራሳቸውን ለመከላከል በጦር መሣሪያ ፍብረካና በሌላውም ሲራቀቁ፣ በጦርነት ጊዜ እንኳን በርካታ የሳይንስ ውጤቶች የሥራ ክንውኖች ታይተዋል። በዚህ ጊዜ በታላቁ ንጉሥ ዓፄ ቴዎድሮስ የብረት ቴክኖሎጂን ከአውሮፓ ለማስገባት መከራ ያዩበትና የኢትዮጵያ ራዕይ ጭላንጭል የታየበት ዘመን ሲሆን፤ ምን ያደርጋል ታዲያ ፈረሰኛው ቴዎድሮስና መጫወቻ ሜዳዋ ኢትዮጵያ በሐሳብ ሳይግባቡ ቀረና የቴዎድሮስ ሕልም በአጭሩ ተቀጨ። የቴዎድሮስን ፈለግ ተከትለው ለመራመድ የሞከሩት ዓፄ ዮሐንስ ብዙም ሳይጓዙ ቢያልፉም ዓፄ ምኒልክ ግን በስከነ የፖለቲካ አካሄድ የዓለምን ጥበብ ለአገራቸው ኢትዮጵያ ለማቅመስ የመጀመሪያው ሰው ሆኑ።

ዓፄ ምኒልክ ከሥራ ጋር የታረቁ እጅግ አስተዋይ ሰው መሆናቸውን ለማስታወስ ብቻ የሀገሪቱን ደን በማገዶ ምክንያት እንዳይመናመን ሲቆረጥ ቶሎ የሚያድግ ባሕር ዛፍ ብማስመጣት በዚያን ዘመን ሊታሰብ የማይችል አስገራሚ የሥራ፣ የልማት ሐሳብ ተይበው አልፈዋል። ከብስክሌት ጀምሮ የንግድ፣ የባቡር፣ የአውቶሞቢል፣ የስልክ የሆቴል ንግድ ቴክኖሎጂን ወደ አገር ቤት በማስገባት የሥራና የጥበብ ናፍቆትን አስተማሩ።



ምኒልክ ቴክኖሎጂን ወደ አገር ማስገባት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን ከሥራ ጋር የማስታረቅ የሥነ ልቡና ጦርነት የጀመሩ በሳል እና አስተዋይ መሪ ነበሩ።

ጥር 17 ቀን 1900 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ውስጥ ምኒልክ እጅግ በሳል የሥራ አዋጅ አውጀው አግኝተናል።

እንዲህ የሚል «ሠራተኛን በሥራው የምትሰድብ ተወኝ» የሚል የብስጭት የቁጣ መልዕክት ያዘለ «ከዚህ ቀድሞ ብረት ቢሠራ ጠይብ፣ ሸማ ቢሠራ ሸማኔ፣ ቢጽፍ ጠንቋይ፤ ቤተ ክርስቲያን ቢያገለግል ደብተራ፣ አርሶ ነጪን ከጥቁር አምርቶ የሚያገባውን አራሽ ከዘውድ ይበልጣል የሚባለውን ገበሬ፣ ወጥቶ ወርዶ ነጋዴን ነግዶ ወርቁን ግምጃውን ይዞ ቢገባ አንተ ነጋዴ ገጣባ አጣቢ እያላችሁ በየሥራው ሁሉ ትሰድባላችሁ። ልጁ ምናምን ሥራ የማያውቀው ሰነፉ ብልሁን እየተሳደበ አስቸገረ። ቀድሞም ቢሆን ሁለተኛ ፍጥረት የለም። ይህ ሁሉ ካለመማር የተነሣ ነው። አዳምንም «ብላዕ በሐፈ ገጽከ» ብሎታል። ይህ ከቀረ፣ ሁሉ ቦዘንተኛ ከሆነ መንግሥት የለ፣ አገር የለ በወዲያ አገር ግን በአውርፓ ሁሉም አዲስ ሥራ አውጥቶ መድፍ፣ ነፍጥ፣ ባቡርና ሌ ላውንም እግዚአብሔር የገለጠለትን ሥራ ሁሉ ቢሠራ መሐንዲስ እየተባለ እየተመሰገነ ሥራውን አብዝቶ ይጨምርበታል እንጂ በሥራው አይሰደብበትም፤ እናንተ ግን እንዲህ እየተሳደባችሁ ማረሻ የሚያሾል እንኳን አሳጥታችሁ አገሬን ባዶ ልታደርጉአትና ልታጠፉአት ነው።

ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንዲህ ብሎ የተሳደበ እኔን የሰደበ ነው እንጂ ሌላውን መሳደቡ አይደለም። ዳግመኛ ግን ሲሳደብ የተገኘ ሰው መቀጫውን አንድ ዓመት ይታሠራል። ሹማምንቱም አስረህ ዓመት ለማስቀመጥ የሚቸግርህ የሆነ እንደሆነ አስረህ ወዲህ ስደድልኝ» ጥር 17 ቀን 1900 ዓ.ም.።

በዚህ አዋጅ 3 ዐበይት ነጥቦች ተጠቃልለው ተጽፈዋል:: የመጀመሪያው ሠራተኛ ይሰደባል ሰነፍ ግን ይከፈሳል:: ስለዚህ ባለሙያ በሥራው በመሰደቡ ምክንያት ሌላው ቀርቶ ጋብቻ እንኳን ቢጠይቅ ስለሚከለከል፣ ሽክላ የሚሠሩትም ሳይቀሩ እንደሰው በላ ስለሚታዩ፣ ባለሙያ የነበረው ሕዝብ እና ሥራ በሙሉ ጠፍቶ በማከያው ማረሻ የሚያሾል የብረት ሠራተኛ እንኳን መጥፋት ደረጃ ሊደርስ መሆኑን እንረዳለን::

ይህ አጉል ባሕል ዳብሮ በዚህ ዘመን እንኳን ብዙዎቹ የስልክ እንጨት ተደግፈው ቀኑን ሙሉ አላፊ አግዳሚውን በዓይናቸው ሲቀበሉና ሲሸኙ ይታያሉ:: ይህ መሰበር ያለበት ባሕል ነው:: ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ጠፋ ወይ? የጠፋው ዝቅ ብሎ ከብረቱና ሸክላው ጋር የሚታገል ሰው ነው:: በገጠር ያሉ ሸክላ ሠሪዎች በአቅማቸው ድስትና ምጣድ ሠርተው ሸጠው እራሳቸውን ካሸነፉ የተማረው ወጣትማ ጥቂት ቢሠራ ምንኛ በተራመደ::

ቀደም ብለን እንዳነሳነው ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ሕዝቡን ለሥራ ማመቻቸት የባሕል ለውጥ ያደርግ ዘንድ መገፋፋት ብቻ ሳይሆን እራሳቸውም የሁሉ ምሳሌ በመሆን ሕዝቡን ሥራ አለማምደዋል:: በዚህም መሠረት በቤተ መንግሥታቸው አቅራቢያ ጠዋት ማታ እየተመላለሱ ለመጉብኘት ከሚያመችበት ቦታ ላይ የተግባረ ዕድ መሥሪያ ቤቶች አቋመው፣ በጊዜያው አስፈላጊያቸው የሆነውን (ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን) ዕቃና መሣሪያዎች ሁሉ ከውጭ አገር ሳያስመጡ እዚሁ ለማዘጋጀት ችለዋል:: ይሠሩም የነበሩት መሣሪያና ጌጦች ሌላውም ሁሉ ከዚህ ቀጥለው በየዓይነቱ የተዘረዘሩት ናቸው:: የብረት ሥራ፣ የወርቅና የብር ሥራ፣ የድንኳን ሥራ፣ የግንበ ሥራ፣ የአናጢ ሥራ፣ የቋም ጽሕፈት፣ የቤት ክዳን እና የመሳሰሉት ናቸው::

ይህንን ስናነብ እኝህ ንጉሠ ነገሥት ስለውጭ ምንዛሪ ስለኢንዱስትሪ እውቀት ጅማሬ በተፈጥሮ ንቃት ብቻ እንዴት እንዲህ ሊረዱት ቻሉ? ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፋናል::



ኢትዮጵያ በ1904 ዓ.ም. የጥይት ፋብሪካ የመሠረተች አገር ናት:: ይኸውም ጠላት እጅግ ቀለበት ውስጥ በከተታት ጊዜ የረዳት ታላቅ ድርጅት በአቃቂ አካባቢ የነበረ ነው:: ለባለእጆች ክብርና መብት በመስጠት በቤተ መንግሥታቸው ዙሪያ በማደራጀት ስድባቸውን በማስወገድ የሥራ አዋጆችን በማወጅ የሚኒስትር መሥሪያ ቤቶችን በማቋቋም ታላቅ ጅምር በማሳየታቸው ደግመን ደጋግመን ስንደነቅባቸው እንኖራለን:: ከዚህ ሁሉ ጋር የውጪ አማካሪዎቻቸውን በመደገፍ የስልክ የባቡር የመንገድ ሥራን የጀመሩ ሲሆን፤ ለእያንዳንዱ ሕግ በማዘጋጀት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርገዋል::

ከዚያ ቀጥሎ በሰፊው የቀጣይ ሥራ ላይ ጥልቀት ያለው መሠረት በመጣል ለሚቀጥለው የሥልጣኔ ዘመን ማዘጋጀት የሚጠበቅባቸው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ከሁሉ በፊት ዓፄ ምኒልክና ጅምራቸውን እጅግ በማክበር ሐውልት ካሠሩላቸውና መታሰቢያቸውን ካኖሩ በኋላ በእያንዳንዷ መሠረታዊ ልማት ላይ ጥልቀት ያለው ክንውን አካሂደዋል:: ለመሆኑ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምን ይጠበቃል? ብለን እንጠይቅ:: እኚህ ለሃምሣ ዓመት ያስተዳደሩ መሪ ከሥራ ጋር ያላቸው እርቅስ ምን ይመስላል?

ከሁሉ በላይ ሕዝቡን ለሥራ ማነቃቃትና ማስተማር ዋነኛ ሥራቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው እጅግ አታላይ በሆነውና ጥቅሙን ብቻ በሚፈልገው ዓለም ውስጥ መፍጠር የነበረባቸው የዲፕሎማሲ ብልጠት፤ ሦስተኛ መሠረታዊ ልማቶች ማለትም የውሃ ግድቦች፣ የመብራት ኃይል፣ የባንክ፣ የቴሌ፣ የመገናኛ ብዙኃን፣ የመከላከያ፣ የትምህርት ቤት መሠረት መጣል:: አራተኛ የሀገሪቱን ዳር ድንበር ማስፋት፤ አምስተኛ የውስጥ ፀጥታን ማስፈን የመሳሰሉት ናቸው:: ሁላችንም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሥልጣን በያዙበት ዘመን የነበረችውን ኢትዮጵያን ቀርቶ ዓለምን እንኳን ብናይ ሥልጣኔው እምብዛም ጉልቶ የሚታይ አልነበረም::

በአዲስ አበባ ከተማ ግፋ ቢል ባለሦስት ጉልላት ጉጆዎች ባለ ክፍክፋት የደጃዝማቾች ቤትና የተገነጣጠሉ መንደሮች ብቻ የነበሩ ሲሆን፤

ሕዝባችንም በአብዛኛው በግብርናና በውትድርና የሚተዳደር ነበር:: የባቡሩ ሐዲድ ሥራ በሙሉ ያልተፈጸመበት ጥቂቶን ግንባታዎች የሚታዩበት:: ሚኒስትሮች ሳይቀሩ በየቤታቸው እጅግ ኋላቀር በሆነ ሁኔታ የሚሠሩበት ጊዜ ነበር::

ስለሆነም ምንም ታላቁ ንጉሥ የሥራውን ዕቅድ አመቻችተው ቢያልፉ በየሚኒስትሩ ቦታ በየክፍሉ የሚሰየሙ ምሁራን ባልነበሩበት በውጭ አማካሪ እየታገዙ በሚሠሩበት ወቅት ነው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን የያዙት::

ስለዚህ ብዙ ወጣቶችን ወደውጪ አገር ልከው ማስተማር ነበረባቸው:: ከዚህ ሁሉ ውጣ ወረድ ጋር የውጪ ወራሪዎች የውስጥ የሥራ ጠላቶች የሕዝቡ ንቃተ ሕሊና ሁሉ ውጊያ ነበረው:: ከሁሉ በላይ አገሪቱም በሚገባ አልተማከለችም:: በወረዳ፣ በአውራጃ ማማከሉ ሌላው ውስብስብ ሥራ ነው::

በዚህ ሁሉ ጫና ውስጥ ዓፄ ምኒልክ የጀመሩትን የየሚኒስቴሩን መሥሪያ ቤት በሚገባ አጠናክረው እስከዚህ ዘመን ኢትዮጵያ የምትመካበት ጠንካራ ባንክ፣ ጠንካራ መከላከያ፣ አየር ኃይል፣ ጠንካራ አየር መንገድ፣ ጠንካራ ቴሌኮሙኒኬሽን እጅግ ተወዳጅ ዲፕሎማሲ እና ጠንካራ የትምህርት ቤት መሠረት መሥርተው በማለፋቸው እኝህም ንጉሠ ነገሥት ከሥራ ጋር ታርቀው አልፈዋል::

ድክመቶች አልነበሩም አንልም ግን የተሰጣቸውን የቤት ሥራ በብቃት ተወጥተዋል ወይ? ለሚለው አዎ ከሁለትና ከሦስት ት/ቤት ተነሥተው በየክፍለ ሀገሩ እና በየአውራጃው እስከ ሁለተኛ ደረጃ ከዚያም የገዛ ቤተ መንግሥታቸውን ለታላቁ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሰጥተው ጥራት ካለው የትምህርት አሰጣጥ ጋራ በመመሥረት ያከናወኑት ተግባር ፈጽሞ ሊዘነጋ ሊቃለልም የሚችል አይደለም::

ይህ እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ የነበሩት ኢትዮጵያ ያከናወነቻቸው ታላላቅ ሥራዎች ሲሆኑ፤ በሥነ ጥበብ በዕደ ጥበብ እጅግ ከመራመድዋ የተነሣ ብሩህ ተስፋ ካላቸው የአፍሪካ አገሮች አንዷ ለመሆን በቅታ ነበር::



በዚህ በእኛ እንቅስቃሴ ውስጥ ዓለም ከየት ወደየት እየተሸጋገረች ነበር?

ባለፉት ምዕራፎች በጥቂቱ እንዳየነው የአዲሱ እና የአሮጌው ዓለም የንግድ እንቅስቃሴ የአውሮፓ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ (ለውጥ) ከዚያም በፊት የነበሩት የሬነሰንስ እና ባዛንታይን ዕድገቶች አውሮፓንና እስያን ሥራ አዋቂዎች ጠቢባን ያደረጓቸው ሲሆን፤ በአውሮፓ የተደረገው የባሕል ተሐድሶ የአመለካከት ለውጥ አስከትሎ ሁሉም የሚኖርበትን አካባቢ ገነት ለማድረግ ደፋ ቀና ሲል ከርሟል::

በቻይና የባሕል እንቅስቃሴ፣ በጃፓንና በሌላውም የእስያ ዓለም አዲስ የሥልጣኔ ቁጥቋጦ ሲያቆጠቁጥ አፍሪካ በጨለማ ተውጣ ታንቀላፋ ነበር:: በዚህ መሀል የኢትዮጵያ ነገሥታት የነገሩ አዝማሚያ ገብቷቸው ዳር ድንበራቸውን በማጠር የአውሮፓን ጥበብ በመቅሰም ለማደግ ሲፍጨረጨሩ ታይተዋል::

ስለዚህም ብረት አቅልጠው ሰባስቶፖል የተባለውን መድፍ ለማምረት ተፍገምግመው የነበሩት ቴዎድሮስን ያስታውሷል::

ዓለማችን በክርስቶፎር ኮሎምቦስ አዲሱን ዓለም በማግኘቷ ከስፌነት ወደ መካከለኛነት መጥታለች ብለናል:: ስለዚህም ታላቁ የዓለማችን ቅርርብ ከመካከለኛው ምሥራቅ በእስያና በከፊል አፍሪካ አልፎ ሁሉንም አህጉር ያካተተ ልዩነቱንም የሰበረ ሆኖ ዓለም አቀፋዊነት ተፈጠረ ማለት ነው::

ከዚህ ቀጥሎ የተከተለው ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ 1800 ዓ.ም. ጀምሮ የተካሄደው ነው:: ይህም ዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅቶች ወይም ድንበር ዘለል የንግድ ኃይላት የፈጠሩት ኃይል ምድራችንን የባለ እንድትከማተር አድርጉ በሩቅ የሚተያዩ አገራት በታላላቅ መርከቦች ሸቀጣቸውን፣ የዕደ ጥበብና የሥነ ጥበብ የመገልገያ ቁሱንና ልብሱን መገበያየት የጀመሩበት፤ የወርቅ፣ የአልማዝ የባሪያ ንግድ ኃይለኛ ደረጃ የደረሰበት፤ ከዚህም አንጻር ዓለም አቀፍ ስግብግብነት ያየለበት፣ ትልቁ አገር ትንሹን በኃይል የሠበረበት ዘመን ነበር:: የመድፍ እና የነፍጥ መሣሪያዎች

የተወደዱበት የጥበብ እና የጦርነት ዘመንም ነበር:: መቼም በዚህ ዓለም መጥፎውና ጥሩው ጐን ለጐን ስለሚሄዱ ቀድመው እራሳቸውን ያላዘጋጁ ሁሉ በአስቃቂ ሁኔታ ተደፍቀው ነበር::

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዚህ ዘመን በሯን የዘጋችበት ዋና ምክንያትም ከዚህ የተነሣ ይመስላል:: ዓላማቸውን በሃይማኖት ሽፋን ደብቀው የሚመጡ ሚሲዮናዊያን እና ተጭኖ የሚመጣውን ግዙፍ ሠራዊት በመፍራት አባቶቻችን የሃይማኖት ሰዎች የተባሉትን ሁሉ ወደ አገራቸው ሲመልሱ ከርመዋል:: በዚህም የተነሣ ሀገራችን ዓለም ከሚገበየው የጥበብ ሲሳይ መሳተፍ ተስኗት ነበር:: ሕዝቧም ለሥራ እጅግም የነቃ ባለመሆኑ የባሕሉም የይሉኝታውም ሁኔታ ሽብቦት ስናዘግም እንደነበር ታሪካችን ይመስክራል::

በዚህ ዘመን አውሮፓውያን በኪነ ሕንፃ ተራቀው ከፍተኛ ደረጃ ደርሰዋል:: በጦር፣ በመንገድ ሥራና በሌሎችም:: ከሁሉ በላይ ግን የሳይንስ ተመራማሪዎቻቸው በየጊዜው በትጋት የሚፈለስፉት ኑሮን የማቅለያ ዘዴ እኛንና ዓለምን በእጅጉ እያራራቀ የሠለጠነውን ዓለም ግን እያጣመረ መጣ:: ስለዚህም በጣሊያን አማካኝነት አገራችን የቀደሙ የሥልጣኔ በሮችዋንና ወደቦችዋን እያጣች ለሕልውናዋ የምትታገል ተጠቂ አገር ወደመሆን ወረደች:: ቢሆንም ምንም የፈጠራው ነገር ባይሆንልንም ኢትዮጵያ በታላቁ ንጉሥ ምኒልክ አማካኝነት የዕደ ጥበብ ሰዎችዋን እየሰበሰበች ጊዜው እጅግ ካለፈ በኋላ ማረሻ መሥራት፣ መሽመንና በበሬ ጫንቃ ማረስዋን ተያያዘችው::

ጣሊያን ከታላቁ መሪ ከዳግማዊ ምኒልክ ጋር ያደረገው ጦርነት ግን ለኢትዮጵያ አንድ ምዕራፍ ከፋቶ እንደነበረ አይዘነጋም:: ይኸውም የውጪ አገር አሠልጣኞች በእኩልነት በኢትዮጵያ መንግሥት ሥር ሕዝቡን ያሰለጥኑ ዘንድ መግባት ጀምረው ነበርና ነው:: ኢትዮጵያውያንም ወደ ውጪ እየሄዱ መማር ሲጀምሩ ጠንክረን ከሠራን እነሱ የሠሩትን በመቅዳት በአጭር ጊዜ ሰው መሆን እንችላለን የሚል ተስፋ ተገኘ::



ግን ዓለም በ19ኛው ክፍለ ዘመን መልኳ ፈጽሞ ተለወጠ:: የዓለማችን የጥበብ ልጆች ቀድመው የተፈላሰፉት በ1869 እኤአ የመጀመሪያው ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ፓወር የሰው ልጅ በኃይል ላይ ያለውን ራዕይ እውን አደረገው:: እኛ ያኔ የላምባ ኩራዝም አልተጠቀምንም ነበር::

በ1876 የተጀመረው የቴሌፎን ኔትወርክ ብዙ ለውጦችንና መሻሻሎችን ፈጠረ:: ወዲያው በ1891 አውቶማቲክ ቴሌፎን ተፈለሰፈ:: ይህ ሁሉ ተአምር ከዓለም ጫፍ ያለው ቀዬ ከሌላው ጫፍ ጋር አንድ መንደር ይሆን ዘንድ የተደረገበት ነው::

በዚህ ዘመን ዓፄ ምኒልክ አሻግረው ዓለምንና እንቅስቃሴዋን የተመለከቱበት መበለጣቸውንም ያመኑበት፤ የዕድገት እንቅስቃሴ የጀመሩበት ዘመን ነበረ:: አሁንም ከተጣጣርን ገና ዕድል አለን በማለት ከአነስተኛ የጐጆ ኢንዱስትሪ የሚጀመረውን የልማት ሥራ ለመጀመር የብረት ሠራተኛውን፣ የወርቅና ብር አንጥረኛውን፣ የሽመናውን፣ የስፌቱን ጠቢባን ሳይቀር በዙሪያቸው ሰብስበው ሥራ ጀምረዋል:: የውጪውን ጥበብም በተመለከተ ሁሉንም በዘመናቸው ለመጀመር ካላቸው ጉጉት የተነሣ ከአይሮፕላን በስተቀር ያላስገቡት ቴክኖሎጂ አይገኝም:: በእያንዳንዱ ሥራ ላይም ሚኒስትሮችን ሾመዋል በወቅቱ ጥሩ ጅምር ነበር::

ይህ የፖለቲካውና የአስተዳደሩ መስመር ከፍጹማዊ ንጉሣዊ አስተዳደር ወደ ሕዝብ የመንሸራተቱ፣ በኅብረት የመሥራቱ ጅምር በ1922 ዓ.ም. ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የመጀመሪያውን ፓርላማ ሲከፍቱ የንጉሠ ነገሥቱንም ሥልጣን ሲወስኑ ሀገሪቱ ከብዙ የእስያና የአፍሪካ አገራት በልጣ እንድትታይ አድርጓታል:: በዛው ሰሞን የንሥረ ተፈሪ አውሮፕላን ሥጋ ሜዳ ማረፍ እና ሌላውም ኢትዮጵያንም እንደሌሎቹ ዓለማት ፈጣን ዕድገት ውስጥ ለመግባት የተንደረደረች አስመሰላት:: በዚህ ዘመን ግን እነአልበርት አነስታይን (special theory of relativity) የፈለሰፈበት ዘመን አልፎ water turbin 1919 አማካይነት ዓለም ወደ ታላቁ ፈጣን ቴክኖሎጂ ለመድረስ በማኮብኮብ ላይ ነበረች::

በዚህ ዘመን ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ አውሮፓ በጥቂቱ ወደ አሜሪካ ተላኩ:: ብዙዎቹ በሕግ፣ በሕክምና፣ በአስተዳደርና በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ እየተማሩ ወደ አገራቸው ተመለሱ:: ኢትዮጵያ በቂም ባይሆን እርሾ የሚሆን ባለሙያ ማግኘት ጀመረች:: የመጀመሪያዎቹ የጥቁር አንበሣ መኰንኖች ተመረቁ፤ በዚህ መሀል ለአምስት ዓመት ኢትዮጵያ በጦርነት ውስጥ ወደቀች:: ጣሊያን ምንም ወራሪ ቢሆን ባርያም አድርጕ ሊገዛ ቢፈልግ በመንገድ ሥራና በሌላውም ዘርፍ ንጉሡ ከጀመሩት ጋር ተጨማሪ መንገድ ከፈተ::

ንጉሡ ከስደት ከተመለሱ በኋላ ካቢኔአቸውን በተማሩ ሰዎች በመሙላትና የመሳፍንቱን አካሄድ ገሸሽ በማድረግ አዲሱን ትውልድ በትምህርት እንዲታጠቅ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለትምህርት ልዩ ትኩረት ሰጡ:: በውጪ ቆይታቸው የቀሰሙትን ሁሉ በተግባር ለማዋል ተጣጣሩ:: በተለይ በአሜሪካ አገር የሚማሩ ወጣቶችን በማሰባሰብ እራሳቸው ማኅበር አቋቋሙ:: ዓላማው በተለያየ ሙያ የሠለጠነውን ምሁር እንዲናበብ የዓለምን ጥበብ ወደገዛ ቋንቋው ገልብጦ የሩቅ ምሥራቅ ሰዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ በኢትዮጵያ የሥልጣኔን መንገድ መዘርጋት ነበር:: ያለመታደል ሆኖ የተሰባሰቡት ተማሪዎች በጥቂት በጥባጮች ተጠልፈው ዋናውን የልማት ሥራ ትተው ወደ ፖለቲካ ፍጅት በሚወስድ ፍልስፍና ውስጥ በመግባታቸው በቅንነት የተጀመሩ ተግባራት ሁሉ መበላሸት ጀመሩ:: ለወገኑ ታላቅ ተስፋ ይሆናል የተባለው የምሁር ኃይል በየሙያው የየግል ድርሻውን መወጣቱን ትቶ በአንዲት የፖለቲካ ኮርቻ መጋደል ጀመረ::

አልበርት አነስታይን የሳይንስ ንጉሥ መሆኑን ያየው ምሁር ኢትዮጵያዊ ለአንዲት የፖለቲካ ወንበር ሲፋጅ መታየቱ አሳዛኝ ትርኢት ነበር:: ከዚህ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ለዕድገት የምታደርገው ግሥጋሴ በተለያዩ ወጥመዶች ውስጥ የገባ ይመስላል::

የመጀመሪያው በእውነት አገሩን የሚወደው ኢትዮጵያዊ ምሁር ሁኔታዎችን በፍጥነት ለማሻሻል ከመፈለግ የመነጨ ተቃውሞ



በመንግሥት ላይ ማሰማት የጀመረበት:: በዚህ ሣቢያም የኢትዮጵያን ውድቀት የሚጠባበቁ የውጪ ኃይላት ቀለበት ውስጥ መግባቱ እውን የሆነበት አጋጣሚም ነበር::

በመንግሥትም በኩል እጅግ እያሰፈበት የመጣውን የንጉሣዊ አስተዳደር ቢያንስ ወደ እንግሊዝ እና ጃፓን መንገድ መርቶ በሕዝብ ለተመረጠ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሙሉ ሥልጣን የመስጠት ሂደቱ መዘግየት:: ሌላው ከንጉሡ ጋር ባለው የቤተሰብ ጸብም ሆነ የፖለቲካ ተቀናቃኝነት የሚወጠን ሴራ እና የተለያዩ ቡድኖች የሚያስነሱት የፀብ ፍልስፍና ተደምሮ የታንሣሥ ግርግሩን ዓይነት ያልተለመደ የመከፋፈልና የመጠፋፋት መንፈስ ተከተለ:: በዚህ ሁሉ ግርግር ተጀምሮ የነበረው ሥራ ሁሉ ውሃ በላው::

በአብዛኛው ተማሪ ከሙያ ትምህርት ይልቅ ፖለቲካውን በመምረጡ አገሪቱ በብዙ ተናጋሪዎች ግን በጥቂት ሠራተኞች እየተሞላች ሄደች:: መራርነት፣ እልኸኝነት፣ ቁጡነት፣ ደፋርነት ስድብ እንደ ታጋይነት መቆጠር ጀመሩ:: በዚህ አጋጣሚ አፍሪካን በተለይ እየበጠበጠ ያለው ኮሚኒዝም እስከነመርዛማ የፀብ ሐሳቡ የኢትዮጵያን ምሁራን አጥለቀለቃቸው::

ግራ የተጋቡ ማንነት የሌላቸው የፖለቲካ አቅጣጫቸው የተሳከረ የውጪ ዓለም ሰዎች የሳቡት የጸብ ፍልስፍና የተቀደሰችውን ኢትዮጵያን እስከ ራዕይዋና እስከነ ልጆችዋ ይበላቸው ጀመር:: በዚህ ጊዜ ዓለምን በቴክኖሎጂ እፍኝ የምታክል ትንሽ መንደር ሊያደርግ የተነሳው የምዕራቡ ዓለም ይስቅብን ጀመር:: ምክንያቱም ወደ ጨረቃ የጀመረውን ጉዞ የውሃ መንገድ አድርጕት ስለነበር:: ከእኛ ቢያንስ የሁለት መቶ ዓመት ርቀት ላይ በመሆኑ በማይጠቅምና በውይይት በሚፈታ የፖለቲካ እንኪያ ሰላንቲያ ተጠምደን ስላየን ነው::

ምዕራቡ ዓለም ብቻ ሳይሆን አሁን አድፍጠው የነበሩ ሩቅ ምሥራቆችም እንደ ሶቪየት ኅብረትና እንደ አሜሪካ እንደ አውሮፓ አዲሱን የሥልጣኔ ዓለም በእኩልነት ተቀላቅለውታል:: እነ ጃፓን

በአውቶሞቢላቸው ዓለምን አስደንቀው የሥራን ኃያልነት አሳይተው የነበረ ቢሆንም እኛ ግን ከዚህ ሁሉ መማር ሳንችል ቀርተናል።

የሰው ነፍስ ሳይጠፋ በጥገና ሊስተካከል የሚችለው አስተዳደር የእናቱን ልጅ ወንድሙን ኢትዮጵያዊውን እንደ ባዕድ እንደፋሺስት በማየት የነውጠኝነት፣ የአደገኝነትና የፋኖነት ጠባይ በገዛ ወገኑ ላይ ሊያሳይ የሚቃጣ ትውልድ ይፈለፈል ጀመር። በዚህ ጊዜ ግን ዓለም ኮምፒዩተር ፈጥራ (world network) ውስጥ በመግባት ለእኛ ሕልም የሚመስለውን ጥበብ በከፍተኛ ፍልስፍና እያራመደችው ነበር።

እንግዲህ በዚህ ዘመን ያለው ሦስተኛው እና እኛ ያየነው ጥበብ ይህ ነው። ከድምጽ ፍጥነት የበለጠ መጓዝ የሚችሉ ብቻ ሳይሆን የሚያስከነዱ ጀቶች የተፈለሰፉበት። ድሮ በዛገ ብረት እየተሰፈረ ምሥራቅና ምዕራቡን ደቡብንና ሰሜኑን የሚሰፈርበት ዘመን አልፎ ማሽን ተጠቅሞ የት እንዳሉ የሚታወቅበት በተራቀቀው አውሮፕላን በአስተማማኝ ዋስትና በሰዓቱ የተፈለገበት ቦታ የሚኬድበት የሚፈለገው መረጃ በየኮምፒውተሩ ተቀምሮ ዕውቀት የሚዛቅበት። አናድግም ብንልም እንኳን ዓለም እምቢ የሚልበት ዘመን ላይ ነን ያለነው።

በዚህ ዘመን ደግሞ ያኔ በኮሚኒዝም አሳበን ሁለት መቶ ዓመት ወደኋላ አሮጥን፣ አሁን ደግሞ በጎሣ ተከፋፍለን አንድ ዓይነት ምስኪኖች አንዱ እንደገዢ፣ ሌላው እንደተገዢ ሆኖ ሲተራመስና እየተበላላ ሲፋጅ በመታየቱ በምድራችን አራተኛው ክፉና አስቀያሚ ዘመን ተጀምሯል። እነ ኒይል አልምስትሮንግ ጨረቃን በ1969 ቅርብ አድርገዋታል፤ ሌላው ቀርቶ በዘመናዊው "dripfeed" irrigation system የመስኖውን ውኃ ከ1950 ጀምሮ መቆጠብ ችሏል። በ1981 "Train of great speed" ታላቅ ፍጥነት ያለው ባቡር (TGV) 380 ኪ.ሜ በሰዓት እየተፈተለከ አውሮፓን፣ ቻይናንና ራሽያን አንድ አገር አድርጓቸዋል። ምኑ ቅጡ በማርስ ላይ የምትሽከረከረው ሰው አልባ ትንሽ መኪና በሰጠችው መረጃ በመታገዝ ማርስ በሚባለው ፕላኔት ላይ የሚሿሿር መኪና በመንኩራኩር ተጭኖ ስለአረፈ ዛሬ ዓለም አስገራሚ የፎቶግራፍ መረጃዎችን ከማርስ እያፈሰ ነው።



የሚያስገርመው ደግሞ ይህ መኪና በሪሞት ኮንትሮል ከዚህ ከምድር መታዘዙ ነው።

አሁን እኛ የቱ ጋ ነን? ማለት አያስፈልገንም። ያለፋትን ብቻ ለመውቀስ እንደበቱን የሚያላቅቅ ቢኖር ትዝብት ላይ ስለሚወድቅ ዝምታ ይሻላል። ምን ይሻላል? ከሥራ ጋር መታረቅ፣ በፖለቲካ አለመራቀቅ፣ ስግብግብ አለመሆንና በየተፈጥሯችን ዝንባሌ ንጉሥ ለመሆን መጣር እንጂ ለወንበር አለመሮጥ፤ ፊጽሞ ዘረኝነትን መቃወም፣ እጅ ለእጅ ተያይዞ ጥርስን ነክሶ መሥራት፤ ከውጪ የሚመጡ የኮሚኒዝምና የጎሣ ፍልስፍናዎችን ከልብ መቃወም፣ በሰው ልጅ መብት ማመን ይህ ነው ከሥራ ጋር መታረቅ።

ዛሬም ገና አልመሸም ቀኑ በዘረኝነት መጋረጃ ሳይጨልም እጅግ ጨካኙ ዘመን ሳይመጣ እንታረቅ ለሥራ ብቻ እንነሳ።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ከታማኝነት ጋር መታረቅ

«እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን (የሌላውን) ጥቅም ያስብ እንጂ የራሱን ጥቅም ብቻ አይፈልግ»። «እኛ ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንድናሰኝ ይገባል። እያንዳንዳችንን እንድናደርገው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ።»* ርዕሳችን ከታማኝነት ጋር እንታረቅ ነው። ስለዚህም ከሁሉ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለን የሌሎችን ጥቅም ለማሟላት በጣርን ቁጥር ስለእራሳችን ብቻ ማሰባችንን እየተውን እንመጣለን።

ያለጥርጥር እምነት አጉዳይነት የደረጀበት ዘመን ላይ ነን ያለነው። ስለዚህም ለግላችን ባሰብን ቁጥር የማኅበራዊ ዋስትናችንም እጅግ እየመነመነ መሄዱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ከሁሉ በፊት ለብዙዎች ሲል እራሱን አሳልፎ የሰጠውን ጌታችን መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን

* ፊልጵ. 2፥1–4
* ጸመ ይ፡3

እያሰብን፤ የሰጠንንም ሕግጋት ልናሰላስለው ይገባል:: ታማኝነት ለማን? ለእግዚአብሔር:: ታማኝነት ለማን? ለሕሊና:: ታማኝነት ለማን? ለኅብረተ ሰቡ:: አንድ ወዳጄ «ከመልካም ስምና ሕሊና ጋር መሞት ታላቅ ዕድል ነው» ያለኝ ዘወትር ትዝ ይለኛል:: እጃችን፣ አንደበታችንና እግራችን እምነትን ከማጉደል የፀዳ ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር እንታረቃለን:: የሕሊና ነፃነት ይሰማናል፤ በኅብረተሰባችን እጁን አንደበቱንና እግሩን የጠበቀ ተብለን እንመሰግናለን::

እምነትን ማጉደል እጅግ ብዙ ክፍሎች አሉት:: የሚጠቃለለው ግን በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት ተመርቶ ክፉ በመፈፀም ነው:: ስለዚህ ነው ቅዱስ ያሬድ ዓይን ይጹም፣ እጅ ይጹም፣ እግር ይጹም፣ ጆሮ ይጹም እያለ የዘመረው:: ከምን መጾም እንዳለባቸው አንባቢው በጉደለ መሙላት ይችላል:: ሕሊናችንና መንፈሳችንን ከሚቆጠቁጥ ለአእምሮ ከማያመች መጥፎ ሥራ ሁሉ በመከልከል ከታማኝነት ጋር መታረቅ አለብን::

በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ እየተነተኑ ለመናገርና ለመጻፍ እጅግ ያስቸግራል፤ ግን አንድ የታማኝነት ሁሉ ምሳሌ የሆነ ሰው በተመደበበት የኃላፊነት ቦታ ታማኝ እንዴት ሊሆን ይችላል? በሚለው ርዕስ ብዙውን ጉዳይ ማጠቃለል ስለሚቻል ዘርዘር አድርገን ለማየት እንሞክራለን::

ከትንሿ ኃላፊነት ቦታ እስከ ትልቁ ሥልጣን የተሾምን ሁሉ ሹመታችንን ከሦስት አቅጣጫ ያገኘነው መሆኑን መረዳት ያስፈልገናል:: ሹመት ከእግዚአብሔር ይሰጣል፤ ሹመት በሙያችን ዓላማ ሥርዓት ይይዛል፤ በተጠቃሚው ሕዝብ ደስተኝነት ወይም መከፋት ይፈተናል:: ስለዚህ ለሥልጣን ያበቃን እግዚአብሔርን በሙያችን እንዳናሳፍረው በሕዝብም እንዳንጠላ ታማኝ አገልጋይ መሆን ይጠበቅብናል::

አንድ የቀበሌ ሊቀመንበር ሕዝቡ ሲመርጠው ታማኝ ነው፣ ባለሙያ ነው፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር አለው ብሎ ነው:: እምነት ማጉደል ደግሞ እነዚህን ሁሉ ማዕረጋት አፈር ላይ የሚጥል ክፉ አደጋ ነው::



ታማኝነትን ከሚያጉድፉ ዐበይት ነገሮች አንዱ በሥልጣን ላይ ለብዙ ጊዜ መቆየት ነው:: እንበል አቶ እንትና የእንተባበር ዕድር ሊቀመንበር ናቸው:: ሲመረጡ በታማኝነታቸው፣ በአስተዋይነታቸው ተወ ደው ነው:: እውነትም ለመጀመሪያ ጊዜ በዕድር ውስጥ ድንኳን የለም ነበር:: እሳቸው ከተመረጡ ወዲህ ድንኳን አሠርተዋል:: ብዙ የዕድሩ ሕግጋት ተስተካክለዋል:: ኩባያ እና አግዳሚ ወንበሮች ተገዝተዋል:: ግን ብዙ በቆዩ ቁጥር እየተሰላቹ የመጡ ይመስላል:: ከተመረጡ 8 ዓመት የሞላቸው ቢሆንም ሂሣቡን አላስመረመሩም:: ምርጫ ይደረግና ያስ ረክቡ ተብለው ቢነገራቸው እንደ አራስ ነበር ተቆጥተው ነበር ይባላል:: ስለዚህም ዕድር ውስጥ ያሉ ጓደኞቻቸውንና ዘመዶቻቸውን አስተባብረው የምርጫ ወሬ ያነሱትን ሁሉ ከዕድር በሰበብ አስባቡ ማባረር ጀምረዋል:: ጭምጭምታው ግን ጥሩ አይመስልም፤ አቶ እንትና ገንዘብ ጉድሎባቸዋል ይባላል:: ንግድ ብጤ የጀመሩት በዕድር ገንዘብ ነው ተብሎ በሰፊው ይወራል:: ምንም እንኳን ስለንጽሕናቸው በመሐላ ቢያስረዱም አዲት መርምሮ እውነተኛውን ካላረጋገጠ በስተቀር ማንም ሊያምናቸው ፈጽሞ አልቻለም:: እሳቸውም አብዝተውታል:: ምን ያህል ገንዘብ አለን ብሎ ለጠየቃቸው የዕድር አባል ከስድብ በስተቀር ሌላ መልስ የላቸውም:: ሚስጢሩ ግን እንዲህ ነው አንዱ ወዳጅ መስሎ የተጠጋቸው አጭበርባሪ ሰው አንድ ቀን ቤታቸው በምሽት መጥቶ ያስቀመጡትን የዕድር ገንዘብ ቢያዋጡ እሱም ያለውን ጨምሮ የሽርክና ንግድ ብንጀምር ብሎ ልባቸውን አሸፈተው:: ያችን የተቀመጠች 50 ሺህ ብር ንግድ ላይ አዋሏት:: ትርፉ ግን አመርቂ አልነበረም እንደውም ሽሪካቸው ገንዘባቸውን አታሎ ወሰደባቸውም ከዳቸውም ይባላል:: አሁን ከዕድር ሊቀመንበርነት ቢወርዱ ምን ያስረክባሉ ጭንቁ ይህ ነው:: ደግሞ የመጀመሪያዋን ገንዘብ ካጠፉ በኋ ላ በየዓመቱ የምትመጣዋ የመዋጮ ገንዘብ በየዕለቱ ለሚሞቱ ሰዎች ከመሆን ባትዘልም ከዛችም ይሸራረፋሉም ተብለው ይታማሉ:: በዚህ ምክንያት በተከበሩበት አገር ውርደት እየከበባቸው ስለመጣ በተቻላቸው መጠን ሊቀመንበርነትዋን ላለመስጠት ወስነዋል:: ንዴቱ ግን ለጨጓራ ለደም ብዛት ለስኳር ዳርጓቸዋል:: በሽምግልና ዘመናቸው ወደ

በመረጣቸው በገዛ ሕዝባቸው ፊት መዋረድ የሞት ሞት ስለሆነ ሥልጣናቸውን የመጥኘ ብለውታል::

በምድራችን እጅግ የተከበሩ ለሕዝብ ታላላቅ ቁም ነገር ያከናውኑ ይሆናል ተብለው የተገመቱ ታላላቅ ሰዎች እምነት በማጉደል ብቻ ታሪካቸው ከአመድ ውስጥ ሲርመጠመጥ ተገኝቷል:: ለምሳሌ ያህል እጅግ ትምህርት የሚሰጠንን የመጀመሪያዎቹን የአፍሪካ መሪዎች በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል::

አፍሪካ ከአስከፊው ቅኝ አገዛዝ መዳፍ ተላቃ መሪዎችዋን ስትሰይም እነዚህ አዳዲሶቹ ወጣት እና በሳል ምሁራን ልጆችዋ ከጨለማ ወደ ብርሃን ይዘዋት ተፈተለኩ ተብሎ ተተንብዮ ነበር:: አንዳንዶቹ ግን የባሰውን እጅግ አስከፊ ወደሆነ አዘቅት ጨመሯት:: በፍልስፍናቸው፣ በሕሊናቸው ብቃትና ጥራት የተመሰገኑት ታላላቅ መሪዎች ከበታቾቻቸው ባለው ወይም በራሳቸው ስግብግብነት ክብራቸውን አጡ:: ለሞት ሁሉ ተዳ ረጉ:: በጠላቶቻቸው ዘንድ መሳቂያ መሳለቂያ ሆኑ::

የመጀመሪያዎቹ የአፍሪካ መሪዎች በታላቅ መስዋዕትነት ለሕዝባቸው ነፃነትን ያጐናፀፉ ነገር ግን በሥልጣን ዘመናቸው ብዙዎቹ ስግብግብ ሆነው የተገኙ ሆነዋል:: ስለዚህ የሠሩት ታላቅ ሥራ የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉበት ሁሉ በስተመጨረሻው በዜሮ ተባዛ::

ለምሳሌ ጋናን መርተዋት የነበሩት ኩዋሚ ንክሩማህ በወንናቸው ታላቅ አክብሮትና ዝናን ያተረፉ መሪ ነበሩ:: በአሜሪካ ዩኒቨርስቲዎች በኢኮኖሚክስ ሳይኮሎጂ እና ፍልስፍና ዲግሪያቸውን የተቀዳጁት:: እኚህ ትልቅ ምሁር በሰላማዊ ጦርነት የእንግሊዝን ጦር ኃይል ያንበረከኩ ፓን አፍሪካኒዝም የተባለ የአፍሪካውያን የአንድነት መርህ ያነሱ ለብዙ ዘመናት ባለትዳር ያልነበሩ ብቸኛ ሰው ናቸው::

ከጋና የዜና ማሠራጫ ስማቸው ተነጥሎ የማያውቅ ሕዝባቸው የአፍሪካ መሲህ እስከሚሏቸው ድረስ የተወደዱ ንክሩሁማ ብቻ ናቸው:: ለማንኛውም የአፍሪካ ጉዳይ ጠያቂ በኩራት በጥበብ የሚመልስ ሰው ማነው ንክሩሁማህ:: ብዙ አገሮች ነጻ ሳይወጡ ገና የነፃነት አርበኞችን



ሰብስቦ ያበረታታ በእያንዳንዱ የአፍሪካ ነፃነት ውስጥ የሞቀ ተሳትፎ ያደ ረገ ሰው:: የአፍሪካ ልጅ ተብለው ነበሩ:: ወደ መድረክ ሲመጡ ፈገግታ የማይለያቸው breath of hope and means of freedom, brother-hood and racial equality በሚለው ዘያቸው የሚታወቁ ብዙ ራዕይ ለአፍሪካ ይዘው የተገኙ መሪ ነበሩ:: እጅግ የሚያስደንቀው እንደ ሩቅ ምሥራቁ ማኦ ሴቱንግ እንደ ሌኒን እና ማርክስ የእራሱ ፍልስፍና አለኝ ብለው እንደ አንድ ክፍለ ትምህርት ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የሚሰጥ "Nkrumahism" (ኒክሩማሒዝም) የተባለ ትምህርትም ነበራቸው::

ይህ በንክሩማህ አይዲዮሎጂ (አስተሳሰብ) የተቀረፀው ሥርዓተ ትምህርት በኋላ Complex political and social philosophy ተብሎም ነበር:: ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ይህ ፍልስፍና ለአዲስዋ አፍሪካ ከኢምፔሪ ያሊዝም ፈጽሞ ነጻ የሚያወጣ ነው ተባለለት:: በአጠቃላይ የምሽቱ የጋና ዜና «የእኛ ታሪክ ወደፊት ሲጻፍ ንክሩሁማ ነጻ አውጪያችን መሲሃችን የዘመናችን ነብይ ተብሎ ይጻፋል» ብሎ ያቀላመጣቸው ንክሩሁማ ሚኒስትሮቻቸው ወዲያውኑ በታላቅ ንቅዘት ውስጥ ሲወድቁ ዝናቸው እየሟሸሸ ፍልስፍናቸው እየተጠላ ቋንቋቸውና ፈገግታቸው የማይጠገበው ድምጻቸውን ለመስማት የማይወደዱ መሆን ጀመሩ:: በጋና ፓርላማ ፊት ለፊት የተቀረፀላቸው ሐውልት በድንጋይ ይደበደብ ጀመር:: ሰላማዊ ሰልፍ ተቀሰቀሰባቸው::

ለምን በሕዝቡና በሹማምንቱ መካከል የነበረው የሕይወት መስመር በመበጠሱ ነው:: ሕዝባቸውን ይመሩ የነበሩት ፋኖዎች ሕዝቡ በቅጽል ፕላቲኒየም ሕይወት ብሎ ወደሚጠራው ቅንጦት በአጭር ጊዜ ስለተሸጋገሩ ነው:: አንድ ጥናት እንዳመለከተው 1964 ዓ.ም. እኤአ ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ የሚሸመተው ውስኪና የተለያዩ መጠጦች ዋጋ ለገበሬው ማዳበሪያ ከሚወጣው ወጪ ስድስት እጥፍ ሆኖ ነበር ይላል::

አርተር ሉዊስ የተባለ ኢኮኖሚስት የገመገመውን ሲናገር በዚህች አህጉር እየተሠራ ያለውን በአጭሩ ለማስቀመጥ ለጥቂት ሰዎች ሥልጣንና ሀብት ተብሎ የሰው ልጆች ጥፋት ውድመት እየተካሄደ ነው

ብሎ ነበር:: ታዲያ በብቃታቸው በሕሊናቸው በመስዋዕትነታቸው የተመሠገኑ የተደነቁ ንክሩማህ የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎች በምግበሬ ከታሪክ መስመር ፈቀቅ ሲደረጉ ሲሳቅባቸው ፍልስፍናቸው ተረት ሆኖ ሲቀር ምሳሌነታቸው ሲቀለድበት ስናይ የየራሳችንን ሕይወት በጥልቀት እንድናየው አያስገድደን ይሆን? ለዓላማቸው ታማኝ የሆኑ የታሪክን አክሊል ሲቀዳጁ ታላቅነት ሳያንሳቸው በንቅዘት ብቻ ዝናቸው ዳዋ ሲበላው አያሳዝንም?

ለምን ንክሩማህ እና አመራሩ ተጠላ:: አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል፤ የንክሩማህ ሹማምንቶች አገራቸውን ሽጠው ለውጭ በዝባዦች የአገራቸውን ንብረት መደለል ደረጃ ደርሰው ስለነበር ነው:: ለምን አሥር በመቶው የእነሱ ስለነበረ:: በተለይ በ1961 Edusei የተባለው ሚኒስትር ሚስቱ ሦስት ሺህ ፓውንድ የሚያወጣ የወርቅ አልጋ ከእንግሊዝ ሱቅ ገዝታ በመገኘቱ ለባልዋ ማስጠንቀቂያ ተሰጠው ይባላል::

እንዲህ ዓይነቱ ሐፍረት ነው የታላቁን ሰው ዓላማ ከአፈር ያገባው:: በመጨረሻው ግን እራሱም ከዚሁ ዝርፊያ ገባበት ይባላል:: የአባትህ ቤት ሲወረር አብረህ ውረር እንደሚባለው::

በታላቅ ዓላማ የተነሳው ይህ ግሩም ሰው በብዙ ማባበል ንቅዘት ውስጥ ከገባ በኋላ ሰዎችን በማሥር አምባገነን የመሆን ጠባይ አሳየ:: ስለዚህ መድረክ ላይ ፈገግታ የሚያሳይ ቢሆንም እንኳን በስጨ እና ተስፋ የቆረጠ ብቸኛ ሰው ሆነ:: ንክሩማህ በ1965 ለኢሪክ ፖል በዐፀት እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር:: «ብቸኛ ሰው መሆኔን አስተውለሽው ታውቂያለሽ? እኔ በጣም ብቸኛ ሰው ነኝ፤ ያ ወይም ይህ ሰው ይወድሃል ብለሽ ልትነግሪኝ ትችያለሽ ወይም ጓደኛዬ ነው የምትይው ሰው ማነው? በ[illegible]ት እየተሰቃየሁ ነው:: በዚህ ምክንያት አንዳንዴ በእምባ እንድታጠብ ያደርገኛል:: እኔ ሁሉ ያገለለኝ ሰው ነኝ:: ሌላው ቀርቶ ከሕይወት እንኳን ተገልያለሁ:: አንቺ ብቻ ይህንን ትረጅዋለሽ:: ምናልባትም ጥቂት ሰዎች ለሕዝብ ስታይ ስስቅ ያዩኛል፤ ፈገግታዬን ያያሉ፤ የነበረኝን ራዕይ ታውቂያለሽ» ብሎ ጽፎ ነበር::



ይገርማል በታላቅ ዝና መድረክ ላይ የሚወጣ የሚስቅና ንግግሩን የሚያጣፍጠው ንክሩማህ ከነበረው ራዕይ ጋር ተጣልቶ ከዓላማው ከታማኝነቱ ጋር ተጣልቶ ለብቻው ያለቅሳል:: ማን ነው የሚያምነው በታላቁ ቤተ መንግሥት ውስጥ እየተንፈላሰሰ የሚኖር የሚመስለው የብዙ ሕዝብ እረኛ ከእምነቱ ውጪ እሱና የእሱ ሰዎች ንቅዘት ውስጥ ገብተው ሌሊት ሲያለቅስ እንደሚያድር::

ይህ አልነበረማ ዓላማው ታማኝነቱ ከውስጥ ሕሊና ጋር መጣላት እንዴት ክፉ ነው:: የሰበሰቡትን የዓላማ ሲሳይ ለጥቂት ንቅዘት ብሎ መበተን ከታማኝነት ጋር እንታረቅ::

ብዙዎቹ የአፍሪካ ሹማምንት አገኘን ብለው ያፈሱት ገንዘብ ለሕዝቦቻቸው ማዳበሪያ ወተትና ለትምህርት ቤት ጠመኔ ከመግዛት የሚዘል አልነበረም:: እጅግ ጥቂት ነው:: ንጽጽሩ የአንዲት ሕፃን ወተት እና የባለሥልጣኖች ግንብ ሕንፃ (ቤት) ነው:: ንጽጽሩ የአንድ ገበሬ ማዳበሪያ እና ለአንዲት ምሽት ተድላ የሚጠጣ ውስኪ ነው:: ይህ ነው ሕመሙ ከታማኝነት ጋር መታረቅ የሚያስኘው፤ ለዚህ ሳይሆን ይቀራል፤ ለሕዝብ የመቆም ፍልስፍናቸው እንዳይበረዝ እነ ማኅተመ ጋንዲ ሥልጣንን የሸሹት:: ለዚህ ይሆን እነ ዋሽንግተን ለአራት ዓመት ብቻ መርተው ሁሉን አደላድለው ሥልጣንን የናቁት:: ለዚህ ይሆን እነ ኔልሰን ማንዴላ ሳይስገበገቡ ጡረታ የወጡት፤ ለዚህ ይሆን እነ ኔሬሬ ሥልጣናቸውን በሰላም አስረክበው ወደ ግብርና የሄዱት፤ ለዚህ ይሆን እነ ኬኔት ካውንዳ ነጭ መሐረባቸውን እያውለበለቡ በክብር ዓለምን የሚዞሩት::

ከታማኝነት ጋር መታረቅ ከትንሿ የክፍል አለቅነት እስከ መምሪያ ኃላፊነት ከዚያም እስከ ሚኒስትርነት አልፎ ተርፎም ወደ መሪነት የሚያመራ ነው::

ከእኛ ትልልቆችም መካከል ሥልጣንን እንቢ ያሉ እንደ ሐዲስ ዓለማየሁ ዓይነት እንደነበሩ ማስታወስ ይገባል::

አገርን በሙያችን ማገልገል ግዴታችን ነው:: ግን ከሁሉ በላይ ከምዝበራ እራስን ማጽዳት:: ሁለተኛ ሳይመነችክ ኃላፊነትን ለሚቀጥለው ባለተራ ማሳለፍ ከታማኝነት ጋር መታረቅ ነው:: የአስተዳደር ጸጋ የሌለን ካልሙያችን ገብተንም መፈትፈት የለብንም::

በእኛ ሕዝብ መካከል የሚሰማው እምነትን ማጉደል እጅግ የበዛ ነው:: ምንም ከሌላው ዓለም ጋር ሲተያይ መካከለኛ ቢሆንም ለምን ወደ ፍጹምነት አንመጣም ብሎም መታገል ያስፈልጋል:: እንደ እውነቱ ከሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ጉቦም ቢኖር ወደ ከፋ ወንጀልነት የመድረስ አቅጣጫውን በቀላሉ መግታት ይቻል ይሆናል:: እንደ ሌላው ዓለም እስከ ነፍስ ግድያ ያደረሰ ባለመሆኑ ሳይቃጠል በቅጠል መረባረብ ይገባል::

ከሁሉ በላይ ሁሉም ሕዝብ ከዓላማ ጋር ጥሩ ዝምድና እንዲኖረው የሚሠርቀው የድኃዋን ሕይወት እንደሆነ ይረዳ ዘንድ የምዝበራን አስከፊ ደረጃ ማሳየት ይገባል:: በሃይማኖት ድርጅቶችም ሆነ በሰብዓዊ መብት አካላት በሕግም በኩል ያለውን ውጤት ተሿሚዎች በጥልቀት እንዲረዱ ማድረግ፤ በተለይ ተጠቃሚው ኅብረተሰብ ጉቦ መስጠትን እንደ አቋራጭ መፍትሔ እንዳይጠቀም በአጽንዖት ማሳሰብ:: በማሠር በመቅጣት ብቻ የሚደረገው መረባረብ ብዙም ውጤት አይሰጥም:: እርግጥ ነው ሁሉ ሕግን ማክበር አለበት:: ግን ከሁሉ በላይ የመንፈስ ተሐድሶ ከታማኝነት ጋር መታረቅ በውስጥ ሕሊናችን ካልታተመ ውኃ ቢወቅጡት ተመልሶ እንቦጭ ዓይነት ነው::

ጉቦ የምትሰጠው ልጅህ ትምህርት ቤት እንዲገባ፤ በሥራህ ላይ መቆየት ከፈለግህ ትከፍላለህ፤ ማንኛውንም በመንግሥት የሚሰጥ ግንባታ ኮንትራት ለመጫረት አሥር በመቶ ትከፍላለህ:: ታክስ የሚሰበስበው ታክሱን እንዲሠርዝልህ ካልሆነም እንዲቀንስልህ ትንሽ ጉርሻ ትሰጠዋለህ፤ ለዶክተሩ ለነርሷ ትከፍላለህ የተለየ ትኩረት እንዲሰጥህ:: ለፖሊስ ትከፍላለህ እንዳያስርህ:: ይህ የሐፍረት ዝርዝር ካለገደብ ይቀጥላል:: ይህ በናይጄሪያ ሕዝብም ሆነ ባለሥልጣናት የሚታወቅ የምዝበራ ዝርዝር ነበር::



ታዲያ በየጊዜው የተሾመ ሁሉ የድኃዋን መቀነት እያስፈታ አፍሪካ ድሃ ሆነች እንዴት ሊባል ይችላል? ገንዘቧ ተመዘበረ እንጂ:: ዳኝነት ሳይቀር የተጣመመ የሚሆነው በጉቦ የተነሣ ነው:: ለዚህ ነው ከኮሎኒ ተላቀኩ ብሎ ደስ ያለው አፍሪካዊ ፊቱ ወዲያው የዳመነው:: ለዚህ ነው የግል ንግዳቸውን በሚያካሂዱ ሹማምንት የሚመራው ድኃ ሕዝብ ከድኅነት ወደ መሐይምነት፣ ከመሐይምነት ወደ ዘረኝነት ከዚያም ወደ ፍጹም መፈረካከስ እየመራ የመጣው:: ለዚህ ሁሉ የሩዋንዳ፣ የናይጄሪያ፣ የአልጄሪያ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ እልቂት ተጠያቂው እምነትን ማጉደል ነው::

ይህ ሲባል ከላይ በአመራር የተንጠለጠለው ብቻ ሳይሆን የጉምሩክ ሠራተኛው፣ ተራው ፖሊስ፣ የግብር ሰብሳቢው እና የማዘጋጃ መሐንዲሱ ሁሉ እምነት ስለአጎደሉ ለአፍሪካ ውድቀት ተጠያቂዎች ናቸው:: በተለይ ሀገራችን ኢትዮጵያ የነፃነት እና የሥርዓት ዓርማ ተደርጋ የአፍሪካ አንድነት ጽ/ቤት ሳይቀር ከዚህ ሆኖ ሳለ እኛ የዚህ ሐፍረት አውራዎች እንዳንሆን መጠንቀቅ ይገባናል:: በአንጻራዊነት የተሻለ የተባለው ሥርዓት ዕለት ዕለት እየተበላሸ እንዳይሄድ ፈጣን ማሻሻያ ሕጎች የሞራል ትምህርቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው::

ይህ ሙስና ከመንግሥት ተቋማት አልፎ ተርፎ የሃይማኖት ተቋሞቻችንን እየነካካ ስለመሆኑ በሰፊው ይወራልና፤ ከዚህ ልብ የሚያፈስ ስንፍና ሁሉም እጁን እንዲሰበስብ ያስፈልጋል:: ምንም ይሁን ምን ከተጠያቂነት የሚያመልጥ ፈጽሞ የለም:: ደግሞ እምነት በማጉደል ከመክሰስ የበለጠ ሞት የለም:: ሌባ ካልዋት ብትመነኩስም አያምኗት እንደሚባለው ለልጆቻችን የሚተርፍ ሐፍረት እንዳናስቀር:: በጉቦ የምናሳድጋቸው ሕፃናት በሽተኛ፣ ሌባ እና መቅኖ ቢስ እንዳይሆኑ ከታማኝነት ጋር እንታረቅ::

በግል የምንወስናቸው ብዙ የሕሊና ዓላማዎች አሉ፤ ምንም ቢርበኝ የወንድሜን ዳቦ አልቀማም ብለን መወሰን አለብን:: እስቲ በኃላፊነት ላይ ያለን ወንድሞች ዘወር ብለን ወገናችንን እንየው::

ወገናችን እጅግ ድኃ ነው። ማዳበሪያ ለመግዛት ከዓመት ዓመት የሚቸገር ለልጆቹ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ መሸፈን ያቃተው ሙልጭ ያለ ድኃ ነው። ግን ከዚህ ሕዝብ ጋር የመንፈስ ብልጽግና አለ። ወገኔ ቢርበውም አይቅለበለብም፤ ካልባሰበት ተቸገርኩ አይልም ግድርድር ነው። እጁን ለልመና ከዘረጋ በኋላ የፊቱ ብርሃን ወደ ዕፍረት ይለወጣል።

አንድ ጳጳስ የውጪ ለጋሾች በተሰበሰቡበት አንድ አስገራሚ ንግግር ተናግረዋል። «የኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ረሃብተኛም እንኳን ቢሆን፤ መንፈሱ ግን እንደጠገበ ነው፤ ጋቢውን ገለጥ ሲያደርግ የተንጠለጠለው በቆዳ ማንገቻ የተያዘው ዳዊት ውስጥ የመንፈስ ምግብ አለ።» ብለው ነበር።

ይህንን ወደ አምላኩ ቢጸልይ ከአፈር የሚደባልቅ ሕዝብ በጉቦ ማንገላታትን መፍራት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ጋቢውን ገልጦ የሣንቲሙን ፍርፋሪ ከፍሎ ለልጆቹ የሰናነቃትን ፓውንድ መኻርጦ ለጉቦ ሲሰጥ። ልቡ ውስጥ የሚንቆረቆረውን እንባ የሚያይ የውስጥ ዓይን ይኖረን ዘንድ ያስፈልጋል። ገበሬው ቤት ያችን ለጉቦ የተሰጠች ፓውንድ የሚጠባበቁ ሕፃናት ሊታዩን ይገባል። ወገናችን ሞልቶለት ጉቦ አይሰጥም ሕግ መስሎት እንጂ። ታማኝነት ባለ ብዙ ዘርፍ ነው። ከተሜውስ ቢሆን የሚኖርባትን ቤት ለማትረፍ ወይም የተለያዩ ጉዳዮችን ለመቅረፍ የሚሰጠው ጉቦ በተመሳሳይ ቤት ወስጥ ለፈሰሱ ሕፃናት ምግብ መግገ ነው።

ባለሀብቱስ ቢሆን ለልማት የመደባት ገንዘብ በየጉቦው መስረግ ረግዋ አግባብ ነው? ስለዚህ የሕዝብ ገንዘብ ላለመዝረፍ በሕሊናችን ፍርድ ቤት እጃችንን ዘርግተን ቃል መግባት አለብን። እምነትን ስለማጉደል እርቅ ያስፈልጋል። የሌላውን ቤት ዘግተን ሌሎችን ሕፃናት አስለቅሰን ልጆቻችንን ለማጥገብ መሞከራችን የግፍ ግፍ ነው። እጅግ የሚገርመው የቤተሰብ ሽማግሌ ለመሽምገል የውሎ አበል መቀበል ደረጃ መድረሱ ነገሩ እንዲጉተት ተንከል መግመዱ ሽማግሌዎች ሳይቀሩ በእርቅ ሰበብ የሰው ትዳር ሲያፋቱ የታየበት አጋጣሚ አለ። ይህም እርቅ ይፈልጋል።



በሐሰት መመስከር መበየን የእምነት ማጉደል ቁንጮ ነው፤ ያላየኸውን አትመስክር፤ በጉቦ አትዳኝ ለልጅ ልጆችህ ጥፋት እንዳታቆይ። እስከዚህ ድረስ ያየነው ታላላቅ መሪዎችም ሆኑ ዓላማ ያላቸው ግለሰቦች እምነትን በማጉደል ብቻ ከታላቅነታቸው እንዴት እንደሚንሸራተቱና እንደሚዋረዱ ነው።

እስቲ ደግሞ በዓላማቸው የጸኑ ምን ማዕረግ ላይ እንደሚደርሱ በተከታዩ የአንድ አፍሪካዊ መሪ ታሪክ ለማየት እንሞክር። ይህ ከዚህ በታች የምናቀርበው መሪ ስህተት የለበትም ሳይሆን ታማኝ ሆኖ በመሰለው አገር ይጠቅማል ብሎ ባመነበት መንገድ የተጓዘ ሰው ነው።

ዶ.ጁሊየስ ኔሬሬ ይባላል። ኬንያን የምትዋሰነዋን አገር ታንዛኒያን ከ1972 እኤአ ጀምሮ የመራ ፕሬዝዳንት ነው። እንደማንኛውም የምዕራቡም ሆነ የምሥራቁ የመካከለኛው የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ታንዛኒያ ነጻ በወጣች ጊዜ የመጀመሪያዋ መሪ ዶ.ጁሊየስ ኔሬሬ ነበር። በሕዝቡ የተሰጠው ስም በስዋሕሊኛ «Mwalimu» «መምህር» የሚል ቅጽል ሲሆን፤ ብሔራዊ ስሜቱ ተነግሮ የማያልቅ በዓለማችን ታላቅ ከበሬታን ካገኙ መሪዎች አንዱ የሆነው ይህ ሰው ላቅ ያለ ለውጥ በዚህች ምሥራቃዊ አፍሪካ አገር ያመጣል ተብሎ የተተነበየለት መሪ ነው። ቀጠን ያለ ቁመና እና ዘወትር ከከንፈሩ በላይ ትንሽ ጢም አስቀርቶ የሚላጨው ብዙ መሽቀርቀር የማይወደው ኔሬሬ ብዙ አጀብ እና መቀማጠልም አያስደስተውም ይባልለታል። በአብዛኛው ለዝቅተኛው ኅብረተሰብ ሲቆረቆር ይታያል። እንደውም አዘውትሮ «Poorest of the poor demanding a new international economic order that would give them a greater share in the world's wealth.» ጉስቋሎችን ከሰው እኩል የሚያደርግ ዓለም አቀፋዊ የሀብት ክፍፍል መደረግ ይኖርበታል ሲል ይሰማ ነበር።

ባለችው ጊዜም ከሼክስፒር ድርሰቶች የቬነሱ ነጋዴን እና ጁሊየስ ቄሣርን ወደ ስዋሕሊኛ ተርጉሟል። ካለው የሥነ ጽሑፍ ችሎታ የሕሊና ብቃት የተነሳ በእንግሊዛውያን ዘንድ የረጋ የሰከነ መንፈስ ያለው በእራሱ

የሚተማመን ሰው አሰኝቶታል:: በ1963 እኤአ የአፍሪካ አንድነት በተመሠረተበት ዘመን የመላው አፍሪካ ዕድገት ያበበት ጊዜ እንደመሆኑ እንደኔሬሬ ዓይነቶቹ በሳል የአፍሪካ ልጆች በአንድነቱ እጅግ ዘመናዊ ሐሳብ በማቅረብ አህጉራዊ መነቃቃት ፈጥረው ነበር::

ጁሊየስ ኔሬሬ ምንም ብሔራዊ ስሜቱ ያየለ ለአህጉሩም አንድነት ከልብ የሚሠራ በንቅዘትም የማይታማ ቢሆንም እንኳን በአንድ ፓርቲ ሥርዓት የሚያምን እንደውም ጠንካራ መንግሥት እና ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር ለመመሥረት መድበለ ፓርቲ እንቅፋት ነው ብሎ የሚያምን ነበር:: ከሁሉ በላይ ይህ መሪ የሚታወቅበት መለያ ሶሻሊዝምን ከሌኒን ወይም ከማርክስ እንደወረደ መቀበልና በአገር ውስጥ ለመተግበር መሞከር ተገቢ አይደለም:: ከየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማዛመድ ያስፈልጋል ብሎ ያምን ነበር:: ይህ አቋሙም በኮሚኒስቶቹ የአፍሪካ አገራት «የኔሬሬ ተምኔታዊ ሶሻሊዝም» የሚል ቅጽል እንዲሰጠው አድርጐታል:: በተለይ በሀገራችን ኮሚኒስቶች ዘንድ የተሳሳተ መሪ አሰኝቶት ነበር::

ዶ.ጁሊየስ ኔሬሬ በኢኮኖሚው መስክ እጅግ አስደሳችና አሳዛኝ ጅምርና ፍጻሜ ያጋጠመው መሪ ነበር:: ይህ ሰው በሐቅ እና በዕቅድ በእርጋታ የታንዛኒያን ኢኮኖሚ ማሳደግ ይቻላል ብሎ የሚያምን ከምዕራባውያን ብድርና እርዳታ መራቅ አስፈላጊ መሆኑን በጥብቅ የሚያምን መሪ ነበር:: እኛ በአንድ ጊዜ እንደ ሙጃ ማደግ እና መጠውለግ ሳይሆን ቀስ በቀስ እንደዝግባ መግዘፍ ነው ያለብን ይልም ነበር:: ስለዚህ ታንዛኒያ ያላትን የውጭ ንግድ በማሳደግ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ መሠረታዊ ልማቶችን በተቻለ ፍጥነት ለማበልፀግ ሞክረዋል:: ሌላው ቀርቶ ለዓለም ድሆች እንኳን የዓለማችንን ሀብት በእኩል በማካፈል ችግረኛ እንዳይኖር ማድረግ አለብን የሚል አቋም እንዳለው በሰፊው ይነገርለታል:: ከግል ባሕሪው የተነሣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝናን በማትረፍ የውጭ እርዳታ በማግኘት ሁሉ ሀገሩን ጠቅሟል:: ቢሆንም በውጪ እርዳታ እና ብድር መተማመንን በእጅጉ ይጠላ ይቃወምም ነበር::



ገንዘብን ለማግኘት ብቻ ወይም እንደዋነኛ ጉዳይ አድርጐ መሮጥ ጅልነት ነው:: አገራችን ድኃ እንደሆነች እኛ ድሆች ነን ብለን ከማመናችን የበለጠ በሌሎች እርዳታ ላይ መተማመኑ የባሰ ጅልነት ነው:: በትክክል ጅልነት ነው፤ ድህነታችንን በለጋሾች ችሮታ መወጣት እንችላለን ብሎ ማመኑ የትም አያደርሰንም:: ከሁሉ በፊት ገንዘብ አናገኝም አይሰጡንም፤ የትኛውም አገር ድህነታችንን በችሮታ፣ በብድር፣ በእርዳታ ሊቀርፍልን አይችልም::

እራስን መቻል ማለት በራስ መተማመን ነው:: አንዲት አገር በሌሎች እርዳታ እና ብድር ልማትዋን ለማካሄድ ከፈለገች እራስዋን የቻለች ልትሆን አትችልም:: እኛ እንዴት መሠረታዊ ዕድገታችንን በሌሎች መንግሥታትና ድርጅቶች ላይ አድርገን እንተማመናለን:: እነርሱ እርዳታና ብድር ሲሰጡን እኛ ደግሞ ታላቁን ነፃነታችንን በምትኩ መስጠት አለብን:: እውነቱ ግን አንችልም ነው::

ይህ ከዚህ በላይ የተነበበው የጁሊየስ ኔሬሬን እምነት የሚያንፀባርቅ ንግግሩ ነው:: ስለዚህ የዚህ ታላቅ መሪ መፍትሔ ወይም ማጠቃለያ ሐሳብ ከዚህ ቀጥሎ ተገልጿል::

«በእርጋታ የሚያድግ ገጠሩን ማዕከል ያደረገ በራስ መተማመን ላይ የተመረከዘ የገጠር ልማትን በማካሄድ ማደግ የሚል ነበር::» በዚህም መሠረት እራሳቸውን የቻሉ መንደሮችን በመመሥረት ረጅሙ የዕድገት ጉዞ ተጀመረ:: አቅም በፈቀደ መጠን የገጠር ከተሞችን በማጠናከር የንጹሕ ውሃ አቅርቦት፣ መብራት፣ ትምህርት ቤትና ክሊኒክ ያላቸው መንደሮችን መመሥረት ጀመሩ:: በአጋጣሚ ግን በጊዜው ፋሽን ሆኖ የነበረውን (mass nationalization) የግል እና የድርጅቶችን ሀብት መውረስን ታንዛንያም ተጋርታለች:: በዚህም ምክንያት ታላላቅ ገበያውን በመቆጣጠር (አፓርታማ) ሕንፃዎች ቪላዎች ሁሉ ተወርሰዋል:: የኮሚኒዝም ጠባይ ስለሆነ ምንም ማድረግ አይቻልም::

ኔሬሬ በመስከረም ወር 1967 ዓ.ም. ከታንዛኒያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ኡጃማ የተባለ ንድፍ አዘጋጀ:: በስዋሕሊኛ ቤተሰባዊነት

ማለት ዓላማው መላው ታንዛኒያዊ እንደ ቤተሰብ ይኖር ዘንድ የተዘጋጀ ነው:: ስለዚህም ሶሻሊዝምን በእራሱ የአስተሳሰብ መንገድ ጠመዘዘው:: ይህ አካሄድ በብዙ አገሮች የተለመደ ነው:: እነ ናስር በግብጽ፣ እነ ጋዳፊና ሌሎቹም እስላማዊ ሶሻሊዝም እያሉ ከባሕሉና ከሃይማኖቱ ጋር ሁሉ ሲያዳቅሉት ታይተዋልና::

የእኛ የእርሻ መዋቅር በኅብረት በአንድነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ለምሳሌ በአንድነት ሆነን መሬቱን እናርሳለን:: ስለዚህ «የእኛ መሬት» እንላለን:: ምርቱም ሲደርስ «የእኛ እህል» ብለን በቤተሰብ ቋንቋ እንናገራለን:: ሱቁ ሁሉ የእኛ ነው እንላለን የሚል መሠረታዊ ሐሳብን ያካተተ የዕድገት መንገድ በንድፍ ደረጃ አቀረበ::

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ታላላቅ የንግድ ድርጅቶች ወደ መንግሥት ንብረትነት ተቀይረዋል፤ መንደሮችም መመሥረት ጀምረዋል:: በዚህ ውስጥ ግን ችግሮች መከሰታቸው አልቀረም፤ የመጀመሪያው ችግር የንግድ ድርጅቶች ከባለቤቶች ተነጥቀው በሥራ አስኪያጅ የሚተዳደሩት ተቋማት፤ ተግቶ ለግሉ እንደሚሠራው ነጋዴ ምርታማ ሊሆኑ አልቻሉም:: ምክንያቱም ሥራ አስኪያጆች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ቡና በመጠጣት ስለሚያሳልፉት ግድ ስለሌላቸው የሆቴሎቹ አስተናጋጆች ዳተኛ በመሆናቸው ይህ ሁሉ ተጨማምሮ ምርቱ ማቆልቆል ጀመረ::

በሠፈራው አካባቢ ኔሬሬ እንደተለመደው ረጋ ያለ ዕድገት ማሳየት ጀመረ:: ይኸውም ከ1968 እ.ኤ.አ 180 መንደሮች በጥራት መመዘኛው መሠረት ብቁ ሆነው ሕጋዊ ዕውቅና አገኙ:: እነዚህ መንደሮች ሲመሠረቱ ኔሬሬ የኡጃማ መንደሮች በፈቃደኝነት የሚመሠረቱ ናቸው ብሎ ስለጀመረ ገበሬው በፈቃዱ የመሠረታቸው መንደሮች ናቸው::

ኔሬሬ በውጤቱ አልረካም፤ በ1969 በፓርቲው ስብሰባ ላይ ተጠናክረን እነዚህን መንደሮች ማሳደግ አለብን በማለት ከፍተኛ ትኩረት እና ቅስቀሳ ተደርጐ እስከ 1973 ዓ.ም. ድረስ አምስት ሺህ መንደሮች ተመሠረቱ:: ይህ ዕድገት በዓለማችን ከፍተኛ እና አመርቂም ነው:: በእነዚህ መንደሮች ወደ 2 ሚሊዮን ሕዝብ ወይም 15 በመቶው ከአገሪቱ ሕዝብ



ውስጥ የተሳተፈ ሲሆን፤ እነዚህ ሁሉ መንደሮች ሲመሠረቱ በመመዘኛው መሠረት ንጹሕ ውኃ፣ መጠለያ፣ ት/ቤት፣ ክሊኒክና ሱቆች በተቻለ መጠን ተሟልተው ነው::

በዚህ እጅግ የተበረታታው ኔሬሬ ከዓለም አድናቆትን በማግኘቱ ዕቅዱም ከግብ እየደረሰ በማየቱ በ1977 ዓ.ም. በከፍተኛ ስሜት ተነድቶ በአንድ ጊዜ ወደ 11 ሚሊዮን ሕዝብ ለማስፈር አንቀሳቀሰ:: ከዚህ በፊት ገበሬዎቹ በፈቃዳቸው ነበር የሚሠፍሩት አሁን ግን ኃይልም የተቀላቀለበት ሆነ:: በዚህም ምክንያት ካለበቂ ጥናት ይህንን ያህል ሕዝብ በአንድ ጊዜ በማንቀሳቀስ ታላቁ በእርጋታ የማደግ ውጥን ከሸፈ::

ከደረጀበት አካባቢ ተነቅሎ አዲስ የሚሰፍረው ግዙፍ ሕዝብ እንደ ሙሴ ጊዜ መና ካልወረደለት በስተቀር ምንም ሊመክተው አይችልምና:: የአገሪቱ ኢኮኖሚ በእጅጉ ተጐዳ:: ታላቁ መሪ ኔሬሬም ከዓለም ኅብረተሰብ ወቀሳ፣ በአገር ውስጥም ረሃብና ብሶት እየተባባሰበት መጣ:: «ዕቅዳችን ታላቅ ነበር፤ግን በአፈጻጸም ስህተት ሠርተናል» ብሎ እራሱን ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፍሪካ መሪዎች የወቀሰው ኔሬሬ ሳይወድ በግድ እጁን ወደ እርዳታ ዘረጋ:: ብድሩንም አፈሰው:: በእራስ መተማመኑን ሲያጣ ታላቅ ዋጋ የተከፈለለትም ነፃነትም እንደሚሸረሸር ቢገባውም ግን ስህተትን በስህተት በመሸፈን የጊዜውን ሕዝብ የማዳኛ መፍትሔ እርዳታንና ብድርን መረጠ::

ቢሆንም ይህ ሰው እጅግ ቅን ስህተት የተሳሳተ የግል ንብረት የሌለው ከዓለም የመጨረሻው ደሃ ርዕሰ ብሔር በመሆኑ ዓለማችን አድናቆትዋን አልነፈገችውም:: በንቅዘት ውስጥ እጁን ባለማስገባቱ ታንዛኒያውያን እንደ ባሕል ልምዱን ይጠቀሙበታል በጣለው ጥልቅ መሠረት የተነሳ በአፍሪካ በሰላምዋ፣ በዕድገትዋ፣ በፀጥታዋ የምትታወቅ አገር አደላድሎ አልፏል:: በነገራችን ላይ የምድራችን የመጀመሪያው ደኻ መሪ የ400 ብር ደሞዝተኛ ነበር::

የተቻለውን ሠርቶ ሥልጣኑን በሰላም ለሚቀጥለው ተረኛ አስረክቦ ታላቅ ውለታ የዋለላቸው ገበሬዎች መንደር ለጡረታ ሲሄድ ገበሬዎቹ ቤት አዘጋጅተው ትራክተር ገዝተው ነው የጠበቁት:: ታላቁ መሪ በመጨረሻ ዘመኑ ገበሬ እና የአፍሪካ አስታራቂ ሆኖ በሰላም አርፏል::

ታዲያ ይህ ሰው የሚያስተምረን በዓላማ መጓዝ፣ በይበልጥም በርዕሳችን እንደተገለፀው ታማኝነትን ነው። ንክሩማህና ኔሬሬ ለአገራቸው ቅን የሚያስቡ ታላላቅ መሪዎች ናቸው። ግን መጨረሻቸው በንቅዘት ተለ ያይቶ አንደኛው በአድናቆት ሌላኛው እንደነገሩ አለፉ፤ የእኛስ ምርጫ የቱ ነው?። በትንሿ ኃላፊነት ሳይቀር በታማኝነት ማገልገልና መከበር አይሻልም፤ ከታማኝነት ጋር እንታረቅ።

ይህንን ርዕስ የምናጠቃልለው ከብዙ ሀብት ይልቅ የሕሊና ንጽሕና የውስጥ ሰላም ስለሚበልጥ ከጥሩ ስም ጋር መሞት ከክፉ ስብዕና ጋር ከመኖር ስለሚሻል በሕሊናችን ከታማኝነት ጋር መታረቅ ይገባናል። ነገር ግን ከቤተሰብ ሕይወት የጀመረው አለመታመን እያደገ መጥቶ አሁን አገርንም እያስቸገረ ይገኛል። ባል ገቢውን ለገዛ አካሉ ለሚስቱ አያሳያትም፤ የወንድ ደመወዝና የሴቶች ዕድሜ አይነገርም በሚል ፈሊጥ ሚስት ከገዛ ትዳርዋ ሠርቃ ለዘመዶችዋ ትሰጣለች የሚባል ሐሜትም ይሰማል። ይህ ግልጽ ያልሆነ ትዳር አንድ ቀን ሲፈርስ ሊያስደነግጥ ቢችልም ነገር ግን ታማኝነት ስለአልነበረው ሲሸረሽር እንደኖረ ማንም ሊረዳ ይገባል።

ይህ የቤተሰብ ችግር ወደ ማኅበረሰቡ ተጋብቷል። ሽሮና በርበሬ ጥራጥሬ የሚቸረችሩ ነጋዴዎች መሥፈሪያ ቆርቆሮውን ከኋላው ወደ ውስጥ ቀጥቅጠው በዓባይ ሚዛን ሲሠፍሩ እርግማን መሆኑን ማስተማር ይገባል። ከታማኝነት ጋር እንታረቅ።

ለሰው ጨጓራ ጤንነት የማያስቡ በርበሬና ቀይ ሸክላ ደባልቀው ሲሸጡ ይህ አለመታመን ምን ያህል እንዳደገ እንዳሸቀበ። ሕዝባችን ውስጥ አሳፋሪ ክህደት እንደገባ ለዚህም ከታማኝነት ጋር በፍጥነት መታረቅ እንዲገባ ልንረዳ ይገባል። ቅቤ እና ሙዝ ቀላቅለው የሚሸጡ ስግብግቦችን ኢትዮጵያ ፈጽሞ እንደማትታገሳቸው፣ አረቂና በረኪና ደባልቀው የሚሸጡት በወንጀል እንደሚፈለጉ ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህ ሁሉ ታማኝ አለመሆን፣ እምነትን ማጉደል ይባላል።



ከዚህ አልፈው ተርፈው ዘመናዊ ባርነት የሚያካሒዱ ድኃ እህቶቻችንን ወደ ዐረብ አገር የሚሸጡ ዓይን ያወጡ የባሪያ አስፈንጋዮች በሕዝባችን እየተጫወቱ ሊኖሩ ፈጽሞ አይችሉም፤ ወይ ከታማኝነት ጋር መታረቅ ወይም በሕግ ሥርዓት ሊያሲዙዋቸው ይገባል።

ወጣቱ ልቡ ወደ ውጭ አገር ተሰቅሎ እንዲቀር፣ የማናውቃቸው ጨካኝ ሕዝቦች በፍጹም ባርነት እየገዙት ይኖር ዘንድ ከዚያም አልፎ ተርፎ ሬሳቸው ከቆሻሻ ጋር እስኪጣል ድረስ በባዕድ አገር ያዋረዱን እነዚህ ግለሰቦች ግፍ የተሞላ ንግዳቸውን የሕግ አምላክ ያይልን ዘንድ፣ መንግሥትም ለወገን ፍጹም በማሰብ ስሜት ቁጥጥር እንዲያደርግ የእርቅ ሐሳባችንን እንሰጣለን።

ወጣቱም የትም ዓለም ተዋርዶ ከሚገኘው ሀብትና ንብረት በአገር ውስጥ ጥሬ ቆርጥሞ በክብር መኖርን እንደማያክል፤ ሌላው ቀርቶ በምዕ ራቡም ሆነ በዐረቡ ዓለም ገንዘብ ፈጽሞ እንደማይታፈስ፣ ይልቅ በሀገራችን ጠንክረን ከሠራን ከሁሉ የምንበልጥ መሆኑን ተገንዝበን ክቡር ማንነታችንን ለአጭበርባሪዎች መሸጥ የለብንም ስንል የእርቅ ሐሳባችንን እናቀርባለን። ይህን የምንለው ያየነው የቀመስነው ነን።

በየመሥሪያ ቤቱ የተሰጠችንን ኃላፊነት በውስልትና ካጉሳቆልናት ለልጅ ልጅ የሚተርፍ የአለመታመን ዕዳ እንዳስተላለፍን ተሰምቶን በታማኝነት መጽናት አለብን። በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በቀበሌ፣ በክፍለ ሀገር እና በመሥሪያ ቤት ከንጹሕ ሕሊና ጋር እንኑር ካሻውም እንሙት ብቻ ከታማኝነት ጋር እንታረቅ።

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ከሥነ ምግባር ጋር መታረቅ

ሥነ ምግባር በትክክለኛ ግብረ ገብ ከተቀረጸ አንደኛ ለግለሰቡ፤ ሁለተኛ ለማኅበረተሰቡ ሁሉ አስተማማኝ ሕይወት የሚሰጥ ነው።

የግብረ ገብነት ትምህርት የሚወረስ እንጂ በአብዛኛው ት/ቤት ገብተው የሚማሩት አይደለም። ከወላጅ እና ከአካባቢ የሚወረስ ጠባይ ነው። ቢሆንም ቅሉ ማሠሮ ውስጥ ከሚቀቀል ጥሬ አንድ እሳት ያልነካት እንደምትወጣ ሁሉ። ከኅብረተሰቡ ሥነ ምግባር ሳይወርሱ የሚያድጉ ሕፃናት መኖራቸውም ደግሞ መዘንጋት የለበትም።

ግብረ ገብነት ለዘመናዊው አስተዳደር መሠረት ነው። ለዴሞክራሲ ቀና መረማመጃ መንገድ እና ብርሃን ነው። እንደውም የዴሞክራሲ መርህ መነሻ ሥነ ምግባር መሆኑ አያጠራጥርም። ምክንያቱም የሁለቱም ጠባይ በእጅጉ የሚቀራረብበት ሁኔታ ስለአለ ዴሞክራሲን ከሥነ ምግባር ጋር ማዛመድ ይቻላል።

አንድ ጥሩ ሥርዓት ያለው ዜጋ የሰዎችን መብት አይደፍርም፤ ይህ ዞሮ ዞሮ የዘመናዊው ዴሞክራሲ መርህ ነው። በሠለጠነ ኅብረተሰብ ዘንድ ስድብ ነውር ነው። የሥነ ምግባርም ዓላማ ይኸው ነው። ሥነ ምግባር ሙስናን ይቃወማል፤ ዴሞክራሲም እንደዚሁ። ዘመናዊውን ሥርዓት ለመማር የሚጓጓ ሁሉ ከሁሉ በፊት መለስ ብሎ ወደ ሥልጣኔ የሚወስዱ ሥነ ምግባሮችን መማር ይኖርበታል። ሥነ ምግባርን የሚያስተምረን ዋነኛው መጽሐፍ የታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ነውና። ከሁሉ በፊት እስቲ ለእኛ የተሰጠን የሥነ ምግባር ሕግ ምን ይመስላል ብለን እንጀምር።

ከሰዎች ጋር በመልካም ወዳጅነት የመኖር ጥበብ ያለበት ሥነ ምግባር በአንደበት ጥፍጥና በውብ ቃላቶች በመልካም ንግግር ይገለጻል። በገጽታው፣ በቋንቋው፣ በአካል እንቅስቃሴው ሁሉ የአንድ ሰው ምግባር ይገመገማል። ከሁሉ በላይ ግን አንደበት የበለጠ መልካም ቢናገር



የሚፈውስ፤ ክፉ ቢናገር የሚያቆስል ስለሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አንደበታችን ከብሔው ከቅመማ ቅመማት ሁሉ የበለጠ ጣፋጭ ቃላት ያወጣ ዘንድ ይመክራል።

«እነሆ ፈረሶች ይታዘዙልን ዘንድ ልጓም በአፋቸው ውስጥ እናገባለን፤ ሥጋቸውንም ሁሉ እንመራለን። እነሆ መርከቦች ደግሞ ይህን ያህል ታላቅ ቢሆኑ በአውሎ ነፋስም ቢነዱ የመሪ ፈቃድ ወደሚወደው ሥፍራ እጅግ ታናሽ በሆነ መቅዘፊያ ይመራሉ። እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል። እነሆ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል። አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶች መካከል አመፀኛ ዓለም ሆኗል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል። በገሃነምም ይቃጠላል። የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል። ደግሞ ተገርቷል፤ ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም። የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፉት ነው። በእርሱ ጌታንና አብን እንባርካለን። በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ።»*

ከላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንደተረዳነው አንደበታችን እንደሚያቃጥል እሳት አስፈሪ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ አስቀምጦታል። ፍጥረታት ሁሉ ሲገሩ መገራት ያልቻለው የሰው ምላስ እንደሆነ ተምረናል። ግን ይህን ዐመፀኛ ዓለም የተባለ አንደበት በሥነ ምግባር ልጓም ወደ ክፋት እንዳያመራ መግራት፣ መለጐም ይቻላል። ከሥነ ምግባር ጋር የታረቀ ሰው በአንደበቱ አይተላለፍም። በቋንቋው አገርን የሚያምስ ዐመፀኛ የሚፈጠረው ሥነ ምግባርን ካላስተማረ ቤተ ሰብና ማኅበረሰብ ነው። ስለዚህ ነው ሰው ከሕፃንነቱ ጀምሮ በሥነ ምግባር መታነጽ አለበት የሚባለው።

ከላይ እንደጠቀስነው የሰው ልጅ በሥነ ምግባር የታነጸ ከሆነ የዴሞክራሲ ጽንሰ ሐሳብ ይገባዋል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ

* ያዕ. 3፥1–12

በሥልጣኔ ያበበ ኅብረተሰብ ለመገንባት የሥነ ምግባር ትምህርት እጅግ ይጠቅማል:: ወደ ዋናው ከሥነ ምግባር ጋር እንታረቅ ወደሚለው ርዕስ ከማምራታችን በፊት ዓላማውንና መነሻውን መረዳት ስለሚገባ እራሱ የቃሉን ትርጉም ማወቅ ይገባል::

ሥነ ምግባር የሰው ልጅ የሕሊና ሥልጣኔ የሚለካበት አብሮ በመኖር ውስጥ በመፈቃቀር፣ በመተሳሰብ ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር ዘይቤ ነው:: ይህ የሕሊና እሴት ያለው ኅብረተሰብ ለመበልጸግ፣ አብሮ ለመኖር እና ለፀጥታው፣ ለሰላሙ ሁሉ ዋስትና ያለው ነው:: ሥነ ምግባር መንፈሳዊ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደውም የመንፈስ ፍሬ ከሚላቸው ዐበይት ጠባዮች ብዙዎቹ የሥነ ምግባር ቅርንጫፎች ናቸው:: እነሱም ፍቅር፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት ራስን መግዛት ናቸው::* እነዚህ ደገኛ የሕሊና ሀብቶች ሰውን ከሕግ ጋር የሚያስታርቁ በሰዎችም መካከል ሰላምን የሚፈጥሩ ናቸው:: ከሥነ ምግባር ጋር መታረቅ ከላይ ከተዘረዘሩት የልቡና ደስታዎች ጋር መጣመር ነው::

ከሥነ ምግባር ውጭ መሆን ደግሞ ከእነዚህ ተቃራኒ በቆሙት ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር እነዚህን የመሳሰሉት ናቸው::* እነዚህን የሚያደርግ ሌላው ቀርቶ ከዚህ ዓለም ሕግ ጋር ይጋጫል:: ስለዚህም በዚህ ዓለም ውስጥ ያለን ሁሉ ከሥነ ምግባር ጋር መታረቅ ይጠበቅብናል::

በመግቢያችን ላይ በጥቂቱ እንዳየነው የዴሞክራሲ መሠረት የሥልጣኔ ድልድይ ሥነ ምግባር ነው ብለናል:: እንዲህ ካልን ዘን ድህነትን ያመጣብንም ሥርዓተ አልበኝነት እንደሆነ፣ ከሥልጣኔ ያስተ ጓጉለንም ከሥነ ምግባር ጋር መጣላት መሆኑን ልናምን ነው::

ግን እንዴት ሥነ ምግባርና ሥልጣኔ ይገናኛሉ? ብለን ስንጠይቅ ሥልጣኔ በአብዛኛው የተመረኮዘው አብሮ መኖርን አብሮ መሥራት

* ገላ. 5፥22–23
* ገላ. 5፥20



ስለሆነ፤ የሚያስተባብረንን የሕሊና ሥልጣኔ ሥነ ምግባራችንን ካጣን ደግሞ ዕድገታችንም ይስተጓጎላል ማለት ነው:: ሰው በሕሊና ፈርጦች በደግነት፣ በፍቅርና መከባበር ካጌጠ ከዕድገት ወደኋላ የሚያስቀረው አንዳችም ምክንያት አይኖርም::

ታማኝነት የሥነ ምግባር ውጤት ነው:: ታማኝነት የሥራ ሁሉ ቁልፍ ነው:: የዴሞክራሲ ዋነኛ ገጽታ ነው:: በዚህ በታማኝነት ውስጥ በፍርድ ታማኝ መሆን፤ ጉቦ ባለመብላት ታማኝ መሆን፤ ታላቅን ወይም ወላጅን በማክበር ታማኝነት ይገለጣል:: የሰውን ንብረት ከመመኘት ጋር ታማኝነት እርቅ የለውም:: ሌብነትና ታማኝነት ተፃራሪ ናቸው:: ውሸት ቀንደኛ የታማኝነት ጠላቱ ነው:: እነዚህ ከዚህ በላይ በታማኝነት ሥር የተ ዘረዘሩት ደግሞ የሥልጣኔ አብሮ የመኖር መሠረቶች ናቸው:: ከሥነ ምግባር ጋር እንታረቅ።

ይህ ሥነ ምግባር የተባለ ቃል ጥልቅ ግንዛቤ ወይም ሐሳብ ያለው ነው:: ብዙ ጊዜ በሀገራችን ኢትዮጵያ የሰው ሰውነቱ የሚለካው በሥነ ምግባሩ ነው::

ከእጁ እንቅስቃሴ እስከ አረማመዱ ቃላቶቹ ሁሉ የሰውን ማንነት ያገልጣሉ:: በሀገራችን የሰው ታላቅነትና ታናሽነት መለኪያ ሚዛን በሕዝባችን ሕሊና ውስጥ አለ:: በዚህ ሚዛን ተሰፍሮ የቀለለ ቢናገር አይሰማ ለመሪነት አይታጭ፤ ሌላው ቀርቶ ለጋብቻ እንኳን እምብዛም አይፈለግ:: የሀገራችን ሰው አንደበትን ከተከለ ቁመና ያስበልጣል:: የሰው ደም ግባቱ ሥነ ምግባሩም ነው:: በጥሩ አንደበት የሚታወቁ ምግባረ ወላንሳዎች በመብራት ነው የሚፈለጉት:: በመንደራቸው ለማስታ ረቅ በሥራቸው ለኃላፊነት እጅግ ይፈለጋሉ::

ሥነ ምግባር የጎደለው ሰው ቢነግሥ እንኳን መንግሥቱ ሰላም የለውም:: ከሚገዛው ሕዝብ ጋር በሰላም ቋንቋ መነጋገር ይሳነዋል:: ሠራር የሆነ አንደበት ያለው ሮብዓም ገና በመጀመሪያ ንግግሩ እስራኤልን የሚከፋፈል ሥነ ምግባር የጎደለው ቋንቋ እንደተጠቀመ ማስታወስ ይገባል::

ሮብአም ገና እንደነገሠ ሕዝቡ ተሰብስበው መጥተው እጅግ ቅ
የሆነ ጥያቄ ጠየቁት «አባትህ ሰሎሞን በእኛ ላይ ከባድ የአገዛዝ ቀንበ
ጭኖ አስጨንቆን ነበር:: አሁን ይህን ከባድ ሸክም ብታቃልልን
ኑሮአችንን ብታሻሽልልን እኛም ለአንተ እንገዛልሃለን» አሉት:: ሮብአም
ከሦስት ቀን በኋላ እንዲመለሱ ቀጠሮ ከሰጣቸው በኋላ የአባቱን አማካ
ምች ሽማግሌዎቹን ከሕዝቡ ላይ የአገዛዝ ቀንበር ያቀል ዘንድ ሰሎሞን
ሲወተውቱ የነበሩትን በቅድሚያ ጠርቶ የሕዝቡን ጥያቄ እንዴት ልመል
ብሎ ይጠይቃቸዋል:: እነዚህ በሥነ ምግባር የሰከኑት ሽማግሌዎች ል
ነው፤ ሕዝቡ የአገዛዙ ቀንበር ጠብቆባቸዋል:: አንተም እሺ የተሻለ እና
ቀና አስተዳደር አደርግላችኋለሁ ብለህ መልስላቸው ይሉታል::

ሮብአምም እንደገና ግን አብሮ አደጐቹን በመሸታ እና በዋልጌነ
የሚታወቁትን ሰብስቦ የሕዝቡን ጥያቄ ያቀርብላቸዋል:: በሥነ ምግባ
የተበላሸ ሕሊና ያላቸው ጓደኞቹ አባቴ በእባብ ከገረፋችሁ እኔ ደግሞ
በጊንጥ እገርፋችኋለሁ ብለህ መልስላቸው ብለው መከሩት፤ ንጉሥ
ሮብአምም ለተጐዳውና ለተጐሳቆለው ሕዝብ ሥነ ምግባር የጐደለው
መልስ ስለመለሰ የእሥራኤል ነገዶች ለሁለት ተከፍለው፣ የናባጥ ልጅ
የሰሎሞን ታማኝ የነበረው ኢዮርብአም እንኳን መንግሥትን እስኪከፍል
አድርሶታል::* ይህ ሁሉ ከሥነ ምግባር ጉድለት የሚመጣ ችግር ነው::

ሌላው ቀርቶ በሥነ ምግባር የተኮተኮተ ሕሊና ያለው ሰው የተ
ጣላውን አገር ያስታርቃል:: ጠማማውን ያቃናል፤ ክፉትን
ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠን ትን መመሪያ እንዲህ ያዘና
«የሚጠሏችሁን ውደዱ፤ የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም በ
አድርጉ፤ ክፉ ለሚያደርጉባችሁና ስለሚያሳድዷችሁ ጸልዩ ይህን ብታደር
በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ»* ይለናል::

አጠቃላይ መልዕክቱ በሥነ ምግባር ያጌጠ ሰው ባይናገር
እንዲሁ የሰውነቱ ንግግር ብቻ ሰላም ሊፈጥር ይችላል:: ሥነ ምግባ

* ነገ. ቀ. 12÷1–20
* ማቴ. 5÷44–48



ያላቸው የመታዘዛቸው ፍሬ ፍቅር፣ አንድነት፣ ሰላም ነው:: ይህንን ፍሬ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይመገበው ዘንድ በትህትና መታዘዝና በቅንነት መታጠር አለብን:: ከሥነ ምግባር ጋር እንታረቅ::

ትዕቢት ከጥሩ ሥነ ምግባር ጋር ፈጽሞ አይስማማም:: እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ይጠላል ይላል መጽሐፍ ቅዱስ:: እንደውም ዲያቢሎስ የወደቀው በትዕቢቱ ነው እብሪተኝነትን የሚያክል ክፉ በሽታ የለም:: ትዕቢት ሌሎች ሁሉ ከበታቻችን እንዳሉ እንድንቆጥር ያደርገናል:: ይህ ከሆነ ደግሞ ተባብሮ ተከባብሮ መሥራት ያቅተናል::

እብሪት መጀመሪያ ወንበርን ያስመኛል፤ ይህ ደግሞ ያዋርዳል:: ክብርን ለማግኘት የሚሻ ትኁት መሆን ይገባዋልና፤ ስለዚህ ከሥነ ምግባር ጋር ስንታረቅ ከእብሪት ጋር ልንጣላ ያስፈልጋል:: ሐሜትን የመሳሰሉ የዕድገት ማነቆዎች ሁሉ በግብረ ገብነት መስተካከል ያለባቸው ባሕርያት ናቸው:: በሹክሹክታ የሚያሙ አንደበቶችን እግዚአብሔር ይዘጋቸዋል:: ጠብን የሚዘሩ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ክፉዎችና ሐሜተኞች ይባላሉ:: እንደውም ጠማማና ሐሜተኛ ትውልድን እንዴት እታገሳለሁ እያለ እግዚአብሔር ሲቆጣ እናየዋለን::

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሁሉ ለማኅበራዊውም ሕይወት እጅግ ጠንቆች ናቸው:: ትዕቢተኛ፣ ሐሜተኛ፣ አሳባቂ፣ ውሸታም፣ ሌባና ጉቦኛ በበዛበት አገር እንዴት ማደግ ይቻላል? ስለዚህ ሰዎቹን ሳይሆን መጥፎዎቹን ሥነ ምግባሮች በግብረ ገብነት መዋጋት ይገባናል::

እኔ ብቻ ልሰማ ወይም እኔ ያልኩት ብቻ ነው ትክክል የሚሉ ጠንካሮች ማኅበራዊውን ሕይወት ይረብሹታል:: ይህ ዓይነቱ አካሄድ ደግሞ አድጐ አምባገነንትን ይወልዳል፤ ይህ ጠባይ ሲበዛ ሽረኝነትን እና ነፍሰ ገዳይነትን፣ ብሎም ሥልጣንን እስከመውደድ የሚያደርስ ክፉ ባሕርይ ነው:: ይህ ሁሉ የሥነ ምግባር ጉድለት የሚያመጣው ጠንቅ ነው::

ሕዝባችን የሚታወቅበት ሰላምታ ሰጥቶ ማለፍና አመስግኖ መቀበል፣ እንዲሁም እጅ መንሳት፤ እነዚህ ሁሉ አስፈላጊ ባሕሎቻችን ስለሆኑ ልንጠብቃቸው ይገባል::

እንደምን አደራችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን
እንደምን አረፈዳችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን
እንደምን አመሻችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን
እንደምን ሰነበታችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን

እነዚህ የሰላም ቋንቋ ልውውጦች ብዙዎቻችንን የሚያቀራርቡ፤ የሚያዛምዱ ውብ አባባሎች ናቸውና መለወጥም ሆነ መጥፋት የለባቸውም:: በተለይ ሥልጣኔ መስለው የሚጉዱ ቸልተኝነት ለአገርም ሆነ ለሕዝብ ጠቃሚ አይደሉም:: የድሮውን ጉጂ ልማድ ማስቀረት አለብን:: እውነት ነው:: ግን ሌላ አዲስ ጉጂ ባሕልም መቀየጥ ደግሞ የባሰ ጉጂ ነው:: ስለዚህ በግልም ሆነ በማኅበር የምናከናውናቸው ነገሮች ሁሉ የማያስጠይቁ ኃላፊነቶች መሆናቸው ሊሠመርበት ይገባል::

በሠለጠነው ዓለም የግል ኃላፊነት ታላቁን ቦታ ይይዛል፡ በዴሞክራሲ የሚተዳደር ሕዝብ ውስጥ እራስን መግዛት፤ የግል ጠባይን ለሌሎች ተስማሚ አድርጉ መገኘት ለዕድገት ከሚጠቅሙ ዐበይት ፋይዳዎች አንዱ ነው::

የሕግ አስከባሪዎችን በየመንደሩ በየአካባቢው ማቆም ፈጽሞ አይቻልም:: ስለዚህ ሁሉም በቅድሚያ የግል ጠባዩን ለአካባቢው በማስገዛት የተረጋጋ ዋስትና ያለው ኅብረተሰብ መገንባት ይጠበቅበታል::

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ስንኖር የግላችንን ሕይወት ብቻ መምራት አንችልም:: ከመላው ማኅበረሰብ ሕግ፣ ባሕልና አስተሳሰብ ጋር መዋሐድ የግድ ነው:: እንዲህ ሲባል ግን ብዙዎች የሚሠሩትን ኃጢአት መጋራት አይደለም:: በመልካሙ ሁሉ መሳተፍ አለብን:: ለአካባቢያችን ሰላም የግል ባሕሪያችን ተስማሚ ነው ወይ? ይህ ካልሆነ የሥነ ምግባር ጉድለት ስለአለብን ልናስተካክል ይገባል:: ብልህ ሰው በአካባቢው ሰላም ፍቅር ይፈጥራል፤ ጤናማ መንደር ይኖረን ዘንድ ጤና ሥነ ምግባር ከሁሉ በፊት ከግላችን መፍለቅ ይኖርበታል:: ለአዛውንቱ ለአካለ ስንኩላን የሚመች፣ ለሕፃናት የሚያስደስት መንደርና ከተማ ለመፍጠር በሥነ ምግባር የተገነባ ኅብረተሰብ ሊኖረን ይገባል:: ከሥነ ምግባር ጋር እንታረቅ::



# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## ነጋዴው ከንግድ ጋር ይታረቅ

ይህ ርዕስ ሲነሳ ብዙ ሁኔታዎችን ስለሚነካካ አጠር አድርገን በጊዜው ከሚታዩ ችግሮች አንጻር የንግዱን አካባቢ ለመቃኘት የእርቅ ሐሳባችንንም ለማቅረብ እንሞክራለን::

ነጋዴው እና ንግዱ ይታረቁ ስንል ለመሆኑ ተጣልተዋል ወይ? የሚል ጥያቄ መከተሉ አይቀርም:: ስለዚህ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ከንግድ ጋር ተጣልተዋል ከሚለው መሳምታዊ ወይም የጅምላ ክስ ለማምለጥ በግፍ እና በአቋራጭ ለመክበር የሚንቀዠቀዡትን ከንግድ ይልቅ ወደ ዝርፊያና ቅሚያ ያዘነበለ ሥራ የሚሠሩትን ለማለት እንጅ ይህ ጽሑፍ ንጹሐኑን እንደማይጠቀልል ለማሳሰብ እንፈልጋለን:: ስለዚህም የንግዱ ኅብረተሰብ በእጅጉ ማረም ያለበት ነው ብለን የምንገምተውን እየጠቃቀስን የሕዝባችንን ብሶት ለተከበሩ ንጹሐን ነጋዴዎች እናቀርባለን::

ከሁሉ በፊት ግን የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ታሪክ እረጅም ዕድሜ ያለውና ለሀገሪቱም ሥልጣኔ ፋና እንደነበረ ሳንጠቅስ አናልፍም:: ይኸውም እንደኛ በንግሥተ ሳባ (የደቡብ ንግሥት፣ ንግሥተ አዜብ ወይም ማክዳ ተብላ የምትጠራዋ ንግሥት) ንጉሥ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም በነገሠበት ዘመን የነበረውን ጥበብ የቤተ መንግሥት አስተዳደር እንዲሁም ሥርዓት ተመልክቶ ተደንቆ ለንግሥቲቱ የነገራት ነጋዴው ታምሪን እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል::* እንዲሁም ከጌታ ልደት በኋላ የነገሠችው ንግሥት ሕንደኬ የገንዘብ ወይም የንግድ ባለሥልጣን የነበረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከኢየሩሳሌም ሲመለስ ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ እንዳስገባ የታወቀ ጉዳይ ነው::

ስለዚህ ንግድና ኢትዮጵያ የጠበቀና የተራቀቀ ግንኙነት እንደነበራቸው ለመረዳት አይከብድም:: ታዲያ ይህንን ያህል የሠለጠነ

* 1ኛ ነገ. 10፥1–10
* የሐዋ. ሥራ 8፡1–፶፰

እንደምን አደራችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን

እንደምን አረፈዳችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን

እንደምን አመሻችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን

እንደምን ሰነበታችሁ ... እግዚአብሔር ይመስገን

እነዚህ የሰላም ቋንቋ ልውውጦች ብዙዎቻችንን የሚያቀራርቡ፣ የሚያዛምዱ ውብ አባባሎች ናቸውና መለወጥም ሆነ መጥፋት የለባቸውም:: በተለይ ሥልጣኔ መስለው የሚጉዱ ቸልተኝነት ለአገርም ሆነ ለሕዝብ ጠቃሚ አይደሉም:: የድሮውን ጉጂ ልማድ ማስቀረት አለብን:: እውነት ነው:: ግን ሌላ አዲስ ጉጂ ባሕልም መቀየጥ ደግሞ የባሰ ጉጂ ነው:: ስለዚህ በግልም ሆነ በማኅበር የምናከናውናቸው ነገሮች ሁሉ የማያስጠይቁ ኃላፊነቶች መሆናቸው ሊሠመርበት ይገባል::

በሠለጠነው ዓለም የግል ኃላፊነት ታላቁን ቦታ ይይዛል፡ በዴሞክራሲ የሚተዳደር ሕዝብ ውስጥ እራስን መግዛት፣ የግል ጠባይን ለሌሎች ተስማሚ አድርጎ መገኘት ለዕድገት ከሚጠቅሙ ዐበይት ፋይዳዎች አንዱ ነው::

የሕግ አስከባሪዎችን በየመንደሩ በየአካባቢው ማቆም ፈጽሞ አይቻልም:: ስለዚህ ሁሉም በቅድሚያ የግል ጠባዩን ለአካባቢው በማስገዛት የተረጋጋ ዋስትና ያለው ኅብረተሰብ መገንባት ይጠበቅበታል::

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ስንኖር የግላችንን ሕይወት ብቻ መምራት አንችልም:: ከመላው ማኅበረሰብ ሕግ፣ ባሕልና አስተሳሰብ ጋር መዋሐድ የግድ ነው:: እንዲህ ሲባል ግን ብዙዎች የሚሠሩትን ኃጢአት መጋራት አይደለም:: በመልካሙ ሁሉ መሳተፍ አለብን:: ለአካባቢያችን ሰላም የግል ባሕሪያችን ተስማሚ ነው ወይ? ይህ ካልሆነ የሥነ ምግባር ጉድለት ስለአለብን ልናስተካክል ይገባል:: ብልህ ሰው በአካባቢው ሰላም ፍቅር ይፈጥራል፤ ጤናማ መንደር ይኖረን ዘንድ ጤና ሥነ ምግባር ከሁሉ በፊት ከግላችን መፍለቅ ይኖርበታል:: ለአዛውንቱ ለአካለ ስንኩላን የሚመች፣ ለሕፃናት የሚያስደስት መንደርና ከተማ ለመፍጠር በሥነ ምግባር የተገነባ ኅብረተሰብ ሊኖረን ይገባል:: ከሥነ ምግባር ጋር እንታረቅ::



# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## ነጋዴው ከንግድ ጋር ይታረቅ

ይህ ርዕስ ሲነሳ ብዙ ሁኔታዎችን ስለሚነካካ አጠር አድርገን በጊዜው ከሚታዩ ችግሮች አንጻር የንግዱን አካባቢ ለመቃኘት የእርቅ ሐሳባችንንም ለማቅረብ እንሞክራለን::

ነጋዴው እና ንግዱ ይታረቁ ስንል ለመሆኑ ተጣልተዋል ወይ? የሚል ጥያቄ መከተሉ አይቀርም:: ስለዚህ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ከንግድ ጋር ተጣልተዋል ከሚለው መላምታዊ ወይም የጅምላ ክስ ለማምለጥ በግፍ እና በአቋራጭ ለመክበር የሚንቀዠቀዡትን ከንግድ ይልቅ ወደ ዝርፊያና ቅሚያ ያዘነበለ ሥራ የሚሠሩትን ለማለት እንጂ ይህ ጽሑፍ ንጹሓኑን እንደማይጠቀልል ለማሳሰብ እንፈልጋለን:: ስለዚህም የንግዱ ኅብረተሰብ በእጅጉ ማረም ያለበት ነው ብለን የምንገምተውን እየጠቃቀስን የሕዝባችንን ብሶት ለተከበሩ ንጹሓን ነጋዴዎች እናቀርባለን::

ከሁሉ በፊት ግን የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ታሪክ እረጅም ዕድሜ ያለውና ለሀገሪቱም ሥልጣኔ ፋና እንደነበረ ሳንጠቅስ አናልፍም:: ይኸውም አንደኛ በንግሥተ ሳባ (የደቡብ ንግሥት፣ ንግሥተ አዜብ ወይም ማክዳ ተብላ የምትጠራዋ ንግሥት) ንጉሥ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም በነገሠበት ዘመን የነበረውን ጥበብ የቤተ መንግሥት አስተዳደር እንዲሁም ሥርዓት ተመልክቶ ተደንቆ ለንግሥቲቱ የነገራት ነጋዴው ታምሪን እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል::* እንዲሁም ከጌታ ልደት በኋላ የነገሠችው ንግሥት ሕንደኬ የገንዘብ ወይም የንግድ ባለሥልጣን የነበረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከኢየሩሳሌም ሲመለስ ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ እንዳስገባ የታወቀ ጉዳይ ነው::

ስለዚህ ንግድና ኢትዮጵያ የጠበቀና የተራቀቀ ግንኙነት እንደነበራቸው ለመረዳት አይከብድም:: ታዲያ ይህንን ያህል የሠለጠነ

* 1ኛ ነገ. 10፥1-10

* የሐዋ. ሥራ 8፡1-፯፡፰

የንግድ ባሕል ያለው የንግዱ ኅብረተሰብ የንግዱ ሥርዓት በሌላቸው ስግብግቦች ስሙ ሲጠፋ ከሕዝብ ጋር ሲጣላና በጥርጣሬ ሲታይ ዝም ብሎ መመልከቱ ይበጃል ወይ?

እንደእውነቱ ከሆነ በዚህ ዘመን ሕዝባችን በተፈጥሮ አደጋው፣ በአስተዳደሩ መከፋቱ ሳያንሰው ያለችውን ጥሪት /ገንዘብ/ ከፍሎ ትነስም ትብዛ ንጹሕ ዕቃ ማግኘት እንዴት ይብዛበት? ቅቤ ለመግዛት ሲሄድ ሙዝ ተቀላቅሎበት ያገኛል:: ማር ልግዛ ቢል ስኳር ተዶሎበት፣ ወተት ልግዛ ቢል ውኃ ተጨምሮበት፣ በርበሬ ልግዛ ቢል ሸክላ፣ አፈር፣ ሠጋቱራው አብሮ ተፈጭቶ ይቀርብለታል:: ለዚህ ነው ነጋዴውና ንግዱ ይታረቁ የሚለውን የብሶት ሐሳብ ያቀረብነው::

የተከበረውና የተወደደው ባንካችን ሳይቀር ሠንሠለት በዘረጉ ማፍያዎች ሲመሰቃቀል በዚህ ጊዜ ያገር ያለህ የመንግሥት ያለህ ብለን መጮኻችን ቢያንስ እንጅ ይበዛ ይሆን?

ይህ ስግብግብነት የሚጀምረው ከተራ የችርቻሮ ንግድ ነጋዴዎች ጀምሮ ነው:: ልብ ብላችሁ ታዝባችሁ እንደሆነ የእያንዳንዱ በቆርቆሮ (በጣሳ) የሚሰፍረው ነጋዴ ቆርቆሮውን ወደ ውስጥ ይቀጠቅጥና ሚዛን (ሥፍር) ሲሠርቅ ታዩታላችሁ:: ይህ ክፉ ባሕል ሲያድግ ነው ወደ ከፍተኛው ደረጃ የደረሰው፤ ልብ የሚሰብር ሐዘን ነው::

አለበለዚያማ ባሌስትራውን ወርቅ ነው ብሎ የሚስማማ አካል በዚህ ዘመን ባልተገኘ ነበር:: ዝርፊያ ዓይነት አለው ግን እንደዚህ አድርጐ የሕዝብን ሃይማኖትና የውስጥ መንፈስ የሚሰባብር ስንፍና ታይቶም ተሰ ምቶም አያውቅ:: ለመሆኑ ይሄ ከምን የሚመደብ ሥራ ነው? ከንግድ? ከዝርፊያ? ከአገር መክዳት? ጥፋቱስ የት ነው? መቆሚያውስ የቱ ጋር ነው? መሸቶ በነጋ ቁጥር ዋጋ ጨምሮ ማደር:: የአገር በርበሬ ሰብስቦ ደብቆ ሕዝብን አሳቅቆ መግደል በዚህ ዘመን የታየ ዘግናኝ ድርጊት ነው:: ስግብግብነት ያየለበት ዘመን::

ይልቅ የንግዱ ኅብረተሰብ የገበያውን ንጉሥ ሕዝቡን አስደስቶ በጥቂቱ አትርፎ እውነተኛ ዕድገት ቢያድግ ነው የሚያዋጣው:: የብዙዎቹ



የዘመናችን ነጋዴዎች ዕድገት አርቴፊሻል ነው:: ከየት መጣ ሳይባል ሚሊዮን ብር የሚቆጥር ነጋዴ እየተፈለፈለባት ያለች ብቸኛ የዓለማችን አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ነች:: ይህ ዓይነት ብልጽግና ዕውን ጤነኛ ነው ወይ ብለን ብንመረምር ከኋላው የብዙ ሰዎች ደም እንደጐርፍ የፈሰሰበት ሆኖ እናገኘዋለን::

የሀብታችን መነሻ የደም ወንዝ (የደም ምንጭ) እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን:: በገንዘብ ስካር ደግ ቅን ባሕርያችን እንዳይለወጥ፣ በገዛ በደላችን እንቅልፍ እንዳናጣ ንግዳችን ቅን ይሁን:: በወርቅ ቁልፍ የምንከፍ ታቸው የኃጢአት የበደል በሮች ሁሉ እኛው ላይ እየተዘጉ የሕሊና እስር ቤቶቻችን ይሆናሉ::

ይህ ኃጢያት የንግዱን ኅብረተሰብ ብቻ ሳይሆን የመንግሥት ተቀ ጣሪዎቹን ሁሉ የሚዳስስ ነው:: አነስተኛ ችርቻሮዎች ሳይቀሩ በመንግሥት ባለሥልጣናት መረብ ሠንሠለት ውስጥ ከገቡ፣ ነጋዴ ፖለቲከኞች ነጋዴ ቢሮክራቶች ከተፈጠሩ ንግዱ እና ተንኮሉ እጅግ ይወሳሰባሉ:: እና ያኔ ለእዚያች አገርና ለእዚያ ሕዝብ ግን ወዮላቸው:: ብዙዎቹ የአውሮፓ፣ የላቲን አሜሪካ እና የኤዥያ አገራት መሪ ዎች (ፖለቲከኞች) የናጠጡ ሀብታሞችም ስለነበሩ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ባርያ አድርገው ቤተ መንግሥቶቻቸው በምርጥ ነፍሰ ገዳዮች ተጥለቅልቀው ነበር:: ፖሊሶች በሌቦች የሚታዘዙ ለሕዝብ ፀጥታም ይሁን ሕልውና ግድ የሌለቸው ሆነው በመገኘታቸው እስከዚህ ዘመን ድረስ የእነዚህ አገራት አደባባዮች በጠራራ ፀሐይ ሰው የሚገደልባቸውና የሚዘረፍባቸው፣ ሐሺሽ (ድራግ) የሚሸጥባቸው የምድር ላይ ሲዖል ሆነው እናያቸዋለን::

እኛስ ወገኖቼ? ሌብነቱ፣ ነፍስ ግድያው፣ የስርቆሹ ሠንሠለት ባንካችን መሀል ሲገባ ለመሆኑ ከዚህ ውጪ ነን ማለት እንችላለን ?

ስለዚህ ለልጅ ልጆቻችን የእንበላው አገር እንዳናቆያቸው ዘንድሮ የተፈለገው መስዋዕትነት ተከፍሎ የንግዱ ሕይወት በተቻለ መጠን ንጹሕ መሆን አለበት ብለን የእርቅ ሐሳባችንን እናቀርባለን:: በመንግሥት

መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ዕቃ ግዢ አካባቢ የሚጭበረበረው አድጐ ዛሬ ሀገሪቱ በውድ ዋጋ ከውጪ የምታስገባቸው ግዢዎች ሳይቀሩ ዝርፊያ የተሞላባቸው መሆናቸው አሳሳቢ ጉዳይ ነው:: በግልጽ በተለያዩ ጋዜጦቻችንና ሚዲያዎቻችን እንደተዘገበው ይህች አገር ወደ ፍጹማዊ ማፊያዎች እጅ እየገባች ይሆን እንዴ ብለን እናድናስብ ያደርገናል::

በአዳዲስ የብር ኖቶች የተለወጡ አሮጌ ብሮች በተወሳሰበ ተንኮል ወደ ግለሰቦች እጅ ተመልሰው ሲገቡ ገበያው ወይም የኢኮኖሚው መዋቅር ላይ የሚፈጥረው መሳከር አገርን ምን ያህል ይጐዳ ይሆን?

## ምዕራፍ አሥራ አራት

## ከተፈጥሮ ጋር መታረቅ

«እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው::»* በአሪት ዘፍጥረት ሰማይና ምድርን ዕፀዋቱንና እንስሳቱን በባሕር የሚገኙትን በሰማይም የሚበሩትን ከዋክብቶችንና ፕላኔቱን ግዙፉንና ረቂቁን ፍጥረት ከፈጠረ በኋላ:: ሰውን ይህንን ሁሉ ፍጥረት ያበጅ ይጠብቅ ዘንድ ብሩሕ ሕሊና አስተዋይ ልቡና ስለሰጠው በረቀቀ ጥበብ ተፈጥሮን ሲገራ ይገኛል::

ስለዚህ ሰው ከተፈጥሮ ጋር የታረቀው ገና ከፍጥረቱ ነው ማለት ይቻላል:: ፈቃደ እግዚአብሔር ስለሆነ ለአምስት ቀናት ይህችን ውብ ዓለም ሲንከባከብ ይከርምና በሁለቱ ቀናት ለዓይን የሚማርከውን ሁሉ እያየ ሲደሰት ይውላል::

የተፈጥሮን ውበት በተመለከተ አበው ሳይጠቅሱ ያለፉበት ጊዜ የለም:: ከሁሉ በላይ ግን በዘፍጥረት «እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ አበቀለ:: ወንዙም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔደን ይወጣ ነበር:: ከዚያም ለአራት ክፍል ይከፈል ነበር::»* እያለ ግሩም ሆኖ የተሠራውን የእግዚአብሔር ኪነ ጥበብ ሲሸላልመው ይገኛል::

* ዘፍ. 2÷15
* ዘፍ. 2÷8



በተለይ በመዝሙረ ዳዊት ላይ ፣
«ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፤
አቤቱ አምላኬ ሆይ አንተ ታላቅ ነህ፤
ክብርንና ግርማን ለበስህ፤
ብርሃንና ግርማን ለበስህ፤
ሰማይን እንደ መጋረጃ ዘረጋህ፤
እልፍኙን በውሃ የሚሠራ፤
ሠረገላውን ደመና የሚያደርግ፤
በነፋስ ክንፍም የሚሄድ፤
መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ፤
አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል፤
ለዘላለም እንዳትናወጥ፤
ምድርን በመሠረትዋ ላይ መሠረትሃት::
በጥልቅ እንደ ልብስ ከደንሃት፤
በተራሮችም ላይ ውኖች ይቆማሉ፤
ከዘለፋህም ይሸሻሉ፤
ከነጐድጓድም ድምጽ ይደነግጣሉ፤
ወደ ተራሮችም ይወጣሉ፤
ወደ ቆላዎችም ወደአዘጋጅህላቸው ሥፍራ ይወርዳሉ::
እንዳያልፋትም ድንበር አደረግህላቸው፤
ምድርን ይከድኑ ዘንድ እንዳይመለሱ፤
ምንጮችን ወደ ቆላዎች ይልካል፤
በተራሮች መካከል ውኖች ይልካል፤
የዱር አራዊትን ሁሉ ያጠጣሉ::
የበረሃ አህያዎችም ጥማቸውን ያረካሉ፤
የሰማይ ወፎችም በእነርሱ ዘንድ ያድራሉ፤
በድንጋይ ስንጥቅ መካከልም ይጮኻሉ::
ተራሮችን በላይ የሚያጠጣቸው፤
ከሥራህ ፍሬ ምድር ትጠግባለች፤

እንጀራን ከምድር ያወጣ ዘንድ፤
ሰምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም፤
ሣርንም ለእንስሳ ያበቅላል፤
ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፤
ዘይትም ፊትን ያበራል፤
እህልም የሰው ጉልበትን ያጠነክራል ...»*

እያለ እግዚአብሔር በዚህ ምድር ለሰው ልጅ ያዘጋጀውን ዕቅድ እና ዝግጅት ረቂቅ ሥራውን በመዝሙሩ ያሰማናል፡፡

ታዲያ ይህ ሁሉ ደስታ የሚፈስበት ተፈጥሮ በሰው ልጆች እውቀት ይጠበቅ ዘንድ አምላካዊ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ለዚህም ነው አትክልቶች ሳይቀሩ የገበሬውን እጅ ሲናፍቁ የሚታዩት፡፡ የሚኮተኩት የሚያርም ሠራተኛ ያስፈለገው ቀድሞ በተላለፈው አምላካዊ ትዕዛዝ የተነሣ ነው፡፡

እንስሳቱ ሳይቀሩ ከሰው ተጠግተው ሰውን አክብረው አንዳንዴም ፈርተው ይኖሩ ዘንድ ቀድሞ የተላለፈ ትዕዛዝ ስላለ በሚያስደንቅ ሁኔታ የሰውና የእንስሳት ትስስር በቋንቋ እስከመግባባት የደረሰ ፍቅር ወይም ጥላቻ መኖሩ ይህንን ሁሉ ያዘጋጀውን እግዚአብሔርን እናከብረው ዘንድ ያደርገናል፡፡

እንስሳት ከሰው ጋር ያላቸው መቀራረብ በሁለት ይከፈላል፡፡ አንደኛው የፍርሀት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ የፍቅር ነው፡፡ ውሾች፣ ድመቶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ላሞችና የጋማ ከብቶች በተለይ ፈረስ ከሰው ጋር መልካም ወዳጅነት የፈጠሩ ሲሆን፤ የዱር አራዊቱ ደግሞ አልገዛም ባይ ይመስላሉ፡፡ ቢሆንም በታላቁ ጥበበኛ ሰው ቁጥጥር ሥር ከመሆን አላመለጡም፡፡ ባሉበት ጫካና ገደል ዛፍ ላይ ሳይቀር የቱሪስት መስህብ ሆነው ተፈጥሯቸው ጭምር በሳይንስ እየተፈተሸ እውሬዎቹ ለማዳ ከሆኑ ሰንበተዋል፡፡

---

መዝ. 103(104)፥1–15



ለዚህ ተአምረኛ ለሆነው የሰው ልጅ የሚሳነው ነገር እንዳይኖር ከአምላኩ ሙሉ ሥልጣንና ችሎታ ስለተሰጠው በተረቱም በምሳሌውም እንስሳቱ ስለሰው ኃይለኛነት ሲጫዋወቱ በዘይቤ ቋንቋ ተደምጠዋል፡፡ ከእነዚህ የእንስሳት ጭውውት አንዱን ከዚህ እንደሚከተለው እናቀርበዋለን፡፡ ጭውውቱ በቤት እንስሳዋ ድመትና በዱር አውሬው አንበሣ መካከል የተደረገ ነው፡፡

እንዲህ ሆነ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ድመቲት በዱር ውስጥ ስትዘዋወር አያ አንበሣን ታገኘዋለች፡፡ ሁለቱም ትኩር ብለው ይተያዩና፤ አያ አንበሣ በመገረም «መልክሽ እና ጠባይሽ እኛን ይመስላል ግን አካልሽ እጅግ ቀጫጫና ትንሽ ነው፡፡ ለመሆኑ እንዲህ ያከሳሽ ምንድን ነው» ብሎ ይጠይቃታል፡፡

ድመቲት ጭራዋን ወደ ላይና ወደታች እያወናጨፈች ሣቅ ብላ «አሄ እኔ ያለሁበትን ስለማታውቅ ነው፡፡ እኔ እጅግ ኃይለኛ ከሚባለው ረቂቅ ፍጡር ሰው ጋር ነው የምኖረው፡፡ ስፈጠር ግን እንደ አንተ ግዙፍ ነበርኩ ግን የሰው ነገር ነው እንዲህ ያከሳኝ» ትለዋለች፡፡

አንበሣው በመገረም «ይሄ ኃይለኛ የምትይው ሰው ምን ዓይነት ነው? ልታሳይኝ ትችያለሽ» ይላታል በኩራት፡፡ ድመት ቀና ብላ አያ አንበሣን ከተመለከተች በኋላ «ኧረ ጌታዬ ከዚህ ጥበበኛ ፍጡር ጋር ባይገናኙ ይሻላል፤ እንደ እኔ ያደርግዎታል፤ ያከሳዎታል» ብላ ለመምከር ትሞክራለች፡፡ አያ አንበሣ ግን በንዴት ከእኔ የበለጠውን ኃይለኛ ፍጥረት ማየት አለብኝ ይላል፡፡

እመት ድመት «ይበሉ ለማየት ከፈለጉ ወደ ሜዳው እንውጣ» ትልና በርቀት ከብቶች የሚያግድ ትንሽ ልጅ ታሳየዋለች፡፡ «ይሄ ነው አስፈሪው እና ጥበበኛ ምናምን ያልሽው ደቃቃ ፍጡር?» ብሎ አያ አንበሣ ከደነፋ በኋላ እየተወረወረ ወደ እረኛው ይሄዳል፡፡

እረኛው ግን ከርቀት አይቶት ስለነበረ አንበሣው ከመድረሱ በፊት ከዛፍ ላይ መውጣት ጀምሯል፡፡ አያ አንበሣ እንደተቆጣ ከዛፉ ሥር ሲደርስ እረኛው ከላይ ከቅርንጫፉ ላይ በተሳካ ሁኔታ ወጥቶ ጠበቀው፡፡

ከድሮ ጀምሮ እረኞች በእጃቸው ገመድ ሲንጠ፣ መርፌ እና የመሳሰሉትን ነገሮች መያዝ ልማዳቸው ነውና:: እረኛው ቀድሞ ያዘጋጀውን ገመድ ሽምቅቆ በመሥራት ከግንዱ ጋር በጥሩ ሁኔታ ካሠረው በኋላ ሌላውን ጫፍ ሽምቀቆ ሠርቶ ወደታች ይለቀዋል:: ያልጠረጠረው አያ አንበሣ በንዴት ዛፉን ሲዞር ሲሽከረከር ያላየው ወጥመድ ውስጥ እንደወደቀ አልገባውም:: ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ ግን እራሱን ከዛፉ ጋር በገዛ ንዴቱ ሲሽከረከር እንዳሠረ ተረዳ:: አንበሣው ከቁጣ ጋር መገረም ያዘው ግን ዕውነትም በኃይል የታሠረበትን ገመድ በጣጥሶ ሌላ ጦስ ከመከተሉ በፊት ወደ ጫካው እግሬ አውጪኝ አለ:: ከዱሩ ውስጥ ሆና ትጠብቀው የነበረችው ድመት አያ አንበሣን «እህ ... እንዴት ነው ሰውን እንዴት አየኸው ትለዋለች::» አያ አንበሣ «አይ የሰውን ነገር ተይኝ ለምን እንደ ከሳሽ ገብቶኛል» አላት ይባላል::

እውነትም ሰው ባለሕሊና በመሆኑ በኃይል የሚመጡትን በብልሀት ሲገራቸው ይታያል:: መርዛማዎቹንና ተናካሾቹን እንስሳት ሳይቀር ጠባያቸውን አጥንቶ በየመልኩ ይጠቀምባቸዋል::

ዕፀዋቱም እንደዚሁ ኃይለኛ መርዛማ እሾኻማ ጠባይ አላቸው:: ብዙዎቹ ደግሞ የዋሆች እራሳቸውን ለመከላከል እንኳን ዝግጅት የሌላቸው ሆነው ተፈጥረዋል:: የእነዚህ ሁሉ ተንከባካቢ ግን ሰው ነው::

የባሕር ዓሦች የባሰውኑ የራሳቸው ብርሃን ያላቸው ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጩ፣ አበባ መስለው የሚያታልሉ እና ዓሦችን ሳይቀር የሚበሉ እጅግ ውብ የባሕር ፍጥረታት በዚሁ በተአምረኛ ሰው ሲፈተሹ ሰንብተዋል::

ዓሦች የተለየ የተፈጥሮ ውበትና ጠባይ የተሰጣቸው ግሩም እና ድንቅ ፍጥረታት ናቸው:: ዓይነታቸው እጅግ ብዙ ከመሆኑም በላይ ባሕርያቸውም የተለያየ ነው:: አንበሬዎች አድብተው ተጠንቅቀው ማደን የሚችሉ እጅግ ብልህ እና ግዙፍ ናቸው:: የዛኑ ያህል ጥቃትኑ ዓሣ እራሱን የሚያድንበት ሌላ ዘዴ ተሰጥቶታል:: ይህንን ሁሉ ተአምር እያየ ይደሰት ዘንድ የተመረጠው፣ ዶልፊኖችንና ለማዳ ዓሦችን ቻስለጥን ዘንድ የተጠራው ከተፈጥሮ ጋር የታረቀው ሰው ነው::



ምን ይሄ ብቻ ግዑዛን ፍጥረታት ሳይቀሩ ለሰው ይታዘዙ ዘንድ ቃል ኪዳን አላቸው:: መሬት በሰው ልትታረስ አንዱን ቅንጣት ስላሣ፣ ስልሳ፣ መቶ አድርጋ ልታበቅል ለእንስሳት ጨሌውን፣ ለአእዋፉ ታላላቅ ዛፎችን፣ ለአራዊቱ ደኑን፣ ለዋልያዎቹ ተራራ እና ቋጥኙን እየለገሰች ፍጥረታት በውስጧ ሊተረማመሱ ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል:: መሬትም ከተፈጥሮ ጋር በታረቀው ሰው ትገራለች::

ነፋሳቱ ደመናውና ነጕድጓዱ ሁሉ ሰውን ያከብራሉ፤ ሌላ የቁጣ ትዕዛዝ ከአምላክ እስከ አልተሰጣቸው ድረስ ነፋስ ቀዝቃዛውን አየር ከውቅያኖስ እየሳበ በፀሐይ ዋእይ ተቃጥሎ የደረቀውን መሬት እርጥበት ይሰጠዋል:: ደመናውን እንደ ሠረገላ ተሸክሞ ምድሪቱን ያረሰርሳታል:: በፀሐይ ሙቀትና በቅዝቃዜው እየተረዳ ዕፅዋቱ ሲለመልሙ ሲያብቡ የዚህን የተፈጥሮ ኡደት እንዳይዛባ አድርጐ ያስተካከለውን እግዚአብሔርን እንድናስታውስ ያደርገናል::

ይህ ሁሉ ሲሆን አንዱ አንዱን እየተመገበ አንዱ በአንዱ እየተጠለለ የሚኖረው ይህ ግዙፍ ሥነ ፍጥረት እግዚአብሔር እስከፈቀደለት ድረስ ሕልውናው ሳይተጓጐል ይኖራል:: በባሕር ያሉ ዓሦች እርስ በእርስ እየተበሉ፣ የምድርም እንስሳት እንዲሁ ካልተጠፋፉ እንዳይኖሩ የተሰጣቸው ትዕዛዝ እጅግ ያስገርማል::

በአንድ ወቅት «ከሁለተኛው ልጄ ጋር አኳርየም ተብሎ ወደሚጠራው ሰው ሰራሽ የጉድጓድ ውስጥ ውቅያኖስ ሄድን:: ይህ አኳርየም የተለያዩ ዓሣዎች የተሞሉበት ሲሆን፤ መሀሉ በመስታወት ተከቦ ለሰው መሄጃ እንዲሆን ተዘጋጅቶለታል:: ስለዚህም በውኃ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ዓሣዎች ወደጐን ቀና ብሎ ማየት ይቻላል:: የሚያስደንቀው ነገር እርስ በእርስ የማይበሉ ዓሣዎች ብቻ ተመርጠው ነው የመጡት:: ስለዚህ ይህ ሰው ሰራሽ ውቅያኖስ የዓሦች ፀብ የማይታይበት ነው:: ጠፍጣፋው አንዳች ብረት ምጣድ የሚያክል ጥቁር ወይም ነጭ ዓሣ አካሉን እንደ ሰፌድ እያወናጨፈ ሲፈተለክ ማየት ያስገርማል:: በተለያየ አንፀባራቂ ሕብር የተዋቡ ጥቃቅን ዓሣዎች፣ አበባ የሚመስሉ ዓሣዎች፣ ጺም ያለው ዓሣ፣ እየተዝለገለገ የሚወናጨፍ ምኑ ቅጡ:: ይህንን ሁሉ ፍጥረት በመስታወት ውስጥ በቅርበት ማየት ይቻላል::

እኔና ልጄ እጅግ በተመሰጠ ስሜት እነዚህን ፍጥረታት ስናይ ቆይተን ወደ ቤታችን ሄድን፡፡ በልጄ ሕሊና ውስጥ ይህ ዓሦች የማይበሏሉበት ሰላማዊ ውቅያኖስ ታላቅ የደስታ ስሜት ፈጥሮበት ኖሮ እቤት ስንደርስ ስዕሉ ሁሉ ዓሣ ብቻ ሆነ፡፡

በሌላ ቀን ደግሞ ይህንን የባሕር ውስጥ ተአምር ለማየት ፊልም ተከራየንና ማየት ጀመርን፡፡ የዚህኛው ሰው ሰራሽ ሳይሆን እውነተኛው ውቅያኖስ ነበር፡፡ ስለዚህም አንዱ ዓሣ ሌላውን ሳይበላ መኖር ስለማይችል እነዛን ቀለም የተደፋባቸውን የሚያማምሩ ዓሦች አንድ አፉ እንደ ዐስፌ የሾለ አንገቱ እንደ ሶሎግ ውሻ የቀጠነ ዓሣ እያደነ ሲሰልቅጣቸው አየን፡፡ ይህ እውነተኛው ዓለም ነው የሚያማምሩት፤ አበባ የሚመስሉት ዓሦች ለካ ለሌሎችም ምግብ ሊሆኑ ነው የተፈጠሩት፡፡

ልጄ አኳሪየም ውስጥ ያየውን ሰላማዊ ሁኔታ በእውነተኛው ውቅያኖስ ማየት ስለአልቻለ እጅግ ተበሳጨ፡፡ ያንን ክፉ እያደነ ዓሦቹን የሚበላቸውን ሹል አፍ ፍጥረት እጅግ ጠላው፡፡ ተሸሎኩሉኮ በመጣ ቁጥር «መጣ መጣ» እያለ ልቡ ተንጠልጥሎ ፊልሙን ጨረስን፡፡ ልጄ እንቅልፍ ሳይወስደው ያደረ መሰለኝ፡፡ በጠዋት ተነስቶ አንድ አስገራሚ ስዕል ሳለ፤ የውሃ ውስጥ ስዕል፡፡ በውቅያኖስ ውስጥ ያሉትን ዓሦች ሁሉ እስከነባሕሩ ሳላቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ፡፡ ምንም ፍጥረት ሳይቀረው ለማስቀመጥ ሞከረ፡፡

ግን ያንን ክፉ ዓሦቹን እና ዕንቁላላቸውን የሚበላውን ሹል አፍ ዓሣ አልሳለውም፡፡ እኔም በመደነቅ «ለምን ያንን ዓሣ ተውከው» አልኩት፡፡ ልጀም ረጋ ብሎ «እሱን ዓሣ ጠልቸዋለሁ፤ የእኔ ውቅያኖስ ሰላማዊ ስለሆነ የማይበላሉ ዓሦችን ብቻ ነው የሳልኩት» አለኝ፡፡ ደነቀኝ፤ ከተፈጥሮ ጋር መታረቅ የጀመረው ልጄ እውነትም ሕሊናውን የሚያስደስተውን ውቅያኖስ መሥራት ጀምሯል፡፡

ኦ... ሰው ሰው ለካ ታላቅ ፍጥረት ነው ከተፈጥሮ ጋር ሊታረቅ የተፈጠረ፡፡ ልብ በሉ ይህ ሕፃን ገና በሕፃንነቱ ውቅያኖሱን መግራት የሚፈልግ ቅን ልብ አለው፡፡



**ከተፈጥሮ ጋር መታረቅ ማለት እንስሳቱን፣ አራዊቱን፣ ሰማይና ምድሩን፣ ነፋሳቱንና ዋእዩን ጥቅም ላይ ማዋል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ ስለሆነ፡፡ በሳይንስ ተራቆ፣ በዕደ ጥበብ፣ በሥነ ጥበብ በምርምር ተፈጥሮን መጠቀም ኃጢአት አይደለም፡፡ እንደውም ሰንፍናን የሚጸየፍ እግዚአብሔር ከተፈጥሮ ጋር ያልታረቀንም ይጸየፋል፡፡ ከየትኛው ተፈጥሮ ጋር፣ ከነፋሱ ጋር፣ ከምንጉዱ ጋር፣ ከውኃ፣ ከፀሐይ ጋር እንታረቅ፡፡**

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

## ከውኃ ጋር መታረቅ

**ቀላይ ቀላያትን ሲጠራ በተራራዎች ላይ የገደል ማሚቱው፣ የፏፏቴውን ድምጽ ሲያስተጋባ ወይም በተጠቀጠቀው ደን ውስጥ የሚስረገረገው የውኃ ድምጽ ቋ. ቋ. ጨልቅሉቅ ሲል፡፡ ወይም ተራራውን ገምሶ ቀስተ ደመና እየሠራ በታላቅ ኃይል ከታች ወርዶ እንዘፍ ሲል፡፡ ድንጋይና ድንጋይ እያማታ ከታች የሚከላው የውሃ ጭስ ምድር ሰማዩን ሲያለብሰው እንደውርጭ ሲጋረፍ ላየው አሁን ውኃን በውበት ማን ነው የሚቀድመው ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል፡፡**

**እንደ ፊጋ በሬ እንዚኝ ልቀቁኝ የሚለው ፏፏቴ በውስጡ ያለው ኃይል ቢለፈር ምን ያክል ይሆን? ተራሮችን የሚገማምሰው፣ ሰማዩን በነጐድጓድ የሚያርሰው ውኃን የሚያክል ጉልበተኛ አሁን የት ተፈልጐ ይገኛል?**

**ይገርማል ደካማ የሚመስል፣ ግን ኃያል ቀለም የሌለው፣ ውብ ጣዕም ያለው፣ ጣፋጭ መዓዛው ይህ ነው የማይባል የውሃ አፈጣጠር ከቶ ምን ዓይነት ይሆን?**

እስቲ በኔ ሞት በታጠበ ጠርሙስ ውስጥ ኩልል ያለ ውኃ ጨምሩና ትክ ብላችሁ እዩት፡፡ ደግሞ በብርጭቆ ውስጥ አንቆርቁሩት ድምጹን ስሙት ትንሽ ትንሽ እያደረጋችሁ ተጎንጩት መልሳችሁ ደግሞ

እዩት እስክትረኩ ስርግብ ስርግብ ስርግብግብ አድርጋችሁ ጠጡት:: እርካታችሁን ይህን ጊዜ ለኩት፤ የሚፈጥረውን የልብ ደስታ መዝኑት::

ለማነጻጸር ከፈለጋችሁ ቆየት ብላችሁ ኮካኮላም ይሁን ሌላ መጠጥ ጠጡ:: የውኃን ያህል እርካታ ጣፋጭነትና ደስታ የሚፈጥር ተፈልጐ የሚገኝ አይመስለኝም::

ስለዚህ ውኃ ለሰው ልጅ ከተሰጡ ሲሳዮች ዋነኛው ነው:: የቧንቧውን ውኃ ካለ ልክ ከፍቼ ፊቴን ስታጠብ በልጅነቴ አባቴ ይቆጣ እንደነበር ትዝ ይለኛል:: በመስፈሪያ ተቆጥቦ የተሰጠውን ውኃ በተቻለ ቁጠባ ሊጠቀም ይጥር የነበረው አባቴ ከልክ በላይ የሚጠነቀቅ ይመስለኝ ነበር::

ካደግሁ በኋላ የውኃን ጥቅም ስረዳ ግን የአባቴ ጥንቃቄ ገባኝ:: ለዛፎች እና ለሣሮች ሳይቀር ለቀን ይህንን ያህል ይበቃችኋል እየተባለ ተሰፍሮ ሲሰጣቸው ሳይ ያኔ ያባከንኩት ውኃ ዋጋ ገባኝ::

በበረሃማ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች ለውኃ ያላቸውን አክብሮት ካላየን በቀር የጠብታዋ ውኃ ግምት ላይገለጥልን ይችላል::

ውኃ ዙረቱን ጠብቆ ለዘለዓለም ምድርን ሲያረሰርስ የሚኖር ምሥጢራዊ የአምላክ ስጦታ ነው:: ከውቅያኖስ ወይም ከምንጭ ወይም ከወንዝ ከሐይቆች ከመሬት እርጥበት እየተነሳ የሚተነው የውኃ ጭስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እግዚአብሔር ባዘጋጀው ቀዝቃዛ አየር ላይ ተጭኖ ወደ ብናኝ ደመናነት ይለወጣል:: ይህ እርጥበት ያለው አየር ሲጠራቀም አየሩ ለመሸከም ያቅተውና ወደ መሬት ይለቀዋል:: አየር አየርን ተሸክሞ በሰፊው የሰማይ ምንጣፍ ላይ ጥቀርሻ እስኪመስል ይቆይና በነጐድጓድ ድምጽ እየታጀበ ዶፍ ይዘንባል፤ ቅዝቃዜው ከበረታም አንዳች የሚያክል በረዶ ይጥላል::

ያ... የዘነበ ውኃ ደግሞ በፀሐይ ንዳድ ወደ አየርነት ተለውጦ ያርጋል፤ እንዲሁ ቀለበቱን ሳይለቅ በዙረቱ ይዞራል:: ይህ ዙረት የሕይወት ሁሉ መሠረት ነው:: ስለውኃ ጠለቅ ያለ ጥናት ያጠኑ ምሁራን በዚህ



ያምናሉ:: እግዚአብሔር አለ «ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾችን ታስገኝ»* ውኃንና ሕይወትን እንዲህ መጽሐፍ ቅዱስ አገናኝቷቸው ስናገኝ የውኃ ምሥጢር ረቂቅነት ተቀድቶ እንደማያልቅ እንረዳለን:: ለነገሩ ዝግመተ ለውጥ ትክክል ነው የሚሉት ፈላስፎችም ጭምር የሕይወት ምንጭ መጀመሪያ ውኃ ነው ይሉ የለ? ግን ሐልወተ እግዚአብሔርን ለመሸሽ ተጠቀሙበት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን ነው የደገሙት::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥነ ፍጥረት ሲናገር ውኃን ሳይጠቅስ አላለፈም:: በውኆች መካከል ጠፈርን ሲያበጅ፣ በውኃና በውኃ መካከል ሲከፍልና የብስን ሲያዘጋጅ ሁሉ ውኃ በሥነ ፍጥረት መከወን ዋነኛ ተዋ ናይ ሆኖ ነበር:: በኖህ ዘመን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የጥፋት ውኃ በመጣ ጊዜ ከሰው ጀምሮ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ሁሉ ሲደመሰሱ ውኃ ዋነኛ አገልጋይ ወይም አጥፊ ነበር:: ለኖህ ቃልኪዳን የገባለት እግዚአብሔር በቀስተ ደመና አምሳል ምልክት ሲሰጠው በውኃ እና በፀሐይ ኅብር እግዚአብሔር ባበጀው ቀስት ነበር::

ይስሐቅም ርብቃን ያገኛት ከውኃ ጉድጓድ ሥር ነው:: ያዕቆብም እንደዚሁ፤ ሙሴ በበረሃ የሕዝቡን ጥም ያረካው ዐለቱን በበትር እየመታ ውኃ አፍልቆ ነው:: ሣምራዊቷ ሴት ከዚህ በኋላ ዳግመኛ እንዳልጠማ እርካታ የሚሰጥ ውኃ ስጠኝ ብላ ነው ጌታን የጠየቀችው:: ስለዚህ ውኃ እና ሕይወት እጅግ የተቆራኙ ናቸው:: በሳይንስ የተራቀቀውም ዓለም የተፈጥሮን (complex ecosystem) ሚዛን ጠብቆ የያዘው ውኃ ነው ካለ ሰንበቷል::

የውሃን የተፈጥሮ ሚዛን ባወደምን ቁጥር የዚህችን ምድር የዑደት አቅጣጫም እንለውጠዋለን:: ስለዚህ የበለጸጉት አገራት ብልጽግናቸው እውን እንዲሆን ያደረጉት ከዘመናት በፊት ቶሎ ብለው ከውኃ ጋር በመታረቃቸው ነው::

ሕይወትን ለማቆየት ውኃ ወሳኝ ነው:: ለቤት ንጽህና፣

* ዘፍ. 1፡20

አትክልቶችን ለማሳደግ፣ ለመጠጥ፣ ለምግብ፣ ልብስን ለማጠብ፣ ለንጽሕና ... ወዘተ ውኃ ያስፈልገናል:: ከዚህ በተጨማሪ በውኃ ላይ ሥራቸውን የመሠረቱ እንደዓሣ አጥማጅ፣ መርከበኛ እና የመሳሰሉት መላ ትኩረታቸውን ውኃ ላይ አድርገው ይኖራሉ::

ብዙ የመዝናኛ ቦታዎች ከሐይቆች ዳርቻ ከባሕር ውስጥ ይሠራሉ:: በተለይ በዚህ ዘመን ነፋሻ አየር ለመቀበል ብዙ ሰው ወደ ሐይቆች ዳር ይሄዳል:: አኳሪየምን የመሳሰሉ የዓሣ መኖብኛና የባሕሩን ትርኢት መመልከቻ ቦታዎች ምን ያህል ሰው ወደ ውኃ እንደተጠጋ ከሚያሳዩ ሁኔታዎች ዋነኛው ነው::

በሞተር ጀልባ እየተሳቡና እየተወነጨፉ ወይም ከማዕበሉ አካሄድ ጋር እራሳቸውን አጣጥመው በማዕበሉ የሚጫወቱ ወጣቶችን ላየ እውን ውኃን የሚመስል መዝናኛ ከየት ይገኛል ይል ዘንድ ያስገድደዋል:: የባሕር ተመራማሪዎቹ ከባሕር ሥር ገብተው ያዩትን ለማሳየት በሚሊዮን የሚቆጠር የውኃ ውስጥ ፊልሞች አዘጋጅተዋል:: ተዋናዮቹ ደግሞ ዓሦች ናቸው::

በፊልሙ ኢንዱስትሪ ቢያንስ 15 በመቶውን የባሕር ውስጥ እና የመርከብ ላይ ፊልሞች ሸፍነዋል:: የቅርቡን ታይታኒክ ማስታወስ ይገባል:: ስለዚህ የሰው ልጅ ከውኃ ጋር ከመታረቅም በላይ ተዛምዶ እናየዋለን::

ከዚህም በላይ ገና በምርምር ያልተደረሰበት የውቅያኖስ ጥልቀት እስከነ ተፈጥሮ ክምችቱ ተዝቆ እስከማያልቀው ሀብቱ ተፈትሾ አልተ ፈጸመም:: የሰው ልጅ ከውኃ ጋር ለመታረቅ እየተፍጨረጨረ ይገኛል::

ከሁሉ በላይ የምግብን ዋስትና በአስተማማኝ ሁኔታ ለማቆየት ትልቅ ጥቅም ይሰጣል:: በተለይ ንጹሕ ውኃ ለጤንነት መሠረት ነው:: ብዙዎቹ በሽታዎች ውኃ ወለድ በመሆናቸው ንጹሕ ውኃ ከጤንነት ጋር ያለው ቁርኝት የጠበቀ መሆኑን ሁሉም ይረዳዋል:: ከውኃ ጋር መታረቅ ስንልም ዐበይት የሆኑ ቁም ነገሮችን በማንሳት ነው::



ከውኃ ጋር መታረቅ ለምን ይጠቅማል፤

ሀ. የምግብን ምርት ከፍ ለማድረግ፣

ለ. ወደውጪ አገር የሚላኩ ሰብሎችንና ፍራፍሬዎችን በብዛትና በጥራት በማምረት የውጪ ምንዛሪን ለማሳደግ፣

ሐ. ከድርቅ ጋር ለመዋጋት እና እያሰለሰ የሚመጣውን የድርቅ ጊዜ አደጋን ለመቆጣጠር፣

መ. የሀገራችንን የኃይል መጠን ከፍ ለማድረግ፣

ሠ. የንጹሕ ውኃ አቅርቦትን በበቂ ሁኔታ ለማሠራጨትና ተጠቃ ሚውን ለማርካት ነው ከውኃ ጋር የምንታረቀው፣

## ኢትዮጵያ እና ውሃ

ወደ ዋናው ርዕሳችን «ከውኃ ጋር መታረቅ» ወደሚለው ስንገባ በዓለም ባንክ የተዘጋጀ ጥናት «ኢትዮጵያ የውኃ ሀብቷን በብልሃትና በጥናት ከጥቅም ላይ አላዋለችውም» የሚል ጽሑፍ እናነባለን:: ይህ ማለት እኛ ከውኃ ጋር አልታረቅንም ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል::

እውነት ነው በባሕላችን መገሳን ብቻ ሳይሆን የጉደለንንም ለመቀበል እራሳችንን ለመውቀስ መዘጋጀት ይኖርብናል:: ዛሬ ሁሉንም ሳንደብቅ በግልጽ ልንነጋገርበት፣ እርምትም ልንወስድበት የሚገባ ብዙ ነገር እንዳለ ልንረዳ ይገባናል:: የውኃ ልማት እንቅስቃሴያችን እጅግ ኋላ ቀር ነው ብለን መነሳት አለብን::

ብዙ ጊዜ በልማት ላይ የሚደረጉ ወቀሳዎች መንግሥትን ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆኑ መላውን ሕዝብም የሚያጠቃልሉ ናቸው:: እርግጥ ነው መንግሥት የፖሊሲ አውጪ በመሆኑ ለሥራዎች ዕቅዶችንና አመቺ ሁኔታዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት ይኖርበታል:: ግን መላው ሕዝብ በዚህ መስክ ካልተንቀሳቀሰና የእኔም ኃላፊነት ነው ካላለ ከግቡ ለመድረስ ያዳግታል::

ከሁሉ በፊት በቅን ሕሊና (policy-makers) ሊያደርጉ የሚገባቸውን አንዳንድ ጥናቶች እንዲህ ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የዝናብ መጠን የነበራት አገር እንደነበረች ይጠቁሙናል። በከፍተኛ ሁኔታ የደን መመናመን ዓለም አቀፍ የአየር መዛባት ወይም መበከል፣ በዓለም አቀፍ ሙቀት መጨመር ምክንያት የውኃ ጥበቃ ጥንቃቄ ጉድለት፣ በቅድመ ጥንቃቄ እጥረትና በመሳሰሉት ምክንያት፣ ኢትዮጵያን የመሳሰሉ አገራት የዝናብ እጥረት አደጋ በተደጋጋሚ ስለአጠቃቸው አማራጭ የውኃ ዘዴዎችን መጠቀም የግድ ይኖርባቸዋል።

መንግሥትን በዚህ መስክ የሚያስተቸው ዋነኛ ነገር በ1960ዎቹ፣ በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ ዓመታትቢያንስ በ7 ዓመት ርቀት ከዛም ባነሰ እየተከታተለ የመጣው የዝናብ እጥረት በተከሰተ ጊዜ የምግብ ደህንነት ማስጠንቀቂያ ደወል ተደጋግሞ መሰማቱን በማስተዋል ጥንቃቄ ማድረግ ይገባው እንደነበረ ነው።

በዚህ ጊዜ የዝናብ ውኃ እምብዛም በሌለባቸው ግብጽ፣ ሊቢያና ሱዳንን በመሳሰሉ አገሮች ምን መፍትሔ ተፈጠረ ብሎ በማሰብና በዝናቡ ውኃ ሳይተማመኑ አማራጭ የውኃ ማግኛ መንገዶች ላይ ማተኮር በተገባ ነበር። በዚህ መስክም በኃላፊነት ላይ የነበሩ ሁሉ መፍጠን ነበረባቸው።

የድርቅ ጊዜን ጠብቆ የእርዳታ መግለጫ ማውጣት፣ በሚገኘውም የምዕራባውያን ፍርፋሪ ማዝገምና ለምዝበራ መዳረግ አደጋው በአስደንጋጭ ሁኔታ ባንዣበበት አገር አሰቃቂ ሁኔታን የሚያስከትል ነው።

ይህንን ችግር ለመፍታት አሁንም መንግሥት ብቻ ሊወጣው ይችላል ማለት የዋህነት ነው። ግን ብልህ አስተዳደሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዴት እንዲህ ዓይነቱን ችግር ፈቱት? እንዴት ከውሃ ጋር ታረቁ ብለን መመራመር ይኖርብናል።

ችግሩን ለመፍታት ሁለት ዐበይት አጠቃላይ መፍትሔዎች እንዳሉ ብዙ ጥናቶች ይስማሙበታል። እነዚህም ፡



አንደኛው በውኃው ልማት የግል ባለሀብቶች እንዲሳተፉበት መንገድ መክፈት፣ በዚህ ሐሳብ ኢትዮጵያ ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ ልማቱ በመንግሥት ተቆልፎ የተያዘ በመሆኑ ዕድገታችንን አቀጭጮታል የሚል መደምደሚያ ላይ የሚደርሱ አሉ። ሌላው እና አንገብጋቢው ነጥብ በዚህ ጉዳይ ላይ ሕዝባዊ ውይይቶችና ተሳትፎዎች በጥልቀት ስለማይካሄዱ ሕዝባችን የውኃ አጠቃቀም፣ ቁጠባ እና የውኃ ማመንጫ ዘዴ ዕውቀቱ ተገድቦ ቆይቷል።

ይህም ዛፎችን ሲቆርጥ፣ የውኃ እጥረት እንደሚከተል አለመገንዘቡ፣ በየመንደሩ ያሉ ምንጮችንና ዥማዎችን በአግባቡ መጠቀም አለመቻሉ። ታላላቅ ጅረቶች በመንደሩ መካከል እያለፉ ጠልፎ እንኳን የጓሮ አትክልት ለመትከል መነሳሳት ያልቻለው በውሃ መስክ ያለው ንቃቱ በመገደቡ ይመስላል። ስለዚህ ሕዝባችን ከውኃ ጋር ይታረቅ ዘንድ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ያስፈልጋል። ከዚህ በፊት ተደጋግመው የተዘመቱት ዘመቻዎች ዓይነት ሳይሆን፣ ከሁሉ በፊት ሕዝባችን ከዓላማው ጋር ጥልቅ ውህደት ያደርግ ዘንድ የሥራውንና የዘዴውን ፍቅር ሥነ ልቡናዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያግዘው መሆኑን ገልጾ መንገር ነው።

በፖሊስ ተገዶ የሚሠራ ገበሬ ከሁሉ በፊት ከሥራው ጋር ስለተጣላ ምርታማ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። ከሁሉ በፊት ከሥራው ጋር ይታረቅ ዘንድ በስክነ መንፈስ ማግባባት ያስፈልጋል። እንዲህ ሲባል በአገራችን መንግሥታት የተከናወኑትን ለማቃለል አይደለም። የተከናወኑትን መልካም ሥራዎች ዋጋ እንሰጣቸዋለን። ግን በሥራ መሀል ጉድለቶችን መጠቆም ስለሚገባ ከውኃ ጋር እንታረቅ እንላለን።

በብዙ በድርቅ በተጠቁ አገሮች እንቅስቃሴ እንደምንረዳው የሕዝቡ ብዛት በአንጻራዊ መልኩ ከፍተኛ ስለሚሆን ዝናብን ጠብቆ በማረስ ብቻ የሕዝቡን ፍጆታ መመከት አይቻልም። ስለዚህ ዘመናዊ የውኃ ልማት አስፈላጊ ነው። በሀገራችን ኢትዮጵያ ዘመናዊ የውኃ ዕድገት የጀመረው ከ1940ዎቹ እኤአ ሲሆን፣ ይህም በሰፋፊ የውሃ ልማት መርሐ ግብር ሁለት ዐበይት ግቦችን ለመምታት የተጀመረ ነው።

የውኃው ልማት በአንድ በኩል የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለመጠገን፤ የንጹሕ ውኃ አቅርቦት በመላው አገሪቱ ማስፋፋት ላይ ያተኮ ረ ሲሆን፤ የመጀመሪያው የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ቅድመ ሶሻሊዝም ለኢንቬስተሮች እጅግ የሚስብና ተስፋ ያለው ሆኖ ተጀምሮ ነበር።

ሁለተኛው ርዕስ ግን እስከ ንጉሡ የመጨረሻ ዘመን ከፍተኛ ዕድ ገት አላሳየም ይላል የዓለም ባንክ ጥናት። ዘመናዊ የውኃ ልማት ለኢትዮጵያ በአንጻራዊነት አዲስ ነበር። የንጉሡ አስተዳደር በአበረታች ሁኔታ በ1940 አጋማሽ ታላላቅ መጠን ያላቸው የውኃ ማስፋፊያ መርሐ ግብር ለታላላቅ እርሻዎችና ለኃይል ማመንጫ ይሆን ዘንድ ገንብቷል። ይህም የእርሻ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት በዕቅድ ተይዞ የነበረውን ከግብ ለማድረስ የተደረገ ነው።

ይህንኑ አሠራር በተደጋጋሚ በስምጥ ሸለቆዎች እና በዋቢ ሸበሌ በማከታተል መንግሥት በነበረው መጠነ ሰፊ የውኃ ልማት ከፍተኛ የኃይል ማመንጫ ለከተሞች ለማዳረስ ጥረት አድርጓል።

በዚህ የንጉሡ ነገሥቱ የልማት ጉዞ ባለሀብቶች በአመዛኙ መሳተፍ የጀመሩበት ጊዜ በመሆኑ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ለማደግ እያኮበኮበ ነበር ለማለት ይቻላል። በዚህ ውስጥ ሊታሰብ የሚገባው የግል ባለሀብቶችን ሊያሠራ የሚችል ነጻ ፖሊሲ ስለነበር ሁሉም ካለመሸማቀቅ ሀብቱን ሊያፈስ ተዘጋጅቷ ል። ስለዚህ ታላቅ ዋስትናን የሚጠይቁ የውኃ ልማቶችን ግለሰቦች ሊሳተ ፉበት የሚችሉት አስተማማኝ ሁኔታ ሲኖር መሆኑን መረዳት ይገባል። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ አዳዲሶቹ የአፍሪካ መንግሥታት የተደራጁ እርሻ ዎችን፣ ኢንዱስትሪዎችንና የልማት አውታሮችን ሁሉ በመውረሳቸው የውጭም ሆነ የውስጥ ባለሀብቶች በአፍሪካ ኢንቨስትመንት ደስተኞች አልነበሩም።

ለምሳሌ የግብጹ ናስር፣ ኑክሩማህ እና ኔሬሬ የሚገዟቸው አገራት የግል ሀብትና ንብረት መውረስን የሶሻሊዝም መግቢያ በር አድርገውት ስለነ በረ እና የኮሚኒስቱም ሥርዓተ ማኅበር የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ስለማያበ ረታታ ከጥቂት የአፍሪካ አገሮች በስተቀር ለኢንቨስትመንት አመቺ አገር አልተገኘም ነበር።



ኢትዮጵያ በዛን ዘመን ለኢንቨስተሮች አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ፖሊሲ ስለምትከተል ለውስጥም ሆነ ለውጪ ነጋዴዎች እንቅፋት የሚሆን ጉዳይ አልነበረም። እስከዚህ ዘመን ድረስ በውል ያልታወቀውን የኢትዮጵያን የውኃ ኃይል መጠን ከሥራ ላይ ለማዋል በእውነቱ ብሩህ ተ ስፋ በሁሉም አቅጣጫ ፈንጥቆ ነበር። ኢትዮጵያ ከውኃ ጋር ለመታረቅ ዳዴ ማለቷ የግድ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የሆነ ሆኖ ዝናብን ተክቶ ሊያገለግል የሚችለው ዘዴ ምንድነው? ቢባል ጥርጥር የለውም መስኖ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፤ ቀደም ብሎ የአገሪቱ ልማዳዊ የመስኖ አጠቃቀም በመጠኑ ስለነበረ ይህንን ጭላንጭል ማስፋት ተቀዳሚ ተግባር ሆኖ አንደኛ (surface water) ሐይቆችንና ኩሬዎችን በስፋት በመጠቀም፣ ወራጅ ውኃዎችን ከወንዝና ከምንጭ አስተማማኝ በሆኑ ቦታዎች እያጠራቀመው የጉድጓድ ውኃን መጠቀምን በማዳበር ማዕከል ያደረገ ልማት ሊካሄድ ይገባዋል ይላል የብዙ ጥናቶች ውጤት።

ባሕላዊ የመስኖ አጠቃቀም በሰሜን ሸዋ፣ በደቡብ ወሎ፣ በምሥራቅ ጉጃም፣ በሐረርጌ ከፍተኛ ቦታዎች በገበሬው በራሱ ፍላጐት ይካሄድ ስለነበረ ይህን ብርሃን የበለጠ እንዲሰፋ ከማድረግ ይልቅ በውርስና በኮሚኒዝም መንፈስ እንዲጨልም ሆኗል። ምንም መጠነ ሰፊ የልማት ትልሞች ቢበረታቱም አነስተኛ እና መካከለኛ መጠን ያላቸው የመስኖ ልማቶችም ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባ ነበር። እስከዚህ ዘመን ድረስ በእርግጠኝነት የውኃ ሀብታችን አይታወቅም ብለናል። በተቀራረበ ግምት ግን የተለያዩ አካላት የተለያየ ቁጥር ያስቀምጣሉ።

ከነዚህ የተለያዩ ግምቶች በመስኖ ሊለማ ይችላል ተብሎ የሚገመተው የአገሪቱ ክፍል የዓለም ባንክ ቀደም ብሎ በ1966 ዓ.ም. ባስጠናው መሠረት ኢትዮጵያ 1.0 እስከ 1.5 ሚሊዮን ሔክታር በመስኖ ልታለማ ትችላለች ይላል። የግብርና ሚኒስቴር በሰጠው መረጃ መሠረት በ1979 ዓ.ም. 2.3 ሚሊዮን ሔክታር ያደርሰዋል። International Fund for agricultural development (IFAD) በ1980 ዓ.ም. ወደ 2.8 ሚሊዮን ሔክታር ሲገምት (Office of national committee for central plan-

ning) በ1983 ዓ.ም. ባወጣው መረጃ WRDA የሰጠውን መረጃ ተመርኩዞ 2.7 ሚሊዮን ሔክታር ነው ይላል:: የባሰውኑ (The Indian engineering firm water and power consulting service) ወደ 3.5 ሚሊዮን ሔክታር ያደርሰዋል፤ ተቀባይነትም ያገኘው ከፍተኛው ግምት ይኸው 3.5 ሚሊዮን ሔክታር ነው::

ይህን ያህል መሬት በመስኖ እየለማ ዓመቱን መሉ ቢታረስ ለመሆኑ ረሃብ ሀገራችንን ይነካት ይሆን? ከውኃ ጋር እንታረቅ ሲባልም ሌላ ትርጉም የለውም ይኸው ነው:: በተለይ ዓባይ በዓለማችን ትልቅ ከሚባለው ከሚሲሲፒ ወንዝ ቀጥሎ በርዝመቱ እና በግዙፍነቱ በሁለተኛ ደረጃ ሲታወቅ ርዝመቱም 67,000 ኪ.ሜ. ነው:: ይህም ናይል የተባለውን በጠቅላላ ይመለከታል::

የናይል ወንዝ በአስዋን ግድብ ላይ ሲለካ ዓመታዊ ፍሰቱ 84 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ነው:: የሚያስደንቀው ከዚህ ውስጥ 72 ቢሊዮን ሚ.ኩ. ወይም 86% የሚሆነውና ከኢትዮጵያ የሚፈሰው አፈር የተሸከመው ውኃ ነው::ይኸውም ጥቁር ዓባይ 58%፣ ባሮ አኮቦ 14%፣ተከዜ አትበራ 14% አዋጥተው የሱዳንና የግብጽ ሲሳይን እያዳበሩ ይገኛሉ:: እኛ ግን ከ3.5 ሚሊዮን ሄክታር በመስኖ ሊለማ ከሚችል መሬታችን ውስጥ ያለማነው ገና ጥቂት የጥቂት ጥቂት ነው::

ይህ በእንዲህ እያለ የከርሰ ምድር ውኃ መጠን በእርግጠኝነት አይታወቅም:: ግን በእጅጉ ሕዝባችንን ሊጠቅም ሊረዳ የሚችል በመሆኑ ሊተኮርበት ይገባል::

ፈረንሣይ ለምን አትራብም? ሌላ ምሥጢር የለውም የውኃ ሀብትዋን በተሳካ ሁኔታ ስለተጠቀመችበት ነው:: እነኖርዌይ እጅግ አስገራሚ የሆነ የመስኖም ሆነ የኃይል ግንባታ በውኃ ላይ ስለአደረጉ ነው፤ ከእኛ ተሽለው ስንዴ የሚመጸውቱን አሜሪካ ኔቫዳ በረሃን ገነት ያደረገችው በምንም ሳይሆን በውኃ ሀብት ልማት ነው:: ለዚህ ነው «This is our strength» የሚለው የኤሌክትሪክ ዓርማ የበለፀጉት አገሮች ምልክት



የሆነው፤ ምን ማለት ነው? ያደጉት አገሮች ጥንካሬ የተፈጥሮ ኃይልን በአግባቡ በመጠቀም በብልሃት መግራቱ ላይ ነው:: ከውኃ ጋር መታረቅ የዕድገት ሁሉ መሠረት ነው::

ከላይ በጠቀስነው መሠረት በ1940 ወይም 1950ዎቹ የተጀመረው የውኃ ልማት ዕድገት ምን ያህል እመርታ አሳይቷል::

በእርግጠኝነት ከ2.7 ሚሊዮን ሔክታር በላይ በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት አለን:: ለምሳሌ ዓባይ ብቻ 760,000 ሔክታር ያለማል:: ተከዜ 200,000 ሔክታር፣ ባሮ 600,000፣ ጊቤ 250,000፣ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች 50,000፣ ገናሌ 300,000፣ ዋቢ ሸበሌ 355,000፣ አዋሽ 185,000 በአጠቃላይ 2,700,000 መሬት አረንጓዴ ምንጣፍ ማልበስ ሕፃናቶቻችንንም ሕልቆ መሣፍርት በሌለው የተንጣለለ የእርሻ መሬት ላይ እንዲቦርቁ ማድረግ እንችላለን:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ከውኃ ጋር ስንታረቅ ነው::

ለመሆኑ ከዚህ ውስጥ ያለማው ምን ያህሉን ነው? አሁንም የተለያዩ ጥናቶች የተለያዩ ቁጥር ያስቀምጣሉ:: ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስከ 1970ዎቹ ወደ 100,000 ሔክታር ብቻ በዘመናዊ እርሻ መስኖ ለምቶ ነበረ ይባላል:: በንጉሡ ዘመን የዋቢ ሸበሌ ፕሮጀክት በ1953 ተጀምሮ በ1965 ዓ.ም. ተጠናቋል:: የተከዜ፣ የመረብና የጋሽ ወንዝ ጥናት ተጠናቆ ነበር:: በአጭሩ የንጉሡ ነገሥቱ መንግሥት በውኃ ልማት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ አተኩሮ ይሠራ እንደነበር የውጪ ባለሀብቶችን ጨምሮ የአገር ቤቶቹን ሁሉ ለማሳተፍ ከፍተኛ ዝግጅት ላይ እንደነበረ በ1957 የወጣው U.S Bureau ጥናት እንዲሁም የጀርመን ኢነርጂ ቡድን አረጋግጠዋል::

በአጠቃላይ ከ2.7 ሚሊዮን ሔክታር ውስጥ ምን ያህሉ በመስኖ ለማ? አንዳንድ ጥናቶች 97,000 ሔክታር ብቻ ለማ ይላሉ:: ሌሎቹ ደግሞ አሳንሰው የለም 64,000 ብቻ ነው የሚሉም አሉ:: ግን ከጥናቶቹ ከፍተኛውን ብንወስድ 168,000 ሔክታር ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል:: መልማት ካለበት በመቶ ሲሠላ 4.5 በመቶ ብቻ የለማ እና ይህም አኃዝ

**በ1980 ዓ.ም የተወሰደ ሲሆን፤ በዚህ ዘመን ከ4.7 በመቶ ከፍ ብሏል የሚል መረጃ አግኝተናል 400 ሺህ ሄክታር ለማልማትም በዕቅድ ላይ ነው የሚል ጽሑፍ አግኝተናል ::**

ካለን የተፈጥሮ የውኃ ሀብት በመስኖ የሚለማው መሬት ብቻ 20 በመቶውን ብንጠቀም ረሃብ የተባለው ቋንቋ ከኢትዮጵያ ይጠፋ ነበር:: ታዲያ ምንድነው ችግራችን? እንጀራና ዳቦ ሊሆን በማይችል የፖለቲካ ንትርክ ጊዜአችንን ከምናጠፋ፣ ወይም እጅግ እየተስፋፋ የሄደውን ቁጭ ብሎ ጫት መቃምን የመሠለ አጉል ባሕል ትተን ወደ ልማቱ ብናመራና ከውሃ ጋር ብንታረቅ ለመሆኑ እኛን ድሆች ብሎ የሚጠራን ማን ነበረ?

እንቅልፍ ሊይዘን አይገባም:: እኛን ከሚመስሉ ጐረቤቶቻችን ጋር ስንነጻጸር ለምሳሌ ኢትዮጵያ 74% ከተሞችዋ ንጹሕ ውኃ ያገኛሉ ሲባል ዝምባብዌ 100% ያገኛሉ:: በውኃ ሀብት ግን እኛ እንበልጣለን:: እጅግ የሚያሳዝነው የኢትዮጵያ ገጠሮች 11.5% ብቻ ንጹሕ ውኃ ሲያገኙ ኬንያ በዚህ ዘመን 35% አድርሳዋለች:: ሌላው ቀርቶ ከአፍሪካ ወንድሞቻችን ጋር እንኳን መወዳደር ያቃተን ለምንድን ነው?

ስለዚህ ሁሉም በኢትዮጵያ ውኃ ዙሪያ ያጠኑ ጠበብት የሚስማሙበት አንድ አጠቃላይ ሐዘን አለ:: ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን በተለይ በገጠሩ ያሉት በተለያዩ ተሐዋስያን የተለከፈና የተበከለ ውኃ ስለሚጠጡ ለከፍተኛ የውኃ ወለድ በሽታዎች ተጋልጠዋል:: የተበከለውንም ውኃ እንኳን ለማግኘት እናቶቻችን እንሥራ ተሸክመው የአንድ ሰዓትና ከዚያም በላይ መንገድ መጓዝ አለባቸው:: የእኛ ሰው የሚኖርባት ዕድሜ በአማካይ ከ45 አይበልጥም:: ስለዚህ ነው ሽማግሌ ለዓይን እንኳን የጠፋው::

ውድ ምሁራን!! ይህ እጅግ አያሳዝንም ወይ? የሚረግፉት ሕፃናት ሆዳቸው የተለያየ በሽታ ጉሬ ሆኖ የተቆዘረው፣ ቀጫጫ እና ደካማ ሕፃናት፣ ቅስማቸው ገና በለጋነት የተሠበረ፣ የሰለለና የከሣ ገላ ያላቸው ወጣቶች አሳዳጊ የሆነችው ኢትዮጵያ ከውኃ ጋር ትታረቅ ዘንድ የሞት ሽረት ትግል ማድረግ ይጠበቅባችኋል::



የውኃ ልማትን ለማበልፀግ አንዳንድ መወሰድ ያለባቸው እርምጃ ዎች መኖር አለባቸው:: ከሁሉ በፊት የውኃ ፖሊሲያችን የተፍታታ እና በተለይም በደርግ የኮሚኒዝም ሥርዓተ ማኅበር የታሠረበትን ሠንሠለት በግልጽ የሰባበረና አርነት የወጣ፣ ሁሉንም ሊያሳትፍ የሚችል ዋስትና ይኖረው ዘንድ እርምጃ ያስፈልጋል:: ለግንዛቤ ያህል ያለፈው የደርግ ሥርዓት ከፍተኛ የውኃ ሥራ ቢያካሂድም ምሁራኑ እንደሚስማሙበት :

በደርግ ዘመነ መንግሥት ለባሕላዊው እና ለአነስተኛው የመስኖ ሥራ እጅግ ጥቂት ትኩረት መስጠቱ አንደኛው ስህተት ሲሆን፤ ሁለተኛ ውና ሦስተኛው ሁለቱ ዐበይት የደርግ ሥርዓተ ማኅበር የውኃ መርሐ ግብር ስህተቶች ሕዝቡን በውኃ ልማት አለማበረታታቱ እና የተ ጠቃሚውም ተሳትፎ ትኩረት ስለአልተሰጠው ነው ይላል የዓለም ባንክ ጥናት::

የውኃው ልማት ተጠቃሚ ኅብረተሰብ ተሳትፎ እና ንቃት ካልተ ጨመረበት፣ የባለቤትነት መንፈስ ሕዝቡ ካልተሰማው የሚሠሩ ልማቶች ሁሉ ወደ ጥፋት ይለወጣሉ:: ስለዚህ ነበር ችግኝ ትከል ተብሎ የተገደደው ገበሬ በሥሩ በኩል ሳይሆን በጭንቅላቱ ሆን ብሎ ዛፎቹን ሲተክል የነበ ረው::

ሌላው ባለሀብቶች በልማቱ ውስጥ እንዳይሳተፉ የኮሚኒስቱ ሥርዓት ስለአገዳቸው ችግሩ እጥፍ ድርብ ሆነ፤ ከዚህም አልፎ ተርፎ በ1968 ዓ.ም. ታታሪ ነጋዴዎችን አሻጥረኛ ብሎ ደርግ ስለረሸነ ባለሀብቶች ከኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፈጽመ ተፍቀው ነበር:: ስለዚህ ምንም መንግሥት ቢፈራገጥ ካለሁለቱ ዋልታዎች ማለትም የሕዝብ ተሳትፎ ንቃት እና ከባለሀብቱ ጥምረት ውጪ የውኃ ልማት ዘበት ነበር:: ቢሆንም መጠነኛ ልማቶች መካሄዳቸው አልቀረም፤ በንጉሡ ዘመን የተነደፉት ልማቶች መካሄዳቸው አልቀረም፤ በጥቂቱ ተፈጻሚነትም አግኝተዋል::

በዚህ ዘመን ሕዝባችን ቁልፍ የልማት አውታሮች ምን እንደሆኑ በመረዳት ላይ ነው:: የምሁራኑ ዝንባሌም ጥናትን ተመርኩዞ ለሚደረጉ ልማቶች ድምጻቸውን እያሰሙ ይገኛሉ:: በዘመናችን የነጻ ገበያ ፖሊሲ

መሠረት ባለሀብቶች ከሞላ ጐደል ነጻ ሆነው መንቀሳቀስ ጀምረዋል:: የሕዝባችን የልማት መንፈስም የሞቀ ነው:: ብልጥ ከሆንን ዘንድሮም ለመሮጥ እንችላለን::

ለዚህ ግን ጥቃቱ ምን ያህል ሊሰማን እንደሚችል አንዳንድ አገሮችን በንጽጽር አሁንም እናያለን:: ለምሳሌ ግብጽ ልታለማው የምትችለው አካባቢ የዓባይን ተፋሰስ ተከትሎ ያለውን መሬት ብቻ ሲሆን፤ ሌላው አሸዋማ በረሃማ መሬት የበዛበት መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው::

ከጥንት ጀምሮ የግብጽ ፈርዖኖች በዓባይ ሲያጌጡና ከኢትዮጵያ የሚንዶለዶለውን ጥቁር አፈር ሲገምጡ እንደኖሩ ግልጽ ነው:: በዚህ ዘመን አልፎ ተርፎ ለመካከለኛው ምሥራቅ ለምዕራቡ ዓለም ሳይቀር በጠርሙስ የታሸገ የፓፓያ፣ የዘይቱን እና የአናናስ ምኑ ቅጡ ጁስ እየቸ ረቸሩ ይገኛሉ:: በእውነቱ መመቅኘት ሳይሆን ከእኛ በተገኘ አፈር እንዲህ የናጠጠችው ግብጽ እኛን ምንኛ ልታስተምረን በቻለች::

በእኛ ዓባይ ግብጾች የዓለምን ገበያ ሲያጨናንቁ እኛስ የዓባይ፣ የጣና፣ የላንጋኖ፣ የሻላ፣ የአብያታ፣ የአዋሣ፣ የባሮ፣ የአዋሽ፣ የዋቢ ሸበሌ፣ የተከዜ፣ የጊቤ ምኑ ቅጡ ወንዞች ባለቤት ሞሶሎኒ ሳይቀር ኢትዮጵያን ገነት ብሎ የጠራት አገር ባለቤት ሆነን ለመሆኑ ከገበሬው ደሳሳ ጐጆ በረሃብ ምክንያት አስከሬን በቃሬዛ ይውጣ ወይ? ከውኃ ጋር እንታረቅ::

በልጅነታችን መሬቱን ቆፍረን የምናወጣው የጣዝማ ማርና በየዛፉ ያሉ ውብ አበቦችን ቀስሞ ማር የሠራው ንብ ሀብት እኮ ነው:: ይህ ሁሉ ከውኃ ጋር የተቆራኘ መሆኑ ሊረሳ አይገባም::

ከዚህ ቀጥሎ የውኃ ሀብት ልማት በ1999 መጋቢት ላይ በሚኒስትሩ አማካኝነት ያስተላለፈውን የኢትዮጵያ የውኃ ይዞታን በተ መለከተ ከቅርብ መረጃ ያጠናቀርነውን እንተነትናለን:



የኢትዮጵያ የገጠር መጠጥ አቅርቦት 23% እንደነበረ እና ወደ 41% እንዳደገ ተገልጿል:: የከተማ መጠጥ አቅርቦት ከነበረበት 74% ወደ 78% ማደጉን ከሪፖርቱ አይተናል:: የመስኖ ልማት ገና እየዳኸ ነው:: ወደ 430,000 ሔክታር ለማልማት ገና ዕቅድ ወጥቷል:: ይህ ሊለማ ከሚችለው ጋር ሲነጻጸር እጅግ ጥቂት ነው ቢሆንም ጅምሩን እናደንቃለን:: የባለሀብቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነው ተብሏል፤ ግን ወደ ልማቱ ገና በብዛት አልመጡም::

## ዓባይ እና መዘዙ

ስለኢትዮጵያ ወንዞች ሲነሳ የዓባይ ችግር ሊዘለል የማይችል ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መጠላለፍ ከፈጠሩብን ዐበይት ጉዳዮች አንዱ ነው::

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብቶችዋ የታደለች አገር ናት ቢባልም ይህ ሀብት ደግሞ የብዙ መዘዞችም ምንጭ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም:: በተ ለይ የቀይ ባሕር ዳርቻን ከመነጠቋ በፊት ከታላላቆቹ አገራት ጋር የሚያወዳድር የባሕር በርና የባሕር ኃይል ያላት ሊፈሩ ከሚገባቸው አገራት አንዷ ነበረች:: ይህም የኃያላኑን ዓይን የሳበ እና የውስጥ ከሃዲ ዎችን በመጠቀም ጉልበቷን ለማዳከም የተሞከረበት ሁኔታ ከዚህ ሁሉ የመጣ ነው::

በተለይ ዓባይ ከምንጩ ከጣና ጀምሮ እስከ ካርቱም ድረስ 1529 ኪሎ ሜትር ተጉዞ ለሱዳን ከዚያም ከነጭ ዓባይ ጋር ተቀላቅሎ ለግብጽ ሕዝብ ሕይወት መሆኑን ስናስብ እኛ የዓባይ ልጆች ግን «ውኃ ጠማን» እያልን ማልቀሳችን ለሰሚው እንግዳ ሊሆን ይገባዋል:: ለም አፈራችንን እየቧጠጠ የሚነጉደውን ባለጌ ውኃ መግራት መቅጣት የነበረብን እኛ እንጅ ተጠቃሚዎቹ እነ ግብጽ አልነበሩም::

ለመሆኑ ፈላስፎች «ግብጽ የዓባይ ስጦታ ናት» ብለው ያውም ታዋቂው የግሪክ ፈላስፋ ሄሮዶተስ ሲናገር በግልባጩ ዓባይ የግብጽ ስጦታ ነው ማለት አቅቶት ነው ወይ ፈላስፋው አባባሉን ያገላበጠው?

እንደ እውነቱ ከሞኝ አገር የዘረፈውን አፈር በስጦታ የሚለግሰው ዓባይ ስጦታው እንጅ ግብጽማ በአቧራ የታወከች በረሃ እንዴት ስጦታ ልትሆን ትችላለች:: በዚህ ስጦታ ተጠቅመው ግብጾች በዓመት 2.8 በመቶ እያደጉ ይገኛሉ::

ስለዚህ የኢትዮጵያን መከፋፈልና መዳከም ግብጾች እጅግ ይፈልጉታል:: ጠንካራና በእራስዋ የምትተማመን አገር ከሆነች በዓባይ ላይ ጥያቄ ማስከተሏ ስለማይቀር በዓለም አቀፉ የፖለቲካ መስመር መሰናክል በመፍጠር ኢትዮጵያን ስትፈትናት ኖራለች:: ይኸውም የውስጥ እረባሾችን በማደራጀት፣ ፖለቲካውን በማወሳሰብና በጐሣ በማጋጨት የሚደረግ ሴራ ነው:: ለዚህ ደግሞ አንዳንድ አገር በቀል ምሁራን እንደዓባይ ለግብጽ የፖለቲካ ስጦታ ሲሳይ ሲያበረክቱ ይታያል::

የጐሣ ፖለቲካ በተለይ ግብጽን ለመሳሰሉ በዓባይ ምክንያት ሊያዳክሙን ለሚፈልጉ ጠላቶቻችን እጅግ ጥሩ ዕድል ፈጥሮላቸዋል:: ካለምንም ድካም የጐሣ ካርታቸውን እየሳቡ እርስ በእርስ ለማፋጀት እጅግ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖላቸዋል:: ብዙዎቹ ፀረ ኢትዮጵያ ስብሰባዎች የሚካሄዱት ግብጽ ውስጥ ነው:: ፀረ ኢትዮጵያ ጦርነቶች የሚነደፉት በግብጽ ጄኔራሎች ነው:: ታዲያ እጃችን አመድ አፋሽ ከሆነ እኛስ በጥንካሬ ካለመከፋፈል መቼ ነው በአንድነት የጐሣ ሽኩቻችንን አሽቀንጥረን እጅ ለእጅ ተያይዘን በአንድነት የምንቆመው?

በእነ ዓፄ አምደጽዮን በ13ኛው ክፍለ ዘመን አል ናስር መሐመድን ያሳፈረች ኢትዮጵያ ዛሬ በገዛ ልጆችዋ መከፋፈል ምክንያት ግብጽን የመሳሰሉ አገራት መጫዎቻ እንዴት ትሁን? ግብጽ ዝናብ ብታገኝ እንኳን በዓባይ ተፋሰስ ዙሪያ (በዓባይ ሸለቆዎችዋ) ያውም 150 ሚሊ ሜትር ዝናብ ብቻ ስታገኝ ሌላው ምድርዋ በረሃ ደረቅ ነው ታዲያ እነዚህ ሕዝቦች ከእኛ የበለጡ ሊሆኑ የሚችሉበት ምክንያቱ ሲታሰብ አይቆጭም ጥቃትስ አይሰማንም:: ለመሆኑ ግብጽ በኢትዮጵያ ዑጋንዳንና ሱዳንን ጨምሮ አለቃ ለመሆን ለምን ትፈልጋለች:: ለምን የዓባይ ጉዳይ የብሔራዊ ደህንነቴ ጉዳይ ነው ብላ ግብጽ ጐረቤትዎችዋን ታምሳለች::



እኛስ በፖለቲካው ብልጫ ለምን አናሳይም ለምን እኛስ አንፈራም:: ለምን እንነጠቃለን? ቢያንስ ለምን የራሳችንን በጥንቃቄ አንጠብቅም:: ለዚህ ሁሉ የፖለቲካ መረጋጋት የፍትህና የሥልጣን ድልድሉ ሚዛን ለሁሉ መብት እና ዕድል መክፈት አለበት:: የውስጥ መረጋጋት ካለን፣ ሁሉ በእኩል በነፃነት ከኖረ የወጪ ጠላቶቻችን ዕድል አይኖራቸውም፤ እኛ አንድ ከሆንን ደግሞ ማንም አያሸንፈንም:: ከጐረቤ ታችን ግብጽ ጋር በእኩልነት በመከባበር ልንኖር የምንችለው እኛ ጠንካሮች ከሆን ብቻ ነው::

## የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተፋሰሶች

ዓባይ፣ ኦሞ፣ ጊቤ፣ ባሮና አኮቦ ሲሆኑ፤ በመረጃው መሠረት 53.2% የያዘው ዓባይ ወንዝ ነው፤ ተፋሰሱ ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት ውስጥ 17.5% ሲሸፍን በክልሉ የሚኖረው ሕዝብ ደግሞ ከጠቅላላው ውስጥ ወደ 27% የሚሆነው ነው::

ከፍተኛ ተፋሰሶች ዓባይ፣ ኦሞ፣ ጊቤ፣ ባሮና አኮቦ ከጠቅላላው የሀገሪቱ ውኃ ውስጥ 77% ከቆዳ ስፋቱ 31% ከሕዝብ ብዛት 44% ይይዛሉ ይለናል::

ኢትዮጵያ በኅብረት በእነዚህ ሀብቶች ላይ በአንድነት ብትሠራ ግን መጠኑ እንኳን ለእኛ ለብዙዎችም ይበቃል ሚሲሲፒ የአሜሪካ እንጂ የሚሲሲፒ ተፋሰስ አካባቢዎች ሀብት ስላልሆነ አገር አቀፍ የልማት ዋስትና ሆኗል::

## ማጠቃለያ

ውኃ እጅግ ጥቅም የሚሰጥና የሕይወት ዋስትናን የሚያረጋግጥ ሀብት ነው፤ ጣዕሙ የማይጠገብ፣ ውበቱ ማራኪ ነው::

ስለዚህም መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙሩ ሰማይን እንደ መጋረጃ ዘረጋህ ይልና እልፍኙን በውኃ የሚሠራ ሠረገላውን ደመና የሚያደርግ የሚለው ውኃ ምድራዊ ጌጥ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊም መሆኑን ሲነግረን

ነው። እንኳን የዚህች ምድር የሰማዩም ውበት ውኃ ነው። ከሰባቱ ሰማያት አንዱ ሰማይ ውዱድ የሚባለው በውኃ የተሠራ ነው። ውኃ መርገፍ ያላት እንደሆነች የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳናል።

በዚህ ምድር ያሉ ውበቶች የውኃ ውጤቶች ናቸው። ልምላሜው ፏፏቴው፣ ደመናው፣ ባሕሩ፣ ማዕበሉ እነዚህ ሁሉ የውኃ ውበቶች ናቸው። ውኃ የሕይወት መሠረት ነው። ማንኛውም የበለፀገ ዓለም ብልጽግናው ውኃን መሠረት ያደረገ ነው። ለውኃ ልማት አራት ዐበይት መሠረታዊ ጉዳዮች ያስፈልጋሉ። አንደኛው አነስተኛ እና መካከለኛ የመስኖ ልማት ባሕላዊውን እና በየገበሬው የሚካሄዱ የልማት መሠረቶችን ማበልፀግ። የመንግሥት ፖሊሲ ለባለሀብቱ ማለትም ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አመቺ ምንጣፍ መሆን ይገባዋል። ለተጠቃሚው ሕዝብ የባለቤትነት መንፈሱን ማበልፀግና የሕዝቡን ንቃት ማሳደግ ናቸው። ይኸውም የታንዛኒያው ፕሬዝደንት ጁሊየስ ኔሬሬ እንዳሉት መሬታችን ምርታችን የሚል ቋንቋ እንዲፈጠር ሕዝቡ በማንኛውም የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ድርሻ ይኖረው ዘንድ ማነሳሳት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ ቢያንስ አፀድዋን በመጥረቢያ ሳታስነካ በዛፎች ድባብ ተከባ የምትገኝ መሆንዋ የተፈጥሮን ቅርስ ጠብቆ ማስጠበቅ እንደሚገባ መናገሯ ነው። ዛፎች ተሟጠው አልቀው ቅሪታቸው በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ መኖሩን ማስተዋል ይገባልና። ይህም ዝናብን ለመሳብ ዋነኛ ምክንያት መሆኑ የታወቀ ነው።

ዛሬም በየአድባራቱ እግዚአብሔር የሰጠንን የአየር ጠባይ ለመጠበቅ ዛፎችን መንከባከብ ለውኃም ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ማስተማር ይገባል። ሌላው ቀርቶ ጥንታዊዎቹ አገር በቀል ዛፎች ችግኝ ከየገዳማቱ መሰብሰብም ይኖርብናል። ስለዚህ የገዳማቱ የደን ጥበቃ ባለበት ማቆየት ብቻ ሳይሆን መስፋፋትም አለበት። የሕዝቡ ዕድገት መሠረት ቤተክርስቲያን ናትና። ሕዝቡ ከውኃ ጋር እንዲታረቅ ቤተክርስቲያን ጥሪ እንድታደርግ ያስፈልጋል። የውኃ ሀብታችንን በአግባቡ እንጠቀምበት፤ በብልሃት እንንከባከበው፤ ከውኃ ጋር እንታረቅ።



አብዛኛው የሰሜን ተራራዎች ገላጣ መሆናቸው ቢያሳዝንም ግን በድንጋይ እየተገነቡ ተራራውን በደረጃ በመክበብ ውኃው እንዳይታጠብ እርከን ተሠርቶ በማየታችን የኢትዮጵያ ተስፋ ሀሁ ተጀመረ እንል ዘንድ አስገድዶናል። ለዚህም የታሪክ ግዴታቸውን በሙያ እየተወጡ ያሉ የግብርና ሠራተኞችና ይህንን ግዙፍ ሥራ መከራውን አይቶ የሠራውን የሰሜን ገበሬ ደግመን ደጋግመን ልናመሰግን አብቅቶናል። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ወንዞቻችን የደፈረሰ አፈር ተሸክመው ባዕዳንን ሲያበለጽጉ አይኖሩም፤ ያኔ ዓባይ ጥቁር ሳይሆን ነጭ ይሆናል።

ከላይ በአይሮፕላን ለተመለከተው ከሸዋ ጀምሮ እስከ ትግራይ የተሠራው አጠገቤ ያሉትን ነጮች ሳይቀር አስገርሞ «ብዙ ሥራ ተሠርቷል» አሰኝቷቸዋል። እዚህ ላይ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ገንዘባችንን በማውጣት፣ ዛፍ በመትከል ብንተባበር አፋችንን ሞልተን አገራችን ኢትዮጵያ እንድንል ድፍረት ይሰጠናል። በተግባር ከገበሬው ጋር ከተጣመርንና ከተባበርን አረንጓዴዋን ኢትዮጵያ መልሰን የማንፈጥርበት ምክንያት የለም። ለዚህ ሁሉ ግን መታረቅ መግባባት ያስፈልገናል።

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

## ከኃይል ጋር መታረቅ

ኃይል ምንድን ነው? የተፈጥሮ ኃይል ወይም ሰው ሰራሽ ኃይል። በዚህ ዘመን የበለፀጉ አገሮች ዋነኛ ትኩረት ወይም እሽቅድምድም ኃይልን በማሳደግ ላይ የተመሰረተ ነው። ኃይል የሚገኝባቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምንጮችን ማበልፀግ መጠቀም የዘመናችን ሥልጣኔ አካል ነው።

እነዚህ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ምንጮች እነማን ናቸው። የተፈጥሮዎቹ ውኃ፣ ነፋስና ፀሐይ የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ ሰው ሰራሾቹ ደግሞ ከዚሁ ተፈጥሮ የሚቀዱት ኤሌክትሪክ የኒዩክለር ኃይል የመሳሰሉት ናቸው። ሞገዱ እና ነፋሳቱ ማዕበሉ ከመጠን በላይ ያልተገራ ኃይል አላቸው። የጥበብ ኃይል ባለው የሰው ልጅ እየተቆጠቡ ጥቅም ላይም ይውላሉ።

በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን አንድን አገር ከሥልጣኔ ተርታ የሚደምራትም የተፈጥሮ ኃይልዋን ምን ያህል ተጠቅማበታለች የሚለውን መጠይቅ መመለስ ስትችል ነው:: የሚፈሱ ፏፏቴዎች የሚነፍሱ ነፋሳት በውስጣቸው ጉልቶ መሣፍርት የሌለው ኃይል አከማችተዋል:: በተለይ በአገራችን ኢትዮጵያ ከፀሐይ የሚገኘው የሶላር ኃይል የውሃ ኃይል ሌሎቹም ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኙ እንደሆኑ የታመነ ነው::

የኤሌክትሪክ ኃይል ዋና መፍለቂያ የሆነው ውኃ የተፈጥሮን አየር ሳይበክል ለግዙፍ ፋብሪካዎች የሚሆን የብርሃን የሙቀትና የቅዝቃዜ ኃይል የሚሰጥ ሲሆን፤ በስፋት የመብራት ሥርጭትን ለማስፋፋት ተወ ዳዳሪ የሌለው መፍትሔ ሆኖ ቆይቷል:: አሁን ግን በበለፀጉት አገራት ኒዩክለር በሩቅ ምሥራቅ ኒኩሊየር ሶላር ሲስተም፤ በአውሮፓ የነፋስ ኃይልና ባዮማስን የመሳሰሉ የኃይል ማመንጫዎች (ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ፓወርን) እንዳንዴ ሲተኩት ይታያሉ:: ከመሬት ውስጥ የሚወጣው እምቅ ኃይልና በተለይ ነዳጅ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ሸፍኖ የሚገኝ ሲሆን፤ እነዚህ ሁሉ የኃይል ምንጮችን ያካተተ መረጃዎችን በማጣቀስ ከኃይል ጋር እንታረቅ እንላለን::

ደጋግመን በሌሎች ርዕሶች ላይ እንዳነሳነው የሚፈሱ ፏፏቴዎች በውስጣቸው ጉልቶ መሣፍርት የሌለው ኃይል አለ:: በምድር የታመቁ በሰማይ የሚወነጨፉ ነፋሳት ኃይላቸው ሊሰፈር አይችልም:: ከፀሐይ የሚገኘው ኃይል ምን ያክላል ተብሎ ቢጠየቅ ብዙ እጅግ ብዙ የብዙ ብዙ ከማለት በስተቀር መልስ የለም::

ስለዚህ የአሥራ ሦስት ወር ፀሐይ፤ ብዙ ወንዞች፤ በከርሠ ምድሯ ተመርምሮ ያልተደረሰበት ክምችት የኃይል ያላት ኢትዮጵያ ከኃይል ጋር ብትታረቅ ማደግዋ ሊያጠራጥር አይገባም::

**ዓለም አቀፍ የኃይል እሽቅድምድም**

አሜሪካ ውስጥ በ2004 እኤአ በተደረገው ምርጫ ጆን ኬሪ የተ ባሉት ከዴሞክራት፤ ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ከሪፐብሊካን በእጩ ምረጡኝ



ክርክራቸው (Debat) ከወትሮው በተለየ መልኩ ኃይልን ማበልፀግ ላይ ጠንካራ እስጥ አገባ አንሥተው እንደነበር የሚታወስ ነው::

ጆን ኬሪ የፔትሮሊየም አምራች የዐረብ አገር ቱጃሮችን ያጠገብናቸው እኛ ነን ለቴሬሪስቶች የሚለግሱትን ገንዘብ እኛ እየሰጠናቸውም (ፔትሮሊየሙን እየገዛን) በገዛ ራሳችን ላይ ይዘምቱ ዘንድ አደረግናቸው የሚል ዘየ ያዘለ ንግግር ነበር:: እንግዲህ ለእነዚህ የዐረብ ቱጃሮች ስንገብር እንኖርም አማራጭ የነዳጅ ምንጭ ብትመርጡኝ አስፋፋለሁ ሲሉ ተሰምተዋል::

የኢራቅ መወረር ዋነኛ መንስኤም የአሜሪካ የነዳጅ ጥማት ነው የሚሉ አልጠፉም:: ስለዚህ በዚህ ዘመን የዘይት ጉዳይ እጅግ አንገብጋቢ ጦርነት የሚያማዝዝ ሆኗል::

በዘይት ሽያጭ የናጠጡት የዐረቡ ዓለማት የዓለም ኃይል ምንጮች በመሆናቸው ድምጻቸው ከሌሎች አገራት ከፍ ብሎ ሲሰማ እናያለን:: ስለዚህ ይህንን መንፈስ ለመለወጥ ምዕራባውያኑ አማራጭ የኃይል ምንጮችን ከማፈላለግ አልቦዘኑም::

በዚህ ዘመን ዓለማችን ይህንን ንጥረ ነገር የዘይት ድፍድፍ እኛ ቤንዚን የምንለውን ለመተካት ሰፊ የሳይንስ ምርምር እየተካሄደ ነው:: የዚሁ ጥረት ውጤት ነው:: የአልኮልና ነዳጅ ቅልቅል የሆነው ይህ ፈጠራ ከማንኛውም አልኮል መፍጠር ከሚችል ነገር የሚቀመም ነው:: ብራዚልን የመሳሰሉ አገራት ከሞላሰስ ይህንን ንጥረ ነገር በመፈልሰፍ በቅርቡ ሥራ ላይ ለማዋል ደፋ ቀና እያሉ ነው::

አውሮፓውያኑ በተለይ የእስካንዲቪያን አገሮች ለአየር ብክለት ስለሚጨነቁ ነፋሻ የወንዝ ዳርቻዎችን በመከተል ከፍታ ያላቸው ባለመዘውር ማማዎችን በመትከል ከነፋስ ኃይልን ሲያከማቹ ሰንብተዋል:: ኢታኖል ኢ ሰማንያ አምስት ሙከራ ወደ ሜቴን ፊውል ተሸጋግረዋል:: ይኸውም 85% ኢታኖል ያለበት 15% ብቻ ቤንዚን የተቀላቀለበት ማለት ነው::

በእኛው አህጉር ያለችው ታላቅዋ የነዳጅ አምራች አገር ናይጀሪያ ወደ 280 ቢሊዮን ዶላር ከነዳጅ በማግኘትዋ እንደ አገራችን አጠራር ሀብታም ሆናለች። ግን ምን ያደርጋል ገንዘቡም ቢገኝ ሕዝቡ ተካፋይ አልሆነም በከፋ ድህነት ውስጥ አሁንም ይማቅቃል። የምዕራባውያን መሪ ዎች እንደነ ቶኒ ብሌየርና (የእንግሊዙ)፤ ጆርጅ ቡሽ (የአሜሪካው) ፕሬዝደንት አሲሳንጐ አባሳንጐን የሚያቀላምጡት ታላቁ የዴሞክራሲ አራማጅ የሚሏቸው የቤንዚን ቧንቧው ቁልፍ በእጃቸው ስላለ ነው።

በዚህ ዘመን የሚደረጉ ጦርነቶች በአብዛኛው ከኃይል ጋር የተ ያያዙ ናቸው። እንደውም ይህ ርዕስ ወደ 3ኛው የዓለም ጦርነት ሊወስደን ይሆን? እያሰኘ ሲያስጨንቅ ይገኛል። ለምን? ከላይ እንደጠቀስነው በዘይት የከበሩት አገራት ኃይል እየተሰማቸው ሲሄድ የፖለቲካውን መሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመጨበጣቸው (አይዶዎሎጂ) መርህአቸው በአመዛኙ የአክራሪ ወይም የሽብርተኛ አዝማሚያ ይይዛል ተብሎ ስለሚገመት ከምዕ ራባውያኑም በነዳጅ ምክንያት የሚደረግባቸውን ጣልቃ ገብነት ለመቋቋም የሽብርን ወይም የጦርነትን አማራጭ ሊይዙ ይችላሉ የሚል ግምት አለ።

መገመት ብቻ ሳይሆን ወደ ጦርነትም ውስጥ ስለተገባ በኢራቅ በቅርቡ ደግሞ ከኢራን ጋር ያለው የፖለቲካ ትኩሳት አቅጣጫው በውል ስለማይታወቅ የዚህ የቤንዚን ጣጣ በቀላሉ ሊፈታ የማይችል ጠንቀኛ ነገር ይመስላል።

በነዳጅ አምራችነቷ የምትታወቀው ኢራን ኒዩክለር አምራች ለመሆን በምትፍጨረጨርበት በአሁኑ ወቅት ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በኢራን ላይ እምነት እያጣ ሄዷል። እሷም ምንም እንኳን ለሰላማዊ ሁኔታ ነው የምጠቀምበት ብትልም በተባበሩት መንግሥታት ተደጋግሞ የትጥቅ ፍቺ ማስጠንቀቂያ ደርሷታል።

ለመሆኑ ይህ ሁሉ የነዳጅ ክምችት ያላት አገር ሌላ አማራጭ ማለትም ኒዩክለር አረር የምትፈልስፍበት ምክንያት ምንድነው? በዚህች ሀገርና አካባቢ ከጥንት ፈርዖኖች ጀምሮ ዓለምን ለመምራት የማይሽቀዳደም የለምና በሀብት ተምነሽንሸው ሲተርፋቸው ደግሞ ምን



ልፍጠር ብለው ባሕር ተሻግረው የሌላውን ጸጥታና ሰላም የሚያደፈርሱ አገራት መሪዎች በኃይል ላይ ኃይልን መጨመር ሲፈልጉና ሲፍጨረጨሩ እንደነበር ታሪካቸው ይመሰክራል።

ስለዚህም የሰው ልጅ በኃይል ማመንጨት መስክ ታላላቅ ዕድ ገቶችን ቢያሳይም ወደ መጠፋፋት የሚወስድ ሩጫው ሁሉንም አስጨንቆ ይገኛል።

## የኒዩክሌር ኃይል

ዛሬ የበለጸጉት አገሮች በሙሉ ከተሞቻቸውን የሚያንቀሳቅሱት በኒዩክለር ኃይል ነው። በአይሮፕላን ሆኖ ወደታች ሲታይ እንደፈርጥ የሚንቀለቀለው የተለያየ ሕብር ያለው የከተሞች መብራት በጨለማ ውስጥ በጥቁሩ የመሬት ወለል ላይ ተነጥፎ ላየው የሰው ልጅ ኃይልን ምን ያህል እየተጠቀመበት እንዳለ መገመት ያስችላል።

ታዲያ በአብዛኛው ይህ ኃይል የሚመነጨው ከኒኩለር ኃይል መሆኑን ለተረዳ በታናሸዋ ንጥረ ነገር በተሠራው ተአምር ከመደነቅ ውጭ በቋንቋ ሊገልጹት ያዳግታል።

ነገር ግን እንደ (የመዋዕለ ንዋይ ጠበብት) ኢኮኖሚስቶች አባባል ይህ የኒኩለር ኃይል እጅግ አነስተኛ በሆነው ንጥረ ነገር ፋብሪካዎች ማሽከርከር ቢችልም አደገኛነቱንም እየተረዱ ይገኛሉ።

## ለመሆኑ የኒዩክለር አደጋ ምንድነው?

አንደኛ የኒዩክለር ዝቃጭ የሚደፋበት ቦታ የተመረጠና በከፍተኛ ጥንቃቄ የተዘጋጀ መሆን አለበት። ሁለተኛ የዚህ ሥራ ጠበብት ጠንቃቃ መሆን ይኖርባቸዋል። (በሶቪየት ኅብረት ከኒዩክለር ተቋሙ አምልጦ የወጣው አደገኛ አረር ብዙ ሰው እንደጨረሰ እስካሁንም ተፈጥሯቸው የተ ዛባ ሕፃናት መፈጠራቸውን ማስታወስ ይገባል።) ዝንጉ ሰዎች ወይም መንግሥታት በድህነትም እንኳን በቂ ጥንቃቄ ካላደረጉ መዘዙ ከፍተኛ ስለሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ሌላው ይህ ኃይል በክፉ ሰዎች እጅ ከወደቀ ጉዳቱ ሊመዘንና ሊገመት ከሚቻለው በላይ ነው:: ለምሳሌ ቢንላዲንን የመሳሰሉ አሸባሪዎች እጅ ቢገባ ጠንቁ የትየለሌ መሆኑ እርግጥ ነውና:: ይህ የኒዩክለር ጥበብ ቀድሞም ባይፈጠር ይሻል ነበር አሰኝቷል::

ታዲያ ኢራን ይህንኑ አዳፍኔ ብትታጠቅ ለነቢንላደን የማታስተ ላለፍበት ምክንያት አይኖርምና ዓለም ጠንካራ አቋም በኢራን ላይ የያዘው ለዚሁ ነው:: ስለዚህ በዚህ ዘመን ዓለምን ካስጨነቁ በሽታዎች ኤድስን ከመሳሰሉት ከአየር መዛባቱና ከረሃቡ የበለጠ ሰው በገዛ እጁ የሠራው አዳፍኔ የበለጠ ሁሉን አስጨንቋል:: እጅግ የሚያስደንቀው ግን በዚህ በኒዩክለር ጥበብ የተራቀቁት እና ጀማሪዎቹ ከዚህ ኃይል ይልቅ ሌሎች አማራጭ ኃይሎችን መጠቀም የበለጠ ውጤታማ ጤናማም እንደሆነ ይመሰክራሉ::

የመዋዕለ ነዋይ ጠቢብ የሆነው (ጆን ፓርከንስ) እንደሚለው «የእኔ የሥራ ድርሻ ኒውሀምሻር በተባለ የአሜሪካ ክፍለ አገር ውስጥ ለሚኖሩ ሕዝቦች የኒዩክለር ኃይል እጅግ መልካም ዝቅተኛ ወጪ የሚጠይቅ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ መሆኑን ማሳመን ነበር:: የሆነው ሆኖ በጉዳዩ ጥልቅ ምርምር ባደረኩ ቁጥር የዚህ አባባል እውነተኛ ነት እያጠራጠረኝ መጣ::»

ብዙ አማራጭ የኃይል ምንጮች ከኒዩክለር የበለጠ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጡ ጠቋሚ ምልክቶች እየጨመሩ ሲመጡ ከጊዜ ወደ ጊዜ አባባሉ እየተለወጠ መጣ::

የጥንቱ ብሒል ሚዛን ኒዩክለር አደጋ የለውም የሚለው አባባል በከፍተኛ ሁኔታ ጥያቄ ማስነሳት ጀመረ:: በቅድመ ጥንቃቄው ዘዴ የሠለጠነው የሰው ብቃት ዝንባሌና ስህተት የመሥራት ወይም ያለመሥራት ሁኔታ በተጨማሪም የኒዩክለር ዝቃጭ የሚደፋበት አዘቅት ዕቃ ብቃት ሁሉ ጥያቄ ውስጥ እየገባና እያጠራጠረ መጥቷል:: የኒዩክለር ዝቃጭ (ተረፈ ምርት) አደገኛ ጨረር ስለአለው ለሰዎች ጤንነትም አስጊ ስለሆነ መጠንቀቅ ያሻል::



ከዚህ በላይ ያለው መደምደሚያ ላይ የደረሱት የዚህ ንጥረ ነገር ፈልሳፊ እና ከሁሉም በላይ ተጠቃሚ የሆኑት የበለጠ ጥንቃቄ የሚያደርጉት ሀብታሞቹ አገራት ምሁራን ከሆኑ በዓለማችን ያሉ በመዋ ዕለ ንዋይ አቅም ደካማ የሆኑ አገሮች በሙያው የብዙ ጊዜ ልምድ የላቸውምና ብቃታቸው ምን ያህል እንደሆነ መገመት አያዳግትም::

ስለዚህ ብዙ አገራት ከዚህ ኃይል ይልቅ የተፈጥሮ ኃይሎችን ሥራ ላይ ማዋልን እየመረጡ መጓዝ ጀምረዋል:: ከኒዩክለር ኃይል ባልተናነሰ የፖለቲካ ሽኩቻ መጠፋፋትን ያስከተለው ሁለተኛው የኃይል ምንጭ ደግሞ የተፈጥሮ ዘይት (ቤንዚን) ሲሆን፤ ይህ የተፈጥሮ ዘይት በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአገሮች መካከል የይስሙላ ሰላም እንዲኖር ያደረገ እውነቱ ሲታይ ግን ሰላምን ያሳጣ፤ ብዙዎችን ያሳበጠ በጥቅም ያጣመ ረ እና ያሳወረ ፈሳሽ ዕንቁ ነው ማለት ይቻላል::

በ1960ዎቹ ኅብረት የፈጠሩት አባላት ዋናው ትኩረታቸው በነዳጅ ኃይል የዓለምን የፖለቲካ አቅጣጫ መቆጣጠር መሆኑ እርግጥ ነው:: ለምሳሌ ሰባቱ እህትማማቾች የተባሉት ነዳጅ አምራቾች በ1973 እኤአ መላው የዐረብ አገሮች እሥራኤልን በወጉበት ጊዜ፤ ፕሬዝደንት ኒክሰን በኮንግረስ እሥራኤልን ረድተው ስለተናገሩ፣ እርዳታ ለእሥራኤል ይሰጥ ዘንድ በመወሰኑ፣ እነዚህ የኦፔክ አገራት በዚሁ ዓመት (oil embarg) የነዳጅ እቀባ በአሜሪካ ላይ ጥለው እንደነበር ይታወሳል::

አሜሪካም በአፀፋው ረጋ ብላ በረቀቀ ፖለቲካ የአጭር ጊዜና የ ረጅም ጊዜ ዕቅድ በቅድሚያ የነዳጅ ፏፏቴ የሆነችው ሳዑዲ ዐረቢያን በመያዝ የአሜሪካና የሳዑዲ የነዳጅ ሽርክና (USAID) የሚባል ድርጅት ፈጥራ ከስድስቱ እህቶችዋ ከመነጠልዋ ባሻገር ዋናዋን የዚህ ፀረ ምዕ ራባውያን ግንባር አንቀሳቃሽዋን ግብጽን እንዲሁም የመንን በድህነታቸው ምክንያት ጠልፋ ከሌሎቹ የዐረብ አገራት በመነጠል በፈጠረችው የፖለቲካ ሽብር የኦፔክ አባላት በፖለቲካ ጥገኝነት ከአሜሪካ ቁጥጥር እንዳይወጡ ሆነዋል::

በተለይ ከ1993 ብላክ ሀክ የተሰኙት ሁለት ሄሌኮፕተሮች ሱማሌ ውስጥ ከወደቁ በኋላ አሜሪካ ወደ አንድ አገር ሠራዊትዋንም ሆነ ሀብቷን የምታፈሰው ብሔራዊ ጥቅሟን የሚያስከብር ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው የሚለውን የቀድሞ ውስጣዊ መመሪያ ይፋ አድርጎታል። በተለይ በዚህ ዘመን ነዳጅ ካላቸው አገራት ጋር አሜሪካም ሆነች ምዕራባውያን ቻይናም ሆነች ራሽያ የቃል ኪዳን ቀለበት ሲያጠልቁ ማየት የተዘወተረ ሆኗል።

የአሜሪካንን ብሔራዊ ጥቅም የማያስከብር ዝምድና ፈጽሞ የለም። ጥቅም ከሌለ ከዚያ አገር የፖለቲካ ውጣ ውረድ የመውጣት ንድፍ ተነድፎ ጊዜን፣ ሀብትንና የሰው ሕይወትን ሳያባክኑ ወደሌላው የጥቅም አቅጣጫ ይኬዳል።

እንዲህ ሲባል ግን የምዕራባውያን የሰብአዊ ተራድኦ ሠራተኞች ከፖለቲካ ነጻ የሆነ ግልጋሎትን መስጠታቸውን አይጨምርም። በዓለማችን እጅግ እያደገ የመጣው ከፖለቲካ ጋር ያልተነካካ የሰብአዊ ሥራ ጥቅምን ሳይሆን በጥቂቱ የሰው ልጅ ደህንነት ላይ ብቻ ያተኮረ ሆኖ ተገኝቷል።

ርዕሳችን ከኃይል ጋር መታረቅ ነውና ወደ ርዕሳችን ተመልሰን ይህ ጠንቀኛ ፈሳሽ የብዙዎችን አገራት ፀጥታ አደጋ ላይ ጥሎ መገኘቱን ስናይ፤ ቤንዚን ለመሆኑ ለአንድ አገር ብልጽግናንና ሰላምን ያስገኝ ይሆን? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል።

የሚገርመው በዚህ በጠንቀኛ ፈሳሽ ምክንያት በእርግጥ የብዙዎች አገራት ሰላም በእጅጉ ተናግቷል። ምንም ብዙ አገራት የነዳጅ አምራች ቢሆኑ ሕዝቦቻቸውን ከድኅነት አረንቋ ማውጣት አለመቻላቸው የነዳጅ ሽያጭ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጪ ጥቂት ቱጃሮች ሲሳይ መሆኑን ስናይ ለመሆኑ ጥቅሙ ምንድነው እንድንል ያደርገናል። የናይጀሪያ ሕዝብ የነዳጅ ጉድጓዶችን በቦምብ ሲያጋይ ስናየው ይህ ቤንዚን ለተራው ሕዝብ ከብልጽግና ይልቅ መቅሠፍት ሆኗልን? ብለን እንድንመረምር ይገፋፋናል።

ለዚህም ዓይነተኛ ምሳሌ የተባለችውን የላቲን አሜሪካ አገር መጥቀስ ይቻላል። በ2005 ብቻ ወደ 84 ቢሊዮን ዶላር ከነዳጅ ያግበሰበሰችው ቬንዝዌላ መሪዋን እንኳን በነጻነት ለመምረጥ እስኪሳናት



ከመድረስዋ ባሻገር ሕዝቦችዋም እስከቅርብ ጊዜ ከድህነት ወለል በታች እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል።

ከዚሁ የነዳጅ ኃይል ተከትሎ በመጣ ጠንቅ የፖለቲካ መረጋጋት ያጡ አገራት ብዙ ናቸው። ስለዚህ የቤንዚን መውጣት ጥቅሙ ምን ላይ ነው?

ቤንዚን ሲወጣ የትልልቆቹ መንግሥታት የጥቅም ዓይንን ከመሳቡ፣ የአስተዳደር ሙስና ከመፍጠሩ በተጨማሪ የጥቂት ነፍሰ በላ ቱጃሮች አሻጥር እና ስውር ነፍስ ግድያን ይከተላል።

አንዲት አገር ነዳጅ ከማውጣትዋ በፊትና ካወጣች በኋላ ያላት ገጽታ ፈጽሞ የተለያየ ነው፤ ይቀየራል። ብዙዎቹ የአገሪቱ ጥቅሞች እና ወታደራዊ ተቋማት የሕግ እና የአስተዳደር ክፍሎች አቅም ባላቸው የውጭ ኃይላት ሊጠለፉ ይችላሉ።

የአገር ውስጥ ስግብግብ ቱጃሮች እና ባለሥልጣኖች ይፈለፈላሉ። ብሔራዊ ጥቅም፣ ማንነትና ባሕል ጥያቄ ውስጥ ይገባሉ። እንደዚህም ሆኖ የሕዝቦች ሕይወት እምብዛም ከፍ ላይል ይችላል። እኛስ ከዚህ ምን እንማራለን?

«ኃይል» የሚለው ርዕስ ቀላል አይደለም እጅግ ሰፊ ነው። ዋናው መነሻችን እኛ ከኃይል ጋር ማድረግ ያለብንን እርቅ በተመለከተ ሲሆን፤ ከዚህ በኋላ በሁለት ዐቢይ ጥያቄዎች ላይ አተኩረን እንነጋገራለን።

አንደኛ ከላይ የተዘረዘረው የዓለማችን ሁኔታ በኃይል ዙሪያ ምን ያስተምረናል። ሁለተኛ እኛ መውሰድ ያለብን እርምጃስ ምን መሆን አለበት የሚሉ ናቸው። ከኃይል ጋር እንታረቅ። ከዚህ በላይ በአጭሩ የተብራራው አጠቃላይ ዓለም አቀፍ የኃይል እሽቅድምድም ለእኛ የሚሰጠን ትምህርት ምንድነው?

ዋናው ዓላማችን የእኛን የኃይል ምንጭ በምን ሁኔታ እንፍታው? የሚል ሲሆን፤ ቀደም ብለን እንዳየነው ዓለም በኒኩሊየር ኃይል ከእኛ ቀድሞ ቢሮጥም በዚህ ዘመን ግን ወደ ሌሎቹ የኃይል ምንጮች መመለስ

ያስፈልጋል፤ በኒዩክለር የሚሠሩ ተቋማትን በሌሎቹ የኃይል ምንጮች መልሰው እየተኩ የኒዩክለርን የኃይል ግንባታ በእጅጉ ለመቀነስ እያቀዱ ስለሆነ በዚህ መሰክ ብዙ ተቀደምን ማለት የለብንም።

ነዳጅ ቢኖረን የፖለቲካና የማኅበራዊ ሕይወታችንን ሳያቃውስ አንዳንድ አገራት ብሔራዊ ሀብት አድርገው እንደሚጠቀሙበት አድርገን ብንጠቀም መልካም ነበር። ግን ይህንን ለማድረግ ጊዜውም አቅማችንም ላይፈቀድ ይችላል። ስለዚህ ኢትዮጵያ አላት እየተባለ በአፈ ታሪክ የሚነገረው የነዳጅ ክምችት በሕዝባችን ውስጥ ከተስፋነት ውጪ ጥቅሙ አደጋም ሊሆን እንደሚችል ልናጤን እንደሚገባ መገንዘብ አለብን። በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ ነዳጅ ለማውጣት ከቻይና ጋር ሽርክና ይዛለች። ስለዚህም የፖለቲካ ሙቀቱ ጨምሮ ይገኛል። ነዳጅ መገኘቱ ለደቀቀው መዋዕለ ንዋይ መድኀን ሊሆን ይችላል። ፀጥታችንና ሰላማችን ግን የፖለቲከኞቻችንን በሳልነትና ችሎታ ይጠይቃል። የአገር ውስጥ የጥቅም ጥያቄ እና የውጭው ዓለም የኃይል ሚዛን በሰከነ አመራር ሊስተናገድ ይገባል።

ምዕራቡም ሆነ መካከለኛው ምሥራቅ በነዳጅ ፖለቲካ የተመሰቃቀለ መሆኑ ግልጽ ነው። ታዲያ ኢትዮጵያን የመሳሰሉ አገራት በዚህ መስክ ሲነቃቁ ስሜታቸውን መለካት ያስፈልጋል በማለት የነዳጅ አምራቾቹም ሆነ ትልልቆቹ አገራት በውስጥና በውጪ ፖለቲካችን ላይ እንቅፋት መፍጠራቸው አይቀርም። የፖለቲካ መፍትሔ ይፈልጋሉ እና። ከሁሉም በላይ ይህንን የቁም ቅዠት አስወግደን በእጃችን ያለውን እንድንጠቀም ቤንዚን ቢኖርም አይጠቅምም ባይኖርም አይጎዳም በማለት ከኃይል ጋር መታረቅ ይሻላል። ቤንዚን የዓለማችንን ፖለቲካ ሸብር ውስጥ የከተተ ነው። ስለዚህ ከሁሉም በላይ የፖለቲከኞቻችንን አንድነት ይጠይቃል። አንዱ ተጠቃሚ ሌላው ተመልካች ሳይሆን የአገርን አጠቃላይ ገጽታ ይለውጥ ዘንድ የሀብት ክፍፍሉ ፍትሐዊ ከሆነ ከውጭ የሚመጣውን ተፅዕኖ በኅብረት መጋፈጥ ይቻላል። ነዳጅ የሚወጣባቸው አካባቢ ያሉ ሕዝቦች በሚገባ እንደሚጠቀሙ ማሳመን ሕይወታቸውንም መለወጥ ከተቻለ የውጭ ጣልቃ ገብነትን መቋቋም ይቻላል። ከሁሉ በላይ ግን የፖለቲካ ሰዎቻችን በኅብረት ለአንድ ዓላማ መቆም ይጠበቅባቸዋል። መካሰስ ለጠላቶቻችን ብቻ ነው የሚጠቅመው።



ስለዚህ የአንደኛው ጥያቄያችን ማጠቃለያ፤ የኒዩክለር ኃይልን ለማመንጨት አቅምም መብትም የለንም፤ ጥቅሙም አደገኛ ነው። ነዳጅ ማውጣቱም በሩቅ የተሰቀለ የተስፋ ዳቦ ነው። ዳቦውም ቢገኝ በላተኛው ሌላ ነው። ለምን?

ጆን ፓርከንስ የተባለ ጸሐፊ «የአሜሪካ ኢንፓየር ሚስጢራዊ ታሪክ» በተባለው መጽሐፉ ውስጥ የምሥራቅ አፍሪካን የከርሰ ምድር ሀብት በተመለከተ ጥልቅ ዕውቀት ያለውን (ጂኦሎጂስት) ወይም የከርሰ ምድር ጥናት ባለሙያ ጆርጅ ሪች የተባለ ምሁር የነገረውን ጠቅሶ ስለኢትዮጵያ ጥንታዊነት የተፈጥሮ ሀብቷን በተለይም ስለ ነዳጅ ክምችቷ እንዲህ ጽፏል። «ሕይወቴን ሙሉ ያሳለፍኩት በከርሰ ምድር ጥናት ነው የምነግርህ ግን ተራራ ሙሉ ቤንዚን (ዘይት) በዚህ እንዳለ ነው። እመነኝ ይህ አካባቢ በሕይወት እያለህ ሳትሞት የቤንዚን ጦርነት ቀጣና ሲሆን ታያለህ» አለኝ ብሎ ጽፏል።

ነዳጅ ቢኖረን እንደሳዑዲ እንሆን ነበር ብሎ መመኘቱን ውጉዝ ከመአርዮስ ብለን ከሕሊናችን ባናጠፋውም በአንጻሩ እኛ የነዳጅ ያለህ ስንል እነሳዑዲ የውሃ ያለህ ማለታቸውን ማስታወስ ያስፈልጋል። ስለዚህ ከሁሉ በላይ በሀይድሮ ኢነርጂ ላይ ማተኮር ይጠቅማል። በነገራችን ላይ የሳዑዲው ንጉሥ ውሃ ለማግኘት ስንቶፍር እሳት አገኘን ነው ያሉት።

በበረሃማው ሪያድ ከተሞች የተገነቡት ሆቴሎች የመዝናኛ ቦታዎች ቀዝቃዛ አየር ለመፍጠር ተብሎ ነው የእዚህ ሁሉ ነዳጅ ገንዘብ የሚፈሰው። በአሸዋ ላይ የተንጣለለውን ፎቅ ማቀዝቀዣ ወይም ውሃ ለማግኘት የሚፈሰው ገንዘብ የሚነጉደው ወደ አሜሪካ ኩባንያዎች ነው።

ዞሮ ዞሮ እነሱ በገንዘብ ሊሸምቱት ያልቻሉትን የአየር ጠባይ እኛ በጸጋ እግዚአብሔር እየተመገብነው እንገኛለን። ልብ አድርጉ እነሱ የሸመቱት አየር አርቴፊሻል ነው (ሰው ሰራሽ) ስለዚህ ይህ የተገዛ አየር ከእኛ ከተፈጥሮ አየራችን ጋር በምንም አይወዳደርም።

ስለዚህ የእኛን አየር እና ውሃ ሰጥተናቸው ሳዑዲዎች ነዳጃችሁን ስጡን ብንላቸው ለመለዋወጥ ዓይናቸውን አያሹም:: ግን የቤንዚን ሀብትም አምላክ ካደለን እንዳያጠፋን ሳንስገበገብ በብልሃት ልንጠቀምበት ይገባል:: የዚህ ሁሉ ማጠቃለያ የብዙ ብዙ ኃይል ምንጮቹ ወንዞቻችንን ይቅርታ እንድንጠይቅ ያስገድዱናል:: ሀብታም በሀብቱ ሊገዛችሁ ያልተቻለው ቀዝቃዛ እና ጣፋጭ ጣዕማችሁን እንደ ወተት የምትለግሱን ወንዞቻችን ሆይ በስንፍናም ይሁን ግራ ገብቶን ስትፈሱ ሳንጠቀምባችሁ ቀርተናል እና ይቅር በሉን ልንል ይገባናል::

ዓባይ ከአገር ወጥቶ ስንዝር ሳይሞላው ተጠልፎ ተገድቦ በውስጡ ያለው ከኒዩክለር የበለጠው ኃይሉ ሲበዘበዝ የአገሬ ሰው «ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል» እያለ በገዛ እራሱ ላይ ደግሞ ደጋግሞ ሲተርት ይሰማል::

ዓባይ፣ ተከዜ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽና ጣና ሌሎችም የጥቃቅን ወንዞች ባለቤት በሆነችው ኢትዮጵያ ከተሞቻችን የኤሌክትሪክ መብራት ማጣታቸውና በተለይ በጋዝ የሚሠራ ላምባ እየሳበች ጥቀርሻ ምጋ ጥቀርሻ መተንፈሷ ይህ ሁሉ ይቅርታ የሚፈልግ ዐብይ ጉዳይ ነው::

በውሃ የሚሠሩ ወፍጮዎች እንኳን ብርቅና ድንቅ ሆነው ለመሐላ ጥቂት መገኘታቸው ገበሬው እህል ለማስፈጨት እርሻውን ትቶ አህያ እያነዳ ከተማ ሲወጣ የሚያጠፋው ጊዜ ቢጠራቀም የኢትዮጵያን ወንዞች ሁሉ ገድቦ ለመጠቀም በበቃ ነበር:: የገበሬው የምርት ሰዓት እጅግ ውድ ነው:: ባለፈው የኮሚኒስት ሥርዓት ካድሬዎች፣ የቀበሌ ሊቀመንበሮች ሳይቀሩ በእርሻ ወቅት ስብሰባ እየጠሩ ሕዝባችንን ከድህነት በታች ወረወሩት:: አሁንም ሊታሰብበት የሚገባው ብሔራዊ የሥራ ሰዓታችንን ሳናባክን ለመጠቀም ለገበሬው የገበያ ቦታ፣ ወፍጮ እና የመሳሰሉት አስፈላጊ ሁኔታዎች ያለበት መንደር ድረስ ሊሄዱለት ያስፈልጋል:: ይህ አሁንም በባለሀብቶች ጥረት ሊከናወን የሚችል ብቻ ስለሆነ የነጻ ንግድ መርህ በዚህ መስክ ብዙ ሊጠቅመን ይችላል::



ወደ ዋናው ርዕስ ስንመለስ በኢትዮጵያ የኃይል ግንባታ ላይ የተጨበጠ ሥራ ያስፈልጋል:: ነፋሱ ውሃውና ፀሐዩ በከርሠ ምድር ያለው የሚንተገተግ ፍላት ጥቅም ላይ ሊውል ይገባዋል::

ከላይ እንደጠቀስነው በልፅገን የኒዩክለር ኃይል ባይኖረንም ወይም እንደነሳዑዲ በነዳጅ ባንሰክርም ጤናማ የተፈጥሮ የኃይል ምንጭ ሞልቶናል ብለናል:: ለመሆኑ በዚህ መስክ ሀገራችን ከመቼ ጀምራ እንቅስቃሴ ጀመረች? የኃይል ሥርጭቷ ምን ይመስላል?

ዓለም አቀፍ የኃይል ድርጅት በምሕጻረ ቃል አይ.ኤፍ.ኤ ኃይልን በተመለከተ ባቀረበው መረጃ በ2002 እኤአ ኢትዮጵያ ለሕዝቧ ያዳረሰችው የመብራት ኃይል 4.7 በመቶ ብቻ ነው ይላል:: ዘጠና በመቶ የሚሆነው ኃይል የሚገኘው ከእንጨት ነው:: ይህ ደግሞ ደኖችን ፈጽሞ እንዲጠፋ አድርጓቸዋል:: ታላላቆቹ ዛፎች በቅለው ግዙፍ ለመሆን ከ40 ዘመን በላይ ይፈልጋሉ:: ግን ከሰል ለማክሰል በአንዲት መጥረቢያ በጣም በትንሽ ደቂቃ መቀሰፋቸው እጅግ ዘግናኝ እርምጃ መሆኑን መላው ዜጋ መረዳት ካልቻለ በትክክል ከኃይል ጋር መታረቅ የሚለው ዓላማ መስተጋባት አለበት::

**ዘመናዊ የኃይል ግንባታ ለኢትዮጵያ ለምን ይጠቅማል?**

የኃይል ግንባታ ችግር ጥንተ መሠረት በኢትዮጵያ ጥልቅ ሥር ያለውና ማኅበራዊ ምጣኔ ሀብታችንንም ያወሳሰበ ጉዳይ ነው:: እጅግ ኋላቀር ካደረጉን ዐቢይ ጉዳዮች መካከልም የኃይል ጉዳይ ዋነኛው ነው:: ለምን?

እንደሚታወቀው ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ከዘመናዊ ኃይል ጋር ያላት ግንኙነት እጅግ ውስን ነው:: በአብዛኛውም በቀላሉ ሊከናወኑ የሚችሉ መፍጨትን ማረስን የመሳሰሉ አድካሚ እና ጊዜ አባካኝ ሥራዎች በሰው ጉልበት የሚከናወንበት አገር ውስጥ ነው ያለነው:: ይሁንና እናቶች በእጃቸው፤ ወንዶችም ጭምር ዘይት ለመጭመቅና ለመሸመን በአጠቃላይ ለዕደ ጥበብ ሙያ ዘመናዊ ኃይልን መጠቀማቸው ፣

ሀ. ጊዜን ይቆጥባል ፤

ለ. የሰውን ጉልበት ያሳርፋል ፤

ሐ. እጅግ የተጣጣመ ሕይወት ይመሩ ዘንድ የሕይወትን ጫናን ያቃልላል፤

መ. የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ምርት ወደ ከተሞች አልፎ ተርፎም ለዓለም በተቻለ ፍጥነት ለማቅረብ እና የገቢ ምንጭንም ለማጉልበት ይረዳል።

ከላይ የዘረዘርናቸው መሠረታዊ ውጥኖች ሊሳኩ የሚችሉት ዘመናዊ የኃይል አጠቃቀማችን ከዳበረ ብቻ ነው። ከዚህም ከፍ ሲል፤

ሀ. ውሃን ከምንጭና ከጉድጓድ ከመሳብ ጀምሮ የንጹሕ ውሃ አቅርቦትን ለማስተማመን ዘመናዊ ኃይል ተጠቃሽ ነው፤

ለ. የገጠሩን ጨለማ በብርሃን ለመለወጥ ለመብራት ዘመናዊ የኃይል መስፋፋት ቁልፍ ጉዳይ ነው።

የሴቶችን ጊዜ በአብዛኛው የሚሻማ ከእህል መፍጨት ጀምሮ የዕደ ጥበብ ሥራዎች ድረስ በቀላል ዘመናዊ ሥልጣኔ ቢታገዝ ለዕድገታችን መፋጠን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረው ነበር። ከዚህ አልፎ ተርፎ የዘመናዊ ኃይል አስፈላጊነት ሕይወትን ለማቆየት ወሳኝ የሆነበት ጊዜ ላይም ደርሰናል። በአብዛኛው ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው ገበሬ ሕዝብ እዚህ ግባ የሚባል መንገድ እንኳን በሌለበት እጅግ አስቸጋሪ ቦታ ነው የሚኖረው። እንዲህ ያለውን አስከፊ የሕይወት ውጣ ውረድ ለመቅረፍ ሊተከርባቸው ከሚገባ ዘርፎች ዋነኛው ኃይል መሆን አለበት።

ኤሌክትሪክ ያገኘው የገጠር ክፍል ገና አንድ በመቶ ብቻ በሆነበት፤ የዘመናዊ ነዳጅ (ዘይት) ሥርጭት ከዓለም አቀፍ ደረጃ ዝቅ ብሎ በሚገኝበት የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም በአብዛኛው የገጠር ክፍል አይታወቅም የሚል መደምደሚያ የያዙ ጥናቶችን ስናነብ የችግሩ ስፋት ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ መረዳት አያዳግተንም።



የድህነቱ እየመረረ መሄድ መንሥኤው የዘመናዊ ኃይል አጠቃቀማችን ነው ካልን በምን መልኩ ይህ ሁኔታ አገሪቱን ለረሃብና ለችግር ዳረገ ወደሚለው ጽንሰ ሐሳብ እንድናመራ መንገድ ይጠቁማናል። በባሕላዊው የኃይል አጠቃቀም ላይ የተደገፈችው የእኛ አገር ይህ ድጋፍ ተንሸራቶ እየከዳት መሆኑ ለሁሉ ግልጽ ነው።

በአብዛኛው የምንጠቀምበት (biomass) ዛፎችን ጨምሮ ፈጽሞ ሊያስተማምን አልቻለም። ስለዚህ በአስቸኳይ ወደ ዘመናዊው ኃይል ካልተሸጋገርን አገሪቱ በኢኮኖሚዋ ላይ አልፎ ተርፎም የዕለት ተዕለት ኑሮም ላይ አደጋ መከሠቱ አይቀሬ ነው።

ለምን? የአገሪቱ ዛፍ ተቆርጦ ባለመተካቱና የሕዝቡም ቁጥር እየጨመረ በመሔዱ የዕለት ተዕለት ኃይል አጠቃቀሙ መጠን ተዳምሮ፤ ከከብቶች የሚገኘውን ፍግ ለማገዶነት ለመጠቀም አሁንም ድርቁና የመሳሰሉት ፈታኝ ሁኔታዎች የቀንድ ከብቶችን በማሳጣታቸው የበረሃነትና የዘላንነት ጠባይ ያየለባቸውን ጨምሮ እንደቀድሞ መኖር ፈጽሞ አልተቻለም። የተፈጥሮ ሀብት መመናመኑ በኃይል አጠቃቀሙም ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል።

ዛፍ፤ ፍግና ቃርሚያን ለኃይል ፍጆታ 93.05 በመቶ አገሪቱ እንደምትጠቀም ሰባት በመቶ ብቻ በዘመናዊ ኃይል እንደምትደግፍ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ይህም በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ እንደሆነ ይታወቃል። ይህም የሕዝባችንን ድህነት ከቆመበት በታች እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ፤ በአማካይ በቀን አንድ የአሜሪካ ዶላር ወይም ከዘጠኝ ብር በታች የሚያገኘው ሕዝብ ብዛት 82 በመቶ ሲሆን፤ ከሁለት ዶላር ወይም ከ16 ብር በታች የሚያገኘው ሕዝብ ደግሞ ወደ 98.4 በመቶ እንዲሆን አድርጉታል። ደጋግመን እንዳነሳነው በብሔራዊ ደረጃ ኤሌክትሪክ ያገኘው የሕዝባችን መጠን በ2001 የተመዘገበው 18 በመቶው ሲሆን፤ ገጠሩ ከዚህ ውስጥ የሚጋራው ግን እጅግ ጥቂት ነው።

ሊተኮርበት የሚገባው የዚሁ ዘመናዊ የኃይል አጠቃቀም እጥረት ኢትዮጵያን ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ የምትገፋ አገር አድርጓታል የሚለው

ጽንስ ሃሣብ ነው:: ገበሬው በአረጁ የምርት መገልገያዎች ስለሚጠቀም የሚያመርተው ከእርሱና ከቤተሰቡ አልፎ ለሽያጭ የሚያቀርበው መጠን ጥቂት በመሆኑ በአማካኝ 80 በመቶ የሚሆነው ሕዝባችን ምርቱን ለቤተ ሰቡ ፍጆታ ያውለዋል:: የዚህ ምክንያት በዘመናዊ ኃይል ተጠቅሞ ምርቱን ከፍ ለማድረግ ከክረምቱ የዝናብ ወቅት ውጪ ማምረት ስለተ ሳነው ምርቱን ለሽያጭ ሲያቀርብ ቀርቶ ለእራሱም ፍጆታ ተቸግሮ እናየዋለን::

ይህም ሆኖ ከላይ እንደጠቀስነው የዕለት ተዕለት ኑሯችን እንኳን አስቸጋሪ እየሆነ የመጣበትን፣ ሴቶች በአድካሚ ሥራ መጠመዳቸውን በጥቂቱ መቅረፍ የሚቻልበት መንገድ የሚገኘው ጥቃቅን የሚመስሉ ግን ዐበይት ችግሮችን መፍታት ከቻልን ብቻ ነው ይላሉ በየጊዜው የቀረቡ ጥናቶች::

ለምሳሌ በየገጠሩ ያሉ ጥቂት ወፍጮዎችን ሁኔታ ብናይ ከላይ የጠቀስነውን ጥቅል ሐሳብ ሊያብራራልን ይችላል:: በቀላሉ የሚታየው የእህል ወፍጮ ኢንዱስትሪ የመስክ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት 87 በመቶ ከግብርና ውጭ ያለውን በቅጥር የሚተዳደረውን የኅብረተሰብ ክፍል ይሸፍናል:: በገጠሩ ክፍል ማሽነሪ የሚያንቀሳቅስ ብቸኛው ብዛት ያለው ክፍል መሆኑ ነው:: ወፍጮዎቹም ዘመናዊ ኃይልን (ነዳጅ፣ ናፍጣ) በመጠቀማቸው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ቀድመው ወደ ኢትዮጵያ ገጠሮች የገቡ ሥልጡን ዕቃዎች ልንላቸው ይገፋፋናል:: ምክንያቱም ሌላው ቀርቶ በመለዋወጫ እጥረት ተስነካክለው ቀሩ እንጅ በ1940ዎቹ ገደማ የገቡት የውሃ ወፍጮዎች እንደ ጅምሩ ዳብረው ቢሆን ኖሮ ዛሬ የተለዋጭ ኃይል ጥቅምና ዘዴ በኢትዮጵያ ዳብሮ በታየ ነበር:: ይህ የወፍጮ ዕቃዎችና ጥቅም አሳሳቢ በገጠሩ አካባቢ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው በሁለት ምክንያቶች ነው::

አንደኛ የገጠሩ ምርት እህል ከወፍጮ ጋር ስለሚጣመር፤ ሁለተኛ በሴቶች ትከሻ የሚፈጨው ምግብ ቤተሰብን በበቂ ሁኔታ ስለማይመክት የግድ ገጠሩ አጋዥ በመፈለጉ ነው:: ስለዚህም ይህ ኢንዱስትሪ መላውን



የአገሪቱን ገጠር ክፍል ባለማዳረሱ ገ??ተኛውን (አስፈጭውን) የኅብረተ ሰብ ክፍል ሊያረካ አልቻለም:: ይህም ሁለት ምክንያት አለው:: ዋነኛው የዘመናዊ ኃይል እጥረት ሲሆን፤ ሌላው የመለዋወጫ እና ጥገና እንዲሁም የዕቃዎቹ ጥራትና ዕድሜ ሁሉ አስተዋፅዖ ያደርጋል::

እንደዚህም ሆኖ የአገልግሎት ዋጋ በ100 ኪሎ ግራም ወይም በኩንታል ከ15 ብር በላይ ስለሚያስከፍል በምርት ጊዜ የሚጨምርበት ሁኔታ አለ በሚገባ ከተሠራበት የገጠሩን መዋዕለ ነዋይ እጅግ የሚያነቃቃ ሆኖ ተገኝቷል:: በጥቅሉ ይህ ሁሉ ሲሳይ ከዘመናዊ ኃይል እጅግ ትንሽ ትንጣት እየቀመስን ያለነው ጥቅም ነው::

የሰው ልጅ የሕይወትን ጫና በማቅለል በብዛት እና በጥራት በቀላሉ ሥራውን ሲያከናውን አገራችን ኢትዮጵያ የጨዋታው ተመልካች ሳትሆን ተዋናይ መሆን አለባት ብለን የእርቅ ሐሳባችንን እንለግሳለን::

ዘንድሮ ዘመናዊው ዓለም ምርቱን በብዛትና በጥራት ማምረቱ ተ ሳክቶለት ከዚህ አልፎ ተርፎም ለአካባቢ የአየር ብክለት ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ቀጠባ ተጨንቆ (Renewable energy sources) ተለዋጭ የኃይል ምንጮችን በተሳካ ሁኔታ ወደ መጠቀም ደረጃ ተሸጋግሯል:: ስለዚህም ሀገራችን ኢትዮጵያ ተቀድቶ የማያልቀውን የተፈጥሮ ኃይል በጥበብ አራቃ ልትጠቀምበት በቁርጠኝነት መነሳት አለባት::

### የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ዕድገት መቼ ጀመረ?

በሚደንቅ ሁኔታ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አገሮችም ሆነ ከአብዛኛው የዓለም ሕዝቦች በፊት ብርሃን ያየች አገር ናት::

ለመሆኑ በ1890 ዓ.ም. የመጀመሪያው የናፍታ ጄኔሬተር ኢትዮጵያ እንደገባ አስበነው እናውቃለን:: በ1896 ዓ.ም. ታላቁ መሪ አፄ ምኒልክ የአገሪቱን ገንዘብ ለመሥራት ሁለት ጄኔሬተር አስገብተው ነበር:: ይህ አባቶቻችን ለሥልጣኔ ዘወትር ፈጣኖች እንደነበሩ ያመላክታል:: በ1905 ዓ.ም. በአቃቂ ወንዝ ላይ የተጀመረው የኃይድሮ ፓወር ግንባታ ትንንሽ ፋብሪካዎች እንዲመሠረቱ ሁሉ ረድቷል:: ለነገሩ የመጀመሪያው

ባቡር ኢትዮጵያ ይገባ ዘንድ ጥረት ሲደረግ ጃፓንም በዚሁ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደበረች ይታወቃል። ዛሬ ጃፓን በዚህ መስክ ዓለምን ስትመራ እኩል ሥራ የጀመረችው ኢትዮጵያ ደግሞ ጭራ ሆናለች።

ልክ እንደዚሁ የሥልጣኔ አቻዎቻችን አውሮፓውያን እንተ ዋቸውና ጐረቤታችን ሱዳን አማካይ የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ አጠቃቀምዋ 63 ኪሎዋት በሰዓት ሲሆን፣ ኮትዲቯር 174 ኪሎ ዋት በሰዓት፣ ኬንያ 121 ኪሎ ዋት በሰዓት ናቸው። በሥልጣኔ ከአውሮፓ እንስተካከላለን የሚሉት በውሃ ሀብት ግን ከእኛ የማይበልጡት ደቡብ አፍሪካውያን 4000 ኪሎ ዋት በሰዓት በማግኘት በኃይል አጠቃቀም ሲፈተ ለኩ እኛ ግን 27 ኪሎ ዋት ብቻ የነፍስ ወከፍ ኤሌክትሪክ አጠቀቀም ስላለን ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች ሆነን ተገኝተናል።

የዛሬ መቶ ዓመት ገደማ የነበሩት ታላቁ መሪ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ መጪውን ትውልድ አስበው በዘመኑ በፍጥነት እያደገ የመጣውን የከተሞች ዕድገት ተከትሎ የሚከሠተውንም የኃይል ፍጆታ በማጤን በቶሎ አድጐ ለማገዶነት የሚያገለግለውን የባሕር ዛፍ ከውጪ በማስመጣት በዘመናቸው የነበረውን የኃይል ፍጆታ ጥያቄ በበቂ ሁኔታ መመለሳቸው አይዘነጋም። ይህ ነቢይነት ከዚያ ወዲህም ቀጥሎ በጥልቀት እና በጥንቃቄ ቢከናወን ኖሮ ዛሬ በዛፍ መመናመን ምክንያት የተፈጠረው የድርቅ አደጋ ደጋግሞ ባልጐሰመን ነበር። ከመቶ ዓመት በፊት ስለኢነርጂና ስለኃይል ያሰበችው ኢትዮጵያ እንደ ሐሳብዋ መራመድ የተ ሳናት ለምን ይሆን? ይህም ይቅርታን ይጠይቃል።

አንድ ስለኢትዮጵያ መሪዎች ያጠና ምሁር «የኢትዮጵያ የቀድሞ መሪዎች እንደ አውሮፓውያን መሪዎች የአካዳሚ ትምህርት ተምረው ባይራቀቁም ከቤተ ክህነቱ ያገኙት ትምህርትና ሥነ ምግባር፣ በዘመናት ውስጥ ሲተላለፍ የኖረው የአስተዳደር ልምድ ብልጥ አድርጓቸው ነበር» ብለዋል።

ታዲያ ዓፄ ቴዎድሮስ «እኛ የሚሸነፈ ወይም የካህን እጥረት የለብንም የእጅ ሙያተኛ ነው የምንፈልገው» ሲሉ፣ ዓፄ ዮሐንስም ይህን



ቃል ሲደግሙት። ዓፄ ምኒልክ በአነስተኛ ኢንዱስትሪ ሲጀምሩት፣ ዓፄ ኃ/ሥላሴ መሠረታዊ ልማቶችን ሲቀረቁሩና ከተማዎችን ሲያስፋፉ አገርን በመውደድ ኃይል ብቻ ተነድተው ነበር። ዛሬም የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ አርቀን አስበን በአገር ፍቅር መንፈስ ለሕዝባችን ሌሊትና ቀን ለመሥራት ታማኝ መንፈስ ያስፈልገናል።

ወደ ርዕሳችን ስንመለስ በ2002 እኤአ የወጣውን መረጃ አይተናል። በዚህ ዘመን አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ኋላቀር በሆነው የኃይል አጠቃቀም ዳዴ እያለች ነው ሕዝባችን ከእንጨት፣ ከኩበት ፍግ ነው የማብሰያ ኃይል የሚያገኘው። በከተማው አካባቢ ያለው ሕዝብ ብቻ የኤሌ ክትሪክ ኃይል ስለሚጠቀም ከባሕላዊ የነዳጅ (የኃይል) ምንጭ ውጭ በኤ ሌክትሪክ ኃይል የምንጠቀመው 6% ብቻ ነው።

ለምሳሌ በ2002 እኤአ ከዓለም የኃይል ውጤት ጥቅም ላይ የዋለው 10 ሜትሪክ ቶን ከነዳጅ ጋር ሲነጻጸር ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የእኛ ዞን ማለትም ከሰሐራ በታች ያሉ አገሮች በአጠቃላይ 552 ሺህ ከጠቅላላው የዓለም ድርሻ ሲጋሩ ኢትዮጵያ ከዚሁ የምትጋራው 17 ሺህ ብቻ ነበር። ግን ከ1980ዎቹ ጋር ሲነጻጸር አገራችን 66 በመቶ መሻሻል አሳይታለች። የሚያሳዝነው ግን ይህንን 17 ሺህ የኃይል ውጤት በጥቅም ላይ የዋለ ኃይል ያገኘችው ደንዋን እየቆረጠች ባገኘችው የከሰል ማገዶ ሲሆን፣ ከጂኦተርማል 22.4 Hydroelectric (በሙብራት) 138 ነበር ይላል ስለዚህ 66 በመቶ የኃይል አጠቀቀማችን አድጓል ሲባል የኤሌክትሪክ እና ሌሎች አማራጭ ቴክኖሎጂዎች አድገዋል ማለት ሳይሆን ደናችንን በሚገባ ጨፍጭፈነዋል ማለት ነው።

እኛ የኤሌክትሪክ ኃይላችንን 22.2 ብቻ ስንጠቀም ኬንያ 129.5 ግብጽ የእኛን ዓባይ ገደባ 861 በመድረስዋ ዛሬ ግብጽ ከአውሮፓ አገሮች አልተናነሰም እያለች ትገኛለች።

አፕሪል 18/2005 የወጣው የውሃ ልማት ዕድገት ግንባታን በተ መለከተ ዓለም ባንክ ባስጠናው ጥናት ላይ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ አገራት ውስጥ ያሉ ወንዞች በሙሉ ጥቅም ላይ ውለዋል። (ተገድበው ማለት

ነው) ይላል:: ታላቁ የኢንቨስትመንት መሠረቅም የውሃ ግንባታ እንደሆነ ያስምርበታል::

ስለዚህ ቀና ብለን የምናያቸው የበለፀጉ አገራት ለምሳሌ ፈረንሣይ ካላት የኃይል የተፈጥሮ ክምችት 90 በመቶ ጥቅም ላይ በማዋል፣ ኖርዌይ ካላት የተፈጥሮ የኃይል ክምችት 80 በመቶ በማበልፀግና በመጠቀም፣ አሜሪካ በዓመት የምትጠቀመውን ቻይና በ10 እጥፍ የኤሌክትሪክ ኃይል በመጠቀም የመጨረሻ የሆነችውን ኢትዮጵያን በ1000 እጥፍ በማስከንዳት ያላቸውን የኃይል ክምችት በአግባቡ ተጠ ቅመውበታል::

እርግጥ ነው በአውሮፓ የሐይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጨት ሥራ ቀደም ብሎ የተጀመረ ነው:: ከዘጠኝ ያላነሱ አገራት የካርታ አከላለል የታላላቅ ወንዞችን ተፋሰስ ተከትሎ መሆኑ አህጉሩ ከውኃ ጋር ዕድገቱ ምን ያህል የተቆራኘ እንደሆነ ያሳያል::

## ኢትዮጵያ እና ኃይል (ኢነርጂ)

የኢትዮጵያ ኢነርጂ (ኃይል) የሚለውን ርዕስ ስንጀምር ከሁሉ በፊት መነሳት የሚገባው ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ከ1890 ዓ.ም. ጀምሮ የነበረውን የኃይል ዕድገት ይሆናል::

በዚህም መሠረት በ1904 ዓ.ም. ጥይት ፋብሪካ የተከለችው ኢትዮጵያ ለዚሁ ተቋም 3 ጄኔሬተር ከማስመጣቷ ባሻገር፣ በ1919 ዓ.ም. የአቡጀዲ ጨርቅ ፋብሪካ ለመትከል 2 ጄኔሬተር የገዛችና እንዲሁም በ1920 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ባለሀብቶች የጄኔሬተር ግዥን አስፋፍተውታል።

ከዚህ በኋላ ግን በ1928 ዓ.ም. ጣሊያን ሀገራችንን ስትወር ለከተ ሞች በዲዝል (ናፍጣ) የሚሠሩ የኃይል ማመንጫዎች አመጣች:: በተለይ በ1928 ዓ.ም. መገባደጃ የኤሌክትሪክ ሥርጭትን ለማስፋፋት አንድ የጣሊያን ኩባንያ ኃላፊነት ተሰጥቶት ሽያጭ ተጀመረ::

ከዓፄ ኃይለ ሥላሴ ስደት መልስ በኋላ (የሸዋ መብራት ኃይል) የተባለው ሥራውን ተረከበ:: በ1948 ዓ.ም. በቻርተር የኢትዮጵያ



ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን በአዋጅ ተቋቋመ:: ከዚህ በኋላ በ1953 ዓ.ም. የቆቃ ኃይል ማሠራጫ፣ በ1956 ዓ.ም. ጢስ ዓባይ 1ኛ፣ በ1958 ዓ.ም. አዋሽ 2ኛ፣ በ1963 አዋሽ 3ኛ፣ በ1965 ዓ.ም. ፊንጫ የኃይል ማመንጫዎች ተገነቡ:: ንጉሡ ከ1948 ዓ.ም. ጀምሮ በኃይል ላይ ያሳዩት እንቅስቃሴ ያስመሠግናቸዋል:: ከዚያ ወዲህ ግን በኮሚኒዝም ሥርዓተ ማኅበር ማነቆ ምክንያት በ1980 ዓ.ም. መልካዋከና ብቻ ሲገነባ በዚህ መስክ እጅግ የተጐተትንበት ዘመን ነበር::

የኢትዮጵያ ኢነርጂ (ኃይል) ስንል ከሁሉ በፊት የሚጠቀሰው (የኃይል ፖሊሲ) ስለሆነ የአገራችን (የኢነርጂ ፖሊሲ) መልክ ይዞ ሥራ የጀመረው በ1940ዎቹ ዓመታት ነው ማለት ይቻላል::

በተለይ በ1950 የኤሌክትሪክ ኃይል ግንባታ በሰፊው ተጀምሮ ነበር:: በንጉሡ ዘመን የተጀመረው የኃይል ዕድገት መሠረት ያደረገው ወደፊት ከተጠቃሚው በሚመጣ ፍላጐት ላይ ሲሆን፤ ይህ ማለት በጥቅሉ መንግሥት ገንዘብ ስለሌለው በብድር የሚያገኛቸውንም ሆነ ከአገሪቱ ደካማ በጀት በመቀነስ ቀደም ብለን በጠቀስነው መሠረት ጥቂት ከተሞችን የሚያዳርስ እና ለጥቂት ፋብሪካዎች የሚውል እስከ 1959 ድረስ 92,078 ኪ.ዋት በሰዓት የሚያመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት ችለን ነበር:: ይኸውም የከተማ መብራት ሥርጭት ለዋና ዋናዎቹ ከተሞች ከአዲስ አበባ ጅማ ደብረ ብርሃን ድሬዳዋ ሲሆን፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ሥርጭቱን ለማስፋፋት የሕዝቡን ፍላጐት፣ ተሳትፎ እና የባለሀብቱንም ጥያቄ መሠ ረት ያደረገ ልማት ነበር:: በወቅቱ እየተስፋፋ የመጣው የኃይል ግንባታ የአግሮ ኢንዱስትሪውን ለማጠናከር ወሳኝ ነበረ እና በጊዜው የነበረው ጥናት እንደሚያመለክተው ከኢትዮጵያ ወንዞች የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል ክምችት 143 ቢሊዮን ኪ.ዋት በሰዓት ሲሆን፤ በሰሜናዊው የሀገራችን ክፍል የሚገኘው የዓባይ ወንዝ ከፍተኛውን መጠን ይዞ ተገኝቷ ል:: ይኸውም 24.9 ቢሊዮን ኪ.ሜጋ.ዋት በሰዓት ነው::

በወጣው የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ መሠረት የአዋሽ ወንዝ ጠለፋ እና ግድብ የቅድሚያ ቦታውን ይዞ የአገሪቱን ዋና ከተማ እና

የአካባቢውን ፋብሪካዎች ፍላጐት ለማሟላት የቆቃ የኤሌክትሪክ ሥራ በ1953 ዓ.ም. ተጠናቀቀ:: በሚቀጥለው የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ አዋሽ 2 በአጥጋቢ ሁኔታ ከፍጻሜ በመድረሱ የዕድገት ግሥጋሴው መፋጠን ጀመረ:: ይህም ወደ 126,000 ኪሎዋት ማመንጨት የሚችል ነበር:: የአዋሽ 3 በ1961 ዓ.ም. መጠናቀቅ ሲገባው ወደ 1963 ዓ.ም. ተጠግቶ ተጠ ናቀቀ::

የ3ኛው አምስት ዓመት መሪ ዕቅድ የፊንጫ 100 ሜጋ ዋት የሚያመነጨው ግድብና የኃይል ማመንጫ ግንባታ መጀመር ነበረበት:: ለዚህም 23.1 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የዓለም ባንክ አበድሮ ነበር:: ይህ ዕቅድ ሲፈፀም ኢትዮጵያ 500 ሚሊዮን ኪሎዋት ኃይል በሰዓት ታገኛ ለች:: እንዲሁም በጊዜው በዩጐዝላቪያ የተጀመረውና Electro Project በጣልያን እርዳታ የተጀመረው ሁሉ የሚያበረታታ የኃይል የግንባታ ሥራ ጅማሬ ነበር::

ታዲያ ይህ ሁሉ ጥናትና ዕቅድ ሲከናወን ብዙ ጥናቶች እንደሚስማሙበት ጅምሩ በመንግሥት ኃይል ብቻ ከግብ ይደርሳል ማለት ሳይሆን ባለሀብቶችን በማነቃቃት በኢንዱስትሪው መስክ ቢሳተፉ የኃይል እጥረቱ ስለሚቃለል የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የኤሌክትሪክ ፍላጐቱን ለማርካት ሲንቀሳቀስ እግረ መንገዱን መብራት ያላገኙ ከተሞችና ገጠር አካባቢዎች ያደርሳል በማለት ነበር:: የሆነው ሆኖ የኤሌክትሪክ ሥርጭት አቅም ማነስ በኢንዱስትሪው መስፋፋት ላይ ዓይነተኛ ተፅዕኖ ማስከተሉ በ1960 መጀመሪያ መታየት ጀምሮ ነበር:: ከእነዚህ ዓመታት በኋላ የተከተ ለው የዓመጽ እንቅስቃሴ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ወደኋላ እንዲሄድ አድርጐታል::

በጊዜው ድኃ የነበረችው ኢትዮጵያ የውጭውንም ሆነ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በከፍተኛ እንክብካቤ መያዝ ሲኖርባት ልማቱን ሊያፋጥኑ የሚችሉ ሠራተኛ ክፍሎችን ቅስም በሚሰብር ሁኔታ በተለይ የፋብሪካዎችና የገበያ ማዕከላትን በመውረሷ ለዕድገት በቁርጠኝነት የተነሳውን የኅብረተሰብ ክፍል እንዲሽመደመድ አድርጐታል::



የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ሊያነቃቁ የሚችሉ ተቋማት፣ ሆቴሎች፣ ትርፍ ቤቶች መወረስ ባለሀብቱ በዚህች ሀገር ሁለተኛ የልማትን ነገር እንዳያስብና የኢኮኖሚ ዕድገታችንም ከቆሙት በታች እንዲሆን ስላደረገው መንግሥት ብቻ ስለግድቦችም ስለሥርጭቱም ስለፋብሪካውም ማሰብ ጀመረ:: ይህ ደግሞ መደነቃቀር እንጂ ትርጉም ያለው የሥራና የዕድገት ብርሃን ማየት ዘበት ሆነ::

የምንነጋገረው ስለኃይል በመሆኑ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እና የመብራት ኃይል ተያይዘው የሚሄዱ ስለሆነ፤ መንግሥት ግድቦችን መገንባቱ የኃይል ማመንጫዎችን ማቋቋሙ በቂ ሆኖ የሥርጭቱን ሁኔታ ተጠቃሚዎች ያስፋፉታል በሚል ግንዛቤ የተቋቋመው የመብራት ኃይል፣ ፋብሪካዎችና ታላላቅ የማምረቻ ተቋማት ሲመቱ የኤሌክትሪክም ጉዳይ ከፍተኛ መሠናክል ገጠመው:: በዚህም መሠረት ገጠሩን እና ከተ ማውን ተጠቃሚ ለማድረግ የተደረገው ጅምር በአጭር ተቀጭቶ መንግሥት ብቻውን ይህንን ግዙፍ ሥራ ለመቋቋም ዳገት መቧጠጥ ጀመ ረ::

ስለዚህ ነው International Energy Agency CIEA በ2002 እኤአ ባወጣው መረጃ መሠረት የመብራት ተጠቃሚ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመቶ ሲሠላ 4.7% ብቻ ሆኖ የተገኘው:: ይህ ከ50 ዓመት በኋላ የተገኘ ዕድገት አሳፋሪ ነው ከማለት በላይ ሌላ ምን ማለት ይቻላል? ይህም የዓባይ ተፋሰስን ተከትላ የምትገኘው ሱዳንን እንኳን ማከል ስላቃተን በኃይል ዙሪያ እርቅ ያስፈልጋል ብለን እንድንነሳ ያስገድደናል:: ሱዳን 30% ሕዝቧን የመብራት ተጠቃሚ አድርጋለች::

የተለያዩ መረጃዎች በ2002 እኤአ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ 17.5% መሆኑን ሲያስረዱ አንዳንዶች ደግሞ ወደ 22.2% ያደርሱታል:: ይህም በሚሊዮን ኪሎ ዋት በሰዓት ማለት ነው:: ከሰሐራ በታች ያሉ አገራት ግብጽ 861 ሲኖራት ኢትዮጵያን በ24 ጊዜ ታጥፋታለች:: ይህ ከዓባይ የተገኘ ሲሳይ ነው::

በ2006 (1997) በተገኘው መረጃ መሠረት 13% የኢትዮጵያ ክፍል የመብራት ተጠቃሚ ሆኗል ይላል:: በቅርቡም ቀደም ብለው በተጠኑ ጥናቶች እና በተዘጋጁ ዕቅዶች መሠረት በዓባይ፣ በተክዜና በሌሎቹም ወንዞች ላይ እየተካሄደ ያለው የልማት እንቅስቃሴ ጥሩ ጅምር ነው::

በቅርቡ የተጀመረው Universal Electricity program ሁሉን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚለው ፕሮግራም አማራጭ የኃይል ግንባታን አካትቶ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ይደረግበታል ብለን እናምናለን:: በቅርቡ በተገኘው መረጃ መሠረት ደግሞ 17% የሚሆነው የአገሪቱ ክፍል ኤሌክትሪክ አግኝቷል:: መረጃው እንደሚያመለክተው ይህ አኃዝ በዓለም ደረጃ የመጨረሻው ትንሹ ነው:: የ50 ዓመት አንጋፋ የሆነው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን ኤሌክትሪክ ያዳረሰባቸው ከተሞች ብዛት ከ900 አልዘለሉም:: ከ75 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ ብርሃን ያገኘው 1 ሚሊዮን ብቻ ነው ይላል በ1999 ዓ.ም. የወጣው የ50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዩ ልዩ እትም መጽሔት::

ካለፈው ተሞክሮ በመነሳት ባለሀብቶችና ሕዝቡን ያሳተፈ የኃይል ግንባታ ትምህርቶች በሰፊው መጀመር ይኖርበታል እንላለን:: ይህም የማገዶ እንጨቶችን ማለትም ባሕር ዛፍን በፍግና በቃርሚያ እየገዛን በተወሰነ ክልል በየጣቢያው በማፍላት ቀናው ደን ሳይነካ ትንሣኤ ሰጥቶ በመንቀሳቀስና የባሕር ዛፍ መሬትን በመከለል እንክብካቤ ማድረግ ነው:: ሌሎች የኃይል ምንጮችን የመጠቀም ዝንባሌን ማዳበርም የዚህ ዘመን ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይኖርበታል::

እንዲህ ሲባል በመስኩ የተሠማሩ ድርጅቶችን፣ መንግሥታዊ ተቋማትን በተለይ ሌሊትና ቀን እየደከሙ ያሉትን ምሁራን እና ተራ ሠራተኞችንም ሁሉ የሠሩትን፣ እየሠሩ ያሉትን እጅግ በማድነቅ እንጂ ለሥራቸው ዋጋ በመንፈግ አይደለም:: እስከዚህ ድረስ የኤሌክትሪክ ኃይልን በተመለከተ የእርቅ ሐሳባችንን ለገስን፣ ለመሆኑ ሌሎች አማራጭ የኃይል ምንጮች የሉንም ወይ?



## ተለዋጭ የኃይል ምንጮች

ኢትዮጵያ ኢነርጂን (ኃይልን) ከየት ከየት ታገኛለች? ዋናው የኃይል ምንጫችን 94 በመቶ የሚገኘው ዛፎችን በመመድመድ እና በማገዶ ነው ብለናል:: ይኸውም በዓመት 17,038 ቶን ደን በመጨፍጨፍ ሲሆን፤ ይህ አኃዝ ኩበትና ፍጉን በአጠቃላይ የሚባለውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው::

የድንጋይ ከሰል ትጠቀማለች ወይ? ቢባል መልሱ አትጠቀምም፤ ድፍድፍ ቤንዚን ወይም ቤንዚን የላትም፤ የተፈጥሮ ጋዝ ትጠቀማለች ወይ ዜሮ በመቶ፤ ግን ከፍተኛ ክምችት አላት ይባላል፤ የኒዩክሌር አይታሰብም፤ ከታላላቅ ግድቦች ከሚገኝ ኃይል የሚሠራ ኤሌክትሪክ 138፤ (Biogas and liquid biomass) ዜሮ፣ ከፀሐይ የሚገኝ ኃይል 22.4፤ ከነፋስ የሚገኝ ኃይል ዜሮ፤ (Tide wave, and ocean) ማዕበሉን ውቅያኖሱን ወይም የሐይቁን እንቅስቃሴ ተጠቅሞ ኃይል ማመንጨት አዲስ ቴክኖሎጂ ስለሆነ ብዙ አገራት ገና አልተገለገሉበትም:: የሠለጠነውም ዓለም ገና እየተፈላሰፈበት ነው::

ከግድቦች የሚገኘውን የኃይል ማመንጫዎች 98 በመቶ፣ ከአማራጭ ኃይሎች ግን 2 በመቶ ብቻ ነው የሚገኘው:: ስለዚህ ልክ ዓለማችን በዚህ ዘመን ከፍተኛ ጥቅም እንዳገኘችበት ሁሉ እኛም በተለዋጭ ኃይሎች (ተለዋጭ ኃይሎች) መስክ ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅብናል::

ይህንን ከእንጨት፣ ከኤሌክትሪክ እና ከፀሐይ የሚገኘውን አነስተኛ ኃይል ለምን እየተጠቀምንበት ነው? ለፋብሪካዎች ለመንገዝ ስንጠቀም ለእርሻ ዜሮ ወይም ግብርናው ኋላቀር በመሆኑ በምንም ዓይነት የኃይል ምንጭ አይረዳም:: ይህ ማለት በበሬና በገበሬው ጉልበት ብቻ ነው ኢትዮጵያ የምትመገበው ማለት ነው:: 80 ሚሊዮን ሕዝብ በማረሻ እየተጫረች በሚገኘው ምርት እንዴት በልቶ አደረ ለሚለው ጥያቄ እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ መገበው ከማለት በስተቀር ሌላ ቋንቋ ሊኖረን አይችልም::

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ደግሞ ግብርናው ላይ የተመረኮዘ ነው። በግምት ወደ 85% የሚሆነው ሕዝብ ሕይወቱን የሚመራው በግብርና ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በግብርና ውጤቶች ነው። 60% የሚሆነው የውጪ ምንዛሬአችን (ቡናም የግብርናው አካል ነው) የሚገኘው ከግብርና ውጤቶች ነው። ግን ይህ ክፍለ ኢኮኖሚ በዘመናዊው የኃይል አጠቃቀም ላይ ያለው ድርሻ በጣም ደካማ ነው። የንግድና የሕዝባዊ አገልግሎቶች ለመኖሪያ ቤቶች ሁሉ የምናገኛት ኃይል ትካፈላለች።

ከላይ ጠቀስ አድርገን እንዳለፍነው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በኃይል ያለመታገዙን ሁኔታ ስናይ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ዘመናዊነት ጐድሎታል። ምክንያቱም በዚህ ዘርፍ ምንም ዓይነት ኃይል ኢትዮጵያ ስለማትጠቀም ነው። ለምሳሌ እርሻው በትራክተር በሰፊው ቢታገዝ የምናወጣው ነዳጅ፣ ውኃን ከምንጭ ለመጥለፍ ወይም ሰፋፊ እርሻዎችን ለማረስ፣ ውኃ የሚረጭ ዘመናዊ መሣሪያ ብንጠቀም በሌሎችም የኃይል ምንጮች ግብርናውን ብናበለጽገው ኖሮ ግብርናና ኃይልን አቀናጅተን ተ ጠቀምን ይባል ነበር። ነገር ግን ገበሬው በኋላቀር ማረሻ ስለሚያርስ የኢትዮጵያ ገበሬና ዘመናዊ የሳይንስ ዘዴ አልተነካኩም እጅግ ያሳዝናል። ስለዚህም እርቅ በዚህ መስክ ያስፈልጋል።

## የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት

ይህ ርዕስ ኃይል ሊያመነጩ የሚችሉ የተፈጥሮ ክምችቶችን ብቻ የሚያጠቃልል ነው። ነገር ግን በጥቂቱ ለማስታወስ ያህል የወርቅ፣ የፕላቲኒየም፣ ፖታሽ እና ዩራኒየም ማዕድን አላት። የድንጋይ ከሰል ለኃይል የሚጠቅሙ የተፈጥሮ ክምችቶች አሉ ይባላል። ዓይነቱ ለኃይል ሥራ ይሆን እንደሆነ መመርመር ይኖርበት ይሆናል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገች አገር ናት። ይኸውም በሀይድሮ ኃይል (ከውኃ የሚገኝ ኃይል)፣ ጂኦተርማል (ከመሬት የሚወጣ እምቅ ኃይል)፣ የተፈጥሮ ጋዝ የድንጋይ ከሰል፣ የፀሐይና የነፋስ ኃይል አላት። በተለይ ከውሃ ኃይል ብዙ ኃይል ሊገኝ እንደሚችል ይገመታል። ከላይ የተጠቀሱት የኃይል ምንጮች ግን ፈጽሞ ጥቅም ላይ ገና



አልዋሉም። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ባወጣው መረጃ መሠረት አማራጭ የኃይል ምንጮች ከአጠቃላዩ የኃይል ምርት 2 በመቶ ብቻ ናቸው። 98 በመቶ ከሀይድሮ የሚገኝ ነው።

ነገር ግን በስምጥ ሸለቆዎች አካባቢ እና ተንዳሆ ጂኦተርማል በጥናት ላይ እንዳለ በኮርፖሬሽኑ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መርሐ ግብር በሚል ርዕስ የተጻፈው ክፍል ያስረዳል። የተፈጥሮ ጋዝን ለማውጣት ለማበልፀግ ወደ 75 ሚሊዮን ዶላር የዓለም ባንክ አበድሮ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ስለዚህ ይህ ኃይል በእርግጠኛ እንዳላ መገመት ይቻላል።

በቅርብ ጊዜ በወጣው መንግሥታዊ መግለጫ (Renewable energy) ለምሳሌ ባዮማስ እና የፀሐይ (Solar) ኃይል ገና እየተጠኑ ስለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

ጥቂት ኢንቨስተሮች የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትን፣ ማከፋፈልን ወይም ማስተዳደርን (መቆጣጠር) ከመንግሥት ለመግዛት ወይም ወደ ግል ሀብትነት ለመለወጥ እንደተነሳሱ መግለጫው ይጠቁማል። ግን እስከዚህ ዘመን ድረስ ይህ ዘርፍ በመንግሥት ተይዞ ይገኛል።

የአዳዲስ መስመሮች መዘርጋት፣ ከአራት የበለጡትን የመጥለፍ፣ የመገደብ እና የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ የሚያበረታታ ነው። ሌሎች አራት ደግሞ እየተጠኑ ነው። የሠለጠነ የሰው ኃይልና የገንዘብ አቅም የሚጠይቁ ጥቂት በቀላሉ ልናከናውናቸው የምንችላቸው በእጃችን ያሉ አማራጭ የኃይል ምንጮችን መጠቀም ብልህነት ነው።

## አማራጭ የኃይል ምንጮች

በዚህ ዘመን ሌላው ቀርቶ ከከብቶች እርድ በኋላ የሚተርፈው ተረፈ ምርት እንኳን በሠለጠነው ዓለም አይጣልም። በስዊድን አገር የምትገኘው ናንኮፒክ የተባለች ከተማ አንድ ባቡር 67 አውቶቡስ 80 ታክሲዎች የሚጠቀሙበት ነዳጅ ከዚህ ተረፈ ምርት የሚገኝ መሆኑ ተረጋግጧል።

ሜታፌዩል የተባለው ከከብቶች ተረፈ ምርት የሚመረት ነዳጅ ነው። ይህ ባዮጋዝ ከቤት ውስጥ መጠቀሚያ ተርፎ የከተማውን መጓጓዣ ሲደግፍ የእኛ ተማራማሪዎች ከዚህ ዓይነቱ የሳይንስ ፋሚ ለአገራቸው ምን ያበረክቱ ይሆን ብለን የእርቅ መንፈስ እናቀርባለን።

ቀደም ብለን ያነሳነው የፀሐይ ኃይል ለአገራችን ታላቅ አስተዋፅዖ የሚያበረክት ምንጭ ነው። በዚህ ዘርፍ የሠለጠነችው ቻይና ምን ሠርታለች? የነዳጅ አጠቃቀምን ለመገደብ ወይም ላለመጠቀም ወይም በሌሎች ኃይሎች ለመለወጥ ትኩረት ማድረግ በሚቀጥሉት አሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ ከሚተኮርባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ቀዳሚው ነው የምትለው ቻይና ሶላር ኢነርጂ በፀሐይ ኃይል አጠቃቀም በመራቀቅ ከዓለም ዋነኛውን ቦታ ይዛ ትገኛለች።

በሕዝቦቿ ብዛት ምክንያት የዓለምን ኃይል የምታገበሰብሰው ቻይና የኤሌክትሪክ ኃይል የሚገኝበትን ዘዴ ሁሉ በመብራት እያፈላለገች ነው። ቻይና በኢንዱስትሪ (በፋብሪካ) ዓለምን በመምራት ላይ ትገኛለች። በዚህ ምክንያት የአካባቢው አየር በእጅጉ ተበክሏል። በዓለም የአየር ብክለት ጥናት መሠረት በተለይ በሦስት የቻይና ከተሞች ሕዝብ ጥቀርሻ ነው የሚምገው። በዚህ እና በተለያየ ምክንያት ቻይና ከፍተኛ የኃይል ነዳጅ ጥማት አለባት።

ከሃያ ዓመታት በፊት ከኤሽያ ከፍተኛ የነዳጅ አምራች አገር ቻይና ነበረች። በአሁኑ ወቅት ግን እራሷ የምታወጣው ነዳጅ አልበቃ ብሏት ከአፍሪካ፣ ከላቲን አሜሪካና ከመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ አምራቾች ጋር መልካም የፖለቲካ ወዳጅነት መሥርታለች። ለምሳሌ ናይጀሪያ የባቡር ሐዲድ ለመዘርጋት መዋዋሏ፤ ለኢራን የጦር መሣሪያ መስገሷ፤ ከላቲን አሜሪካ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መፍጠሯ ለዚሁ ነዳጅ ሲባል ነው። ቻይና በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሌለውን ትልቅ ሐይድሮ ኤሌክትሪክ ዳምፕ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ የወንዝ ግድብ ገንብታ ጨርሳለች። የተፈጥሮ ከሰል ማምረቻዋንም በከፍተኛ ሁኔታ አጠናክራዋለች። የኒዩክለር ማመንጫ ፋብሪካዎቿንም እጅግ አሳድጋቸዋለች።



ይህ ሁሉ ሆኖ ግን የቻይና የኃይል ጥማት አልረካም። ሌላ ኃይል ትፈልጋለች ስለዚህም አገሪቱ አዲስ አማራጭ የኃይል ምንጭ ሕግ ቀርጻለች። አገሪቱ በቀረፀችው በአዲሱ ከብክለት ነጻ የሚያደርግ ተተኪ የኃይል ማመንጫ ሕግ ታላቅ ጥቅም አግኝታበታለች። ይህ ኃይል ከነፋስ፣ ከውኃና ከፀሐይ የሚገኝ ኃይል ነው። የቻይና አማራጭ የኃይል ምንጮች ባለሥልጣን «እኛ ሁሉንም ዓይነት የኃይል ማመንጫ ዘዴ በዚህ ጊዜ እንፈልጋለን። ነዳጅ፣ ኒዩክለር፣ የድንጋይ ከሰል፣ የተፈጥሮ ኃይልን ምንጭ ነገር ግን ለዘለቄታው ልንጠቀምበት የምንፈልገው ከተፈጥሮ የሚገኘውን ማለትም የነፋሱን የውኃንና የፀሐዩን ጤናማ ኃይል ነው። ምክንያቱም ለአየር ብክለት ስለማይዳርግ አደጋም ስለሌለው ነው።» ነው አባባላቸው።

ስለዚህ በዚህ ጊዜ ቻይና ነፋሱን፣ ውኃውንና ፀሐዩን ወደ ኃይል ለመለወጥ 5.5 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር ወጪ አድርጋለች። ይኸውም መላው ዓለም 30 ቢሊየን ዶላር ካወጣው ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ቻይና በዚህ ዘርፍ የተነደፈ ሕግ ሲኖራት፤ ታላቋ ልዕለ ኃያል አሜሪካ ግን ይህንን ዘርፍ የሚመለከት ምንም ዓይነት ሕግ ገና አላወጣችም።

የፀሐይ ሙቀት ማጠራቀሚያ ሞተሮች በቻይና ከተሞች ወይም ገጠሮች በየቤቱ ጣሪያ ተሰቅለው እየታዩ ነው። ይህ ማለት የሚሞቁና የሚበስሉ ምግቦች በፀሐይ ሙቀት እየተዘጋጁ ነው። ከዚህ በኋላ የኤሌክትሪክ ኃይል የለም፤ የመታጠቢያ ቤት ውሃ ለማሞቅ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ሲፈስ የሚኖረውን የፀሐይ ሙቀት መጠቀም ብቻ ነው። የሚገርመው ይህ መሣሪያ የፀሐይን ሙቀት ማከማቸቱና እየቆጠበ አገልግሎት መስጠቱ ነው። የዚህ ማሽን ፈልሳፊ ፋብሪካ ይህንን አዲስ ግኝት ለመሸጥ ሲያቀርብ 200 ዶላር ብቻ መጠየቁ ለሕዝቡ እንዴት ሕይወትን እንዳቀለለለት መገመት ይቻላል።

የከተማው ሲገርመን የቻይና ገበሬዎች በየመንደሩ በነፋስ ኃይል የሚሠሩ ረጃጅም ማማዎችን ተክለው ሲጠቀሙ ስናይ ይህች ቻይና ምን

ጉደኛ አገር ነች ማለታችን አይቀርም። ነገሮች ተራቀው ዛሬ በአማራጭ ኃይሎች (ተተኪ ኃይሎች) መጠቀም ልምድ ሆኗል። እንዲያውም በ2008 በቻይና ለሚደረገው የኦሎምፒክ ዝግጅት ቤጂንግ ስቴዲየም 130 ኪሎ ዋት የሚያወጣ ሶላር ኢነርጂ በፀሐይ ኃይል የሚሠራ ሰንተች ፓወር ተገ ጥሞለታል። የቻይና የዚሁ ኳስ ሜዳ መኪና ማቆሚያ 20 በመቶ መብራቱን የሚያገኘው ከነፋስ ከሚገኘው ኃይል ነው። ዛሬ እጅግ ገጠራማ በሆኑ ቦታዎች የቻይና መንግሥት የነፋስና የፀሐይ ኃይልን እየተጠቀመ መብራት በመብራት አድርጓቸዋል።

ስለዚህ ቻይና ይህንን የሚያህል የሕዝብ ብዛት ተሸክማ በኃይል ማመንጫዎች መስክ ከአሜሪካ እና ከመላው አውሮፓ ሥልጣኔና ዕድገት ብዙም አልራቀችም። ምን ይህ ብቻ በእነዚሁ ኃይሎች በፀሐይና በነፋስ የሚሠሩ መሣሪያዎችን እያመረተች ለዓለም እየሸጠች ነው። በዓለም ላይ ይህችን አገር የምትከተል ሕንድ ነች።

ይህን ሁሉ ተአምር ካየን በኋላ ወደ ሀገራችን እንመለስ። የቻይና ሕዝብ ከደረሰበት ለመድረስ ምን የሚያዳግተን ነገር አለ? የተማረ ሰው ማነስ ነውን? ባይገርማችሁ አሜሪካ በኢትዮጵያውያን ኢንጂነሮች ተጥለ ቅልቃለች የገንዘብ እጥረት ነውን? እንደኛ ሀብታም ማን አለ፤ ከልብ በኅብ ረት ማሰብ ከቻልን። ምንድን ነው ችግራችን? ይህ ጉዳይ በእጅጉ እርቅ ይፈልጋል።

የተፈጥሮ ሀብት አለን። የሰው ኃይል አለን። የተማረ የሰው ኃይል አለን። ታዲያ በጥንካሬ ብንሠራ ምን የሚያቅተን ነገር ይኖራል? ቻይናውያን እኮ በጥንካሬ ሠርተው ነው ሀገራቸውን ያለሙት። ወገኖቼ ጊዜ እያለፈብን ነው ፀብና ጭቅጭቁን የፖለቲካውን ግርግር ትተን ለሥራ እንሰለፍ። ከኃይል ጋር እንታረቅ።

ከላይ እንደጠቃቀስነው በኃይል ዙሪያ የተፈጥሮን ኃይል በመግራት ብንጠቀም ዕድገታችንና ያልተበከለ ተፈጥሮ ተመጣጥነው ስለሚጓዙ አየሩም ጤነኛ ይሆናል። ስለዚህ ከሁሉ በላይ ወንዞቻችንንና ነፋሱን ተለዋጭ የኃይል ግንባታ ላይ ለማዋል ማተኮር ይጠበቅብናል፤



ለዚህም ገንዘብ ያስፈልገናል፤ አዎ በእርግጥ ያስፈልጋል፤ ይህንን ቀዳዳ ለመድፈን ባለሀብቶች ቡና ቤት ብቻ ከሚያስፋፉ በዚህ መስክ ይሠማሩ ዘንድ ፖሊሲው፣ ትምህርቱ፣ ቅስቀሳው መጠናከር ይኖርበታል። የሁሉም ነገር ግልጽ፣ ቀልጣፋ እና ታማኝ ከሆን ባለሀብቱ ይሳተፋል ውጤቱም ያምራል። በውጪ ያሉ ዜጐች በዕውቀትና በገንዘብ ይረባረቡ ዘንድ ተነሳሽነቱ እና መተማመኑ መንገድ ሊይዝ ይገባዋል። ተወያ ይተንና ተማምነን ችግሮቻችንን በይቅርታ መፍታት በእውነት ያለ ሐሰት ለጋራ ጥቅማችን መስማማት ይኖርብናል።

ቤንዚኑም ሲወጣ መላው ዜጋ ቤንዚናችን ይል ዘንድ ግልጽነትና ተጠቃሚነት ሊያስተሳስረን ይገባል። እንደናይጄሪያ ጥቂት ስግብግቦች የሚያግበሰብሱት ከሆነ ግን አስፈሪ ወደመሆን ያዘነብላል። ስለዚህ ዘንድሮ እንደ ዶ/ር ጁሊየስ ኔሬሬ ስናርስ እርሻችን፣ ስንወቃ እህላችን፣ ቤንዚን ሲወጣ ቤንዚናችን እያልን በኅብረት ልናድግ ይገባል።

በኃይል ዙሪያ አገር አቀፍ የውይይት መድረኮች ትምህርት ያስፈልጋል። ሕዝባችን በንቃት ይሳተፍና ባለቤት ሆኖ ይቆረቆር ዘንድ፣ ከመንግሥትም ጋር ይተባበር ዘንድ ዕውቀት ያስፈልገዋል።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ከዓላማ ጋር መታረቅ

ዓላማ ራዕይ ነው። ብዙ ግለሰቦች በተለያየ ዓላማ ይመሰጡ እና ለቆሙለት ዓላማ ብለው መሥዋዕት ሲሆኑ ይታያሉ። በግል የቆምንበት ዓላማ ምን ይመስላል? ከሁሉ በላይ ክፉ ነው ደግ ነው? ጥበብ የጐደለው ነው ወይ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ማንም ዓላማ ያለው ሰው በክፉ ሰዎች አይሰናከልም በመልካም ሕሊና የሚመራ ሰው ድካም አያውቀውም። ጠንካራና ንቁ ነው። ስለዚህ ከዓላማ ጋር መታረቅ ይገባናል።በዚህ ዘመን ብዙ ጊዜ ተሸ ናፊዎች ሆነን ተገኝተናል። በኢኮኖሚ ተሸንፈናል፤ ተባብሮ በመሥራት ተሸ ንፈናል፤ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል ደጋግመን የምናሸንፈው እግር ኳስ እንኳን አራት እና ከዚያም በላይ እየቃምን በቅሌት ከሜዳ እንድንባረር አድርጐናል።

ሌላው ቀርቶ የእኛን ዓላማ አይተው እኛን ተከትለው ነጻ የወጡ አገራት ሳይቀሩ ወደኋላ እያዩን ነው። ይህ ከዓላማ ጋር ያለመታረቅ ውጤት ነው። የሕይወት ቃል ኪዳን ከሌለን ራዕያችን ዘወትር ይሸነፋል፤ ያፍራል። ለመሆኑ የእኛ ራዕይ ምን ይመስላል? በተለያዩ መንገዶች ቃል ኪዳን የገባንለት ነገር ቢኖርም ከሁሉ በላይ ግን ማኅበራዊ ጤንነታችን ራዕይ እንዲኖረው ያስፈልጋል። የት ነው መድረስ የምንፈልገው? ዛሬ ሁሉ ነገር እኛ እንደምንጠብቀው የተንቀራፈፈ አይደለም። የሰው ልጅ ዛሬ ዘመናቱን አርጌው ዓለም እና አዲሱ ዓለም ብሎ ከፍሏቸዋል።

የጊዜው ፍጥነትና የመራቀቁ ሁኔታ ብዙ አገሮችን አደናግሯቸዋል። ያልታሰቡ አገራት በብርሃን ፍጥነት ወደፊት እየተፈተለኩ ነው። እንደኛ ዓይነቱ ደግሞ በብርሃን ፍጥነት ወደኋላ እየተምዘገዘገ ነው። ኮሎምበስ የተባለው አገር አቅኝ አሜሪካንን ካገኘበት ከዛሬ 300 ዓመት ወዲህ የሰው ልጅ ርቀት ከሚገመተው በላይ ነው። በስፔይኑ ንጉሥ ፍሬዴሪክ እና ንግሥት አዝቢላ ሕሊና የነበረው ራዕይ ኮሎምበስ አዲሱን ዓለም ለመፈለግ ዓለምን ከዞረ በኋላ ተለውጧል።

የሬነሰንስ የፈረንሣይ ነውጽ፣ የእንግሊዝ ወረራ፣ የናፖሊዮን ሩጫ፣ የሒትለር ሰይጣናዊ ሥራ፣ የሞሶሎኒ ትዕቢትና የሊግ ኦፍ ኔሽን መፍረስ፣ የተባበሩት መንግሥታት መመሥረትና የአምስቱ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት ያላቸው አገራት ዕድገት፣ የሰባቱ ልዕለ ኃያላን ማሶትም ባለሰባት እራሱ ቀይ ዘንዶ ራዕይ ምንድነው ብለን ስንመረምር አንዳንዴም አስደንጋጭ ወይንም አስደሳች ሌላ ጊዜ ደግሞ ባዶ እየሆነ ስንገለባበጥ መኖራችን የዓለማችንን ሂደት ያመለክታል።

የአዲሶቹ የኤሺያን ታይገርስ ቻይናና እና ጃፓን ራዕይ፤ የኮሚኒዝም ጠንካራ እጅ መሽመድመድ፤ የበርሊን ግንብ መናድ የፈጠረው በምሥራቅና በምዕራብ በኩል ያለው የመተያያ መስኮት፤ ደቡብ አፍሪካ ነጻ ትሆን ዘንድ አፓርታይድ መውደቁ የፈጠረው ዕድል ወይም አጋጣሚ ሊባል ይችላል።



የእነቢንላደን ሰይጣናዊ ራዕይ፤ የአክራሪ እስላም መነሳሳት፤ የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ የኢራቅ፣ የኢራን፣ የአፍጋኒስታን ጉዞ እጅግ በተፋጠነ በተካለበ ሁኔታ ተደራርቦ መምጣቱ የዓለማችን ራዕይ ምን ይመስላል ብለን እንድንጨነቅ ያደርገናል። በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ የእኛ ጉዞ ምንድነው? ከየት ወዴት እየሄድን ነው? ብለን ከዓላማችን ጋር መታረቅ አለብን።

ማንም እንደሚያምነው ታሪክ አለን። ይህንን ሊያስክደን የሚመጣ ኃይል ከዓላማችን ውጭ ነው። እና የሕሊና ዝምድና ልንሰጠው ያቅተናል፤ ማንነታችንን ሊያድበሰብስ ወይም ሊያጉድፍ የሚከጅል ሁሉ ከሁሉ በፊት ስለእኛ ያላወቀ ወይም አውቆ ላይቀበል የፈለገ ሊሆን ይችላል። አሜሪካኖች እነዋሽንግተንን፣ አብርሃም ሊንከንን፣ ማርቲን ሉተር ኪንግን ሲነኩባቸው አይወዱም። ሕንዶች ማኅተማ ጋንዲን፤ አውሮፓውያን ናፖልዮንን፤ ጣልያኖች ጋሪባልዲን። ሁሉም የገዛ ማንነቱን ታሪኬ ብሎ በዓላማ ይጠብቃል ይከተላል። እኛም ቀዳማዊ ምኒሊክን፣ ፋሲለደስን፣ ይኩኖአምላክን፣ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖትን፣ ቴዎድሮስን፣ ዮሐንስን፣ እምዬ ምኒሊክን፣ ጉበናን፣ ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስን፣ ባልቻ አባ ነፍሶን፣ ጣይቱ ብጡልን፣ ኃይለ ሥላሴን ቢነኩብን አንወድም።

የታሪክ ሰዎችም ቢሆኑ ከራሳቸው የጥላቻ አቅጣጫ እየተወረወሩ አባቶቻችንን ጥላሸት ሊቀቡ አይገባም። ለዚህ ትውልዱ ሊቆረቆር ይገባዋል። እኛ ቀን የጐደለብን ቀድሞ ሳይሆን አሁን ነው። አውሮፓውያን ቅርስ አላቸው ወይ? እኛም አለን። ታሪክ አላቸው ወይ? እኛም አለን። አባት አላቸው ወይ? እኛም አለን። ሃይማኖት አላቸው ወይ? እኛም አለን። ዕድሜ ለአባቶቻችን ምንጊዜም ነጻ የሆነ የልቡና ግዛትና አገር ሰጥተውን አልፈዋል። ይህ ለታሪካዊ ጠላቶቻችን እሬት ነው ለእኛ ግን ክብራችን ነው።

ማንም በጤናማ አእምሮው ቢያስበው ዓፄ ምኒልክ አሁን ያለችውን አገር በተቻለ መጠን ባያስተላልፉልን በዚህ ዘመን አገር፣ ነፃነትና ማንነት አልባ ብሎም የተበታተነ ሕዝብ ነበር የምንሆነው።

ስለዚህ እነሱ የጀመሩትን አንድነት ከግብ ለማድረስ ዓለማችን ጽኑ ሆኖ ከዕውነት ጋር መታረቅ አለብን።

ይህ ዓላማ በቀላሉ ሊሟላ ሊደላደል ፈጽሞ አይችልም። በሳ-ልነት፣ ቆራጥነትና ትዕግሥተኝነትን ሁሉ ይጠይቃል። እኛ ዓላማችን ማደግ እንደሆነ ሁሉ ካለጥርጥር ሊያፈርሱን ዓላማ ያላቸው እንዳሉ ማመን ያስፈልጋል። ስለዚህ እንደብልጦቹ አባቶቻችን በእርጋታና በብልሃት እራሳችንን መከላከል ይኖርብናል። ይህም ለቤተሰባችን፣ ለመንደራችን፣ ለከተማችንና ለአገራችን ጥቅም ሲባል ነው።

ለሚቀጥለው ትውልድ የሚሆን ቅሪት፣ ታሪክና ጥበብ ካላቆየን መወቀሳችን የግድ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመሣፍንት ዘመን እየተባለ የሚጠራው ጊዜ ጨለማ የነበረና ምንም ዓይነት ታሪካዊ ክንውኖች እንዳልተፈጸሙበት ይታወቃል። ይህ ማለት ከዓላማ ጋር ያልታ ረቁ ገዥዎች የነበሩበት ዘመን ነበር ማለት ነው። በእኛ ዘመንስ የጥበብ ዓላማ አለን ወይ? አገርን የመከላከልና የመጠበቅ ዓላማ አለን ወይ? ለቤተ ሰባችንና፣ ለአካባቢያችን፣ ለወረዳው፣ ለአውራጃውና ለአገሪቱ ያለን ራዕይ ምንድነው?

በመንደራችን ለሚሠሩ ወንጀሎች ያለን መቆርቆር ሕፃናቱ በሥነ ምግባር በትምህርት እንዲያብቡ ኃላፊነትን መውሰድ ይጠበቅብናል። ምንድነው ዓላማችን? ለሚቀጥለው ትውልድ የምናቆየው ደካማ ኢኮኖሚና የተበታተነች አገር ነውን? የባሕር በር ያላት ጠንካራ፣ በመፈራትና በመከበር እንዲሁም በፍቅር ከጎረቤቶችዋ ጋር በስምምነት የምትኖር አገር መፍጠር መሆን አለበት ዓላማችን።

የሀገርን ክብር፣ ድንበር እና ጥቅም ሸጦ ከጎረቤቶች ጋር ሰላም መፍጠር አይቻልም፤ የውስጥንም እምቅ ቁጭት እልህና ንዴት መገደብ ያስፈልጋል። ለባሰ የትውልድ ፀብ የሚዳርገው ለጊዜው በሩጫ የታ ሠረ ወይም የታጠቅነው መቀነት ብጤ ነገር ነው። የእኛ ሀገር ከየት እስከየት ነች? የቱ በግፍ ተወሰደብን? የሚለውን ጥያቄ በይደር አቆይቶ ማለፍ ከዓላማ ጋር መታረቅ አይደለም። ከታሪክና ከእውነት አንጻር



ለትውልድ የእኛ የቱ ነው ብለን ችግርን እንደውርስ ላለማስተላለፍ ዓላማችን ጽኑ መሆን አለበት። ዓለም ሁሉ የሌለውን ድንበር ሲያሰፋ እኛ ታሪክም ዓለምም ያወቀልንን ድንበር በቸልታ ለሌሎች መሸለማችን የውስጥ ረመጥ ሆኖ ይቆያል። ዛሬን በኃይል ቢሻገር የነገው ትውልድ ግን በቸልታ አያልፈውም፤ ስለዚህ ዛሬውኑ ከዓላማችን ጋር በመታረቅ የኢትዮጵያን ጥቅም ማስከበር ይጠበቅብናል፤ ከዓላማ ጋር እንታረቅ።

## ምዕራፍ አሥራ ስምንት

## ከትምህርት ጋር መታረቅ

የሰው ልጅ የኑሮ ውጣ ውረዱን ለማቅለል በብዙ ዘመናት ውስጥ ያጠራቀመውን ዕውቀት፣ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያዳበረና እያሳደገ ለዛሬው የብልፅግናና የሥልጣኔ ዓለም አብቅቶታል።

ሰው ከትምህርት ጋር ያደረገው እርቅ ለዚህ በጥበብ ላጌጠ የሳይንስ ዘመን ለመድረስ አስችሎታል። ብዙ ጊዜ መመራመርና መራቀቅ ደረጃውን ከጠበቀ አልፎ ተርፎ የሰው ልጅ ከባሕርዩ ውጪ የሆነውን መለኮታዊ ኩነት አይጋፋ እንጂ የባሕሩ ጥልቀት፣ ጠፈሩ (ዩኒቨርስ) የምድር ከርሥ ሳይቀር በሰው ልጅ ይመረመር ዘንድ ተፈቅዷል።

የሥነ ከዋክብት ጥናቱን፣ የክረምቱን መፀውን፣ ሐጋይና ፀደይን እንሰፍርበት ዘንድ የሰጠን ጥንቱን ከዛሬ እንድንለይበት ሲሆን፤ ከዚያም በላይ የዘንድሮውን ከሰማይ ያለውን ድንቅ ኪነ ጥበብ ለማየትና ለማወቅ ደረጃ በደረጃ የተጠራቀመው የትምህርት ሂደት ዛሬ ከሚታሰበውና ከሚገመተው በላይ ተራቋል።

ርዕሳችን ከትምህርት ጋር መታረቅ ነው። ከሁሉ አስቀድመን እኛና ትምህርት ምን ዓይነት ዝምድና ነበረን በሚለው ርእስ ከተወያየን በኋላ ዛሬስ ምን ይዘት ላይ ነን ወደሚለው ሐሳብ እናመራለን።

## እኛና ትምህርት

ኢትዮጵያ እንደታላላቆቹ የጥበብ ዓለማት የራስዋ ሥርዓተ ትምህርት ያላት መሆንዋ እርግጥ ነው። ይህ ጥንታዊ ትምህርት በአብዛኛው ከቤተ ክርስቲያን ጋር የተያያዘ ነበር። ቤተ ክርስቲያን አጸድዋን ት/ቤት፣ ካህናቷን መምህራን አድርጋ እስከዚህ ዘመን በትምህርት ተቋምነት ስታገለግል ቆይታለች። እጅግ በጣም የሚደንቀው ትምህርቱ መሠረቱን ጠብቆ በደረጃ የሚሄድ ነበረ። ለምሳሌ ከፊደል ገበታ፣ አቡጊዳ፣ (ፊደል ሐዋርያ) ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ ዕውቀቶች፣ ከሕፃንነት እስከ ውርዝውና በቀጥታ የሚንቆረቆሩ የዕውቀት ጠሎች ሲያረሰርሱን ኖረዋል። በኢትዮጵያ መልካም የአየር ሁኔታ በመታገዝ የዋርካዎቹ ጥላ ሳይቀሩ ዩኒቨርስቲዎች ሆነው አገልግለዋል። ሕዝባችንም ያለውን ቁራሽ በመቸር ተማሪዎችን ደግፏል።

ይህ እጅግ ጥልቅ የሆነ የትምህርት መሠረት የሚያጠቃልላቸው ብዙ ቁም ነገሮች ነበሩ። ሥነ ምግባርን፣ ፍቅርን እና ታዛዥነትን በአንድ አጣምሮ የያዘ፣ ሕፃናትን በጥሩ ሥነ ምግባር የሚቀርጽ ሥርዓተ ትምህርት ነበረን።

ትምህርት ባሕላችን ነበረ፤ እንኳን ትምህርት ቤት በየመንደሩ ያለው የአረጋውያን ዕውቀት ስሜት የሚነካ እንደነበረ የታወቀ ነው። ከትምህርት ጋር እንታረቅ ስንልም የጥንቱን ሳንንቅ አዲሱንም ሳንተው ሁለቱንም አዛምደን እንያዝ ማለታችን ነው።

ለመሆኑ ጥንታዊው የኢትዮጵያ ትምህርት ምን ይመስላል? የትኛውም ሕዝብ ከፋም ለማም የራሱ የሥልጣኔ የትምህርት ክበብ አለው። ፋይዳው ከፋም ይሁን ደግ ጥበብ ያለውም ይሁን የሌላው ግን የሕዝቦች አኗኗር ከትምህርት ተለይቶ አያውቅም።

የጥንት ግብጾች በኪነ ሕንፃ ሥራ ተራቀው ሕዋውን በሥነ ኮከብ ትምህርት ዳሰው ይኖሩ እንደነበር ግልጽ ነው። ግሪኮች በዴሞክራሲ ፈላስፋነታቸው በአጠቃላይም በጥልቅ ትምህርታቸው የታወቁ በዩኒቨርስቲ ደረጃ በጥንት ዘመን የሚያስመርቁ ነበሩ። ዐረቦች በሂሣብ ትምህርት



ቀደምት ናቸው። እንደዚሁም የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በዓለማችን ከፍ ብሎ የሚታይ እንደነበር የታሪክ መዛግብትን፣ የአርኪዎሎጂ ግኝትንና በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የሠፈረውን በማገናበብ መረዳት ይቻላል።

ካለጥርጥር ኢትዮጵያ ከትምህርት ጋር የታረቀች ሀገር ነበረች። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በሚኒያፖሊስ ከተማ ኖቬምበር 4/2006 የስዕል ኤግዚቢሽን አሳይቶ ነበር። ታዲያ ከስዕል ኤግዚቢሽኑ ጋር ተጣምሮ የቀረበው ከዩኒቨርስቲ በውሰት የመጣ የኢትዮጵያ ፋብሪክ ጨርቅ ነበር። ጉዳዩ እንዲህ ነው የተለያየ ውስብስብ ሐረጋት እና ቀለማት ያሏቸው በርካታ ቁርጥራጭ ልብሶች በትንንሽ ፍሬም ተካተው በመስታወት የተከበበ ማስጉብኛ ውስጥ ይታዩ ነበር። ቁም ነገሩ እነዚህ ከ10 የበለጡ ፍሬሞች የሚናገሩት ጥበብ ነው። ይህም የእነዚህ የልብስ ዲዛይኖች ከዛሬ 1600 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያውያን ይሠሩባቸው የነበሩ የክብር አልባሳት ሲሆኑ፤ ጥያቄው እንዲህ ዓይነት የዲዛይን ጥራት ያላቸው ፋብሪክ ጨርቆች በዛ ዘመን ኢትዮጵያውያን ያመርቱ ነበር ወይ? የሚል ነው። እነዚህ ለኤግዚቢት ከአገራቸው የተሰደዱ ቁርጥራጭ ፍሬሞች የሚናገሩት ኢትዮጵያ ራሷን የቻለ የአልባሳት ማምረቻ ኢንዱስትሪ የነበራት ሀገር እንደነበረች ነው።

ልብ በሉ በብዛትና በጥራት አልባሳትን ማምረት የሚያስችል ጥበብ ያለው ሕዝብ ሌላ ያልተመዘገበ ጥበብ ያጣል ተብሎ ይገመታል። የልብሱ ጥበብ ተጓዳኝ ሌሎች ትምህርቶች እንዳሉት ይናገራል። ለምሳሌ የሚቀልሙ ቀለማት የመፍጠር፣ ልብሱን በረቂቅ ዲዛይን የማስዋብ ትምህርትና ሌሎችም የመሳሰሉት ይገኙበታል። በዚህ ባለንበት ዘመን እንደ አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ ያሉ ሊቃውንት በሀገር በቀል ዲዛይን አልባሳቱን በማንቆጥቆጥ የእኛን ጥበብ እያበለፀጉት ይገኛሉ።

በነገራችን ላይ አሜሪካ ውስጥ በሚኒሶታ ግዛት በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ፈቃድ በየገዳማቱ ያሉ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ማይክሮፊልም ተነሥተው ተጠርዘውና ተዘጋጅተው ይገኛሉ። ቁጥራቸውም ከ20 ሺህ በላይ ነው። የሚያስደንቀው እኚህ መንፈሳዊ

አባት አርቀው በማሰብ ድንገት መጻሕፍቱ ቢሠረቁ፣ ቢቃጠሉ፣ ቢደመሰሱ ለትውልድ የሚቀር ቅርስ ስለምናጣ፣ እጅግ በሚገርም ዕውቀት የተሞሉትን የብራና መጻሕፍት በዘመናዊው ጥበብ ይቀረፁ ዘንድ እዚሁ ሴንት ክላውድ ዩኒቨርስቲ መጥተው በማነጋገር የሠሩት ታላቅ ሥራ አርቆ አሳቢነታቸውን ከመግለጹ ሌላ ዛሬ ምንም እንደዋናው መጽሐፍም ባይሆን በታላቅ ጥበብ የተቀረፀውን ማይክሮ ፊልም ለማግኘት ተችሏል፡፡

ታዲያ ቅዱስ አባታችን እንደተጠራጠሩት በዚህ ዘመን መጻሕፍቱ ከግራኝ መሐመድ ጥፋት ባልተናነሰ መልኩ በእሳት ሲቃጠሉና ሲሠረቁ በመታየታቸው እውነትም ይህ የሩቁን የሚያሳይ ዕውቀታቸው መንፈሳዊ ብቃትም ነበረው እንድንል ያደርገናል፡፡ ግን የሚገርመው የገዛ መጻሕፍቶቻችንን በጥንቃቄ መያዝ ተስኖን ዛሬ ማይክሮ ፊልሙን ለማግኘት ወደ ፈረንጆች እጃችንን ዘርግተን ተገኝተናል፡፡ ይህም የተገኘው ለትውልድ በሚጨነቁ አባቶች ጥረት ነው፡፡

መጽሐፍ ማለት ዕውቀት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ዕውቀት የጥንቱ በግዕዙ ውስጥ ነው ያለው፡፡ የዚህ ዘመኑ ዘመናዊው ደግሞ እንግሊዝኛ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ግዕዙን መተርጐም የሚችሉ ምሁራን እያለቁ እየመነመኑ በመሄዳቸው ከእንግሊዝኛ ወይም ከሌሎች ቋንቋዎች ዘመናዊውን ጥበብ ይተረጉሙ ዘንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለትምህርት ወደ ውጪ የላካቸው ተማሪዎች ደግሞ የውሃ ሽታ ወይም የቁራ መልዕክተኛ ሆነው በመቅረታቸው ዛሬ ትውልዱ ከጥንቱም ሆነ ከዛሬው ዕውቀት ሳይሆን ግራ የገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የጥንቱን ሳያውቀው የናቀ ትውልድ የዛሬውን ሳያውቀው የናፈቀ ሆኖ ግን ጥበብ የሌላቸው ፋሽኖችን ሲያግበሰብስ ዕድሜውን እየጨረሰ ነው፡፡ ለእዚህ ነው ከዕውቀት ከትምህርት ጋር መታረቅ አለብን የምንለው፡፡

ትምህርታችን አይናበብም ሁሉም የኮምፒውተር ሳይንስ ወይም ነርሲንግ ነው የሚማረው፡፡ ስለዚህ በኅብረት ለመሥራት ፈጽሞ አልቻልንም፤ እንዲህ ሲባል ሞያውን ለማቃለል ሳይሆን በየሞያው መመረቅ አለብን ለማለት ነው፡፡



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ታላቁ ሥራቸው ወጣቶችን ወደ ውጪ ልኮ ዘመናዊውን ጥበብ እንዲቀስሙ ማድረግ ነበር፡፡ በትክክልም የቤት ሥራቸው ሰው መፍጠር ነበር፡፡ በትምህርት የበለፀገ ትውልድ መቅረጽ ለሥልጣኔ ሁሉ ቁልፍ መሆኑን የተረዱት እኚህ መሪ ብዙ ወጣቶችን ወደ አሜሪካና ወደ አውሮፓ ከላኩ በኋላ በአሜሪካ ውስጥ የተማሪዎች ማኅበር አቋቁመው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ምክንያታቸውም ወሳኝ እና እጅግ ቁልፍ ነበር፡፡ ይኸውም የተለያየ ሙያ ያጠኑ ወጣቶች በአንድ ተሰብስበው ሙያቸውን ወክለው እንዲወያዩና እንዲማከሩ፣ ለአገራቸውም የተጣራ ዕውቀት ያላቸው የሥልጣኔ ቁልፍ መጻሕፍትን እንዲጽፉ ነበር፡፡ ይህ በዘመኑ የነበሩ ጃፓንን የመሳሰሉ አገራት በሰፊው ይጠቀሙት የነበረ ዘዴ ነው፡፡

ሁልጊዜ የሰው ቋንቋ እያመለከ መኖር የማይፈልገው የምሥራቁ ዓለም ዋናው ሥራ ጥበባትን እየተሻሙ በራስ ቋንቋ መተርጐም ነው ብሎም ያምናል፡፡

ታዲያ የኢትዮጵያ ዕድል አሥር በመቶ ቢሳካም ከተላከው ወጣት ግን ዘጠና በመቶው የተላከበትን ቁልፍ ሐሳብ ትቶ ባልተመረቀበት ሙያ ሁሉም ፖለቲከኛ መሆን ስላማረው ለዚያውም ኮሚኒስትነት በጊዜው ፋሽን ሆኖ የነበረውን ፋኖነት ሳይቸግረው እየሳበ ወደ ኢትዮጵያ አስገባ፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ከገበሬዎችዋና ከድኃዋ ኢትዮጵያ መቀነት የሰበሰበችውን ገንዘብ ከፍላ ያስተማረችው ወጣት ትምህርቱን ትቶ የሽብር ትምህርት ለመቅሰም ወደ ጠላቶቻችን ጉያ እየገባ መወሸቅ ጀመረ፡፡ ውጤቱም ዛሬ የምናየውን ሆነ፡፡ ይህ ዓይነት ስህተት የሚከሰተው ከዕውቀት ጉድለት ነው፡፡ ይኸውም ከአገር በቀሉ ትምህርት የተቆራረጠው ዘመነኛው ትውልድ ዕውቀት አብዮት እስኪመስለው የተደናበረበት ምክንያት መሆኑ ነው፡፡

### የኢትዮጵያ ዕውቀት

ከፊደሉ ጀምሮ ያለው ጥልቅ ፍልስፍና እና አመክንዮ ያለው ትምህርት ያላት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ነች፡፡ በዓለማችን የራሳቸው ፊደል

ያላቸው አገራት ከአሥር አይበልጡም፤ እነዚህም የቻይናው እንደ ስዕል የተቆላለፈ በቀላሉ የማይለመድ፣ እንግሊዝኛው ሲጻፍ ማንም ፍጹም እስፔሊንግ አስተካክላለሁ የሚል አናባቢውንና ተናባቢውን አጣምሮ መጻፍ የማይችልበት፣ አንድን ድምጽ በሁለት ፊደላት በመጻፍ ብዙ ቦታ የሚፈጅበት ሲሆን፤ የኢትዮጵያ የግዕዙን ፊደላት እንከተል ብንል 26 ፊደላት የግዕዝ ዲቃሎቹን ብንጨምር 30 የአማርኛ ፊደሎቹ 6 የአማርኛው ዲቃላ 2 ብቻ ያሉት ሲሆን፤ አናባቢን ከተናባቢ ጋር ደምሮ ከማደናገር አናባቢውን ሊተካ የሚችል ምልክት ድምጽ ሰጪዎቹን በመደመር ማባዛት ይቻላል:: ይኸውም ግዕዙን፣ ካዕቡን፣ ሣልሱን፣ ራብዑን፣ ሐምሱን፣ ሳድሱን፣ ሳብዑን ለመለየት ነው:: ስለዚህ የሠለጠነው ዓለም ቋንቋ ከእኛ ፊደል የበለጠ በቀላሉ ሊጻፍ ይችላል ብሎ ማመን እጅግ ስህተት ነው::

የኢትዮጵያ ዕውቀት ከፊደል ጀምሮ በቁጥር ስልት ወደ ሂሣብ ትምህርት ይገባል:: የቁም ጽሑፍ (የጽሕፈት ትምህርት)፣ የሥነ ፍጥረት፣ የሃይማኖት፣ የግብረ ገብ፣ የቃል፣ የዜማ፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ፣ የታሪክ፣ የሕግ ትምህርትና ፍልስፍና ከዚህ ሁሉ በኋላ እጅግ ሊመረመር የሚገባው የባሕረ ሐሳብ ቀመር፣ ሐሳበ ዐውድ፣ አበቅቴ፣ መጥቅዕ .. ወዘተ እያለ ለወሮች፣ ለዓመታት፣ ለቀናት፣ ለሰዓታት መሥፈሪያ ያበጀና እስከ ሥነ ከዋክብት ጥናት የሚደርሰው የትምህርት ዓይነት ነው:: የባሕረ ሐሳብ ዓላማ ቅሉ የአጽዋማትና የበዓላትን ስፍር ለመለካት ቢሆንም ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያ የራስዋ የዘመን አቆጣጠር እንዲኖራት አድርጓታል:: ሥነ ስዕሉ ኪነ ሕንፃው ሁሉ የትምህርት ውጤት ነው::

ልብ ብለን ወደ ኢትዮጵያዊው ትምህርት ስንመለከት የደረጀ፣ የተማከለና የተሳካ ወጥነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ማንነት ያለው ሕዝብ፣ ግርማ ያለው ሕዝብ ይሆን ዘንድ የእኛ ትምህርት በጣም ጠቅሞናል:: ለመሆኑ በምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያ መጻሕፍት ልዩ ክብር የተሰጣቸው ለምን ይሆን ብለን ስንጠይቅ፤ መልሱ አዋቂዎች ስለሆኑ ነው:: መጻሕፍቱ ብዙ ጥበብ ሸክፈው ስለያዙ በእርጅና ብዛት እንዳይወድቁ



ምርኩዝ ተበጅቶላቸው ሲገለጡ በላብ እንዳይበላሹ በጓንት ወይም በልዩ መቆንጠጫ ይገለጡ ዘንድ የጀርመን፣ የሮማ፣ የአሜሪካ ሙዚየሞች ተጠንቅቀው ሲንከባከቧቸው እናያለን:: ምክንያቱም በጥበብ የተራቀቀው ዓለም ጠቢባኑን መጻሕፍት ስለለያቸው ነው::

ለመውቀስ ሳይሆን የእኛ ምሁራን በዚህ ዘመን ከዚህ የጥበብ ውሃ ያልቀመሱ በመሆናቸው ከባዕዱ ሕዝብ የበለጠ ባዕድ ሆነው ተገኝተዋል:: በዚህም ምክንያት ለመጻሕፍቱ ማለትም ለኢትዮጵያዊው ዕውቀት አንዳንዱ ጠላትም ሲሆኑ ይታያሉ:: ጥላቻ የሌላቸው ደግሞ እጅግ ቸልተኛ ሆነው የትውልዱን የማንነት ሀብት ሲያዘርፉ ይታያሉ::

ትምህርት የቻይናዎቹ ባሕላዊ መድኃኒት ውጤት ነው:: ማንነቱን የማይንቀው ቻይናዊ ዶክተር በመርፌ የሰውን አካል እየጠቀጠቀ ሲፈውስ ዓለም ጥበቡን በአድናቆት ነው ያየው፡ የእኛ የባሕል መድኃኒት ቀማሚዎች ግን አንድም ቀን ከቁም ነገር ተቆጥረው ከዕፅዋት የቀመሙት መድኃኒት ምንነት በተመለከተ መጽሐፍ የጻፈ ዶክተር የለንም::

ከመነሻው ኢትዮጵያ የራስዋ የጥበብ መንገድ ያላት አገር ናት ብለናል:: ስለዚህም እስከዚህ ዘመን ያዳበረችው የሕክምና ጥበብ ይኖራታል:: አጉል እምነቱን ከዋናው የመድኃኒት ቅመማ ለይቶና ተመራምሮ ባለውጤት የሆነ ምሁር የለንም:: ይህ የመጣው የገዛ ሕዝብን ከመናቅና ማንነትን ከመርሳት ክፉ መንፈስ ነው::

ሌላው ቀርቶ አባቶቻችን በየሙያቸወ ያዳበሩትን መጻሕፍት መጻፍን እንኳን ዘመናዊው ምሁር ሲያዘወትረው አይታይም:: በየገዳማቱ በቃላቸው ያጠኑትን ጉልቆ መሳፍርት የሌለውን ዕውቀት በብራና ሲገለብጡ የኖሩትን አባቶች በዚህ ዘመን ያለን እኛ መናቅ የምንችልበት አቅም የለንም:: እነገዘከረ ነገርን የመሳሰለ የኢትዮጵያን ባሕላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ ዕውቀት በ903 ገጽ የጻፈውን ፀሐፌ ትዕዛዝ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀልን ቀና ብለን ማየት የሚቻለን በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን ረቂቅ ብስለት ካየን በኋላ ይሆናል:: የእነተክለ ጻድቅ መኩሪያ የታሪክ መጻሕፍት የሚያስተምሩን ከጥንታዊው የኢትዮጵያ

ትምህርት የተቀዳው የዕውቀት ወንዝ ጥራትንና ብዛትን ነው፡፡ መዝገበ ቃላት የተጻፈበት የዕውቀት መሥፈሪያ ሚዛን በዚህ ዘመን አለ ለማለት ይቸግራል፡፡

ስለዚህ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ዘመናዊ ምሁር ከልጅነቱ መሠረታዊውንና አገርኛውን ትምህርት ቢማር ኖሮ የኢትዮጵያ ገጽ እንደ ዘንድሮ አይሆንም ነበር ይላል የእርቅ ሐሳብ፡፡ አብዛኛው ምሁር ለአገሩ ዜማ ባዕድ፣ ለአገሩ ቅኔ ባይተዋር፣ የገዛ ሕዝቡን ታሪክ የሚያንቋሽሽና የማያውቀውን ዓለም የሚናፍቅ እንዴ ኢምፔሪያሊስት፣ አንዴ ሶሻሊስት እየሆነ የሚገለባበጥ ከመሠረቱ የተነቀለ ስለሆነ ነው፡፡

የነገይቱን ኢትዮጵያ ለመገንባት የሕዝቡን ባሕል እና ማንነት መሠረት ያደረገ ባለቅኔ፣ ሳይንቲስት፣ የድጓ መምህርና ኢንጂነር ምሁር ለመፍጠር ኢትዮጵያ ወደ ማንነትዋ መመለስ አለባት፡፡ ይህ ነው እውነተኛው ከትምህርት ጋር የመታፈቅ መንፈስ፡፡ እንደማንኛውም ሕዝብ ለበሽታዎቻችን የሕክምና ጥበብ አለን፡፡ ጥንቆላንና የመድኃኒት ቅማመን ደባልቀን በክፉ ዓይን የምናየው ሥራ ከአጉል እምነት ተነጥሎ ከየቅጠሉ ተቀምሞ የሚፈውሰውን መድኃኒት በምርምር ለማበልፀግ የተ ማሩ ኬሚስቶች ሊያገለግሉን ስለሚችሉ ወደ ሕዝቡ ልማድ ጠልቀው እንዲገቡ ያስፈልጋል፡፡ የጥንቱ ኢትዮጵያዊ የመድኃኒት ጥበብ ከክፉ እምነት ጋር መዛመዱና ክፉ መሆኑ ከታወቀ ከዚህ እሥር ቤት ይፈታ ዘንድ ዘመናዊው ሰው ሥራ ሊሠራ ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም ዕፀዋቱን በዓይነት ለይቶ ቤተ ሙከራ አስገብቶ ዓይነታቸውንና መጠናቸውን ለፍሮ ጥቅም ላይ በማዋል ነው፡፡

የሀገራችን ወጌሾች የዶክትሬት ማዕረግ የላቸውም እንጂ እያንዳንዱን ብልት በስም ለይተው ምትሀት በሚመስል መልክ የተሰበ ረውንና የወለቀውን አጥንት ካለቀዶ ጥገና ሲገጣጥሙት ለተመለከተ የእነዚህ ሰዎች ጥበብ ቢጻፍ ምን ያህል ገጽ ምን ዓይነት ጥበብስ በተገኘ በት ያሰኛል፡፡ በነገራችን ላይ ማንኛውም የምናየው መድኃኒትና የሕክምና ጥበብ በዘመናት ከዳበረው የሰው ልጅ ልምድ የተቀዳ ነው፡፡



ማንኛውም ሳይንቲስት በአንድ ጊዜ ታላቅ የምርምር ደረጃ ላይ አልደረሰም፤ ለምሳሌ የበረራ ታሪክ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ሰፊ ታሪ ክ ካላቸው ነገሮች አንዱ ነው፡፡ በዚህ ሙስክ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረገው በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ሊዮናርዶ ዳቬንቺ ለ500 ዓመታት የዳበ ረው የተለያዩ ፈጠራዎች ጥርቅምም ነው፡፡ ዲሴምበር 13/1903 ኦልቪል እና ዊልቡር በተባሉት ወንድማማቾች የመጀመሪያ በረራ ያደርጉ ዘንድ ያበቃቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ለዚህ የበቁት የጥንቱን ሳይንቁ በማጥናታቸው ነው፡፡

በስልክ ጥበብ ላይ በርቀት ከሚጣሩ ገበሬዎች ጀምሮ እስከ 1876 ዓ.ም. ድረስ እጅግ የዳበረ ሙከራ ነው ለዛሬው የሳተላይት ዘመን ማለትም እጃችን ላይ ለምትገኝ ሽቦ አልባ ረቂቅ ስልክ ያደረሰን፡፡ ማንኛውም ብልጥ ምሁር አባቶችን መሠረት ሳያደርግ አይነሳም፡፡

በዘመናችን ያሉ አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች ጥንታዊውን የታሪክ መጽሐፍ አይዲያሊስት ነው፤ ግነት የበዛበት ነው ብለው ስንክሳሩን፣ ክብረ ነገሥቱን አሽቀንጥረው ጥለውታል፡፡ በተለይ ኮሚ ኒስቶቹ የኢትዮጵያ ታሪክ ሳይንሳዊ አይደለም ይላሉ፡፡ ግን ኮሚኒስቶቹ አገራት ታሪካቸውን ንቀው አያውቁም፡፡

ብዙ ጊዜ በአገራችን ኢትዮጵያ ሪቮሊዩሽን (አብዮት ወይም ለውጥ) ተካሂዷል ተብሎ ሲነገር ይሰማል፡፡ እርግጥ ነው በ1967 ዓ.ም. በቀድሞው አስተዳደር የነበሩ ባለሥልጣናት ከታች እስከላይ ተለውጠዋል፡፡ ከሪቮሊዩሽን ጋር ዝምድና የሌላቸው የጭካኔ እና የዘረፋ ሥራዎች ግን ያለፍርሃትና ያለሐፍረት ተከናውነዋል፡፡

ግን የዚህ የለውጥ አብዮት መሠረታዊ ሐሳብ ምንድነው? ከሁሉ በፊት ሪቮሊዩሽን የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ይተረጉም ዘንድ የተመ ረጠው ቃል አብዮት ከግዕዙ አበየ፣ ዐመፀ፣ እምቢአለ፣ አልገዛም፣ አሻፈ ረኝ አለ የሚለው ቃል ይተካው ዘንድ ሲመረጥ የቃሉ ጥቅል ሐሳብ በአንድ ነጠላ ትርጉም የተጨፈለቀ ይመስላል፡፡ ልብ አድርጉ ሙሪ ቃል አድርገን የምንጠቀምባቸው ቃላት አገርን ሊገድሉ ወይም ሊያድኑ

ይችላሉ:: ላለፉት 30 ዓመታት መመሪያ ያደረግነው አብዮት ዐመፀ የሚለውን ትርጉም የሚያቀነቅን ከሆነ እውነትም የሪቮሊዩሽን ትርጉም ተዛብቷል ማለት ነው::

የለውጥ ወይም አብዮት ጥንተ ነገር ከእንግሊዝ ጀምሮ ፈረንሣይ ላይ አድጐ አሜሪካንን ያበለፀገ፣ ሶቪየት ኅብረትን ግን የገደለ ቃል መሆኑን መገንዘብ ይገባል:: ለቻይናዎች ብርሃን ሆኖ አገልግሏል::

እውነትም አብዮት መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ሐሳብ ነው:: ችግሩ በቀልና አብዮት በተቀላቀሉባቸው ቦታዎች ሁሉ የተጣመመ ትርጉም ስለነበረው ብዙ አገራትን ሲያከስር ተገኝቷል:: አብዮት ዐመጽ አይደለም፤ እንደሱ ከሆነ አብዮትና ሪቮሊዩሽን ፈጽሞ አይገናኙም ሁልጊዜ ቃላት ከውጭ አገር ስንሸምት በተርጓሚው ስሜት እየተመሰጥን እንጂ የቃሉ ባለቤቶች ይህንን ቃል የተጠቀሙበት በተለየ መንገድ ነው::

ልብ ብለን የእንግሊዝን ሪቮሊዩሽን (አብዮት) ስንመለከት የኢንዱስትሪ ሪቮሊዩሽን (አብዮት) የባሕል ሪቮሊዩሽን ሆኖ እናገኘዋለን:: የጽንሰ ሐሳብ ለውጥ፣ የሥራ ለውጥ፣ የአኗኗር ለውጥ እንጂ የሰው ለውጥ አይደለም:: ሪቮሊዩሽን በዕድሜ የገፉ ሽማግሌዎችን መግደል አይደለም:: ይልቁንም በዕድሜ ብዛት ያከማቹትን ዕውቀት በሰከነ ኅሊና መቅዳት፣ ያለምቀኝነት ያለፈውን ጥሩ የታሪክ ጉዞ ከዛሬው መልካም አስተሳሰብ ጋር ማገናኘት ነው::

የዛሬዋ አሜሪካ የሪቮሊዩሽን ውጤት ነች ስንል፤ የዛሬዋ ኢትዮጵያንና አሜሪካንን ማስተያየት ብቻ የቱ ጋ እንደተሳሳትን ሊያስረዳን ይችላል:: ታዲያ ይህ ሪቮሊዩሽን ከትምህርት ጋር በምን ይገናኛል? ብለን ስንጠይቅ በብዙ ዘርፍ የሚል መልስ እናገኛለን::

ቻይናዎቹ እንዳደረጉት የባሕል ሪቮሊዩሽን ለማካሄድ በሀገራችንም ተሞክሯል:: የእኛ አካሄድ ግን የጥፋት ሆኖ ለዚህ አብቅቶናል:: ምን ማለት ነው? ቻይናዎቹ የሕዝቡን ባሕል በከፍተኛ ጥናት የሚጠቀመውን ከማይጠቀመው ሲለዩ ነው የከረሙት:: እኛ ግን አዋቂውንም፣ መጻሕፍቱንም ስንረሽን ነው የከረምነው:: ስለዚህ ከጥንት



ሲያያዝ የመጣው ግሩም ባሕል አሸንፎ ባይወጣ ኖሮ ዛሬ እኛነታችን ፈጽሞ ባልተገኘ ነበር:: የመከራ ቀን ለተመረጡት ሲባል ያጥራል እንደተባለው ይህ የአብዮት የአመጽ ዘመን ካላጠረ ኋላቀር አገር፣ ሰላም እና ፍቅር አልባ ሕዝብ እንዳንሆን ያስፈራል::

ለውጥ ወይም አብዮት (ሪቮሊዩሽን) አስፈላጊ ነው፤ ግን የቃሉ ትርጉም ከትምህርት ጋር ከተያያዘ ብቻ እንጂ ከአመጽ ጋር ዝምድና ካለው ጉጂ ነው::

ለውጡ ትምህርት መሆን ይኖርበታል:: በእርጋታ እንዳይሰበር እንዳይሸረፍ ተንከባክበው የሚይዙት የዕውቀት ዕድገት ነው:: አብዮት ማለት ግን ማዕበል ነው፤ እሳት ነው፤ ሰደድ ነው ስንል ከርመናል እውነትም በእነዚህ አውዳሚ የተፈጥሮ ኃይላት የተመሰለ አብዮት ጥፋቱ ምን ያህል ይሆን?

ይህ ሰደድ ያጨናገፈው የቀረጠው ሁለት ድልድዮችን ነው:: አንደኛው የኅብረተሰቡን የደረጃ ተከታታይነት ያለው የሶሻል እንቅስቃሴ፤ ሁለተኛ በአመዛኙ የትምህርትን የዕውቀትን ስፋትና በአራቱም ማዕዘን የማሰብ ወይም ዲያሚንሽናል ርዕዮቱን ነው:: ስለዚህም ለውጥንና ነፍስ ግድያን አይተንና ለይተን ማወቅ እስኪሳነን ድረስ የጋሪ ፈረስ አድርጎናል:: አብዮት አዙሮ ለማየት የምንችልበትን አንገት የቀረጠ አደጋ ነው፤ አደጋውም በአመዛኙ ከትምህርት ጋር የተያያዘ ነው::

የታሪክ መንገዶችን ሶሻሊስታዊ አብዮታዊ የታሪክ ጥናት (Soialist, realist, historians) የሥነ ጥበብ መንገዶችንም እንደዚሁ ከራሺያ የተቀዳ (Socialist, realist) አስተዳደራችን ሶሻሊስት፣ የልማት ፖሊሲው ሥርዓተ ትምህርት ሁሉ አዙረው የማያስቡ ይሆኑ ዘንድ ስለተፈረደባቸው ነው::

ከአብዮቱ በፊት የነበሩት የታሪክ ፀሐፊዎች እንደ አሮጌ ቁና ሲጣሉ ማየት የተለመደ ሆኖ ነበር:: የሥነ ጥበብ ፈላስፋዎቹ እነገብረ ክርስቶስ ደስታ፣ እነአፈወርቅ ተክሌ ሌሎቹም ሌሎቹም ያዳበሩት የሥነ ጥበብ

መንገድ በመፌክርና በእነሌኒን ስዕል ተተክቶ ነበር:: አንባቢው የአብዮት ውጤት ምን ዓይነት ዝቅጠት መሆኑን እዚህ ላይ መረዳት ይቻላል::

እስከዚህ ዘመን ድረስ የብዙ ዘመናውያን ሕሊና ከአብዮት አልጸዳም ዛሬም ፋኖነት የዕውቀት መለኪያ ሆኗል:: ግን በዚህ ዘመን የዓለምን ለውጥ ያጣጣሙ ምሁራን በእርጋታ የአገሪቱን የለውጥ እንቅስቃሴ ለማከም ሲሯሯጡ እናያቸዋለን:: በብረት ሳይሆን በአስተሳሰብ ብልጫ የምናምንበት የዕውቀት ደረጃ ላይ ለመድረስ ወሳኙ በገዛ መሠረት ላይ ፀንቶ መቆም ብቻ ነው::

ከላይ እንደጠቀስነው ከመሐይም እስከ ዶክተሩ፤ ወታደርና ተማሪ ያጥለቀለቀው የአመጽ እርምጃ ጥበብን ከመጨፍለቅ በስተቀር ከውጤት ስለማያደርስ ረጋ ብለን እናስብ ዘንድ ትምህርት ያስፈልገናል::

ይህ ትምህርት የጥንቱንም የዛሬውንም የያዘ ይሆን ዘንድ በጥንቃቄ መቀረጽ አለበት:: አንድ ሕፃን የአገሩን ቋንቋ ሰዋስው እስከነአገባቡ ቅኔውንና ጥንታዊውን ግዕዝ ሊማር ይገባዋል:: የአያቶቹን የእነቅዱስ ያሬድን፣ የእነአባ ጊዮርጊስ ዜማ ሊያጠና ይገባል:: ለምን አይማርም? ፈረንጅ የአያቱን የሞዛርትን፣ የቤትሆቨንን ኦፔራ ካጠና እና ይህ ትክክል ከሆነ፤ እኛ የቅዱስ ያሬድን ድጓ፣ ዝማሬና መዋሥዕት የአቋቋም ትምህርት ልጆቻችንን ማስተማራችን ስህተቱ የቱ ላይ ነው? ሪቮሊዩሽን ማለት ይህ ነው:: የባሕል ተሐድሶ፤ የሞተውን ማንሳት፤ ያንቀላፋውን መቀስቀስ ትንሣኤ መስጠት:: እንዲህ ከሆነ ባለቅኔዎቹ እነዮፍታሔ፣ እነፀጋዬ፣ እነ መንግሥቱ ለማ ከመቃብር ይነሳሉ:: እነዚህ ሁሉ ባለቅኔዎች ጥንታዊውን ትምህርት የተመረኮዙ ናቸው:: እስቲ አስቡት የእነዚህን ሰዎች ታላቅነት ከሁለቱም ዓለም ያጣቀሱ በመሆናቸው ለዘመናዊው ትውልድ እንደአብነት ሊቆጠሩ ይችላሉ::

**የመረጃ እርቅ ወይም የመገናኛ ብዙኃን እርቅ**



በኃይለኛው የቴክኖሎጂ ኃይል የሚገፋው ይህ ዓለም ወደ አንዲት መንደርነት እየተለወጠ መምጣቱን ለማስተዋል ብዙም አስቸጋሪ አይደለም ብለን ደጋግመን ተነጋግረናል::

በልጅነታችን አያቶቻችን በመጨረሻው ዘመን ምድር ትጠባለች ሲሉ ትዝ ይለናል:: የዚህ አባባል ትርጉም ግን እያደር እውነት እየሆነ የሚመጣው በሰው ልጅ የፈጠራ ኃይል ነው:: ልክ ነው ይህ የዓለም መሰብሰብ በቴክኖሎጂው ርቀት መሆን አለበት::

በዚህ በሀገራችን እንኳን ከደብረ ዘይት አዲስ አበባ ለመግባት ምን ያህል ሰዓት ይፈጅ እንደበር ግልጽ ነው:: ዛሬ ሊምንቺና ከአዲስ አበባ ደሴ መግባትና በፈጣኑ አውሮፕላን ከለንደን ኒውዮርክ መግባት ሊገናኝ የማይችል የሰዓት ልዩነት ፈጥረዋል:: በተለይ ከአዲሱ ዓለም መገኘት ጀምሮ የታየው ዕድገት ፈጣንና አስደናቂም ነው:: ይህ ለውጥ የኢንፎርሜሽን ለውጥ ነው::

በ1492 ኮሎምበስ ጠንካራውን የንግድ ልውውጥ በመርከብ ሲጀምር አዲሱን ዓለም ከአሮጌው ዓለም ጋር አገናኘው:: ከስድስት አህጉራት ሌላ ሰባት አህጉር መገኘቱን ያበሰረው ይህ ጉዞ የዓለምን ዙሪያ ክብነትም አረጋግጧል:: እንደ ቶማስ ሊፍሬድማን አጠራር እስከ 1800 ድረስ የነበረው ዘመን ግሎባላይዜሽን አንድ ይባላል:: ይህም ትልቁን ዓለም ወደ መካከለኛነት ያወረደ ነው:: ግልጽ ለማድረግ ጉዞው የነበረውን የግንኙነት ክብደት በመካከለኛ ደረጃ ላይ ያደረሰ በመርከብ ጉዞ ከአውሮፓ፣ አሜሪካ መንዝ እየተራቀቀ እየተፋጠነ የመጣበት ነው፤ ንግዱም ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች ናቸው::

ሁለተኛው ብርሃን መታየት የጀመረው ከ1800 እስከ 2000 ድረስ ያለው ነው:: ይኸውም ከታላቁ የአሜሪካ የችግር ዘመን፣ የአንደኛው ዓለም ጦርነትና ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ክስተትና ውጤት ነው:: ይህ ዘመን ዓለምን ከመካከለኛነት ወደ ጠባብ አውርዷታል:: ይህም በተከታታይ እጅግ ብዙ ፈጠራ የታየበት ዘመን ሲሆን፤ የብሮድካስት ዕድገት በ1920 በአንድ ሺህ ሰው መጠን ከደረሰ ወዲህ እጅግ በፍጥነት በማደጉና በተ

ለይም አዶልፍ ሒትለር የተባለው የጀርመን ጨካኝ መሪ የመገናኛ ብዙኃንን ጠቃሚነት በከፍተኛ ሁኔታ በመረዳቱ በተቀረፁ ቴፖች ለመጀመሪያ ጊዜ የቅስቀሳ ንግግሮችን እያደረገ በፕሮፓጋንዳ ብቻ ዓለምን ቀውጢ በማድረጉ ምንም ድርጊቱ ክፉ ቢሆንም በመስኩ ግን ከፍተኛ ዕድገትን አሳይቷል።

ከዚያ በፊትም በ1918 የባይነሪ ኮምፒውተር መወለድ፣ በጣም በትንሽ ደቂቃ የሂሣብ ስሌቶችን ማስብና ውጤቱንም መናገር መቻል ለዛሬው ግዙፍ የኮምፒውተር ኢንፎርሜሽን አብቅቶናል።

የእስፒስክራፍት መፈልሰፍ በ1946 ዓ.ም. አሜሪካ እና ሶቪየት ኅብረት በጥምረት በላኩት ሮኬት ጨረቃን የመፈተሹና የመጀመሪያው ሰው የማረፉ በ1971 ዓ.ም. የመጀመሪያው የሕዋ ላይ ጣቢያ በከፍተኛ ፍጥነት 6120 ማይል ተጠግቶ ማርስን እና አፈጣጠሯን ማየቱ አልፎ ተርፎ በ1976 ዓ.ም. ለሙከራ ማሳረፉን ይህ ሁሉ አዲሱን ግሎባላይዜሽንን (ዓለም አቀፋዊነትን) ያፋጠነ ክስተት ነው። ከዚህ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አዲሱ የሕዋ ዘመን (space age) ዓለምን በከፍተኛ ፍጥነት እንድትጣመር አድርጓታል።

ይህ የሕዋ ዘመን ደግሞ የሳተላይት ጥበብን ወልዶ አሮጌውን በኮምፓስ አቅጣጫ መፈለግን አስወግዶ በጂፒኤስ የትም ቦታ ሆኖ አንዲት እፍኝ በማትሞላ ቴሌቪዥን መሠል ነገር አቅጣጫን ማወቅ ከሚቻልበት ዘመናዊ ጥበብ ላይ ተደርሷል። ይህም ጥበብ ከመሬት እየተነሣ ሰማይ ላይ ከተንጠለጠለው ሳተላይት ጋር ተጋጭቶ ሰው ሳይነካው በፍጥነትና በጥራት አቅጣጫ የሚጠቁም መሣሪያ ሲሆን፤ መኪና እያሽከረከሩ እዚህ ቦታ ውሰደኝ ብለው ሲጠይቁት ማለትም አድራሻ በጽሑፍ ሲሰጡት ይህን መንገድ ያዝ በዚህ ታጠፍ እያለ የሚመራ በር ማንኳኳት ብቻ ሲቀረው ሁሉን የሚፈጽም ነው።

ግሎባላይዜሽን ሦስት የተባለው ዓለምን ፈጽሞ አንድ መንደር ወደመሆን ደረጃ አድርሷታል። ዛሬ በየትም አገር የሚካሄዱ ጦርነቶች፣ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በአጠቃላይ የታወቁ እና የተለዩ ናቸው። ካስፈለገም



ይቀረጻሉ፤ ይህ ሁሉ የሕዋው ዘመን ውጤት ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሳተላይት ብሮድ ካስት በተፈለገው ቦታ የተፈለገውን ፕሮፓጋንዳ ለማስተላለፍ ተዘጋጅቷል፤ ቴሌቪዥኑም እንደዛው። ከሁሉ የበለጠው ግን የኢንተርኔት አገልግሎቱ ነው። ማንም ሰው የሚፈልገውን ሐሳብ በኢንተርኔት የማስተላለፍ ችሎታ እስኪኖረው ድረስ ነጻ የኢንፎርሜሽን ዘመን ላይ ደርሰናል።

ፖለቲካውና ሽብርተኝነት ካላደናቀፉት፣ መሀል ካልገቡ በቀር አስደናቂው ጮራ ለብልጽግና፣ ለአዲስ መንገድ እና ለትብብር እጅግ ጠቃሚ ነው። ይኸውም ድርጅት ከድርጅቶች ጋር፣ ሕዝብ ከሕዝቦች ጋርና በግለሰቦች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት ነው። ዘመናዊው የመገናኛ ብዙኃን ዕድገት ይህችን ምድር በእጅጉ አቀራርቧታል። በዚህ ምክንያት ዛሬ ዕውቀት በስፋው በየኮምፒዩተሮቹ መስኮቶች እንደጉርፍ እየፈሰሰ ይገኛል። በየትኛውም መስክ ያሉ ቁልፍ ሐሳቦች በፕሮግራም ተነድፈውና ተቀምረው ለተጠቃሚ ተዘጋጅተዋል። ሕፃናት ሳይቀሩ በረቂቅ ዕውቀት እየተሞሉ ይገኛሉ። ታዲያ ክፋውም የዚያኑ ያህል ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን የቤት ሥራ ለማሠራት የኮምፒውተሩን መስኮት መክፈት ብቻ ይበቃቸዋል።

### እኛና መረጃ

ከዚህ ሁሉ የምድራችን የመገናኛ ብዙኃን ሞገድ ጋር ሀገራችንን ኢትዮጵያን ስናያት በብዙ ነገሮች አበረታች ሁኔታ ሲታይ በደፈናው እኛ ከዓለም ተዘለን ያለን ሕዝቦች ነን ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርሰን ብዙ ክስተትም አለ።

እኛ ከኢንፎርሜሽን ጋር መታረቅ አለብን ብለን ስንነሳ የሚታተሙ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎቶችን ሁሉ የሚዳስስ መሆን አለበት።

ስንት መጽሔቶች አሉን? ምን ላይ ያተኮሩ ናቸው? ቀደም ብለን

እንደተነጋገርነው ሁሉም የፖለቲካ መሪነት ለመጨበጥ ስለሚፈልግ በዚህ ዘመንም ሰደድና እሳት እያለ መጽሔት ሲያሳትም በእርግጥ ታይቷል፡፡ እርግጥ ነው የዴሞክራሲ መብቱ በፖለቲካው መስክም እጅግ ጠቅሟል፤ አስተምሯል፤ የዛኑ ያህል ውሸቱ መረጃ የሌላቸው መልእክቶች ማቅረቡ ሁሉ ባለፉት ዓመታት የታዘብነውም ጉዳይ ነው፡፡ ከተጻራሪ ጐራ ነጻ ሆኖና ማዛኑን ጠብቆ የሚወጣው አነስተኛም ነበር፡፡ ጅምሩ ጥሩ ነው፡፡ ግን ሌሎቹስ መስኮች የሳይንስ እና የሥነ ጥበብ መጽሔት ለምን አልታዩም ድንገት የሚያነባቸውም ሊጠፋ ይችል ይሆናል በሚል የገበያ ጥናት አስገዳጅነት ከሆነም ሕዝባችን መልካም ትምህርት የሚያነብ፤ ጥበብን የሚናፍቅ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

የሬዲዮ አገልግሎቱ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በጣት የሚቆጠር ሆኖ ሳለ እሱም ራሱ በመንግሥት የተቆለፈ መሆኑ ሕዝባችንን በእጅጉ ጉድቶታል፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም ሆነ ሬዲዮ መርሐ ግብሮች እውነቱን ለመናገር መስሕብ የላቸውም በመግለጫ፣ በኢንተርቪው፣ በዲስኩር የተሞሉ ናቸው፡፡

በምዕራቡ ዓለም ፕሬዝደንቱ እንኳን ከአምስት ደቂቃ የበለጠ የአየር ጊዜ አይሰጠውም፡፡ የእኛ ግን ስንት ንግድ የሚካሄድበትን የአየር ሰዓት አንድ የወረዳ አስተዳዳሪ ሲያጭደው ማየት የተዘወተረ ነው፡፡ እንዲት የቀበሌ ድልድይ በመገንባቷ በመገናኛ ብዙኃን የማይቀርብ ዲስኩር አድራጊ የለም፡፡ በምዕራቡ ዓለም ግን ከአገር አገር የሚያካልል ሐይዌይ የሠራው ኢንጂነር አንድም ቀን በቴሌቪዥን መስኮት ቀርቦ አያውቅም፡፡ ሥራው ሳይከበር ቀርቶ አይደለም ግን ጊዜ የለም ለሌላ ግንባታ ማሰብ እንጂ አንዳች ጊዜ ማባከን አያስፈልግም፡፡ በመሆኑም ጊዜያቸውን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡

ሕዝቡን የሚያዝናኑ መርሐ ግብሮች እምብዛም ስለሌሉ እንደ ላስቲክ የተጐተተ የባለሥልጣን ወሬ ለመስማት ማንም ሬዲዮ አይከፍትም፡፡ ቆዳ ወንበር ላይ የሚወዛወዝ ባለሥልጣን ለማየት ማንም ቴሌቪዥን አያይም፡፡ ስለዚህ መገናኛ ብዙኃን ከሕዝቡ ጋር ሊታረቁ



ይገባል፡፡

በምዕራቡ ዓለም እነ ሲ.ኤን.ኤን፣ ኒውዮርክ ታይምስ፣ ቢቢሲ እና የመሳሰሉት ወሬ እየሸጡ ነው የከበሩት ወሬው ግን እውነተኛ እና ጣፋጭ ነው፡፡ ብዙዎቹ በዓለማችን ያሉ እንግሊዝኛ የሚያደምጡ ሕዝቦች የቢቢሲ ሬዲዮ ሱሰኞች ናቸው፡፡ ሲ.ኤን.ኤ. ጋዜጠኞቹን በሞቀ ጦርነት ውስጥ የሚልካቸው ትኩስ ወሬ ከአፍታው ለመቅዳት ካለው የሙያ ፍቅርና ጉጉት የተነሳ ነው፡፡

በአብዛኛው የሦስተኛው ዓለም ጋዜጦች የግለሰቦች ባሪያ፣ ቃል አቀባይ እንጂ የራሳቸው ነፍስ የሌላቸው ስለሆኑ ነፍሳ ገዳዮችን በቃላት ቅቤ ሲያሳምሩ፤ ያልተሰማውን ተሰማ፤ ያልተሠራውን ተሠራ እያሉ ሪፖርት ሲዘግቡ ነው ኑሯቸው፡፡ ግን በዓሉ ግርማን የመሳሰሉ እውነትን ያገለገሉም ተፈጥረዋል፡፡ ለሞያቸው ዋጋ ከፍለው ተከብረው ያለፉ ጋዜጠኞቻችንን እናከብራቸዋለን፡፡

ጋዜጠኝነት ታላቅ ሙያ ነው፡፡ በእሳት መካከል የሚያልፉ አርበኞች የተገኙት ከዚህ ሞያ ሥር ነው፡፡ ሙያውን ለጥቅም ያውም ለወር ደመወዝ የሸጡ ጋዜጠኞች አስተሳሰብ እስካልተለወጠ ድረስ ለሕዝብ የሚያገለግል ንጹሕ ሬዲዮ ማግኘት ዘበት ነው፡፡

ስለዚህ ነው ኢትዮጵያ እስከዚህ ዘመን (አይሲቲድ) የተገለለች አገር ሆና የምትኖረው፤ ከቴክኖሎጂ የተገለለች ከኢንፎርሜሽን የተገለለች ሆናለች፡፡ የራስዋ ስለሌላት የሌሎች ክፉ መረጃ /ኢንፎርሜሽን/ ማራገፊያ ወደመሆን እየተሸጋገረች ነው፡፡ ለዚህም በየቤቱ ተንጠልጥለው ያሉ ከውጪ አገር ወሬ የሚስቡ መሣሪያዎች ምሥክሮች ናቸው፡፡

ሥነ ጥበብ /ኢንፎርሜሽንን/ የሚገልጥ መሣሪያ ነው፡፡ ፊልሙ፣ ዘፈኑ ሌላውም ሌላውም በዚህ ዘመን በሌላው ዓለም ክፉ ሐሳብ ሲመስጥ እየታየ ነው፡፡

ለምሳሌ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ፊልሞች እንደ አሜሪካ ፊልም

መሆን ይቃጣቸዋል:: አሜሪካ ውስጥ ሰውን በግልጽ መግደል ከባድ ወንጀል ነው:: ስለዚህ ፖሊስ እንዳይደርስበት በረቀቀ መንገድ ለመግደል ረቂቅ ጥበብ ይጠቀማሉ:: ኢትዮጵያ ግን በይፋ ገድሎ የሚሸፈትባት አገር ነች:: እንደውም በሀገራችን ነፍሰ ገዳይ ነጻ ሆኖ በአውራ ጐዳና ሲሸከረከር ንጹሓኑ ግን እሥር ቤት ናቸው ይባላል:: ተሠውሮ መግደልም የተለመደ ቢሆን ግን በረቂቅ ተንኮል የተሰወረ ግድያ አይዘወተርም:: እንዲህ ሲባል ግን ሁሉን ለመኮነን አይደለም::

ታዲያ ደራሲዎቻችን ግድያውን ከፈረንጅ ፊልም ቀድተው ሲያወሳስቡት እውን ይህ ኢትዮጵያ ተደረገ ያሰኛል:: ፊልሞቻችን ከአሁኑ ባዕድ ባዕድ ይሸታሉ:: ቀልዱ ግልጽ የነውር ቃላትን መጠቀም ደረጃ ደርሷል:: አንዳንድ ሠለጠንን የሚሉ ደግሞ እርቃን ቃላት በመጠቀም በ1ኛ ደረጃ ት/ቤት እያባዙ ይበትናሉ:: ይህ ሁሉ የሕዝቡን የባሕል ካባ ለማውለቅ እና እርቃኑን ለማስቀረት ነው:: ከመሠልጠን ወይም ለገበያ ከመስገብገብ እንደሆነ አይታወቅም ልቅ የወሲብ መጽሔት በኢትዮጵያ ውስጥ የጀመሩ ነውረኞችንም አሳልፈናል::

**ማጠቃለያ**

ከላይ በጠቀስነው መሠረት የመረጃ /የኢንፎርሜሽን/ ጠባይ ዓለም አቀፋዊነትን አምጥቷል:: ዛሬ አንወቅ ብንል እንኳን በግድ እናውቃለን:: በራችንንም ዘግተን መቀመጥ እንደድሮው ፈጽሞ አንችልም:: ይልቅ ከመረጃ /ከኢንፎርሜሽኑ/ ማዕበል ውስጥ ለመግባት መዘጋጀት አለብን:: ዝግጅቱም የሥነ ልቡና ነው:: ከሁሉ በላይ የዚህን ዓለም ክፉ ወሬ እና ምስል መራቅ ያስፈልጋል:: መከበር ያለበትን ጠቃሚ ሐሳብ ግን ተጠንቅቀን መቅዳት አለብን:: ጥንታዊው ባሕላችን የኅብረተሰቡ እሴት ሥነ ጥበብ እና ታሪክ ሳይነካ:: እነዚህን የእኛን ፈርጦች የሚያንፀባርቅ ቴክኖሎጂ መግዛት አለብን::

ጋዜጠኞች ከፖለቲካዊ አዙሪት ወጥተው እውነትን ማገልገል አለባቸው:: መገናኛ ብዙኃን ሠንሠለቱ እምብዛም ያልጠበቀ እምብዛም ያልላላ ነፃነት ያስፈልገዋል:: በግል ባለሀብቶች መደገፍም አለበት ይህም



ነፃነቱን ሳይነጠቅ ነው:: እውነት ነው ነፃነት ያለው መገናኛ ብዙኃን ያስፈልገናል:: ነፃነቱ ግን ነውር መሆን የለበትም:: የሙያ ወሰኑን አልፎ ያላየውን፣ ያልሰማውን ማንበብ የለበትም::

ኮምፒውተሩ ለሕፃናቱ ትምህርት እንዲያገለግል በቋንቋቸው ይዘጋጅ ዘንድ በውጪም በውስጥም ያለው የምሁር ኃይል ሌሊትና ቀን መሥራት ይጠበቅበታል:: በዚህ ነው ኢትዮጵያ ከኢንፎርሜሽን ጋር ልትታረቅ የምትችለው::

አንድ አሜሪካዊ የተናገረው ዘወትር ከሕሊና ታትሞ የሚቀር ነው:: «ሁሉም ምሁር የሚማረው የገዛ ሕዝቡን ኮሚኒቲውን ሊያገለግል ነው:: አሜሪካም ሆነች ሌሎቹ የበለፀጉ ዓለማት የራሳቸው በቂ ምሁር ኖሯቸው ሳለ ኢትዮጵያውያን ምሁራን የተራበ፣ የተጠማ፣ የታረዘ፣ የታመመ ሕዝባቸውን ትተው የጠገበ የሚያገለግሉበት ሁኔታ እንቆቅልሽ ሆኖ ዘወትር ይገርመኛል::» ብሎ ነበር::

ብዙዎቹ ወደው አይደለም በኮሚኒዝም ቁራኘነት ተለክፈው ነው አገር ቤት የነበሩ ምሁራንን በወረንጦ እያሳደዱ ይፈጁ የነበሩት፤ ከዚያ አልፎ ተርፎም ለመሥራት የነበረው እንቅፋት፣ የፖለቲካው ወጥመድ፣ ከሞያው ጋር ዝምድና የሌላቸው ሰዎች የበላይ ሆኖ ማዘዝ እነዚህ ሁሉ ሆድ የሚያስብሱ የሚያባርሩ ሆነውበት ነው ምሁሩ ሳይወድ የገዛ ሕዝቡን ትቶ የተሰደደው:: እንዲህ ሲባል ደግሞ አገራቸውን ለማገልገል ትምህርታቸውን አጠናቀው የሞቀ ደሞዝ ንቀው ሕዝባቸውን እስከሞት እያገለገሉ ያሉትን እግዚአብሔር ውለታችሁን ይክፈል እያልን ነው::

ሁሉም ምሁር በሙያው የሚያውቀውን በቋንቋችን ከተረጐመና የቴክኖሎጂውን መፍቻ ቁልፍ ቃል ካገኘን ተራው ኢትዮጵያዊ ሳይቀር የፈጠራ ሰው ይሆናል:: ቴክኖሎጂው በቋንቋ ተሸፍኖበት እንጂ ሕዝባችን ለሥራ እንግዳ አይደለም:: የሥራ ኢንፎርሜሽን የጥበብ ኢንፎርሜሽን ያስፈልገናል:: ከኢንፎርሜሽን ጋር እንታረቅ::

የመገናኛ ብዙኃን ቢበለጽጉ በዚህ መስክ በሺህ የሚቆጠሩ ሙያተ

ኞችን ማሠማራት ይቻላል:: የሕትመት ሥራ፣ የፊልም ሥራ ሌላውም እንደ ሶኬት እየተቀጣጠለ የሥራ ሰዎች እንሆናለን:: ጥራትና ሥርዓት የጠበቁ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን አገልግሎት ለባለሀብቶች ቢለቀቅ ብዙ ሰው በመስኩ ይሠራል:: መንግሥት የኢንፎርሜሽን ፖሊሲውን በእጅጉ እንዲቀይረው የእርቅ ሐሳብ እናቀርባለን::

የሞያው ሰዎችም በአንድ ፖለቲካ ግርግር ላይ ብቻ ከማተኮር ወደተለያየ የሙያና የጥበብ መስክ የመገናኛ ብዙኃንን አፈሙዝ ሊያዞሩት ይገባል:: ይህም እርቅ ይፈልጋል:: ሥርዓት የሌላቸው የመገናኛ ብዙኃን ሽፍቶች ሕዝቡን ሰዶማዊ ሕይወት በማስተማር በአቋራጭ ሊበለጽጉ መሞከራቸው ኃጢአት ስለሆነ መልካም ሥነ ምግባር ካለው የኢንፎርሜሽን ዓለም ጋር ሊታረቁ ይገባቸዋል::

ከመረጃ /ከኢንፎርሜሽን/ ጋር እንታረቅ::

## ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

## ከአስተዳደር ጋር መታረቅ

አስተዳደር የሁሉ ነገር መሠረት ነው:: አስተዳዳሪዎች የአመራር ብቃት ብቻ ሳይሆን ራዕይም ጭምር ያስፈልጋቸዋል:: የአምስት፣ የአሥር፣ የሃያ አምስት ዓመት የሩቅና የቅርብ ጊዜ ዕቅድ ያለው ተግባራዊነቱም የሚፈተሽ ሥራ የሌላቸው አመራሮች ከዚህ ዓለም እሽቅድምድም በአጭር ተቀጭተው ወደኋላ ይቀራሉ:: ከቤተሰብ አስተ ዳደር ጀምሮ የመንደሩ እና የወረዳው የድርጅትና የመንግሥት አስተዳደር ሁሉ በበሳል መሪዎች ከተመራ ውጤቱ ያማረ ይሆናል:: የአስተዳደር ታሪክ ጥንታዊ ነው:: ጨካኝ፣ መሠሪ፣ ንዝህላል፣ አሠልቺ አመራሮች በምድራችን ተፈራርቀዋል:: በአንጻሩም ፈጣን፣ ቅን፣ ሰላማዊ፣ ዕድገት የተሞሉ በጐ አመራሮችም ታይተዋል::

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በተከፋፈሉት ታላላቅ ዘመናት ስላለው



አስተዳደር በትንቢተ ዳንኤል የተመዘገበውን ተመርኩዘን የሙሴንም በመከተል በደረጃ የአስተዳደርን ጥበብ እናያለን::

በትንቢተ ዳንኤል የተመዘገበው በአሕዛብ ወይም በማያምኑ ባቢሎናውያን ላይ የተሾመው ንጉሥ ናቡከደነፆር ሕልምን አለመ:: በባቢሎን የነበሩ ሕልም ፈቺዎችን እና አስማተኞችን ሰብስቦ ሌሊት ሕልም ማለሙን፣ ግን ያየው ሕልምም ሆነ ፍችው እንደተሠወረበት፣ ፍችውን ባይነግሩት እንደሚገላቸውና እንደሚቆርጣቸው ይነግራቸዋል:: በዘመኑ በየምክንያቱ ነገሥታት የፈለጉትን ሰው መግደል ይችሉ ነበርና እጅግ ጭንቅ ሆነ::

የይሁዳ ቤት ምርኮኛ የነበረ ዳንኤል ከጸለየ በኋላ የሕልሙን ፍች ከእግዚአብሔር ይረዳል:: ስለዚህ ለዚህ ግድያ የታዘዘውን አርዮክን ወደ ንጉሡ እንዲያስገባው ይጠይቀዋል እንደገባም ንጉሡ ያየውን ሕልም እስከ ፍችው ይነግረዋል:: ዋናው ቁም ነገር ንጉሡ ያየው ሕልም ነው:: ይህም እግዚአብሔር ለዳንኤል የገለጠለት ምሥጢር ከንጉሡ ናቡከደነፆር በኋላ ስለሚመጡት ዘመናት በሰፊው ይተነትናል::

«አንተ ንጉሥ ታላቅ ምስል አየህ ይህም ምስል ታላቅና ብልጭልጭታው የበዛ ነው:: በፊትህም ቆሞ ነበር:: መልኩም ግሩም ነበረ:: የዚህ ምስል ራሱ ጥሩ ወርቅ ደረቱና ክንዱም ብር ሆዱና ወገቡ ናስ ጭኖቹም ብረት እግሮቹም እኩሉ ብረት እኩሉም ሸክላ ነበር:: እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ:: የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፣ ነሐሱና ብሩን ወርቁም በአንድነት ተፈጨ፤ በመከርም ጊዜ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ፤ ነፋስም ወሰደው፤ ቦታውም አልታወቀም፤ ምስሉንም የመታው ድንጋይ ተመልሶ ታላቅ ተራራ ሆነ፤ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ::

ሕልሙ ይህ ነው፤ አሁንም ፍቺውን በንጉሡ ፊት እንናገራለን:: አንተ ንጉሥ ሆይ የሰማይ አምላክ መንግሥትንና ኃይልን ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ ነህ:: በሚቀመጡበትም ሥፍራ

ሁሉ የሰው ልጆችንና የምድር አራዊትን የሰማይ ወፎችንም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል። ለሁሉም ገዥ አድርጎሃል አንተ የወርቁ ራስ ነህ። ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ ሌላ መንግሥት ይነሳል። ከዚያም በኋላ በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛ ሌላ ሦስተኛ የናስ መንግሥት ይነሣል፤ አራተኛ ውም መንግሥት ሁሉን ይቀጠቅጋል ይፈጭማል፤ እግሮቹና ጣቶቹም እኩሉ ሸክላ እኩሉም ብረት ሆኖ እንዳየህ እንዲሁ የተከፋፈለ መንግሥት ይሆናል። ብረቱ ከሸክላው ጋር ተደባልቆ እንዳየኸው የብረት ብርታት ለእርሱ ይሆናል። የእግሮቹ ጣቶች እኩሉ ብረት እኩሉም ሸክላ እንደነበሩ እንዲሁ መንግሥቱ እኩሉ ብርቱ እኩሉም ደካማ ይሆናል።»*

በዚህ የዳንኤል ትንቢት ላይ እንደምናነበው የሰው ልጅ የአስተ ዳደር ዘመኖች በአራት የተከፋፈሉ ሆነው ቀርበዋል። የመጀመሪያው የወርቅ ዘመን ነበር። ይኸውም እስከ ናቡከደነፆር የነበረው ዘመን ነበር። እጅግ ሰፋፊ ግዛትን በአንድ ላይ አድርጎ ይገዛ የነበረ አስተዳደሩ እንደወርቅ የሚያንፀባርቅ ጠንካራ የሆነና እጅግ የበረታ ነው።

ሁለተኛው ዘመን የብር ዘመን ኃይሉ ምንም ቢበረታ እንደናቡከደነፆር አልነበረም፤ ግን ዓለምን አንድ አድርጎ ይገዛ የነበ ረ ነው። ሌላው የነሐስ ዘመን ሲሆን፤ ለየግዛቱ የሮማ ዜግነት የነበራቸው የአገሪቱን ተወላጆች ይሾም የነበረው አሁንም ሰፊ ግዛት ያስተዳድር የነ በረ መንግሥት ነው። ከዚህ በኋላ ታላላቅ መንግሥታት ኃይል እያጡ እየተከፋፈሉ የመጡበት የብረት (የጭካኔ) የመከፋፈል የውጊያ ዘመን ነበር። ይህ ዘመን ሲያልፍ የአሁኑ እጅግ የተከፋፈለ በየድንበሩ ጦርነት የሚደረግበት የሸክላና የብረት ድብልቅ ዘመን ነው።

ይህ ሰፊ የሰው ልጅ የታሪክ ዘመን የሚያሳይ ራዕይ እግዚአብሔ ርን የማያመልከው ናቡከደነፆር እንዲያየው የተደረገው ምስክር ይሆን ዘንድ ሲሆን፤ የወርቅ፣ የብር፣ የነሐስ፣ የብረት እና ሸክላ ድብልቅ አስተዳደር እየተፈራረቀባት ያለፈችው ዓለማችን እስከፍጻሜዋ

* ትን.ዳን. 2፥1–45



የሚያጋጥማትን ለማወቅ የእነዚህን ማዕድናት ጠባይ ማጥናት ብቻ ይበቃል።

ሌላው በአስተዳደር መስክ የሚጠቀስ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሙሴ እና የሕዝበ እስራኤል ታሪክ ነው። ሙሴ ይመራው የነበረውን ሕዝብ ከግብጽ አስወጥቶ ወደ እስራኤል ሲወስድ አመራር ያስፈልግ ስለነ በረ የተጣላውን ሊያስታርቅ፣ የተበደለውን ሊያስክስ ሁሉም ወደ እርሱ ይመጣ ነበር። ሙሴ ለሕዝቡ ሊፈርድ በተቀመጠ ጊዜ ከጠዋት እስከ ማታ አንዱ ሲሄድ አንዱ ሲከተል ለሁሉም የሚፈርደው ሙሴ ብቻ በመሆኑ የተደነቀው የኢትዮጵያዊቷ የሙሴ ሚስት የሲፓራ አባት ዮቶር ምክር መከረው። «ይህን ለሕዝቡ የምታደርገው ምንድን ነው? ሕዝቡ ሁሉ ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ በዙሪያህ ቆመው ሳሉ አንተ ብቻ ህን ስለምን ተቀመጥህ አለው። ሙሴም አማቱን ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ይመጣሉ። ነገርም ቢኖራቸው ወደኔ ይመጣሉ። በዚህና በዚያ ሰውም መካከል እፈርዳለሁ የእግዚአብሔርንም ሥርዓትና ሕግ አስታውቃቸዋለሁ አለው። የሙሴም አማት አለው - አንተ የምታደርገው ይህ ነገር ልክ አይደለም። አሁንም እመክርሃለሁና ቃሌን ስማ፤ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል። አንተ በእግዚአብሔር ፊት ለሕዝቡ ሁን፤ ነገራቸውንም ለእግዚአብሔር አድርስ፤ ሥርዓቱንም ሕጉንም አስተ ምራቸው፤ የሚሄዱበትን መንገድ የሚያደርጉትንም ሥራ ሁሉ አሳያቸው። አንተም ከሕዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፣ የታመኑ፣ የግፍንም ረብ የሚጠሉትን ሰዎች ምረጥ ከእነርሱም የሺህ አለቆችን፣ የመቶ አለቆችን፣ የሃምሣ አለቆችን፣ የአሥርም አለቆችን ሹምላቸው። በሕዝቡ ላይ ሁልጊዜ ይፍረዱ። አውራውን ነገር ሁሉ ወደ አንተ ያምጡት ታናሹንም ነገር ሁሉ እነርሱ ይፍረዱ እነርሱም ከአንተ ጋር ሸክሙን ይሸከማሉ፤ ለአንተም ይቀልልሃል።» ብሎ አለው።*

ይህ ኢትዮጵያዊ ምንም ከእግዚአብሔር የተላከ ቢሆን ከሙሴ

* ዘጸ. 18፥13-26

በፊት በአገሩ ኢትዮጵያ መልካም አስተዳደርን ማየቱ አያጠራጥርም። በዚህ ዘመን ያለውን የሥራ ክፍፍል አጠቃላይ ገጽታ በአጭር ንግግር አስቀምጦታል። እንዲህ ዓይነት ምክር የሚመክሩ ታላላቅ ጠቢባን ባለቤት ኢትዮጵያ በእውን በዚህ ዘመንስ ዮቶርን የመሳሰሉ ብልህ ሰዎች የሏት ይሆን? እንደሙሴ የሚሰማ ቢያገኙ አስተዳደሩን ለማቃናት በቂ የሕሊና ብቃት ያላቸው ምሁራን ሞልተውናል። ምሁራኑን ትተን ያልተማሩ የሚባሉ አዛውንትና ባልቴቶችን እንዴት ቤተሰባችሁን መራችሁ? ብለን ብንጠይቃቸው በአስተዳደር ከተመረቁት ምሁራን የበለጠ በሳል መልስ ይኖራቸዋል።

እንደውም አንድ ከአሜሪካ በኢኮኖሚክስ የተመረቀ ምሁር መንግሥት ያሸከመውን 1500 ብር ከወር ወር በአግባቡ መጠቀም ቢያቅተው አምስት ልጅ በሁለት መቶ ብር የሚያስተዳድሩ ወይዘሮ ጋ ደብተርና ወረቀት ይዞ ሄዶ «እሜቴ ለመሆኑ በሁለት መቶ ብር ይህንን ሁሉ ማቲ የማስተዳደር ጥበብዎን ሊያካፍሉኝ ይችላሉ» ብሎ ጠይቋቸው ነበር ይባላል።

ካረሊያን ኮውሮቢ የተባለች ፀሐፊ «ሕዝቦች ታላላቅ መሪዎችን ካለመታከት ይፈልጋሉ። እነዚህ የተለዩ ግለሰቦች የተለየ ባሕሪ አላቸው። ስለተከታዮቻቸው (ስለሚመሯቸው) ያስባሉ፤ ይጨነቃሉ፤ ወደ መልካም የወደፊት ሕይወት የመምራት ብቃትም አላቸው።» ብላለች። እዚህ ጽንሰ ሐሳብ ላይ ያሉ ዐበይት ቃላትን በመምረጥ ወደ ማጠቃለያ እናመራለን።

ዓለማችን መልካም መሪዎችን ትፈልጋለች። ክፉዎቹን አጋግን የመሳሰሉትን ደግሞ ዕድሜያቸው ያጥር ዘንድ ትፀልያለች። እንደ ኤዲያሚን ያሉትን አይታ የደነገጠችው ዓለም፣ እነሒትለርን አስተናግዳ ያፈረችው ምድራችን፣ ጸሎትዋ ደጋግ መሪዎችን እባክህ ስጠኝ የሚል ነው።

ክፉ አስተዳዳሪዎች ያሉበትን ዘመን ብቻ ሳይሆን መጪውንም አጨልመውት ነው የሚያልፉት። የቀድሞው የሱማሌ መሪ ዚያድባሬ በዘመኑ ሕዝቡ ላይ ያደረሰው በደል አንሶ እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል እንዳለችው አህያ «When I leave Somalia, I will leave behind buildings but no people እኔ ሱማሌን ለቅቄ ስወጣ ሕንጻ ብቻ እንጂ የሰው ዘር አላስቀርም» እንዳለው ሁሉ። መጥፎ መሪዎች እንደ ሮማው ዘፋኝ ንጉሥ ከተማ አቃጥለው ከተራራ ላይ ወጥተው መሳቅና መዝፈን ይወዳሉ።



ስለዚህ ለሚመራው ሕዝብ የሚጨነቅ መሪ ማግኘት ማለት ዕድለኝነት ነው። ብዙዎቹ የበለፀጉ አገራት ባጋጠማቸው የመሪ ጸጋ ታግዘው ነው እዚህ ደረጃ የደረሱት። አሜሪካውያን አባቶቻችን የሚሏቸው ሕንዶች ነቢያቸውን እስራኤላውያን እንግሊዞችና ቻይናዎች አያቶቻቸውን የሚመርቁት በተሠራላቸው የአመራር ውለታ ነው። «በተለይ በዚህ ዘመን ጥሩ መሪ መሆን ብቻ በቂ አይደለም እጅግ በጣም ጥሩ መሪ እንጂ» አሁን የምናወራው በብርሃን ፍጥነት ስለሚጓዘው የዛሬው ዓለም ነው። በአመራር ብቃታቸው የሰውን ልጅ ያስደነቁ ግለሰቦች ያሉባትን የዛሬዋን ዓለም ነው የምናነሳው።

ስለዚህ በዚህ ዘመን አመራር ምን መምሰል አለበት የሚለውን አንባቢ በሕሊናው ያስብ ዘንድ እንተውለት እና መልካም አመራር ምን ማለት እንደሆነ በጥልቀት እንመለከታለን።

አመራር ለመንግሥት፣ አመራር ለትርፋ ላልሆኑ ድርጅቶች፣ አመራር ለሃይማኖት ተቋማት፣ ለሕክምና ማዕከል፣ ለትምህርት ተቋማት ሌላው ቀርቶ ለቤተሰብ መዋቅር፤ በተለይ በዚህ የዴሞክራሲ ጽንሰ ሐሳብ ባየለበት ወይም በሰይጣናዊ ኢምፔሪያሊዝም አገሮች በተቀሰፉበት ጊዜ ወይም በጥሎ ማለፍ ትልቁ ዓሣ ትንሹን በሚውጥበት ፈጣን እና ጨካኝ ዓለም አመራር ከወሳኝነት አልፎ የሕልውናም ጥያቄ ነው።

ዴሞክራሲ የነፃነት ሒደት ነው ብዙ አገራት እየተጓዙበት ያለ፤ ግን በዚህ ውስጥ የገቢያ መቀማማት የሩጫው ፍጥነት በብርሃን ፍጥነት ከሚለካበት ዘመን ላይ የደረስንበት ጊዜ ነው። ለማንኛውም ዴሞክራሲ ለአስተዳደር ያደለው ወይም የለገሰው አራት ታላላቅ ስጦታዎች አሉ። እነሱም 1 Empowerment, 2. Individual responsibility 3. Earning/ accountability mode 4. Rising entrepreneurism.

ናቸው::

በዴሞክራቲክ ሕዝብ ውስጥ ሌላው ቀርቶ በዴሞክራሲ የሚመራ ድርጅትን ጨምሮ ብዙው ኃይል በግለሰቦች እጅ ነው ያለው:: ይህ አካሄድ (Empowerment) ይባላል:: ታዲያ እነዚህ ሥልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች ኃይላቸውን በብልሀት እንዲጠቀሙበት ይገደዳሉ:: አለበለዚያ ግን የድርጅታቸውም ሆነ የሚመሩት አካል ሕልውና አደጋ ላይ ይወድቃል::

በዚህ አካሄድ ውስጥ ድንገት የሚሰየሙት ሰዎች ዕውቀት ውስን ከሆነና በበታቾቻቸው የሚበለጡ ከሆነ ወደ አመጽ ስለሚለወጡ የሚበልጣቸውንም ስለሚያጠቁ ቀድሞውኑ በራሳቸው የማይተማመኑ ደካሞችን ከዚህ ኃይል ማራቅ ይገባል::

## (Individual responsibility) የግለሰቦች ኃላፊነት

ጥርት ያለ ዴሞክራሲያዊ ኅብረተሰብን ለመፍጠር እያንዳንዱ ግለሰብ ኃላፊነት ይኖርበታል:: ፖሊስ በየቦታው ተገኝቶ ሕግ ሊያስከብር አይችልም:: ስለዚህ ፀጥታን፣ ሥርዓትንና ታማኝነትን በማገልገል እያንዳንዱ ዜጋ ጥብቅ ኃላፊነት ይጠበቅበታል::

በዴሞክራሲ የሠለጠነ ኅብረተሰብ ውስጥ ፖሊስ አደጋ የደረሰበትን ወይም መንገድ የጠፋውን ለመርዳት እንጂ የተጣሉ የተጋደሉ ሰዎችን ለማሠር አይደለም የሚንቀሳቀሰው:: ይህ የግል ኃላፊነት ሁሉም ሲሰማው ሲችል የዴሞክራሲ ብርሃን መፈንጠቅ ይጀምራል::

## Earning (Accountability Mode)

በጥሩ ምርታማ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ውስጥ ራሱን የመራ ወይም የሚጠበቅበትን የሠራ ሁሉ በቂ ክፍያ ወይም ሽልማት ማግኘት ይገባዋል:: ልክ እንደዛው ጥሩ ክፍያን ለማግኘት ሁሉም የሚጠበቅበትን ማከናወን ይኖርበታል:: ግን ይህም ጥቅም ባይኖረውም እንኳን ሥነ ምግባር ታላቅ ዋጋ አለው::



## (Rising Entreprenerurism)

በነጻው ኅብረተሰብ ውስጥ ብዙ ግለሰቦች ወደ ፈጠራው ዓለም ለመሄድ ድፍረት አላቸው:: ለዚህም ሁኔታዎችን ለማቀናጀት ለማላካት ኃላፊነትን ይወስዳሉ:: በከፍተኛ ጥበብ ትጋትና የኃላፊነት ስሜት ከውጤት ይደርሳሉ:: ስለዚህም ድርጅቶች ግለሰቦችን በሥራው ላይ ከፍተኛ የኃላፊነት ድፍረትን ይጠይቃሉ:: ይህ ሁኔታ የሚገለፀው በሥራቸው ላሉ ግለሰቦች ኃላፊነት በማከፋፈል ነው:: (Empowerment)

ይህ አካሄድ ለሠራተኞች የድርጅቱን የተወሰነ የባለቤትነት መብት እስከማጋራት ይሄዳል:: ለሠራተኞች ሰፋ ያለ ነፃነትን በመስጠት የግለሰቦችን ነፃ የፈጠራ ችሎታ ለመበዝበዝ (ለማግኘት) የነጻው ገበያ የዴሞክራሲ አስተዳደር በዘዬ የተሞላ ነፃነት የሰጠ ይመስላል:: ስለዚህ የእኔነት መንፈስ የሚሰማው ሠራተኛ አዳዲስ የፈጠራ ሐሳቦችን ሲያመነጭ ድርጅቶች ባልታሰበ የብርሃን ፍጥነት ያድጋሉ::

## ለውጥ

በአስተዳደር ውስጥ ለውጥ ከሌለ ባለህበት እርገጥ አካሄድ ሊያዛልቅ አይችልም:: አንድ ተቋም ወይም ድርጅት ወይም አገር በተመሳሳይ ሁኔታ ለሦስት ዓመት ከተመራ ለ15 ዓመት ሊነሳ የማይችል ውድቀት ውስጥ ይዘፈቃል:: ለውጥ ሦስት ዐበይት ቅርንጫፎች አሉት:: አንደኛው ፍጥነት ነው:: ሌላው አመራር ዋናው ግን መዋቅር ነው:: ከእነዚህ ሦስት ዐቢይ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ከተቀየረ መንገዱ በለውጥ ላይ ነው ማለት ነው::

## ፍጥነት

ሁሉም ነገር ከፈጣን ወደ እጅግ ፈጣንነት እየተለወጠ ነው:: ታላላቅ መሪዎች ይህንን የተረዱ መሆን ይኖርባቸዋል:: የሕይወት ዑደት ምርቱ እና የሰዎች ችሎታ አጭር ነው:: ስለዚህ አንድን ነገር ለማምረት ያለው ውጣ ውረድ እጅግ ማጠርና ፈጣን መሆን አለበት:: ምርት በአጭር

ጊዜ ገበያ ላይ መገኘት አለበት። ለሸማቹ ኅብረተሰብ ፈጣን እና ብዙ አማራጭ ስላለ ከሁሉ ፈጥኖ መገኘት ያስፈልጋልና። ስለዚህ በነጻው ገበያ ዴሞክራቲክ ድርጅትም ሆነ አገር በፍጥነት ሰዎችን መቅጠር ላላስፈላጊ ሲሆኑ፤ (downsize) የሠራተኛን ብዛት መቀነስ የተለመደ ነው። ስለዚህ ግለሰቦች በበቂ ችሎታ ንቃትና ፍጥነት በልጠው መገኘት የግድ አለባቸው። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ጨካኝ ይመስላል። ግን ምንም ሊደረግ የማይቻልበት ዕውነታ እና የነጻ ገበያ ጠባይ ነው። ይህም እየሆነ ያለ ሁኔታም ስለሆነ በሀገራችን ይህንን ለመደገፍ አንድ መንገድ መፍጠር ያስፈልጋል።

በዓለማችን የፈሉት (The aerospace industry) በዚህ የታወቁ ናቸው። በተለይ (Virtual Corporatiors) በዚህ መንገድ የተቀረፁ በመሆናቸው በድሆቹ አገራት ሠራተኞችን ሊጐዱ ስለሚችሉ ሁልጊዜ በሳል መሪዎች እነዚህን አካሄዶች መንገድ ይፈጥሩላቸዋል።

## የአመራር ሕግ (Rules)

አመራርን ወይም መንገዱን መለወጥ ድርጅቶችን በከፍተኛ ፍጥነት ይለውጣቸዋል። በተለይም ከአንዱ ግለሰብ ወደሌላው ሥልጣን ሲቀያየር አመራሩ በፍጥነት ይለወጣል። አገሮችም ሆኑ ድርጅቶች ዛሬ ከተለመደ አሠራር ወደ ፍጹም ለውጥ እየተቀየሩ ያሉት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ግለሰቦቹን በመለዋወጥ ነው።

ይህም ሰዎች የተለያየ የተፈጥሮ ጸጋ ስላላቸው ከፊታቸው የመለወጫ ጊዜያቸው ተወስኖ ከተሰጣቸው በዛ ጊዜ ግን ማንም ጣልቃ ሳይገባ በተረጋጋ ሁኔታ ከሠሩ ያልተጠበቀ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ። ምክንያቱም የተቀመጡበት ወንበር በውድድር የተገኘ ስለሆነ ፍጥነታቸውን ቢቀንሱ በሌላ ሊተኩ ስለሚችሉ ነው። በነጻ ኅብረተሰብ ውስጥ ጤናማ ውድድር ጤናማ ዕድገት አስገኝቷል።



## የመዋቅር ለውጥ (Structure)

በዚህ ባለንበት ዘመን የአደረጃጀት የአሠራር መዋቅር ለውጥ ማድረግ እጅግ የተዘወተረ ነው። ለምሳሌ የሥራው፣ የአመራሩ ኃይል ከላይ ባሉት ሰዎች ላይ ተቆልሎ የነበረበት ዘመን ተሽሮ አሁን ሥራ ወደታች የሚንሸራሸርበት አንድ ግለሰብ የተወሰነ ኃላፊነት ላይ ብቻ እንዲጨነቅ የቀረውን ለሌሎች እንዲያከፋፍል የሥራ መዋቅር ወጥቷል።

ይህ መዋቅር የሚያተኩርባቸው ሥራን ከላይ እስከታች ማካፈልን፣ የተቀጣሪ ሠራተኞች ችሎታ እና ብቃት ጠቃሚ ከሆነ በሥራ ማቆየት፤ ካልሆነ ግን ሌላ ሥራ እንዲፈልጉ ማሠናበት፤ ስለዚህም ከተቀጣሪዎች ጋር የጽሑፍ ስምምነት ማድረግ ያጠቃልላል። ይህ ብዙ አገራት የተቀበሉት የነጻ ገበያ ፖሊሲ ነው።

ለዚህ ሁሉ ማጠቃለያ የሚሆነን በነጻ ገበያ መርህ የመጀመሪያው ንጉሥ ሸማቹ ገበያተኛው፣ ተጠቃሚው፣ አገልግሎት ተቀባዩ ነው። ሁለተኛ ንጉሥ የድርጅት ባለንብረቶች ወይም ቀጣሪዎች ናቸው። ሦስተኛ ንጉሥ ብቃት እና ሞያ ያላቸው ሠራተኞች ናቸው። በዚህ ውስጥ ብቃትም ችሎታም የሌለው ግለሰብ ግን ባርያ ወይም ቤት አልባ ነው።

ስለዚህ ከራስ አስተዳደር፣ ከቤተሰብ አመራር ጀምሮ እስከ ድርጅትና አገር መምራት ያለው የሰዎች ብቃት በእርግጠኝነት አስተማማኝ መሆን አለበት። ብቃት የሌለው ግለሰብ ለማኝ ሊሆን ይችላል። እንዲያውም በፈጣኑ ዓለም መለመንም አያዋጣም በንዝህላል መሪ የሚመራ ድርጅትም ይፈርሳል። በመሆኑም በእንጉል መሪ የምትመራ አገር ዕጣዋ ምንድነው? ለዚህ ነው ዛሬ መምራት በብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች አንገት ላይ መቆም ነው የሚባለው።

መጽሐፍ ቅዱስ ወየው ሕፃናት ለነገሡባት አገር ይላል።* ሕፃን ማለቱ ሕፃን አይደለም የሕሊና ብቃታቸው ሕፃን የሆነ ማለቱ ነው። ለውሣኔ የሚቸኩል ረጋ ብሎ የብዙ አማካሪዎችን ሐሳብ ሰምቶ አሥር ጊዜ መትሮ አንዴ የማይቆርጥ መሪ ከሆነ ዕድሜው የዘገየ ቢሆንም እንኳን ሕፃን ይባላል።

* መክ. 10፡16

ከአስተዳደር ጋር መታረቅ ላለመሳሳት አልሞ መደቆስ ሐሳብን መላልሶ ማሸት ማለት ነው። በኦሮሞ ጉሣ አነጋገር በየትኛውም አከራካሪ ሐሳብ ላይ «ዱቢ ኦሮሞ ኪሣ፤ ሃቡሉን በየሳ» «እስቲ ነገሩን እናስተኛው» የሚል ብሂል አለ። በረጋ ሕሊና ሌሊት ሲያመላልሱት ያደሩትን ሐሳብ ቀን በተግባር ላይ ማዋል አያስቸግርም።

## እኛና አስተዳደር

ሀገራችን ለብዙ ዘመናት በፍጹማዊ የንጉሥ አስተዳደር ትመራ ነበር። በመካከሉ ወደመሣፍንት አስተዳደር የገባንበት የእንቅልፍ ዘመን ሳይቆጠር በርካታ የተማከለ የአስተዳደር ታሪክ አለን።

ተክለጻድቅ መኩሪያ የተባሉት የታሪክ ፀሐፊያችን «የኢትዮጵያ መንግሥት የነፃነት ዘመን ረዥም እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረዥም ዘመን ውስጥ በአገሪቱ ላይ የውስጥ ጦርነትም የአስተዳደር፣ የዳኝነት፣ የንግድና የሽቀጥ መለዋወጥ እንደነበረ» ጠቅሰዋል። ሌላው ቀርቶ በአስተዳደር የሚታወቁት የኢትዮጵያ መሪዎች ፍትህ ቀጥተኛ በመሆኑ በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 12 ጌታችን እራሱ በመጨረሻው ዘመን ንግሥተ አዜብ በዚህ ሕዝብ ለመፍረድ ትነሳለች ... ብሎ ነበር። ኢትዮጵያ በታሪክ የታወቀች ስለመሆንዋ ባለፉት ምዕራፎች ተነጋግረናል። አንድን አገር በአገርነት ከሚያሳውቁ ቁም ነገሮች አንዱ ደግሞ አስተዳደር ነው።

አንዳንዴም ያማረ ሌላ ጊዜም ግፍ የተቀላቀለበት አስተዳደር እንደማንኛውም መንግሥት አሳልፈናል። እጅግ ፈጣን ዕድገት የታየባቸው ጊዜያት እንደነበሩን ሁሉ የተጎተትንበትም ከዓለም እይታ የተሰወርንበትም የጨለማ ዘመን ነበረን።

መቼም በዚህ ዓለም አንዱም እየወደቁ ሌላ ጊዜም እየተነሱ ነውና ጉዞው፤ የኑብያ-አክሱም ዘጉዌ ሥርወ መንግሥት ጊዜያት የሠለጠነ ምናልባትም ከዚህ ዘመን ያልተናነሰ የአስተዳደር ስልት የነበረባቸው ዘመናት ነበሩ ተብሎ ይገመታል።



የኢትዮጵያን የሥነ መንግሥት ታሪክ ከሀገር ውስጥ ፀሐፊ ትዕዛዞቻችን ውጪ ጀምስ ብሩስን፣ ሞሪዮ ኮልቦኮንቲ ሮሲኒ ካሚረር የመሳሰሉ የውጪ ጸሐፍት ጽፈውት በመገኘቱ መቶ በመቶም ባይሆን ለዚህ ለ3000 እና 4000 ዓመታት በአብዛኛው ተከታታይ የመንግሥታት ዘመን ነበረን ማለት ይቻላል። ጥቂቶቹ የውጪ ጸሐፍት ሳይቀሩ ቀይ ባሕርን ዞረው የሕዝባችንና የመንግሥታችንን ሁኔታ መዝግበው ተገኝተዋል። ከነዚህ መካከል ዲዮዶር እና አርቲሚዶር ይገኙበታል። የጥንት የግሪክ ታሪክ ጸሐፍት ናቸው። ጽሑፉም ፔሪፕሉ ማሬ ኤሪትሬዎ በሚባል መጽሐፍ የተጻፈ ነው። በተለይ ቶሎሜ የተባለ ጸሐፊ ካርታውን ሳይቀር ያካተተ መጽሐፍ አለው።

ሙሴ ዲልማን የተባለ የታሪክ ጸሐፊ እንደዘገበው ከአርዌ እስከ ብዕሲ ባዚን ከክርስቶስ ልደት በፊት 21 ነገሥታት ነግሠው ነበር በማለት የዘገበ ሲሆን፤ ይህም የሚጀምረው ከክርስቶስ ልደት በፊት 400 ዓመተ ዓለም ነው። ዓመተ ምሕረት ከተጀመረ በኋላ ደግሞ እስከ አብርሃ ወአጽብሃ 31፤ ሌላው ቀርቶ ከአብርሃ እስከ ገብረ መስቀል ድረስ እንኳን 29 ነገሥታት በአጠቃላይ 81 የዓለም ታሪክ የሚያውቃቸው ነገሥታት እስከ 500 ዓመተ ምሕረት ነበሩን። ይህ የታሪክ ተከታታይነት ካለመልካም አስተዳደር እዚህ ሊደርስ ፈጽሞ እንደማይችል ማስተዋል ይገባል። ከዚያ ወዲህም እንደ ድልነዓድ፣ ነአኩቶለአብ እና ይኩኖ አምላክ ያሉ በሳል መሪዎችን በ10 እና በ12ኛው ክፍለ ዘመን ያገኘችው ኢትዮጵያ የዘርዐያዕቆብ፣ የዓፄ ቴዎድሮስን፣ የዓፄ ዮሐንስን የዓፄ ምኒሊክን እጅግ በሳል አመራር የተጎናፀፈች ኢትዮጵያ ዛሬ በተሰናከለ ዕድል በአስተዳደር ጭራ በመሆኗ የሰብአዊ መብት በአግባቡ የማይከበርባት የጉቦ እና የአድልዎ መናኸሪያ መሆንዋ እጅግ ግራ የሚያጋባ ነው። ለእዚህ ነው ከአስተዳደር ጋር መታረቅ አለብን የሚለው ጥሪ ከፍ ብሎ መሰማት ያለበት።

ዝክረ ነገር በተሰኘው መጽሐፍ ላይ የሰዎች መብት እንዴት ይከበር እንደነበር በጥቂቱ ተጽፎ ይገኛል። ለምሳሌ ንጉሠ ነገሥቱ ግብር በሚያገባበት ጊዜ ከሕዝቡ ጋር በአንድ አዳራሽ ሲመገብ (የሚያስደንቅ ባሕል ነው አስተዳዳሪዎችና ሕዝቡ በአንድ ማዕድ መቁረስ) ታዲያ በዚህ

መሀል አንዱ ተራ ተጋባዥ ሰውን ሁሉ ረጋግጦ ቀድሞ ሊቀመጥ ሲሯሯጥ ያየው ደጃዝማች ወልደማርያም የተባለ አጋፋሪ ለምን አቧራ አስነስተህ ሹማምንቱን ጥሰህ ከማዕድ ለመቀመጥ ሞከርክ? ብሎ በጉራዱ ጥፊ ስለመታው (ንጉሠ ነገሥቱ ከትልቅ ድፍረት ቆጥረውት በመንግሥት አደባባይ እንዲህ ያለ የኃይልና የግፍ ሥራ ያደረገውን አጋፋሪ መቀጫ ጥለው) እንደነበረ ተጽፎ ይገኛል::

ሌላው በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት የነበሩትን ቀደም ብለው በዓፄ ምኒሊክ ዘመን የተሾሙት ሚኒስትሮች ከሥራ ገበታቸው የማይገኙ የግል እርሻቸውን ሲያሳርሱ የሚውሉ ቸልተኞች ስለሆኑ ሥራ በመበደሉ ሕዝቡ ጃንሜዳ ተሰብስቦ ሚኒስትሮች ከሥልጣን እንዲባረሩ ጠይቆ በሦስት ቀን ውስጥ በምትካቸው ሌላ ሰው ተተክቷል:: እነዚህን እና ሌሎቹንም ሥራዎች ስንመለከት መቶ በመቶም ባይሆን የአስተዳደር እርሾ የሥልጣኔ መንገድ ነበረን ማለት ይቻላል:: ይህ ሆኖ ሳለ ብዙዎቹ አገራት ከእኛ የሥልጣኔ ደረጃ ያልደረሱ፤ በዚህ ዘመን ቁልቁል እንዲያዩን ያደረገው በነበረን ፍጥነት መጓዝ ስላቃተን ነው::

የዘመናችን እሽቅድምድም እንደድሮው አይደለም:: በየደቂቃዋ አዳዲስ ፈጠራ አዳዲስ ስልት የሚነደፍበት ዘመን ላይ ነን ያለነው:: ድሮ በሰው ሕሊና ዕቅድ ይወጣላቸው የነበሩ ነገሮች ሁሉ ዛሬ ከመሣሪያ ጋር እጅግ ወደ እውነት የተጠጋ መመሪያ ሲነደፍላቸው ማየት የተለመደ ሆኗል:: በጥራት፣ በዓይነትና በብዛት የተለካ የተመጠነ አስተዳደር ባለቤት የሆነችው ዓለማችን እኛን እንደጋሪ ፈረስ አስከትላ ልትጓዝ የምትችል አይመስልም፤ አንድ ቦታ ላይ ትተወናለች ያኔ የሚከተለው አደጋ ምን ይሆን? በአስተዳደር የዳበረ ልምድ ያለው ሕዝብና መንግሥት በዕቅድ አምርቶ የተረፈውን በቁጠባ እና በእርዳታ እየለገሰን እስከመቼ እንኖራለን፤ ምዕራባውያኑ «አሰልችው ልመና» ብለው እስኪሳለቁብን ራሳችንን መምራት ለምን ተሳነን?

መጠነ ሰፊ የአስተዳደር ስልት ያስፈልገናል:: አመጋገባችን ሁሉ ለረኃባችን መንስኤ ነው:: የምግብ አስተዳደር ስለሌለን



የሚበላው ተትረፍርፎ እኛ ግን ረኃብተኛ ሆነናል:: ምድሪቱ የምታበቅላቸው የፍራፍሬ ዓይነቶች የእህል ዘር የዓሣውና የሥጋው ዘር የሚመገበው የለም:: በአርካሽ የሚሸጠው ቲማቲም ተጨምቆ ጁስ ተከ ትፎ ከቁራጭ ዳቦ ጋር ቁርስ ሊሆን ይችላል:: ፍራፍሬው ማርማላት ሆኖ ሕፃናቱን ቀጥ አድርጐ ይይዝ ነበር:: ማሩ አደንጓሬውና የቅጠላ ቅጠሉ ዓይነት ገና ወደ ምግብነት አልተለወጠም::

አስተዳደሩ ሀገሪቱን በሆቴል ኢንዱስትሪ ከሚያጥለቀልቃት የምግብ አምራቾች ይበዙ ዘንድ ቢገፋፋ ሴተኛ አዳሪዎች የፋብሪካ ሠራተ ኞች በሆኑ ነበር:: አዋሽ አካባቢ በቅርጫት ተሠፍሮ የሚሸጠውን ቲማቲም ጁስ ማድረግ ይቻላል:: ለዚህ የሚያስፈልገው እጅግ ጥቂት ወጪ ነው:: እንጀራ፣ ክትፎ፣ ጥብስ፣ ቀይ ወጥና አልጫ ወጥ እንደ መድሃኒት የታዘዘላት አገር የምግብ አስተዳደርዋን ብትለውጥ ረኃብዋን መቀነስ በቻለች:: የዓሣ ምግብ ሁዳዴን ጠብቆ መምጣቱ ይለወጥ ዘንድ በዚህ መልክ ሕዝቡን ማለማመድ ያስፈልጋል:: ሱፉ፣ አኩሪአተሩ እነዚህ ሁሉ ሕዝባችንን የሚደግፉ ናቸውና ሁሉም አዘውትሮ እንዲመገባቸው ማለማመዱ የምግብ አስተዳደሩን ይለውጠዋል::

እጅግ ውድ የሆኑ መኪናዎች ወደ ሀገራችን ሲገቡ የጂቡቲ ወደብ አስተዳደር ለመሆኑ ኢትዮጵያ መኪና ነው ወይ የምትበላው ብለው እንደተሳለቁብን ይነገራል:: ውድ መኪና ወደ 100 ሺህ ዶላር የሚያወጣ ነው:: መጓጓዣውና ቀረጡን ጨምሮ ወደ 200 ሺህ ዶላር ያወጣል:: በ8.50 ወደ 9.00 ብር ብላክ ማርኬት ምንዛሪ ሲባዛ የትየሌለ ነው:: ይህ ገንዘብ ደግሞ አሥር መኪና የሚያስገዛ ፋብሪካ ኢትዮጵያ ውስጥ መገንባት ይችላል:: አንዳንድ መኪናዎች ሲገዙ ውድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚወስደው ነዳጅ መለዋወጫ እና ምናምን እንኳን ለእኛ ለአሜሪካም አላዋጣት፤ ሀብታሞቻችን ገንዘባቸውን በየሀብታሙ አገር ለመኪና ግዢ መበተናቸው ዞሮ ዞሮ የሚጐዳው ሀገሪቱን ነው:: ሀብታቸው ከሀገሪቱ ያገኙት የሕዝብ ሀብት መሆኑን መዘንጋት አይገባም:: በዚህ ዘመን ሀብታሞቻችን ገንዘባቸውን ምዕራባዊያን ባንክ ነው የሚያስቀምጡት ይባላል:: ይህ ደግሞ ይዘገንናል:: ማንም ሰው ከአሜሪካ ወደሌላ አገር

ሲጓዝ ከ10 ሺህ ዶላር በላይ ይዞ መውጣት አይችልም:: የእኛ ብር ግን ያለከልካይ ወደውጭ እየበረረ ነው:: ከሀገር ውስጥ እየጐረፈ የሚወጣው ገንዘብ ምንም በእኛ አካውንት ይቀመጥ እንጂ የሀገር ሀብት መሆኑ እሙን ነው::

ለመሆኑ በቻይና ሸቀጥ የተጥለቀለቀው ገበያ የሀገር ቤቶቹን ፋብሪካዎች መጨፍለቁ ይታወቅ ይሆን? ልክ ነው የነጻ ገበያው መርህ በማንኛውም የንግድ ልውውጥ ላይ ማዕቀብ ማድረግን ይከለክላል:: ግን ጥራቱስ የግራና ቀኝ ጫማው አንድ ያልሆነ ዝፍቅ የሚራገፍብን ከእኛ የአስተዳደር ጉድለት እኮ ነው:: ሸማቹ ከሜዳ የገዛውን ቻይና ሠራሽ ሲያጠልቁት ገና የሚተረተር ከሆነ የጥራት ቁጥጥር ማድረጉ እኮ የነጻ ገበያ ሕግ የሚፈቅደው ነው:: በዚህ መልክ ሕዝቡም ንቃት ሊኖረው ይገባል:: የነፃ ገበያ ሥርዓት ማንንም መጥቀም ሳይሆን በዚህም በዚያም ብሎ ሀብታም መሆን ከሆነ ግቡ ሕዝባችንስ የሀገሩን የኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፣ የአዋሣ ጨርቃጨርቅን ትቶ ለምን የሌላውን ዓለም ሀብት ያጋብሳል? ለምን ሱፍ ከእንግሊዝ እንሸምታለን? ሠንጋተራ እና ፒያሣ ያሉ የሱፍ አምራቾች የሚሠሩት በጥራትና በዋጋ አስንቆ ሳለ ሰው ብልጥ ከሆነ እኛም ብልጥ መሆን አለብን:: አስተዳደር ማለት እንደቤተሰብ ማሰብ ነው እርስ በእርስ መገበያየትን መልመድ አለብን::

የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት ለገበያ ኢኮኖሚ እጅግ ጠቃሚ ነው:: ነጋዴው ለሕዝቡ አዝኖ በመጠነኛ ትርፍ ቢሸጥ ሕዝቡም የሀገሩን ባለሀብቶች ቢያሳድግ በዚህ ብቻ ለማደግ እንችላለን:: ባለሀብቱ ሳይስገበገብ ወጣቶችን 8:00 ሰዓት በማሠራት ለሕይወታቸው በቂ ክፍያ ቢከፍል ሌላ ውን 8:00 ሰዓት ሌላ ሥራ ቢሠሩበት ሀገር የማያድግበት ምክንያት የለም:: በምዕራቡ ዓለም ቀን በፀሐይ ሌሊት በኤሌክትሪክ መብራት በፈረቃ ነው የሚመረተው: ይህ ሁሉ የአስተዳደር ውጤት ነው::

አንድ አስተዳዳሪ በሚዛን የሚለካው በሥራው ወጤት እና በሠራተኛው ዓይን ነው:: እነዚህን ሁለቱን ማርካት የተሳነው አስተዳዳሪ ሥራውን ሊመረምር ይገባል:: በአጠቃላይ ከአስተዳደር ጋር መታረቅ



ያለብን በብዙ ዘርፍ ነው:: ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያና መጠጣችን በሚገባ ሊስተዳደር የሚችለው ከአስተዳደር ጋር ስንታረቅ ነው:: ከአስተዳደር ጋር እንታረቅ::

## ማጠቃለያ

መልካም አስተዳደር ለአንዲት አገር ወሳኝ ብቻ ሳይሆን የሕልውና መሠረትም ነው:: አመራር እንኳን ለአገር ለአንድ ድርጅት ስኬታማነትም ሆነ ውድቀት ወሳኝ ነው:: መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ከታች ላለው ሥራ በበቂ ዕውቀት የሚተላለፉ የተናጠል ውሳኔዎች ለመሪዎች የመተባበር ለውጥን ለማምጣት፣ በገበያውም ሆነ በማኅበራዊ አገልግሎቱ መስክ አስተዳደሩ አዲስ የለውጥ መንገድ ያስፈልገዋል:: ዓለማችን በብርሃን ፍጥነት መልኳን እና አሠራርዋን እየለዋወጠች ባለችበት በዚህ ዘመን ለአዲሱ አመራር በቂ ዕውቀትና ቅልጥፍና የሌላቸው ፈሪ አስተዳዳሪዎች ትርፋቸው ኪሣራ ነው::

ራዕይ የሌለው መሪ የሥራውን ብርሃን ብቻ ሳይሆን ከበታቹ ያሉ በፈጠራ ያጌጡ ሰዎችንም ሕሊና ይገድላል:: አደገኛም ነው:: (ጂኒየስ ኪለር) ተብለው የሚታወቁ አስተዳዳሪዎች በአጋጣሚ የአመራር ቁልፍ በእጃቸው ከገባ ወየው ለአዋቂዎች፣ ወየው ብሩህ ሕሊና ላላቸው የፈጠራ ሰዎች:: በአመራር ውስጥ የመረጃ አሰባሰብ ጥራት ለውሳኔ ያመቻል:: የአምስት ዓመት፣ የአሥር ዓመት፣ የአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የሚከወኑ መሪ ዕቅዶች ያላቸው መሪዎች የዛሬውን እርምጃ በውል ያውቁታል:: የሠለጠነው ዓለም ግን በመቶ ዓመታት የሚቆጠር መሪ ዕቅድ ቀምሯል:: ከአስተዳደር ጋር መታረቅ እራሱን የቻለ ረቂቅ ፍልስፍና ያለው ርዕስ ነው:: መሪዎችንም ተራ ሠራተኞችንም የሚያሳትፍ በመሆኑ በዚህ ባለንበት ዘመን በሀገራችን ኢትዮጵያ በሰፊው ልንመክርበት የሚገባ ዋና ጉዳይ ነው::

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው «ታላላቅ መሪዎች የወደፊቱን ያያሉ» በሚል ርዕስ (Caralyn Corbin) የተባለች ፀሐፊ እንዳሰፈረችው «መልካም ያልሆኑ አስተዳዳሪዎች ባሉበት አመራር አስፈሪ ዛፉ ብ!!"

ሳይሆን አስደንጋጭ ነገም ይከተላል በተመሳሳይ መንገድ ለሦስት ዓመት የተመራ ድርጅት በመጨረሻው ይሞታል» ብላለች:: አሁን የምንናገረው ስለድርጅት ሳይሆን ስለአንድ ግዙፍ ኅብረተሰብ ነው:: እርቅ የሚያስፈልገውም አስተዳደር በ80 ሚሊዮን ሕዝብ ሕይወት ላይ ወሳኝ ነውና አንድ ኢትዮጵያዊ አስተዳዳሪ በወንበሩ ቁጭ ሲል በትንሽዋ ቢሮ ውስጥ 80 ሚሊዮን ሕዝብን ወክሎ ካለዕውቀት ቢወስን፣ ወይም በግዴለሽነት ቡና እየጠጣ ቢያንጐላጅ ጉልቶ መሣፍርት የሌለውን ሕዝብ ወደ ረሃብ እየገፋ መሆኑ ሊገለጥለት ይገባል:: ስለዚህ ካለአንዳች ለውጥ በተሰጠው አመራር ላይ የሚቀልድ መሪ በብዙ ሰው ሕይወት ላይ የፈረደ ነው ማለት ነው::

ብታምኑም ባታምኑም ለገዛ ራስ ብልጽግና የአስተዳደር እርከን ላይ የሚፈናጠጡ ሁሉ ከደም መጣጮቹ ከእነ ኤዲያሚን ፊጽመው አይለዩም:: እነሱ በሚሰጡት አመራር የብዙዎች ሕይወት ያለአግባብ መቀጠፍ ምክንያት ነውና::

ስለዚህ ስለመልካም አመራር ከመነጋገራችን በፊት ለምንቀመጥበት የአመራር ቦታ ብቁ ነን ወይ? ታማኝ ነን ወይ? ብለን እራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል:: ብዙ ጊዜ በእኛ ሕይወት ውስጥ «የአባትህ ቤት ሲወረር አብረህ ውረር» የሚባለውን ተረት በስፋት ስንጠቀምበት ይስተዋላል:: «ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» የሚል እጅግ ጸያፍ ተረትም አለን:: እነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች ቀላል አንድምታ ያላቸው ቢመስሉም ግን መሪዎች በተሾሙ ጊዜ ለራሳቸው ብቻ እንዲያስቡ እንዲስገበገቡ የሚያደርጋቸው መሪ ጥቅስ ሆኗል:: ዘረፋ በይፋ የሚሞካሽባቸው እነዚህ ቀልዶች ግን በድህነት ባሕር ውስጥ እያሰመጡን ተገኝተዋል:: እርቅ ከሚፈልጉ የአስተዳደር ጽንሰ ሐሳቦች አንዱ ተሿሚ የተሾመው ሊበላ፣ ሊበዘብዝ፣ ሊያሥር፣ ሊፈታ፣ ሊገድል፣ ሊቆርጥ፣ ሊፈልጥ ሳይሆን በሰከነ መንፈስ ሥራንና ሠራተኛን ሊያገናኝ መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ይጠበቅበታል::



በዘመናዊው አስተዳደር አስተዳዳሪ ከመሆን ተራ ሠራተኛ መሆን ይሻላል:: ምክንያቱም አስተዳዳሪ እንደ ኢትዮጵያ ማዘዝ ብቻ ሳይሆን አብሮ መሥራትም ስለአለበት ነው:: በሀገራችን ኢትዮጵያ አንድ ሰው አስተዳዳሪ ሲሆን ሱፍና ከረቫት ለብሶ ባዶ ሳምሶናይት አንከርፍፎ ነው ቢሮ የሚገባው:: በምዕራቡ ዓለም ግን ለሥራ የሚያመች ጅንስና ጫማ ለብሶ ነው የሚመጣው:: የምዕራቡ ዓለም አስተዳዳሪ የመጀመሪያ ቀን ሥራው ሠራተኞችን ሰብስቦ እየሳቀና አብሮ እየበላ እየጠጣ በእኩልነት የተረጋጋ የሥራ መንፈስ መፍጠር ነው::

የእኛ አስተዳዳሪዎች የመጀመሪያ ሥራቸው ፊትን እንደፎጣ አጣጥፎ፣ የሌለውን ድምጽ አጕርንኖ፣ ከጥበቃ ሠራተኛ እስከ ጽዳት፣ ከዚያም አልፎ አዋቂዎችና ትጉህ ሠራኞችን እያበሻቀጠ አንበሣ መሆን ነው:: የሥራውን መንፈስ ከገዳደሉ በኋላ በየስብሰባው መደንፋት፣ የሌለ ሪፖርት ማቅረብ ይህ ነው እኛን የገደለን:: ይህ ታዲያ በዚህ በ30 ዓመት ውስጥ በእጅጉ ያበለፀግነው ክፉ መንፈስ ነው:: በአብዛኛው በኮሚኒዝም ርዕዮት የተለከፉ አገራት የሥራ ነፃነት የሌላቸው ድንጉጥና እጃቸው ለሥራ የተቆለፈ ነው:: በዚህ ዓይነት መንፈስ ውስጥ ያሉ ሕዝቦች የፈጠራ ልባቸውም የተሰለበ ነው::

«አንድ የምሥራቅ ጀርመን ሰው ወደኔ መጣና ምሥራቁንና ምዕራቡን ለይቶ የነበረውን ከበርሊን ግንብ ፍርስራሽ አንዱን ብረት እጄ ላይ አስቀመጠው:: እንዴት አሳዛኝ ጊዜ ነው:: ድንጋይ የሚቆርጥ ጠርዝ ያለው ጥቁር ባልጩት ነበረ:: ቁም ነገሩ ግን ይህ ድንጋይ መውደቁ ነው፤ በ1989 ይህ የበርሊን ግምብ ሲፈርስ የምሥራቁም ነፃነት ተረጋግጧል:: ይህ ነፃነት ግን መረበሽና መደናገር ፈጥሮ ነበር:: ምክንያቱ ይህ ሕዝብ ፈጽሞ ነጻ ሆኖ አያውቅም ነበርና:: ከመንግሥት ጥገኛ አድርጓቸው የነበረው ግንብ ተገረሰሰ:: ይህ ዓይነቱ ነፃነትን አለመልመድ ችግር በሺ ትናም ተከስቶ ነበር» Caralyn Corbin (Great Leaders see the Future first) ታላላቅ መሪዎች መጻኢዮትን በማየት ማስተዋል ይችላሉ::

ኮሚኒስቶቹ መንግሥታት ሌኒኒዝም ባወጣው (Dictatorship of the proletariat theory) በተባለው የወዝአደሩን የስም የበላይነት አፀደቀ በተባለ ግን በተግባር (totalitarian government) በፈጠረ አመራር አንድ ሰው እስኪሞት ይመራ ዘንድ ሌላ ፈላጭ ቆራጭ አመራር በመፍጠሩ ኮሚኒስቶቹን አስተዳዳሪዎች ቀና ብሎ እንኳን ለማየት ስለተቸገረ ኢትዮጵያን ጨምረው መላው ኮሚኒስት አገራት የሥራ ነፃነታቸውን አጥተው ቆይተዋል።

የሚገርመው በሶሻሊስት ሥርዓት የኅብረት (የማኅበር) ነፃነት እንጂ የግለሰብ ነፃነት ብሎ ነገር የለም። ግራ የሚያጋባው ግን ግለሰቦች ነጻ ሳይሆኑ እንዴት ማኅበረሰቡ ነፃነት ይኖረዋል? (የመደብ) የስም ነጻነት እንጂ የግለሰብ ነጻነት የማያውቀው ይህ ሥርዓት ማኅበር የዓለማችንን ዕድገት ቀልፎ መያዙ የታወቀው ሶቪየት ኅብረት ስትከፋፈል ሌሎች አገሮች ወደ ነጻ ገበያ ለማምራት በሚያደርጉት ጥረት የተሸማቀቀውን፣ ጥላውን እንኳን የማያምነውን ሕዝብ ወደ ነጻነት ለማምጣት ብዙ ዓመታት በመፍጀቱ ነው። ወደ ሀገራችን ስንመጣም አስተዳዳሪዎቻችን ልክ እንዳለፈው ያረጀ እና የወደቀ የኮሚኒስት ሥርዓት ማኅበር እስታሊንነት ይሰማቸዋል። ሠራተኞችም አንደበታቸው፣ እጃቸውንና ሕሊናቸውን ፈታ አድርገው ለመሥራት ነጻነቱን ገና አልተለማመዱትም።

ስለዚህ ከአስተዳደር ጋር መታረቅ ለዕድገታችን ወሳኝ በሆነበት በአሁኑ ወቅት ሁለንተናችንን የኮሚኒዝም ቅሪት የሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ሠንሠለት አስሮታል። ከሁሉ በላይ ሥራ ቀድሞ ጀምሮ ተዋርዶ ይገኛል። በሚገርም ሁኔታ ሁሉም የቢሮ ሠራተኛ መሆን ይናፍቀዋል። ስለዚህ ጥቂት ሰው የሚፈልጉት የቢሮ ሥራዎች በብዙዎች ተጣበው ይገኛሉ። ይህ ማለት ሥራ ፈትነት በቢሮ ተንሠራፍቶ ይገኛል ማለት ነው። ቢሮ ያለው በዘኔ ደግሞ ለምዝበራና ለወሬ የተጋለጠ ነው።

ስለዚህ ውሃን ቢወቅጡት እንቦጭ ሆኗል። በነገራችን ላይ አስተዳደር ማለት ትርፋማነቱ የተለካ፤ ውጤቱ የታወቀ ግብና ዕቅድ ያለው ስልት ነው። የበለፀገው ዓለም በየሰከንዱ የሚያድገው ይህንን ጽንሰ ሐሳብ



ስለተረዳ ነው። እስቲ አንድ በበለፀገ አገር ያለን የባንክ እንቅስቃሴ እና አስተዳደሩን ለምሳሌ እንይ፤ ከሁሉ በፊት ባንኩ እና አስተዳዳሪዎቹ በሌሎች ባንኮችና አስተዳዳሪዎች ወድድር ውስጥ እንዳሉ የሚያውቁ ናቸው። ስለዚህ ለሦስት መሠረታዊ ቁም ነገሮች ታላቅ ዋጋ ይሰጣሉ። አንደኛ ለሰዓት፣ ሁለተኛ ለፍጥነት፣ ሦስተኛ ጥራት።

አንድ ሠራተኛ በሰዓት የሚከፈለውን ስንት ስንተኛ በደቂቃ ይሠራል። በምን ዓይነት ጥራት እና ፍጥነት? ለእያንዳንዱ ውጤት ፍጹም ሰዓት ተዘጋጅቶለታል። አንድ ሠራተኛ በደቂቃ ምን እንደሚሠራ ደረጃ ወጥቶ ተቀምጧል። ኮምፒውተር ላይ ከሠራ ሠራተኛው የጀመረበት ሰዓት ዕረፍት የወሰደበት ሳይቀር ይመዘገባል። በሠራው ጥራትና ብዛት መጠን በየወሩ ማበረታቻ ይደረግለታል። (recognition) አድናቆቱ የሠራተኛውን መንፈስ ያነቃቃል። አለቃ ሠራተኛን እንዳይጉዳ ሕግ ተበጅቶ ተቀምጧል።

ግን እንዲህም ቢሆን ምዕራቡ ዓለም መንግሥተ ሰማይ ነው ማለት አይደለም። ቢሆንም የሥራው ነጻነት ከፈጠረው ብዙ መስክ የተነሳ። ከአንዱ ሥራ ቢወጡ ሌላው ጋ እየሄዱ መሥራት ይቻላል። የግል ክፍለ ኢኮኖሚው መበረታታቱ ብዙ ሀገራትን እጅግ እንዲያድጉ አድርጓቸዋል። አስተዳደርና ሥራ በእውነት ተግባር ላይ ውለው የሚታይበትን ዓለም አይቶ ወደ አገራችን ሲመለከቱ እጅግ ያስደነግጣል።

የንግድ ድርጅቶች ሁኔታ በዚህ ጊዜ ፈጣን ነው። ሁሉም በፍጥነት እየተለወጠ ነው። በጣም የሮጠ ብቻ ነው በሁኔታዎች መካከል መቆየት የሚችለው። በእርግጥ የንግድ መጋዘኖች ፈጣን የተሳካላቸው ካምፓኒዎችን ሰይሟል። በአጭሩ የዘመኑ ፍጥነት ሲተረጐም ፈጣን መሆን ብቻ በቂ አይደለም የሚል ብሒል አለው። በጣም ፈጣን መሆን እንጂ።

ከዚህ አባባል ጋር እኛነታችንን ስናነጻጽረው ነው እንግዲህ የምንደነግጠው። ለዓይን የማይታዩ ድኃ እና ጉስቁላ አገራት ዘንድሮ ፈጣን ሆነዋል፤ ቀድመው የደረጁት ምዕራባውያኑ ደግሞ የሕዋው ዘመን

ውስጥ ገብተዋል፤ ፍጥነታቸውን በብርሃን ፍጥነት ለመለካት እየተ ሽቀዳደሙ ይገኛሉ:: የምዕራቡ ዓለም ይህንን ዕድገት ለመቀዳጀት ያዳበራቸው ዋና መሣሪያዎች ምንድን ናቸው?

እኛነታችንን በአስተዳደር ሚዛናዊነት፣ ጥራት እና ፍጥነት ስናየው ምን ይሰማናል? ወደፊት እየሄድን ነው ወይስ ወደኋላ? ይህንን ለሕሊናችን ፍርድ ትተን ቁርጡን ለመነጋገር ግን በዚህ ዓይነት ዝርክርክነትና ጉቦኝነት ከተንዝን የጉቦ ሰጪውም ተቀባዩም ልጆች ከፍለው የማይጨርሱት ውስብስብ ዕዳና ችግር ውስጥ ይገባሉ::

ጥርት ያለ የአስተዳደር መስመር መፈጠር አለበት:: እጅግ እያደገ የመጣውን የጉቦ ባሕል ሥር ሳይሰድና ከዚህ ሳይብስ መቁረጥ አለብን:: ማስተዳደር ማለት የበታችን ማስቃየት አይደለም:: ሕዝብ ወይም የበታች በፍቅር ከያዙት የሚለውን ከሰሙት ወዳጅ ይሆናል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃይል ነው የሚገዛው የሚለው ቋንቋ ከአስተዳዳሪዎች ሕሊና መውጣት አለበት:: አስተዳዳሪዎች በሥልጣን ወንበር ላይ እስኪሻግቱ ቢቆዩና ሕዝቡ ባይስማማ እውነት አለው:: መታፈር በከንፈርና በምግባር ስሰሆነ ቅን እረኛ (አስተዳዳሪ) ሆነን በጊዜ ሳይንዛዛ ለሌላው ቦታችንን እንልቀቅ፤ እንዲህ ከሆነ ከሕዝብ አንጣላም:: አስተዳዳሪዎች ከፍቅር ወደ መጠላት፤ ከመጠላት ወደ መደንገጥ፤ ከመደንገጥ ወደ ነፍስ ግድያ ከዚያም ወደ ኢዴያሚንነትና ወደ ሒትለርነት ከመለወጣቸው በፊት የሚገባቸውን ሠርተው ዘወር ቢሉ ይበጃቸዋል::

እግዚአብሔር የኢትዮጵያን እርምጃ ይባርክ::

# ዋቢ መጻሕፍት


1. መጽሐፍ ቅዱስ
2. ዝክረ ነገር ፀሐፊ ትዕዛዝ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል
3. ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ

   ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ክፍል 1 እና 2
4. የኢትዮጵያ ታሪክ 1ኛ መጽሐፍ

   ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ
5. ፍትሐ ነገሥት
6. ሥርዓተ ትምህርት (አባ ሀብተማርያም ወርቅነህ) አሁን አቡነ መልከጸዴቅ
7. የሚያባራ ዝናብ መታን

   በአብርሃም ሰለሞን የግጥም መጽሐፍ 2007
8. The Fate of Africa

   A history of Fifity years of independence by Martin Mecredith
9. Martin Luther King. JR

   Edited by Clayborne Carson
10. Area handbook of Ethiopia

    Foreign area studies
11. Popular Science

    A Marshall Edition
12. Great Leaders see the Future First

    By Carolyn Corbin
13. Gandni's Truth

    Erik H.Erikson
14. The world is Flat

    By Thomas L.Friedman

15. To Forgive ... But not Forget

By MAJA'S Abramovitch

16. Finding Freedom in Forgiveness

Charlis "T" Jones and Daniel R.Ledwith

17. Confessions of an Economic Hit MAN

By John Rerkins

18. Mandela

Anthony Sampson

19. The constitution of the U.S

Floyd G.Cullop

20. Foreign Policy

January/February 2006

21. News week, April 3, 2006

22. Forgiveness

አቡነ ዴዝሞን ቱቱ

23. Popular Mechnanics (March 2006)

Squeezing Gas From Gow

24. Earth trends 2003 — Energy and Resources

25. Water Resources, Growth and Development

18 April 2005 A working paper of Discussion


26. Wonders of the African world Henky Lovis Gates. Jr. PBS 1999

27. Energy situation and trends in Ethiopia Part VI

(PROF. Wolde Ghiorgis Woldemariasm)

28. The Secret History of the American Empire

By John Perkins



የብዙ ሙያ ባለቤት የሆነው ታዋቂው ዘማሪ ይልማ ኃይሉ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥነ ጥበብና ዲዛይን ት/ቤት በሥዕል ጥበብ ተመርቋል። በርካታ የሥዕል ኢግዚቢሽኖችን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በማቅረብም ልዩ አድናቆትን ያተረፈ ሰዓሊ ነው። እንደ በሳሎቹ መዝሙሮቹ ሁሉ ሰዓሊ ይልማ በተለያዩ ጊዜያት በሚጽፋቸው የሥነጽሁፍ ቱሩፋቶች ይታወቃል።

እነሆ አሁን ደግሞ የይቅርታንና የእርቅን እሳቤ ሁፋ አድረጎ በመተንተን ይህን መጽሐፍ ይዞልን ቀርቧል።

«ቂምንና ጥላቻን በአጭሩ መቅጨት ይቻላል እንደ እሳት ከተቀጣጠለ ሥር ከሰደደ በኋላ ግን የሚጠይቀው ዋጋ ከ--- እስከ አይባልም። ለትልቁም ለትንሹም ጥቅም ሲባል የሚፈሰው የሰውደም ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ይቅርታ በየትኛውም ዋጋ ሊተመን አይችልም» ።

Africa Printing PLC

ዋጋ 30.00 ብር